*መጽሐፍ ቅዱስን ሊረዱት ይችላሉ!*

# የብሉይ ኪዳን አሰሳ

# ከዘፍጥረት - ሚልክያስ

*ቦብ አትሊ*

*የትርጓሜ ፕሮፌሰር*

*(የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ)*

የጥናት መመሪያ ተከታታይ ሐተታ

አዲስ ኪዳን፣ ቅጽ 6

ዓለም አቀፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት፣ ማርሻል፣ ቴክሳስ

2002 (በ2010 የተከለሰ)

# ከዘፍጥረት - ሚልክያስ

DR. BOB UTLEY
Bible Lessons International

## ማውጫ

I. መልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ መመሪያ፡ 4

II. የመክፈቻ ትምህርት 10

ሀ. ጥቅም ላይ የዋሉ ቃሎች 10
ለ. ብሉይ ኪዳንን ለምን እናጠናለን 10
ሐ. ብሉይ ኪዳንን እንዴት እንደምናጠና 11
መ. መሰረታዊ ካርታዎች 12
ሠ. መሰረታዊ የጊዜ ሂደቶች 13

III. ህግጋት

ሀ. ዘፍጥረት 19
ለ. ዘፀአት 30
ሐ. ሌዋዊያን 38
መ. ዘኍልቁ 49
ሠ. ዘዳግም 55

IV. የቀደሙት ነብያት

ሀ. ኢያሱ 62
ለ. መሳፍንት 68
ሐ. ሩት 74
መ. ሳሙኤል 78
ሰ. ነግስት 85

V. ቅፅ — የተከፋፈሉ መንግስታት ነገስታት

VI. ሥነ ፅሁፎች

ሀ. ዜና 109
ለ. እዝራ 113
ሐ. ነህምያ 118
መ. አስቴር 123

VII. የጥበብ መፃህፍት

ሀ. የእብራይስጥ ቅኔዎች 131
ለ. መፃህፍት
ኢዮብ 133
መዝሙር 139
ምሳሌ 146
መክብብ 151
መኃልየ መኃል 157

VIII. ታላላቅ ነቢያት

ሀ. ለብሉይ ኪዳን ትንቢቶች መግቢያ 163
ለ. መፃህፍት
ኢሳይያስ 166
ኤርምያስ 181
ሰቆቃ ኤርምያስ 187
ሕዝቅኤል 192
ዳንኤል 197

IX. ደቂቀ ነቢያት

ሆሴዕ 201
ኢዮኤል 206
አሞፅ 211
አብድዩ 218
ዮናስ 223
ሚክያስ 228
ናሆም 233
ዕንባቆም 238
ሰፎንያስ 242
ሐጌ 246
ዘካሪያስ 251
ሚልክያስ 256

# መልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ መመሪያ፡ የተፈተነ እውነትን በግል ለመፈለግ

እውነትን ለማወቅ እንችላለን? የት ይገኛል? ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ለማረጋገጥ እንችላለን? የመጨረሻ ወሳኝ ይኖር ይሆን? ሕይወታችንንም ሆነ ዓለማችንን ሊመሩ የሚችሉ የተሟሉ (ፍጹማን) ይኖራሉ? ለሕይወት ትርጉም አለው? እዚህ መሆናችን ለምድነው? የትስ እንሄዳለን? እነዚህ ጥያቄዎች፣ አስተዋይ ሰዎች የሚሰላሰሏቸውና ከዘመናት መጀመሪያ አንሥቶ የሰዎችን እውቀት የሚፈትሹ ናቸው (መክ. 1፡13-18፤ 3፡9- 11)። የኔን ግላዊ ጥናት የማስታውሰው የሕይወቴ ዋነኛ ማእከል አድርጌ ነው። በየሱስ አማኝ የሆንኩት በወጣትነት ጊዜዬ ነው፤ በቅድሚያም በዋነኛነት በሌሎች የቤተሰቤ አባላት ምስክርነት። እየጎለመስኩ ስመጣ ስለራሴም ሆነ ስለ ዓለሜ ያሉኝ ጥያቄዎች እያደጉ መጡ። ተራ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ድግግሞሾች ስለ አነበብኳቸውና ስለተረዳኋቸው የሕይወት ልምዶች፣ ትርጉም ሊሰጡ አልቻሉም። የውዥንብር ፤ የምርምር፣ የመናፈቅ እና ብዙውን ጊዜም ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ነበር፣ በምኖርበት በድን በሆነው ደንዳና ዓለም ውስጥ።

ለእነዚህ ዋነኛ ጥያቄዎች ብዙዎች ምላሽ እንዳላቸው ይናገራሉ፣ ነገር ግን ከፍተኛ እና ከማገናዘብ በኋላ የእነሱ መልሶች የተመሠረቱት (1) በግል የሕይወት ፍልስፍናዎች፣ (2) በጥንታዊ አፈ-ታሪኮች፣ (3) በግል የሕይወት ልምዶች፣ ወይም (4) በሥነልቦናዊ ቅድመ እይታዎች ላይ ነው። በማስተዋል የሆነና ስለ ዓለም ያለኝ አመለካከት መሠረት፣ የሕይወቴ ዋነኛ ማእከል፣ የመኖሬ ዋነኛ ምክንያት ላይ ማረጋገጫ አስፈልጎኝ ነበር፣ ማስረጃ። እነዚህን መጽሐፍ ቅዱስን ሳጠና አገኘኋቸው። ታማኝ እንዲሆንም ማስረጃ መፈለጌን ጀምሬ ያገኘሁትም፣ (1) በጥንታዊ ቅርስ ምርምር ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የተገኘው ታሪካዊ ማረጋገጫ፣ (2) የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ትክክለኛለት፣ (3) በአስራ ስድስት መቶ የመጻፍ ጊዜው ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ የመልእክት ኅብርና መኖር እና (4) ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ከተገናኙ በኋላ ፍጹም የሕይወት ለውጥ ያገኙት ሰዎች የግል ምስክርነት ናቸው። ክርስትና ኅብር እንዳለው የእምነትና የሃይማኖት ሥርዓት የሰው ልጆችን ውስብስብ ጥያቄዎች የመመለስ ችሎታ አላቸው። ይህን ማድረግም የማስተዋል ውቅር ብቻ አይሰጥም፣ ነገር ግን በፍትነታዊ ገጽታው የመጽሐፍ ቅዱስ እምነት የስሜት ደስታ እና መረጋጋትን ይሰጣል።

እንደማስበው፣ የሕይወቴን ዋነኛ ማእከል— ክርስቶስን በቃሉ ውስጥ አግኝቼዋለሁ። በሕይወት ልምዴ ንቁ እና ስሜተ-ስሱ ነበርኩ። ቢሆንም እስካሁን ድረስ የማስታውሰው ወገግ ሊልልኝ ሲል የነበረብኝን ነውጥ እና ሥቃይ ሲሆን፣ የቱን ያህል የመጽሐፉ ትርጓሜዎች እንደሚከራከሩና፣ አልፎ አልፎም በአንድ አብያተ ክርስቲያን እና አስተምህሮዎች እንዳሉ ሳይ ነው። መጽሐፍ ቅዱስን የተመስጦ መሆንና ጠቃሚነቱን ማረጋገጥ የመጨረሻው ሳይሆን የመጀመሪያው ብቻ ነው። የተለያዩ እና ተቃርኖ ያላቸውን የመጽሐፉን ከባባድ አንቀጾች ትርጓሜዎች፣ ሁሉም ትክክለኛ እና በሥልጣን ነን እያሉ እንዴት አድርጌ እንደምቀበል ወይም እንደምተው ላውቅ እችላለሁ? ይህም ተግባር የሕይወቴ ግብ እና የእምነቴ ምናኔ ሆነ። የተረዳሁት ነገር በክርስቶስ ያለኝ እምነት፣ (1) ታላቅ ሰላምና ደስታ እንዳመጣልኝ፣ (2) የተቀናቃኝ ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች (የዓለም ሃይማኖቶች) ቀኖናዊነት፤ እና (3) የአንድ ክፍለ ሃይማኖት እብሪተኝነት እንዳለበት ተረድቻለሁ።

የጥንታዊውን ሥነ ጽሑፍ ትርጓሜ ተገቢ ዋጋ ያለው ፍለጋዬን ሳካሂድ ያስደነቀኝ ነገር ቢኖር የራሴን የግሌን ታሪካዊ፣ ባህላዊ፣ ክፍለ ሃይማኖታዊ እና በሕይወት ልምድ አድልዐዎች መለየት ነው። የራሴን አመለካከት ለማጠናከር መጽሐፍ ቅዱስን እንደዋዛ አዘውትሬ አነባለሁ። የራሴን ያልተሟላ ዋስትናና የብቃት ማነስ ያመላክተኝ ሌሎችን የማጠቃበት ቀኖናዊ ምንጭ አድርጌ እወስደዋለሁ። ይህንን ሀቅ መረዳት ለእኔ የቱን ያህል አስቸጋሪ ነበር! ምንም እንኳ የተሟላ ተጨባጭነት ባይኖረኝም የመጽሐፍ ቅዱስ ደኅና አንባቢ ለመሆን እችላለሁ። ያሉብኝን አድሏዊነቶች ለመለየትና እንዳሉም እውቅና በመስጠት የተወሰኑ ላደርጋቸው እችላለሁ። ከእነሱ ገና አሁንም ነጻ አይደለሁም፣ ነገር ግን ከራሴ ድክመት ተሟግቻለሁ። ተርጓሚ ዘወትር የመልካም መጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ጠላት እንደሆነ ነው! እስቲ ጥቂት ቅድመ ግምቶችን፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቴ ገኘኋቸውን እርሶ አንባቢው ከእኔ ጋር ሆነው ይመረምሯቸው ዘንድ ልዘርዝራቸው፡

(1) መጽሐፍ ቅዱስ ተመስጧዊ የሆነ የእውነተኛው አምላክ የራሱ መገለጥ መሆኑን አምናለሁ። ስለሆነም፣ መተርጎም ያለበት በዋነኛው መነሻ ብርሃን ለኮታዊ ጸሐፊ (መንፈስ) ሆኖ በተወሰነ ታሪካዊ ወቅት በነበረ ሰው ጸሐፊነት ነው።
(2) መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው ለተራ ሰዎች፣ ለሁሉም ሰዎች እንደተጻፈ አምናለሁ! እግዚአብሔር ለእኛ በግልጽ ለመናገር በታሪካዊና በባህላዊ ግባብ ራሱን አዘጋጅቶልናል። እግዚአብሔር እውነትን አይሸሽግም— እንድንረዳው ይፈልጋል! ስለሆነም በእኛ ሳይሆን በራሱ ጊዜ ብርሃን የግድ ተርጎም አለበት። መጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያ ከሰሙት ወይም ካነበቡት በተለየ መንገድ የምንረዳው ማለት አይደለም። በተራ ሰው ልቦና ሊረዱት የሚችል እና ተገቢ የሆነ የሰው ልጆች መግባቢያ አግባቦችና ስልቶችን የሚጠቀም ነው።
(3) መጽሐፍ ቅዱስ ኅብር ያለው መልእክትና ተግባር እንዳለው አምናለሁ። ምንም እንኳ አያአዎአዊ የሆኑ አንቀጾች ቢኖሩትም ራሱን በራሱ ይቃረንም። ስለሆነም፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ዋነኛው ተርጓሚ መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ነው።
(4) እያንዳንዱ አንቀጽ (ትንቢታትን ጨምሮ) አንድ እና አንድ ብቻ ትርጉም እንዳላቸውና ይህም በዓይነተኛው ተመስጧዊ ጸሐፊ መነሻ ሐሳብ ሆኑን አምናለሁ። ምንም እንኳ ፍጹም ርግጠኞች ባንሆንም የዓይነተኛውን ጸሐፊ ሐሳብ እንረዳዋለን፣ ብዙ ጠቋሚዎች አቅጣጫውን ስለሚያመላክቱን፡
    (ሀ) የዘውግ (የሥነ ጽሑፋዊ) ዓይነቱ፣ መልእክቱን ለማስተላለፍ የተፈለገበት
    (ለ) ጽሑፉ ሊያወጣ የፈለገው እውነት ታሪካዊ ዳራ እና /ወይም የተለየ አውድ
    (ሐ) የአጠቃላይ የመጽሐፉ ሥነ ጽሐፋዊ ሁኔታ እና እንዲሁም የእያንዳንዱ የጽሑፍ አሀድ
    (መ) መጽሑፋዊ ንድፉ (ዋና ዋና ይዘቱ) ማለትም እያንዳንዱ ጽሑፍ አሀድ ከአጠቃላይ መልእክቱ ጋር ያለው ዝምድና
    (ሠ) መልእክቱን ለማስተላለፍ የተጠቀመበት የተለየ ሰዋሰዋዊ ባሕርይ
    (ረ) መልእክቱን ለማቅረብ የተመረጡት ቃላት ትይዩ አንቀጾች

በእነዚህ በእያንዳንዳቸው አካባቢ የሚደረገው ጥናት በአንቀጽ ላይ የምናደርገው ጥናት ላማ ሆኗል።ለመልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚሆነውን የእኔን ዘዴ ከመግለጤ በፊት ጥቂት ተገቢ ያልሆኑ በአሁን ጊዜ ጥቅም ላይ በመዋል ላይ ያሉትንና በርካታ የተለያዩ ትርጉሞች እንዲፈጠሩ ያደረጉትና ግድ መወገድ ያለባቸውን ላመላክት፡


(1) የመጽሐፍ ቅዱስን መጻሕፍት ሥነጽሑፋዊ አውድ ችላ በማለት እያንዳንዱን ዓረፍተ ነገር፣ ሐረግ እንዲያውም ግለሰባዊ ቃላትን እንደ እውነታዊ ግለጫ፣ ከጸሐፊው ዓላማ ባልተገናኘ መልኩ ወይም ከሰፊው የጽሑፉ ክፍል ጋር ባልተያያዘ ሁኔታ መውሰድ። ይህም ዘወትር "የጽሑፍ ማጣራት" ይባላል።

(2) የመጻሕፍቱን ታሪካዊ አውድ ችላ በማለት እና በግምታዊ ታሪካዊ ዳራ በመቀየር ከጽሑፉ ጋር መጠነኛ ግንኙነት ወይም ምንም ዓይነት ድጋፍ በሌላቸው ጋር ማያያዝ


(3) የመጻሕፍቱን ታሪካዊ አውድ ችላ በማለት እንደ አካባቢያዊ የጧት ጋዜጣ ዓይነት ቀድኖውኑ ለዘመናዊ ክርስቲያን እንደተጻፈ ዓይነት ማንበብ

(4) የመጻሕፍቱን ታሪካዊ አውድ ችላ በማለት ለጽሑፉ ተምሳሌታዊ ፍቺ በመስጠት ፍልስፍናዊ/ሥነ- መለኮታዊ በማድረግ በመጀመሪያ ቃሉን ከሰሙት እና ዋናው ጸሐፊ ሊል ከፈለገው ሐሳብ በማይገናኝ መልኩ መያዝ

(5) ዋነኛውን መልእክት ችላ በማለትና የራስን የሥነ-መለኮት ሥርዓት፣ አባባይ መሠረተ- እምነት፣ ወይም የወቅቱን ጉዳይ በመቀየር፣ እና ከማይገናኝ ጋር በማያያዝና፣ ዋናው ጸሐፊ ሊል ከፈለገው ቁምነገርና ከተቀመጠው መልእክት መውጣት። ይህ የአካሄድ ክስተትም ዘወትር የሚደረገው የተናጋዊውን ሐሳብ ለማጠናከር በቅድሚያ ከመጽሐፍ ቅዱስ ማንበብን ነው። ይህን ዘወትር፣ "የአንባቢ ምላሽ" ("ጽሑፉ ለእኔ የሚሰጠኝ" ትርጉም ተብሎ ይታወቃል። በሰዎች የጽሑፍ መግባቢያ ላይ ቢያንስ ሦስት አካላት ያስፈልጋሉ፡




ቀደም ሲል የተለያዩ የምንባብ ስልቶች ከሦስቱ በአንደኛው ክፍሎች አተኩረው ነበር። ነገር ግን በእውነት ለማጽናት ልዩ የሆነው የመጽሐፍ ቅዱስ መስጦ የተሻሻለው ንድፍ ይበልጥ ተገቢነት አለው።




እንደ እውነቱ ሦስቱም አካሎች በትርጓሜ ሂደት የግድ መካተት ይኖርባቸዋል። ለማረጋገጥ ያህልም የእኔ ትርጓሜ ያተኮረው በቀዳሚዎቹ በሁለቱ ካላት ላይ ነው፡ ዋነኛው ጸሐፊ እና ጽሑፉ። ምናልባት የእኔ ተቃርኖ ባስተዋልኩት ተገቢ ያልሆነ ሁኔታ ላይ ይሆናል። (1) ተምሳሌታዊ ወይም መንፈሳዊ በተደረጉ ጽሑፎች እና (2) "የአንባቢ ምላሽ" (ለእኔ የሚረዳኝ) ትርጓሜዎች። በዛባት በሁሉም ደረጃ ላይ ሊከሰት ይችላል። ዘወትር የእኛን መሻት፣ አድሏዊነት፣ አግባብ፣ እና አፈጻጸማችንን መመርመር ይኖርብናል። ምንም ዓይነት ወሰኖች ለትርጉሞች በሌሉበትን፣ ገደብና መስፈርት በሌለበት እንዴት አድርገን መፈተሽ እንችላለን? ለዚህ ነው የጸሐፊው መነሻ ሐሳብና የጽሑፉ አወቃቀር የተወሰኑ መስፈርቶችን ሰጥቶኝ ዳራውን ለመወሰንና ተገቢ የሆነ ይሁንታ ያለው ትርጓሜ እንዳደርግ ያስቻለኝ።

በእነዚህም ተገቢ ባልሆኑ ስልቶች ጭላንጭል ምን ዓይነት ታሳቢ አግባቦች ለመልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ እና ትርጓሜ በተረጋገጠ ደረጃ የሚያመጡ እና ቋሚነት ያላቸው ሊኖሩ ይችላሉ?

በዚህ ነጥብ የተወሰኑ የትርጓሜ ዘውጎችን የተለዩ ስልቶችን አላብራራም፤ ነገር ግን ለሁሉም ዓይነት የቅዱሳን መጻሕፍት አጠቃላይ የጽሑፍ ትርጓሜ ተገቢ መርሖዎች ላይ ነው። ለተወሰነ ዘውጋዊ አግባብ መልካም የሆነው መጽሐፍ፣ (*How To Read The Bible For All Its Worth*, by Gordon Fee and Douglas Stuart, published by Zondervan) መጽሐፍ ቅዱስን በሙሉ ጠቀሜታው እንዴት እንደሚነበብ፣ በጎርዶን ፊ እና ዳግላስ ስቱአርት፣ በዞንደርቫን የታተመው ነው) ። የኔ ዘዴ በመነሻው ያተኮረው አንባቢ ለመንፈስ ቅዱስ መጽሐፍ ቅዱስን ያበራላቸው ዘንድ ሲፈቅዱ የሚያልፉባቸውን አራት የግል የንባብ ሀደቶችን ነው። ይህም መንፈስን፣ ጽሑፉን እና አንባቢውን ቀዳሚ ያደርጋቸዋል፣ ተከታይ ሳይሆን። ይህም ደግሞ አንባቢው በተንታኞች ሐሳብ አለቅጥ እንዳይወሰድ ያደርገዋል። ሲባል የሰማሁትም፣ "መጽሐፍ ቅዱስ እጅግ ብርሃን በሐተታዎች ላይ ያበራል" የሚል ነው። ይህም ማለት ግን የጥናት መርጃዎችን ለማንኳሰስ አይደለም፣ ነገር ግን ለአጠቃቀማቸው ተገቢ ጊዜ ማስፈለጉን ለማመላከት ነው እንጂ። ትርጓሜዎቻችንን ከቃሉ ከራሱ ለማስደገፍ መቻል ይኖርብናል።

የኔ ዘዴ በመነሻው ያተኮረው አንባቢ ለመንፈስ ቅዱስ መጽሐፍ ቅዱስን ያበራላቸው ዘንድ ሲፈቅዱ የሚያልፉባቸውን አራት የግል የንባብ ሀደቶችን ነው። ይህም መንፈስን፣ ጽሑፉን እና አንባቢውን ቀዳሚ ያደርጋቸዋል፣ ተከታይ ሳይሆን። ይህም ደግሞ አንባቢው በተንታኞች ሐሳብ አለቅጥ እንዳይወሰድ ያደርገዋል። ሲባል የሰማሁትም፣ "መጽሐፍ ቅዱስ እጅግ ብርሃን በሐተታዎች ላይ ያበራል" የሚል ነው። ይህም ማለት ግን የጥናት መርጃዎችን ለማንኳሰስ አይደለም፣ ነገር ግን ለአጠቃቀማቸው ተገቢ ጊዜ ማስፈለጉን ለማመላከት ነው እንጂ። ትርጓሜዎቻችንን ከቃሉ ከራሱ ለማስደገፍ መቻል ይኖርብናል።

አምስቱ አካባቢዎች ምናልባት የተወሰኑ የእውነት ማረጋገጫ ይሰጡናል፡፡

(1) ታሪካዊ መቼት
(2) ሥነ-ጽሑፋዊ አውድ
(3) ሰዋሰዋዊ መዋቅር (አገባብ)
(4) የተመሳሳይ ሥራዎች አጠቃቀም
(5) የጊዜው ትይዩ አንቀጾች

ከትርጓሜአችን ጀርባ ምክንያቶችንና አመክኖዎችን (ሎጂክ) ማሳየት መቻል አለብን። መጽሐፍ ቅዱስ ብቸኛው የእምነትና የድርጊት ምንጫችን ነው። ቢያሳዝን መልኩ፣ ክርስቲያኖች በሚያስተምረው ወይም በሚያጸናው ላይ ዘወትር አይስማሙም። ይህም መጽሐፍ ቅዱስ ተመስጧዊ መሆኑን ተቀብሎ ከዚያም አማኞች ለሚያስተምረውም ሆነ ለሚጠይቀው ላለመስማማት መቻል በራስ እንደመሸነፍ ነው!

አራቱ የንባብ ሀደቶች የተነደፉት የሚከተለውን ጠለቅ ያለ ትርጓሜ ለመስጠት ነው።

(1) የመጀመሪያው የንባቡ ኡደት
   (ሀ) መጽሐፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ ያንብቡት። ከተለያዩ የትርጉም ንድፈ ሐሳቦች አገኛለሁ ብለው ተስፋ በማድረግ በድጋሚ በተለያዩ ትርጉሞች ያንብቡት
      (i) ቃል በቃል (NKJV, NASB, NRSV)
      (ii) ንቁ ቀጥተኛ TEV, JB)
      (iii) ማብራሪያ (ሕያው ቃል፣ የተብራራ መጽሐፍ ቅዱስ)
   (ለ) የሙሉ ንባቡን ማእከላዊ ሐሳብ ይፈልጉ። ጭብጡን ይግለጡት።
   (ሐ) የጽሑፋዊ አሀዱን (ከተቻለ) ይለዩት፤ ምእራፍ፣ አንቀጽ ወይም ዓረፍተ ነገር በትክክል ሊያብራራ የሚችለውን፣ የጭብጡን ማእከላዊ ሐሳብ ለማግኘት።
   (መ) ዋነኛውን ገገር የሥነ-ጽሑፋዊ ጭብጥ ዘውግ (ዓይነት) ይግለጡት

      (i) ብሉይ ኪዳን
         1) ይእብራይስጥ ትረካ
         2) የእብራይስጥ ቅኔ (መጽሐፈ- ጥበብ፣ መዝሙራት)
         3) የእብራይስጥ ትንቢት (ስድ ንባብ፣ ቅኔ)
         4) ሕግጋት
      (ii) አዲስ ኪዳን
         1) ተራኪ (ወንጌላት፣ ግብረ-ሐዋርያት)
         2) ደብዳቤዎች/መልእክቶች
         3) ትንቢታዊ ሥነ-ጽሑፍ

(2) ሁለተኛው የንባብ ኡደት
   (ሀ) ሙሉ መጽሐፉን እንዳለ በድጋሚ ያንብቡት፣ ዋናውን ርልሰ-ጉዳይ፣ ቁም-ነገሮች ለመለየት ፈልጉ
   (ለ) ዋናዎቹን ርእሶች በዋና ሐሳብ ለይተው አጠር ባለ እና በቀላል መግለጫ ይዘቱን ያስቀምጡ
   (ሐ) የድርጊት መግለጫውን ይፈትሹና ሰፋ ያለ የርእሰ ጉዳይ ዝርዝር በጥናት መርጃ ይጠቀሙ
(3) ሦስተኛው የንባብ ኡደት
   (ሀ) ሙሉ መጽሐፉን በድጋሚ ያንብቡት፣ ለጽሑፉ ታሪካዊ መቼትና የተለየ አውድ ለማግኘትና ለመለየት ከራሱ ከመጽሐፍ ቅዱስ ይሞክሩ
   (ለ) በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱትን ታሪካዊ ዓይነቶች ይዘርዝሩ
      (i) ጸሐፊው
      (ii) ዘመኑ
      (iii) ተቀባዮች
      (iv) ለመጻፍ የተለየ ምክንያት
      (v) ከመጽሐፉ ዓላማ ጋር የተያያዙ ባህላዊ መቼቶች ገጽታ
      (vi) ከታሪካዊ ሰዎችና ሁነቶች የሚጠቀሱ
   (ሐ) የምትተረጉመውን ያንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የዋና ፍሬ ሐሳቡን ዝርዝር ወደ አንቀጽ ደረጃ አስፋፉት። ዘወትር የሥነ ጽሑፉን አሀድ ለዩት፣ እንዲሁም የፍሬ ሐሳቡን ዝርዝር አውጡ። ይህም ምናልባት በርካታ ምእራፎች ወይም አንቀጾች ይሆናል። ይህም የዋናውን ጸሐፊ የሐሳብ ተገቢነት (ሎጂክ) ጽሑፋዊ ንድፍ ለመከተል ያስችልዎታል።
   (መ) የጥናት መረጃዎችን በመጠቀም የርሶን ታሪካዊ መቼት ይፈትሹ።
(4) አራተኛው የንባብ ኡደት

   (ሀ) የተለየውን የጽሑፍ ክፍል በልዩ ልዩ ትርጉሞች ያንብቡት
   (ለ) ሥነ-ጽሑፋዊ ወይም ሰዋሰዋዊ መዋቅሮችን ይፈልጉ
      (i) ተደጋጋሚ ሐረጎች፣ ኤፌ. 1፡6፣12፣13
      (ii) ተደጋጋሚ ሰዋሰዋዊ መዋቅሮች፣ ሮሜ. 8፡31
      (iii) ተጻጻራሪ ጽንሰ-ሐሳቦች

(ሐ) የሚከተሉትን ዓይነቶች ይመዝግቡ
- (i) ወሳኝ ቃላት
- (ii) ያልተለመዱ ቃላት
- (iii) ዋነኞቹ ሰዋሰዋዊ መዋቅሮች
- (iv) የተለዩ አስቸጋሪ ቃላት፣ ሐረጎች፣ እና ዓረፍተ ነገሮች

(መ) ዋነኞቹን ትይዩ አንቀጾች ይለዩ
- (i) ከርእሰ ጉዳዩ ጋር በጣም ግልጽ የሆነውን የማስተማሪያ አንቀጽ ይፈልጉ
  - ሀ) "ስልታዊ ሥነ-መለኮት" መጻሕፍት
  - ለ) የማጣቀሻ መጽሐፍ ቅዱስ
  - ሐ) የቃላት ዝርዝር
- (ii) በርእሰ ሐሳብህ ዙሪያ ተስማሚ አያዎአዊ ጥንዶችን ከጽሑፉ ይፈልጉ። አብዛኞቹ የቅዱሳት መጻሕፍት እውነታዎች ሚቀርቡት በአከራካሪ ጥንዶች ነው፤ በርካታ የመሠረተ እምነት ግጭቶች የሚመነጩት ከጽሑፍ አቃቂር ማውጣት ለትም ከፊል ከሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ክርክሮች ነው። መላው መጽሐፍ ቅዱስ ተመስጧዊ ነው፣ እኛም የተሟላውን መልእክት በመፈለግ፣ የመጽሐፍ ቅዱስን ሚዛን በትርጓሜአችን መጠበቅ ይኖርብናል።
- (iii) በዛው በመጽሐፉ ውስጥ ፣ በዛው ጸሐፊ ወይም በዛው የሥነ ጽሐሁፍ ዓይነት፣ አቻዊ ትይዩ ይፈልጉ፤ መጽሐፍ ቅዱስ የራሱ ምርጥ ተርጓሚ ነው፤ ምክንያቱም፣ አንድ ብቸኛ ጸሐፊ ስላለው— መንፈስ ቅዱስ።

(ሠ) ታሪካዊ መቼቱንና የተለየ አውዱን ለመፈተሽና ለማስተዋል የጥናት መረጃዎችን ይጠቀሙ።
- (i) ሀ. የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ
- (ii) ለ. የመጽሐፍ ቅዱስ አውደ-ጥበባት፣ መምሪያ መጻሕፍ እና መዝገበ ቃላት
- (iii) ሐ. የመጽሐፍ ቅዱስ መግቢያዎች
- (iv) መ. የመጽሐፍ ቅዱስ ሐተታዎች (በዚህ ነጥብ ላይ በጥናትዎ፣ አማኝ የኅብረተሰብ ክፍሎችን፣ ለትም የቀደምቱም ሆኑ ያሁኖቹ የራስዎን ጥናት ለማገዝና ለማረም ይጠቀሙባቸው።)

በዚህ ነጥብ ወደ አተገባበር እንቃኛለን። ጽሑፉን ከዋናው መቼት አንጻር ለመረዳት ጊዜ ወስደዋል፤ አሁን ደግሞ ይሄንኑ በሕይወትዎ፣ በባህልዎ ተገብሩት ይገባል። የመጽሐፍ ቅዱስ የመረዳት ሥልጣን ማለት በእኔ አገላለጽ፣ "ዋናው የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊ በእሱ ጊዜ ሊለው የፈለገውን መረዳትና ያንን በራሳችን ጊዜ መተርበር" ማለት ነው። ድርጊት መከተል ያለበት የዋናውን ጸሐፊ የትርጓሜ ሐሳብ በጊዜም ሆነ በሎጂክ አኳያ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስን አንቀጽ በጊዜው ምን ለማለት እንደፈለገ እስካላወቅን ድረስ በዘመናችን ልንተገብረው አንችልም! የመጽሐፍ ቅዱስ አንቀጽ ለው ያልፈለገውን ፈጽሞ ሊሆን አይችልም! የእርስዎ የተዘረዘረ የዋና ሐሳቦች ዝርዝር በአንቀጽ ደረጃ (የንባብ ሀደት ቁጥር 3)፣ የእርስዎ መመሪያ ይሆናል። ትግበራ መደረግ ያለበት በአንቀጽ ደረጃ እንጂ በቃላት ደረጃ መሆን የለበትም። ቃላት ትርጉም የሚኖራቸው በከፊለ- ጽሑፍ ደረጃ ነው፤ ሐረጎች ትርጉም የሚኖራቸው በከፊለ- ጽሑፍ ደረጃ ነው፤ ዓረፍተ ነገሮች ትርጉም የሚኖራቸው በከፊለ- ጽሑፍ ደረጃ ነው።

ብቸኛው ተመስጧዊ ሰው በትርጓሜው ሂደት ውስጥ ዋነኛ ጸሐፊው ነው። በመንፈስ ቅዱስ አብራሪነት (ማብራሪያ) የእሱን ምሪት ብቻ መከተል ይኖርብናል። ማብራሪያ ግን ተመስጦ ማለት አይደለም። "እግዚአብሔር እንደዚህ ይላል፣" ለማለት ከዋናው ጸሐፊ ሐሳብ ጋር የግድ መኖር አለበት። ትግበራ በተለይ መያያዝ ያለበት በሙሉ መጽሐፉ ሐሳብ ላይ ሲሆን፣ የተለየው የጽሑፍ አሀድ እና በአንቀጽ ደረጃ እያደገ በሚሄድ መልኩ። የዘመናችን ጉዳዮች መጽሐፍ ቅዱስን እንዲተረጉሙ አትፍቀዱ፤ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገር! ይህ ምናልባት የተወሰኑ ከጽሑፉ እንድናወጣ ይጠይቀን ይሆናል። ይህም ተገቢ የሚሆነው ጽሑፉ ለመርሖቹ ድጋፍ ሲሆን ነው። በሚያሳዝን መልኩ ግን፣ ብዙውን ጊዜ የእኛ መርሖዎች፣ "የእኛ" መርሖዎች ናቸው— የጽሑፉ መርሕ በመሆን ፈንታ።

መጽሐፍ ቅዱስን ለመተግበር፣ (ከትንቢት ብቻ በቀር) ማስታወስ የሚገባን ጠቃሚ ነገር ለእያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አንድና አንድ ብቻ ርጉም እንዳለው ነው። ያም ትርጉም ግንኙነቱ ከዋናው ጸሐፊ ሐሳብ ጋር፣ እሱም የዘመኑን ውድቀትም ሆነ ፍላጎት እንዴት እንዳቀረበው ነው። በርካታ ተስማሚ ድርጊቶች ከዚህ ከአንዱ ትርጉም ሊመነጩ ይችላሉ። አተገባበሩም የሚመሠረተው በተቀባዮቹ መሻት ላይ ሆኖ፣ መገናኘት ያለበት ግን ከዋናው ጸሐፊ ሐሳብ ላይ ነው።

እስካሁን አመክኖአዊ የሆነ እና የሥነ ጽሑፋዊ ሂደት በምን መልኩ በትርጉምና በአተገባበር ላይ መሆን እንዳለበት ለማብራራት ሞክሬአለሁ። አሁን ደግሞ ስለ ትርጉም መንፈሳዊ ገጽታ በአጭሩ ላብራራ። የሚከተሉት የመቆጣጠሪያ ዝርዝሮች ረድተውኛል፡

(1) ለመንፈስ ርዳታ ይጸልዩ (1ኛ ቆሮ. 1፡26-2፡16)።
(2) ከሚታወቅ ኃጢአት በግልዎ ምሕረትንና መንጻትን እንዲያገኙ ይጸልዩ (1ኛ ዮሐንስ 1፡9)።
(3) ስለ እግዚአብሔር ለማወቅ ከፍተኛ ፍላጎት እንዲያድርብዎ ይጸልዩ (መዝ. 19፡7-14፤ 42፡1፤ 119፡1)።
(4) አዲስ ማስተዋልን በሕይወትዎ ወዲያውኑ ይተግብሩ።
(5) ትሑትና ለመማር የተዘጋጁ ይሁኑ።

በሎጂካዊ ሂደት እና በመንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊ መሪነት መካከል ያለውን ሚዛን ለመጠበቅ በጣም አዳጋች ነው። የሁለቱን ሚዛን ለመጠበቅ የሚከተሉት ጥቅሶች ረድተውኛል፡

(1) ከ James W. Sire, *Scripture Twisting*, IVP, p. 17-18
"ማብራሪያ የሚመጣው ወደ እግዚአብሔር ሕዝቦች ሐሳብ ነው— ወደ መንፈሳዊ ምሑር ሳይሆን።በመጽሐፍ ቅዱስ ክርስትና የተለየ የመማሪያ ክፍል የለም፣ ምንም የተለየ የሚያብራራ፣ ተገቢው ትርጓሜ የሚመጣላቸው የተለዩ ሰዎች የሉም። እና ስለዚህ፣ መንፈስ ቅዱስ ልዩ የጥበብ፣ እውቀት፣ እና መንፈስን የመለየት ጸጋ ሲሰጥ፣ እነዚህ ባለጸጋ ክርስቲያኖች ብቻ የቃሉ ሥልጣናዊ ተርጓሚዎች እንዲሆኑ

መመደቡ አይደለም። ሁሉም የራሱ ሕዝቦች ሊማሩ፣ ሊዳኙ እና ሊለዩ፣ በእነሱ፣ እግዚአብሔር የተለየ ችሎታ ለሰጣቸው እንኳ ሥልጣን ያለውን መጽሐፍ ቅዱስ መጥቀስ እንደሚችሉ ነው። ለማጠቃለል፣ በሙሉው መጽሐፍ ያቀረብኩት ሐሳቤ መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛው የእግዚአብሔር መገለጥ ለሰው ልጆች ሁሉ ነው፣ በሚናገረው ሁሉ የመጨረሻው ባለሥልጣን ነው፤ በጥቅሉ ምሥጢራዊ ሳይሆን በማንኛው ባህል ባሉ ተራ ሰዎች በበቂ መልኩ ለመረዳት የሚቻል ነው።"

(2) በ በኬርኪጋርድ፣ በቤርናንድ ራም በሚገኘው፣ *Protestant Biblical Interpretation*, (Grand Rapids, Mich.: Baker Book House, 1970) p.. 75:

እንደ ኬርኪጋርድ ከሆነ ሰዋሰዋዊ፣ ቃላዊ፣ እና ታሪካዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች አስፈላጊ ናቸው፤ መቅደም ያለበት ግን የመጽሐፍ ቅዱስ ልባዊ ንባብ ነው። "መጽሐፍ ቅዱስን እንደ እግዚአብሔር ቃል ለማንበብ፣ ማንም አፍ ከልብ ሆኖ፣ በተጠንቀቅ ሆኖ፣ በጉጉትና ተስፋ በማድረግ፣ ከእግዚአብሔር ጋር እየተነጋገረ ማንበብ አለበት። መጽሐፍ ቅዱስን በሐሳብ ቢስነት ወይም በግዴለሽነት ወይም እንደ ትምህርት ወይም እንደ ልዩ ሞያ ማንበብ መጽሐፍ ቅዱስን እንደ እግዚአብሔር ቃል ማንበብ አይደለም። አንዱ የፍቅር ደብዳቤ እንደሚነበብ የሚያነበው ከሆነ እሱ እንደ እግዚአብሔር ቃል እያነበበው ነው።"

(3) H. H. Rowley in *The Relevance of the Bible*, p. 19

"የተሻለ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሑራዊ መረዳት፣ ምንም ያህል ፍጹም ቢሆን ሁሉንም ሀብቶች ሊያስገኝ አይችልም። ይህን መሰሉን መረዳት ዝቅ ለማድረግ አይደለም፣ ለፍጹም መረዳት አስፈላጊ ነው። ነገር ግን ፍጹም ይሆን ዘንድ ወደ መጽሐፉ መንፈሳዊ ሀብቶች የሚያመራ መንፈሳዊ መረዳት ማስፈለጉን ለማሳየት ነው። እናም ለዛ መንፈሳዊ መረዳት ከምሑራዊ ንቁነት የተሻለ ነገር ያስፈልጋል። መንፈሳዊ ነገሮች በመንፈሳዊነት የሚለዩ ናቸው፤ እናም የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ የመንፈሳዊ ተቀባይነት አዝማሚያ ሊኖረው ይገባል፣ ራሱን ይሰጥ ዘንድ እግዚአብሔርን ለመፈለግ ጉጉት ያለው፣ ከሳይንሳዊ ጥናቱ ባሻገር ወደ ተትረፈረፈ ሀብት ወራሽነት ወደሚያስገኝ ወደዚህ ከመጻሕፍት ሁሉ ታላቅ ወደ ሆነ።"

የጥናት መመሪያ ሐተታው የተሰናዳው የእርስዎን የትርጉም አግባብ በሚከተሉት መንገዶች ለማገዝ ነው፦

1. እያንዳንዱን መጽሐፍ የሚያስተዋውቅ አጭር ታሪካዊ የዋና ሐሳብ መግለጫ። "የንባብ ሀደት ቁጥር 3" ካነበበቡ በኋላ ይህን መረጃ ያረጋግጡት።
2. ጽሑፋዊ ማብራሪያዎች በየአንዳንዱ ምእራፍ መጀመሪያ ላይ ይገኛል። ይህም ሥነ ጽሑፋዊ አሀዱ እንዴት እንደተዋቀረ ለመመልከት ይረዳል።
3. በእያንዳንዱ ምእራፍ ወይም ሥነ ጽሑፋዊ አሀድ፣ የአንቀጽ ክፍሎች እና መግለጫ ጽሑፎች ከተለያዩ በርካታ ዘመናዊ ትርጉሞች ተሰጥተዋል፦
   ሀ. የመጽሐፍ ቅዱስ ኅብረት ሶሳይቲ የግሪክ ጽሑፍ፣ አራተኛ እትም (UBS4)
   ለ. አዲሱ የአሜሪካ መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ፣ 1995 የተሻሻለ (NASB)
   ሐ. አዲሱ ኪንግ ጀምስ እትም (NKJV)
   ሠ. አዲሱ የተከለሰው መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ (NRSV)
   ረ. አዲሱ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ (TEV)
   ሰ. የኢሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ (JB)

   የአንቀጽ ክፍሎች ተመስጧዊ አይደሉም። ከጽሑፉ መረጋገጥ ይኖርባቸዋል። ከተለያዩ የትርጉም ንድፈ ሐሳቦች እና ሥነመለኮታዊ አስተሳሰቦች የተለያዩ ዘመናዊ ትርጉሞችን በማወዳደር የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን ለመተንተን እንችላለን። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድ ዋነኛ እውነት ይዟል። ይህም "መሪ ዓረፍተ ነገር" ወይም "የጽሑፉ ማእከላዊ ሐሳብ" ተብሎ ይጠራል። ይህም ኅብር ያለው ሐሳብ አግባብነት ላለው ታሪካዊ፣ ሰዋሰዋዊ ርጉም ቁልፉ ነው። ማንም ከአንድ አንቀጽ ባነሰ መተርጎም፣ መስበክ ወይም ማስተማር ይኖርበትም! በተጨማሪም እያንዳንዱ አንቀጽ ከአካባቢው አንቀጾች ጋር እንደሚዛመድ አስታውሱ። ለዚህ ነው በአንቀጽ ደረጃ ያለ የዋና ሐሳቦች ርዝር ለሙሉ መጽሐፉ
   በጣም አስፈላጊ የሆነው። በዋናው ተመስጧዊ ጸሐፊ የተገለጠውን ርእስ ጉዳይ አመክኖአዊ ፍሰት መከተል መቻል ኖርብናል።

4. የቦብ ማስታወሻዎች በትርጓሜ የሚከተሉት ቁጥር በቁጥር የሆነውን አግባብ ነው። ይህም የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ እንድንከተል ያስገድደናል። ማስታወሻዎቹ ከብዙ አካባቢዎች መረጃዎችን ይሰጡናል።
   ሀ. ሥነ ጽሑፋዊ ተጓዳኝ ጽሑፍ
   ለ. ታሪካዊ፣ ባህላዊ መረዳቶች
   ሐ. ሰዋሰዋዊ መረጃ
   መ. የቃላት ጥናቶች
   ሠ. ጠቃሚ ትይዩ አንቀጾች
5. በተወሰኑ ነጥቦች በሐተታው ውስጥ፣ አዲሱ የአሜሪካን መደበኛ ትርጉም (በ1995 የተሻሻለ) የኅትመትጽሑፍ፣ ከሌሎች በርካታ ዘመናዊ ትርጉሞች በደጋፊነት ይኖራሉ፦

   ሀ. አዲሱ የኪንግ ጀምስ ቅጂ (አኪጀቅ)፣ የጽሑፋዊ እጅ ጽሑፎችን ማለት "ቴክስተስ ሪሴፕተስ" የሚከተል ነው።
   ለ. አዲሱ የተከለሰው መደበኛ ቅጂ (አየተመቅ)፣ ማለትም ቃል በቃል የሆነ ትርጉም ሲሆን፣ እሱም የተከለሰው መደበኛ ትርጉም ከቤተክርስቲያን ብሔራዊ ምክር ቤት ነው።
   ሐ. የጊዜው እንግሊዝኛ ትርጉም (የጊእት)፣ ከአሜሪካን የመጽሐፍ ቅዱስ ሶሳይቲ የተሻሻለ አቻ ትርጉም ነው።
   መ. የየሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ (1መቅ)፣ ከፈረንሳይ ካቶሊክ የተሻሻለ አቻ ትርጉም ላይ የተመሠረተ የእንግሊዝኛ ትርጉም ነው።
6. ግሪክኛን ለማያነቡ፣ ተነጻጻሪ እንግሊዝኛ ትርጉሞች በጽሑፉ ውስጥ ያሉትን አስቸጋሪ ክፍሎች ለመረዳት ይጠቅማሉ፦
   ሀ. የእጅ ጽሑፍ ልዩነቶች

ለ. አማራጭ የቃላት ፍቺዎች
ሐ. ሰዋሰዋዊ አስቸጋሪ ጽሑፎችና አወቃቀሮች
መ. አሻሚ ጽሑፎች

የእንግሊዝኛ ትርጉም እነዚህን ችግሮች ባያቃልልም እንኳ፣ ጠለቅ እና ውስጣዊ የሆነ ጥናት ይደረግ ዘንድ አላማና ስፍራውን ያሳያሉ።

7. በእያንዳንዱ ምእራፍ መዝጊያ ላይ ጠቃሚ የውይይት ጥያቄዎች ተሰጥተዋል፣ እነዚህም የምእራፉን ዋነኞቹን የትርጓሜ ጉዳዮች ዓላማ ለማድረግ የሚሞክሩ።

የጥናት መመሪያ የሆኑ ኮመንተሪዎች አሁን ማግኘት ይቻላል፡

ቅፅ. 0 "መጽሐፍ ቅዱስን መረዳት ይችላሉ " ሴሚናር
ቅፅ. 1 ለመጀመሪያዉ ክርስትና ቀዳሚ የሆነ፡ ማቴዎስ
ቅፅ. 2 ማርቆስ ወንጌል፡ ማርቆስ እና 1 ኛ እና 2ኛ ጴጥሮስ
ቅፅ. 3 ሀ. ሉቃስ ታሪክ ፀሐፊ: (የሉቀስ ወንጌል በ2003 ነበር)
ቅፅ. 3 ለ. ሉቃስ ታሪክ ፀሐፊ። የሐዋሪያት ሥራ (2003)
ቅፅ. 4 ጌታ ይወደው የነበር ደቀመዛሙርት ማስታወሻና ደብዳቤዎች: የዮሃንስ ወንጌል፣ 1ኛ፣2ኛ፣3ኛ ዮሐንስ
ቅፅ. 5 የጳውሎስ ወንጌል ፡ ሮሜ
ቅፅ. 6 የጳውሎስ መልእክት ለታወከችው ቤተ ክርስቲያን : 1ኛ እና 2ኛ ቆሮንቶስ (2002 ጀምሮ አለ)
ቅፅ. 7 የምጀምርያው የጳውሎስ መልእክት፡ ገላተያ 1ኛና እና 2ኛ ተሰሎንቄ
ቅፅ. 8 የጳውሎስ የእስር ቤት መልእክቶች፡ ቆላስይስ ኤፌሶን ፊልሞና ፊልጵስዩስ
ቅፅ. 9 የጳውሎስ 4ኛ ሚሲዮናዊ ጉዞ: 1ኛ ጢሞቴዎስ ጢቶ እና 2ኛ ጢሞቶስ
ቅፅ. 10 የአዲሱ ኪዳን የበላይነት፡ ዕብራዊያን
ቅፅ. 11 የኢየሱስ ግማሽ ወንድሞች ያዕቆብና ይሁዳ
ቅፅ. 12 ተስፋ በፈተና ጊዜ የመጨረሻ መጋረጃ የዮሐንስ ራዕይ
ቅፅ. 1 ሀ. ብሉይ ኪዳን፡ ሑሉ በነገር እንዴት እንደተጀመረ ዘፍጥረት 1፡ 1-11

# የመከፈቻ ትምህርት

I. ተዘውትረው ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላት ፍች

ሀ. የአምላክ ስሞች

1. ኤል

2. ኤሎሂም

3. ያህዌ

4. አዶን

5. ኤልሻዳይ

ለ. የጽሑፎችና የትርጉሞች ስሞች፡

1. ማሶረቲክ ጽሑፍ (MT)

2. ሴፕቱዋጂንት (LXX)

3. ቫልጌት

4. ሚድራሽ
   ሀ. ሃላካህ - የቶራህ ሐተታ
   ለ. ሃጋዳ - በሙሉው ብኪ ውስጥ ያሉ ታሪኮችና ምሳሌዎች

5. ታልሙድ
   ሀ. ሚሽናህ - የቶራህ ሥነ-ቃሎች ከጥንታዊ ዝነኛ ራቢዎች
   ለ. ጌማራ - የሚሽናህ ሐተታ በኋለኞቹ ራቢዎች

6. ታርጉምስ

7. የሙት ባሕር ጥቅሎች

II. ብሉይ ኪዳን ለምን ይጠናል

ሀ. እሱ ብቸኛው ቅዱስ ቃል ስለነበረ፣ ኢየሱስና ሐዋርያት የነበራቸው። እነርሱም አዘውትረው ከእርሱ ላይ ጠቅሰዋል።

ለ. እሱ የእግዚአብሔር የራሱ መገለጥ ነው። እሱ ተመስጧዊ ነው።
ማቴዎስ 5፡17
1. II ጢሞቴዎስ 3:15-17
2. I ቆሮንቶስ 2:9-13
3. I ተሰሎንቄ 2:13
5. I ጴጥሮስ 1:23-25
6. II ጴጥሮስ 1:20-21
7. II ጴጥሮስ 3:15-16

ሐ. እሱ ለእኛ ተጽፏል።
1. ሮሜ 4:23-24፤ 15:4
2. I ቆሮንቶስ 9:9-10፤ 10:6፣ 11

መ. ክርስቲያኖች ለእርሱ ምላሽ የሚሰጡት እንዴት መሆን አለበት?
1. በርካታ ታሪካዊ አገባቦች
2. ሙሉ ለሙሉ በመጠበቅ
3. ሙሉ ለሙሉ በመተው
4. እንደ መገለጥነቱ በማክበር፣ ግን በአሳሪነቱ ሳይሆን
5. የደኅንነት ማግኛ አይደለም
   ሀ. ሮሜ 4
   ለ. ሐዋርያት ሥራ 15፤ ገላትያ 3
6. ዕብራውያን

7. እሱ የእግዚአብሔር መገለጥ ነው ለሰዎች። እሱ በሕይወታችን ዓላማ አለው። እሱ ለአዲስ ኪዳን መሠረቱን ያበጃል (የሚፈጸም ተስፋ።)

III. ብሉይ ኪዳንን (መጽሐፍ ቅዱስ) እንዴት እንደምናጠና፣ አንዳንድ መሠረታዊ የትርጓሜ መርሖዎች፡

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው በሁነኛ የሰው ቋንቋ ነው፡
1. እግዚአብሔር እውነትን አይደብቅም።
2. እግዚአብሔር ራሱን በችሎታችን ልንረዳው በምንችለው መጠን አቅርቧል።

ለ. ለተገቢው ትርጉም ቁልፉ የዋነኛው ተመስጧዊ ደራሲ ሐሳብ ነው። ይህም በቃላቱ ግልጽ ፍቺ ላይ ይገኛል፣ በደራሲው ጥቅም ላይ እንደዋለበትና ዋነኞቹ ሰሚዎች እንደተረዱበት። ስለዚህ፣ አንዱ አንቀጹን በተገቢው ለመተርጎም የሚከተሉትን መረጃዎች ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡
1. ታሪካዊው መቼት፤
2. ጽሑፋዊው ዐውድ፤
3. ዘውጉ (ሥነ-ጽሑፋዊ ዓይነቱ)፤
4. ሰዋሰው (አገባብ)፤
5. የቃላቱ የወቅቱ (ዐውዱ) ፍቺ፤
6. የደራሲው ጽሑፋዊ አወቃቀር።

ሐ. መጽሐፍ ቅዱስ በሙሉ ተመስጧዊ ነው (II ጢሞ. 3፡16)፣ ስለዚህ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ እጅግ የተሻለው ተርጓሚ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ይህንንም "የእውነት ተመሳስሎ" ወይም ትይዩ አንቀጾች ብለን እንጠራዋለን፡
1. ግልጽ የሆነውን አንቀጽ እንሻለን፤
2. የእግዚአብሔርን ዋነኛውን ሐሳብ እንሻለን፤
3. በአያዎ (ፓራዶክስ) ጥንዶች የቀረበውን እውነት እንሻለን።

መ. አንዱ ባህላዊውንና በቅርብ ሀላፊውን ከሰዎች ባህል ወሰን ከሚያልፈውና ከዘላለማዊው እውነት እንዴት ሊለይ ይችላል?
1. የብኪ እውነት በአኪ ደራሲ ተረጋግጧልን?
2. መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ እውነት አቀራረቡ ላይ ወጥነት አለውን?
3. እውነቱ ግልጽ የሆኑትን ባህላዊ ቃላት ተላብሷልን?

IV. የጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ መሠረታዊ ካርታ፣ ከብኪ ጋር በተዛመደ

ሀ. የውኃ አካላት (ከምዕራብ ወደ ምስራቅ)
1. ሜዲትራኒያን ባሕር (ታላቁ ወይም ላይኛው ባሕር)
2. ዐባይ ወንዝ
3. ቀይ ባሕር
4. አቃባ ባሕረ-ሰላጤ
5. የግብጽ ወንዝ (ወይም ፏፏቴ)
6. ጨው ባሕር (ሙት ባሕር)
7. ዮርዳኖስ ወንዝ
8. ጃቦክ ወንዝ
9. አርኖን ወንዝ
10. የገሊላ ባሕር (ቺነሬስ ሐይቅ)
11. ኤፍራጥስ ወንዝ
12. ጤግሮስ ወንዝ
13. ፋርስ ባሕረ-ሰላጤ (ታችኛው ባሕር)

ለ. በብኪ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ተጽዕኖ ያላቸው ሀገራት (ከምዕራብ ወደ ምስራቅ)
1. ሮም
2. ግሪክ
3. ካፍቶር (ክሬቲ)
4. ኬጢም (ቆጵሮስ)
5. ግብፅ
6. ፍልስጥኤም
7. ይሁዳ
8. እስራኤል
9. ኤዶም
10. ሞአብ
11. አሞን
12. ፍንቄ (ሊባኖስ)
13. ሶርያ
14. ኬጢ (አናቶሊያ)
15. ዓረብ
16. አሶር
17. ባቢሎን
18. ፋርስ
19. ሜዶን
20. ኤላም

ሐ. የዋነኞቹ አገሮች ዋና ከተማዎች [ሁለተኛ ሙከራ]
1. ሜምፊስ (ግብፅ)
2. ኢየሩሳሌም (ይሁዳ)
3. ሰማርያ (እስራኤል)
4. ጢሮስ (ፍንቄ)
5. ደማስቆ (ሶርያ)
6. ነነዌ (አሶር)
7. ባቢሎን (ባቢሎን)
8. ሱሳ (ፋርስ)

መ. ሌሎች ሁነኛ ከተሞች [ሦስተኛ ሙከራ]
1. ዑር
6. ቤተልሔም

2. ካራን
3. ሜጊዶ
4. ሴኬም
5. ኢያሪኮ
7. ሔብሮን
8. ቤርሳቤህ
9. አቫሪስ/ዞን/ታኒስ
10. ቴብስ

ሠ. ተራሮች [ሦስተኛ ሙከራ]
1. አራራት
2. ሔርሞን
3. ታቦር
4. ኤላብ ወይም ገሪዛን (ሴኬም)
5. ቀርሜሎስ
6. ኔቦ/ፒስጋህ
7. ጽዮን/ሞሪያ (ኢየሩሳሌም)
8. ሲና/ኮሬብ

V. የብሉይ ኪዳን መሠረታዊ የጊዜ መስመር

ሀ. ቀናቸው ያልተመዘገበ ሁነቶች (ዘፍ. 1-11)
1. ፍጥረት
2. ውድቀት (የሰው)
3. የጥፋት ውኃ
4. የባብኤል ግንብ


ለ. አስር ቀናት እና ሁነቶች፡
1. የአባቶች ዘመን (ዘፍ. 12-50 እና ኢዮብ) — 2000 ቅ.ል.ክ.
2. ዘጸአት (ዘጸአት) — 1445/1290 ቅ.ል.ክ.
3. ድል (ኢያሱ) — 1400/1250 ቅ.ል.ክ.
4. የተባበረው መንግሥት (አገዛዝ) (ሳኦል፣ ዳዊት፣ ሰሎሞን) — 1000 ቅ.ል.ክ.
5. የተከፋፈለው መንግሥት (ርሆቦም-ይሮቦአም I) — 922 ቅ.ል.ክ.
6. የሰማርያ ውድቀት (እስራኤል) — 722 ቅ.ል.ክ.
7. የኢየሩሳሌም ውድቀት (ይሁዳ) — 586 ቅ.ል.ክ.
8. የቂሮስ አዋጅ/ትዕዛዝ (ፋርስ — 538 ቅ.ል.ክ.
9. ሁለተኛው መቅደስ — 516 ቅ.ል.ክ.
10. የብኪ መዝጊያ (ሚልክያስ) — 430 ቅ.ል.ክ.


ሐ. የእግዚአብሔር ሕዝብ ዋነኛ ጠላቶች፡
1. ግብፅ
2. ከነዓን
3. ፍልስጥኤም
4. ሶርያ
5. አሦር
6. ባቢሎን
7. ፋርስ
8. ግሪክ
9. ሮም


መ. የጊዜው መስመር ነገሥታት፡
1. የተባበረው መንግሥት
   ሀ. ሳኦል
   ለ. ዳዊት
   ሐ. ሰሎሞን
2. እስራኤል
   ሀ. ይሮብአም I
   ለ. አካብ
   ሐ. ይሮብአም II
   መ. ሆሼአ
3. ይሁዳ
   ሀ. ሮቦአም
   ለ. ኡዚአ
   ሐ. ሕዝቅያስ
   መ. ምናሴ
   ሠ. ኢዮስያስ
   ረ. ይሆሃዝ (3 ወራት)
   ሰ. ዮሀኪም
   ሸ. ዮሐኪም (3 ወራት)
   ቀ. ሰዴቅያስ
   በ. ጌድሊያህ (የፋርስ ገዥ)
4. ፋርስ
   ሀ. ሲረስ II (550-530 ቅ.ል.ክ.)
   ለ. ካምቢሰስ (530-522 ቅ.ል.ክ.)
   ሐ. ዳርዮስ I (522-486 ቅ.ል.ክ.)
   መ. ዘረክሲስ I (486-465 ቅ.ል.ክ.)

ሥ. አርጤክስስ I (465-424 ቅ.ል.ክ.)


5. የይሁዳንና የእስራኤልን ነገሥታት እንዲሁም የአሦርን፣ የባቢሎንን፣ የፋርስን፣ እና የግሪክን ነገሥታት ሙሉ ዝርዝር በI እና II ነገሥት መጨረሻ ላይ ተመልከት።



MALACHI
WALLS OF JERUSALEM - NEHEMIAH
THIRD RETURN - EZRA
ARTAXERXES I (P)
XERXES I - AHASUERUS (P)
EZRA 7-10
NEH.
ESTHER
DARIUS I (P)
CAMBEES II (P)
CYRUS II (P)
OBADIAH
JOEL
HAGGAI
ZECHARIAH
EZRA 1-6
SECOND RETURN - ZERUBBABEL
FIRST RETURN - SHESHBAZZAR
BABYLON
PERSIA
BELSHAZZAR (B)
NABONIDUS (B)
EXILE
NEBUCHADNEZZAR (B)
JEREMIAH
EZEKIEL
DANIEL
NAHUM
HABAKKUK
ZEPHANIAH
NABOPOLASAR (B)
ASHURBANIPAL (A)
ESARHADDON (A)
SENNACHERIB (A)
ASSYRIA
SARGON II (A)
SHALMANEZAR V (A)
TIGLATH PILESER III (A)
JONAH
AMOS
HOSEA
ISAIAH
MICAH
I & II KINGS
II CHRONICLES
p - GEDALIAH (P)
o - ZEDEKIAH (J)
n - JEHOIACHIN (J)
m - JEHOIAKIM (J)
l - JEHOAHAZ (J)
k - JOSIAH (P)
j - MANASSEH (J)
i - HEZEKIAH (J)
h - UZZIAH (J)
g - JEROBOAM II (I)
SYRIA
ELIJAH
ELISHA
ISRAEL
JUDAH
f - AHAB (I)
e - JEROBOAM I (I)
d - REHOBOAM (J)
c - SOLOMON (UM)
b - DAVID (UM)
a - SAUL (UM)
PHILISTIA
S (SDS)
R.
JD.
I & II SAMUEL
I CHRONICLES
CANAAN
JOSH.
DEUT.
NUM.
EGYPT
LEV.
EX.
GEN. 12-50
JOB
1
2
3
4
5
6
7
8
9
10
TLEY
SONS IN'L '96


WATERWAYS
ANCIENT NEAR EAST
N
S
E
W
11
12
13



NATIONS
HITTITE
KITTIM
SYRIA
PHOENICIA
ISRAEL
AMMON
PHILISTIA
JUDAH
MOAB
EDOM
EGYPT
MIDIAN
ARABIA
ASSYRIA
MEDIA-
PERSIA
ELAM
BABYLON
N
W
E
S
ANCIENT
NEAR EAST


ANCIENT NEAR EAST
MOUNTAINS
CAPITALS
N
S
E
W
1
2
3
4
5
6
7
8



OTHER CITIES
1.
2.
3.
4.
5.
6.
7.
8.
9.
10.
N
W
E
S
ANCIENT
NEAR EAST

# አሪት ዘፍጥረት መግቢያ

I. የመጽሐፉ ስም

ሀ. በዕብራይስጥ (ኤምቲ) የመጽሐፉ የመጀመሪያ ቃል ነው፣ (*Bereshith ቤሪሺዝ*) ፤ "በመጀመሪያ" ወይም "በመጀመሪያው ላይ።"

ለ. በሴፕቱዋጂንት ትርጉም እሱ "ዘፍጥረት" ማለት ነው፣ ፍችውም "መጀመሪያ" ወይም "መገኛ" ይኸውም ከ2፡4ሀ ላይ የተወሰደ። ይህ የደራሲው ቁልፍ "የፍሬ ሐሳብ ሐረግ" ወይም ምስያ ሊሆን ይችላል፣ የተለያዩ ሥነ-መለኮታዊ ባዮግራፊዎችን አንድ ላይ ለማያያዝ፣ የባቢሎናውያን ጥንታዊ ጽሑፍ (ኩኒፎርም) ጸሐፊዎች እንደሚያደርጉት። ቁልፉ የፍሬ-ሐሳብ ሐረግ ወደ ኋላ ነው የሚመለከተው፣ ከወደፊት ይልቅ።

II. ካኖናዊ (ቅዱስ ቃል)

ሀ. ይህ የዕብራይስጥ ካኖን የመጀመሪያው ምድብ ክፍል ነው "ቶራ" ወይም "አስተምህሮዎች" ወይም "ሕግ" ተብሎ የሚጠራው።

ለ. ይህ ምድብ በሴፕቱዋጂንት ፔንታቲዩች (አምስት ጥቅሎች) በማለት ይታወቃል።

ሐ. እሱም አንዳንድ ጊዜ "አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት" ይባላል፣ በእንግሊዝኛ።

መ. ከዘፍጥረት — ዘዳግም ቀጣይነት ባለው መልኩ በሙሴ የተመዘገበ ነው፣ ፍጥረትን በተመለከተ በሙሴ ሕይወት።

III. ዘውግ - የዘፍጥረት መጽሐፍ በቀዳሚነት ሥነ-መለኮታዊ፣ ታሪካዊ ትርክት ነው፣ ነገር ግን ደግሞ ሌሎች ዓይነቶች ጽሑፋዊ ዘውግን ያካትታል፡

ሀ. ቅኔ፣ ምሳሌ፣ 2:23፤ 4:23 (1-2 ይሆናል)

ለ. ትንቢት፣ ምሳሌ፣ 3:15፤ 49:1 (ደግሞም ቅኔያዊ)

IV. ደራሲው

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ የደራሲውን ስም አይገልጽም። ዘፍጥረት የ "እኔ" ክፍሎች የሉትም፣ እንደ ዕዝራ፣ ነህምያ ወይም የ "እኛ" ክፍል የለውም፣ እንደ ሐዋርያት ሥራ።

ለ. የአይሁድ ልማድ/ወግ፡
1. የጥንታዊ አይሁድ ጸሐፍት የሚሉት ሙሴ እንደ ጻፈው ነው፡
    - ሀ. ቤን ሲራህ "መክብብ" 24፡23፣ በ185 ቅ.ል.ክ. አካባቢ ተጻፈ
    - ለ. ባባ ባትራ 14ለ፣ የታልሙድ ክፋይ
    - ሐ. ፊሎ የአሌክሳንደርያ፣ ግብፅ፣ የአይሁድ ፈላስፋ ከኢየሱስ አገልግሎት ጥቂት ቀደም ብሎ የጻፈ
    - መ. ፍላቪዩስ ጆሴፈስ፣ የአይሁድ ታሪክ ጸሐፊ (ባለ ታሪክ)፣ ከኢየሱስ አገልግሎት ወዲያው የጻፈ።
2. ቶራ አንድ ወጥ ኅብር ያለው ታሪካዊ መዝገብ ነው። ከዘፍጥረት ቀጥሎ እያንዳንዱ መጽሐፍ የሚጀምረው "እናም" በሚለው መስተዋድድ ነው (ከዘኁልቍ በቀር)
3. ይህ ለሙሴ የሆነ መገለጥ ነበር
    - ሀ. ሙሴ እንዲጽፍ የተባለው፡
        - (1) ዘጸአት 17፡14
        - (2) ዘጸአት 24፡4፣ 7
        - (3) ዘጸአት 34፡27፣ 28
        - (4) ዘኁልቁ 33፡2
        - (5) ዘዳግም 31፡9፣22፣ 24-26
    - ለ. እግዚአብሔር በሙሴ በኩል መናገሩ ተገልጿል፡
        - (1) ዘዳግም 5፡4-5፣ 22
        - (2) ዘዳግም 6፡1
        - (3) ዘዳግም 10፡1
    - ሐ. ሙሴ የቶራን ቃል ለሕዝቡ መናገሩ ተገልጿል
        - (1) ዘዳግም 1፡1፣ 3
        - (2) ዘዳግም 5፡1
        - (3) ዘዳግም 27፡1

(4) ዘዳግም 29፡2
(5) ዘዳግም 31፡1፣ 30
(6) ዘዳግም 32፡44
(7) ዘዳግም 33፡1

4. የብኪ (ብሉይ ኪዳን) ደራስያን ሙሴ እንደጻፈው ገልጸዋል፡
   ሀ. ኢያሱ 8፡31
   ለ. II ነገሥት 14:6
   ሐ. ዕዝራ 6:18
   መ. ነህምያ 8:1፤ 13:1-2
   ሠ. II ዜና 25:4፤ 34:12፤ 35:12
   ረ. ዳንኤል 9:11
   ሰ. ሚልክያስ 4:4

ሐ. ክርስቲያናዊ ልማድ/ወግ

1. ኢየሱስ ከቶራ ለሙሴ የሆኑትን ጥቅሶች ወስዷል፡
   ሀ. ማቴዎስ 8:4፤ 19:8
   ለ. ማርቆስ 1:44፤ 7:10፤ 10:5፤ 12:26
   ሐ. ሉቃስ 5:14፤ 16:31፤ 20:37፤ 24:27፣ 44
   መ. ዮሐንስ 5:46-47፤ 7:19፣ 23
2. ሌሎች የአኪ (አዲስ ኪዳን) ደራስያን ከቶራ ለሙሴ የሆኑትን ጥቅሶች ወስደዋል:
   ሀ. ሉቃስ 2:22
   ለ. ሐዋ. 3:22፤ 13:39፤ 15:1፣ 15-21፤ 26:22፤ 28:23
   ሐ. ሮሜ 10:5፣ 19
   መ. I ቆሮንቶስ 9:9
   ሠ. II ቆሮንቶስ 3:15
   ረ. ዕብራውያን 10:28
   ሰ. ራዕይ 15:3
3. አብዛኞቹ የጥንት ቤተ-ክርስቲያን አባቶች የሙሴን ደራሲነት ተቀብለዋል። ኢሬኒዩስ፣ የአሌክሳንደሪያ ክሌመንት፣ ኦሪጅን እና ተርቱሊያን ሁሉም በአሁኑ የዘፍጥረት ካኖናዊነት ጋር ሙሴ ስላለው ግንኙነት ጥያቄዎች አሏቸው።

መ. ዘመናዊው አስተምህሮት

1. በቶራ ላይ አንዳንድ የአዘጋጆች ተጨማማሪዎች መደረጋቸው ግልጽ ነው (ይኸውም ጥንታዊው ሥራ ለአሁኑ አንባቢ እንዲረዳ ለማድረግ ታሳቢ ያደረገ ይመስላል)፡
   ሀ. ዘፍጥረት 12:6፤ 13:7፤ 14:14፤ 21:34፤ 32:32፤ 36:31፤ 47:11
   ለ. ዘጸአት 11:3፤ 16:36
   ሐ. ዘኍልቍ 2:3፤ 13:22፤ 15:22-23፤ 21:14-15፤ 32:33
   መ. ዘዳግም 3፡14፤ 34፡6
   ሠ. የጥንቶቹ ጸሐፊዎች እጅግ የሠለጠኑና የተማሩ ነበሩ። ስልታቸውም ከአገር አገር ይለያያል፡
      (1) በሞሶፖታሚያ ምንም ነገር ላለመቀየር እጅግ ጥንቁቆች ነበሩ፣ እንዲያውም ለርግጠኝነት ሥራቸውን ይፈትሹ ነበር። እዚህ ጥንታዊ የሱሜርያን የጽሑፋዊ የግርጌ ማስታወሻ ይገኛል፣ ("ሥራው ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ይጠናቀቃል፣ ቅጅም ይደረግለታል፣ ይከለሳል፣ ይነጻጸራል፣ እናም ፊርማ በፊርማ ይረጋገጣል" ከ1400 ቅ.ል.ክ. አካባቢ)
      (2) በግብፅ ነጻ ሆነው የጥንታዊ ጽሑፎችን ይከልሱ ነበር፣ ለዘመነኛው አንባቢ እንዲመቹ ለማድረግ። በቁምራን ያሉ ጸሐፍትም ይሄንን አግባብ ይከተሉ ነበር።
2. የ19ኛው ክፍለ-ዘመን ሊቃውንት ባወጡት ንድፈ-ሐሳብ መሠረት፣ ቶራህ ድብልቅ ሰነድ ነው፣ ከበርካታ ምንጮች የሆነ፣ በተራዘመ የጊዜ ቀመር ውስጥ (ግራፍት - ዌልሃዩሰን)። ይህም የተመሠረተው፡
   ሀ. የእግዚአብሔር ልዩ ልዩ ስሞች፣
   ለ. ግልጽ የሆኑ ተመሳሳይ ጥንዶች፣ በጽሑፉ ውስጥ የሚገኙ፣
   ሐ. ያለፉት ትረካዎች መልኮች፣
   መ. ያለፉት ትረካዎች ሥነ-መለኮት።
3. ታሳቢ ምንጮችና ቀናት፡
   ሀ. የ *ጀ/J* ምንጭ (ለያህዌ ጥቅም ላይ የዋለ) – 950 ቅ.ል.ክ.
   ለ. የ *ኢ/E* ምንጭ (ለኤሎሂም ጥቅም ላይ የዋለ) – 850 ቅ.ል.ክ.
   ሐ. *ጀኢ/JE* ተደባልቆ - 750 ቅ.ል.ክ.

መ. የ *ዲ/D* ምንጭ ("የሕግ መጽሐፍ፣" II ነገሥ. 22:8፣ በኢዮስያስ የተሐድሶ ጊዜ የተገኘ፣ ቤተ-መቅደሱ ዳግም ሲታነጽ፣ ምናልባትም የዘዳግም መጽሐፍ ሊሆን ይችላል፣ በኢዮስያስ ጊዜ በነበረ ያልታወቀ ካህን የተጻፈ፣ ተሐድሶውን ለመደገፍ።) - 621 ቅ.ል.ክ.

ሠ. የ *ፒ/P* ምንጭ (ሁሉም የካህናዊ ቁሳቁስ፣ በተለይም የአምልኳዊና የደንብና ሥርዓት) 400 ቅ.ል.ክ.

ረ. ቶራህ ላይ የአዘጋጆች ተጨማማሪ መደረጉ ግልጽ ነው። እንዲህ የሆነበትን አይሁድ ሲያስረግጡ፡

(1) ሊቀ-ካህኑ፣ ጽሕፈቱ በሚከናወንበት ጊዜ፣

(2) ነቢዩ ኤርምያስ፣

(3) ጸሐፊው ዕዝራ - IV እስድራስ የሚለው እሱ ድጋሚ መጻፉን ነው፣ ምክንያቱም ዋነኛው በ586 ቅ.ል.ክ. በኢየሩሳሌም መውደቅ ጊዜ ስለ ጠፋ፣

ሰ. ሆኖም፣ የ ጄ. ኢ. ዲ. ፒ. ንድፈ-ሐሳብ የሚለው በአብዛኛው ስለ እኛ ዘመናዊ ጽሑፋዊ ንድፈ- ሐሳቦችና ምድቦች ነው፣ ከቶራ ከተገኘው ማስረጃ ይልቅ (R.K. Harrison, *Introduction to the Old Testament,* pp. 495-541 *Tyndale's and Commentaries* "Leviticus"pp 15-25)።

ሸ. የዕብራይስጥ ሥነ-ጽሑፍ ባሕርያት

(1) ተመሳሳይ ጥንዶች፣ እንደ ዘፍ. 1 እና 2 የመሳሰሉት በዕብራይስጥ የተለመዱ ናቸው። ዘወትርም አጠቃላይ ገለጻ ይደረጋል፣ ከዚያም የተለየ (ዝርዝር) ትረካ ይቀርባል። ይህም ምናልባት እውነትን የማስረገጫ መንገድ ወይም አፍአዊውን ትርክት ለማስታወስ የሚያግዝ ይሆናል።

(2) ጥንታውያኑ ራቢዎች የሚሉት ሁለቱ እጅግ የተዘወተሩት የእግዚአብሔር ስሞች ሥነ-መለኮታዊ ጠቀሜታ አላቸው፡
(ሀ) ያህዌ - የመለኮት የኪዳን ስም፣ እሱም ከእስራኤል ጋር በተዛመደ፣ እንደ አዳኝና እንደ ተዋጂ (መዝ. 103)።
(ለ) ኤሎሂም - መለኮት እንደ ፈጣሪ፣ ሰጪ፣ እና አኗሪ በምድርላይ ላለው ፍጥረት ሁሉ (መዝ. 104)።

(3) እሱም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባልሆኑ ላይ የተለመደ ነው፣ በቅርብ ምስራቅ ሥነ-ጽሑፍ፣ ለተለያዩ ስልቶች (ስታይልስ) እና ቃላት፣ ወጥነት ያላቸው ጽሑፋዊ ሥራዎችን ለመፍጠር (Harrison, pp. 522-526 *ሀሪሰን፣ ገጽ* 522-526)።

ሠ. የጥንታዊው ቅርብ ምስራቅ ሥነ-ጽሑፍ ማስረጃ የሚያመለክተው ሙሴ የተጻፉ የኩኒፎርም ሰነዶችን ወይም የሞሶፖታሚያን የሥነ-ቃል ስልት መጠቀሙን ነው፣ ዘፍጥረትን ለመጻፍ። ይህም በምንም መልኩ ተመስጧዊነቱን ለማሳነስ አይደለም፣ ነገር ግን የዘፍጥረትን መጽሐፍ ጽሑፋዊ ክስተት (ገጽታ) ለማስረዳት መሞከር እንጂ ነው። ከዘፍ. 37 ጀምሮ የግብፅ ስልት ተጽዕኖ ተመልክቷል፣ ቅርጽና ቃላት እያመለከቱ የሚመስሉት፣ ሙሴ አንድም ጽሑፋዊ ውጤቶችን ወይም የኢይዝራኤላውያንን ጊዜ ሥነ-ቃል መጠቀሙን ነው፣ በግብፅ። የሙሴ መደበኛ ትምህርት ባጠቃላይ ግብፃዊ ነው! የፔንታቲሁች ትክክለኛ ጽሑፋዊ አወቃቀር ርግጠኝነት የለውም። እኔ እንደማምነው ሙሴ የእጅግ አብዛኛው የፔንታቲሁች አቀናባሪና ደራሲ መሆኑን ነው፣ ምንም እንኳ ጸሐፍትን እና/ወይም የጽሑፍ እና ሥነ-ቃሎችን ተጠቅሞ ቢሆንም። የእነዚህ የመጀመሪያዎቹ ጥቂት መጻሕፍት ታሪካዊነትና ታማኝነት ርግጠኛ ነው።

V. ጊዜው

ሀ. ዘፍጥረት የሚሸፍነው ከኮስሞስ (ፍጥረታት) መፈጠር እስከ አብርሃም ቤተሰብ ያለውን ጊዜ ነው። የአብርሃምን ሕይወት ከምድራዊው (ሥጋዊው) ሥነ-ጽሑፍ ጊዜ ቀኑን ማስቀመጥ ይቻላል። ግምታዊው ጊዜ 2000 ቅ.ል.ክ. ይሆናል፣ ሁለተኛው ሚሊኒየም ዓ.ዓ። የዚህም መሠረቱ የሚሆነው፡

1. አባት ለቤተሰቡ እንደ ካህን ማገልገሉ (እንደ ኢዮብ)፣
2. ሕይወት ዘላንነት መሆኑ፣ መንጎችንና ከብቶችን በመከተል፣
3. በዚህ ጊዜ የነበረው የሴማዊ ሕዝቦች ፍልሰት፣ ።

ለ. የዘፍጥረት 1-11 የቀድሞ ሁነቶች እውነተኛ "ታሪካዊ" ሁነቶች ናቸው ("ታሪካዊ ድራማ" ሊሆን የሚችል) ነገር ግን በወቅቱ በነበረው እውቀት ቀኑን ማስቀመጥ ያልተቻለ።

ሐ. ዘፍጥረት ሲጠና የግድ መታወስ የሚኖርበት ታሪካዊ ሁነቶቹ የተመዘገቡት በሙሴ መሆኑን ነው፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከግብፅ ሲወጣ የመራው፣ አንድም፡ (1) 1445 ቅ.ል.ክ.፣ 1 ነገሥት 6:1 ላይ በመመሥረት፤ ወይም (2) 1290 ዓ.ዓ በጥንታዊ ቅርስ (አርኪዎሎጂ) ላይ በመመሥረት። ስለዚህ፣ አንድም በሥነ-ቃል፣ ባልታወቁ ጽሑፋዊ ምንጮች ወይም በቀጥተኛ መለኮታዊ መገለጥ፣ ሙሴ "ሁሉም እንዴት እንደጀመረ" እና "ለምን" እንደሆነ ጽፏል።

VI. ታሪካዊ መቼቱን የሚያስረግጡ የማስረጃ ምንጮች

ሀ. ሌሎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ መጻሕፍት

1. ፍጥረት - መዝሙር 8፣ 19፣ 50 እና 104
2. የአብርሃም ጊዜ - ኢዮብ

ለ. *ሥጋዊ የጥንታዊ ቅርስ ምንጮች*

1. የቀድሞ የታወቁ ጽሑፋዊ ትይዩዎች፣ የዘፍጥረት 1-11 ባህላዊ መቼት፣ የኢብላ ኩኒፎርም ሰሌዳዎች (የድንጋይ ላይ ጽሑፎች)፣ ከሰሜን ሶርያ፣ 2500 ቅ.ል.ክ. አካባቢ ጊዜ ያስቆጠሩ፣ በአካድያን የተጻፉ።
2. ፍጥረት
   ሀ. ከሜሶፖታሚያ የፍጥረት ጽሑፍ ጋር ቅርበት ያለው፣ *Enuma Elish*, ከ1900-1700 ዓ.ዓ አካባቢ ጊዜ ያስቆጠረ፣ በአሹርባኒፓል ቤተ-መጻሕፍት የተገኘ በነነዌና በሌሎች በበርካታ ስፍራዎች። ሰባት የኩኒፎርም ሰሌዳዎች (የድንጋይ ላይ ጽሑፎች) በአካድያን በማድሩክ የተጻፉ፣ እነርሱም ፍጥረትን የሚገልጹ አሉ።
      (1) አማልክት፣ *Apsu* (ንጹሕ ውኃ ወንዴ) እና *Tiamat* (የጨው ውኃ ሴቴ) የማይታዘዙ፣ ረብሸኛ ልጆች አሏቸው። እነዚህ ሁለት አማልክት ወጣቶቹን አማልክት ጸጥ ሊያሰኙ ይሞክራሉ።
      (2) አንደኛው የአማልክቱ ልጅ፣ ማርዱክ፣ ቲያማትን ለማሸነፍ ረድቷል። እሱም ከእርሷ ሰውነት ምድርን አበጅቷል።
      (3) *Marduk*, ሰውነትን (ሰውን) አበጅቷል፣ ከሌላ ከተሸነፈ አምላክ (ጣኦት)፣ ኪንጉ፣ እሱም *Tiamat* የወንድ ጓደኛ የነበረ፣ ከአፐሱ ሞት በኋላ። ሰብዕና የመጣው *Kingu's* ደም ነበር።
      (4) ማድሩክ የባቢሎናውያን አማልክት (ጣዖታት) አለቃ ተደርጓል።
   ለ. "የፍጥረት ማኅተም (እሽግ)" የኮኒፎርም ጽሑፍ ነው፣ እሱም ራቁት ወንድና ሴት ምስል ያለው፣ ከፍሬአማ ዛፍ አጠገብ፣ ከዛፉ ቅርንጫፍ ዙሪያ የተጠመጠመ እባብ ያለበት፣ በሴቲቱ ትከሻ ላይ አቅጣጫ የያዘ፣ እሷን እንደሚያናግር ያለ።
3. ፍጥረትና የጥፋት ውሀ - "*The Atrahasis Epic*" *"የአትራሀሲስ ረጅም ግጥም (ኢፒክ)" የአነስተኞቹን ጣዖታት (አማልክት) ዐመጻ መዝግቧል፣ ከሥራ ብዛት የተነሣና ሰባቱ የሰው ጥንዶች በመፈጠራቸው ምክንያት፣ የእነዚህን አነስተኛ አማልክትን ሥራ ለማካሄድ። ምክንያቱም: (1) የሰው ብዛት፣ እና (2) ጫጫታ። የሰው ልጆች ቁጥር እንዲቀንስ ሆነ፣ በመቅሠፍት፣ በሁለቱ ረሀቦች እና በመጨረሻም በጥፋት ውሀ፣ Enlil በታቀደ። እነዚህ ዋነኛ ሁነቶች በተመሳሳይ ቅደም ተከተል ዘፍጥረት 1-8 ላይ ተመልክተዋል። ይህ የኩኒፎርም ጽሑፍ ጊዜው በግምት በተመሳሳይ ጊዜ ላይ ነው፣ እንደ Enuma Elish* and the *Gilgamesh Epic* (ረጅም ግጥም)፣ 1900 – 1700 ቅ.ል.ክ. አካባቢ። ሁሉም በአካዲያን ናቸው።
4. የኖኅ የጥፋት ውሀ
   ሀ. የሱሜርያን የድንጋይ ጽሑፍ፣ ከኒፑር፣ *ኢሪዱ ጀነሲስ* ተብሎ የሚጠራው፣ 1600 ቅ.ል.ክ. አካባቢ የሆነው፣ ስለ Zivsudra እና ስለሚመጣው ጎርፍ (የጥፋት ውኃ) ይናገራል።
      (1) *Enka*,የውኃ አምላክ፣ ስለሚመጣው ጎርፍ አስጠንቅቋል።
      (2) *Zivsudra ንጉሥ*-ካህን፣ በትልቅ ጀልባ ዳነ።
      (3) ጎርፉ በሰባት ቀን አበቃ።
      (4) *Zivsudra* የጀልባውን መስኮት ከፍቶ መጠነኛ ወፎችን ለቀቀ፣ ደረቅ ምድር መኖሩን ለማረጋገጥ።
      (5) እሱ ደግሞ የበሬና በግ መሥዋዕት አቀረበ፣ ጀልባውን ትቶ ሲወጣ።
   ለ. የባቢሎናውያን የጥፋት ውኃ ጽሑፍ ቅንብር ከአራት የሱሜርያን ተረቶች፣ *Gilgamesh Epic* በመባል የሚታወቀው በዋነኛነት ጊዜው ከ2500 – 2400 ቅ.ል.ክ. ነው የሚያመለክተው፣ ምንም እንኳ የጽሑፍ ቅንብሩ መልክ ኩኒፎርም አካዲያን ቢሆንም፣ እጅግ ወዲህኛ ነው። እሱም ከጥፋት ውኃ ስለተረፈው ይናገራል፣ አትናፒሽቲም፣ እሱም *ለጊልጋሚሽ* ይነግረዋል፣ ለ *Uruk* ንጉሥ፣ እንዴት ከታላቁ የጥፋት ውኃ እንደዳነና የዘላለም ሕይወት እንደተሰጠው።
      (1) *Ea*, ፣ የውኃ አምላክ፣ ስለ ሚመጣው የጥፋት ውኃ አስጠንቅቋል፣ እናም *Utnapishtim* (የባቢሎናውያን *Zivsudra* ዓይነት) ጀልባ እንዲሠራ ነግሮታል።
      (2) *Utnapishtim* እና ቤተሰቡ፣ ከተመረጡ የፈውስ ዕጽዋት ጋር ከጥፋት ውኃ ተረፉ።
      (3) ጎርፉ በሰባት ቀን አበቃ።
      (4) ጀልባውም በሰሜን ፋርስ ዐረፈ፣ ኒሲር ተራራ ላይ።
      (5) እሱም ሦስት የተለያዩ ወፎችን ለቀቀ፣ ደረቅ ምድር መኖሩን ለማረጋገጥ።
5. *የሚሶፖታሚያ ሥነ-ጽሑፍ፣ ጥንታዊውን የጥፋት ውኃ የሚገልጸው ሁሉ ከተመሳሳይ ምንጭ የተቀዳ (የተወሰደ) ነው። ስሞቹ ዘወትር ቢለያዩም ታሪኩ ግን ተመሳሳይ ነው። ምሳሌ የሚሆነው Zivsudra፣ Atrahasis እና Utnapishtim ሁሉም ተመሳሳይ የሰው ንጉሥ ናቸው።*
6. የዘፍጥረት የጥንት ሁነቶች ታሪካዊ ትይዩዎች በሰው ልጅ ቅድመ-ብተና (ዘፍ. 10-11) እውቀትና ስለ እግዚአብሔር ባለው ልምድ ሊገለጽ ይችላል። እነዚህ እውነተኛ ታሪካዊ ዋነኛ ነገር ማስታወሻዎች ለአሁኑ ጊዜ የጥፋት ውኃ ጽሑፍ እንደሚሆኑ ተብራርተዋል፣ አፈ-ታሪካዊም ሆነዋል፣ በመላው ዓለም እንደሚታወቀው። በተመሳሳይ መልኩም ሊባል ይችላል፡ ስለ ፍጥረት (ዘፍ. 1-2) እና ስለ ሰውና መልአክ ኅብረት (ዘፍጥረት 6)።
7. የአባቶች ጊዜ (መካከለኛ ነሐስ)
   ሀ. ማሪ ሰሌዳዎች (የድንጋይ ላይ ጽሑፎች) - የሕግ ኩኒፎርም (የአሞናውያን ባህል)እና ግለሰባዊ ጽሑፎች፣ በአካድያን የተጻፉ፣ 1700 ቅ.ል.ክ. አካባቢ።
   ለ. ኑዚ ሰሌዳዎች - የኩኒፎርም መዛግብት፣ የተወሰኑ ዓይነቶች (የሆራይቲ ወይም ሆሪያን ባህል) በአካድያን የተጻፈ፣ ከነነዌ ደቡባዊ ምስራቅ 100 ማይል በግምት፣ ከ1500-1300 ዓ.ዓ። እነርሱም የቤተሰብና የንግድ ደንቦችን ይመዘግባሉ። ለተጨማሪ የተወሰነ ምሳሌ፣ Walton, pp. 52-58.
   ሐ. አላላክ ሰሌዳዎች - የኩኒፎርም ጽሑፎች ከሰሜን ሶርያ፣ 2000 ቅ.ል.ክ. አካባቢ።
   መ. በዘፍጥረት ላይ የሚገኙት አንዳንድ ስሞች በማሪ ሰሌዳዎች ላይ የተሰየሙ የቦታ ስሞች ናቸው፡ ሴሩግ፣ ፒሌግ፣ ቴራህ፣ ናሆር። ሌሎቹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስሞችም የተለመዱ ናቸው፡ አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብ፣ ላባ እና ዮሴፍ።

8. "አወዳዳሪ ታሪካዊ ጥናቶች እንደሚያሳዩት፣ ከኬጢያውያን ጋር በተጓዳኝ፣ ጥንታዊ ዕብራውያን እጅግ ትክክለኛ፣ ተጨባጭ እና ሀላፊነት የሚወስዱ መዛግብት ናቸው፣ በቅርብ ምስራቅ ታሪክ ላይ፣" R. K Harrison in *Biblical Criticism*, p 5።
9. የጥንታዊ ቅርስ ምርምር (አርኪዎሎጂ) የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪካዊ ገጽታ ለማደራጀት ረጂ መሆኑ ተረጋግጧል። ሆኖም፣ የጥንቃቄ ቃል አስፈላጊ ነው። አርኪዎሎጂ በፍጹምነት ሊታመን የሚችል መመሪያ ሊሆን ስለማይችል፣ ምክንያቱም፡
   ሀ. በድሮ ቁፋሮ ጊዜ የነበረው ደካማ ብልሃት
   ለ. በርካታ፣ እጅግ ተጨባጭ ያልሆኑ ትርጓሜዎች በተገኙት ቅርሶች ላይ መካሄዳቸው፣
   ሐ. በጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ ዜና መዋዕል (የታሪክ ቅደም ተከተል) ላይ ስምምነት ላይ መድረስ አለመቻሉ (ምንም እንኳ አንደኛው ከዛፍ ቀለበቶች (ክቦች) ላይ የዳበረ ቢሆንም)።

ሐ. የግብፃውያን ሐተታ-ተፈጥሮ በ John H. Walton's, *Ancient Israelite Literature in Its Cultural Context.* Grand Rapids, MI: Zondervan, 1990. Pp. 23-34, 32-34.ይገኛል፡፡

1. በግብፅ ሥነ-ጽሑፍ ፍጥረት የሚጀምረው ቅርጽ በሌለው፣ በተናወጠ፣ ጥንታዊ መልክ በያዘ ውሀ ነው። ፍጥረት የሚታየው እያደገ እንደመጣ አወቃቀር ነው፣ ከተናወጠ ውሀ ውስጥ።
2. በግብፅ ሥነ-ጽሑፍ ከሜምፊስ፣ ፍጥረት የተፈጠረው (የተከሰተው) በፓታህ የንግግር ቃል ነው።

መ. በኮስሞሎጂ ላይ የተመለከቱ ወንጌላውያን ወገኖች (ቡድኖች) አድራሻ፡
1. Institute for Creation Research (Young Earth)
   P. O. Box 2667
   El Cajon, CA 92021-0667
2. Reasons to Believe (Old Earth)
   P. O. Box 5978
   Pasadena, CA 91117

VII. ጽሑፋዊ ምድቦች (ዐውደ-ጽሑፍ)

ሀ. የፍሬ ሐሳብ ዝርዝር፣ በሙሴ "የፍጥረት" ሐረግ አጠቃቀም ላይ የተመሠረተ (*toledoth*)፡
1. የሰማይ እና የምድር አፈጣጠር ፣ 1:1-2:3
2. የሰው አፈጣጠር፣ 2:4-4:26
3. የአዳም አፈጣጠር (ትውልድ)፣ 5:1-6:8
4. የኖኅ ትውልድ፣ 6:9-9:17
5. የኖኅ ልጆች ትውልድ፣ 10:1-11:9
6. የሴም ትውልድ፣ 11:10-26
7. የታራ (አብርሃም) ትውልድ፣ 11:27-25:11
8. የእስማኤል ትውልድ፣ 25:12-18
9. የይስሐቅ ትውልድ፣ 25:19-35:29
10. የኤሳው ትውልድ፣ 36:1-8
11. የኤሳው ልጆች ትውልድ፣ 36:9-43
12. የያዕቆብ ትውልድ፣ 37:1-50:26 (ቁ. 1-11 የሜሶፖታሚያ ጽሑፋዊ ዳራ አለው፣ ቁ. 12 ግን የግብፃውያን ጽሑፋዊ ቃና አለው።)

ለ. የዓላማ ፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር:
1. የሰው አፈጣጠርና ሰው፣ 1-2
2. ሰብዓዊነት እና የፍጥረት ውድቀት፣ 3:1-11:26
3. አንድ ሰው ለሁሉም ሰዎች (3:15)፣ 12-50
   ሀ. አብርሃም (12:1-3)፣ 11:27-23:20
   ለ. ይስሐቅ፣ 24:1-26:35
   ሐ. ያዕቆብ፣ 27:1-36:4
      1. ይሁዳ (የመሲሑ የዘር ግንድ)
      2. ዮሴፍ (የድርብ ምድር ውርስ)፣ 37:1-50:26

VIII. ዋነኛ ሐቆች

ሀ. ሁሉም እንዴት ጀመረ?

1. እግዚአብሔር (1-2)። የመጽሐፍ ቅዱስ ርዕዮተ-ዓለም ብዝሀዊ አምልኮ አይደለም፣ ነገር ግን አሀዳዊ አምልኮ እንጂ ነው። እሱም "እንዴት" በሚለው የፍጥረት ሁኔታ ላይ አያተኩርም ነገር ግን "ማን" በሚለው እንጂ። እሱም ሙሉ ለሙሉ የተለየ ነው፣ በራሱ ጊዜ።
2. እግዚአብሔር ኅብረትን ይሻል። ፍጥረት ለእግዚአብሔር እንደ መድረክ ብቻ ነው፣ ከሰዎች ጋር ላለው ኅብረት።
3. የተቀረውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የመረዳት ችሎታ አይኖርም፣ ያለ ዘፍጥረት 1-3 እና 12።
4. ሰዎች በእምነት ምላሽ መስጠት ይኖርባቸዋል፣ የእግዚአብሔርን ፍቃድ እንደተረዱት መጠን (ዘፍ. 15፡6 እና ሮሜ. 4)።

ለ. ምድር እጅግ ክፉ እና ፍትሐዊ ያልሆነ ለምን ሆነ? እሱ "እጅግ መልካም" ነበር (1፡31)፣ ሰው ግን ኃጢአትን ሠራ (3)። አስፈሪ ውጤቶቹ ግልጽ ናቸው፡
1. ቃየን አቤልን ገደለ፣ (4)
2. የላሜህ በቀል (4:23)
3. የሰው ኃጢአተኝነት፣ (6:5፣11-12፤ 8:21)
4. የኖኅ ስካር (9)
5. የባቢሎል ግንብ፣ (11)
6. የውር ብዝኃ (ጣዖት) አምላኪነት

ሐ. እግዚአብሔር እንዴት ሊያስተካክለው ነው?
1. በመሲሑ መምጣት (3:15)
2. እግዚአብሔር አንዱን ጠራ፣ ሁሉንም ለመጥራት (ዘፍ. 12:1-3 እና ዘጸ. 19:5-6)
3. እግዚአብሔር ከወደቀው ሰው ጋር ለመሥራት ፍቃነኛ ነው (አዳም፣ ሔዋን፣ ቃየን፣ ኖኅ፣ አብርሃም፣ አይሁድ እና አሕዛብ) ጸጋውን በመስጠት፡
   ሀ. ተስፋዎች
   ለ. ኪዳናት (ሁኔታዊ ያልሆነ እና ሁኔታዊ)
   ሐ. መሥዋዕት
   መ. አምልኮ

IX. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት እና ሰዎች አጭር ገለጻ የሚደረግባቸው

ሀ. ቃላት እና ሐረጋት
1. "እግዚአብሔር አለ..." 1:3፣6፣9፣14፣20፣24 (NASB እና NIV)
2. "እና(ድርግ)..." 1:26፤ 3:22፤ 11:7 (NASB እና NIV)
3. "በመልካችን" 1:26፣27፤ 5:1፣3፤ 9:6 (NASB እና NIV)
4. "ጌታ አምላክ ይራመዳል" (ሰዋዊ ገጽታ) 3:8 (NASB እና NIV)
5. ኔፍሊም 6:4 (NASB እና NIV)
6. ኪዳን 6:18፤ 9:9-17 (NASB እና NIV)
7. "አብርሃም በእግዚአብሔር አመነ፤ እሱም ጽድቅ አድርጎ ቆጠረለት 15:6 ( NIV፣ "አብራም በእግዚአብሔር አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት")
8. ምሕረት (*hesed*) 24:12፣27፤ 32:10 ( NIV፣ "ቸርነት")
9. የቤተሰብ ጣዖታት (*teraphim*) 31:19፣30፣34 ( NIV፣ "የቤተሰብ አማልክት")
10. መናፍስታዊነት 44:5 (NASB እና NIV)

ለ. ማንነታቸው በአጭሩ የሚገለጽ ሰዎች
1. ሴት 4:25
2. ሄኖክ፣ 5:21-24
3. ማቱሳላ፣ 5:22፣25-27
4. ሴም፣ 9:18፤ 10:27-31
5. ከነአን፣ 9:20-27
6. ናምሩድ፣ 10:8-10
7. ታራ፣ 11:24-32
8. ሎጥ፣ 11:31
9. አብርሃም፣ 12:18
10. መልከጼዴቅ፣ 14:18
11. አጋር፣ 16:1
12. እስማኤል፣ 15:15፤ 25:12-19
13. ይስሐቅ፣ 21:3
14. ላባ፣ 24:29
15. ኬጡራ፣ 25:1
16. ያዕቆብ (እስራኤል)፣ 25:26፤ 32:28
17. ዲና፣ 30:21
18. ጲጥፋራ፣ 37:36
19. ትዕማር፣ 38
20. ምናሴ እና ኤፍሬም፣ 41:51፣52

X. የካርታ ስፍራዎች

ሀ. የመጀመሪያ ካርታ - ዘፍጥረት 1- 11 (በቁጥር)

1. የዔድን ገነት፣ 2፡8
2. ጤግሮስ ወንዝ፣ 2:14
3. ኤፍራጥስ ወንዝ፣ 2:14
4. አራራት ተራራ፣ 8:4
5. ሰናዖር፣ 10:10፤ 11:2
6. ባብኤል፣ 10:10፤ 11:9
7. ነነዌ፣ 10፡12
8. ኢያቡስ፣ 10:16
9. ሰዶም፣ 10:19፤ 13:10
10. ዑር የከለዳውያን፣ 11:28
11. ካራን፣ 11:31-32

ለ. ሁለተኛው የዘፍጥረት ካርታ 12-50 (በቁጥር)

1. ሴኬም፣ 12:6፤ 33:18
2. ቤቴል፣ 12:8፤ 13:3፤ 35:6
3. ኔጌብ፣ 12:9፤ 13:1
4. ዮርዳኖስ ወንዝ፣ 13:10-11
5. ኬብሮን፣ 13:18፤ 23:2
6. ጨው ባሕር፣ 14:3
7. ቃዴስ በርኔ፣ 14:7፤ 16:14
8. ደማስቆስ፣ 14:15
9. ሳሌም፣ 14:18
10. የግብፅ ወንዝ፣ 15:18
11. ሱር ምድረ-በዳ፣ 16:7
12. ሞአብ፣ 19:37
13. አሞን፣ 19:38
14. ቤርሳቤህ፣ 21:14፤ 26:33
15. የፍልስጥኤም ስፍራ፣ 21:32
16. ፋራን ምድረ-በዳ፣ 21:21
17. የሞርያ ምድር፣ 22:2
18. አራም፣ 24:10
19. ኤዶም፣ 25:30፤ 36:1፤8-9፣19
20. ያቦቅ ወንዝ፣ 32:22
21. ቤተልሔም፣ 35:19
22. ጌሻም ምድር፣ 45:10፤ 46:34


## XI. የተማሪ ይዘት ጥያቄዎች


ጥያቄዎች በዘፍጥረት 1-11 ላይ


1. መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን መገኛ ያብራራልን?
2. መጽሐፍ ቅዱስ ከሳይንስ ጋር ይጋጫልን፣ ስለ ፍጥረት?
3. ዘፍጥረት 1 ከሌሎቹ የቅርብ ምስራቅ ሐተታ- ተፈጥሮ ጋር እንዴት ይዛመዳል?
4. *Fiat* እና *ex nihilo* የሚሉትን ቃላት ግለጽ።
5. ለመለኮት ለምን ሁለት የተለያዩ ስሞች ተሰጡ፣ ምዕራፍ 1 እና 2 ላይ?
6. ስለ ሰው አፈጣጠር ሁለት የተለያዩ መዛግብት (መግለጫዎች) አሉ ወይ?
7. ወንድና ሴት የተሠሩት በእግዚአብሔር መልክ ነው፣ ማለት ምን ማለት ነው?
8. ከአንዱ አምላክ ጋር በተያያዘ ለምን የብዙ ቁጥር ጥቅም ላይ ዋለ? 1:26፣ 27፤ 3:22፤ 11:7
9. ምዕራፍ 3 ቀሪውን መጽሐፍ ቅዱስ ለመረዳት ዋነኛ (ወሳኝ) የሆነው ለምንድነው?
10. የሚናገሩ እንስሳት (3፡1) ይሄንን መግለጫ ከአፈ-ታሪክ አኳያ ያረጋግጣሉን?
11. 3፡15 እጅግ ጠቃሚ የሚሆነው ለምንድነው?
12. 3፡16 በዘመናዊ ሕይወት እንዴት ይተገበራል?
13. በዔድን ገነት የሚገኙት ሁለት ልዩ ዛፎች ናቸው ወይስ አንድ?
14. በቃየን የዘር ሐረግ የመጡትን ኅብረተሰብ ዕድገት ዘርዝር፣ 4፡16-24።
15. የጥፋት ውኃ ዓላማ ምንድነበር?
16. ሰው የባብኤልን ግንብ የሠራበት ዓላማ ምንድነበር?


በዘፍጥረት 12-50 ጥያቄዎች

1. በኖኅና በአብርሃም መካከል የተደረጉት ኪዳናት እንዴት ይለያያሉ?
2. የአብርሃም ኪዳን አይሁድ ካልሆኑት ጋር እንዴት ይዛመዳል?
3. በምዕራፍ 12 በአብራም ላይ የታዩ ሁለት የድካምና እምነት የማጣት ምልክቶች ምንድናቸው?
4. መልከ ጼዴቅ ማነው፣ አብርሃምስ ለእርሱ አስራት ያወጣው ለምንድነው?
5. 15፡12-21 እጅግ ጠቃሚ የሆነው ለምንድነው?
6. ምዕራፍ 18 ላይ ሦስቱ ሰዎች እነማናቸው? (ለምን እና የት)?
7. አብርሃም ከሳራ ጋር መጋባቱን ለምን ካደ? ለማነው የካደው?
8. ርብቃና ያዕቆብ ይስሐቅን ለምን አታለሉት? (27)
9. ሮቤል፣ ሌዊ እና ስምዖን የመሲሑ የዘር ግንድ እንዳይሆኑ ያልተመረጡት ለምን እንደሆነ አብራራ? (34 እና 49)
10. የዮሴፍን ሕልሞች በራስህ ቃል ግለጽ። (37)
11. ዮሴፍ ሆን ብሎ ወንድሞቹን እንዳላወቃቸው የሆነው ለምንድነው?
12. የዮሴፍ ልጆች እያንዳንዳቸው ከሌሎቹ የያዕቆብ ልጆች እኩል እንዲወርሱ የተደረገው ለምንድነው?


Genesis 1-11
N
W
E
S
ANCIENT
NEAR EAST


Genesis 12-50
N
W
E
S
ANCIENT
NEAR EAST


ANCIENT
NEAR EAST
N
S
E
W


PALESTINE
0 10 20 30 40
SCALE IN MILES

# ኦሪት ዘጸአት መግቢያ

I. የመጽሐፉ ስም

ሀ. በዕብራይስጥ (ኤምቲ) እሱ የመጽሐፉ የመጀመሪያ ቃል ነው፣ "እነዚህም ቃላቱ (ስሞቹ) ናቸው።"

ለ. በLXX ትርጉም እሱ (*ek ´odos* ኢኬ 'ኦዶስ) ነው፣ ፍችውም "መውጫ መንገድ" ወይም "መውጫ ፍኖት" ማለት ነው።

ሐ. በጀሮም ላቲን ቫልጌት "ዘጸአት" ነው።

II. ቅዱስ ቃላዊነቱ (ካኖናይዜሽን)

ሀ. እሱም የዕብራይስጥ ካኖን የመጀመሪያው ምድብ ክፋይ ነው፣ "ቶራህ" ወይም "አስተምህሮ" ወይም "ሕግ" ተብሎ የሚጠራው።

ለ. ምድቡ ፔንታቲሁች (አምስቱ ጥቅሎች) ተብሎ ይጠራል፣ በ LXX

ሐ. እሱም አንዳንድ ጊዜ "አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት" ተብሎ ይጠራል፣ በእንግሊዝኛ።

መ. እሱም የሚያካትተው ቀጣይነት ያለውን ታሪካዊ መዝገብ ነው፣ ከዘፍጥረት — ዘዳግም በሙሴ የተመዘገበ፣ ፍጥረትን በተመለከተ በሙሴ ሕይወት።

III. ዘውግ - የዘጸአት መጽሐፍ ሦስት ዓይነት ጽሑፋዊ ዘውጎችን ያካትታል።

ሀ. ታሪካዊ ትርከት፣ ዘጸ. 1-19፤ 32-34

ለ. ቅኔ፣ ዘጸ. 15

ሐ. በተለየ መልኩ ለማደሪያው ድንኳን (መቅደስ)፣ ዘጸ. 25-31፣ እና ለአወቃቀሩ፣ 35-40

IV. ደራሲው

ሀ. ቶራህ አንድ ወጥ ጽሑፍ (መዝገብ) ነው። ዘጸአት የሚጀምረው "እናም፣" በሚል መስተጻምር ነው። ረዘም ያለውን ማብራሪያ ዘፍጥረት የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር ላይ ተመልከት።

ለ. በዘጸአት መጠነኛ ቦታዎች ላይ ሙሴ ጻፈ የሚል ስፍራ አለ፡
1. 17:14፤ 2. 24:4፣ 12፤ 3. 34:27፣ 28

ሐ. ኢያሱ 8:31 ዘጸአት 20:25ን ይጠቅሳል፣ ሙሴ እንደጻፈውም ይገልጻል። ኢየሱስ ዘጸ. 20:12፣17ን ጠቅሷል፣ ሙሴ እንደጻፈውም አመልክቷል፣ ማር. 7:10።

V. የዘጸአት ጊዜ

ሀ. ሁለት የሊቃውንታዊ አስተያየቶች አሉ፣ የዘጸአትን ጊዜ በተመለከተ፡
1. ከ1 ነገሥት 6፡1 እንደሚለው፣ "480 ዓመት ከዘጸአት እስከ ሰሎሞን መቅደስ መገንባት ድረስ"፡
   ሀ. ሰሎሞን መንገሥ የጀመረው በ970 ቅ.ል.ክ. ነው። ይህም የተቆጠረው (የተሰላው) የቋርቋርን ጦርነት በመጠቀም ነው (853 ቅ.ል.ክ) እንደ ርግጠኛ የመነሻ ዕለት።
   ለ. መቅደሱ የተገነባው በአራተኛ ዓመቱ ነው (965 ቅ.ል.ክ.)፣ እናም ዘጸአት የተከሰተው 1445/6 ቅ.ል.ክ. አካባቢ ነው።
2. ይህም በ18ኛው የግብፅ ሥርወ-መንግሥት እንዲከሰት ያደርገዋል።
   ሀ. ጨቋኙ ፈርዖን የሚሆነው ቱትሞስ III ነው (1490-1436 ቅ.ል.ክ)።
   ለ. የዘጸአቱ ፈርዖን የሚሆነው *Amenhotep* II ነው (1436-1407 ቅ.ል.ክ)።
   (1) አንዳንዶች የሚያምኑት ከኢያሪኮ የሆነውን ማስረጃ ነው፣ ምንም ዓይነት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት በኢያሪኮና ግብፅ መካከል *Amenhotep III* የግዛት ዘመን አልነበረም በሚለው ሐቅ ላይ በመመሥረት (1413-1377 B.C.)
   (2) *Amarna* ጽሑፎች እንደመዘገቡት፣ ዲፕሎማሲያዊ መጻጻፎች በኦስትራካ ላይ ስለ *Habiru* የከነዓንን ምድር በኃይል መውረር የተጻፉት በ *Amenhotep* III የግዛት ዘመን ነው። ስለዚህ፣ ዘጸአት የተከሰተው በ *Amenhotep* II የግዛት ዘመን ነው።
   (3) የመሳፍንት ዘመን ርዝማኔ በቂ ሊሆን አይችልም፣ 13ኛው ክፍለ-ዘመን የዘጸአት ጊዜ ከሆነ።
3. የእነዚህ ቀናት ታሳቢ ችግሮች የሚሆኑት፡
   ሀ. ሴፕቱዋጂንት (LXX) 440 ዓመታት አለው፣ 480 ሳይሆን።

ለ. ሊሆን የሚችለው፣ 480 ዓመት 12 ትውልዶችን እንደሚወክል ነው፣ እያንዳንዳቸው 40 ዓመት ታሳቢ ቢኖራቸው፣ ስለዚህ ተምሳሌታዊ (ዘይቤአዊ) ቁጥር ነው።

ሐ. 12 የካህናት ትውልዶች አሉ፣ ከአሮን እስከ ሰሎሞን (1 ዜና. 6)፣ ከዚያም 12 ከሰሎሞን እስከ ሁለተኛው መቅደስ። አይሁድ፣ እንደ ግሪኮች፣ ትውልድን የሚቀምሩት በአርባ ዓመት ነው። ስለዚህ፣ የ480 ዓመት ጊዜ ወደ ኋላና ወደፊት ይኖራል (የቁጥሮች ተምሳሌታዊ አጠቃቀም) (cf. Bimson's *Redating the Exodus and Conquest*)::

4. ሦስት ሌሎች ጊዜን የሚጠቅሱ ጽሑፎች አሉ፡፡

ሀ. ዘፍጥረት 15:13፣16 (ሐዋ. 7:6)፣ 400 የባርነት ዓመታት፤

ለ. ዘጸአት 12:40-41 (ገላ. 3:17)፤

(1) ኤምቲ - 430 ዓመታት የግብፅ የእንግድነት ኑሮ

(2) LXX - 215 ዓመታት የግብፅ የእንግድነት ኑሮ

ሐ. መሳፍንት 11:26 - 300 ዓመታት በዮፍታሔ ጊዜና ድል በማድረግ (1445 ቀንን ያጸናል)

መ. ሐዋ. 13:19፣ ዘጸአት፣ መዞር እና ድል ማድረግ - 450 ዓመታት

5. የነገሥት ደራሲ የተወሰኑ ታሪካዊ ማጣቀሻዎችን ይጠቀማል፣ እናም የተቀራረቡ ቁጥሮችን ሳይሆን Edwin Thiele, *A Chronology of the Hebrew Kings*, pp. 83-85፡፡

ለ. ከጥንታዊ ቅርስ ምርምር (አርኪዖሎጂ)የተገኘው ጊዜያዊው ማስረጃ የሚያመለክተው ቀን ወደ 1290 ቅ.ል.ክ ነው፣ ወይም 19ኛው የግብፅ ሥርወ-መንግሥት።

1. ዮሴፍ አባቱን መጎብኘት የቻለውና ፈርዖን በዚሁ ተመሳሳይ ጊዜ ነው። የመጀመሪያው የአገሬው ፈርዖን፣ የግብፅን ዋና ከተማ ከቴብስ መልሶ ወደ ዐባይ ዴልታ (ወንዝ ዳርቻ) ማዛወር የጀመረው፣ *Avaris/Zoan/Tanis* ተብሎ እሚጠራው ስፍራ፣ እሱም የድሮው *Hyksos* ዋና ከተማ፣ *ሴቲ I* ነበር (1309-1290)። እሱም ጨቋኙ ፈርዖን ሊሆን ይችላል።

ሀ. ይህም ከሁለት መረጃዎች ጋር የሚገጥም ይመስላል፣ ስለ *Hyksos* ግብፅን መግዛት።

(1) የራምሴስ II ጊዜ ትክል ደንጊያ ተገኝቷል፣ ይኸውም የአቫሪስን መመሥረት መታሰቢያ የሆነ፣ አራት መቶ ዓመት ቀደም ብሎ (1700 ቅ.ል.ክ በ *Hyksos*)

(2) የዘፍጥረት 15፡13 ትንቢት የሚናገረው ስለ 400 ዓመት ጭቆና ነው

ለ. ይህም የሚያመለክተው፣ የዮሴፍ ወደ ሥልጣን መምጣት *Hyksos* (ሴማዊ) ፈርዖን ጊዜ እንደ ነበር ነው። አዲሱ የግብፅ ሥርወ-መንግሥት ዘጸ. 1፡8 ላይ ተጠቅሷል።

2. *Hyksos* የሚለው የግብፃውያን ቃል ፍችው "የባዕድ አገር ገዥዎች" ማለት ነው እነርሱም ግብፃውያን ያልሆኑ ወገኖች፣ ሴማዊ ገዥዎች ናቸው፣ ግብፅን በ15ኛ እና 16ኛ ሥርወ መንግሥታት የተቆጣጠሩ (1720-1570 ቅ.ል.ክ)። አንዳንዶች እነርሱን ከዮሴፍ ወደ ሥልጣን መምጣት ጋር ሊያያይዙት ይሻሉ። የዘጸ. 12፡40ን 430 ዓመት ከ1720 ቅ.ል.ክ ላይ ብንቀንስ፣ 1290 ቅ.ል.ክ ቀንን እናገኛለን።

3. የሰቲ I ልጅ ራምሰስ II ነበር (1290-1224)። ይህ ስም የንግድ ከተማ ከሆኑትና በዕብራውያን ባሮች በተገነቡት ለአንደኛው (ስም) ተጠቅሷል፣ ዘጸ. 1፡11 ላይ። ደግሞም ይኸው ተመሳሳይ ወረዳ (ስፍራ) በግብፅ ውስጥ፣ በጌሤም አጠገብ ራምሴ ተብሎ ተጠርቷል፣ ዘፍ. 47፡11። *Avaris/Zoan/Tanis* ተብሎ የሚታወቀው "የራምሴ ቤት" በሚል ነው 1300-1100 ቅ.ል.ክ።

4. ቱትሞሰስ III ታላቁ ገንቢ (መሐንዲስ) በመባል ይታወቃል፣ ራምሴ II እንደነበረው ሁሉ።

5. ሬምሴ II 47 ሴቶች ልጆች ነበሩት፣ በተለዩ ቤተ-መንግሥታት የሚኖሩ።

6. የጥንታዊ ቅርስ ምርምር (አርኪዖሎጂ) እንደሚያሳየው አብዛኞቹ የከነዓን ከተሞች ትላልቅ ቅጥሮች (ግንቦች) (ሀዞር፣ ደቢር፣ ላቺሽ) መደምሰሳቸውና በፍጥነት ዳግም መገንባታቸውን ያመለክታል፣ 1250 ቅ.ል.ክ አካባቢ። 38 ዓመት በምድረ-በዳ የመዞር ጊዜን በመተው ይህም ከ1290 ቅ.ል.ክ ጋር ይገጥማል።

7. በጥንታዊ ቅርስ ምርምር (አርኪዖሎጂ) እንደተገኘው ፣ እስራኤላውያን በደቡብ ከነዓን ይኖሩ እንደነበር ያጣቅሳል፣ በራምሴ ወራሽ *Merneptah* ትክል ድንጋይ ላይ (1224-1214 ቅ.ል.ክ [የሜርኒፕታህ ትክል ድንጋይ፣ ዕድሜ የሚያስቆጥረው 1220 ቅ.ል.ክ ነው])።

8. ኤዶም እና ሞአብ ጠንካራ ብሔራዊ ማንነት የተላበሱ ይመስላል፣ በ1300 ቅ.ል.ክ መጨረሻ ላይ። እነዚህ አገሮች በ15ኛው ክፍለ-ዘመን የተደራጁ አይደሉም (ግሉኢክ)።

9. ቢምሰን ያሳተመው መፅሀፍ *Redating the Exodus and Conquest* by John J. Bimson, published, by the University of Sheffield, 1978 ሁሉንም የአርኪዖሎጂ ማስረጃዎችን ተቃርኖ ይከራከራል፣ ለቀደመው ጊዜ።

VI. ሌሎች ርግጠኝነት የሌላቸው ነገሮች፣ ከዘጸአት ጋር በተያያዘ

ሀ. በዘጸአት የወጡት ሰዎች ቁጥር፣ አጠራጣሪ ነው

1. ዘኍልቁ 1:46፤ 26:51 የሚያስረዳው 600፣000 ሰልፍ የሚያውቁ (ተዋጊ ዕድሜ ላይ ያሉ) ወንዶች መሆናቸውን ነው (20-50 ዓመት ዕድሜ ዘጸ. 38:26)። ስለዚህ፣ አንዱ ሴቶችን፣ ልጆችንና ሽማግሌዎችን ቢገምት ቁጥሩ 1.5 እስከ 2.5 ሚሊዮን ሊሆን ይችላል።

2. ሆኖም፣ የዕብራይስጡ ቃል ለሺህ፣ *Eleph*, ሊሆን የሚችለው:

ሀ. የቤተሰብ ወይም ነገድ ምድብ፣ ኢያሱ 22:14፤ መሳፍንት 6:15፤ I ሳሙኤል 23:23፣ ዘካ. 9:7

ለ. የወታደር ምድብ፣ ዘጸ. 18:21፣25፤ ዘዳ. 1:15

ሐ. አንድ ሺህ በጥሬው፣ ዘፍ. 20:16፤ ዘጸ. 32:28

መ. በተምሳሌትነት ጥቅም ላይ የዋለ፣ ዘፍ. 24:60፤ ዘጸ. 20:6 (ዘዳ. 7:9)፤ 34:7፤ ኤር. 32:18

ሠ. ከዑጋሪቲክ (የሴማዊ ቋንቋ ተዛማጅ)፣ ተመሳሳይ ተናባቢዎች ሓሉፍ፣ ፍችውም "የጎሳ አለቃ" (ዘፍ. 36:15)። ይህም ማለት ለዘኍ. 1:39፣ 60 የጎሳ አለቆች እና 2700 ሰዎች ከዳን ነገድ አሉ ማለት ነው። ችግሩ በግልጽ የሚመጣው እጅግ በርካታ የጎሳ አለቆች ለተመሳሳይ ነገድ ሰዎች ቁጥር ሲኖሩ ነው።

ረ. የተሻለ ማብራሪያ NIV የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ ገጽ 186 ላይ አለ።

3. አርኪዖሎጂ የግብፅንና የአሶርን ሠራዊት መጠን በዚህ ጊዜ የሚገምተው በአስር ሙቶ ሺሆች ነው። አንዳንድ ምንባቦች በኢያሱ ላይ የሚያመለክቱት እስራኤል 40፣000 ሠራዊት እንደነበረው ነው (ኢያ. 4:13፤ 7:3፤ 8:3፣11፣12)።

ለ. የዘጸአት የጉዞ መስመር በጥርጣሬ ነው

1. ስፍራው፡ (1) የግብፅ ከተሞች፤ (2) የውኃ አካላት፤ እና (3) የቀድሞ የዕብራውያን የሰፈር ቦታዎች ሁሉ ርግጠኝነት የላቸውም።
2. "ቀይ ባሕር" የሚለው ቃል በጥሬው *Yam Suph* (*Yam Suph* )ማለት ነው፣ ይኸውም፡

   ሀ. ፍችው "የአረም ባሕር" ወይም "የሸምበቆ ባሕር።" እሱም የጨው ውኃን ያመለክታል፣ ዮናስ 2:5፤ 1 ነገ. 9:26 ወይም ንጹሕ ውኃ፣ ዘጸ. 2:3፤ ኢሳ. 19:26። LXX እሱን በቅድሚያ የተረጎመው "ቀይ ባሕር" በሚል ነው፣ ቫልጌትን ተከትሎ፣ ከዚያም ኪንግ ጀምስ ቅጅ።

   ለ. "የደቡብ ባሕር" ወይም "በዳርቻ ያለ ባሕር (የምድር) ያመለክታል።" እሱም ዘመናዊውን ቀይ ባሕር፣ የሕንድ ውቅያኖስን ወይም የፋርስ ባሕረ-ሰላጤን ያመለክታል።

   ሐ. በርከት ያሉ አጠቃቀሞች በብኪ አሉት (ዘኍ. 33:8፣ 10)።
3. ሦስት ታሳቢ የጉዞ መስመሮች አሉ፣ ሦስት የተለያዩ የውኃ አካላትን በማካተት፡

   ሀ. ሰሜናዊ የጉዞ መስመር - ይህ በሜዲትራኒያን ባሕር ዳርቻ በኩል ነው፣ የንግድ አውራ-ጎዳናውን ተከትሎ፣ "የፍልስጥኤማውያን መንገድ" በመባል የሚታወቀውን። ይህም ለተስፋይቱ ምድር እጅግ በጣም የቀረበው መንገድ ነው። ያለፉበት የውኃ አካል ጥልቀት ከሌላቸው፣ ረግረጋማ አካባቢዎች አንዱ ሲሆን፡ ሰርቦኒስ ሐይቅ ወይም ሜንዛልች ሐይቅ ተብሎ ይጠራል። ሆኖም፣ አንዱ ግምት ውስጥ ማስገባት የሚኖርበት ዘጸ. 13:17 ይህንን አማራጭ መቃረኑን ነው። ደግሞም የግብፃውያን ምሽግ በዚህ የጉዞ መስመር ላይ መኖሩ በዚህ አማራጭ ላይ ተጽዕኖውን ያሳርፋል።

   ለ. መካከለኛ የጉዞ መስመር - ይህ ማዕከላዊዎቹን ሐይቆች ያካትታል፡ እነርሱም (1) "ቢተር ሐይቆች"፤ (2) "ባላህ ሐይቅ"፤ (3) "ቲምሳህ ሐይቅ" በመባል ይጠራሉ። ይህም የቅፍለት (የእንስሳት ጀርባ) የንግድ የጉዞ መስመርን የሚከተል ይሆናል፣ በሱር ምድረ-በዳ ውስጥ።

   ሐ. ደቡባዊ የጉዞ መስመር - ይህ ሰፊ ጨውማ ውኃ አካልን ሲያካትት፣ ዛሬ ቀይ ባሕር ብለን የምንጠራው ነው። እዚህ ስፍራ አካባቢም የቅፍለት (የእንስሳት ጀርባ) የንግድ የጉዞ መስመር የነበረ ሲሆን፣ እርሱም "የነገሥታት አውራ-ጎዳና" ከሚባለው ጋር ይገናኛል፣ (ዮርዳኖስን ወደ ደማስቆ የሚያቋርጥ መንገድ) ኢዚኦን-ጌቤር።

      (1) ይሄንን የሚቃረነው ተጽዕኖ በዚህ የውሀ አካል ላይ የሸንበቆ (ደንገል) አለመኖር ነው።

      (2) ወደዚህ በማመልከት 1 ነገ. 9:26 የሚለው፣ ኢዚኦን-ጌቤር በያም-ሳፍ ላይ መሆኑን ነው። ይህም የአቃባ ባሕረ-ሰላጤ ወይም የቀይ ባሕር ክፋይ ሊሆን ይችላል (ዘኍ. 21:4፤ ዘዳ. 27፤ መሳ. 11:16፤ ኤር. 49:12)።

   መ. ዘኍልቁ 33 ችግሩን በግልጽ ያሳያል። ቁ. 8ሀ ላይ እነርሱ "በባሕር መካከል አልፈዋል፣" ከዚያም ቁ.10 ላይ "ቀይ ባሕር" አጠገብ ሰፍረዋል፣ የተለያዩ የውኃ አካላት።

   ሠ. የትኛውንም ዓይነት የውኃ አካል ቢያቋርጡ፣ እሱ የእግዚአብሔር ተአምር ነው። እስራኤል የጦር መሣርያ ተሰጥቶታል፣ ከሞቱትና በእነርሱ በኩል ባለው የውሃ አካል ላይ ከተንሳፈፉት የግብፅ ወታደሮች ላይ፣ ሌለኛው ተአምር፣ ዘጸ. 14:30፤ 15:4-5።

   ረ. ከሌላው ጽሑፍ ማለት የሚቻለው "the *yom suph*" ያልታወቀ፣ ምሥጢራዊ የውሀ አካል ወደ ደቡብ ሲል እንደነበረ ነው። በአንዳንድ ጽሑፎች ሕንድ ውቅያኖስ ወይም ቤንገሊ የባሕር ወሽመጥ "the *yom suph* " ተብሎ ይጠራል።
4. የሲና ተራራ አቅጣጫም (ስፍራ) ደግሞ አጠራጣሪ ነው

   ሀ. ሙሴ በጥሬው የሚናገር ከሆነ፣ በዘይቤነት ሳይሆን፣ ፈርዖንን ሊጠይቅ የሄደባቸውን ሦስት ቀናት (3:18፤ 5:3፤ 8:27)፣ ያ በቂ ጊዜ ሊሆን አይችልም፣ ልማዳዊውን ስፍራ ለማግኘት፣ በደቡባዊ ሲና ባሕረ-ገብ መሬት በኩል። ስለዚህ፣ አንዳንድ ሊቃውንት ተራራውን የሚያስቀምጡት ከቃዴስ በርኔ የበረሀ ገነት አጠገብ ነው።

   ለ. "ጀቤል ሙሳ" ተብሎ የሚጠራው ልማዳዊው ስፍራ፣ በሲን ምድረ-በዳ፣ በርከት ያሉ ማለፊያ ነገሮች አሉት፡

      (1) ሰፊ ሜዳ ከተራራው ፊት፣

      (2) ዘዳ. 1:2 የሚለው ከሲና ተራራ እስከ ቃዴስ በርኔ ድረስ የአስራ አንድ ቀን ጉዞ መሆኑን ነው፣

      (3) "ሲና" የሚለው ቃል የዕብራይስጥ ያልሆነ ቃል ነው። ከሲን ምድረ-በዳ ጋር ተያያዥነት ሊኖረው ይችላል፣ እሱም አነስተኛ የበረሀ ቁጥቋጦን የሚያመለክት።

      (4) ሲና ተራራ ባህላዊ ስፍራ ተደርጎ ተወስዷል፣ ከ4ኛ ክፍለ-ዘመን ዓ.ም ጀምሮ። እሱም በ "ምድያም ምድር" ነው ያለው፣ ይኸውም የሲናን ባሕረ-ገብ መሬትና የዓረቢያን ሰፊ ስፍራ የሚያካትት።

      (5) አርኪዖሎጂ እንዳረጋገጠው የአንዳንድ ከተማዎች ስፍራ፣ ዘጸአት ጽሑፍ ላይ የተጠቀሰው *Elim, Dophkah, Rephidim* ከሲና ባሕረ ገብ መሬት ምዕራባዊ በኩል መሆኑን ነው።

VII. ታሪካዊ መቼቱን የሚያጠናክሩ ምንጮች፡

ሀ. ስለ ዘፀአት ምንም ዓይነት የጽሑፍ ማስረጃ ከግብፅ ፈጽሞ አልተገኘም። ይህ ያልተለመደ አይደለም፣ ያህዌ የግብፃውያንን ጣዖታት ሙሉ ለሙሉ ከማሸነፉ አንጻር።

ለ. አንዳንድ ባህላዊ የሕግ ምሳሌዎች አሉ፣ ከአስርቱ ትዕዛዛት ጋር የሚመሳሰሉ፡

1. የ *Laws of Lipit-Ishtar* (ሱሜርያን) ሕግጋት፣ ከኢስን ንጉሥ (1934-1924 ቅ.ል.ክ)
2. የ *Laws of Eshnunna* ኢሽኑና ሕግጋት (የድሮ ባቢሎናውያን)፣ ዘመኑም 1800 ቅ.ል.ክ ከዳዱሻ አገዛዝ፣ ከአሽኑና ንጉሥ
3. የሐሙራቢ ሕግ (የድሮ ባቢሎናውያን) ከባቢሎን ንጉሥ፣ ሐሙራቢ (1728-1686 ቅ.ል.ክ)
4. የሕግ ጽሑፎች፣ የኬጢያዊ ነገሥታት፣ ሙፕሲሊስ I ወይም ሃቱሲሊስ I፣ ከ1650 ቅ.ል.ክ አካባቢ
5. የሜሶፖታሚያ የሕግ ጽሑፎች በቀዳሚነት የሚያተኩሩት በሲቪል ሕግ ላይ ሲሆን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሕግጋት በቀዳሚነት የሚያተኩሩት ደግሞ ሃይማኖታዊ/አምልኮ ሥርዓታዊ ላይ ነው። "… የሲቪል ቅድመ-አቋም አስተያየት በኩኔፎረም ሕግ ላይ ልንሰጥ እንችላለን፣ እንዲሁም የአምልኮ ሥርዓታዊ ቅድመ-አቋም በእስራኤል ሕግ ላይ ልንሰጥ እንችላለን…፣ በሜሶፖታሚያ፣ ሕግን መተላለፍ በዋነኛነት የሚታየው ከኅብረተሰቡ ጋር ባለው ግንኙነት ሲሆን፤ በእስራኤል ደግሞ፣ ሁሉም ሕግን መተላለፍ በእግዚአብሔር ላይ እንደተደረገ ተቃውሞ ነው።" ዋልቶን ገፅ 80፣ (Walton, p. 80)፡፡
6. አልብሬክት (Albrect Alt in Essays on Old Testament History and Religion, Oxford, 1966, pp. 81-132 ሁለት ዓይነት ሕግጋትን ለይቷል፡
   ሀ. የሞራል ሕግ፣ ይኸውም ሁኔታዊ ሐረጎችን የሚጠቀም። እሱም ባሕርይ ያደረገው "እንዲህ ከሆነ/ካደረገ… ከዚያም እንዲህ ይሆናል" የሚል አወቃቀር ነው። እሱም ከሃይማኖታዊ ወይም ማኅበረሰባዊ ደንቦች ጋር አይያያዝም፣ ነገር ግን ክልከላዎችንና የሚያስከትሉትን መዘዝ/ውጤት ያስቀምጣል።
   ለ. አመክኗዊ (ሎጂካዊ)፣ እሱም ሁኔታዊ ሐረጋትን አይጠቀምም።
      (1) ዘጸ. 21 እና ዘዳ. 27:15-26 ሦስተኛ መደብን የሚጠቀም ሲሆን፣ ከግለሰቦች፣ የተወሰኑ ጉዳዮች ጋር ይያያዛል
      (2) ሌዋ. 18:7-17 እና ዘጸ. 20/ዘዳ. 5 ሁለተኛ መደብን ሲጠቀም፣ ባብዛኛው አጠቃላይ መልክ/ወሰን አላቸው።

   ሐ. የሜሶፖታሚያ ሕግ በቀዳሚነት የሞራል ሕግ ሲሆን፣ የእስራኤላውያን ሕግ ደግሞ በቀዳሚነት አመክኗዊ/ሎጂካዊ ነው።

ሐ. እንደ ድሮው ሊበራላዊ ክርክር ሙሴ እንዴት መጻፍ እንዳለበት ሊያውቅ አይችልም፣ አርኪዎሎጂ የድሮውን የከነዓን ፊደል፣ እሱም በግብፅ በሙሴ ጊዜ የነበረውን ሕልውና አረጋግጧል።

1. በ1400 ቅ.ል.ክ የተደረጉት መጻጻፎች፣ ሴማዊ ባሮች፣ እነርሱም በግብፅ ሲና ማዕድን ስፍራ እንደነበሩ ተገኝተዋል (cf. Albright, BASOR, #110 [1948], p 12-13).
2. አስትራኮን (የተሰበረ ሸክላ፣ ጽሑፍ ለመቀበል ጥቅም ላይ ይውል የነበረ) ከንግሥት (ኪዊን) ሸለቆ፣ Thebes, Albright, BASOR, #110 (1948), p 12. ላይ ተገኝቷል፡፡

VIII. ጽሑፋዊ ምድቦች (ዐውደ-ጽሑፍ)

ሀ. አጭር የፍሬ-ሐሳብ መግለጫ

1. እስራኤል በግብፅ፣ 1-11
2. እስራኤል ከግብፅ ወጣ፣ 12-18
3. እስራኤል በሲና ተራራ፣ 19-40
   ሀ. የሕይወት ሕግ በሲና ተራራ፣ 19-24
   ለ. የአምልኮ ሕግ በሲና ተራራ፣ 25-40
      (1) የማደሪያው ድንኳን (መቅደስ) ንድፍ፣ 25-31
      (2) ዓመጻና የኪዳን እድሳት፣ 32-34
      (3) የማደሪያው ድንኳን መገንባት፣ 35-40

ለ. መቅሠፍቶች

1. እነርሱም የእግዚአብሔርን ፍርድ ያሳያሉ፣ በግብፅ ጣዖታት ላይ። እነርሱም ከ18 ወራት በላይ የቆዩ ይመስላል። እነርሱም የተፈጥሮ ሁነቶችን ያካትታሉ፡
   ሀ. ከተፈጥሮ በላይ በሆነ የጊዜ ቀመር
   ለ. ከተፈጥሮ በላይ በሆነ ብርታት
   ሐ. ከተፈጥሮ በላይ በሆነ ስፍራ
2. የ10ሩ መቅሠፍት አጭር የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር
   ሀ. ዐባይ ወደ ደም ተቀየረ፣ 7:14-25
   ለ. ጓጉንቸሮች (እንቁራሪቶች)፣ 8:1-15
   ሐ. ቅማል፣ ትንኝ፣ 8:16-19
   መ. ዝንቦች፣ 8:20-32
   ሠ. የከብት በሽታ፣ 9:1-7
   ረ. እባጭ፣ 9:8-12

ሰ. በረዶ፣ 9:13-35
ሸ. አንበጣ፣ 10:1-20
ቀ. ጨለማ፣ 10:21-29
በ. መልአከ-ሞት፣ የበኵሮች ሞት፣ 11:1-8

ሐ. የበዓላት ዝርዝር/የምዕራፍ 23 የጾም (የበዓል ቀናት):
1. ሳምንታዊ ሰንበት፣ 23:3
2. ፋሲካ (14ኛ የኒሳን (ወር))፣ 23:5፤ ዘጸ. 12
3. ቂጣ እንጀራ (ያልቦካ) (15ኛ-21ኛ የኒሳን)፣ 23:6-8፤ ዘዳ. 16:1-8
4. በኵራት (22ኛ የኒሳን)፣ 23:9-14
5. በዓለ ኀምሳ ወይም የሳምንታት በዓል (50 ቀናት ከኒሳን 21ኛ በኋላ፣ 6ኛ ሲቫን)፣ 23:15-21፤ ዘዳ. 16:9-12
6. መለከት መንፋት (1ኛ ቲሽሪ)፣ 23:23-25፤ ዘኍ. 29:1-6
7. የመቀደስ ቀን (10ኛ ቲሽሪ)፣ 23:26-32፤ ዘኍ. 29:7-11
8. የዳስ በዓል (15ኛ ቲሽሪ)፣ 23:33-44፤ ዘኍ. 29:12-40፤ ዘዳ. 16:13-17

መ. ዝርዝር የፍሬ -ሐሳብ ዝርዝር
1. R. K. Harrison, *Introduction to the OT*, p 560-562 ተመልከት
2. E. J. Young, *An Introduction to the OT*, p 63-72 ተመልከት
3. NIV Study Bible, p 85-87 ተመልከት

IX. ዋነኛ ሐቆች

ሀ. እሱ በዘፍጥረት የተጀመረው ታሪክ ቀጣይ ነው። እሱ ለተመረጠው ሕዝብ የተመረጠውን ቤተሰብ እድገት ሰንዷል (ሰነዱን፣ (ታሪኩን) ይዟል)። ምንም እንኳ በግብፅ ባሪያዎች ቢሆኑም፣ የተስፋይቱን ምድር ይወርሳሉ (ዘፍ. 12:1-3፤ 15:16)።

ለ. እሱም የኪዳኑን ሕግጋት ሲና (ኮሬብ) ተራራ ላይ መዝግቧል።
1. እንዴት መኖር አለብን! (አስርቱ ትዕዛዛት እና ተጨማማሪዎች)
2. እንዴት ማምለክ አለብን! (የማደሪያ ድንኳን፣ ካህናት፣ ደንቦች (አገባቦች)፣ ጊዜ፣ እና የአምልኮ ሥርዓት)
3. እሱ "እንዴት መሆን" የሚለው፣ የማደሪያ ድንኳኑ መመሪያ ነው (ሌዋውያን)

ሐ. እሱም የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ ሰንዷል (በሰነድ ይዟል)፣ ለእስራኤል ያለውን ፍቅሩን እና ምሕረቱን፣ ለአብርሃም የተተነበየለትን፣ ዘፍ. 15፡16።

መ. እግዚአብሔር ከፈርዖን ጋር ያደረገው ግንኙነት የሚያመለክተው በእግዚአብሔር ሉዓላዊነት እና በሰው ነጻ ፍቃድ መካከል ያለውን ሚዛናዊነት ነው፡
1. እግዚአብሔር የፈርዖንን ልብ አደነደነ
ሀ. 7:3፣ 13
ለ. 9:12
ሐ. 10:1፣ 20፣ 27
መ. 11:10
ሠ. 14:4፣ 8

2. ፈርዖን የገዛ ራሱን ልብ አደነደነ
ሀ. 8:15፣ 32
ለ. 9:34

X. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት እና ሰዎች በአጭሩ የሚገለጹ

ሀ. ቃላት እና ሐረጋት
1. የመውለጃ በርጩማ፣ 1:16 (NIV፣ የመውለጃ በርጩማ)
2. ጫማህን አውልቅ፣ 3:5 (NASB እና NIV)
3. "የሦስት ቀን ጉዞ" 3:18፤ 5:3፤ 8:27 (NASB እና NIV)
4. "ልቡን አደነድናለሁ፣" 4:21፤ 7:3፣ 13፤ 9:12፣ 35፤ 10:1፣ 20፣ 27 (NASB እና NIV)
5. ጠንቋዮች፣ 7:11፣ 22 (NASB እና NIV)
6. ነውር የሌለበት፣ 12:5 (NIV፣ ያለ እንከን)

7. የዳመና ዓምድ፣ 13:21-22 (NASB እና NIV)
8. ነቢይት፣ 15:20 (NASB እና NIV)
9. እንጀራ (ዳቦ) (መና)፣ 16:4፤ 8፤ 14-15፤ 31 (NASB እና NIV)
10. የካህናት መንግሥት፣ 19:4-6 (NASB እና NIV)
11. ፈጽሞ ማጥፋት (*herem*)፣ 22:20 (NIV፣ ማጥፋት)
12. የተቀደሱ ዓምዶች፣ 23:24 (NIV፣ የተቀደሱ ድንጋዮች)
13. ኤፉድ፣ 25:7 (NASB እና NIV)
14. የምሕረት መቀመጫ፣ 25:17 (NIV፣ የማስተሠረያ ክዳን)
15. *Urim* እና *Thummin* ፣ 28:30 (NASB እና NIV)
16. መጽሐፍ፣ 32:32-33 (NASB እና NIV)
17. የገጽ ኅብስት፣ 35:13 (NASB እና NIV)

ለ. በአጭሩ የሚገለጹ ሰዎች

1. Hyksos፣ 1፡8
2. የእግዚአብሔር መልአክ፣ 3:1፤4
3. እኔ ነኝ (ያህዌ)፣ 3:14፤ 6:3 (NIV፣ NIV፣ ያለና የሚኖር)
4. ራጉኤል/ሩኤል፣ 2:18፤ ዮቶር፣ 3:1፤ 18:11-12
5. ፊንሐስ፣ 6:25
6. አጥፊው፣ 12:23
7. ናዳብ እና አቢሁ፣ 24:1
8. አማሌቅ፣ 17:8-16
9. ኪሩብ፣ 25:19


XI. የካርታ ስፍራዎች (በቁጥር)


1. ፒቶም፣ 1:11
2. ራምሴስ፣ 1:11
3. ምድያም፣ 2:15
4. ኮሬብ ተራራ፣ 3:1
5. ጌሻም፣ 8:22
6. ያም ሱፍ፣ 10:19 (NIV፣ ቀይ ባሕር)
7. የሲር ምድረ-በዳ
8. የጺን ምድረ-በዳ
9. ፋራን ምድረ-በዳ
10. የባሕር መንገድ (ፍልስጥኤም)፣ 13:17
11. አቃባ ባሕረ-ሰላጤ

XII. የተማሪ ይዘት ጥያቄዎች

1. ፈርዖን ዕብራውያንን የፈራው ለምድነው? 1:7-10
2. ወንዶች ሕፃናት ወደ ዐባይ የተጣሉት ለምድነው? የፈርዖን ቤተሰቦች ዐባይ ውስጥ የሚታጠቡት ለምንድን ነበር? የዐባይ ወደ ደም መቀየር ለምን እጅግ አስፈላጊ ሆነ?
3. ሙሴ ወደ ምድያም የሸሸው ለምንድነው?
4. እግዚአብሔር ስሙን ለሙሴ መግለጡ እጅግ ጠቃሚ የሆነው ለምንድነው?
5. 3፡22 በያህዌ እና በግብፅ ጣዖታት መካከል ስለተደረገው ግጭት ምን ይላል?
6. ዘጸ. 6፡3ን ያህዌ ዘፍጥረት 4፡26 ላይ ከመከሰቱ አንጻር እንዴት እናብራራዋለን?
7. መቅሠፍቶቹ በግብፅ ሃይማኖት ላይ ያሳደሩት ተጽዕኖ እንዴት ይታያል?
8. እግዚአብሔር የፈርዖንን ልብ ማደንደኑ፣ የእርሱን ነጻ ፍቃድ ወስዶበታልን?
9. የበኵሮች ሞት ጠቀሜታው ምንድነው?
10. ዕብራውያን ወታደራዊ መሣርያቸውን ያገኙት ከየት ነው?
11. ምዕ. 18 ላይ ሙሴ ለዮቶር ያደረገው ሥራ፣ የያህዌ አማኝ መሆኑን ያሳየው በምን መንገድ ነው?
12. እስራኤል የካህናት መንግሥት መሆኑ አንድምታው ምንድነው?
13. አስርቱን ቃላት ዘርዝር።
14. የምዕራፍ 23ን የበዓል ቀናት ዘርዝር።
15. የማደሪያ ድንኳኑን እና ዕቃዎቹን ስዕል ሳል።
16. የምዕራፍ 32 የወርቅ ጥጃ ተምሳሌትነቱ ምንድነበር?

# EXODUS




PALESTINE
0 10 20 30 40
SCALE IN MILES

# አሪት ሌዋውያን መግቢያ

I. የመጽሐፉ ስም

ሀ. በዕብራይስጥ ጽሑፍ (ኤምቲ) እሱ የመጽሐፉ የመጀመሪያ ቃል ነው፣ "እሱም (YHWH ያህዌ) ጠራ።"

ለ. ታልሙድ (Mishnah ሚሽናህ) "የካህናት ሕግ" በማለት ይጠራዋል።

ሐ. ከLXX የተተረጎመው "የሌዋውያን መጽሐፍ" በሚል ነው።

መ. የላቲን ቫልጌት የጀሮም "ሌዋውያን" የሚል ርዕስ ነው የሰጠው።

II. ቅዱስ ቃላዊነቱ (ካኖናዊነት)

ሀ. እሱም የዕብራይስጥ ካኖን የመጀመሪያው ምድብ ክፋይ ነው፣ "ቶራ" ወይም "አስተምህሮቶች" ወይም "ሕግ" ተብሎ የሚጠራው።

ለ. ምድቡም ፔንታቲሁች (አምስቱ ጥቅሎች) በመባል ይታወቃል፣ በ LXX።

ሐ. እሱም አንዳንዴ "አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት" በሚል በእንግሊዝኛ ይጠራል።

መ. እሱም እሱም የሚያካትተው ቀጣይነት ያለውን ከዘፍጥረት — ዘዳግም በሙሴ የተመዘገበውን ነው፣ ፍጥረትን በተመለከተ በሙሴ ሕይወት።

III. ዘውግ - ይህ መጽሐፍ ባብዛኛው ሕግን ማገግ (ማውጣት) ነው፣ ከምዕራፍ 8-10 ከሚገኙት ታሪካዊ ትርክቶች በቀር።

IV. ደራሲው - ምዕራፍ 1፡1 ተዘውትሮ የሚደጋገመውን አግባብ (ፈርጅ) ያስቀምጣል (35 ጊዜ) "ያህዌ ሙሴን አለው።" ዝርዝር ማብራሪያውን ዘፍጥረት የፍሬ ሐሳብ ዝርዝር ላይ ተመልከት።

V. ጊዜው - ዘጸ. 40፡2፣ 17 ከዘኁ. 1፡1 ጋር አነጻጽር። ይህ የሚያሳየው እሱ በእግዚአብሔር ለሙሴ መሰጠቱን ነው፣ በ2ኛው ዓመት በ1ኛው ወር፣ ከዘጸአት በኋላ። ዝርዝር ማብራሪያውን በዘጸአት የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር ላይ ተመልከት።

VI. ታሪካዊ መቼቱን የሚያጠናክሩ ምንጮች

ሀ. የሜሶፖታሚያ የአምልኮ ሥርዓት ሕግጋት

1. መሥዋዕት በቀዳሚነት ለጣዖት የተሠዋ ምግብ ነበር። መሠዊያው የጣዖት ጠረጴዛ ነበር፣ ምግቡ የሚቀመጥበት። ከመሠዊያው በስተጎን የዕጣን ማጨሻ ነበር፣ የጣዖቱን ቀልብ ለመሳብ። በደሙ ላይ ምንም ዓይነት አምልኳዊ አንድምታ አልነበረም። ሰይፍ ያዡ የእንስሳውን ጉሮሮ ይቆርጣል። ምግቡ ለጣዖታቱ፣ ለካህን-ንጉሡ፣ እና ለቋሚዎች ይከፋፈላል። መሥዋዕት አቅራቢው ምንም አይቀበል።
2. የማስተሥርያ መሥዋዕት አልነበረም።
3. በሽታ ወይም ሕመም ከአማልክት የሆነ ቅጣት ነበር። እንስሳው መጥቶ ይደመሰሳል፤ ይህም ለአቅራቢው እንደ ምትክ ድርጊት ይወሰዳል።
4. የእስራኤል የአምልኮ ሥርዓት የተለየና የተወሰነ ነበር። እሱም በዋነኛነት የወጣው አንድ ሰው ከሥራው ፍሬ ክፋዩን ለእግዚአብሔር መልሶ መስጠት ነበር፣ ለአስፈላጊው ምግብነት (ዘፍ. 4፡1-4፤ 8:20-22)።

ለ. የከነአን የአምልኮ ሥርዓት ሕግጋት (ከእስራኤል ጋር እጅግ ተመሳሳይ)

1. ምንጮች
   ሀ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጽሑፎች
   ለ. የፍንቄአውያን ሥነ-ጽሑፍ
   ሐ. የራስ ሻምራ ሰሌዳዎች ከዑጋሪት፣ የከነዓንን አማልክት እና አፈ-ታሪክ በተመለከተ፣ 1400 ቅ.ል.ክ አካባቢ።
2. የእስራኤልና የከነዓናውያን መሥዋዕት እጅግ ተመሳሳይ ናቸው። ሆኖም፣ በመሥዋዕቱ ደም ላይ ምንም ዓይነት ተጽዕኖ (ትኩረት) በከነዓናውያን አይደረግም።

ሐ. የግብፅ የአምልኮ ሥርዓት ሕግጋት

1. መሥዋዕቶች ይቀርቡ ነበር፣ ግን ተጽዕኖ (ትኩረት) አልነበራቸውም
2. መሥዋዕቱ ጠቃሚ አልነበረም፣ ነገር ግን መሥዋዕቱ የቀረበበት አዝማሚያ (ሁኔታ) እንጂ
3. መሥዋዕት የሚቀርበው የአማልክትን ቁጣ ለማስቆም ነበር
4. መሥዋዕት አቅራቢው መዳንን ወይም ይቅርታን ተስፋ ያደርግ ነበር

መ. የእስራኤል የመሥዋዕት ሥርዓት - የእስራኤል መሥዋዕቶች ከከነዓን ጋር ይቀራረቡ ነበር፣ ምንም እንኳ ከእነርሱ ጋር ፈጽሞ ባይዛመዱም።

1. ገላጭ ሐረጋት
   - ሀ. መሥዋዕት የስሜታዊነት መግለጫ ነበር፣ የሰው ልጅ የእግዚአብሔርን እርዳታ ሲሻ
   - ለ. የብኪ ሕግጋት መሥዋዕትን የተመለከቱት፣ የመሥዋዕት መነሻ (መነሳሻ) ናቸው ማለት አይቻልም (ዘፍ. 7፡8፤ 8፡20)
   - ሐ. መሥዋዕት አስተዋጽዖ የሚደረግ (የሚቀርብ) ነበር (እንስሳ ወይም እህል)
   - መ. የሚቀርብ መሆን ይኖርበታል፣ በሙሉ ወይም በከፊል መሠዊያው ላይ የሚወገድ፣ ለእግዚአብሔር ክብር
   - ሠ. መሠዊያው የመሥዋዕቱ ስፍራ ነበር እናም የመለኮት መገኘት ተምሳሌት
   - ረ. መሥዋዕት የውጫዊ አምልኮ ድርጊት ነበር (ጸሎት በድርጊት የሚፈጸም)
   - ሰ. የመሥዋዕት ፍቺ "የድርጊት ጸሎት" ወይም "አምልኮታዊ ጸሎት" ነው። የአምልኮ ሥርዓት ጠቀሜታ እና የእኛ ባህላዊ ቅድመ-አቋም፣ በእርሱ ላይ በተቃርኖ ያለን፣ (Gordon J. Wenham (Tyndale,*Numbers*, p. 25-39) ላይ ተገልጿል ሌዋውያን እና ዘኍልቍ ሁለቱም ይሄን ዓይነት ነገር በብዛት ይዘዋል፣ ይኸውም ለሙሴና ለእስራኤል ጠቀሜታውን የሚያሳይ።
2. መሥዋዕት የሚያካትተው
   - ሀ. ለእግዚአብሔር ስጦታ
     - (1) ይኸውም ምድርና ሞላዋ የእግዚአብሔር መሆንዋን ዕውቅና የሚሰጥ
     - (2) ሰው ያለው ሁሉ ከ/የእግዚአብሔር የሆነ ነው
     - (3) ስለዚህ፣ ሰው ለእግዚአብሔር ስጦታ ማምጣቱ ተገቢ ነው
     - (4) እሱም የተለየ ዓይነት መባ ወይም ስጦታ ነበር። እሱ፣ ሰው ለገዛ ራሱ ሕልውና አስፈላጊ የሆነ አንዳች ዓይነት ነገር ነበር። እሱ አንድ ነገርን እንዲያው ከመስጠት ያለፈ ነበር፣ እሱ የሚያስፈልገው ነገር ነበር። እሱ ከገዛ ራሱ ክፋይ ለእግዚአብሔር የሚሰጠው ነበር።
     - (5) ስጦታውን በማጥፋት/በማስወገድ፣ ዳግም መጠየቅ አይቻልም
     - (6) የሚቃጠል መሥዋዕት የሚታይና ወደ እግዚአብሔር ማደሪያ ሽቅብ የሚወጣ ነው
     - (7) ቀዳሚዎቹ መሠዊያዎች የተተከሉት እግዚአብሔር የተከሰተባቸው (የታየባቸው) ስፍራዎች ላይ ነበር። መሠዊያ እንደ ቅዱስ ስፍራ መታየት ጀመረ፣ ስለዚህ፣ መሥዋዕቱ ወደዚያ ይወሰድ ጀመር።
   - ለ. የአንዱን ሙሉ ሕይወት ለእግዚአብሔር መቀደስ (መስጠት) መግለጫ
     - (1) የሚቃጠል መሥዋዕት ከሦስቱ በፍቃድ ከሚቀርቡት መሥዋዕቶች አንደኛው ነበር።
     - (2) የእንሰሳው ሙሉ ለሙሉ መቃጠል ለእግዚአብሔር ያለንን ጥልቅ አክብሮት የሚገልጽ ነበር።
     - (3) ይህ ለእግዚአብሔር እጅግ ገላጭ ስጦታ ነበር።
   - ሐ. ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት
     - (1) ቍርባናዊ የመሥዋዕት ገጽታ
     - (2) ምሳሌ የሚሆነው የሰላም ስጦታ ነው፣ እሱም እግዚአብሔርና ሰው ኅብረት ማድረጋቸውን ተምሳሌት የሆነ
     - (3) መሥዋዕት ይደረግ የነበረው ይሄንን ኅብረት ለማግኘት ወይም ዳግም ለመመለስ ነበር
   - መ. የኃጢአት ሥርየት
     - (1) ሰው ኃጢአት ሲሠራ እግዚአብሔርን መጠየቅ ይኖርበታል፣ ኅብረቱ እንዲመለስ (ኪዳን) ይኸውም ሰው ያፈረሰው
     - (2) ምንም ዓይነት ቍርባናዊ (የኅብረት) ማዕድ አልነበረም፣ በኃጢአት መሥዋዕት ጊዜ፣ በፈረሰው ኅብረት ምክንያት
     - (3) የደሙ ጠቀሜታ
       - (ሀ) መሠዊያው ላይ ስለ ሰው ይቀርባል
       - (ለ) መሸፈኛው ላይ ስለ ካህኑ ይቀርባል
       - (ሐ) የምሕረት መቀመጫው ላይ ስለ ሊቀ-ካህኑ እና ስለ ሕዝቡ ይቀርባል (ሌዋ. 16)
     - (4) ሁለት ዓይነት የኃጢአት መሥዋዕቶች ነበሩ። ሁለተኛው የኃጢአት/በደል ወይም መተላለፍ መሥዋዕት ተብሎ ይጠራል። በእርሱም ተላላፊው እስራኤላዊ ወዳጅነቱን/ወንድምነቱን ለመመለስ ነው፣ የተወሰደበትን ወይም የተጎዳውን፣ በእንስሳው መሥዋዕት በኩል።
     - (5) ቀደም ብሎ ለታሰበበት ወይም ሆን ተብሎ ለተደረገ ኃጢአት ምንም ዓይነት መሥዋዕት አልነበረም 4:1፣ 22፣ 27፤ 5:15-18፤ 22:14

ሠ. የተለያዩ መሥዋዕቶች ያቀራረብ ደንብ/አገባብ

1. ምዕራፍ 1
   - ሀ. የመግቢያ ደንብ፣ "እግዚአብሔርም ሙሴን አለው፣" 1:1-2፤ 4:1፤ 5:14፤ 6:1፤19፤ 7:22፣ 28
     - (1) ከመንጋዎች ወይም ከብቶች
     - (2) "ጊዜ፣" ቁ. 2፣ የሚያመለክተው አስገዳጅ አለመሆኑን ነው፣ የፈቃድ እንጂ
   - ለ. የሚቃጠል መሥዋዕት፣ ቁ. 3-17 (6:8-13)
     - (1) መሠዊያ
       - (ሀ) የነሐስ መሠዊያ፣ እሱም ደግሞ የሚቃጠል መሥዋዕት መሠዊያ ተብሎ ይጠራል፣ ከማደሪያው ድንኳን (መቅደሱ) አጠገብ ያለ መሠዊያ፣ ወይም የግራር እንጨት መሠዊያ፣ በነሐስ የተለበጠ (የተሸፈነ) (ዘጸ. 27)
       - (ለ) ይህም ከዕጣን መሠዊያ የተለየ ያደርገዋል (የወርቅ መሠዊያ) በቅዱስ ስፍራ (ዘጸ. 30)
       - (ሐ) ከነሐስ መሠዊያው የከሰል ፍም ወደ ዕጣን መሠዊያው ይወሰዳል
       - (መ) የነሐስ መሠዊያው ወደ ማደሪያ ድንኳኑ (መቅደሱ) መግቢያ በኩል በመካከሉ ላይ ነው
       - (ሠ) መሠዊያው ቀንዶች አሉት፣ ይኸውም እጅግ የተቀደሰ ክፍል። ደሙ ወደ ቀንዶቹ እንዲወርድ ይደረጋል (ዘጸ.30፡10)።
       - (ረ) ቀንዶቹ ሊሆኑ የሚችሉት፡
         - i. የእጆች ተምሳሌት፣ መሥዋዕቱን ከፍ አድርጎ ለመያዝ
         - ii. የብርታት ወይም የጠንካራ ኃይል ተምሳሌት (ዘዳ. 33:17፤ II ሳሙ. 22:3።)

iii. ኋላ ላይ፣ ማንም የመሠዊያውን ቀንዶች የያዘ ደኅንነቱ የተጠበቀ ነበር፣ ጉዳዩ በፍርድ ቤት እስከሚታይ ድረስ (1 ነገ. 1:50-51፤ 2:28)

(2) *መሥዋዕቱ*
(ሀ) ነውር የሌለበት ወይፈን፣ እሱም በቅድሚያ የተጠቀሰ፣ ከጠቀሜታውና ከዋጋው አኳያ፣ ቁ. 3
(ለ) ተባዕት (ወንድ) ፍየል ወይም በግ፣ ቁ. 10
(ሐ) ርግብ ወይም ዋኖስ፣ ቁ. 14 (ለደሀ የሚሆን)

(3) የሚቃጠል *መሥዋዕቱ* የሚደረገው በመገናኛው ድንኳን በራፍ ላይ ነበር

(4) እጆችን ስለ መጫን - ይህ የሚደረገው ለከብቶች ብቻ ነበር፣ ለፍየሎች፣ ለበጎች ወይም ወፎች ሳይሆን፣ ቁ. 4
(ሀ) *መሥዋዕት* አቅራቢው ራሱ ነበር የሚያደርገው (ካህኑ ሳይሆን)
(ለ) አብዛኞቹ የሚወስዱት ኃጢአትን እንደማስተላለፍ ተምሳሌታዊ ድርጊት ነው
(ሐ) አንዳንዶች የሚያምኑት እሱ ማለት፡
i. ይህ እንስሳ የመጣው ከዚህ የተለየ ግለሰብ ነው
ii. *መሥዋዕቱ* የሚቀርበው በአቅራቢው ስም ነው
iii. የዚህ *መሥዋዕት* ፍሬ ባለቤትነቱ እጆቹን በእንስሳው ላይ ለጫነው ነው

(5) እርድ
(ሀ) ወይፈን - "በጌታ ፊት" *መሥዋዕቱን* በሚያቀርበው ሰው። *መሥዋዕት* አቅራቢው እንሰሳውን ማረድ፣ መግፈፍ፣ እና መቆራረጥ ይኖርበታል። የካህኑ ሚና (ከአደባባይ *መሥዋዕቶች* በተቀር) የሚጀምረው ሰውየው እንሰሳውን ወደ መሠዊያው ሲያመጣ ነው።
(ለ) በግ ወይም ፍየል፣ ቁ. 11 – "ከመሠዊያው በስተሰሜን በኩል፣ በጌታ ፊት።" ይህ የተወሰነ ስፍራ ይመደብለታል፣ ለእነዚህ አነስተኛ እንሰሳት።
(ሐ) ወፍ - ካህኑ ይሄንን *መሥዋዕት* አርዶ ያቀርባል። *መሥዋዕት* አቅራቢው የወፉን የሆድ-ዕቃ ያስወግዳል።

(6) የደሙ አያያዝ
(ሀ) እንሰሳት
i. ካህኑ ደሙን ወደ መሠዊያው ይረጫል፣ እና እናም በመሠዊያው ዙሪያ ይረጫል።
ii. የእንሰሳው ሕይወት በደሙ ውስጥ ነው (ዘፍ. 9:4፤ ሌዋ. 17:11)። ሕይወት ቀደም ሲልም የእግዚአብሔር ነው፣ ስለዚህ፣ ደሙ የትኛውንም የሰውየውን ስጦታ ክፍል አይወክልም።
iii. የወፉ ደም በመሠዊያው በኩል ይቀዳል (ይወርዳል)፣ በእሳት አይቃጠልም።

(7) የሥጋው አያያዝ
(ሀ) ወይፈን፣ ቁ. 6
i. *መሥዋዕት* አቅራቢው ከብቱን ይገፍፋል። ካህኑ ቆዳውን ያኖረዋል (ዝኪ. 7፡8)
ii. *መሥዋዕት* አቅራቢው በየብልቱ ይቆራርጠዋል
iii. ካህኑ *መሥዋዕቱን* መሠዊያው ላይ ያኖረዋል፣ በሕይወት እንደነበረ፣ በየብልቱ
iv. እግሩና የሆድ ዕቃው በሳህኑ ውኃ ይታጠባሉ
v. ካህኑ ሁሉንም ነገር መሠዊያው ላይ ያቃጥላል

ሐ. የሚቃጠል *መሥዋዕት* የሚቀርብበት ሁነት
(1) የማደሪያው ድንኳን በዓል፣ የዳስ በዓል
(2) የስርየት ቀን
(3) የሳምንታት በዓል፣ የበዓለ ኀምሳ በኵራት
(4) የመለከት በዓል
(5) ነዶ መወዝወዝ (ሌዋውያን 23)
(6) የቂጣ በዓል፣ ፋሲካ
(7) የወራት መጀመሪያ፣ አዲስ ጨረቃ
(8) ሰንበት

መ. የሚቃጠል *መሥዋዕት* ጠቀሜታ (ረብ)
(1) ለእግዚአብሔር ስጦታ
(2) እጅግ ዋጋ እንዳለው *መሥዋዕት* ዓይነት ተደርጎ ይታያል።
(3) እሱም በአጠቃላይ የኃጢአትን ጽንሰ-ሐሳብ ወይም ምስጋና ማቅረብን የያዘ ይመስላል።
(4) እጅግ ፍጹም የሆነ የመሥዋዕት ሐሳብን ይወክላል።
(5) የአንዱ ሕይወት ተምሳሌታዊ ስጦታ (መባ)
(6) የአንድን ግለሰብ ሕይወት ለእግዚአብሔር አገልግሎት ፍጹም መስጠትን (መቀደስን) ይወክላል
(7) የመሥዋዕት ዋጋ ደረጃዎች
(ሀ) ወይፈን
(ለ) በግ - ፍየል
(ሐ) ወፎች
(8) ይህ የሚያመለክተው ማንም ሰው ለመንፈሳዊ መሻት ንቁ ከሆነ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ መቻሉን ነው። እግዚአብሔር ለሰዎች ሁሉ መጋቢነትን (ስጦታ) አድርጓል።

ሠ. የተለየ ትዕዛዝ ለካህን፣ 6፡8-12
(1) የሚቃጠለው *መሥዋዕት* ሌሊቱን ሁሉ በመሠዊያው እሳት ላይ ይሆናል
(2) እሳት በሚቃጠለው *መሥዋዕት* ሥር እንደ ነደደ ይቀራል (አይጠፋም)
(3) የካህኑን ልብስ በተመለከተ የተሰጡ ትዕዛዛት
(4) የአመዱን አወጋገድ በተመለከተ የተሰጡ ትዕዛዛት

2. ምዕራፍ 2፡ 1-16 (6:14-23)

ሀ. መግቢያ

(1) ይህ ምዕራፍ የሚገልጸው የእህል ቍባንን ነው
(2) የእህል ቍርባን "ስጦታ" ከሚለው ሥር ፍቺ ነው። እሱም ብልሃታዊ (ቴክኒካል) ቃል ሆኗል፣ እንስሳ ላልሆኑ፣ ወይም ለዕጽዋት ስጦታዎች።
(3) ከግዞት በኋላ የእህል ቍርባን ለሚቃጠል መሥዋዕት እና ለሰላም መሥዋዕት ተጨማሪ ሆኖ ቀርቧል፣ ራቢዎችም የሚሉት እሱ ብቻውን ሊቀርብ ይችላል፣ በፍጹም ድሆች።
(4) የጨው ኪዳን ደግሞ ዘኍ. 18:19 እና 11 ዜና. 13:5 ላይ ተጠቅሷል። ጨው የቡኮ ተቃራኒ ነው። እሱም ለእግዚአብሔር ኪዳን ተምሳሌት ሆኖ ጥቅም ላይ ውሏል፣ ምክንያቱም እሱ የማይበላሽና የማያበቃ ስለሆነ ነው።

ለ. የእህል ቍርባን የሚያካትተው የአንዱን የሥራ ፍሬ ለእግዚአብሔር መስጠቱን ነው።

(1) እሱም ለእግዚአብሔር የሚሆን ስጦታ ነው፣ ከሰዉ የዕለት ምግብ ላይ።
(2) እሱ ባጠቃላይ ተጨማሪ ነው (በተለይም በድኅረ-ስደት ቀናት) ለሚቃጠል ወይም ለሰላም መሥዋዕት።
(3) መሥዋዕት ለካህኑ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። የተወሰነ ክፍል ብቻ ይቃጠላል፣ ለሞላው መታሰቢያ።
(4) "መታሰቢያ" የሚለው ቃል የሚሠዋውን ክፋይ፣ ወይም ያንን ክፍል፣ ማለትም በእግዚአብሔር ፊት ሙሉውን ያመጣውን ይገልጻል።
(5) የአዲስ ኪዳን የጌታ ራት ጽንሰ-ሐሳብ እንደ "መታሰቢያ" መሆኑ ይሄንን የብሉይ ኪዳን ጽንሰ-ሐሳብ ይገልጻል።
(6) በ "ቅዱስ" እና "ቅዱሰ ቅዱሳን" በሚሉት ቃላት መካከል ያለው ልዩነት፡
   (ሀ) "ቅዱስ" - ካህኑና የካህኑ ቤተሰቦች በማንኛውም ንጹሕ ስፍራ ሊመገቡት ይችላሉ
   (ለ) "ቅዱሰ ቅዱሳን" - በካህናት ብቻ የሚበላ ነው፣ በመገናኛው ድንኳን ስፍራ (ውስጥ)

ሐ. ዓይነቶች

(1) ያልተጋገረ ዱቄት (ለሃብታም)፣ 2፡1-3
(2) የተጋገሩ ኅብስቶች ወይም ዳቦ፣ 2፡4-11
(3) የእህል ወይም የስንዴ ዛላ (ለደሀ)፣ 2፡12-16
   (ሀ) ያልተጋገረ ዱቄት ከፍ ያለ ስጦታ ነው። እሱም ከመልካም የስንዴ ዱቄት ነው።
   (ለ) የተጋገሩ ኅብስቶች
      i. ዘይት አንደኛው ማጣፈጫ ነበር
      ii. በምድጃ ላይ ይሰናዳል፣ ቁ. 4።
      iii. በመጋገሪያ ብረት፣ ቁ. 5።
      iv. በሸክላ መጋገሪያ ምጣድ፣ ቁ. 7።
   (ሐ) የእህል ወይም የስንዴ ዛላ
      i. የደረቀ መሆን ይኖርበታል
      ii. በየመልኩ ይሰባበራል
      iii. ለእንግዶች እንደሚቀርብ ምግብ ይሰናዳል።

መ. ውህዶች

(1) መልካም ዱቄት ነውር ከሌለው እንስሳ ጋር ይተካከላል
(2) ዘይት የብልጽግና ተምሳሌት ነው፣ እና ስለዚህ፣ የእግዚአብሔር መገኘት ተምሳሌት
   (ሀ) ለምግብ፣ ለመሥዋዕት፣ ለመድኃኒትነት፣ እና ለመቀባት ጥቅም ላይ ይውላል
   (ለ) ዘይትን መጠቀም የዘይት መሥዋዕትን ለመተካት ነበር
(3) ዕጣኑ ከህንድ ወይም ዓረቢያ ነበር
   (ሀ) እንደ እጅግ ንጹሕ ነገር ይታያል፣ ከአስደናቂ መዓዛ ጋር
   (ለ) የጸሎትና ምስጋና ተምሳሌት ነው
(4) ጨው
   (ሀ) ሕይወት ሰጪ ብሎም የመጠበቅ ባሕርይ (ጥራት) ያለው
   (ለ) ባብዛኛው ለማዕድ ኅብረት ከመጠበቅ ይልቅ
(5) የማይካተቱ ንጥረ-ነገሮች
   (ሀ) እርሾ አይካተትም፣ ቁ. 11
      i. በመቡካቱ ምክንያት ይሆናል
      ii. እርሾ ከመበላሸት ጋር ይያያዛል
      iii. ከበኩራት ጋር መቅረብ ይኖርበታል፣ ለካህኑ
   (ለ) ማር አይካተትም
      i. ጭማቂው ከፍራፍሬ እንጂ ከማር አልነበረም
      ii. በከነዓን የአምልኮ ሥርዓት ስለሚጠቀሙበት ይሆናል

ሠ. የመሥዋዕት የአምልኮ ሥርዓት

(1) ወደ ካህኑ ይመጣል። እሱም አጠቃላይ ሥነ-ሥርዓቱን ይመራል (2፡2፣ 9፣ 16)
(2) የመሥዋዕቱ ከፊል በካህኑ የሚበላ ይሆናል፣ በመቅደሱ። እሱም እጅግ ቅዱስ ነው።

ረ. ጠቀሜታው

(1) ከዝቅተኛው እስከ ከፍተኛው ይቀርባል (ደሀም ሃብታምም)
(2) የእሱ ከፊል መቃጠሉ የአንዱ የሥራ ፍሬ ከፊል ለእግዚአብሔር መቀደሱን ይወክላል
(3) አጠቃላይ ፍችው
   (ሀ) የሚቃጠል መሥዋዕት - የአንዱ ሕይወት መቀደስ (መሰጠት)
   (ለ) የምግብ መሥዋዕት - የአንዱ የየቀኑ የሥራ ፍሬ መሰጠት

ሰ. ስለ እህል ቍርባን ልዩ ትዕዛዝ (መመሪያ)፣ 6፡14-23

(1) በመሠዊያው ፊት ለፊት መቅረቡ
(2) የሥራ ፍሬ ለእግዚአብሔር ይቀርባል፣ ነገር ግን በተጨባጭ የክህነት ተግባሩን ለመደገፍ ነው

3. ምዕራፍ 3፡1-17 (7፡13-34) የሰላም መሥዋዕት

ሀ. መግቢያ

(1) ለምን

(ሀ) የቊርባን መሥዋዕት

(ለ) የኪዳን መሥዋዕት

(ሐ) የአንድነት መሥዋዕት

(መ) የማጠቃለያ መሥዋዕት

(2) እሱም ለእግዚአብሔር የሆነ ምስጋና መግለጫ ነው፣ ከእግዚአብሔር፣ ከቤተሰብ እና ከጓደኞች ጋር ኅብረት ከመኖሩ የተነሣ።

(3) እሱም ዘወትር የመጨረሻ ድርጊት ነው፣ ተከታታይነት ባላቸው መሥዋዕት አቅርቦት፣ እርቅ (መልካም ግንኙነት) በመፈጠሩ።

(4) የሚቃጠል መሥዋዕት የመታዘዝን ውድነት ሲገልጽ፣ የሰላም መሥዋዕት ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር በተፈጠረው ኅብረት የተገኘውን ደስታና ፍስሐ ይገልጻል።

(5) ተባዕትም ሆነ እንስት (ወንድ/ሴት) ግን ነውር የሌለበት

(6) የመሥዋዕት ዓይነቶች

(ሀ) ከመንጋው፣ ወንድ ወይም ሴት

(ለ) በበግና በፍየል መካከል ልዩነት የተደረገው በበግ ላት ላይ ባለው ስብ ምክንያት ነው

i. የመንጋው ጠቦት - ወንድ ወይም ሴት

ii. የመንጋው ፍየል - ወንድ ወይም ሴት

ለ. የአምልኮ ሥርዓት

(1) የመሥዋዕት አቅርቦት

(ሀ) በመሥዋዕቱ ላይ እጅ ይጫናል

(ለ) በመገናኛው ድንኳን በር ላይ ይታረዳል

(ሐ) የመሥዋዕቱ መለያ ተመሳሳይ ነው፣ እንደሚቃጠል መሥዋዕት

(መ) ደሙን በመሠዊያው ዙሪያ መርጨት

(ሠ) የተመረጡ ክፍሎችን በመሠዊያው ላይ ለእግዚአብሔር ማቃጠል

i. ስብ (የበግ ላት) የብልጽግና ተምሳሌት ነው

ii. ኵላሊቶች፣ በጉበቱ ላይ ያለው መረብ ተምሳሌትነቱ የፍቃድና የስሜት መቀመጫ መሆኑ ነው

iii. ስብማ ክፍሎች በመሥዋዕት አቅራቢው የሚቃጠል መሥዋዕት ወይም በየማለዳው የበግ -ጠቦት መሥዋዕት ላይ ይደረጋሉ

(2) የምስጋና መሥዋዕት የሚያካትተው (7፡11-14)

(ሀ) ያልቦካ ዳቦ በዘይት የተለወሰ

(ለ) ያልቦካ ኅብስት፣ ዘይት የተቀባ

(ሐ) መልካም ዱቄት፣ በዘይት የተለወሰ

ሐ. የካህኑ ድርሻ፣ 7፡28-34

(1) ፍርምባ የካህኑ ድርሻ ነው እንደሚወዘወዝ መሥዋዕት

(2) መወዝወዝ የሚያካትተው መሥዋዕቱን በአቅራቢው እጅና በካህኑ እጅ ላይ ማኖርንም ነው። እሱም የሚያሳየው ለእግዚአብሔር በአቅራቢው የሚቀርበውን መሥዋዕት ነው፣ ከዚያም ተመልሶ በካህኑ መቀበሉን።

(3) የቀኙ ወርች ለአገልጋዩ ካህን ይሆናል

(4) የማንሣት ቊርባን፣ ወደ እግዚአብሔር ይነሣና ተመልሶ በካህኑ ይቀበላል

መ. የመሥዋዕት አቅራቢው ድርሻ፣ 7፡15-18

(1) የምስጋና ማቅረብ መሥዋዕት በሚቀርብበት ቀን ይበላል፣ ቁ. 15

(2) የስዕለት (መሳል) ወይም የፍቃድ መሥዋዕት በሚቀርብበት ቀን ወይም በሚቀጥለው ቀን ይበላል፣ ቁ. 16

(3) ይህ ድርሻ ለእግዚአብሔር የማይሰጠው ሁሉ ነው፣ እንዲሁም በእግዚአብሔር ለካህኑ

(4) እግዚአብሔር በተምሳሌትነት ከመሥዋዕት አቅራቢው እና ከቤተሰቡ እና ከጓደኞቹ ጋር ከዚህ መሥዋዕት አብሮ ይበላል

(5) ይህም መሥዋዕት አጽንዖት የሚሰጠው ወዳጃዊ ግንኙነት መመለሱን ነው

4. ምዕራፍ 4፡1-5፡13 (6፡24-30) የኃጢአት መሥዋዕት

ሀ. መግቢያ

(1) ይህ የመጀመሪያው መሥዋዕት ነው ሥርየት ዋነኛው ነገር ለመሆኑ።

(2) ይህ መሥዋዕት በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለውን ኪዳን ዳግም ያጸናል። እሱም ኅብረትን ይመልሳል።

(3) ይህ መሥዋዕት የሚያካትተውም፡

(ሀ) ባለማወቅ የተፈጸመ ኃጢአት

(ለ) በቸልታ የተፈጸመ ኃጢአት

(ሐ) የስሜት ኃጢአት

(መ) የግድፈት ኃጢአት

(ሠ) ሆን ተብሎ ለተሠራ ኃጢአት፣ በእግዚአብሔር ላይ በትዕቢት ዓመጻ ለተፈጸመ ማስተሠረያ የለውም። ሆን ተብሎ፣ በትዕቢት (ሌሎችን በመናቅ)፣ ቀደም ብሎ ታስቦበት ለተፈጸመ ኃጢአት ማስተሠረያ የለውም (ዘኍ. 15፡27-31)።

ለ. ፍችው

(1) ይህ መሥዋዕት በደልንና የኃጢአት ቅጣትን ያስተሠርያል
(2) ይህም የሚያካትተው ጸጋን በእግዚአብሔር በኩል፣ እንዲሁም እምነትን በሰው በኩል ነው።
(3) ማንኛውም መሥዋዕት በአምልኮ ሥርዓታዊ መሥዋዕት መልኩ ምንም ነገር አያስገኝም። ከድርጊቱ በስተጀርባ ያለው የመሥዋዕት አቅራቢው እምነት እንጂ ነው።
(4) ሆኖም፣ መሥዋዕት፣ በአቅራቢው ከሚገለጸው ድርጊት ላቅ ያለ ነው። ለእርሱም አንድ ነገር ያደርግለታል። ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ኅብረት ዳግም ያጸናለታል።
(5) የአምልኮ ሥርዓት እግዚአብሔር ያበጀው የመዋጃ (መቤዣ) አገባብ (መንገድ) ነው፣ የግል እምነትን የሚተካ ሳይሆን።
(6) እግዚአብሔር ማንኛውንም ዓይነት ሃይማኖታዊ ድርጊት ይጠላል፣ እምነትን ተጎዳኝቶ ካልቀረበ፣ ኢሳ. 1:10-20፤ አሞጽ 5:21- 24፤ ሚኪያስ 6:6-8።

ሐ. የአምልኮ ሥርዓት

(1) ለሊቀ-ካህኑ፣ ቁ. 3-12
(ሀ) ሊቀ-ካህን - የተቀባ ካህን
i. ኃጢአት መሥራት፣ ሕዝቡን በስህተት በመምራት
ii. ኃጢአት መሥራት፣ በሰብዓዊ ተፈጥሮው
iii. ሊቀ-ካህን የማኅበረሰቡ መንፈሳዊ ተወካይ ነው። እሱ ኃጢአት ከሠራ፣ ሁሉም በእርሱ በኩል ሠርተዋል። ይህ የአይሁድ አንድ አካል (የጋራ) አስተሳሰብ ነበር (ኢያሱ 7፤ ሮሜ 5፡12)።
(ለ) አገባቦች (ደንቦች)
i. ሊቀ-ካህኑ ነውር የሌለበትን ወይፈን ወደ መሠዊያው ያመጣል።
ii. እጁንም በራሱ ላይ ይጭንበታል
iii. ሊቀ-ካህኑ እንስሳውን ያርደዋል
iv. ሊቀ-ካህኑ ደሙን 7 ጊዜ መሸፈኛው (መጋረጃው) ላይ ይረጨዋል
ሀ)ይህም የማደሪያውን ድንኳን ያነጻዋል
ለ) በተምሳሌትነትም ወደ እግዚአብሔር የሚወስደውን መንገድ ይከፍታል
ሐ) ደሙ በዕጣኑ መሠዊያ ቀንዶች ላይ ይደረጋል
መ) የቀረው ደም በሚቃጠል መሥዋዕቱ መሠዊያ ሥር እንዲፈስስ ይደረጋል
v. ስቡ ሁሉ በመሠዊያው ላይ ተደርጎ ይቃጠላል
vi. ቀሪው የእንስሳው አካል ከሰፈሩ ውጭ ወደ ንጹሕ ስፍራ ይወሰዳል፣ ቁ. 12፣ ከመሠዊያው ላይ ከሚወጣው አመድ ጋር። እዚያም ቀሪው የእንስሳው አካል ይቃጠላል።

(2) ለሕዝቡ፣ ቁ. 13-21
(ሀ) ኃጢአት የሚሠሩት የሕግ ትዕዛዛት ሲጣሱ ነው፣ ቁ. 13-21።
(ለ) አገባቦች (ደንቦች)
i. ሽማግሌዎች ነውር የሌለበትን ወይፈን ወደ መሠዊያው ያመጣሉ።
ii. ሽማግሌዎች በራሱ ላይ እጃቸውን ይጭናሉ።
iii. ሽማግሌዎች እንሰሳውን ያርዳሉ።
iv. ሊቀ-ካህኑ ደሙን 7 ጊዜ በመሸፈኛው (መጋረጃው) ላይ ይረጫል።
ሀ) ይህም የማደሪያውን ድንኳን ያነጻል
ለ) በተምሳሌትነትም ወደ እግዚአብሔር የሚወስደውን መንገድ ይከፍታል
ሐ) ደሙ በዕጣኑ መሠዊያ ቀንዶች ላይ ይደረጋል
መ) የቀረው ደም መሥዋዕቱ መሠዊያ ሥር እንዲፈስስ ይደረጋል
v. ሁሉም መሠዊያው ላይ ይሠዋል
vi. ቀሪው የእንስሳው አካል ከሰፈሩ ውጭ ወደ ንጹሕ ስፍራ ይወሰዳል፣ ቁ. 12፣ ከመሠዊያው ላይ ከሚወጣው አመድ ጋር። እዚያም ቀሪው የእንስሳው አካል ይቃጠላል።

(3) ለአለቆች፣ ቁ. 22-26
(ሀ) አለቃ (ገዥ) ቁ. 22-26
i. የነገድ አለቃ
ii. በማኅበረሰቡ ውስጥ ኃላፊነት ያለው ሰው
iii. ሽማግሌ
(ለ) አገባብ (ደንብ)
i. አለቃው ወንድ ፍየል (የጠና፣ ፀጕራም ፍየል) ወደ መሠዊያው ያመጣል።
ii. አለቃው እጁን በራሱ ላይ ይጭናል።
iii. አለቃው እንሰሳውን ያርዳል።
iv. ሊቀ-ካህኑ ደሙን በሚቃጠል መሥዋዕት መሠዊያ ቀንዶች ላይ ያደርጋል፣ የቀረው ደም መሥዋዕቱ መሠዊያ ሥር እንዲፈስስ ይደረጋል።
v. ስቡ ሁሉ መሠዊያው ላይ ይቃጠላል።
vi. ካህናት ቀሪውን ሥጋ ይበሉታል።

(4) ለግለሰብ፣ ቁ. 27-35
(ሀ) ለግለሰብ - ኃጢአት መሥራቱን ካወቀ ይሄንን መሥዋዕት ያቀርባል
(ለ) አገባብ (ደንብ)
i. ግለሰቡ ሴት ፍየል ወይም ሴት በግ ያቀርባል።
ii. ግለሰቡ እጁን በራሱ ላይ ይጭናል።
iii. ግለሰቡ እንሰሳውን ያርዳል።
iv. ካህኑ በመሥዋዕቱ መሠዊያ ቀንዶች ላይ ደሙን ያኖራል - ቀሪው በመሠዊያው ሥር እንዲፈስ ይደረጋል።

v. ስቡ ሁሉ በመሠዊያው ላይ ተደርጎ ይቃጠላል።
vi. ካህናት ቀሪውን ሥጋ ይበሉታል።

(5) በኃጢአት መሥዋዕት የሚካተቱ ልዩ ጉዳዮች፣ 5፡1-13 (እነዚህም የሚካተቱት በኪዳን ባልንጀራ ላይ ሆን ተብለው የተደረጉ ኃጢአቶች ናቸው)
(ሀ) ምስክር ቀርቦ የማይመሰክር ከሆነ (መረጃ ያለመስጠት ችግር) 5፡1
(ለ) ርኩስ እንሰሳ ከተነካ፣ 5፡2
(ሐ) የረከሰ ሰው ከተነካ፣ 5፡3
(መ) ሳያስቡ (በቸልታ) የመሐላ ቃል መናገር፣ 5፡4
(ሠ) ከላይ ለተጠቀሱት ኃጢአቶች የሚቀርበው መሥዋዕት፡
i. ሴት ፍየል ወይም በግ
ii. ሁለት ርግቦች ወይም ሁለት ዋኖሶች
iii. የኤፉድ 1/10ኛ መልካም ዱቄት

(6) የኃጢአት መሥዋዕት የአምልኮ ሥርዓት፣ 6፡24-30
(ሀ) ካህኑ የተረፈውን ሊበላ ይችላል።
(ለ) ደም ልብስን ከነካ፣ ልብሱ መታጠብ ይኖርበታል።
(ሐ) ደሙ የሸክላ ዕቃ ከነካ ፣ ዕቃው ይሰበራል።
(መ) ደሙ የነሐስ ዕቃ ከነካ፣ ዕቃው ይታጠባል።
(ሠ) የሚቃጠለው መሥዋዕት ደም ወደ ተቀደሰው ስፍራ ከመጣ፣ እንግዲያውስ ሥጋው መቃጠል ይኖርበታል፣ በካህኑም አይበላም።

(7) የኃጢአት መሥዋዕት ጠቀሜታ
(ሀ) ቀደም ብሎ ታስቦበት (ሆን ተብሎ) ለተሠራ ኃጢአት የሚቀርብ መሥዋዕት የለም - ሳይታሰብ ለተሠራ ኃጢአት ወይም ባለማወቅ ለተደረገ ብቻ ነው፣ 5፡15፣ 18።
(ለ) ምሕረት (ይቅርታ) ምንን ያካትታል፡
i. በሰው በኩል እምነት
ii. በእግዚአብሔር በኩል ምሕረት

5. ምዕራፍ 5፡14-19 የበደል ወይም የመተላለፍ መሥዋዕት
ሀ. መግቢያ
(1) ለተፈጸመው ኃጢአት የኃጢአት መሥዋዕት እንደሚደረግ፣ የበደል መሥዋዕት ደግሞ በኪዳን ባልንጀራ ላይ ለተፈጸመ ጉዳት ይደረጋል፣ የሚቻለውን ያህል ካሣ።
(2) የኃጢአትና የመተላለፍ መሥዋዕቶች እጅግ ተመሳሳይ ናቸው።
(3) የግለሰብ መብቶች በአስርቱ ትዕዛዛት ላይ ተጠቅሰዋል (ዘጸ. 20፤ ዘዳ. 5)።
(ሀ) ቤት
(ለ) ዕቃዎችን ማከማቸት
(ሐ) በሕይወት መኖር
(4) ይህ መሥዋዕት አጽንዖት የሚሰጠው በወንድማችን ላይ ስለተፈጸመው ጉዳትና በደል (ኃጢአት) ሲሆን፣ የጉዳት ካሣው ዋጋና 1/5 ታክሎበት ይከፈላል።
ለ. መሥዋዕት የሚያስፈልጋቸው ኃጢአቶች
(1) በእግዚአብሔር ላይ እና የእሱ በሆነ ላይ
(ሀ) በኵራት
(ለ) በኵር፣ 14-16
(ሐ) መባ
(መ) ያላግባብ የተሰጠ መሥዋዕት (መባ)
(ሠ) ዝቅተኛ ዋጋ ያለው (የማይረባ) ስጦታ
(2) "ማናቸውም ሰው ኃጢአት ቢሠራ፣ እግዚአብሔርም አትሥሩ ካላቸው ትዕዛዛት አንዲቱን ቢተላለፍ፣ ባያውቅም፣ ያ ሰው በደለኛ ነው፣ ኃጢአቱንም ይሸከማል።"

ረ. የጥንት መሥዋዕት በብዙ ምክንያት ይቀርብ ነበር፡
ሀ. የተቆጣ አማልክትን ለማለዘብ
ለ. አማልክትን ለመመገብ
ሐ. ከአማልክት ጋር ኅብረት (አንድነት) ለመፍጠር
መ. የምስጋና ድርጊት
ሠ. ይቅርታ ወይም እርቀ-ሰላም እንደሚያስፈልግ ለመግለጽ

VII. ጽሑፋዊ ምድቦች (ዐውደ-ጽሑፍ)

ሀ. አጭር የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር፡
1. ምዕራፍ 1-16 - ወደ ቅዱስ አምላክ እንዴት ይቀረባል?
2. ምዕራፍ 17-26 - አንዱ ከቅዱስ አምላክ ጋር ያለውን ግንኙነት (ኅብረት) እንዴት ይቀጥላል?

ለ. የደራሲው የራሱ የመግቢያ ቃል (መግለጫ) አጠቃቀም፣ "እግዚአብሔርም ሙሴን (ወይም አሮንን) እንዲህ ብሎ ተናገረው..."
1. ይህ የሚያመለክተው፣ ይህ መገለጥ በጊዜና ሰዓት ሁኔታ ውስጥ መሰጠቱን ነው።

2. ይህ ቃል (መግለጫ) የሚገኝባቸው ስፍራዎች፡ 1:1-3:17፤ 4:1-5:13፤ 5:14-19፤ 5:20-26፤ 6:1-11፤ 6:12-16፤ 6:17-7:21፤ 7:22-38፤ 8:1-10:20፤ 11:1-47፤ 12:1-8፤ 13:1-59፤ 14:1-32፤ 14:33-57፤ 15:1-33፤ 16:1-34፤ 17:1-16፤ 18:1-3፤ 19:1-37፤ 20:1-27፤ 21:1-24፤ 22:1-16፤ 22:17-25፤ 22:26-33፤ 23:1- 8፤ 23:9-22፤ 23:26-32፤ 23:33-44፤ 24:1-23፤ 25:1-26:46፤ 27:1-34፤

ሐ. የተስፋፋ የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር:

1. ርኵሰትን ማስወገድ፣ ምዕ. 1-16
   - ሀ. የመሥዋዕት ሕግጋት፣ 1:1-7:38
     - (1) የሚቃጠል መሥዋዕት፣ ምዕ. 1:3-17 እና 6:8-13
     - (2) የእህል ቍርባን፣ ምዕ. 2:1-17 እና 6:14-23
     - (3) የሰላም (ደኅንነት) መሥዋዕት፣ ምዕ. 3:1-17፤ 7:33 እና 7:11-21
     - (4) የኃጢአት መሥዋዕት፣ ምዕ. 4:1፤ 5:13 እና 6:24-30
     - (5) የበደል መሥዋዕት፣ ምዕ. 5:14-6:7፤ 7:1-10
       - (ሀ) ሆን ተብሎ ያልተደረገ ኃጢአት፣ በያህዌ ኪዳን ላይ፣ 4:1-35፤ 5:14-19
       - (ለ) ሆን ተብሎ በኪዳን ጓደኛ ላይ የተደረገ ኃጢአት፣ 5:1-13፤ 6:1-7
     - (ምዕራፍ 1-6:7 ለሕዝብ፤ ምዕራፍ 6:8-7:36 ለካህናት)
   - ለ. የካህናት መቀደስ (መለየት)፣ 8:1-10:20
     - (1) የዘይቱ አዘገጃጀት፣ 8:1-5
     - (2) መታጠብ፣ መልበስ እና መቀባት፣ 8:6-13
     - (3) የቅብዓት መሥዋዕት፣ 8:14-32
     - (4) ሙሴ ለአሮን ትዕዛዛትን ሰጠው፣ 9:1-7
     - (5) አሮንና ልጆቹ ጀመሩ፣ 9:8-21
     - (6) አሮን ሕዝቡንና እግዚአብሔርን ባረከ
     - (7) የናዳብ እና አብዩድ ኃጢአት፣ 10:1-3
     - (8) የእነርሱ ዕጣና መወገድ፣ 10:4-7
     - (9) በሥራ ላይ ከወይን ጠጅ ስለመታቀብ፣ 10:8-11
     - (10) ካህናትን የተመለከቱ መሥዋዕቶች፣ 10:12-20
   - ሐ. ንጹሕ እና ንጹሕ ያልሆነ፣ ምዕራፍ 11-15
     - (1) እንስሳት፣ ምዕ. 11 (ዘዳ. 14:6-20)
     - (2) ልጅ መውለድ፣ ምዕራፍ 12
     - (3) የቆዳ በሽታ፣ ምዕራፍ 13-14
       - (ሀ) በሰው፣ 13:1-46
       - (ለ) በልብሶች፣ 13:47-59
       - (ሐ) መንጻት፣ 14:1-32
       - (መ) በቤቶች፣ 14:33-53
       - (ሠ) ማጠቃለያ፣ 14:54
     - (4) ከሰውነት ከሚወጣ ፈሳሽ መንጻት (ወንዶች እና ሴቶች)፣ ምዕራፍ 15
   - መ. የስርየት ቀን (ዮም ኪፑር)፣ ዓመታዊ የመንጻት ቀን፣ ምዕራፍ 16 (ይህ የምዕራፍ 1-16 ከፍተኛ ጫፍ ይመስላል)
     - (1) የክህነት ዝግጅት፣ 16:1-4
     - (2) የኃጢአት መሥዋዕት፣ ለሊቀ-ካህኑ፣ 16:5-10
     - (3) የአምልኮ ሥርዓት፣ 16:23-28
     - (4) ዓመታዊ የትዕዛዝ ሥርዓት፣ 16:29-34
2. ቅድስናና ከእግዚአብሔር ጋር ያለ ኅብረት መመለስ፣ ምዕ. 17-26
   - ሀ. የመሥዋዕቱ ደም፣ 17:1-16
   - ለ. የሃይማኖታዊና ሞራል ልኬቶች (ደረጃዎች)፣ 18:1-20:27
     - (1) በዘመዶች መካከል የሚደረግ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት
     - (2) የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ኃጢአቶች
     - (3) ቅጣቶች፣ ምዕራፍ 20
   - ሐ. የካህናት መቀደስ፣ 21:1-22:33
   - መ. ዓመታዊ የበዓል ቀናት መቀደስ፣ 23:1-24:23
     - (1) ሰንበት፣ 23:1-3
     - (2) ፋሲካ እና የቂጣ በዓል፣ 23:5-8
     - (3) በኵራት፣ 23:9-14
     - (4) መኸር፣ 23:15-24
     - (5) በዓለ ኀምሳ፣ 23:23-25
     - (6) የማስተስረያ ቀን፣ 23:26-32 (የጾም ቀን ብቻ)
     - (7) የማደሪያ ድንኳን (ዳሶች)፣ 23:33-43
   - ሠ. ልዩ ዓመታት፣ 25:1-55
     - (1) የምድር ሰንበት፣ ቁ. 2-7
     - (2) ኢዮቤልዩ፣ 8-55
       - (ሀ) ክብረ በዓል፣ ቁ. 8-12
       - (ለ) ተጽዕኖው፣ ቁ. 13-34
       - (ሐ) የእያንዳንዱ ኪዳን የሰዎች ጠቀሜታና ነጻነት፣ ቁ. 35-55
   - ረ. የኪዳን ባርኮቶችና ርግማኖች፣ 26:1-46

3. ዕዝል (ስዕለት)፣ 27:1-34
   ሀ. ሰዎች፣ ቁ. 1-8
   ለ. እንስሳት፣ ቁ. 9-13
   ሐ. መኖርያ፣ ቁ. 14-15
   መ. መሬት፣ ቁ. 16-25
   ሠ. በኵራት ቁ. 26-27
   ረ. የተለየ ነገር፣ ቁ. 28-39
   ሰ. መባ፣ ቁ. 30-34

VIII. ዋነኛ ሐቆች

ሀ. የሌዋውያን መጽሐፍ የሚመለከተው ሕጋዊ መሠረቶችን ነው፣ ለእስራኤል ሕዝብ፣ለሲቪልና ሃይማኖታዊ ሕይወት፣ እና የክህነት ሚና። እሱም በማደሪያው ድንኳን ስለመገልገል መመሪያ ይሰጣል፣ ዘጸ. 25-40 ላይ እንደተገለጸው።

ለ. እሱም ኃጢአተኛ ሰው ቅዱስ የሆነውን አምላክ እንዴት እንደሚቀርብ ይገልጻል፣ ደግሞም ኅብረቱን እንዴት እንደሚያጠናክርና "ቅድስና" የመጽሐፉ ቁልፍ እንደሆነ (ዘኪ. 11:44 {ማቴ. 5:48})።

ሐ. የድንቆች ድንቅ፣ እግዚአብሔር የሚሻው ኃጢአተኛ ሰው ወደ እርሱ እንዲመጣ ነው፣ እሱም መንገድ ሰጥቶታል፣ መሥዋዕታዊ ሥርዓት።

መ. የእግዚአብሔር ባሕርይ የተገለጠው፡
1. መሥዋዕታዊ ሥርዓትን በመስጠቱ፣ ምዕራፍ 1-7 (ጸጋ)
2. በታሪካዊ ድርጊቶች፣ ምዕራፍ 8-10 (ፍትሕ)
3. የእርሱ ቀጣይነት ባለው መልኩ በሕዝቡ ዘንድ መገኘት (ታማኝነት)

IX. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት እና ሰዎች፣ በአጭሩ የሚገለጹ


ሀ. ቃላት እና ሐረጋት
1. ማስተስረያ፣ 1:4፤ 4:26 (NASB እና NIV)
2. መልካም መዓዛ፣ 1:9፣13፣ (NIV፣ የሚያስደስት መዓዛ)
3. ባለማወቅ፣ 4:1፣22፣27፤ 5:15-18፤ 22:14 (NASB እና NIV)
4. የጉዳት ካሣ፣ 6:5 (NASB እና NIV)
5. የመወዝወዝ መሥዋዕት፣ 7:30 (NIV፣ መወዝወዝ)
6. ቅዱስ (*kadosh*)፣ 11:44 (NASB እና NIV)
7. ለምጽ፣ 13:1፣ (NIV፣ የቆሰለ የቆዳ በሽታ)
8. የሚለቀቅ ፍየል፣ 16:8 (NASB እና NIV)
9. የአጋንንት ፍየል (የሚሠዋ)፣ 17:7፣ (NIV፣ የፍየል ጣዖታት)
10. መናፍስት ጠሪነት፣ 19:26 (NIV፣ አስማት)
11. ኢዩቤልዩ፣ 25:30 (NASB እና NIV)


ለ. በአጭሩ የሚገለጹ ግለሰቦች
1. ናዳብ እና አብዩድ፣ 10:1
2. አዛዜል፣ 16:8፣ 10 (NIV፣ ለሚለቀቀው ፍየል)
3. ሞሎክ፣ 18:21፤ 20:2

X. የካርታ ስፍራዎች (ማመላከቻዎች) - የለውም

XI. የተማሪ ይዘት ጥያቄዎች

1. መሥዋዕታዊው ሥርዓት ምንን ይወክላል? "ደሙ" በተደጋጋሚ የሚጠቀሰው ለምንድነው፣ (3:17፤ 7:26፤ 17:11)?
2. የእንስሳ መታረድ የሰውን ኃጢአት እንዴት ሊያስተሰርይ ይችላል?
3. ከአምስቱ የመሥዋዕት ዓይነቶች ሦስቱ ለምን የፍቃድ ሆኑ?
4. የአሮን ልጆች ለሞት የሚያበቃቸውን ምን ሠሩ?
5. ንጹሕ በሆኑና ንጹሕ ባልሆኑ እንስሳት መካከል ልዩነት ለምን ተደረገ?
6. ከሁሉም የእስራኤል በዓላት መካከል የማስተስረያ ቀን የተለየ የሚያደርገው ምንድነው?
7. በሰንበት ዓመት እና በኢዩቤልዩ ዓመት ጀርባ ያለው እውነት ምንድነው?


ANCIENT
NEAR EAST
N
S
E
W


PALESTINE
0 10 20 30 40
SCALE IN MILES

# አሪት ዘኍልቍ መግቢያ

I. የመጽሐፉ ስም

ሀ. በዕብራይስጥ (ኤምቲ) ርዕሱ "በምድረ-በዳ" ነው። ይህ የመጀመሪያው ቃል አይደለም፣ ነገር ግን በመጀመሪያው ዓረፍተ-ነገር ላይ ነው፣ አምስተኛ ቃል።

ለ. በLXX የተሰጠው ርዕስ "ዘኍልቍ" ነው፣ ቆጠራ ሁለት ጊዜ በመካሄዱ ምክንያት፣ ምዕራፍ 1-4 እና 26 ላይ።

II. ቅዱስ ቃልነቱ (ካኖናዊነት)

ሀ. እሱም የዕብራይስጥ ካኖን የመጀመሪያው ምድብ ክፋይ ነው፣ "ቶራ" ወይም "አስተምህሮቶች" ወይም "ሕግ" ተብሎ የሚጠራው።

ለ. ምድቡም ፔንታቲሁች (አምስቱ ጥቅሎች) በመባል ይታወቃል፣ በ LXX።

ሐ. እሱም አንዳንዴ "አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት" በሚል በእንግሊዝኛ ይጠራል።

መ. እሱም እሱም የሚያካትተው ቀጣይነት ያለውን ከዘፍጥረት — ዘዳግም በሙሴ የተመዘገበውን ነው፣ ከፍጥረት ጊዜ ጀምሮ በሙሴ ሕይወት።

III. ዘውግ

ይህ መጽሐፍ ከዘዳግም ጋር እጅግ ይመሳሰላል። እሱም የታሪካዊ ትርክትና ሕግጋት እንዲሁም የጥንታዊው የበለዓም ቅኔያዊ ንግር (ትንበያ)ድብልቅ ነው (ዘኍ. 23-24)።

IV. ደራሲው

ሀ. ይህ የቶራ የመጀመሪያው መጽሐፍ ነው፣ የጽሑፍ ምንጩን "የእግዚአብሔር የጦርነት መጽሐፍ፣" ተብሎ ለመሰየም 21፡14-15። ይህም በግልጽ የሚያሳየው ሙሴ ሌሎች የጽሑፍ ምንጮችን መጠቀሙን ነው።

ለ. ይህ መጽሐፍ፣ ሙሴ በምድረ-በዳ የመዞርን ሁነቶች ሊጽፍ እንደሚችልና እንደጻፈ ያስቀምጣል።

ሐ. ዘኍልቍ ደግሞ ምሳሌ የሚሆኑ፣ በርከት ያሉ ግልጽ የእርማት ተጨማሪዎችን ይዟል (ኢያሱ ወይም ሳሙኤል ይሆናሉ)፡

1. 12:1፤3 2. 13:22 3. 15:22-23 4. 21:14-15 5. 32:33ff 6. 32:33

መ. በብዙ ጉዳዮች ሙሴ በሦስተኛ መደብ ነው የተጠቀሰው፣ ከቀጥተኛ ጥቅሶች በቀር። ይህም የሚያሳየው ሙሴ የጸሐፊዎችን እገዛ መጠቀሙን ነው፣ እነዚህን ጽሑፎች ለማጠናቀር።

ሠ. መገንዘብ የሚያስፈልገው (የሚማርከው)፣ ዘኍልቍ ሁለት የእስራኤላዊ ያልሆኑ ውጤቶችን ማካተቱ ነው። (1) የአሞራውያንን የቀልድ ግጥም 21፡27-30 ላይ (ቁ. 30 የእስራኤላዊ ተጨማሪ ሊሆን ይችላል)፤ እና (2) በለዓም ከባላክ፣ የሞአብ ንጉሥ ጋር የደረገው ንግግር፣ 23-24 ላይ። እነርሱም የተጻፉ ወይም ቃላዊ ነገሮች በመጽሐፉ ማጠናቀር ላይ እንደተካተቱ ያሳያሉ (cf. *The Book of the Wars of the Lord*(*የእግዚአብሔር የጦርነት መጽሐፍ*)።

V. ጊዜው

ሀ. መጽሐፉ ራሱ ጊዜውን ይሰጠናል፡

1. 1፡1፤ 10፡10 ከዘጸአት በኋላ በ2ኛው ወር፣ በ2ኛው ዓመት ይላል። ከዚህ በኋላ የ38 ዓመት የመዞር ጊዜ አለ።
2. 9፡1 ከዘጸአት በኋላ በ1ኛው ወር፣ በ2ኛው ዓመት ይላል።

ለ. የዘጸአት ጊዜ ርግጠኝነት የለውም። አንድም 1445 ቅ.ል.ክ ወይም 1290 ቅ.ል.ክ ይሆናል።

VI. ታሪካዊ መቼቱን የሚያጠናክሩ ምንጮች

ሀ. ከዘኍልቍ መጽሐፍ ላይ አራት ዓይነት ነገሮች አሉ፣ በተለየ መልኩ የግብፅን ባህል የሚያንጸባርቁ፡

1. የዕብራውያን ሰፈር አሰፋፈር በየነገዶቹ መሆኑ (ዘኍ. 2:1-31፤ 10:11-33) እና የየነገዶቹ የሰልፍ (የጉዞ) ቅንብር (አደረጃጀት) (ዘኍ. 1፡7)። ይህም የራምሴስ II ትዕዛዝ በትክክል ይመስላል፣ በሶርያ ዘመቻው ላይ፣ ከአርማርና ጽሑፎች እንደሚታወቀው። እነዚህ የከነአናውያን ሰነዶች፣ ከ1300 ቅ.ል.ክ ጊዜ በከነዓን እና በግብፅ መካከል የነበረውን ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ሃይማኖታዊ መስተጋብሮችን ይገልጻሉ። ደግሞም ጠቃሚ የሚሆነውይህ የግብፃውያን አሰላለፍና አደረጃጀትመቀየሩን ነው፣ ከአሶር የአሰላለፍ የቅርጽ ለውጥ፣ እሱም በአንደኛው ሚሊኒየም ቅ.ል.ክ ከነበረው እንደምንረዳው። አሶራውያን አሰፋፈራቸው ክብ ነው።
2. የዘኍልቍ 10 የብር መለከቶች የግብፅን ምንጭነት ያንጸባርቃሉ። የጥንታዊ ቅርስ ምርምር (አርኪዎሎጂ) እነርሱን ለይቶ አግኝቷቸዋል፣ በቱታንክሃሜን ግዛት እንደተጠቀሰው፣ 1350 ቅ.ል.ክ አካባቢ ዕድሜ። ደግሞም እነዚህ የብር መለከቶች ለሃይማኖታዊና ለሲቪል ጉዳዮች ጥቅም ላይ መዋላቸው የተለመደ ነው፣ በአርማርና ጽሑፎች።
3. በፈረስ የሚጎተቱ ሠረገሎች ለግብፅ የተዋወቁት በ *Hyksos* ነው፣ ሴማዊ ገዥዎች፣ የ15ኛ እና 16ኛ ሥርወ-መንግሥት። በበሬ የሚጎተቱ ጋሪዎችም ለግብፅ ያልተለመዱ ናቸው። እነርሱ በሶርያ ዘመቻ ታይተዋል፣ በቱትሞስ III 1470 ቅ.ል.ክ። የከነዓን ሰዎች ተጎታች ጋሪ አያውቁም፣ ምናልባትም ከነዓን ገደላማና ኮረብታማ ስለሆነ ይሆናል። እነዚህ ጋሪዎች ያዕቆብን ለማምጣት ተልከዋል (ዘፍ. 45:19፣ 21፣ 27)። እነርሱም ደግሞ በዕብራውያን ጥቅም ላይ ውለዋል፣ ዘጸአት ላይ (ዘኍ. 7፡3፣ 6፣ 7)።
4. አንድ የመጨረሻ ግብፃዊ ነገር፣ እሱም በዕብራውያን የተኮረጀ፣ ሙሉ ለሙሉ የተላጩ ካህናት ናቸው (8፡7)።

ለ. ሁለቱ የሕዝብ ቆጠራዎች፣ እነርሱም ምዕራፍ 1-4 እና 26 ላይ የሚገኙት ትይዩ ናቸው፡

1. በማሪ ሰሌዳዎች ላይ፣ ከ1700ዎቹ ቅ.ል.ክ

2. ከጥንታዊ የግብፅ መንግሥት ዘመን የሆነ ሰነድ ላይ፣ 2900 – 2300 ቅ.ል.ክ

VII. ጽሑፋዊ ምድብ (ዐውደ ጽሑፍ)

ሀ. አጭር የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር፣ በመልክዓ ምድራዊ አቀማመጡ (መቼቱ) ላይ በመመሥረት፡
1. በሲና ተራራ ላይ የተደረገ ዝግጅት፣ ለተስፋይቱ ምድር ጉዞ፣ 1-10:10።
2. ወደ ተስፋይቱ ምድር ጉዞ፣ 10:11 - 21:35
ሀ. ወደ ቃዴስ፣ 10:11-12:16
ለ. በቃዴስ፣ 13:1-20:13
ሐ. ከቃዴስ፣ 20:14-21:35
3. ሁነቶች በሞአብ ሜዳ ላይ፣ 22:1-36:13

ለ. የተብራራ የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር
1. R.K. Harrison, *Introduction to the Old Testament*, pp. 614-615.
2. E. J. Young, *An Introduction to the Old Testament*, pp. 84-90.
3. NIV Study Bible, pp. 187-188.

ሐ. ዘኍልቍን ለመተንተን አንደኛው ችግር፣ ያልተለመደ የነገሮች አደረጃጀቱ ነው፤ ማለትም፣ የሕግና የትርክት መደበላለቅና፣ የተለያዩ ነገሮች መካተት። አንዳንድ ንድፈ-ሐሳቦች ስለ አወቃቀሩ፡
1. ይህ በግልጽ የሚያገለግለው ለ "ለዶክሜንተራዊ መላምት" ተንታኞች ነው፣ ጄ.ኢ.ዲ.ፒ. መጽሐፉን ለበርካታ ታሪካዊ ላልሆኑ፣ ሙሴአዊ ላልሆኑ ምንጮች ለመከፋፈል።
2. ጄ.ኤስ. ራይት (J.S. Wright) እንዳቀረበው ሐሳብ፣ የሙሴአዊ ነገሮች (ጽሑፎች) መጠናቀር በሕይወቱ ፍጻሜ ላይ ነው፣ ከጸሐፊዎች ጋር በመመካከር። የዘኍልቍ "በአንድ ጊዜ አንድ ነገር" (ደረጃ በደረጃ) ባሕርይ ተመዝግቧል፣ ነገር ግን ከሙሴ የሕይወት ዘመን ወደ ሌላ ያመለክታል።
3. *Gordon J. Wenham (Tyndale Commentary on Numbers) ገጽ 14-18) ሦስትዮሽ ትይዩ ሐሳብ አቅርቧል፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ* ነገሮችን ከዘጸአት፣ ከሌዋውያን እና ከዘኍልቍ በመጠቀም፣ እናም እነርሱን ከሦስቱ ጉዞዎች ጋር በማዛመድ፡ (1) ከቀይ ባሕር ወደ ሲና፤ (2) ከሲና ወደ ቃዴስ፤ እና (3) ከቃዴስ ወደ ሞአብ። ይሄንን በማድረግም፣ ከሁለቱም ጋር ከሚዛመዱት ነገሮች፣ ማለትም "መጓዝ" እና "መቆም" ጋር በማያያዝ ሁነኛ ትይዩዎች ማስረጃ መሆን ችለዋል። እሱም በተጨማሪ ይሄንን ሦስትዮሽ ትይዩ ከዘፍ. 1-11፤ ዘፍ. 12-50 እና ዘዳ. ጋር አዛምዷቸዋል። ይህም እጅግ ተስፋ-ሰጪ ይመስላል። ይህ የሚያሳየን የጥንት የቅርብ ምስራቅ ደራስያን (ጸሐፍት) ጽሑፋዊ ቅርጻቸውን የሚቀጣጠሩበት ጽሑፋዊ አወቃቀሮች ወይም ፈርጆች እንደነበሯቸው ነው፣ ለእኛ ለምዕራባውያን ግን የተለመደ ያልሆነ።

VIII. ዋነኛ ሐቆች

ሀ. እሱ የታሪካዊ ትርክት ቀጣይ ነው፣ ዘፍጥረት ላይ የተጀመረ። ነገር ግን መታወስ የሚኖርበት፣ ይሄ "የምዕራባውያን ታሪክ" አለመሆኑ ነው፣ የቅርብ ምስራቅ ሥነ-መለኮታዊ ታሪክ እንጂ። ሁነቶች ተሟልተው በቅደም ተከተላቸው አልተመዘገቡም፣ ነገር ግን እግዚአብሔርን እና የእስራኤልን ባሕርይ ለመግለጽ ተመርጠዋል።

ለ. እሱም የእግዚአብሔርን ባሕርይ ያሳያል፡
1. መገኘቱ በደመና ይታያል፡
ሀ. ደመናው በመቅደሱ "በቅድስተ-ቅዱሳን" ላይ ያርፋል፣ 9፡15። እግዚአብሔር እሱንና ደንቡን (አገባቡን) ተቀብሎታል፣ እግዚአብሔርና ሰው እንደሚገናኙበት መንገድና ስፍራ!
ለ. ደመናው ሕዝቡን ይመራል፣ 9፡17-23። እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ነበር፣ ይመራቸውም ነበር፣ በእርሱ ፍጹም መገኘት።
ሐ. ደመናው የእግዚአብሔርን በአካል መገኘት ማሳያ ነው፣ ለሙሴ ራሱን የገለጠበት 11:17፣ 25፤ 16:42-43።
መ. ደመናው የእግዚአብሔር መገኘት ተምሳሌት ሆኗል፣ በፍርድ እንዲሁም በመገለጥ፣ 12:1-8፤ 14:10።
ሠ. ደመናው የእግዚአብሔር መገኘት የሚታይ ተምሳሌት ነው፣ ለእስራኤል ብቻ ሳይሆን ለአካባቢው ሕዝቦችም ጭምር፣ 14፡14፤ 23፡21።
ረ. በደመና ተምሳሌት የሆነው የእግዚአብሔር መገኘት፣ እሱም በዘጸአት እና በምድረ-በዳ መዞር ዘመን፣ እስራኤላውያን ወደ ተስፋይቱ ምድር ሲገቡ ተቋርጧል፣ ነገር ግን ያም ቢሆን እግዚአብሔር በተምሳሌትነት ከእነርሱ ጋር ነበር፣ በታቦቱ በኩል፣ 35፡34።
2. የእርሱ ጸጋ እና ምሕረት፡
ሀ. የእርሱ ቀጣይነት ያለው ከእነርሱ ጋር መገኘት፣ በማጉረምረማቸው መሀልና መሪዎቹን ባልተቀበሉበት ጊዜ፣ 11:1፤ 14:2፣27፣29፣ 36፤ 16:11፣42፤ 17:5፤ 20:2፤ 21:5።
ለ. እሱ በበረሀ ይሰጣቸው የነበረው፡
(1) ውኃ
(2) ምግብ
(ሀ) መና (በየቀኑ፣ ከሰንበት በቀር)
(ለ) ድርጭት (ሁለቴ)
(3) ልብስ፣ የማያረጅ
(4) ደመናው
(ሀ) መጠለያ
(ለ) ብርሃን
(ሐ) ምሪት (መሪ)

(መ) መገለጥ

ሐ. የሙሴን ምልጃ መስማቱ፡
(1) 11:2
(2) 12:13
(3) 14:13-20
(4) 16:20-24
(5) 21:7

3. የእርሱ ፍትሐዊነት (ቅድስና) በ፡
ሀ. የእስራኤል ቅጣት፣ ለ38 ዓመት በምድረ-በዳ በመዞር ዘመን (14)።
ለ. የሙሴ ቅጣት፣ ወደ ተስፋይቱ ምድር እንዳይገባ በመከልከል (20:1-13፤ 27:14፤ ዘዳ. 3:23-29)።
ሐ. የቆሬ ሞት፣ እንዲሁም የሮቤል አለቆች፣ (16፡1-40)።
መ. በሕዝቡ ላይ የሆነ መቅሠፍት፣ የሙሴና አሮንን መሪነት (አመራር) ባለመቀበላቸው፣ (16፡41-50)።
ሠ. በሰጢም በተፈጸመው ምዝርና እግዚአብሔር ፈረደ፣ በተሳላፊዎች ላይ በሆነው ሞት፣ በሌዋውያን እጅ፣ (25)።

ሐ. እስራኤል በሲና ተራራ በተደረገው የኪዳን ውል ሲስማማ፣ በያህዌም ሲታመን እና ጥብቅ የሆነ መታዘዝ ለቃሉ ሲያደርግ፣ ማዕከላዊው ጉዳይ ሆነ።

## IX. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት እና ሰዎች በአጭሩ የሚገለጹ

ሀ. ቃላት እና ሐረጋት (NASB)፡
1. የመገናኛው ድንኳን፣ 1፡1 (NASB እና NIV)
2. መዋጃ፣ 3:46 (NIV፣ መዋጀት)
3. ናዝራዊ፣ 6:2 (NASB እና NIV)
4. ባዕድ ስደተኞች፣ 9:14 (NIV፣ ባዕድ)
5. ደመና፣ 9:15 (NASB እና NIV)
6. "በመካከላቸው የነበሩ ምናምንቴዎች፣" 11:4 (NASB እና NIV)
7. "ልብሳቸውን ቀደዱ፣" 14:6 (NASB እና NIV)
8. የልብስ ዘርፍ፣ 15:38 (NASB እና NIV)
9. ሲኦል (*Sheol*)፣ 16:30 (NIV፣ መቃብር)
10. ቀይ ጊደር፣ 19:2 (NASB እና NIV)
11. ተናዳፊ እባቦች፣ 21:6 (NIV፣ መርዛም እባቦች)
12. የመማጠኛ ከተማ፣ 35:6 (NASB እና NIV)
13. ደም ተበቃይ፣ 35:19፣21 (NASB እና NIV)

ለ. በአጭሩ የሚገለጹ ሰዎች፡
1. ኵሻዊቷ ሴት፣ 12:1 (NIV፣ "ኩሻዊ/ኢትዮጵያዊ ሚስቱ)
2. ዔናቅ፣ 13:28፣33
3. ኢያቡሳውያን፣ 13:29
4. ቆሬ፣ 16:1 (NIV፣ "ቆራዝ")
5. በለዓም፣ 22:5
6. በአል፣ 22:41


## X. የካርታ ስፍራዎች (አመላካች) (በቁጥር)


1. የኤሽኮል ሸለቆ፣ 13:23 (ከኬብሮን በስተሰሜን)
2. የነገሥታት አውራ ጎዳና፣ 20:17
3. ፈስጋ ተራራ፣ 21፡20
4. አርኖን ወንዝ፣ 21፡24
5. ያቦቅ ወንዝ፣ 21፡24
6. አሦር፣ 24፡22
7. ሰጢም፣ 25፡1
8. ቺነሬዝ ባሕር፣ 34፡11 (NIV፣ "ኬኔሬት ባሕር")

## XI. ተማሪ ይዘት ጥያቄዎች

1. ሌዊ ከሌሎቹ ነገዶች ጋር ለምን አልተቆጠረም፣ 1፡49?
2. ሌዋውያን ከበኵር ጋር እንዴት ይዛመዳሉ፣ 3፡12-13?
3. የምንዝርናን (ዝሙት) ፈተናን ግለጽ፣ 5፡16
4. የናዝራዊነት ስእለት መስፈርትን ዘርዝር፣ 6፡1
5. ምዕራፍ 4፡3ን ከ8፡24 ጋር እንዴት ትገልጸዋለህ?
6. 12፡3ን ሙሴ ጽፎታልን?
7. እግዚአብሔር የ40 ዓመት የምድረ-በዳ መዞር ጊዜ እንዲሆን ለምን አደረገ?

8. “ባለማወቅ/ሆን ብሎ ሳይሆን” ምን ማለት ነው፣ ከኃጢአት እና ከመሥዋዕት ጋር በተያያዘ፣ ምዕራፍ 15 ላይ በሚገኘው ሁኔታ?
9. የሙሴ ኃጢአት ምንድር ነበር፣ ምዕራፍ 20 ላይ? የእሱስ ውጤት/መዘዝ ምንድነው?
10. የበለዓም አህያ በርግጥ ተናግራለችን? 22፡28። በለዓም በምን መልኩ ሐሳብ አቀረበ፣ ባላቅ እስራኤልን እንዲያሸንፍ?


ANCIENT
NEAR EAST
N
S
E
W


PALESTINE
0 10 20 30 40
SCALE IN MILES

# ኦሪት ዘዳግም መግቢያ

I. ጠቀሜታው

ሀ. እሱም ከአራቱ የብኪ መጻሕፍት፣ በአዲስ ኪዳን ተደጋግመው ከሚጠቀሱት አንደኛው ነው (ዘፍጥረት፣ ዘዳግም፣ መዝሙር፣ እና ኢሳይያስ)። ዘዳግም 83 ጊዜ ተጠቅሷል።

ለ. ይህ ኢየሱስ ይወደው የነበረ የብኪ መጽሐፍ ነው፡
1. እሱም በተደጋጋሚ ይጠቅሰው ነበር፣ በምድረ-በዳ በሰይጣን በተፈተነበት ጊዜ (ማቴ. 4፡1-16፤ ሉቃስ 4፡1-13)።
2. እሱም የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር ሊሆን ይችላል፣ ከተራራው ስብከት ጀርባ፣ ማቴ. 5-7።
3. ኢየሱስ ዘዳ. 6፡5ን እንደ ታላቁ ትዕዛዝ ጠቅሶታል፣ ማቴ. 22:34-40፤ ማር. 12:28-34፤ ሉቃ. 10:25-28።
4. ኢየሱስ ይሄንን የብኪ ክፍል እጅግ አብዝቶ የጠቀሰበት ምክንያት (ዘፍ. - ዘዳ.) በእሱ ጊዜ የነበሩት አይሁድ የቅዱስ ቃሉ (ካኖን) እጅግ ሥልጣናዊ ክፍል አድርገው ስለሚቆጥሩት ነው።

ሐ. ይህ ዋነኛው የቅዱስ ቃሉ ምሳሌያችን ነው፣ በእግዚአብሔር የተደረገው ቀዳሚው መገለጥ ዳግም የሚተረጎምበት፣ በአዲስ ሁኔታ ውስጥ። ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን መጠነኛ ልዩነት ያለው አስርቱ ትዕዛዛት በዘጸ. 20 እና /በትይዩ ዘዳ. 5 መካከል ያለው ነው። ዘጸአት 20 በምድረ-በዳ የመዞር ጊዜ ሲሆን ዘዳ. 5 ደግሞ ሕዝቡን ለከነዓን የተረጋጋ ሕይወት/ኑሮ በሚያዘጋጁበት ጊዜ ነበር።

መ. ዘዳግም በገዛ ራሱ መግለጫ፣ ተለጣጣቂነት/ተከታታይነት ያለው መልዕክት ነው፣ በሙሴ የሆነ፤ ለ፡
1. እግዚአብሔር ለእስራኤል ያደረገውን ሥራ ዳግም ማስታወስ (መቁጠር)፤
2. በሲና ተራራ የተሰጠውን ሕግ ዳግም አጽንዖት ለመስጠት፤
3. የእሱን አንድምታ በከነዓን ለሆነው የግብርና ሕይወት ዳግም መተርጎም፤
4. በተስፋይቱ ምድር ለሚሆን ለኪዳን ማደስ ክብረ-በዓል ዝግጅት ለማድረግ (ኢያሱ)፤
5. የሙሴን ሞት እና የሥልጣን ሽግግር ለኢያሱ መደረጉን ለመሰነድ/ለመመዝገብ፤

ሠ. ዘዳግም አሁንም ቢሆን በሥነ-መለኮት ሊቃውንት መካከል የመነጋገሪያ ማዕከል ነው፣ ጽሑፋዊ አመሠራረቱን በተመለከተ። ዘመናዊው አስተምህሮት በእሱ ንድፈ-ሐሳቦች ተከፋፍሏል፣ በፔንታቲሁቻዊ (አምስቱ የኦሪት መጻሕፍት) ቅንብሩ (ጽሑፉ)።

II. የመጽሐፉ ስም

ሀ. በዕብራይስጥ የፔንታቲሁች መጻሕፍት ርዕሶች ከቀዳሚዎቹ አስር ቃላት መካከል አንደኛው ነው፣ ዘወትርም የመጀመሪያው ቃላቸው፡
1. ዘፍጥረት፣ "በመጀመሪያ"
2. ዘጸአት፣ "ስሞችም እነዚህ ናቸው"
3. ሌዋውያን፣ "እሱም ጠራው"
4. ዘኍልቍ፣ "በምድረ-በዳ"
5. ዘዳግም፣ "ቃላት እነዚህ ናቸው"

ለ. ታልሙድ ላይ (ሚሽናህ ሀቶራህ 17፡18 ላይ) እሱ "ደጊሞ - ሕግ" በሚል ተጠርቷል።

ሐ. በግሪክ የብኪ ትርጉም፣ እሱም ሴፕትዋጂንት ተብሎ በሚጠራው (LXX)፣ በ250 ቅ.ል.ክ በተጻፈው፣ "ሁለተኛው ሕግ" በሚል ተጠርቷል፣ በ17፡18 የተሳሳተ ትርጓሜ ምክንያት።

መ. የእንግሊዝኛውን ርዕስ ከጀሮም የላቲን ቫልጌት ላይ እናገኛለን፣ እሱም "ሁለተኛው ሕግ" ብሎ የሚጠራው (ዲዩትሮ-ኖሚያን)።

III. ቅዱስ ቃልነቱ - ይህ የቶራ የመደምደሚያ መጽሐፍ ነው፣ እሱም የዕብራይስጡን ቅዱስ ቃል (ካኖን) የመጀመሪያዎቹን ሦስት ምድቦች የሚያስገኝ

ሀ. ሕግ ወይም ቶራ -- ዘፍጥረት-ዘዳግም

ለ. ነቢያት፡
1. ቀዳሚ ነቢያት -- ኢያሱ-ነገሥት (ከሩት በቀር)
2. ኋለኛ ነቢያት -- ኢሳይያስ-ሚልኪያስ (ከዳንኤልና ከሰቆቃወ-ኤርምያስ በቀር)

ሐ. ጽሑፎች፡
1. ሜገሎዝ (6 ጥቅሎች)፡
   ሀ. መኃልየ መኃልይ
   ለ. መጽሐፈ መክብብ
   ሐ. ሩት
   መ. ሰቆቃወ ኤርምያስ
   ሠ. መጽሐፈ አስቴር
2. ዳንኤል
3. የጥበብ ጽሑፎች
   ሀ. ኢዮብ
   ለ. መዝሙር

ሐ. ምሳሌ
4. I እና II ዜና መዋዕል

IV. ዘውግ

ሀ. ዘዳግም ተለጣጣቂነት ያለው መልዕክት ነው፣ በአጠቃላይ መግቢያና በሙሴ ሞት መዝጊያ መግለጫ፣ ማለትም ሙሴ ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምስራቅ  በኩል ያለውን አገር የሰጠበት፣ እስራኤል ወደ ተስፋይቱ ምድር ከማቋረጡ በፊት።

ለ. ይህ መጽሐፍ ደግሞ ጥንታዊውን የሙሴ ዝማሬ/መዝሙር ይዟል፣ ምዕራፍ 31:30-32:43

ሐ. ልክ እንደ ዘፍ. 49፣ ዘዳ. 33ም ትንቢት ነው።

መ. ይህ መጽሐፍ ደግሞ የሙሴን ሞት ጽሑፍ ይዟል፣ ምዕራፍ 34።

V. ደራሲው

ሀ. የአይሁድ ወግ/ልማድ፡
1. ጥንታዊው ወግ/ልማድ ፍጹም ስምምነት ያደረገው፣ ደራሲው ሙሴ መሆኑን ነው።
2. ይህም ተመልክቷል በ፡
ሀ. ታልሙድ - ባባ ባትራ 14ለ
ለ. ሚሽናህ
ሐ. የቤን ሲራ የጥበብ መጽሐፍ 24፡23 (185 ቅ.ል.ክ በፊት የተጻፈ)
መ. የአሌክሳንደርያ ፊሎ
ሠ. ፍላቪየስ ጆሴፈስ
3. ቅዱስ ቃሉ ራሱ፡
ሀ. መሳፍንት 3፡4 እና ኢያሱ 8፡31
ለ. “ሙሴ ተናገረ”፡
(1) ዘዳ. 1:1፣3
(2) ዘዳ. 5:1
(3) ዘዳ. 27:1
(4) ዘዳ. 29:2
(5) ዘዳ. 31:1፣ 30
(6) ዘዳ. 32:44
(7) ዘዳ. 33:1
ሐ. "እግዚአብሔር ሙሴን ተናገረው":
(1) ዘዳ. 5:4-5፣ 22
(2) ዘዳ. 6:1
(3) ዘዳ. 10:1
መ. "ሙሴ ጻፈ":
(1) ዘዳ. 31:9፣ 22፣ 24
(2) ዘጸዓት 17:14
(3) ዘጸአት 24:4፣ 12
(4) ዘጸአት 34:27-28
(5) ዘኍልቍ 33:2
ሠ. ኢየሱስ ከዘዳግም ጠቅሷል ወይም አመልክቷል፣ “ሙሴ አለ” / “ሙሴ ጻፈ” በሚል:
(1) ማቴዎስ 19:7-9፤ ማርቆስ 10:4-5 - ዘዳ. 24:1-4
(2) ማርቆስ 7:10 - ዘዳ. 5:16
(3) ሉቃስ 16:31፤ 24:27፣ 44፤ ዮሐንስ 5:46-47፤ 7:19፣ 23
ረ. ጳውሎስ የሙሴን ደራሲነት አስረግጧል:
(1) ሮሜ 10:19 - ዘዳ. 32:21
(2) I ቆሮ. 9:9 - ዘዳ. 25:4
(3) ገላ. 3:10 - ዘዳ. 27:26
(4) ሐዋ. 26:22፤ 28:23
ሰ. ጴጥሮስ በበዓለ ኀምሳ (ጰንጠቆስጤ) ስብከቱ የሙሴን ደራሲነት አስረግጧል - ሐዋ. 3:22
ሸ. የዕብራውያን ደራሲ የሙሴን ደራሲነት አስረግጧል - ዕብራውያን 10:28፤ ዘዳ. 17:2-6

ለ. ዘመናዊው አስተምህሮት
1. አብዛኞቹ የ18ኛ እና 19ኛ ክፍለ-ዘመን የሥነ-መለኮት ሊቃውንት፣ የግራፍ-ዌልሃሰንን የድርብ (ባለ ብዙ) ደራሲነት ንድፈ-ሐሳብን ተከትለው (ጄ.ኢ.ዴ.ፒ.) እንደሚያስረግጡት ዘዳግም የተጻፈው በካህን/ነቢይ ነው፣ ኢዮስያስ በይሁዳ ሲገዛ በነበረበት ጊዜ፣ የእርሱን መንፈሳዊ ተሐድሶ ለመደገፍ። ይህ ማለት የሚሆነው መጽሐፉ በሙሴ ስም የተጻፈው በ621 ቅ.ል.ክ. አካባቢ ነው።
2. በዚህ ላይ የተመሠረቱትም፡
ሀ. II ነገሥት 22፡8፤ II ዜና. 34፡14-15። “የሕጉን መጽሐፍ በእግዚአብሔር ቤት አገኘሁት።”
ለ. ምዕራፍ 12 የሚያብራራው የቤተ-መቅደሱን ክፊል ስፍራና ኋለኛውን መቅደስ ነው፤

ሐ. ምዕራፍ 17 የሚያብራራው ኋለኛውን ንጉሥ ነው፤
መ. እውነተኛ የሆነው፣ ባለፉት ጊዜያት በታዋቂ ሰው ስም መጽሐፍ መጻፍ፣ በጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ እና በአይሁድ ክበብ የተለመደ ነው።
ሠ. በአጻጻፍ ስልት፣ በቃላት እና በሰዋሰው በዘዳ. እና ኢያሱ፣ በነገሥት እና በኤርምያስ መካከል ተመሳሳይነት አለ።
ረ. ዘዳግም የሙሴን ሞት መዝግቧል፣ ምዕራፍ 34፤
ሰ. ግልጽ የሆነ ኋለኛ የአዘጋጆች ተጨማሪ ፔንታቲሁች ላይ አለ፡
   (1) ዘዳግም 3፡14
   (2) ዘዳግም 34፡6
ሸ. አልፎ አልፎ ሳይብራሩ የተቀመጡት ልዩ ልዩ የመለኮት ስም አጠቃቀሞች፡ ኤል፣ El Shaddai፣ ኤሎሂም፣ ያህዌ፣ ከገጽታ አኳያ አንድነት ያላቸው ዐውደ-ጽሑፎች እና ታሪካዊ ጊዜያት ናቸው።

VI. ጊዜው

ሀ. በሙሴ የተጻፈ ከሆነ ሁለት ዓይነት የይሁንታ አማራጮች አሁንም አሉ፣ ከግብፅ ዘጸአት ጊዜና ሂደት ጋር በተያያዘ፡
1. I ነገሥት 6፡1 በጥሬው የሚወሰድ ከሆነ፣ እንግዲያውስ በግምት 1445 ቅ.ል.ክ (18ኛ የቱትሞስ III እና አሜንሆቴፕ II ሥርወ-መንግሥት)፡
   ሀ. LXX 440 ዓመት አለው፣ በ480 ዓመት ምትክ።
   ለ. ይህም ቁጥር ትውልድን የሚያንጸባርቅ ይሆናል፣ ዓመትን ሳይሆን (በተምሳሌትነት)።
2. የጥንታዊ ቅርስ ምርምር (አርኪዎሎጂ) ማስረጃ፣ ለ1290 ቅ.ል.ክ.፣ ለዘጸአት (19ኛ የግብፅ ሥርወ-መንግሥት)፡
   ሀ. ሴቲ I (1390-1290) የግብፅን ዋና ከተማ ከቴብስ ወደ ባሕር ዳርቻ ክልል አዘዋውሮታል -ዞአን/ታኒስ።
   ለ. ራምሴስ II (1290-1224)፡
      (1) የእርሱ ስም የሚገኘው በዕብራውያን ባሮች በተገነባው ከተማ ላይ ነው፣ ዘፍ. 47፡11፤ Ex. 1፡11፤
      (2) እርሱ 47 ሴቶች ልጆች ነበሩት፤
      (3) እርሱም በትልቅየው ወንድ ልጁ አልተተካም።
   ሐ. ሁሉም ዋነኞቹ የፍልስጥኤም የተቀጠሩ (ባለ ግንብ) ከተሞች ተደምስሰዋል፣ እንደገናም በፍጥነት ተገንብተዋል፣ በግምት በ1250 ቅ.ል.ክ፤

ለ. የዘመናዊው አስተምህሮት ባለብዙ ደራስያን ንድፈ-ሐሳብ፡
1. ጄ (ያህዌ) 950 ቅ.ል.ክ.
2. ኢ (ኤሎሂም) 850 ቅ.ል.ክ.
3. ጄኢ (በጥምረት) 750 ቅ.ል.ክ.
4. ዲ (ዲትሮኖሚ/ዘዳግም) 621 ቅ.ል.ክ.
5. ፒ (ፕሪስትስ/ካህናት) 400 ቅ.ል.ክ.

VII. ታሪካዊ መቼቱን የሚያጠናክሩ ምንጮች

ሀ. የ2ኛው ሚሊኒየም ቅ.ል.ክ የኬጢያውያን ውሎች፣ ጥንታዊውን፣ ታሪካዊ አቻውን፣ ከዘዳግም መዋቅር ጋር ትይዩ የሆነውን ያቀርቡልናል (እንዲሁም ዘጸ. - ሌዋ. እና ኢያ. 24)። የዚህ ውል ፎርጅ (መልክ) በ1ኛው ሚሊኒየም ቅ.ል.ክ. ተቀይሯል። ይህም ለዘዳግም ታሪካዊነት ማስረጃ ይሰጠናል። በዚህ አካባቢ ለተጨማሪ ንባብ፣ G.E. Mendenhall's *Law and Covenants in Israel and the Ancient Near East* ተመልከት። .

ለ. የኬጢያውያን ፎርጅ እና የእሱ የዘዳ. ትይዩዎች፡
1. መግቢያ (ዘዳ. 1፡1-5፣ የተናጋሪው ማስተዋወቂያ፣ ያህዌ)
2. የንጉሡ ያለፉ ድርጊቶች ቅኝት (ዘዳ. 1፡6-4፡49 የእግዚአብሔር ያለፉ ድርጊቶች ለእስራኤል)
3. የውል ቃላት (ዘዳ. 5-26)፡
   ሀ. አጠቃላይ (ዘዳ. 5-11)
   ለ. ዝርዝር (የተለየ) (ዘዳ. 12-26)
4. የውሉ ውጤቶች (ዘዳ. 27-29):
   ሀ. ጠቀሜታዎች (ዘዳ. 28)
   ለ. ውጤቶች (መዘዞች) (ዘዳ. 27)
5. የመለኮት ምስክር (ዘዳ. 30፡19፤ 31፡19፣ ደግሞ 32፣ የሙሴ መዝሙር እንደ ምስክር ያገለግላል)፡
   ሀ. አንድ ቅጂ በመለኮት ቤተ-መቅደስ፤
   ለ. አንድ ቅጂ በዕቃ ውስጥ፣ በየዓመቱ እንዲነበብ፤
   ሐ. የኬጢያውያን ውሎች ከኋለኞቹ የአሦር እና የሶርያ ውሎች የሚለዩባቸው፡
      (1) የንጉሡ ያለፈ ድርጊት ታሪካዊ ቅኝት፤
      (2) የርግማኑ ክፍል አናሳ ገላጭነት።

VIII. ጽሑፋዊ ምድቦች (ዐውደ-ጽሑፍ)

ሀ. የመጽሐፉ መግቢያ፣ 1፡1-5

ለ. የመጀመሪያው ስብከት፣ 1፡6-4፡43 (ያለፉ የያህዌ ድርጊቶች፣ ለዛሬ):

ሐ. ሁለተኛው ስብከት፣ 4:44-26:19 (የእግዚአብሔር ሕግ ለዛሬ እና ለሁሉም ቀናት):
1. አጠቃላይ - አስርቱ ቃላት (5-11)
2. የተወሰኑ ምሳሌዎች እና አተገባበሮች (12-26)

መ. ሦስተኛ ስብከት፣ 27-30 (የእግዚአብሔር ሕግ ለወደፊቱ 27-29):
1. ርግማኖች (27)
2. በረከቶች (28)
3. የኪዳን መታደስ (29-30)

ሠ. የሙሴ የመጨረሻ ቃላት፣ 31-33:
1. "ደጎና ሁኑ" ስብከት፣ 31:1-29
2. የሙሴ መዝሙር፣ 31:30-32:52
3. የሙሴ ባርኮት 33:1-29

ረ. የሙሴ ሞት፣ 34

IX. ዋነኛ ሐቆች

ሀ. የመጨረሻው ዝግጅት፣ ወደ ተስፋይቱ ምድር ከመግባት በፊት። የእግዚአብሔር ኪዳን ለአብርሃም (ዘፍ. 12፡1-3) ምድር እና ዘር ተስፋ ሰጥቶታል። ብኪ ያተኮረው ምድር ላይ ነው።

ለ. ሙሴ ሕዝቡን አዘጋጀ፣ ለሁነኛ የግብርና ሕይወት (ኑሮ) ከዘላንነት (ከከብት አርቢነት) ሕይወት ይልቅ። እሱም የሲናን ኪዳን ለተስፋይቱ ምድር ተቀበለ።

ሐ. መጽሐፉ አጽንዖት የሚሰጠው የእግዚአብሔርን ታማኝነት ነው፣ ላለፈው፣ ለአሁኑ፣ እና ለሚመጣው። ሆኖም ኪዳኑ ሁኔታዊ ነው! እስራኤል በእምነት፣ በንስሐ እና በመታዘዝ ምላሽ መስጠትና መቀጠል ይኖርባታል። እሷ ይሄንን ካላደረገች የምዕራፍ 27-29 ርግማኖች ይፈጸማሉ።

X. ሰዎች፣ ቃላት እና/ወይም ሐረጎች በአጭሩ የሚገለጹ

ሀ. ቃላት እና ሐረጋት፡

1. "ሰማይ እና ምድርን ምስክርነት ጠርቻለሁ፣" 2፡26 (NASB እና NIV)
2. "የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ...፣" 5፡9 (NIV፣ በአባቶች ኃጢአት እስከ ሦስተኛ እና አራተኛ ትውልድ ድረስ ልጆችን የምቀጣ")
3. "...ነገር ግን እስከ ሺህ ... ድረስ ምሕረትን የማደርግ፣" 5፡10 (NIV፣ "ነገር ግን ፍቅሬን እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ የማሳይ")
4. "ስማ፣" (ሼማ) 6፡4 (NASB እና NIV)
5. "በግንባርህም ላይ እንደ ክታብ፣" (ክታብ) 6፡8 (NIV፣ "እንደሚደረግ ምልክት...")
6. "በደጅህም መቃኖች ላይ ጻፋቸው፣" (mezuza) 6፡9 (NIV፣ "የበር መቃኖች")
7. "ክልክላ ያለበት" herem፣ 13፡17 (NIV፣ "የተኮነኑ/የተወገዙ ነገሮች")
8. "የሰማይ ሠራዊት፣" 17፡3 (NIV፣ "የሰማይ ከዋክብት")
9. "በእሳት ማሳለፍ፣" 18፡10 (NIV፣ "መሥዋዕት")
10. መናፍስት ጠሪ/አስማተኛ፣ 18፡11 (NASB እና NIV)
11. የተዋጀ፣ 21፡8 (NASB እና NIV)
12. "ያልተወደደ፣" 21፡15 (NIV፣ "ለሌሎች ያልሆነ")
13. "በዛፍ/እንጨት ላይ የተሰቀለ፣" 21፡23 (NASB እና NIV)
14. "የውሻ ዋጋ፣" 23፡18 (NIV፣ "የወንድ ጋለሞታ... ዋጋ")
15. "የፍች ወረቀት፣" 24፡1 (NASB እና NIV)
16. "ራስህን ዘይት ተቀባ፣" 28፡40 (NIV፣ "ዘይት ተጠቀም")

ለ. በአጭሩ የሚገለጹ ሰዎች፡

1. ዔናቅ፣ 1:28 (NIV፣ "ዔናቃውያን")
2. ራፋይም፣ 3:11 (NIV፣ "ራፋይውያን")
3. ኬጢያውያን፣ 7:1
4. ሐውልት፣ 7:5 (NIV፣ "የማምለኪያ አጸድ")
5. ነቢዩ፣ 18:15-22
6. ይሽሩን፣ 32:15፤ 33:5፣ 26


XI. የካርታ ስፍራዎች/አመላካቾች (በቁጥር)


1. ኮሬብ ተራራ፣ 1:2፣6፣19፤ 4:10፣15
2. ሴይር፣ 1:2፣44፤ 2:1፣4፣5፣8፣12፣22 ( የተራራ ሰንሰለት)

3. ቃዴስ በርኔ፣ 1:46፤ 32:51 (NIV፣ “ቃዴስ”)
4. ባሳን፣ 1:4፤ 3:1፣3፣4፣10፣11፣13፤ 4:43፣47
5. ዔላት፣ 2:8 (ዔጽዮንጋብር)
6. ሔርሞን ተራራ፣ 3:8፣9፤ 4:48
7. ጌባል ተራራ፣ 11:29፤ 27:4፣13
8. ገሪዛን ተራራ፣ 11:29፤ 27:12
9. ሆር ተራራ፣ 32:50 (ጀበል ሀሩን)

## XII. የተማሪ ይዘት ጥያቄዎች

1. ዘዳግም ከዘጸአት እና ዘኍልቁ እንዴት ይለያል (ዘውግ)?
2. ሙሴ የዘጸአትን ታሪክ ለምን ደገመ?
3. ልጆቻችሁን ስለማስተማር በርካታ ማጣቀሻዎች የተደረጉት ስለምንድነው፣ (4:9፤ 6:7፣ 20-25፤ 11:19፤ 32:46)?
4. የዘዳግም 5 አስርቱ ትዕዛዛት (ዲካሎግ) ቅጂ/ጽሑፍ ከዘጸአት 20 እንዴት ይለያል?
5. እነርሱ ሐውልቶቻቸውን እንዲሰባብሩ እና የማምለኪያ አጸዶቻቸውን እንዲያፈርሱ/ እንዲቆርጡ ለምን ተነገራቸው (7፡5)?
6. 10፡12-21 ዘዳግምን (ባሕርይ) እንዴት ያሳያል?
7. ምዕራፍ 27-29፣ ሙሉውን ብሉይ ኪዳን ለመተርጎም እጅግ አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድነው?
8. የሙሴን ሞት ማን መዘገበው/ጻፈው (34)?


ANCIENT
NEAR EAST
N
S
E
W


PALESTINE
0 10 20 30 40
SCALE IN MILES

# የመጽሐፈ ኢያሱ መግቢያ

I. የመጽሐፉ ስም

ሀ. የመጽሐፉ ስም የመጣው ከሙሴ ተተኪና ከመጽሐፉ ዋነኛ ገጸ-ባሕርይ ነው።

ለ. የእርሱ ስም የመጣው ከሁለት የዕብራይስጥ ቃላት ነው፡
1. ያህዌ (ጄ አናባቢ ታክሎበት)
2. ደኅንነት/መድኃኒት (ሆሼ/ሴ)

ሐ. ይህም በትክክል ተመሳሳይ የዕብራይስጥ ስም ነው፣ እንደ ኢየሱስ (ማቴ. 1፡21)።

II. ቅዱስ ቃልነቱ (ካኖናይዜሽን)

ሀ. ኢያሱ የዕብራይስጥ ካኖን የመጀመሪያው መጽሐፍ ነው፣ "ነቢያት" ተብሎ የሚታወቀው ምድብ።

ለ. ይህም ምድብ በሁለት ክፍሎች ይከፈላል፡
1. ቀዳሚዎቹን ነቢያት፣ እነርሱም ኢያሱ-ነገሥት (ከሩት በቀር) የሚካተቱበት።
2. ኋለኞቹ ነቢያት፣ እነርሱም ኢሳይያስ-ሚልክያስ (ከዳንኤል እና ከሰቆቃወ ኤርምያስ በቀር) የሚካተቱበት።

III. ዘውግ

ሀ. እነዚህ ታሪካዊ መጻሕፍት የእግዚአብሔርን ሕዝብ ታሪክ የሚቀጥሉ ናቸው፣ ዘፍጥረት ላይ የተጀመረውን። እሱም የምዕራባዊ ቅደም ተከተላዊ ታሪክ አይደለም፣ የተመረጠ ሥነ-መለኮታዊ ታሪክ እንጂ ነው። ይህም ማለት፣ እሱ እውነተኛ ወይም ትክክለኛ አይደለም የሚል አንድምታ ለማስቀመጥ አይደለም፣ ነገር ግን ደራስያኑ የተወሰኑ ሁነቶችን መርጠዋል፣ ስለ እግዚአብሔር፣ ሰው፣ ኃጢአት፣ ድኅነት (ደኅንነት)፣ ወዘተ... ያሉትን ሥነ-መለኮታዊ እውነቶች ለማስተማር ማለት ነው እንጂ። በዚህ መልኩ እነርሱ ከአዲስ ኪዳኑ ወንጌላት እና ሐዋርያት ሥራ ጋር ይመሳሰላሉ።

ለ. ታሪክ ለአይሁድ በዑደት ተመልሶ የሚመጣ ዓይነት አይደለም፣ እንደ አካባቢው ጎረቤቶቻቸው፣ በተፈጥሮ ዑደት ላይ የተመሠረተ፣ ነገር ግን እሱ "ቴሊኦሎጂካል" (የክስተት ውጤት) ነው እንጂ። እሱ ግብ፣ ዓላማ አለው። እግዚአብሔር ወደ ቀድሞ የተወሰነው ግብ እየተንቀሳቀሰ ነው፣ ማለትም፣ የወደቀውን ዓለም መዋጀት (ዘፍ. 3፡15)።

IV. ደራሲው

ሀ. ወግ/ልማዳዊው ደራሲ ኢያሱ ነው፡
1. የእርሱ ስም በዋነኛነት/ከመነሻው አውሴ (መዳን/መድኃኒት) ነበር፣ ዘኍ. 13፡8።
2. ሙሴ ስሙን ወደ ኢያሱ ቀየረው (እግዚአብሔር መድኃኒቴ "ነው")፣ ዘኍ. 13፡16።
3. በአንዳንድ ያልታወቁ ምክንያቶች ስሙ በአራት የተለያዩ መንገዶች ይባላል፡
   ሀ. የሾሹአ (*yeshoshu'a*) ፣ (የተለመደ) ኢያ. 1፡1
   ለ. የሆሹአ (*yehoshu'a*) ፣ ዘዳ. 3፡21
   ሐ. ሆሼአ (*hoshe'a*)፣ ዘዳ. 32፡44
   መ. የሹአ (*yeshu'a*) ፣ ነህ. 8፡17

ለ. ባባ ባትራ 14ለ የሚለው ኢያሱ መጽሐፉን ጽፏል፣ ከሞቱ ጽሑፍ በቀር፣ እሱም በካህኑ አልአዛር የተመዘገበ፣ 24፡29-30 እና ልጁ ፊንሐስ (ዘኍ. 25፡7-13፤ 31፡6-8፤ኢያ.22፡10-34)፣መጽሐፉን አጠናቀቀ፣ ይኸውም የአልአዛር ሞት የተመዘገበበት፣ 24፡31-33።

ሐ. ኢያሱ ሰውየው፡
1. በግብፅ በባርነት ተወለደ
2. ከአስራ ሁለቱ ሰላዮች አንደኛው፤ እሱ እና ካሌብ ብቻ የእምነት ዜና አመጡ (ዘኍ. 14፡26-34)
3. የሙሴ ታማኝ ረዳት በዘጸአት ልምምድ (ተሞክሮ) ሁሉ። እሱ ብቸኛ ነው ወደ ሲና ተራራ ከሙሴ ጋር የወጣ (ግማሽ መንገድ - ዘጸ. 24፡13-14)።
4. የእስራኤል ሠራዊት አዛዥ (ጀነራል) (ዘጸ. 17፡8-13)
5. የከነዓንን ድል መርቷል፣ እንደ ሙሴ ተተኪ (ዘዳ.31፡23)

መ. አንዳንድ ማስረጃዎች፣ ስለ ኢያሱ ደራሲነት፡
1. መጽሐፉ የሚያስቀምጠው ኢያሱ፣ እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር የገባውን ኪዳን መመዝገቡን ነው፣ 24፡26፣ ስለዚህ እሱ ሊጽፍ እንደሚችል እናውቃለን።
2. እሱ በግልጽ የዓይን ምስክር ነው፡
   ሀ. "እኛ፣" 5፡1 (ኤምኤስኤስ ለየት ይላል)
   ለ. "ኢያሱ ገረዛቸው፣" 5፡7-8
   ሐ. የኢያሱ የግሉ ግጥሚያ፣ ከእግዚአብሔር መላእክት ጋር፣ 5፡13-15
   መ. "እሷ (ረዓብ) በእስራኤል መካከል እስከ አሁን ድረስ ተቀምጣለች፣" 6፡25 (ይህ ኋለኛ አዘጋጅ አይደለም፣ ነገር ግን የዘመኑ የዓይን ምስክር ነው)
3. እሱ አንዳንድ የጽሑፍ ምንጮችን ተጠቅሟል፡

ሀ. የያሻር መጽሐፍ፣ 10፡13 (II ሳሙ.1፡8)
ለ. "በመጽሐፉ፣" 18፡9
4. የጥንት ከተሞች ስሞች ትክክለኛ ዝርዝር የሚጥመው የዘመኑን ደራሲ ነው እንጂ ኋለኛውን አዘጋጅ(ጆች) አይደለም፡
ሀ. ኢየሩሳሌም፣ ኢያቡስ ይባል ነበር፣ 15፡8፤ 18፡16፣ 28
ለ. ኬብሮን፣ ቂርያትአርባቅ ይባል ነበር፣ 14፡15፤ 15፡13፣54፤ 20፡7፤ 21፡11
ሐ. ቂርያትይዓሪም፣ በኣላ ይባል ነበር - 15፡9፣ 10
መ. ሲዶን እንደ ዋነኛ የፍንቄያውያን ከተማ ይጠቀስ ነበር፣ ጢሮስ ሳይሆን፣ 11፡8፤ 19፡28፣እሱም ኋላ ላይ ዋና ከተማ የሆነ።
5. ኢያሱ፣ እንደ ፔንታቲዩች (የአራት መጻሕፍት) አንዳንድ የአዘጋጆች ተጨማሪ አለበት፡
ሀ. የኢያሱ ሞት
ለ. ኋለኛው የኬብሮን ድል፣ 14፡6-15፤ 15፡13-14
ሐ. ኋለኛው የዳቤር ድል፣ 15፡15፣49
መ. የዳን ወደ ሰሜን መውጣት/መሄድ፣ 19፡47
ሠ. "እስከ ዛሬ ድረስ" የሚለው ሐረግብዙ ጊዜ ይከሰታል፣ እሱም ኋለኛ ጽሑፍ መሆኑን ያመለክታል፣ 4፡9፤ 5፡9፤ (6፡25)፤7፡26 (ሁለቴ)፤ 8፡28-29፤ 9፡27፤ 10፡27፤ 13፡13፤ 14፡14፤ 15፡63፤ 16፡10፤ 22፡3

ሠ. ዘመናዊው አስተምህሮት፡
1. በፔንታቲዩች እና በኢያሱ መካከል ያለውን ተመሳሳይነት መመልከት፡
ሀ. ስልት (የአጻጻፍ)
ለ. ቃላት
2. የጄ፣ኢ፣ዲ፣ፒ ዶክሜንተሪ መላምት መጽሐፉን የሚመለከተው በረጅም ጊዜና ሰዓት በብዙ እጆች እንደተጻፈ ነው፡
ሀ. የጄ/J ምንጭ ከምዕራፍ 1-12 ከፊሉን ጻፈ፣ እሱም በተለያዩ/ተናጠላዊ ጦርነቶች ላይ የሚያተኩር (950-850 ቅ.ል.ክ)
ለ. የኢ/E ምንጭ ከምዕራፍ 1-12 ከፊሉን ጻፈ፣ እሱም በኅብረት በተደረጉ ጦርነቶች ላይ የሚያተኩር (750 ቅ.ል.ክ.)።
ሐ. የጄ እና ኢ/J እና E ድብልቅ የተከሰተው በ650 ቅ.ል.ክ. አካባቢ ነው፣ ይኸውም አብዛኛው ጄ ያልተካተተበት
መ. መጽሐፉ ድጋሚ ታርሟል፣ በኢዮስያስ ጊዜ በነበረ ካህን/ነቢይ፣ እሱም ዘዳግምን የጻፈ። ይህ ግለሰብ ወይም ቡድን ዱቶሮሚስት (ዘዳግማዊ) ምንጭ ተብሎ ይጠራል። ይህ ምንጭ ደግሞ ዘዳግምን ጽፏል፣ የኢዮስያስን ተሐድሶ ለማጠናከር፣ በ621 ቅ.ል.ክ፣ ኢየሩሳሌም ብቸኛው እውነተኛው ቅዱስ ስፍራ/ቤተ-መቅደስ መሆኑ ላይ በማተኮር።
ሠ. የፒ/P ምንጭ የካህናት ስብስብ ሲሆን እሱም ምዕራፍ 13-21 የጻፈ ነው፣ በ400 ቅ.ል.ክ. ጊዜ።
ረ. ከዚያም፣ የሚታከል ድጋፍ ያላቸው ተጨማሪዎች በ3ኛ ክፍለ-ዘመን ቅ.ል.ክ. ላይ ተደርገዋል።
3. የንድፈ-ሐሳቡን ቅድመ-ግምት ይገንዘቡ! እሱም እንዴት አድርጎ ጽሑፉን ከታሪካዊ መቼቱ እና ከደራሲው እንደቆረጠው ተገንዘቡ! እሱ ዘመናዊ ሙከራ ነው፣ የጥንት ጽሑፎችን በአዲስ ጽሑፋዊ ንድፈ-ሐሳቦች አኳያ ለመተንተን የሚሻ። የሆነ ሆኖ፣ መቀመጥ የሚኖርበት፡
ሀ. የመጽሐፈ ኢያሱ ደራሲ በውል አልተቀመጠም።
ለ. የኢያሱ ሞት፣ እንደ ሙሴ ሞት፣ በመጽሐፉ ላይ ተመዝግቧል።
ሐ. በብኪ መጻሕፍት ላይ የሚደረጉ አንዳንድ እርማቶች እንደቀጠሉ መሆናቸው።
መ. የብኪን ተመስጧዊነት፣ እሱም እንዲገኝ የተደረገውን ሂደቱንና አሠራሩን እንቀበላለን።
ሠ. በሄክሳቲዩች (ዘፍ. - ኢያ.) ላይ የሚነሡ ተቃርኗዊ ማስረጃዎች፡
(1) በአይሁድ ወግ/ልማድ ግልጽ የሆነ ልዩነት በአምስቱ የሙሴ መጻሕፍት (ፔንታቲዩች) እና በኢያሱ መካከል አለ፣ ይኸውም "የነቢያት" ክፍል ብሎ የሚጀምር፣ የዕብራይስጥ ካኖን፡
(ሀ) ቤን ሲራ (Ben Sira) Ecclesiasticus(*የጥበብ መጽሐፍ* ) ደራሲ፣ በ185 ቅ.ል.ክ. የተጻፈ፣ ልዩነትን ያደርጋል፣ 48፡22-45፡12።
(ለ) ፋልቪየስ ጆሴፈስ በመጽሐፉ *ኮንትራ አፒኦነስ* (*Contra Apioness)* ላይ 1፡17 ልዩነት አድርጓል።
(ሐ) የፔንታቲዩች ማሶረቲክ ጽሑፍ (ኤምቲ) የጸሐፊው የመዝጊያ ማስታወሻ፣ ልዩነት አድርጓል።
(መ) በምኩራብ የሚደረገው ሳምንታዊው የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፣ *"ሃፕታሮዝ "* (*Haphtaroth*") ተብሎ የሚጠራው ልዩነት አድርጓል።
(ሠ) ሳምራውያን ፔንታቲዩችን እንደ ቅዱስ ቃል ይወስዱታል፣ ኢያሱን ሳይሆን።
(2) ውስጣዊ ማስረጃ (ዮንግ፣ ገጽ 158)፡
(ሀ) ኢያሱ ላይ የተለየ የተውላጠ ስም  አጠቃቀም አለ፣ እሱም ፔንታቲዩች ላይ የሌለ።
(ለ) የኢያሪኮ ከተማ የፊደል አጻጻፍ ይለያል።
(ሐ) የመለኮት መጠሪያ፣ "የእስራኤል አምላክ፣" ኢያሱ ላይ 14 ጊዜ ሲከሰት፣ ፔንታቲዩች ላይ ግን ፈጽሞ የለም።
ረ. መቀበል የሚኖርብን ስለእነዚህ የብኪ መጻሕፍት አቀነባበር/አጻጻፍ ብዙ የማናውቀው ነገር መኖሩን ነው፣ አሁን ባሉበት ሁኔታ።

V. ጊዜው

ሀ. ይህ መጽሐፍ የሚገልጸው የተስፋይቱን ምድር ድል ነው። የዘጸአትን እና በምድረ-በዳ የመዞርን ጊዜ ርግጠኞች እንዳልሆንን ሁሉ፣ እንዲሁ የድል ማድረግን ጊዜ ርግጠኞች አይደለንም፡
1. 1445 - 40 — 1400ቅ.ል.ክ. አካባቢ (1 ነገ. 6፡1)
2. 1290 - 40 —1250ቅ.ል.ክ. አካባቢ (አርኪዖሎጂ)

ለ. ኢያሱ የተጻፈው ወይም የተዘጋጀው በመሳፍንት ጊዜ ነው፤ አንዳንድ ከተሞች ስማቸው ተቀይሯል፣ ከእስራኤል ድል በኋላ። አንድ ምሳሌ የከነአናውያን ከተማ ጽፋት ነው፣ እሱም ኋላ ላይ ሔርማ ወደሚል ተቀየረ፣ መሳፍንት 1፡16-17። ሆኖም፣ ኋለኛው ስም ወደ ኢያሱ ወደ ኋላ ተመልሶ ይነበባል፣ 12፡14፤ 15፡30፤ 19፡4።

ሐ. አር.ኬ. ሃሪሰን (R. K. Harrison) እንደገመተው፣ እሱ የተጻፈው በዳዊት የአገዛዝ ጊዜ በሳሙኤል ነው፣ ሳሙኤል ከሴሎ የወግ/ልማድ ምንጭ ሊሆን ይችላል Introduction to the Old Testament, p. 673፡፡

VI. ታሪካዊ መቼቱን የሚያስረግጡ ምንጮች

ሀ. አርኪዎሎጂ እንደሚያሳየው አብዛኞቹ ባለ ትልልቅ ቅጥር (ግንብ) የከነዓን ከተሞች ተደምስሰው በፍጥነት ድጋሚ ተገንብተዋል፣ በ1250 ቅ.ል.ክ አካባቢ፡
1. ሃዞር
2. ላቺሽ
3. ቤቴል
4. ዳቤር (ቀደም ሲል ቂርያትሤፍር ወይም ኪራዝሴፍር ተብሎ ይጠራ የነበር፣ 15፡15)

ለ. አርኪዎሎጂ የኢያሪኮን ውድቀት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጽሑፍ/ቃል ማረጋገጥ ወይም መተው/ አለመቀበል አልቻለም። ይህም የሆነው ስፍራው በጉስቁልና (በማያመች) ሁኔታ ላይ በመሆኑ ነው፡
1. የአየር ጠባዩ/ስፍራው
2. ኋላ ላይ የተካሄዱት ዳግም ግንባታዎች፣ በአሮጌ ስፍራዎች ያረጁ ነገሮችን በመጠቀማቸው
3. የንብርብሮቹን (የግንቡን) ዕድሜ በርግጠኝነት አለማወቅ

ሐ. አርኪዎሎጂ በጌባል ተራራ ላይ መሠዊያ አግኝቷል፣ እሱም ምናልባት ከኢያሱ 8፡30 -31 ጋር ይያያዝ ይሆናል (ዘዳ. 27፡2-9)። እሱም Mishnah (ታልሙድ) ላይ ካለው ገለጻ ጋር እጅግ ተመሳሳይ ነው።

መ. የራስ ሻምራ ጽሑፎች፣ በዑጋሪት የተገኙት የከነአንን ሕይወትና ሃይማኖት ያሳያሉ፣ የ1400ዎቹን ቅ.ል.ክ.፡
1. ባለብዙ አማልክት ተፈጥሯዊ አምልኮ (የመራባት አምልኮ)
2. ኤል ዋነኛው መለኮት ነበር
3. የኤል የትዳር ጓደኛ አሼራህ ነበረች (ኋላ ላይ እሷ የበአል ጓደኛ ሆነች)
4. ልጃቸው በአል ነበር (ሃዳድ)፣ የማዕበል አምላክ
5. በአል "ከፍተኛ አምላክ" ሆነ፣ የከነአናውያን አማልክት ሁሉ። አናት የእርሱ ጓደኛ ነች።
6. ክብረ-በዓላዊ ተመሳስሎ ከግብፆቹ አይሲስ እና ኦሲሪስ ጋር አለው
7. የበአል አምልኮ የሚያተኩረው በአጥቢያዊ "ከፍተኛ ቦታዎች" ወይም በድንጋይ ንጣፋማ ሜዳዎች ላይ ነበር (ለአምልኳዊ ግልሙትና/ዝሙት)።
8. በአል ተምሳሌት የሚያደርገው በቆመ የድንጋይ ዓምድ ሲሆን (የወንድ ብልት ተምሳሌት)፣ አሽራህ ወይምአስታርቴ ተምሳሌት የሚያደርገው የተቀረጸ የእንጨት ዘንግ፣ ወይም በቁሙ ያለ ዛፍ ነው፣ እሱም "የሕይወት ዛፍን" ተምሳሌት ያደረገ።

ሠ. አርኪዎሎጂ እንደሚያስረግጠው የአካባቢው ዋነኛ መንግሥታት (ኬጢያውያን፣ ግብፃውያን እና ሜሶፖታማውያን) በፍልስጥኤም ላይ ተጽዕኗቸውን ማሳረፍ አልቻሉም፣ ኋለኛው የነሐስ ዘመን ተብሎ በሚታወቀው በዚህ ጊዜ (1550 – 1200 ቅ.ል.ክ.)።

ረ. የጥንታውያን ከተሞች ትክክለኛ የስም ዝርዝር የሚገጥመው ከዘመነኛ (ከዛን ጊዜ) ደራሲ ጋር ነው ከኋለኞቹ አዘጋጅ(ጆች) ጋር ሳይሆን፡
1. ኢየሩሳሌም፣ ኢያቡስ ትባል ነበር፣ 15፡8፤ 18፡16፣28 (15፡28 ኢያቡሳውያን አሁንም በኢየሩሳሌም ክፍል ውስጥ ይገኛሉ ይላል)
2. ኬብሮን፣ ቂርያትአርባቅ ይባል ነበር፣ 14፡15፤ 15፡13፣54፤ 20፡7፤ 21፡11
3. ቂርያትይአሪም፣ በአላ ይባል ነበር፣ 15፡9፣10
4. ዳቤር፣ ቂርያትሰና ይባል ነበር፣ 15፡49
5. ሲዶን እንደ ዋነኛ የፍንቄአውያን ከተማ ይጠቀሳል፣ ጢሮስ ሳይሆን፣ 11፡8፤ 13፡6፤ 19፡28፣ እሱም ኋላ ላይ ዋና ከተማ የሆነ።

ሠ. ኢያሱ 24 በትክክል ከኬጢያውያን ውል ፈርጅ ጋር ይገጥማል (እንደ ዘዳግም) የሁለተኛው ሚሊኒየም ቅ.ል.ክ.

VII. ጽሑፋዊ ምድቦች (ዐውደ-ጽሑፍ)

ሀ. መልከዓ ምድራዊ እንቅስቃሴዎች ለመጽሐፉ የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር ያበጃሉ፡
1. በሞአብ ሜዳ ላይ ይጀምራል፣ 1-2
2. የዮርዳኖስን ወንዝ ማቋረጥ፣ ወደ ጌልጌላ፣ ከኢያሪኮ አጠገብ፣ 3-4
3. የማዕከላዊ ከነአን ወታደራዊ ዘመቻ፣ 5፡1-10፡15
4. የደቡብ ከነአን ወታደራዊ ዘመቻ፣ 10፡16-43
5. የሰሜን ከነአን ወታደራዊ ዘመቻ፣ 11፡1-23
6. መልከዓ ምድራዊ የመሬት ክፍፍል፣ በነገዶች መካከል፣ 12-21

ለ. አጭር የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር፡
1. የከነአን ድል፣ 1-11
2. የተስፋይቱን ምድር ለየነገዶቹ ማከፋፈል፣ 12-21
3. የኢያሱ የመጨረሻ ቃላት እና ሞት፣ 22-24

VIII. ዋነኛ ሐቆች

ሀ. የእግዚአብሔርን ችሎታና ታማኝነት ለመግለጽ፣ ለአብርሃም በሰጠው ተስፋ (ዘፍ. 12፡1-3) ስለ ምድሩ (ዘፍ. 15፡16)።

ለ. እሱም ከዘፍጥረት የተጀመረውን ታሪክ ይቀጥላል፣ እናም ወደ አዲስ ጊዜ ያመጣዋል። በዚህ ጊዜ፣ ፍቃደኛ ነገዳዊ ማኅበራት፣ ማዕከላዊዎቹ የአንድነት ሁነኛ አካላት ነበሩ። ማዕከላዊ መንግሥት አልነበረም።

ሐ. የ "ቅዱስ ጦርነት" ጽንሰ-ሐሳብ (*herem* - "የተከለከለ") ለእኛ እጅግ ጨካኝ ይመስለናል፣ ነገር ግን እግዚአብሔር እስራኤላውያንን አስጠንቅቋቸዋል፣ ከከነአናውያን ኃጢአት እንዲጠበቁ። እግዚአብሔር እነርሱን ስለ ኃጢአታቸው ከምድሩ ላይ እንደነቀላቸው፣ እሱ ደግሞ አይሁድን ይነቅላቸዋል፣ ስለ ተመሳሳይ ኃጢአት (የአሦርና የባቢሎን ስደት)።

IX. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት እና ሰዎች በአጭሩ የሚገለጹ


ሀ. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት፡
1. *ማቋረጫ/መሻገሪያ* 2፡7 (NASB እና NIV)
2. የባልጩት *መቁረጫ*፣ 5፡2 (NASB እና NIV)
3. "ወተትና ማር የምታፈስሰው ምድር፣" 5፡6 (NASB እና NIV)
4. "ጫማህን ከእግርህ አውልቅ፣" 5፡15 (NIV፣ "ጫማህን ከእግርህ  አውልቅ")
5. "ቅዱስ" (*kadosh)፣* 5፡15
6. "እርም የሆነ፣" *(herem)፣* 6፡17 (NIV፣ "የተለየ")
7. "በገባኦን ፀሐይ ይቁም፣" 10፡12 (NASB እና NIV)
8. "እግሮቻችሁን በእነዚህ ነገሥታት አንገት ላይ አኑሩ፣" 10፡24 (NASB እና NIV)
9. (የሌዋውያን ከተሞች)፣ 21፡1-3 (NIV፣ "እንኖርባቸው ዘንድ ከተሞቹን እንድትሰጠን ሙሴ አዘዛል")
10. "የእግዚአብሔር ባርያ፣" 24፡29 (NASB እና NIV)


ለ. በአጭሩ የሚገለጹ ሰዎች፡
1. ረዓብ፣ 2፡1
2. "የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ፣" 5፡14 (NIV፣ "የእግዚአብሔር ሠራዊት አዛዥ፣"
3. አካን፣ 7፡1
4. ሰለጰአድ፣ 17፡3
5. ፊንሐስ፣ 22፡12

X. የካርታ ስፍራዎች (ጠቋሚዎች) (በቁጥር)

1. ታላቁ ባሕር፣ 1፡4
2. ሰጢም፣ 2፡1
3. አዳም፣ 3፡16
4. ጋይ፣ 7፡2
5. ገባዖን፣ 9፡3
6. ኔጌብ፣ 11፡16
7. ዓረባ፣ 11፡16
8. ሐሴቦን፣ 12፡5
9. የግብፅ ወንዝ፣ *(wadi al 'arish),*15፡4 (NIV፣ "የግብፅ ዋዲ")
10. የሔኖም ሸለቆ፣ 15፡8 (NIV፣ "የቤን ሔኖም ሸለቆ")
11. ሴኬም፣ 17፡7
12. መጊዶ፣ 17፡11
13. ሴሎ፣ 18፡1
14. ቤርሳቤህ፣ 19፡2

XI. የተማሪ ይዘት ጥያቄዎች በአጭሩ የሚመለሱ
1. እግዚአብሔር ኢያሱን እንዴት አበረታታው፣ ለሙሴ ያደርግ እንደነበረው (1፡1፤ 5፡13-15)?
2. እስራኤላውያን እንዴት አድርገው ዮርዳኖስን በእምነት እንደተሻገሩ አብራራ (3)።
3. መና ለምን ቀረ?
4. የእስራኤል ሠራዊት ለምን ጋይ ላይ ተሸነፈ?
5. ገባዖን እንዴት አድርው ኢያሱን አታለሉት?
6. ምዕራፍ 10 ተአምር ለመሆኑ ርግጠኝነት አለ? ለምን/ለምንስ አይደለም?
7. የሌዋውያን ከተሞችና የመማጸኛ ከተሞች ያላቸውን ግንኙነት አብራራ።
8. ምዕራፍ 22 ላይ የተፈጠረው ችግር ምንድነው?


ANCIENT
NEAR EAST
N
E
S
W


PALESTINE
0 10 20 30 40
SCALE IN MILES

# የመጽሐፈ መሳፍንት መግቢያ

I. የመጽሐፉ ርዕስ

ሀ. ርዕሱ የመጣው ከዕብራይስጥ ቃል "ሾፈቲም" ነው፣ ፍችውም "ግጭትን መፍታት" የሚል። ይህ የዕብራይስጥ ቃል ተመሳሳይነቱ፡
1. ከፍንቄአውያን ቃል ከ "ገዥ" ጋር
2. ከአካድያን ቃል ከ "አለቃ" ጋር
3. ከካርታጊኒአን ቃል ከ "ዋና ፈራጅ" ጋር

ለ. በLXX ላይ የተተረጎመው "*krital*" ወይም ፈራጆች በሚል ነው።

ሐ. የእንግሊዝኛ ርዕሳችን የመጣው ከቫልጌት "*judicum*" ነው።

መ. የእንግሊዝኛው ርዕስ አሳሳች ነው፣ ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች የሚሠሩት እንደ ፍርድ ዓይነት ሳይሆን እንደ ብርቱ ከባቢያዊ መሪዎች ነው፣ በእግዚአብሔር እንደተነሡ፣ በእርሱ መንፈስ ኃይል እንደተሞሉ (3:10፤ 6:34፤ 11:29፤ 14:6፣19፤ 15:14)፣ የተለየ ዓላማ ለማሳካት፣ ሕዝቡን ከባዕድ ጨቋኞች ለማዳን (ዝኪ. 2፡16)። የተሻለ ርዕስ ሊሆን የሚችለው "አዳኞች" ነበር።

II. ቅዱስ ቃልነቱ (ካኖናይዜሽን)

ሀ. ይህ የዕብራይስጥ ካኖን ሁለተኛው ምድብ ሁለተኛው መጽሐፍ ነው። እሱም ነቢያት ተብሎ ይጠራል።

ለ. ሁለተኛው ምድብ ሁለት ንዑሳን ምድቦች አሉት፡
1. ቀዳሚዎቹ ነቢያት፣ ታሪካዊ መጻሕፍት ብለን የምንጠራቸው፡ ኢያሱ - ነገሥት (ከሩት በቀር)
2. ኋለኞቹ ነቢያት፣ ነቢያት ብለን የምንጠራቸው፡ ኢሳ. - ሚል. (ከዳን. እና ከሰቆቃ. በቀር።)

III. ዘውግ - ይህ በቀዳሚነት ታሪካዊ ትርክት ነው

IV. ደራሲው

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ምንም አይልም

ለ. ባባ ባትራ 14ለ የሚለው፣ ሳሙኤል ስሙን የያዘውን መጽሐፍ ጽፏል፣ እና መሳፍንትን እና ሩትን

ሐ. መጽሐፉ የብዙ ዓመታትን ጊዜ ይሸፍናል፣ ስለዚህ፣ አንድ የዓይን ምስክር የሚሆን ደራሲ ሊኖር አይችልም

መ. መጽሐፉ ሊጠናቀር የሚችለው፡
1. በርከት ካሉ፣ ስማቸው ካልተጠቀሰ የጽሑፍ ምንጮች፣ ማለትም፡
ሀ. "የእግዚአብሔር የጦርነት መጽሐፍ" እሱም አንደኛው ታሪካዊ ምንጭ፣ ዘኍ. 21፡14 ላይ የተጠቀሰ
ለ. "የያሻር መጽሐፍ" እሱም ሌለኛው ታሪካዊ ምንጭ፣ ኢያሱ 10፡13 እና II. ሳሙኤል 1፡18 ላይ የተጠቀሰ
2. በርከት ያሉ ሥነ-ቃላዊ ምንጮች ሊሆኑ ይችላሉ። ርግጠኛ (እውነተኛ) ሥነ-ቃላዊ ታሪኮች በጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ የተለመዱ ናቸው፣ ጽሑፋዊ ነገሮች እጅግ ውድ በመሆናቸውና ለመያዝ ስለሚያስቸግሩ። አንድ ምሳሌ የሚሆነን፡
ሀ. "የነቢዩ ሳሙኤል ዜና መዋዕል፣... ነቢዩ ናታን፣ ... ነቢዩ ጋድ" 1 ዜና. 29፡29

ሠ. ዋነኛው አጠናቃሪ የጻፈው በፊተኛው የኅብረት ሥርወ-መንግሥት ጊዜ ይመስላል፡
1. ቤተልሔም አዘውትሮ መጠቀሱ የዳዊትን ጊዜ ለማንጸባረቅ ይመስላል (ዝኪ. 17:7፣8፣ 9፤ 19:1፣2፣18 [ሁለቴ])።
2. በርከት ያሉ ጽሑፎች ንጉሣዊውን ጊዜ ያንጸባርቃሉ፣ "በዚያም ጊዜ በእስራኤል ንጉሥ አልነበረም" በሚለው ሐረግ (ዝኪ. 17:6፤ 18:1፤ 19:1፤ 21:25)። በአካባቢው ሕዝቦች ዘንድ ነገሥታት ነበሩ፣ በእስራኤል ባይኖሩም።

ረ. ስለ ኋለኛ አዘጋጅ/አራሚ ማስረጃ አለ፡
1. 18፡30 የሚያንጸባርቀው፡
ሀ. የአሦራውያን ስደት፣ ሰሜናዊው አስር ነገዶች፣ በ722 ቅ.ል.ክ.
ለ. በዔሊ ጊዜ የታቦቱ በፍልስጥኤማውያን መማረክ ሊሆን ይችላል፣ 1 ሳሙ. 1-7።
2. የአይሁድ ወግ/ልማድ የሚያስረግጠው፣ ኤርምያስ እና/ወይም ጸሐፊው ዕዝራ ከፊሉን ብኪ. እንዳረሙት/እንዳዘጋጁት ነው። የብኪ. አዘገጃጀት፣ በአሁኑ መልኩ፣ ለእኛ ጠፍቶብናል። የሆነ ሆኖ፣ ይህ የብኪ. መጻሕፍት መለኮታዊ ተመስጧዊነት ላይ ተጽዕኖ አይኖረውም።

V. ጊዜው

ሀ. ምንም እንኳ፣ ምናልባት በዳዊት ያገዛዝ ዘመን በአጠናቃሪ የተጻፈ ሊሆን ቢችልም፣ ታሪካዊ ነገሩ ከዓይን ምስክር ምንጮች አይደለም የሚል አንድምታ የለውም። ለዚህ ሁለት የተሻሉ ምሳሌዎች አሉ፡
1. 1፡21 ላይ ኢያቡሳውያን እስከ አሁን ድረስ በኢያቡስ (ኋላ ላይ ኢየሩሳሌም) ውስጠኛውን ምሽግ መያዛቸው። ዳዊት ይሄንን ምሽግ ድል አላደረገም፣ እስከ II ሳሙ. 5፡6 ድረስ።
2. 3፡3 ላይ ሲዶን፣ ጢሮስ ሳትሆን፣ እንደ ፍንቄያውያን ዋና ከተማ ተመዝግባለች።

ለ. መጽሐፉ የሚሸፍነው ጊዜና ሰዓት፣ ወዲያውኑ ከኢያሱ ድል ማድረግ በኋላ፣ እስከ ሳሙኤል ልደት ነው። የመጀመሪያ ጊዜው በዘጸአት ጊዜ ላይ ይወሰናል (1445 ቅ.ል.ክ.ወይም 1290 ቅ.ል.ክ.)፣ 1350 ቅ.ል.ክ.ወይም 1200 ቅ.ል.ክ። የመጨረሻው ጊዜ 1020 ቅ.ል.ክ. አካባቢ ሊሆን ይችላል፣ ይኸውም የሳኦል አገዛዝ መጀመሪያ (ብራይት)።

ሐ. ለመሳፍንት የተሰጠው ጊዜ ሁሉ ቢደመር፣ ከ390 - 410 ዓመት ይመጣል። ይህ በታሪክ ቅደም ተከተልነት ሊወሰድ አይችልም፣ ምክንያቱም 1 ነገ. 6፡1 መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው በዘጸአት እና በሰሎሞን ቤተ-መቅደስ መሠራት መካከል 480 ዓመት መኖሩን ነው፣ 965 ቅ.ል.ክ.። ይህ ማለት መሳፍንት በመጀመሪያ የአጥቢያ (አካባቢያዊ) መሪዎች እንደሚሆኑ ነው፣ እናም የእነርሱ ጊዜ ይነባበራል ማለት ነው።

VI. ታሪካዊ መቼት

ሀ. የመሳፍንት የመጀመሪያዎቹ ምዕራፎች የሚያሳዩን የኢያሱ ድል ምን ያህል ውሱን መሆኑን ነው። ኢያሱ በመሠረቱ ዋነኞቹን የከነአንን የተቀጠሩ ከተሞች (ባለ ግንብ) እና ወታደራዊ አቅም ድል አድርጓል። እግዚአብሔር ስፍራዎቹን የመያዙን ከባድ ሥራ ለእያንዳንዱ ነገድ በየራሱ ስፍራ ትቶት ነበር፣ 2፡6። ይህ ዕቅድ (ስትራቴጂ) አዲሱን የእስራኤልን ትውልድ፣ እሱም የእግዚአብሔርን ተአምራት በዘጸአትና ድል በማድረግ ጊዜ ያላየውን ለመፈተን ነው፣ 2፡1-10፤ 3፡1።

ለ. አዲሱ ትውልድ ፈተናውን ወደቀ፣ 2፡11፤ 3፡7፣12፤ 4፡1፤ 6፡1፤ 10፡6፤ 13፡1። እግዚአብሔር ለኃጢአታቸው ምላሽ ሰጠ፣ የባዕዳን ጨቋኞችን በመላክ፣ ሕዝቡን ለመቅጣት። ሕዝቡ ንስሐ ገባና ለዕርዳታ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ። እግዚአብሔርም "አዳኝ" ላከላቸው። ከዚያም ለጥቂት ዓመታት ምድሪቱ ሰላም ሰፈነባት። ይህ በመሠረቱ መጽሐፈ መሳፍንት የሚገልጸው ፈርጅ (አካሄድ) ነው፣ 2፡6-16፡31። ("ኃጢአት፣ ኀዘን፣ ልመና (ጸሎት)፣ ደኅንነት።" )።

VII. ጽሑፋዊ ምድቦች

ሀ. የመሳፍንት ጊዜ ከሥነ-መለኮት አኳያ በሦስት የተለያዩ መንገዶች የሚገለጽ ይመስላል። እነዚህ ሦስት እይታዎች የመጽሐፉን የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር ያበጃሉ፡

1. የኢያሱ ድል ውጤቶች
2. የአዳኞች አስፈላጊነት
3. የክህደት (እምነትን የመተው) ምሳሌዎች

ለ. የመጽሐፉ አጭር የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር፡

1. የድሉ አጭር መግለጫ፣ 1፡1-2፡5
2. የእግዚአብሔር ሕዝብ ኃጢአት፣ ፍርድ እና መዳን፣ 2፡6-16፡31
3. የእግዚአብሔር ሕዝብ ኃጢአት ሦስት ምሳሌዎች፣ እነርሱም የጊዜውን የሞራል (ሥነ-ምግባር) ሁኔታ የሚያመላክቱ፡
   ሀ. የሚካ አመንዝራነት (ጣዖት አምላኪነት)፣ 17
   ለ. የዳን መውጣት (ለቅቆ መሄድ)፣ 18
   ሐ. የጊብዓ የዝሙት ኃጢአት፣ 19-21

ሐ. ዋነኞቹ ፈራጆችና ጠላቶቻቸው፡

| ስም | ጽሑፍ | ጠላት | የሰላም ጊዜ (1) ወይም የፍርድ ጊዜ (2) |
|---|---|---|---|
| 1. ጎቶንያል | 3፡7-11 | መሰጴጦምያ<br>(ኩሻዊው - ኵስርስቲም | 40 ዓመት (1) |
| 2. ናዖድ | 3፡12-30 | ሞአብ (ዔግሎም) | 80 ዓመት (1) |
| 3. ዲቦራ (ባርቅ) | 4፡1-24 (ዝርው)<br>5፡1-31 (ቅኔ) | ከነአናዊ<br>(ኢያቢስ እና ሲሣራ) | 40 ዓመት (1) |
| 4. ጌዴዎን | 6-8 | ምድያማውያን እና አማሌቃውያን | 40 ዓመት (1) |
| 5. ዮፍታሔ | 10፡17-12፡7 | አሞናውያን<br>(እና ኤፍሬም) | 6 ዓመት (2) |
| 6. ሳምሶን | 13 - 16 | ፍልስጥኤማውያን | 20 ዓመት (2) |

መ. መለስተኞቹ ፈራጆች፡

| ስም | ጽሑፍ | ጠላት | የፍርድ ጊዜ |
|---|---|---|---|
| 1. ሰሜጋር | 3:31 | ፍልስጥኤማውያን | ? |
| 2. ቶላ | 10:1-2 | ? | 23 ዓመት |
| 3. ኢያዕር | 10:3-5 | ? | 22 ዓመት |
| 4. ኢብጻን | 12:8-10 | ? | 7 ዓመት |
| 5. ኤሎም | 12:11-12 | ? | 10 ዓመት |
| 6. ዓብዶን | 12:13-15 | ? | 8 ዓመት |

ሠ. አቤሜሌክ፣ 9፡1-57፡

1. ይህ የጌዴዎን ልጅ ነው፣ ከዕቍባቱ
2. እሱ ተጽዕኖ ያሳደረው በአንዲት ከተማ ላይ ብቻ ነው፣ ሴኬም
3. እሱ ከሌሎቹ ፈራጆች ይለያል

VIII. ዋነኛ ሐቆች

ሀ. ይህ መጽሐፍ በግልጽ የሚያሳየው የውድቀትን ቀጣይ ውጤቶች ነው፡
1. እያንዳንዱ ተተኪ ትውልድ ኪዳኑን ጥሷል፣ እናም ከከነአናውያን የመራባት ጣዖታት ኋላ ሄዷል።
2. በተስፋይቱ ምድር እንኳ ቢሆን፣ የየነገዱ ይዞታ በእግዚአብሔር በተሰጠበት፣ የዳን ነገድ ወደ ሰሜን ጫፍ ይዞታ መያዝን መረጠ፣ በእግዚአብሔር ታምኖ ፍልስጥኤማውያንን ድል ከማድረግ ይልቅ።

ለ. እግዚአብሔር ጣዖት አምላኪ ሕዝቦችን ተጠቀመ፣ በራሱ ሕዝብ ላይ ለመፍረድ (ኋላ ላይ ሶርያ፣ አሦር እና ባቢሎን)። ይህም የዘዳ. 27-29ን የርግማን ክፍሎች ያንጸባርቃል።

ሐ. ይህ መጽሐፍ የጻድቅን ንጉሥ አስፈላጊነት ያሳያል፣ የተባበሩትን ነገዶች ለመምራት።

መ. ይህ መጽሐፍ የአይሁድ ሕዝብን ታሪክ ይቀጥላል፣ ዘፍጥረት ላይ የተጀመረውን።

IX. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት እና ሰዎች በአጭሩ የሚገለጹ


ሀ. ቃላት እና ሐረጋት፡
1. የእጃቸውና የእግራቸው አውራ-ጣት የተቆረጡ፣ 1፡7 (NASB እና NIV)
2. ቀንደ-መለከት ነፋ፣ 3፡27 (NIV፣ “መለከት”)
3. የበሬ መውጊያ፣ 3፡31 (NASB እና NIV)
4. ነቢይት፣ 4፡4 (NASB እና NIV)
5. መከር መሰብሰብ፣ 8፡2 (NASB እና NIV)
6. “የአድባር ዛፍ” (*terebinth*)፣ 9፡37 (NIV፣ “የባለ ንግርቱ ዛፍ”)
7. ሺቦሌት፣ 12፡6 (NASB እና NIV)
8. “ሰውም ሁሉ በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር” 17:6፤ 18:1፤ 19:1፤ 21:25 (NIV፣ እያንዳንዱ ተስማሚ የሚመስለውን ያደርግ ነበር”)
9. “የቤተሰብ ጣዖታት፣” *(teraphim)* ፣ 18፡17 (NIV፣ “የቤተሰብ አማልክት”)
10. “ወስላታ ሰዎች” *(belial)*፣ 19፡22 (NIV፣ “ክፉ ሰዎች”)


ለ. በአጭሩ የሚገለጹ ሰዎች፡
1. ሲሳራ፣ 4:2
2. ባርቅ፣ 4:6
3. ኢያኤል፣ 4:17
4. ይሩበአል፣ 6:32፤ 7:1(NIV፣ “ይሩ-በአል”)
5. አቤሜሌክ፣ 9:1
6. ካሞሽ፣ 11:24
7. ዳጎን፣ 16:23

X. የካርታ ስፍራዎችች (አመላካቾች) (በቁጥር)
1. የዘንባባ ከተማ፣ 1:16፤ 3:13
2. ዓራድ፣ 1:16
3. ቤቴል፣ 1:22
4. መጊዶ፣ 1:27
5. ጌዝር፣ 1:29
6. ዓኮ፣ 1:31
7. ሀዞር፣ 4:2
8. ራማ፣ 4:5
9. ታቦር ተራራ፣ 4:6
10. ቂሶን ወንዝ፣ 4:7
11. ኢይዝራኤል ሸለቆ፣ 6:33
12. ሴኬም፣ 9:1
13. ምጽጳ፣ 10:17
14. አርኖን ወንዝ፣ 11:13
15. ያቦቅ ወንዝ፣ 11:13
16. ተምና፣ 14:1
17. አስቀሎና፣ 14:19
18. ጋዛ፣ 16:1
19. ሴሎ፣ 18:31
20. ኢያቡስ፣ 19:10
21. ጊብዓ፣ 19:12

XI. የተማሪ ይዘት ጥያቄዎች

1. የኢያሱ 1-12 ድል ጽሑፍ ከመሳፍንት 1-2 እጅግ የተለየው ለምንድነው?
2. የእስራኤል ነገዶች ከነአናውያንን ሁሉ እንዲገድሉና ከእነርሱም ጋር ቃል ኪዳን እንዳይገቡ የተደረገው ለምንድነው?
3. አንዳንድ ፈራጆች ዋነኛ፣ እንዲሁም አንዳንድ መለስተኛ ተብለው ለምን ተጠሩ?
4. ምዕራፍ 4-5 ስለ እግዚአብሔር ምን ይላሉ፣ የሴት መሪዎችን በመጠቀሙ?
5. እግዚአብሔር ለምን ጌዴዎን ሠራዊቱን እንዲቀንስ ፈለገ፣ ምዕራፍ 7 ላይ?
6. ዮፍታሔ ሴት ልጁን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርጓልን (11:30-40)?
7. እግዚአብሔር እንደ ሶምሶን ዓይነቱን ስሜተኛ (ሴሰኛ) እንዴት ሊጠቀም ይችላል?
8. የዳን ነገድ ስፍራውን ጥሎ መሄዱ እጅግ ኃጢአት የሆነበት ለምንድነው?


ANCIENT
NEAR EAST
N
S
E
W


PALESTINE
0 10 20 30 40
SCALE IN MILES

# የመጽሐፈ ሩት መግቢያ

I. የመጽሐፉ ስም

መጽሐፉ የተሰየመው ከዋነኞቹ ገጸ-ባሕርያት በአንዷ ነው፣ ሩት፣ ሞአባዊቷ፣ የዳዊት እና የኢየሱስ የዘር ግንድ፣ ማቴ. 1፡5።

II. ቅዱስ ቃልነቱ (ካኖናይዜሽን)

ሀ. ይህ መጽሐፍ የዕብራይስጥ ካኖን፣ ሦስተኛ ምድብ እሱም "ጽሑፎች" ተብሎ የሚታወቀው ክፋይ ነው።

ለ. እሱም ደግሞ የአምስቱ አናሳ መጻሕፍት ልዩ ምድብ ክፋይ ነው፣ ሜጊሎዝ ወይም "አምስቱ ጥቅሎች" ተብሎ የሚጠራው። እነዚህ እያንዳንዳቸው አምስት አናሳ መጻሕፍት፡ ሩት፣ አስቴር፣ መክብብ፣ መኃልየ መኃልይ እና ሰቆቃወ ኤርምያስ በተለያዩ የበዓል ቀናት ይነበባሉ። ሩት በበዓለ ኀምሳ (ጰንጠቆስጤ) ወይም የሳምንታት በዓል ላይ ይነበባል።

ሐ. LXX ሩትን ከመሳፍንት ኋላ ያስቀምጠዋል። ጆሴፈስ *Contra Apion* 1፡8 የሚለው በብኪ 22 መጻሕፍት ብቻ ነበሩ። ይህ ማለት መሳፍንት እና ሩት እንደ አንድ መጽሐፍ ይቆጠሩ ነበር ማለት ነው። ስለሆነም፣ የእሱ በ "ጽሑፎች" ምድብ ውስጥ መካተቱ ኋላ ላይ ይሆናል (ጀሮም)።

III. ዘውግ

ሀ. ይህ መጽሐፍ በግልጽ ታሪካዊ ትርክት ነው፣ በምልልስ (ንግግር) መልኩ የቀረበ። መጽሐፉ የተበጀው በ85 ቁጥሮች (መስመር ጽሑፎች) ነው፤ ከዚህ ቁጥር ላይም 50ው ምልልስ ነው። ይህ ደራሲ አስደናቂ ተራች (ታሪክ ነጋሪ) ነው።

ለ. አንዳንድ ሊቃውንት የሚሰማቸው ይህ መጽሐፍ ድራማ እንደሆነ ነው፣ ታሪክ ሳይሆን፣ ምክንያቱም፡
1. የገጸ -ባሕርያቱ ስሞች ተምሳሌታዊ ፍቺ
   ሀ. መሐሎን = ሕመም
   ለ. ኬሌዎን = ማባከን
   ሐ. ዖርፋ = አንገተ-ግትር
   መ. ኑኃሚ = ጣፋጯ
2. በተለየ መንገድ የተገለጹበት፣ ሁሉም ገጸ-ባሕርያት እጅግ አስገራሚ ናቸው
3. በገጸ-ባሕርያቱ የተገለጠ ብርቱ ሃይማኖታዊ እምነት፣ በመሳፍንት ጊዜ፣ 1፡1

IV. ደራሲው

ሀ. እንደ ሌሎቹ በርካታ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ምንጩ አይታወቅም።

ለ. ባባ ባትራ 14ለ የሚለው ሳሙኤል የራሱን መጽሐፍ ጻፈ፣ እንዲሁም መሳፍንት እና ሩት። ሩት 4፡17፣22 አንድምታው፣ ዳዊት በደንብ የታወቀ እስከሆነ ድረስ ይህ የሚሆን አይመስልም፣ ነገር ግን ሊሆን የማይችልም አይደለም።

ሐ. ሩት 4፡7 የሚያመለክተው ኋለኛውን ደራሲ ወይም አዘጋጅ ነው፣ "ይህ በጥንት ጊዜ ልማድ ነበር" የሚለው ሐረግ።

V. ጊዜው

ሀ. የታሪኩ ሁነቶች የተከሰቱት በመሳፍንት (ፈራጆች) ጊዜ ነው፣ 1፡1 (1350 ወይም 1200 ቅ.ል.ክ.እስከ 1020 ቅ.ል.ክ.)። ይህም ምናልባት LXX መጽሐፉን ከመሳፍንት በኋላ ያስቀመጠበት ምክንያት ይሆናል።

ለ. እሱም የተከሰተው በሰላም ጊዜ መሆን ይኖርበታል፣ በእስራኤል እና በሞዓብ መካከል፡
1. ይህ ከመሳፍንት 3፡12-30 አኳያ አስገራሚ ነው
2. ሆኖም፣ በየጊዜያቱ ሰላም ይኖራል፣ 1 ሳሙ. 22፡3-4 (ማለትም፣ ሳኦል)።

ሐ. መጽሐፉ መቼ ነው የተጻፈው?፡
1. የጽሑፉ ጊዜ በዳዊት ያገዛዝ ዘመን መሆኑ ግልጽ ነው፣ 4፡17፣22። የጽሑፉ ታሪካዊነት የተረጋገጠበት ሐቅ በዳዊት የዘር ግንድ ያለችው ሞአባዊት ለእርሱ ክብር አይደለም! (ዘዳ. 23፡3)
2. የመጽሐፈ ሩት ስልት እና ቃላት ከሳሙኤል ጋር ይመሳሰላል፣ ከዜና መዋዕል ጋር ሳይሆን

VI. ታሪካዊ መቼቱን የሚያጠናክሩ ምንጮች - የዚህ መጽሐፍ ብቸኛው ገጽታ፣ እሱም በአርኪዎሎጂ ምርምር የተገኘው የጫማ ማስተላለፍ ሕጋዊ ምልክት ነው፣ የውርስ መብትን ለማስተላለፍ። ተመሳሳይ ልማድ በኑዚ ሰሌዳዎች ላይ ተገኝቷል። እነዚህ የአካድያን ኩኒፎርም ሰሌዳዎች ከሁለተኛው ሚሊኒየም ቅ.ል.ክ. ዘመን ናቸው፣ እሱንም አባታዊ ዘመን ብለን የምንጠራው።

VII. ጽሑፋዊ ምድቦች (ዐውደ-ጽሑፍ)

ሀ. የኑኃሚ ቤተ-ሰብ ከእስራኤል የእግዚአብሔርን ፍርድ ሸሽቶ ወደ ሞዓብ ምድር ሄደ፣ እዚያም ሁሉም ወንዶች የሞቱበት፣ 1፡1-5

ለ. ኑኃሚ ወደ ቤተ -ልሔም ተመለሰች፣ ከሞዓባዊት ምራቷ ጋር፣ 1፡6-22

ሐ. ሩት ቦዔዝን አገኘችው፣ በገብስ አጨዳ ላይ። እሱም ለእርስዋ መልካም ነበር፣ 2፡1-23

መ. ኑኃሚንና ሩት ቦዔዝን ለማግባባት አቀዱ፣ ተሳካላቸውም፣ 3፡1-18

ሠ. ቦዔዝ የኑኃሚንን ጥገኛ፣ ሩትን ለማግባት፣ የቅርብ ዘመድነት (ጎኢል) ተነሣሽነቱን ወሰደ፣ 4፡1-22

VIII. ዋነኛ ሐቆች

ሀ. የአማኝ አሕዛብ መልካም ገጸ-ባሕርይ፣ 1፡16-17፤

ለ. መልካም የሴት ገጸ-ባሕርይ፣ ሁለቱም አይሁድ እና አሕዛብ፤

ሐ. የንጉሥ ዳዊት እና የመሢሑ ንጉሥ የዘር ግንድ፣ የባዕድ ሴትን ማካተቱ፣ ማቴ. 1፡5፣ ሉቃ. 3፡32፣ እና የእግዚአብሔር ዕቅድ መሆኑ።

IX. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት እና ሰዎች በአጭሩ የሚገለጹ

ሀ. ቃላት እና ሐረጋት፡
1. ኤፍራታ፣ 1:2፤ 4:11 (NASB እና NIV)
2. ማራ፣ 1:20 (NASB እና NIV)
3. ሁሉን ቻይ (*El Shaddai*)፣ 1:20 (NASB እና NIV)
4. "ከክንፉም በታች መጠጊያ እንድታገኚ በመጣሽበት፣" 2:12 (NASB እና NIV)
5. ኢፍ፣ 2:17 (NASB እና NIV)
6. የቅርብ ዘመድ *(go'el)*፣ 2:20፤ 3:9፤ 4:14፣ (NIV፣ "የቅርብ ዘመድ")
7. (የውርስ ጋብቻ)፣ዘዳ. 25:5-10
8. "እግሩን ግለጪ፣" 3:4፣7-8፣14 (NASB እና NIV)
9. "ሰውየው ጫማውን እንዲያወልቅ ለባልንጀራውም እንዲሰጠው፣" 4:7 (NASB እና NIV)

ለ. በአጭሩ የሚገለጹ ሰዎች፡
1. አቤሜሌክ፣ 1፡2
2. እሴይ፣ 4፡22

X. የካርታ ስፍራዎች (አመላካቾች) (በቁጥር)

1. ሞዓብ፣ 1፡1
2. ቤተ-ልሔም፣ 1፡2


XI. የተማሪ ይዘት ጥያቄዎች


1. በዕብራውያን ካኖን የዚህ መጽሐፍ ዓላማ ምንድነው?

2. ይህ ቤተሰብ ከእስራኤል የሸሸው ለምንድነው?

3. *go'el* የሚለው ቃል ከውርስ ጋብቻ ልማድ ጋር እንዴት እንደሚዛመድ አብራራ።

4. ይህ መጽሐፍ ለዳዊት የሚያሳፍር የሆነው ለምንድነው?


ANCIENT
NEAR EAST
N
S
E
W


PALESTINE
0 10 20 30 40
SCALE IN MILES

# መግቢያ ለመጽሐፈ ሳሙኤል I እና II

I. የመጽሐፉ ስም

ሀ. እሱ የተሰየመው በመጀመሪያው ዋነኛ ገጸ-ባሕርይ ነው፣ ሳሙኤል። የስሙ ፍቺ፡
1. “ስሙ ኤል ነው፣” ወደ ሴም ተመልሶ በመሄድ፣
2. “ኤልን በመለመን፣” (1 ሳሙኤል 1፡20)

ለ. እሱም የነበረው፡
1. ፈራጅ -1 ሳሙ. 7፡6፤ 15-17
2. ነቢይ - 1 ሳሙ. 3፡20 (ነቢያት በዋነኛነት/በመነሻው “ባለ ራዕይ፣” ይባሉ ነበር I ሳሙ. 9:9፤ I ዜና. 29:29
3. ካህን - I ሳሙ. 10:8፤ 16:5

II. ቅዱስ ቃልነቱ (ካኖናይዜሽን)

ሀ. ይህ ነቢያት ተብሎ የሚጠራው የዕብራይስጥ ካኖን ሁለተኛ ምድብ ክፋይ ነው። ይህ ምድብ በሁለት ክፍሎች ይከፈላል፡
1. ቀዳሚዎቹ ነቢያት፣ ከኢያሱ - ነገሥት የሚያካትቱ (ከሩት በቀር)
2. ኋለኞቹ ነቢያት፣ ነቢያት ከኢሳይያስ - ሚልክያስ የሚያካትቱ (ከዳንኤልና እና ከሰቆቃወ ኤርምያስ በቀር።)

ለ. በዋነኛነት/በመነሻው፣ I እና II ሳሙኤል አንድ መጽሐፍ ነበሩ፣ በዕብራይስጥ ካኖን፡
1. ባባ ባትራ 14ለ (የኤምቲ መዝጊያ ማስታወሻ በII ሳሙኤል መጨረሻ ላይ ብቻ የሚገኝ)
2. Eusebius *Ecclesiastical History.* VII:25:2

ሐ. ሴፕቱዋጂንት (LXX) መጽሐፉን ለሁለት ይከፍለዋል፣ በርዝመቱ ምክንያት ሊሆን ይችላል። እሱም ደግሞ ታሪካዊ መጻሕፍት በሚል በሚከተለው መልኩ ተሰይሟል፡
1. I ሳሙኤል - I የንጉሣዊ አገዛዝ መጽሐፍ (በቫልጌት፣ I ነገሥት)
2. II ሳሙኤል - II የንጉሣዊ አገዛዝ መጽሐፍ (በቫልጌት፣ II ነገሥት)
3. I ነገሥት - III የንጉሣዊ አገዛዝ መጽሐፍ (በቫልጌት፣ III ነገሥት)
4. II ነገሥት - IV የንጉሣዊ አገዛዝ መጽሐፍ (በቫልጌት፣ IV ነገሥት)

III. ዘውግ

ሀ. ይህ በዋነኛነት በሕይወት ታሪክ ላይ ያተኮረ፣ ታሪካዊ ትርክት ነው።

ለ. ማለትም፣ እሱ ታሪካዊ ወንችንና ሁነቶችን መዝግቧል፣ እነርሱም በሁሉም አማኞች ዘንድ ትኩረት ሊያገኙ የማይችሉ!

ሐ. ይህ ዘመናዊ የምዕራባዊ ታሪክ አይደለም፣ ነገር ግን የጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ ታሪክ እንጂ። እሱም የሚያተኩረው በተመረጡ ሁነቶች ላይ ነው፣ ሥነ-መለኮታዊ እውነቶችን ለማስተላለፍ (ተግባቦት ለመፍጠር)። ስለዚህ፣ እሱ ከወንጌላት እና ሐዋርያት ሥራ (አኪ) ጋር ይመሳሰላል። እሱም መተርጎም የሚኖርበት አግባብ፡ (1) በተመረጠ፤ (2) በተጣጣመ፤ (3) በተስተካከለ እና (4) በተመስጧዊ መልኩ ነው።

ሆኖም፣ መታወቅ የሚኖርበት፣ ዕብራውያን እና ኬጢያውያን እጅግ ርግጠኛ የታሪክ ሰዎች መሆናቸው ነው። ሌሎቹ የጥንት ሕዝቦች ድሎቻቸውን አጋንነው ሲያቀርቡ፣ ሽንፈታቸውን ግን ይተዉታል።

መ. የቅርብ ምስራቅ ሥነ-ጽሑፍ ብልጽግናን አሁን ዘመናዊው አርኪዎሎጂ ለሊቃውንት አቅርቦልናል፣ ታሳቢ የሆነውን የሳሙኤልን ዘውግ ይዘት፣ በተለይም I ሳሙ. 15 – II ሳሙ. 8። በተለይ የ1200ዎቹ ቅ.ል.ክ. የኬጢያውያን ሰነድ፣ እሱም “የሀሉሲቲስ አቋም መግለጫ” ከሳሙኤል ጋር በርካታ ተመሳሳይነት አለው። እሱም በመሠረቱ የአዲሱ ሥርወ-መንግሥት መከላከያ አቋም ነው፣ አዲሱ ገዥ ሌለኛውን ሕጋዊ ገዥ በመተካቱ (ሥልጣኑን በመያዙ) እንዳይጠየቅ፣ (*Zondervan Pictorial Encyclopedia*, vol 5 p. ገጽ 259-260)።
1. ከአዲሱ ንጉሥ ጋር ለተያያዙ ሁነቶች አጽንዖት መስጠት
2. የሁነቶችን ማጠቃለያ በመያዝ ዘወትር መቀጠል፣ ጥብቅ የሆነ ታሪካዊ ቅደም ተከተልን ከመከተል ይልቅ
3. የፊተኞቹን ገዥዎች ክስፈት (ውድቀት) በግልጽ ማሳየት
4. የአዲሱን ገዥ ወታደራዊ ድል ማሳየት
5. የአዲሱን ገዥ እያደገ የመጣውን ዝና (ታዋቂነት) መግለጽ
6. የአዲሱን ገዥ ጠቃሚ የፖለቲካ ጋብቻዎች ሰንዷል (በሰነድ ይዟል)
7. የአዲሱን ገዥ ሃይማኖታዊ ጥብቅነትና ብሔራዊ ግንዛቤ አጽንዖት መስጠት
8. የአዲሱን ንጉሥ አገዛዝ፣ መለኮታዊ ቡራኬ (ባርኮት) እና አስተዳደራዊ ስኬቶች ማጠቃለያ

IV. ደራሲነት

ሀ. የአይሁድ ወግ/ልማድ ዘወትር የሚያስረግጠው ሳሙኤል ደራሲ እንደሆነ ነው፡
1. ባባ ባትራ 14ለ የሚለው ሳሙኤል መጽሐፉን ጽፏል፣ ስሙን የያዘውን፣ ደግሞም መሳፍንትን እና ሩትን።

2. መጽሐፉ ራሱ የሚያስቀምጠው ሳሙኤል እንደጻፈው ነው (I ሳሙ. 10:25 [ይህ ዘወትር የሚታሰበው፣ የመጀመሪያዎቹን 12 ነው ከ15 ምዕራፎች])።
3. ኋለኞቹ የአይሁድ ሊቃውንት ደግሞ ለዚህ እውቅና ሰጥተዋል፣ እንደ ዘዳግም እና ኢያሱ፣ ይህ መጽሐፍ የእሱን አሊቃ ገጸ-ባሕርይ ሞት መዝግቧል፣ I ሳሙ. 25፡1፤ 28፡3፣ እና ደግሞም ከሞተ በኋላ በረዥም ጊዜ የተከናወኑ ሁነቶችንም መዝግቧል። ስለዚህ፣ እነርሱ የሚያቀርቡት ሐሳብ፡
ሀ. ጸሐፊው ሲራክ፣ II ሳሙ. 8:17፣ መጽሐፉን አጠናቆት ሊሆን ይችላል
ለ. ካህኑ አብያታር መጽሐፉን አጠናቆት ሊሆን ይችላል
ሐ. የነቢዩ ናታንም ልጅ ዛቡድ (NIV)፣ አጠናቅሮት ሊሆን ይችላል (1 ነገሥት 4፡5)

ለ. ዘመናዊው አስተምህሮት፡
1. እውቅና ያገኘው፣ የመጻሕፍቱ ይዘቶች የሁነቶቹ የዓይን ምስክሮች እንደሆኑ ነው (ብራይት)።
2. ደግሞም እውቅና የገኘው፣ ጥቅም ላይ የዋሉት ምንጮች፡
ሀ. "የያሻር መጽሐፍ፣" II ሳሙ. 1:18
ለ. የሳሙኤል ዜና መዋዕል፣ I ሳሙ.10፡25፤ I ዜና. 29፡29
ሐ. የነቢያቱ የናታን እና የጋድ ዜና መዋዕል፣ I ዜና 29፡29
መ. ሌሎች የጊዜው ዜና መዋዕል፣ I ዜና. 27፡24
ሠ. ብዙ ዘመናዊ ሊቃውንት መገመት የሚወዱት ሳሙኤል፣ ናታን እና ጋድ (I ዜና. 29፡29) የሦስት ትረካዎች ደራሲዎች ናቸው፣ እነርሱም በናታን ልጅ በዛቡድ የተጠናቀሩ (1 ነገሥት 4፡5)፣ እሱም ደግሞ የቤተ-መንግሥትን ሰነዶች ማግኘት የሚችል።
3. ደግሞም የኋለኛ አዘጋጆች (አራሚዎች) ማስረጃ ይገኛል፣ ከሳሙኤል ጊዜ በኋላ፣ "እስከ ዛሬ ድረስ፣" በሚል በምሳሌነት የሚጠቀስ ሐረግ፣ (I ሳሙ. 5:5፤ 6:18፤ 27:6፤ 30:25፤ II ሳሙ. 4:3፤ 6:8፤ 18:18)።
4. ደግሞም ማስረጃ ይገኛል፣ ይህ አዘጋጅ ወይም አዘጋጆች የኖረውና የሠራው የተባበረው ሥርወ-መንግሥት ከተከፋፈለ በኋላ ለመሆኑ፣ በ922 ቅ.ል.ክ. (ብራይት) ወይም 930 ቅ.ል.ክ. (ሃሪሰን እና NIV) ወይም 933 ቅ.ል.ክ. (ያንግ) ወደ ሰሜናዊው አስር ነገዶች፣ እስራኤል፣ ኤፍሬም ወይም ሰማርያ ተብሎ የሚጠራው እና፣ ወደ ደቡባዊ ሦስቱ፣ ይሁዳ ተብሎ የሚጠራው (I ሳሙ. 11:8፤ 17:52፤ 18:16፤ 27:6፤ II ሳሙ. 5:5፤ 24:1)።
5. ሳሙኤል መልካም ምሳሌ ነው፣ ዘመናዊዎቹ ተንታኝ ሊቃውንት እንደሚመለከቱት እንደ ተጠናቀረ/ተወሳሰበ ጽሑፍ ምልክቶች፡
ሀ. የዔሊ ቤተሰብ ፍጻሜ፣ እንደ ካህናት፡
(1) I ሳሙኤል 2:31
(2) I ሳሙኤል 3:1
ለ. የሳኦል መቀባት:
(1) በምሥጢር፣ I ሳሙኤል 9:26-10:1
(2) በይፋ (ሁለቴ)፣ I ሳሙኤል 13:14፤ 15:23
ሐ. የዳዊት ከሳኦል ጋር መተዋወቅ:
(1) I ሳሙኤል 16:21
(2) I ሳሙኤል 17:58
መ. ዳዊት ከሳኦል ቤተ-መንግሥት አመለጠ:
(1) I ሳሙኤል 24:3
(2) I ሳሙኤል 26:5
ሠ. የዳዊትና የዮናታን ቃል-ኪዳን:
(1) I ሳሙኤል 18:3
(2) I ሳሙኤል 20:16፣ 42
(3) I ሳሙኤል 23:18
ረ. ዳዊት ወደ ጌት:
(1) I ሳሙኤል 21:10
(2) I ሳሙኤል 27:1
ሰ. የጎልያድ ገዳይ:
(1) ዳዊት - I ሳሙኤል 17:51
(2) ኤልያናን - II ሳሙኤል 21:19
(3) I ዜና. 20:5 እያሳየ የሚመስለው ጎልያድ እና ወንድሙ (ለሕሚ) በትይዩ መጠቀሳቸውን ነው
ሸ. የሳኦል መትረፍ:
(1) I ሳሙኤል 24:3
(2) I ሳሙኤል 26:5
ቀ. እንደ ታሳቢ ትይዩዎች እና/ወይም ተመሳሳይ ጥንዶች፣ አር.ኬ. ሃሪሰን የሚለው፣ "እንደገና በትኩረት መታየት ያለበት፣ አብዛኞቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካዎች አጠራጣሪ ውዝግቦች፣ የቸልታ ንባብ ወይም አንዳንዴ ሆን ተብሎ የተደረገ የዕብራይስጥ ጽሑፍን አላግባብ በማጣረስ/በማዛባት የተፈጠሩ ቀጥተኛ ውጤቶች ናቸው... እሱም በርግጥ በምናባዊ ትንተና ላይ ብቻ የሚገኝ፣" *የብሉይ ኪዳን መግቢያ* ገጽ 703 (*Introduction to the Old Testament*, p.703)::

6. የግድ መቀበል የሚኖርብን፣ ደራሲው አለመታወቁን ነው (ኢ.ጄ. ያንግ/ E.J. Young) እንዲሁም ደግሞ የእነዚህ የብኪ መጻሕፍት የማጠናቀር ሂደት አይታወቅም። ሆኖም፣ አሁንም የምናስረግጠው፡
ሀ. ሂደቱ በእግዚአብሔር መመራቱን፤
ለ. ሁነቶቹ በርግጥ ታሪካዊ መሆናቸው፣ ልቦለዳዊ/ፈጠራ ሳይሆኑ፤
ሐ. ሁነቶቹ ሥነ-መለኮታዊ ግፊት መያዛቸውን ነው።

V. ጊዜው

ሀ. ሁነቶቹ መቼ እንደተከሰቱ
1. I ሳሙኤል የሚሸፍነው ጊዜና ሰዓት ከሳሙኤል ልደት፣ 1105 ቅ.ል.ክ. (NIV) እስከ ሳኦል ሞት ድረስ ያለውን አካባቢ ነው፣ (1011/10 ሃሪሰን እና NIV፤ 1013 ያንግ፤ 1000 ብራይት)።
2. II ሳሙኤል የሚሸፍነው ከሳኦል ሞት አንሥቶ፣ 1011 ቅ.ል.ክ. አካባቢ፣ እስከ ዳዊት አገዛዝ ፍጻሜ ድረስ ነው (971/70 ሃሪሰን፤ 973 ያንግ፤ 961 ብራይት)። ሰሎሞን መግዛት የጀመረው በ969 ቅ.ል.ክ. አካባቢ ነው።

ለ. መጽሐፉ መቼ እንደተጻፈ
1. I ሳሙኤል 11:8፤ 27:6 የሚያሳዩት ቢያንስ አንዳንዱ መጽሐፍ አሁን ባለው መልኩ የተጻፈው፣ የተባበረው ሥርወ-መንግሥት ከተለያየ (ከተከፈለ) በኋላ ነው፣ በ922 ቅ.ል.ክ. ወይም 930 ቅ.ል.ክ።
2. "እስከ ዛሬ ቀን ድረስ፣" የሚለው ተደጋጋሚ ሐረግ የሚያሳየው፡
ሀ. አንዳንዱ መጽሐፍ የተጻፈው ከሁነቶቹ ከረጅም ጊዜ በኋላ መሆኑን፡ I ሳሙ. 5:5፤ 6:18፤ 27:6፤ 30:25፤ II ሳሙ. 4:3፤ 6:8፤ 18:18።
ለ. ቀደም ብለው ጥቅም ላይ የዋሉት ምንጮች ይሄንን ሐረግ ያካትታሉ።
3. አንደኛው የዚህ ዘመን ቀን አቆጣጠር ችግር የ I ሳሙ. 13:1 ጽሑፍ ነው፣ እሱም የሳኦልን አገዛዝ ጊዜ የሚገልጸውና፣ ነገር ግን በመልዕክት ማስተላለፍ ላይ የተጎዳው/የተበላሸው። ቁጥሩ በርግጥ ጠፍቷል።

## VI. ታሪካዊ መቼት

ሀ. I ሳሙኤል የመሳፍንት ጊዜን ሥርዓተ-አልበኝነት እና የሞራል ውድቀት/ብልሽት ታሪክ ይዟል፡
1. ኃጢአት፣ ወረራ፣ የይቅርታ ጸሎት፣ እና የእግዚአብሔር አዳኝ፣ የመሳፍንት 1-17 ባሕርይ (መለያ) ነው
2. የሞራል ውድቀቱ ምሳሌዎች መሳፍንት 18-21 ላይ ተዘርዝረዋል

ለ. የሞሶፖታሚያ እና የግብጽ ዋነኞቹ ሰፋፊ ግዛቶች (ኢምፓየር) ያልተስፋፉበት ጊዜ ነበር፡
1. ግብጽ፡
ሀ. የመጨረሻው የግብጽ ጎሳ (ዘር) የXX ሥርወ-መንግሥት ንጉሥ (1180-1065 ቅ.ል.ክ.፣ ብራይት) ራምሴስ XI ነበር
ለ. አሦር በውድቀት ላይ ነበር፣ ከቲግላዝ-ፒሌሰር I በኋላ (1118-1078 ቅ.ል.ክ.፣ ብራይት)

ሐ. ፍልስጥኤማውያን፣ በብዙ ቁጥር (የኤጅያን ባሕር ሕዝቦች)፣ ግብጽን ለመውረር ሙከራ አድርገዋል 1300 ቅ.ል.ክ. አካባቢ፣ ነገር ግን ተሸንፈዋል። እነርሱም በፍልስጥኤም ደቡባዊ ምዕራብ ጥግ ሰፈሩ፣ በ1250 ቅ.ል.ክ አካባቢ። እነርሱም የብረት ዘመን ቴክኖሎጂን ከኬጢያውያን ላይ አገለበጡ፣ እናም እነርሱ ራሳቸውን በአምስት ከተሞች ዙሪያ ለማደራጀት ቻሉ፡ አስቀሎና፣ አሽዶድ፣ ኤክሮን፣ ጌት እና ጋዛ። እነርሱም እንደ ግሪክ የከተማ አገሮች ነው የተደራጁት፣ እያንዳንዱ በገዛ ራሱ ንጉሥ። እነርሱም የእስራኤላውያን ዋነኛ ጠላቶች ሆኑ፣ በፊተኛው የንጉሥ ግዛት ዘመን።

## VII. ጽሑፋዊ ምድቦች (ዐውደ-ጽሑፍ)

ሀ. አጭር የፍሬ ሐሳብ ዝርዝር፣ በዋነኞቹ ገጸ-ባሕርያት፡
1. ዔሊ እና ሳሙኤል፣ I ሳሙ. 1-7
2. ሳሙኤል እና ሳኦል፣ I ሳሙ. 8-15
3. ሳኦል እና ዳዊት፣ I ሳሙ. 16 - II ሳሙ. 1
4. የዳዊት አገዛዝ፣ II ሳሙ. 2-12
5. ዳዊት እና ተተኪዎቹ፣ II ሳሙ. 13-20
6. ልዩ ልዩ ነገሮች፣ ስለ ዳዊትና አገዛዙ፣ II ሳሙ. 21-24

ለ. የI እና II ሳሙኤል የፍሬ ሐሳብ ዝርዝር የተደረገው በደራሲው/አዘጋጁ ይመስላል፣ የማጠቃለያ መግለጫዎችን በማከል፡
1. I ሳሙኤል 7:15-17
2. I ሳሙኤል 14:49-51
3. II ሳሙኤል 8:15-18
4. II ሳሙኤል 20:23-26

ሐ. ዝርዝር የፍሬ-ሐሳብ መግለጫ፡
1. R.K. Harrison, *Introduction to the Old Testament*, p. 695-696 ተመልከት፡፡
2. E.J. Young, *An Introduction to the Old Testament*, p. 180-187ተመልከት፡፡
3. NIV Study Bible, p. 373 and 422ተመልከት፡፡

## VIII. ዋነኛ ሐቆች

ሀ. ሳሙኤል ሥርወ-መንግሥቱን ለማቆም መድረኩን አመቻቸ፣ ልክ ሙሴ ሕዝቡን (ብሔረ-እስራኤልን) ለማበጀት መድረኩን እንዳመቻቸ ሁሉ፡
1. ሙሴ፣ እስራኤል ንጉሥ እንደሚያገኝ ተንብዮአል፣ ዘዳ. 17:14-20 ላይ፣ እዚያም ጻድቅ ንጉሥ ምን እንደሚያደርግና እንደማያደርግ በገለጸበት።
2. በI ሳሙኤል ላይ ንጉሥን በተመለከተ ተቃርኖ (የተቃርኖ ሚዛን) አለ፡
ሀ. አሉታዊ ገጽታ፡

(1) እነርሱ ያህዌን እንደ ንጉሥ አለመቀበላቸው፣ I ሳሙ. 8:7፤ 10:19
(2) እነርሱ ንጉሥን የጠየቁት "እንደ አካባቢው ሕዝቦች መሆኑ፣" I ሳሙ. 8:5፤ 12:19-20
(3) ይህም ሳሙኤልን ደስ አላሰኘውም፤ በግሉም የተናቀ መሰለው፣ I ሳሙ. 8:6

ለ. አዎንታዊ ገጽታዎች፡
(1) ያህዌ ትንቢቱን ፈጸመ፣ ዘዳግም ላይ ያለውን፣ ለእነርሱ ንጉሥ በመስጠት፣ I ሳሙ. 8:7፣9፣22፣ "የሕዝቡን ቃል ስማ"
(2) ለአዲሱ ንጉሥ መልካሙን መመሪያ ነገረው፣ I ሳሙ. 8:9 (ዘዳ. 17:14-20)
(3) ንጉሡ ሕዝቡን ያድናል፣ I ሳሙ. 9:16 (ፈራጆች/መሳፍንት የሕዝቡን ልመና እንደሚያደምጡ ሁሉ I ሳሙ. 12:13)

ለ. ሳሙኤል በመዝገብ ላይ አስፍሮታል፣ መንፈሳዊ ሥልጣን ከሊቀ ካህኑና ከቤተ-መቅደስ፣ እየመጣ ወዳለው ትንቢታዊ ቃል አቀባይ/ተናጋሪ መሸጋገሩን። ይህም ምላሽ የሚሆነው፡

1. እግዚአብሔር በዔሊ እና በቤተሰቡ ላይ በሰጠው ፍርድ፣ I ሳሙ. 2:22-3:18
2. በካህናት የአምልኮ ሥርዓት መልክ እና፣ በነቢያት ላይ ባተኮረ ግላዊ ልባዊ እምነት መካከል ሚዛን መጠበቅ በማስፈለጉ
3. ሁለቱም ካህናትና ነቢያት ለሕዝቡ በአንድነት የኪዳን መካከለኞች (አማላጆች) ናቸው
4. ሳኦል ወደ ሳሙኤል ይመለከት ነበር፣ ዳዊት ወደ ናታን እና ጋድ ሲመለከት፣ የእግዚአብሔርን ፍቃድ ለማጽናት

ሐ. II ሳሙኤል የሰነደው (በሰነድ የያዘው)፡

1. የእግዚአብሔርን መልካምነት ለዳዊት
2. የዳዊትን ጥንካሬና ድክመት
3. የእግዚአብሔር ፍርድ በዳዊት ላይ፣ በኃጢአቱ ምክንያት፣ የእሱም መዘዝ (ውጤት)፡
   ሀ. በሕዝቡ ላይ
   ለ. በኦርዮ ቤተሰብ ላይ
   ሐ. በቤርሳቤህ ልጅ ላይ
   መ. በዳዊት ልጆች ላይ

መ. I እና II ሳሙኤል የእግዚአብሔርን ሕዝብ ታሪክ የቀጠለ ነው፣ ዘፍጥረት ላይ የጀመረውን።

IX. ቃላት እና ሐረጋት እና ስፍራዎች በአጭሩ የሚገለጹ

ሀ. ቃላት እና ሐረጋት፡

1. I ሳሙኤል፡
   ሀ. የበፍታ ኤፉድ፣ 2፡18፣28 (NASB እና NIV)
   ለ. "ቀንዴ ከፍ ከፍ አለ፣" 2፡1፣ 10 (NASB እና NIV)
   ሐ. "ከዳን እስከ ቤርሳቤህ፣" 3፡20 (NASB እና NIV)
   መ. በኪሩቤል ላይ የሚቀመጥ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፣" 4፡4፣(NIV፣ "ኃያል ጌታ፣ በኪሩቤል መካከል በዙፋኑ የሚቀመጥ")
   ሠ. "እያንዳንዱ ወደ ድንኳኑ፣" 4፡10 (NASB እና NIV)
   ረ. የወርቅ እባጮች፣ 6፡4 (NIV፣ "የወርቅ እጢዎች")
   ሰ. አቤንኤዘር፣ 7፡12 (NASB እና NIV)
   ሸ. "እንደ ልቡ የሆነ ሰው፣" 13፡14 (NASB እና NIV)
   ቀ. "በእስራኤል ምድር ሁሉ ብረት ሠሪ አልተገኘም፣" 13፡19 (NASB እና NIV)
   በ. "መታዘዝ ከመሥዋዕት ይበልጣል፣" 15፡22 (NASB እና NIV)
   ተ. "እግዚአብሔር ተጸጸተ..." 15፡35 (NIV፣ "...አዘነ")
   ቸ. "ክፉም መንፈስ ከእግዚአብሔር ዘንድ አሣቀየው፣" 16፡14 (NIV፣ "አስጨነቀው")
   ኀ. "ልጋጉም በጢሙ ላይ ይወርድ ነበር፣" 21፡13 (NASB እና NIV)
2. II ሳሙኤል፡
   ሀ. የያሻር መጽሐፍ፣ 1፡18 (NASB እና NIV)
   ለ. ሚሎ፣ 5፡9 (NIV፣ "የድጋፍ ቅጥር")
   ሐ. ቋንጃ ቆረጠ፣ 8፡4 (NASB እና NIV)

ለ. በአጭሩ የሚገለጹ ሰዎች፡

1. I ሳሙኤል፡
   ሀ. ሐና፣ 1፡1
   ለ. አፍኒንና ፊንሐስ፣ 1፡3
   ሐ. ኢካቦድ፣ 4:21
   መ. ቂስ፣ 9:1
   ሠ. ዮናታን፣ 14:1፤ 19:1
   ረ. ሜልኮል፣ 14:49
   ሰ. አበኔር፣ 14:50
   ሸ. ጎልያድ፣ 17:4
   ቀ. ዶይቅ፣ 21:7
   በ. አብያታር፣ 22:20
   ተ. የዓይንዶር መናፍስት ጠሪ፣ 28:7 (NIV፣ "መናፍስት ጠሪ... በዓይንዶር")
   ቸ. አቢግያ፣ 30:5

2. II ሳሙኤል፡
   ሀ. ኢያቡስቴ፣ 2:8
   ለ. ኢዮአብ፣ 2:13
   ሐ. አምኖን፣ 3:2
   መ. አቤሴሎም፣ 3:3
   ሠ. አዶንያስ፣ 3:4
   ረ. ሜምፊቦስቴ፣ 4:4
   ሰ. ዖዛ፣ 6:3
   ሸ. ኦርዮ፣ 11:3
   ቀ. ትዕማር፣ 13:5
   በ. ሳዶቅ፣ 15:24
   ተ. ሳሚ፣ 16:5

X. የካርታ ስፍራዎች (አመላካቾች) (በቁጥር)


ሀ. I ሳሙኤል፡
1. ቂርያትይዓሪም፣ 6:21
2. አርማቴም፣ 7:17
3. ቤርሳቤህ፣ 8:2
4. ኢያቢስ ገለዓድ፣ 11:1
5. የዓዶላ ዋሻ፣ 22:1
6. ኖብ፣ 21:1
7. ዓይንጋዲ፣ 23:29
8. ጺቅላግ፣ 30፡1
9. ጊልቦዓ ተራራ፣ 31፡8


ለ. II ሳሙኤል፡
1. አስቀሎና፣ 1:20
2. ኬብሮን፣ 2:3
3. ኢይዝራኤል፣ 2:9
4. ጌዝር፣ 5:25
5. ደማስቆ፣ 8:5
6. ረባት፣ 12:27
7. ቴቁሔ፣ 14:2
8. የኢያቡሳዊው ኦርና አውድማ ፣ 24:16 (ኢየሩሳሌም)

XI. የተማሪ ይዘት ጥያቄዎች

ሀ. I ሳሙኤል፡
1. የሳሙኤል ልደት የተመዘገበው ለምንድነው፣ የሳኦል ወይም የዳዊት ግን ለምን ቀረ?
2. እግዚአብሔር ዔሊንና ቤተሰቡን ለምን ናቃቸው (ተወ)?
3. ፊንሐስና አፍኒን ታቦቱን ለምን ወደ ጦርነት ይዘውት ሄዱ?
4. ሳሙኤል ለምን ተቆጣ፣ ሕዝቡ ንጉሥ እንዲኖራቸው ስለጠየቁ?
5. ሳኦል ከንጉሥነት የተናቀው ለምንድነው?
6. "ክፉ መንፈስ ከእግዚአብሔር ዘንድ፣" የሚለውን አብራራ።
7. ሳኦል ዳዊትን ለመግደል የሞከረው ለምንድነው?
8. ሳኦል እንዴት ሞተ?

ለ. II ሳሙኤል፡
1. ዳዊት በኢያቡስቴ ሞት የተበሳጨው (ያዘነው) ለምንድነው?
2. ዳዊት በአበኔር ሞት የተበሳጨው (ያዘነው) ለምንድነው?
3. ዳዊት ሜምፎቦስቴን ለምን ረዳ?
4. እግዚአብሔር ኦዛን ለምን ገደለ?
5. እግዚአብሔር ለዳዊት ምዕራፍ 7 ላይ የሰጠው ተስፋ እጅግ ጠቃሚ የሚሆነው ለምንድነው?
6. ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር የፈጸመው ኃጢአት በቤተሰቡ ላይ እንዴት ጉዳት አደረሰ?
7. በሳዶቅና በአብያታር መካከል ያለውን ልዩነት አብራራ።
8. እግዚአብሔር በዳዊት ላይ የተቆጣው ለምንድነው፣ ሕዝቡን በመቁጠሩ?


ANCIENT
NEAR EAST
N
S
E
W


PALESTINE
0 10 20 30 40
SCALE IN MILES

# መጽሐፈ ነገሥት I እና II መግቢያ

I. የመጽሐፉ ስም

ሀ. እንደ I እና II ሳሙኤል እና I እና II ዜና መዋዕል፣ I እና II ነገሥት በመነሻው (በዋነኛነት) በዕብራይስጥ አንድ መጽሐፍ ነበር። እሱም "*Melakim*" ወይም ነገሥት ተብሎ ይጠራ ነበር። ይህንንም መጠሪያ ያገኘው የይሁዳንና የእስራኤልም ነገሥታት ታሪክ ስለሚሸፍን ነው።

ለ. እንደ I እና II ሳሙኤል እና I እና II ዜና መዋዕል፣ I እና II ነገሥት በመጀመሪያ ወደ ሁለት መጻሕፍት ተከፍሎ ነበር፣ LXX ላይ። በግልጽ እንደሚታየው፣ ይህ የተደረገው በእነዚህ መጻሕፍት ዝርመት ነው። እነርሱ በቀላሉ በአንድ ብራና ጥቅል ላይ ሊካተቱ አይችሉም፣ ከቆዳው ክብደትና ብዛት የተነሣ። መጽሐፉን ለመከፋፈል የመጀመሪያው የዕብራይስጥ ጽሑፍ እስከ 1448 ዓ.ም ድረስ አልነበረም።

ሐ. የእነዚህ ሁለት መጻሕፍት ርዕስ የነበረው፡
1. በዕብራይስጥ - "ነገሥት"
2. በ LXX - III እና IV ንጉሣዊ አገዛዝ
3. በቫልጌት - III እና IV ነገሥት (I እና II የነበረው I እና II የንጉሣዊ አገዛዝ እና ነገሥት)

II. ቅዱስ ቃልነቱ (ካኖናይዜሽን)

ሀ. እነዚህ መጻሕፍት የዕብራይስጥ ካኖን፣ "ነቢያት" ተብሎ የሚጠራው፣ ሁለተኛ ምድብ ክፍሉ ናቸው።

ለ. ምድቡ በሁለት ክፍሎች ይከፈላል፡
1. ቀዳሚዎቹ ነቢያት፣ እነርሱም ኢያሱ - ነገሥትን የሚያካትቱ፣ ከሩት በቀር።
2. ኋለኞቹ ነቢያት እነርሱም ኢሳይያስ - ሚልክያስን የሚያካትቱ፣ ከዳንኤልና ከሰቆቃወ ኤርምያስ በቀር።

ሐ. የዕብራይስጥ ብኪ መጻሕፍት ዝርዝር የዕብራይስጥ ሃይማኖታዊ ምሥጢራዊነት ተጽዕኖ ሳያሳርፍበት አይቀርም። 22 ፊደላት በዕብራይስጥ የፊደል ገበታ (ጽሑፍ) ውስጥ ይገኛሉ። በርከት ያሉ መጻሕፍትን በማቀላቀል 22 መጻሕፍት ይገኛሉ፡
1. መሳፍንት እና ሩት
2. ሳሙኤል
3. ነገሥት
4. ዜና መዋዕል
5. ዕዝራ - ነህምያ
6. ኤርምያስ እና ሰቆቃወ ኤርምያስ
7. አስራ ሁለት መለስተኛ ነቢያት።

III. ዘውግ

ሀ. እነዚህ መጻሕፍት በመሠረቱ ታሪካዊ ትርክት ናቸው፣ ተደጋጋሚ ጥቅሶች ያሏቸው፡
1. ከቤተ-መንግሥት መዛግብት (ጽሑፎች)
2. ከነቢያት

ለ. አንዱ ሦስቱን መጻሕፍት፣ ሳሙኤል፣ ነገሥት እና ዜና መዋዕልን ቢደባልቅ፣ የተለያዩ ዓይነቶች ታሪካዊ ትርክቶች ይወጣሉ፡
1. ሳሙኤል በመሠረቱ የሕይወት ታሪካዊ ነው። እሱም የሚያተኩረው በዋነኞቹ ገጸ-ባሕርያት ላይ ነው፡
   ሀ. ሳሙኤል
   ለ. ሳኦል
   ሐ. ዳዊት
2. ነገሥት በመሠረቱ አጠናቅሮ የያዘው፡
   ሀ. የንጉሣዊ ቤተ-መንግሥት መዛግብት፡
      (1) "የሰሎሞን ዜና መዋዕል መጽሐፍ፣" I ነገ. 11፡41
      (2) "የይሁዳ ነገሥታት ዜና መዋዕል መጽሐፍ፣" I ነገ. 14:29፤ 15:7፣23
      (3) "የእስራኤል ነገሥታት ዜና መዋዕል መጽሐፍ፣" I ነገ. 14:19፤ 15:31።
   ለ. ትንቢታዊ ነገሮች፡
      (1) ኤልያስ
      (2) ኤልሳዕ
      (3) ኢሳይያስ (ምዕ. 36-39)
      (4) የትንቢታዊና ታሪካዊ ጽሑፎች ማስረጃ በዜና መዋዕል በግልጽ ይታያል፡
         (ሀ) I ዜና መዋዕል 29:29
         (ለ) II ዜና መዋዕል 9:29
         (ሐ) II ዜና መዋዕል 12:15
         (መ) II ዜና መዋዕል 13:22
         (ሠ) II ዜና መዋዕል 26:22
3. ዜና መዋዕል በመሠረቱ የነገሥታት የተመረጠ የአዎንታዊ ሥነ-መለኮት አቅርቦት (ጽሑፍ) ነው፡
   ሀ. የተባበረው ሥርወ-መንግሥት።

ለ. የይሁዳ ነገሥታት።

IV. ደራሲነት

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ I እና II ነገሥት ደራሲነት ያለው ነገር የለም፣ በአብዛኞቹ በቀዳሚዎቹ ነቢያት መጻሕፍት ላይ እንደሆነው።

ለ. ባባ ባትራ 15ሀ የሚለው ኤርምያስ ይሄንን መጽሐፍ ጽፎታል፣ መጽሐፈ ነገሥትንና ሰቆቃወ ኤርምያስን፡
1. ይህ ሊሆን ይችላል፣ ምክንያቱም የII ነገሥት፣ 24፡18-25፡30 መጨረሻ በዕብራይስጥ ከኤርምያስ 52 ጋር እጅግ ስለሚመሳሰል።
2. ግልጽ የሆነው፣ ደራሲው የኢየሩሳሌም መውደቅ የዓይን ምስክር መሆኑ ነው።

ሐ. በእውነታው (በተጨባጭ) ግን እነዚህ መጻሕፍት የአጠናቃሪ ሥራ ናቸው፣ የደራሲ ሳይሆን።

መ. ሌላው መታወስ የሚኖርበት አጠናቃሪው በርከት ያሉ ምንጮችን መጠቀሙ ነው፡
1. የመጀመሪያው ምንጭ ቅዱስ ቃሉ ነው። እሱ ዘወትር ከዘዳግም እና ከአንዳንድ ነቢያት ይጠቅሳል፣ ወይም ጠቃሽ ያደርጋል።
2. ተለይተው የተሰየሙ በርከት ያሉ የጽሑፍ ምንጮች አሉ፡
ሀ. "የሰሎሞን ሥራ መጽሐፍ፣" I ነገ. 11፡41
ለ. "የይሁዳ ነገሥታት ዜና መዋዕል መጽሐፍ፣" 1ነገ. 14፡29፤ 15፡7፣23
ሐ. "የእስራኤል ነገሥታት ዜና መዋዕል መጽሐፍ፣" I ነገ. 14፡19፤ 15፡31
መ. ደግሞም 1 ዜና. 29፡29 ላይ ስለ ነቢያት የጽሑፍ መዝገብ የተጠቀሰ አለ፡ ሳሙኤል፣ ናታን እና ጋድ። ይህም ሥነ-ቃሎች መጻፋቸውን ያሳያል።

ሠ. በI እና II ነገሥት ላይ አንዳንድ የአራሚዎች/አዘጋጆች ጭማሪ አለ፣ ወይም አጠናቃሪው "እስከ ዛሬ ድረስ" የሚለውን ሐረግ ጠቅሷል፣ ካገኘበት ምንጭ፡
1. I ነገሥት 8፡8
2. I ነገሥት 9፡21
3. I ነገሥት 12፡19
4. II ነገሥት 8፡22

V. ጊዜው

ሀ. የመጽሐፉ ሁነቶች የሚሸፍኑት ጊዜ፡
1. ከዳዊት ሞት እና ከሰሎሞን አገዛዝ መጀመሪያ፡
ሀ. ብራይት - 961 ቅ.ል.ክ
ለ. ሃሪሰን - 971/970 ቅ.ል.ክ
ሐ. ያንግ - 973 ቅ.ል.ክ.
መ. NIV - 970 ቅ.ል.ክ
2. እስከ ባቢሎናውያን ንጉሥ ኢቨል ሜሮዳክ፣ ደግሞም አሜል-ማርዱክ ተብሎ የሚታወቀው፣ 562-560 ቅ.ል.ክ. (ብራይት)
3. ነገር ግን II ነገሥት የምድያም-ፋርስ ንጉሥ "ታላቁ" ቂሮስን አይጠቅስም፣ የእሱም ሠራዊት የባቢሎንን ከተማ በ539 ቅ.ል.ክ የደመሰሰ።

ለ. መጽሐፉ የተጻፈው ወይም የተጠናቀረው በባቢሎን ግዞት ጊዜ ወይም በኋላ ወዲያውኑ ሊሆን ይችላል።

ሐ. ነገሥታቱ የገዙበት ዘመን ርዝመት አንድ ላይ ሲደመር ከመጻሕፍቱ የጊዜ ቅንብብ ጋር ለመግጠም እጅግ ይረዝማል። በዛ ያሉ ታሳቢ መፍትሔዎች አሉ፡
1. የተዘረዘሩት ቁጥሮች የጋራ አገዛዝን ግምት ውስጥ ያላስገቡ ናቸው።
2. ጥቅም ላይ የዋሉ ሁለት የዓመታት መቁጠሪያ (ካሌንደር) ነበሩ፡
ሀ. የተቀደሰው የቀን መቁጠሪያ (ካሌንደር) በበልግ ይጀምራል።
ለ. ሃይማኖታዊው የቀን መቁጠሪያ (ካሌንደር) በጸደይ ይጀምራል።
3. የነገሥታቱ ቁጥርና ዜና መዋዕሉ ሲነጻጸር፣ አንዳንድ የጽሕፈት ስሕተት መፈጠሩ ግልጽ ነው።

VI. ታሪካዊ መቼቱን የሚያጠናክሩ ምንጮች

ሀ. የአርኪዎሎጂ ማስረጃ፡
1. የሜሻ ትክል ድንጋይ፣ ደግሞም የሞአባውያን ድንጋይ፣ የሜሻን፣ የሞአብን ንጉሥ፣ በእስራኤል ላይ ማመጽ መዝግቧል፣ ከንጉሥ አምሪ በኋላ፣ ወዲያውኑ (876-869 ቅ.ል.ክ፣ ብራይት፤ 874/3 ቅ.ል.ክ፣ ሃሪሰን [II ነገ 3፡4])።
2. የሶርያ ንጉሥ የሻልማንሰር III ጥቁር ሐውልት (859-824 ቅ.ል.ክ.፣ ብራይትና ሃሪሰን)፡
ሀ. የቋርቋር ጦርነት በ853 ቅ.ል.ክ. የተካሄደው በኦሮንተስ ወንዝ ላይ ነው። ከሻልማንሰር III ጥቁር ሐውልት የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው፣ እስራኤላዊው አካብ ብሎ ነው የሰየመው፣ እሱም ብርቱ ወታደራዊ ኃይል እንዳለው እውቅና ይሰጣል (ከሶርያ አኳያ፣ I ነገ. 22፡1)። ይህ ውጊያ ብኪ ላይ አልተመዘገበም።
ለ. እሱም የእስራኤልን ቀጣይ ንጉሥ፣ ኢዩን ያሳያል (842-815 ቅ.ል.ክ፣ብራይት [II ነገ. 9-10])፣ ለአሦርም ግብር ይከፍል እንዲሁም ታማኝ ነበር። ይህም ደግሞ ብኪ ላይ አልተመዘገበም።
3. የብርጭቆ (ጃስፐር) ማኅተም ሜጊዶ ላይ ተገኝቷል፣ በይሮቦአም II ጊዜ (786-746 ቅ.ል.ክ፣ብራይት፤ 782-753 ቅ.ል.ክ. ሃሪሰን) ይሮቦአም የሚል ስያሜ ያለው።

4. የከሆርሳባድ የሁነቶች ዜና መዋዕል ክልሉን ይገልጻል፣ እንዲሁም የሰማርያን በሳርጎን II እጅ መውደቅ (722-705 ቅ.ል.ክ.) በ722 ቅ.ል.ክ. (II ነገ. 17)።
5. የሰናክሬ ጽሑፍ፣ ስለ ኢየሩሳሌም መከቡብ የሚገልጸው፣ በ701 ቅ.ል.ክ. በሕዝቅያስ አገዛዝ ዘመን (715-687 ቅ.ል.ክ. ብራይት [II ነገ. 18፡13-19፡37፤ኢሳ. 36-39])።
6. ደጋፊ ሊሆኑ የሚችሉ ቀናትን በመውሰድ (የአሦራውያንን ሰነዶችና ብኪን)፡ (1) የቋርቋር ውጊያ (ሻልማኒሰር III ከእስራኤልና ከሶርያ ጋር) 853 ቅ.ል.ክ.፤ እና (2) የፀሐይ ግርዶሽ (የአሦራውያን ስያሜ (ኢፖኒም) ዝርዝር ኢሻዱ-ሰገሌ 763 ቅ.ል.ክ.)፤ (3) የኢዩ ለሻልማንሰር III ግብር መክፈል (841 ቅ.ል.ክ.)፤ የነገሥት ሁነቶች ቀናት ሊረጋገጥ ይችላል።

ለ. *የሜሶፖታሚያ ኃይላት አጭር ታሪካዊ ቅኝት/ጥናት* (በጆን ብራይት *የእስራኤል ታሪክ* ላይ የተቀመጡትን ቀናት በቀዳሚነት በመመሥረት፣ ገጽ 462 John Bright's *A History of Israel* p 462ff)፡

1. የአሦር ሰፊ ግዛት (ኢምፓየር) (ዘፍ. 10፡11)፡
   *ሀ. ሃይማኖትና ባህል በእጅጉን ተጽዕኖ አድሮበታል፣ በሱሜርያን/ባቢሎናውያን ኢምፓየር።*
   *ለ. የገዥዎችና የገዙበት ጊዜ ጊዜያዊ ግምታዊ ዝርዝር፡*
   (1) 1354-1318 አሽሁር - ዑባሊት I፡
      (ሀ) የኤዊያውያን ከተማ የሆነችውን ከርከሚሽን ድል አደረገ
      (ለ) የኤውያውያንን ተጽዕኖ ማስወገድ በመጀመር፣ የአሦር እንዲጎለብት ፈቀደ
   (2) 1297-1266 አዳድ-ኒራሪ I (ብርቱ ንጉሥ)
   (3) 1265-1235 ሻልማኔስር I (ብርቱ ንጉሥ)
   (4) 1234-1197 ቱኩልቲ-ኒኑርታ I
      - የባቢሎን ኢምፓየር የመጀመሪያው ድል፣ ወደ ደቡብ
   (5) 1118-1078 ቲግላዝ-ፒሌሰር I
      - አሦር ዋነኛው ኃይል ሆነ፣ በሜሶፖታሚያ
   (6) 1012- 972 አሸር-ራቢ II
   (7) 972- 967 አሸር-ረሽ-ኢሱዩ II
   (8) 966- 934 ቲግላዝ-ፒሌሴር II
   (9) 934- 912 አሸር-ዳን II
   (10) 912- 890 አዳድ-ኒራሪ II
   (11) 890- 884 ቱኩልቲ-ኒኑርታ II
   (12) 883- 859 አሸር-ናሲር-አፓል II
   (13) 859- 824 ሻልማኔሰር III
      የቋርቋር ጦርነት በ 853
   (14) 824-811 ሻማሺ -አዳድ V
   (15) 811-783 አዳድ-ኒራሪ III
   (16) 781-772 ሻልማኒሰር IV
   (17) 772-754 አሸር-ዳን III
   (18) 754-745 አሸር-ኒራሪ V
   (19) 745-727 ቲግላዝ-ፒሌሰር III:
      (ሀ) በባቢሎናዊ የዙፋን ስሙ የተጠራ፣ ፑል፣ II ነገሥት 15፡19 ላይ
      (ለ) እጅግ ብርቱ ንጉሥ
      (ሐ) የተሸነፉ ሕዝቦችን ካገር የማስወጣት ፖሊሲ የጀመረ
      (መ) በ735 ቅ.ል.ክ. "የሶርያ-ኤፍራጥስ ማኅበር" ምሥረታ ነበር፣ ይኸውም በዮርዳኖስ አካባቢ ሀገራት የሚገኘውን ወታደራዊ ኃይል፣ ከኤፍራጥስ የውኃ መነሻ እስከ ግብፅ ድረስ የማስተባበር ሙከራ ለማድረግ ነበር፣ ዓላማውም በማቆጥቆጥ ላይ የሚገኘውን የአሦርን ኃይል ማዳከም። የይሁዳው ንጉሥ አካዝ ለመደብለቅ እምቢ ስላለ በእስራኤልና ሶርያ ተወርሯል። እሱም ለቲግላዝ-ፒሌሰር III ለዕርዳታ ጽፏል፣ የኢሳይያስን ምክር ባለመቀበል (II ነገ. 16፤ኢሳ. 7-12)።
      (ሠ) በ732 ቲግላዝ-ፒሌሰር III ሶርያንና እስራኤልን ወርሮ ድል አደረገና በእስራኤል ዙፋን ላይ ታዛዥ ንጉሥ አስቀመጠ፣ ሆሺያ (732-722)። በሺሆች የሚቆጠሩ አይሁድ ከሰሜናዊው ንጉሣዊ ግዛት ወደ ምድያም ተሰደዱ (II ነገሥት 15)።
   (20) 727-722 ሻልማነሰር V
      (ሀ) ሆሺያ ከግብፅ ጋር የወዳጅነት ትብብር መሠረተ፣ እናም በአሦር ተወረረ (II ነገሥት 17)
      (ለ) በ724 ቅ.ል.ክ. ሰማርያን በወታደራዊ ኃይል ከበበ
   (21) 722-705 ሳርጎን II፡
      (ሀ) በሻልማነሰር V ከተጀመረው የሦስት ዓመት ከበባ በኋላ፣ የእሱ ወራሽ ሳርጎን II የእስራኤልን ዋና ከተማ ሰማርያን ድል አደረገ። ከ27፣000 በላይ ወደ ምድያም እንዲወጡ ተደረገ።
      (ለ) የኤዊያውያን ኢምፓየርም ድል ሆነ።
      (ሐ) በ714-711 ሌላው የዮርዳኖስ ዙሪያ አገሮች ቅንጅትና ግብፅ በአሦር ላይ ዓመጹ። ይህ ቅንጅት "የአሽዳድ ዓመጽ" በመባል ይታወቃል። የይሁዳው ሕዝቅያስ እንኳ በመነሻው ላይ ገብቶበታል። አሦር በርካታ የፍልስጥኤም ከተሞችን ወርሮ ደምስሷል።
   (22) 705-681 ሰናክሬ፡
      (ሀ) በ705 ሌላ የዮርዳኖስ ዙሪያ አገሮች ቅንጅት እና ግብፅ ከሳርጎን II ሞት በኋላ ዓመጹ። ሕዝቅያስ ይሄንን ዓመጽ በሙሉ ደገፈ። ሰናክሬብ በ701 ወረረ። ዓመጹ ተደመሰሰ፣ ነገር ግን ኢየሩሳሌም በእግዚአብሔር ድርጊት ልትተርፍ ቻለች (ኢሳ. 36-39 እና II ነገ. 18-19)።

(ለ) ሰናክሬ ደግሞ በዔላም እና በባቢሎን የተነሣውን ዓመጽ አከሸፈ።

(23) 681-699 ኢሳርሃዶን፡

(ሀ) የመጀመሪያው የሶርያ ገዥ፣ ግብፅን ለማጥቃትና ድል ለማድረግ

(ለ) ለባቢሎን ታላቅ ድጋፍ ያለው፣ እናም ዋና ከተማዋን ዳግም ገንብቷል

(24) 669-663 አሸርባኒፓል፡

(ሀ) ደግሞም ኦስናፓር በመባል ይጠራል፣ ዕዝራ 4፡10 ላይ

(ለ) ወንድሙ ሻማሽ-ሹም-ዑኪን የባቢሎን ንጉሥ ሆኗል። ይህም በአሦር እና በባቢሎን መካከል የብዙ ዓመታት ሰላምን አስገኝቷል፣ ነገር ግን የተዳፈነ/ ያልሰመረ የነጻነት ትግል በ652 በወንድምየው የሚመራ ተነሥቷል።

(ሐ) የቱብስ ውድቀት፣ 663 ቅ.ል.ክ.

(መ) ዒላምን ድል አደረገ፣ 653፣ 645 ቅ.ል.ክ.

(25) 633-629 አሸር-ኢቲል-ኢላኒ

(26) 629-612 ሲን-ሻር-ኢሽኩን

(27) 612-609 አሸር-ዑባሊት II፡

በካራን በስደት ላይ በዙፋኑ የተቀመጠ ንጉሥ፣ ከአሸር መውደቅ በኋላ፣ በ614 ቅ.ል.ክ. እና በነነዌ በ612 ቅ.ል.ክ።

2. አዲሱ-የባቢሎናውያን ኢምፓየር፡

ሀ. 703-? ሜሮዳክ-ባላዳን

በርከት ያለ ዓመጽን ጀመረ፣ በአሦር ገዥ ላይ

ለ. 652 ሻማሽ-ሹም-ዑኪን፡

(1) የኢሳርሃዶን ልጅ እና የአሸርባኒፓል ወንድም

(2) እሱ በአሦር ላይ ዓመጽ ጀመረ፣ ነገር ግን ተቸነፈ

ሐ. 626-605 ናቦፖላሳር፡

(1) የመጀመሪያው ሥርወ-መንግሥት የአዲሱ-ባቢሎን ኢምፓየር

(2) እሱም አሦርን በደቡብ በኩል አጠቃ፣ የምድያሙ ሳያከሳረስ በስተ ሰሜናዊ ምስራቅ ሲያጠቃ

(3) አሮጌው የአሦር ዋና ከተማ የአሸር በ614 ወደቀ፣ እንዲሁም ብርቱይቱ አዲሲቷ ዋና ከተማ ነነዌ በ612 ቅ.ል.ክ. ወደቀች።

(4) ቅሬታው የአሦር ሠራዊት ወደ ካራን አፈገፈገ። እነርሱ ይልቁንም ንጉሥ አቆሙ/አነገሡ።

(5) በ608 ፈርዖን ኒካዑ II (II ነገሥት 23:29) ወደ ሰሜን አቀና የአሦርን ሠራዊት ቅሬታዎች ለመርዳት፣ ነጻ ቀጣና ለማቋቋም ዓላማ፣ እየተነሣ ያለውን የባቢሎንን ኃይል በመቀናቀን። ኢዮስያስ፣ መልካሙየይሁዳ ንጉሥ (II ነገሥት 23)፣ የግብፅ ሠራዊት በፍልስጥኤም ውስጥ መንቀሳቀሱን ተቃወመ። ሜጊዶ ላይ መጠነኛ ግጭት ተካሄደ። ኢዮስያስ ቆስሎ ሞተ (II ነገ. 23:29-30)። ልጁንም ኢዮአክስን አነገሡት። ፈርዖን ኒካዑ II እጅግ ዘግይቶ ደረሰ፣ የአሦር ኃይላት በካራን ላይ የሚያደርሱትን ጥፋት ለማስቆም። እሱም የባቢሎንን ኃይላት ገጠመ፣ በመስፍኑ በናቡከደነፆር II የሚመሩትን፣ እናም በከፋ ሁኔታ ድል ሆነ፣ በ605 ቅ.ል.ክ. ከርከሚሽ ላይ፣ ኤፍራጥስ ወንዝ።

እሱም ወደ ግብፅ የመልስ ጉዞ በሚያደርግበት ወቅት ኢየሩሳሌምን ቆመና ከተማይቱን በዘበዛት። እሱም ኢዮአክስን ገና በሦስት ወሩ አወረደው። እሱም ሌለኛውን የኢዮስያስ ልጅ ኤልያቄምን በዙፋኑ ላይ አስቀመጠው ( IIነገሥት 23:31-35)።

(6) ናቡከደነፆር II የግብፅን ሠራዊት ወደ ደቡብ አባረረ፣ በፍልስጥኤም ውስጥ፣ ነገር ግን የአባቱን ሞት በመረዳቱ ወደ ባቢሎን ተመለሰ።

ኋላ ላይ በዛው ዓመት ወደ ፍልስጥኤም ተመለሰ። እሱም ኤልያቄምን በይሁዳ ዙፋን ላይ ተወው፣ ነገር ግን መሪ ከሆኑት ዜጎች ብዙ ሺህዎችን፣ እንዲሁም ከንጉሣውያን ቤተሰብ አባላት በርካቶችን ኢጋዘ። ዳንኤልና ጓደኞቹ ከእነዚህ ግዞተኞች መካከል ናቸው።

መ. 605-562 ናቡከደነፆር II፡

(1) ከ597-538 ባቢሎን ሙሉ ለሙሉ በፍልስጥኤም ቁጥጥር ሥር ነበረች።

(2) በ597 ሌላ ማፈናቀል (ካገር ማስወጣት) ከኢየሩሳሌም ተከሰተ፣ ኤልያቄም ከግብፅ ጋር ባደረገው ኅብረት ምክንያት (II ነገሥት 24)። እሱም ናቡከደነፆር II ከመድረሱ በፊት ሞተ። ልጁ ኢዮአክስ ገና የሦስት ወር ንጉሥ ነበር፣ ወደ ባቢሎን ሲጋዝ። አስር ሺህ ዜጎች፣ ሕዝቅኤልንም ጨምሮ በባቢሎን ከተማ አጠገብ ዳግም ሰፈሩ፣ በካናል ካባር በኩል።

(3) በ586፣ ከግብፅ ጋር በነበረው ቀጣይነት ባለው መነሣሣት/መገፋፋት ምክንያት የኢየሩሳሌም ከተማ ሙሉ ለሙሉ ወደመች (II ነገሥት 25) እናም የብዙ ሰው መፈናቀል ደረሰ። ሴዴቅያስ፣ ኢዮአክስን የተካው ተጋዘ፣ እናም ጎዶልያስ በገዥነት ተሾመ።

(4) ጎዶልያስ በአይሁድ ዓማጽያን ወታደራዊ ኃይላት ተገደለ። እነዚህ ኃይላት ወደ ግብፅ ሸሹ፣ ኤርምያስም አብሯቸው እንዲሄድ አስገደዱት። ናቡከደነፆር ለአራተኛ ጊዜ ወረረ (605፣ 596፣ 586፣582) እናም ያገኛቸውን ቀሪዎቹን አይሁድ በሙሉ አፈናቀላቸው (ካገር አስወጣቸው)።

ሠ. 562-560 ኢቪል- ሜሮዳክ፣ ደግሞም አሜል-ማርዱክ በመባል የሚታወቀው

እሱም ዮአኪምን ከእስር ፈታው ነገር ግን በባቢሎን እንዲቀር ሆነ (II ነገሥት 25:27-30፣ኤር. 52:31).

ረ. 560-556 ነሪግሊሳር

እሱም የናቡከደነፆር የጦር መሪ (ጀነራል) ነበር፣ ኢየሩሳሌምን የደመሰሰ።

ሰ. 556- ላባስኪ-ማርዱክ

እሱ የነሪግሊሳር ልጅ ነበር፣ ነገር ግን ከዘጠኝ ወራት ብቻ በኋላ ተገደለ።

ሸ. 556-539 ናቦኒደስ፡

(1) ናቦኒደስ ከንጉሣውያን ቤት ጋር ዝምድና አልነበረውም፣ ስለዚህ የናቡከደነፆር II ልጅን አገባ።

(2) እሱም አብዛኛውን ጊዜውን ያሳለፈው ለጨረቃ አማልክት (ጣዖት) "ሲን" መቅደስ በመገንባት ነበር፣ ቴማ ላይ። እሱም የዚች ጣዖት ሊቀ ካህኒት ልጅ ነበር። ይህም የማድሩክን፣ የባቢሎንን ዋነኛ ጣዖት ካህናት ጠላትነት አፈራለት።
(3) እሱም አብዛኛውን ጊዜውን ዓመጾችን በማዳፈንና መንግሥቱን በማጠናከር ነበር ያሳለፈው።
(4) እሱም ወደ ቴማ ተንቀሳቅሶ፣ የመንግሥትን ጉዳይ ለልጁ ለብልጣሶር ተወ፣ በዋና ከተማው በባቢሎን (ዳን. 5)።

ቀ. ? – 539 ብልጣሶር (የጋራ አገዛዝ)
የባቢሎን ከተማ እጅግ በፍጥነት ወደቀች፣ በፋርስ ሠራዊት፣ በጉቲዩሙ ጎብርያስ እጅ፣ የኤፍራጥስን ውኃ መስመሩን አዙሮ ወደ ከተማዋ እንዲገባ በማድረግ፣ ያለ ምንም ተቃውሞ። ካህናቱና የከተማይቱ ሕዝብ ፋርሳውያንን እንደ ነጻ አውጭና፣ ማርዱክን እንደሚመልሱ አድርጎ ነው የቆጠራቸው። ጎብርያስ የባቢሎን ገዥ እንዲሆን በቂሮስ II ተሾመ። ጎብርያስ የሜዶኑ ዳርዮስ፣ ዳን. 5፡31፤ 6፡1 ሊሆን ይችላል። "ዳርዮስ" ማለት "የንጉሣዊው" ማለት ነው።

3. የሜዶ-ፋርስ ኢምፓየር፡ የቂሮስ II አነሣስ ጥናት (ኢሳ. 44፡28፤ 45፡1-7)፡
   ሀ. 625-585 ሳያክስረስ የሜዶን ንጉሥ ነበር፣ እሱም ባቢሎን አሦርን ድል እንዲያደርግ የረዳ።
   ለ. 585-550 አስትያገስ የሜዶን ንጉሥ ነበር። ቂሮስ የልጅ ልጁ ነበር፣ ከማንዳኔ።
   ሐ. 550-530 ቂሮስ IIየአንሻሙ፣ ታዛዥ ንጉሥ ነበር፣ ኋላ ላይ ያመጸው፡
      (1) ናቦኒደስ፣ የባቢሎን ንጉሥ፣ ቂሮስን የሚደግፍ።
      (2) ቂሮስ II አስተያገስን ከዙፋን አወረደ።
      (3) ናቦኒደስ የኃይል ሚዛኑን ለማስመለስ ኅብረት ፈጠረ፡
         (ሀ) ከግብፅ
         (ለ) ከክሮሰስ፣ ከልዳ ንጉሥ (ታናሹ እስያ)
      (4) 647- ቂሮስ II ሳርዴስ ላይ ዘመተ (የልዳ ዋና ከተማ)።
      (5) 539- ኅዳር 2፣ የጉቲዩም ጎብርያስ ከቂሮስ ሠራዊት ጋር ባቢሎንን ወሰደ፣ ያለ ምንም መቋቋም/ተቃውሞ። ጎብርያስ የባቢሎን ገዥ ተደረገ።
      (6) 539- በጥቅምት ቂሮስ II "ታላቁ" በግሉ እንደ ነጻ አውጪ ገባ። ለብሔራዊ ቡድኖች ያለው የቸርነት አቋም (ፖሊሲ) የመፈናቀል ዓመታትን ቀይሮ/ገልብጦ ብሔራዊ ፖሊሲ ሆነ።
      (7) 538- አይሁድና ሌሎችም ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ተፈቀደላቸው፣ እንዲሁም የየአገራቸውን መቅደስ ዳግም እንዲገነቡ።
      (8) 530- የቂሮስ ልጅ ካምቢሰስ II ተካው/ወረሰው።
   መ. 530-522 የካምቢሰስ II አገዛዝ
      (1) የግብፅን ኢምፓየር በ525 ቅ.ል.ክ. ከሜዶ-ፋርስ ኢምፓየር ጋር ደመረው፤
      (2) እሱ አጭር አገዛዝ ነበረው፡
         (ሀ) አንዳንዶች ራሱን እንዳጠፋ ይናገራሉ፤
         (ለ) ሔሮዱቱስ የሚለው እሱ በገዛ ራሱ ሰይፍ ራሱን ቆረጠ፣ ፈረሱ ላይ እወጣለሁ ሲል፣ እናም በቁስሉ ምክንያት ሞተ።
      (3) ሕጋዊ ያልሆነ (የሱዶ ስሜርዲስ) አጭር አገዛዝ -522
   ሠ. 522-486 ዳርዮስ I (ሃይስታፒስ) መግዛት ጀመረ
      (1) እሱ የንጉሣዊ ቤተሰብ አልነበረም፣ ወታደራዊ ጀነራል እንጂ።
      (2) እሱ የፋርስን ኢምፓየር አደራጀ፣ ቂሮስ ለሳትራፐስ ያወጣውን ዕቅድ በመጠቀም (ዕዝራ 1-6፤ ሐጌ፤ ዘካርያስ)።
      (3) እሱም እንደ ልዳ የብረት ሳንቲም አዘጋጀ።
   ረ. 486-465 የዘረክሲስ I አገዛዝ፡
      (1) የግብፅን ዓመጽ አከሸፈ
      (2) ግሪክን ለመውረር ፈለገ፣ የፋርስን ሕልም ለማሳካት፣ ነገር ግን በቴርሞፖሊ በ480 ቅ.ል.ክ. እና በሳላሚስ በ479 ቅ.ል.ክ. ውጊያ ድል ሆነ።
      (3) የአስቴር ባል፣ እሱም አሃሹረስ ተብሎ በመጽሐፍ ቅዱስ የሚጠራው፣ በ465 ቅ.ል.ክ. ተገደለ።
   ሰ. 465-424 አርጤክስስ I (ሎንጊማነስ) ነገሠ (ዕዝራ 7-10፤ ነህምያ፤ ሚልክያስ)፡
      (1) ግሪኮች ርምጃቸውን ቀጠሉ፣ ከፔሎፖኒሲአን የርስ በርስ ጦርነት ጋር እስከሚገጥሙ ድረስ
      (2) ግሪክ ተከፋፈለች (አቴናውያን - ፔሎፖኒሲያን)
      (3) የግሪክ የርስ በርስ ጦርነት በ20 ዓመት አበቃ
      (4) በእነዚህ ጊዜያት የአይሁድ ማኅበረሰብ ተጠናከረ
      (5) የዜረክሰስ II እና ሴኪዲያኖስ አጭር አገዛዝ - 423
   ሸ. 423-404 ዳርዮስ II (ኖቶስ) ነገሠ
   ቀ. 404-358 አርጤክስስ II (ምኔሞን) ነገሠ
   በ. 358-338 አርጤክስስ III (ኦኮስ) ነገሠ
   ተ. 338-336 አርሰስነገሠ
   ቸ. 336-331 ዳርዮስ III (ኮዶማኑስ) ነገሠ

4. የግብፅ ጥናት፡
   ሀ. Hyksos (እረኛ ነገሥታት - ሴማዊ ገዥዎች) – 1720/10-1550
   ለ. 18ኛ ሥርወ-መንግሥት (1570-1310)፡
      (1) 1570-1546 አሞሲስ
         (ሀ) ቴብስን ዋና ከተማ አደረገ
         (ለ) ደቡብ ከነአንን ወረረ
      (2) 1546-1525 አሜኖፊስ I (አሜንሆቴፕ I)
      (3) 1525-1494 ቱትሞሲስ I

(4) 1494-1490 ቱትሞሲስ II - የቱትሞሲስ I ልጅ፣ ሃትሺፕሱትን አገባ
(5) 1490-1435 ቱትሞሲስ III (የሃትሺፕሱት የወንድም/እኅት ልጅ)
(6) 1435-1414 አሜኖፊስ II (አሜንሆቴፕ II)
(7) 1414-1406 ቱትሞሲስ IV
(8) 1406-1370 አሜኖፊስ III (አሜንሆቴፕ III)
(9) 1370-1353 አሜኖፊስ IV (አክሄናቴን)
(ሀ) ፀሐይን፣ አቴን ያመልካሉ፣
(ለ) የሊቀ-አማልክት (ጣዖት) አምልኮ አቋቁመዋል (አሀዳዊነት)
(ሐ) ቴል-ኤል-አማርና ፊደላት በዚህ ጊዜ ነበሩ
(10) ? ስሜንክሃሪ
(11) ? ቱታንክሃሙን (ቱታንክሃተን)
(12) ? አይ (አዩ-ኢዩ)
(13) 1340-1310 ሃሬምሃብ

ሐ. 19ኛ *ሥርወ-መንግሥት* (1310-1200):
(1) ? ራምሴስ I (ራምሰስ)
(2) 1309-1290 ሴቲ I (ሴቶስ)
(3) 1290-1224 ራምሴስ II (ራምሰስ II)
(ሀ) ከአርኪዎሎጂ ማስረጃ የዘጸአት ፈርዖንን እጅግ ይመስላል
(ለ) የአቫሪስን፣ ፒቶም እና ራምሴስ ከተሞችን ገንብቷል በሃባሩ (ሴማዊ ወይም ዕብራዊ ሊሆኑ ይችላል) ባሮች
(4) 1224-1216 ማርኒፕታህ (ሜሪንፕታህ)
(5) ? አሜንሜሰስ
(6) ? ሰቲ II
(7) ? ሲፕታህ
(8) ? ቴዎስሬት

መ. 20ኛ *ሥርወ-መንግሥት* (1180-1065):
(1) 1175-1144 ራምሴስ III
(2) 1144-1065 ራምሴስ IV - XI

ሠ. 21ኛ*ሥርወ-መንግሥት* (1065-935):
(1) ? ስሜንደስ
(2) ? ሄሪሆር

ረ. 22ኛ*ሥርወ-መንግሥት* (935-725 - ልብያዊ):
(1) 935-914 ሺሻክ (ሾሴንክ I ወይም ሺሾንግI)
(ሀ) ይሮብአም I ን ጠበቀው/ተከላከለለት እስከ ሰሎሞን ሞት ድረስ
(ለ) ፍልስጥኤምን ድል አደረገ 925 አካባቢ (I ነገ. 14-25፤ II ዜና. 12)
(2) 914-874 ኦሶርኮን I
(3) ? ኦሶርኮን II
(4) ? ሾሽኔክ II

ሰ. 23ኛ *ሥርወ-መንግሥት* (759-715 - ልብያዊ)
ሸ. 24ኛ*ሥርወ-ምንግሥት* (725-709)
ቀ. 25ኛ *ሥርወ-መንግሥት* (716/15-663 - ኢትዮጵያዊ/ኑብያዊ):
(1) 710/09-696/95 ሻባኮ (ሻባኩ)
(2) 696/95-685/84 ሺብቴኮ (ሺቢትኩ)
(3) 690/689፣ 685/84-664 ቲርሃካን (ታሃርቃ)
(4) ? ታንታሙን

በ. 26ኛ *ሥርወ-መንግሥት* (663-525 - ሳይቲክ):
(1) 663-609 ሳሜቲከስ I (ሳምቲክ)
(2) 609-593 ኒኮ II (ኒቾ)
(3) 593-588 ሳሜቲከስ II (ሳምቲክ)
(4) 588-569 አፕሪስ (ሆፍራ)
(5) 569-525 አማሲስ
(6) ? ሳሜቲከስ III (ሳምቲክ)

ተ. 27ኛ*ሥርወ-መንግሥት* (525-401 - ፋርሳዊ):
(1) 530-522 ካምቢሰስ II (የቂሮስ II ልጅ)
(2) 522-486 ዳርዮስ I
(3) 486-465 ዘረክሲስ I
(4) 465-424 አርጤክስስ I
(5) 423-404 ዳርዮስ II

* ለተለያዩ የሁነት ቅደም ተከተላዊ ዝርዝሮች የዞንደርቫንን ሥዕላዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ኢንሳይክሎፔዲያ ቅጽ 2 ገጽ 231 ተመልከት። (*Zondervan's Pictorial Bible Encyclopedia*, vol. 2 p. 23)

5. የግሪክ ጥናት፡
ሀ. 359-336 ፊሊፕ II የመቄዶንያው

(1) ግሪክን ገነባ
(2) በ336 ቅ.ል.ክ. ተገደለ

ለ. 336-323 አሌክሳንደር II "ታላቁ" (የፊሊጵስ ልጅ)፡
(1) የፋርስን ንጉሥ ዳርዮስ IIIን አሰወጣ፣ በኢሱስ ውጊያ
(2) በ323 ቅ.ል.ክ. በባቢሎን በንዳድ (ትኩሳት) ሞተ፣ በ32/33 ዓመት ዕድሜው
(3) የአሌክሳንደር የጦር አዛዦች (ጀነራሎች) ኢምፓየሩን ከፋፈሉ፣ በሞተ ጊዜ፡
(ሀ) ካሴንደር - መቄዶንያ እና ግሪክ
(ለ) ሊሲማኪስ - ትሬሲ
(ሐ) ሴሊዩከስ I - ሶርያ እና ባቢሎን
(መ) ፕቶለሚ - ግብፅ እና ፍልስጥኤም
(ሠ) አንቲጎነስ - ታናሹ እስያ (ብዙም አልቆየ)

ሐ. ሴሊዩሲደስ እና ፕቶለሚስ ፍልስጥኤምን ለመቆጣጠር ተቀናቃኝ ሆኑ፡
(1) ሶርያ (የሴሊዩሲድ ገዥዎች)፡
(ሀ)312-280 ሴለዩከስ I
(ለ) 280-261 አንቲኦከስ I ሶተር
(ሐ) 261-146 አንቲኦከስ II ቲዩስ
(መ) 246-226 ሴለዩከስ II ካሊኒከስ
(ሠ) 226-223 ሴለዩከስ III ሲራዩነስ
(ረ) 223-187 አንቲኦቾስ III ታላቁ
(ሰ) 187-175 ሴለዩከስ IV ፊሎፓቶር
(ሸ) 175-163 አንቲኦከስ IV ኢፒፋነስ
(ቀ) 163-162 አንቲኦቾስ V
(በ) 162-150 ዲሜጥሮስ I
(2) የግብፅ (ፕቶለማይክ ገዥዎች):
(ሀ) 327-285 ፕቶለሚ I ሶተር
(ለ) 285-246 ፕቶለሚ II ፊላዴልፈስ
(ሐ) 246-221 ፕቶለሚ III ኢቪጌተስ
(መ) 221-203 ፕቶለሚ IV ፊሎፓቶር
(ሠ) 203-181 ፕቶለሚ V ኢፒፋነስ
(ረ) 181-146 ፕቶለሚ VI ፊሎሜቶር
(3) አጭር ቅኝት (ዳሰሳ)፡
(ሀ) 301- ፍልስጥኤም በፕሎቶሚ አገዛዝ ሥር ለ181 ዓመታት።
(ለ) 175-163 አንቲኦከስ IV ኢፒፋነስ፣ ስምንተኛው የሴሌዩሲድ ገዥ፣ አይሁድን ካስፈለገ በኃይል ጭምር ሔለናዊ ለማድረግ የፈለገ፡
i. የስፖርት ጨዋታ ስፍራዎችን ገነባ
ii. የአምልኮተ-ባዕድ (ጣዖት) መሠዊያ ለዜውስ ኦሎምፒያስ መቅደስ ገነባ
(ሐ) 168 - ታኅሳስ 13 - በኢየሩሳሌም መሠዊያ ላይ አሳማ ሠዋ፣ አንቲኦቾስ IV ኢፒፋነስ። አንዳንዶች ይሄንን ዳንኤል 8 ላይ ያለው "የጥፋት ርኵሰት" አድርገው ወሰዱት።
(መ) 167 - ማታቲአስ፣ የሞዲን ካህን፣ ልጆቹ ዓመጹ። እጅግ የታወቀው ልጁ ጁዳስ ማካቤስ፣ "ጁዳ መዶሻው" ነው።
(ሠ) 165 - ታኅሳስ 25 - መቅደሱ ዳግም ተመረቀ። ይህም *Hanukkah* ወይም "የብርሃናት በዓል" በመባል ይታወቃል።

6. ለቀናት ችግሮች፣ ደንቦች እና ቅድመ-ግምቶች የተሻለ መግለጫ *የአብራሪዎች/ተንታኞች የመጽሐፍ ቅዱስ ሐተታ*፣ (*The Expositors Bible Commentary,* vol. 4) p. 4 ገጽ 10-17 ተመልከት፡፡

VII. ጽሑፋዊ ምድቦች (ዐውደ-ጽሑፍ)

ሀ. ግልጽ የሆነ የመረጃ ፎርጅ አለ፣ ደራሲው ስለ እያንዳንዱ የሰሜን እና ደቡብ ንጉሥ የሚሰጠው። ዘወትርም የይሁዳ ነገሥታት መረጃ የተሟላ ነው (ከዶር. ሁይ ኤስደብሊዩቢቲኤስ የማስተማርያ ማስታወሻ የተወሰደ)፡

1. የነገሥታቱ የግዛት ጊዜ ከተቃራኒ ጥንዱበሰሜን ወይም ደቡብ በትይዩ ተቀምጧል፤
2. የንጉሡ ስም፤
3. የአባቱ ስም፤
4. ወደ ሥልጣን ሲመጣ ዕድሜው፤
5.የግዛት ዘመኑ ርዝማኔ፤
6. የመኖርያ ስፍራ፤
7.የእናቱ ስም፤
8. ስለ አገዛዙ አንዳንድ መረጃ፤
9. ስለ ሕይወቱ የማጠቃለያ መግለጫ፤
10. ስለ አሟሟቱና ቀብሩ ጽሑፍ፤
11. ዘወትር ቁ. 4 እናቁ.7 የእስራኤልነገሥታት ተገድፏል

ለ. በርከት ያሉ የተለያዩ መንገዶች አሉ፣ ይሄንን ረጅም ታሪካዊ ነገር የፍሬ ሐሳብ ዝርዝር በአጭሩ ለማዘጋጀት፡
1. በዋነኛ ገጸ ባሕርያት፡
ሀ. ዳዊት/ሰሎሞን
ለ. ሮቦአም/ጀሮቦአም I
ሐ. አክአብ (ኤልዛቤል) /ኤልያስ
መ. ኤልያስ/ኤልሳዕ

ሠ. ሕዝቅያስ/ኢሳይያስ
ረ. ኢዮስያስ/ፈርዖን ኒካው
ሰ. ኢዮአቄም/ኢዮአኪን/ናቡከደነፆር

2. በተካተቱበት *መንግሥታት*፡
ሀ. የተባበረው *ሥርወ-መንግሥት*
ለ. እስራኤል/ይሁዳ
ሐ. ሶርያ
መ. አሦር
ሠ. ባቢሎን

ሐ. ለተብራራ የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር፡
1. E.J. Young, *An Introduction to the Old Testament*, pp.190-200
2. R.K. Harrison, *Introduction to the Old Testament*, pp.720-721
3. NIV Study Bible, pp. 468-469

VIII. *ዋነኛ ሐቆች*

*ሀ.* ይህ የምዕራባውያን ታሪክ አይደለም፣ ነገር ግን የጥንታዊ ቅርብ ምስራቃዊ *ሥነ-መለኮታዊ ታሪክ* እንጂ፡
1. የሰሜን *ነገሥታት* ሁሉ ተኮንነዋል/ተወግዘዋል፣ በይሮቦአም I በተቀመጡት የወርቅ ጥጆች ምክንያት፣ ያህዌን እንዲወክሉ።
2. ሁለቱ እጅግ ጠንካራ የሰሜን *መሪዎች*፣ ኦምሪ እና ይሮቦአም II በአጭር መልኩ ቀርበዋል፣ እናም የእነርሱ ፖለቲካዊም ሆነ ወታደራዊ ክንውኖች/ስኬቶች ፈጽሞ አልተጠቀሱም።
3. ሁለቱ ደቡባዊ *ነገሥታት* እጅግ በተብራራ/በተጠናከረ መልኩ የቀረቡት ሕዝቅያስ እና ኢዮስያስ ናቸው። እነርሱ በከበረ መልክ የቀረቡት ለሙሴያዊው ኪዳን ባላቸው *ታማኝነት* እና ባደረጉት የመንፈሳዊ ተሐድሶ ሙከራ ነው።
4. ሌለኛው ብቸኛ የተጠናከረ ማብራሪያ የተቀበለ ንጉሥ ምናሴ፣ የሕዝቅያስ ልጅ ነው። ነገር ግን ይህ የአባቱ ተቃራኒ ስለሆነ ነው፣ ሕዝቡንም ወደ ታላቅ *ኃጢአት* የወሰደ።

ለ. *ነገሥት* የሳሙኤልን ጭብጥ ይቀጥላል። እነርሱ የዘመኑን ነጠላ/አንድ ወጥ ታሪክ ያበጃሉ። ትንቢታዊነት በክህነት ላይ *መግኑን* ቀጥሏል። ጽሑፋዊ ያልሆኑት ነቢያት፣ ኤልያስና ኤልሳዕ የI እና II *ነገሥትን ሙሉውን* አንድ *ሦስተኛ* ሸፍነዋል!

ሐ. ነገሥት የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከሙሴያዊ ኪዳን እየጨመረ ያለውን *ማፈንገጥ* ያሳያል። ይህም በመዳረሻው የሰማርያን ውድቀት አምጥቷል (722 ቅ.ል.ክ.)እንዲሁም የኢየሩሳሌምን ውድቀት (586 ቅ.ል.ክ.)። ይህም በያህዌ ድክመት ምክንያት አይደለም፣ ነገር ግን በሕዝቡና በመሪዎቻቸው *ኃጢአት* እንጂ! የኪዳን *ታማኝነት* ዋነኛው ጉዳይ ነው። እግዚአብሔር *ታማኝ* ነው! ሰሎሞን፣ ይሁዳ እና እስራኤል *ታማኝ* አልነበሩም!

IX. *ቃላት* እና/ወይም *ሐረጋት* እና ሰዎች በአጭሩ የሚገለጹ

*ሀ.* I *ነገሥት*፡
1. *ቃላት* እና *ሐረጋት*፡
*ሀ.* "ሕያው እግዚአብሔርን፣" 1፡29 (NASB እና NIV)
ለ. "በበቅሎዬ ላይ አስቀምጡት፣" 1:33 (NASB እና NIV)
ሐ. "የመሠዊያውንም ቀንድ ያዘ፣" 1:50፤ 2:28 (NASB እና NIV)
መ. ጃኪን/ያቁም እና ቦአዝ/በለዝ፣ 7:21 (NASB እና NIV)
ሠ. "እጆቹን ዘረጋ፣" 8:22 (NASB እና NIV)
ረ. "ታናሽቱ ጣቴ ከአባቴ ወገብ ትወፍራለች" 12:10 (NIV፣ "...ከአባቴ ወገብ ትወፍራለች")
ሰ. የወርቅ ጥጆች፣ 12:28 (NASB እና NIV)
ሸ. "በመሠዊያው ዙሪያ እያሸበሸቡ...ገላቸውን እየቧጩሩ/እየቆረጡ" 18:26፣28 (NIV፣ "እየጨፈሩ...እና እየቧጨሩ...")
ቀ. "መሥዋዕተ-ሠርክ በሚቀርብበት ጊዜ፣" 18:36 (NIV፣ "በመሥዋዕት ማቅረቢያ ጊዜ")
በ. "ትንሽ የዝምታ ድምጽ" 19:12 (NIV፣ "ትንሽ የሹክሹክታ ድምጽ")

2. ሰዎች በአጭሩ የሚገለጹ፡
*ሀ.* አቢሳ፣ 1፡3
ለ. ሳሚ፣ 2፡8
ሐ. ኪራም፣ 5፡1፣ 7፡13
መ. የሳባ *ንግሥት*፣ 10:10
ሠ. አስታሮት፣ 11:5
ረ. ሞሎክ፣ 11:7
ሰ. ሺሻቅ፣ 11:40
ሸ. ዘምሪ፣ 16:16
ቀ. ናቡቴ፣ 21/20:1
በ. ሚኪያስ፣ 22:24

ለ. II *ነገሥት*
1. *ቃላት* እና *ሐረጋት*፡
*ሀ.* "የእሳት ሰረገላና የእሳት ፈረሶች፣" 2:11፤ 6:17 (NASB እና NIV)

ለ. "በእግዚአብሔርም ፊት ክፉ አደረገ" 3:2 (NIV፣ "...ዓይኖች ፊት...")
ሐ. "ወገብህን ታጠቅ" 4:29 (NIV፣ "ልብስህን በቀበቶ ታጠቅ")
መ. "የርግብ ኩስ" 6:25 (NIV፣ "ወፍ አራሽ (ኩስ)")
ሠ. "ሙሴ የሠራውን የናሱን እባብ፣" (*nehshtan*) 18:4 (NASB እና NIV)
ረ. "ኩሬውንና መስኖውን ሠራ" 20:20 (NIV፣ "...ቦይ/መፋሰሻ")
ሰ. "የሰማይ ሠራዊት" 21:3 (NIV፣ "የኮከብ ሠራዊት")
ሸ. "የሕጉን መጽሐፍ፣" 22:8 (NASB እና NIV)
ቀ. ቶፌት፣ 23:10 (NASB እና NIV)
በ. "የናስ ኩሬ፣" 25:13 (NASB እና NIV)

2. ሰዎች፣ በአጭሩ የሚገለጹ፡
ሀ. ግያዝ፣ 4፡11
ለ. ንዕማን፣5:1
ሐ. ጎቶልያ፣ 11:1፣ 3
መ. ፎሐ፣ 15:19
ሠ. ሰናክሬም፣ 18:13
ረ. ምናሴ፣ 21:1
ሰ. ሕልዳና፣ 22:14
ሸ. ኒካው፣ 23:29
ቀ. ዮአኪን፣ 24:8
በ. ሠራያ፣ 25:18
ተ. ጎዶልያስ፣ 25:22

X. የካርታ ስፍራዎች/አመላካቾች (በቁጥር)

ሀ. I ነገሥት፡

1. ዓይንሮጌል፣ 1፡9 (ኢየሩሳሌም)
2. ግዮን፣ 1:33 (ኢየሩሳሌም)
3. አናቶት፣ 2:26
4. የግብፅ ወንዝ፣ 8:65 (NIV፣ "የግብፅ ፈፋ")
5. መጊዶ፣ 9:15
6. ዔጽዮንጋብር፣ 9:26
7. ሴኬም፣ 12:1
8. ጵኒኤል፣ 12:25
9. የቄድሮን ፈፋ፣ 15:13 (NIV፣ "የቄድሮን ሸለቆ")
10. ቺነሬት፣ 15:20 (NIV፣ "ኪኔሬት")
11. ሰማርያ፣ 16:24
12. ቀርሜሎስ ተራራ፣ 18:20
13. ቂሶን ወንዝ፣ 18:40 (NIV፣ "ቂሶን ሸለቆ")
14. ኢይዝራኤል፣ 18:45

ለ. II ነገሥት


1. አቃሮን፣ 1:2
2. አባናና ፋርፋ ወንዞች፣ 5:12
3. ዶታይን፣ 6:13
4. ሴላ፣ 14:7
5. ኤላት፣ 14:22
6. ለኪሶ፣ 18:14
7. በሄኖም ልጆች ሸለቆ፣ 23:10 (NIV፣ "...በቤን ሄኖም")
8. መጊዶ፣ 23:30
9. ሪብላ፣ 25:6


XI. የተማሪ ይዘት ጥያቄዎች

ሀ. I ነገሥት፡
1. በዳዊት ቤተሰብ ላይ እጅግ የበዛ መከራ የመጣበትን ምክንያት ጥቂቱን ዘርዝር።
2. ሰሎሞን እጅግ የበዙ ሚስቶች ስለምን ኖሩት? እነርሱስ በዕርጅና ዘመኑ እንዴት ተጽዕኖ (ጉዳት) አሳደሩበት?
3. ለመቅደሱ እጅግ ሰፊ ስፍራና ዝርዝር መግለጫ ለምን ተሰጠው?
4. የተባበረው መንግሥት ለምን ተለያየ?
5. የበአልን/አሼራህ አምልኮን ግለጽ።
6. የ22፡18-23 ሥነ-መለኮታዊ አንድምታዎች ምንድናቸው?

ሰ. II ነገሥት፡

1. የ5፡15-18 አንድምታዎች ግለጽ።
2. የ19፡19 አንድምታዎች ግለጽ።
3. የሕዝቅያስን ጥንካሬዎች እና የምናሴን ኃጢአት ዘርዝር።
4. “የሕጉን መጽሐፍ አገኘሁት” የሚለው ሐረግ (22፡8)፣ ምንድነው የሚጠቅሰው?
5. የያህዌ ኪዳን ሁኔታዊ ነው ወይስ ሁኔታዊ አይደለም?


ANCIENT
NEAR EAST
N
S
E
W


PALESTINE
0 10 20 30 40
SCALE IN MILES

# የተከፋፈለው ንጉሣዊ መንግሥት ነገሥታት

**የይሁዳ ነገሥታት (1 ዜና . 3:1-16 ፤ማቴ. 1:6-11)**

| ስምና ጊዜው | ብራይት | ያንግ | ሃሪሰን | የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎች |
|---|---|---|---|---|
| ሮብዓም | 922-915 | 933-917 | 931/30-913 | 1 ነገሥ. 11:43-12:27፤ 14:21-31<br>II ዜና. 9:31-12:16 |
| አብያህ(አብያም) | 915-914 | 916-914 | 913-911/10 | 1 ነገሥ. 14:31-15:8<br>II ዜና. 11:20፣22 |
| አሳ | 913-873 | 913-873 | 911/10-870/69 | 1 ነገሥ. 15:8-30፤ 16:8፣10፣<br>23፣29፤ 22:41፣43፣46<br>ኤር. 41:9 |
| ኢዮሳፍጥ | 873-849 | 873-849 | 870/69-848 | 1 ነገሥ. 15:24፤ 22:1-51<br>II ነገሥ. 3:1-12፤ 8:16-19<br>1 ዜና. 3:10<br>II ዜና. 17:1-21:1 |
| (ኢዮራም የጋራ አገዛዝ) | ............ | .............. | 853-848 | 1 ነገ. 22:50<br>II ነገ. 1:17፤ 8:16፤ 12:18 |
| ኢዮራም (ጆራም) | 849-842 | 849-842 | 848-841 | 1 ዜና. 221:1-20<br>ማቴዎስ 1:8 |
| አካዝያስ | 842 | 842 | ................. | II ነገሥ. 8:24-9:29<br>II ነገሥ. 22:1-9 |
| ጎቶልያ<br>(ንግሥት) | 842-337 | 842-836 | 841-835 | II ነገሥ. 8:26፤ 11:1-20<br>II ዜና. 22:2-23:21 |
| ኢዮአስ (ጄሆአሽ) | 837-800 | 836-797 | 835-796 | II ነገሥ. 11:2-3፤ 12:1-21<br>II ዜና. 22:11-12፤ 24:1-27 |

**የእስራኤል ነገሥታት**

| ስምና ጊዜው | ብራይት | ያንግ | ሃሪሰን | የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎች |
|---|---|---|---|---|
| ኢዮርብዓም 1 | 922-901 | 933-912 | 931/30-910/09 | 1 ነገሥ. 11:26-40፤ 12:12-14፡20 |
| ናዳብ | 901-900 | 912-911 | 910/09-909/08 | 1 ነገሥ. 14:20፤ 15:25-31 |
| ባኦስ | 900-877 | 911-888 | 909/08-886/85 | 1 ነገሥ.15:16-16:7፤ II ነገሥ.9:9<br>II ዜና. 16:1-6<br>ኤር. 41:9 |
| ኤላ | 877-876 | 888-887 | 886/85-885/84 | 1 ነገሥ. 16:8-14 |
| ዘምሪ<br>(የሠራዊት ጀነራል) | 876 | 887 | 885/84 | 1 ነገሥ. 16:9-20<br>II ነገሥ. 9:31 |
| አምሪ<br>(የሠራዊት ጀነራል) | 876-869 | 887-877 | 885/84-874/73 | 1 ነገሥ. 16:15-28<br>II ነገሥ. 8:26<br>ሚክያስ 6:16 |
| አክአብ | 869-850 | 876-854 | 874/73-853 | 1 ነገሥ. 16:29-22:40 |
| አካዝያስ | 850-849 | 854-853 | 853-852 | 1 ነገሥ. 22:40፣41፣49፣51-53<br>II ዜና. 18:1-3፣19 |
| ኢዮራም<br>(ጆራም) | 849-842 | 853-842 | 852-841 | II ነገሥ. 1:17፤ 3:1-27፤ 8:16-<br>9:29 |
| ኢዩ<br>(የሠራዊት ጀነራል) | 842-815 | 842-815 | 841-814/13 | 1 ነገሥ. 19:16-17<br>II ነገሥ. 9:1-10:36፤ 15:12<br>II ዜና. 22:7-9<br>ሆሴዕ 1:4 |

**የይሁዳ ነገሥታት (1 ዜና . 3:1-16 ፤ማቴ. 1:6-11) [የቀጠለ]**

| ስምና ጊዜው | ብራይት | ያንግ | ሃሪሰን | የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎች |
|---|---|---|---|---|
| አሜስያስ | 800-783 | 797-779 | 796-767 | II ነገሥ. 12:21፤ 14:1-22<br>II ዜና. 25:1-28 |
| (ዓዛርያስ የጋራ አገዛዝ) | ---------- | --------- | 791/90-767 | II ነገሥ. 14:21፤ 15:1-7 |
| ዖዝያን (አዛርያ) | 783-742 | 779-740 | 767-740/39 | II ዜና. 26:1-23<br>ሆሴዕ 1:1፤አሞጽ 1:1<br>ዘካርያስ 14:5 |
| (ኢዮአታም የጋራ አገዛዝ) | 750-742 | --------- | 750-740/39 | |
| ኢዮአታም | 742-735 | 740-736 | 740/39-732/31 | II ነገሥ.15:7፣32-38<br>1 ዜና. 5:17 |


**የእስራኤል ነገሥታት [የቀጠለ]**


| ስምና ጊዜው | ብራይት | ያንግ | ሃሪሰን | የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎች |
|---|---|---|---|---|
| ኢዮአካዝ | 815-801 | 814-798 | 814/13-798 | II ነገሥ. 10:35፤ 13:1-9 |
| ዮአስ | 801-786 | 798-783 | 798-782/81 | II ነገሥ. 13:9-13፣25<br>II ዜና. 25:17-25<br>ሆሴዕ 1:1፤አሞጽ 1:1 |
| (ይሮ. II የጋራ አገዛዝ) | --------- | -------- | 793/92-782/81 | II ነገ. 13:13፤ 14:16፣23-29<br>ሆሴዕ 1:1 |
| ይሮቦአም II | | | | |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | II ዜና. 26:23-27:9<br>ኢሳ. 1:1፤ 7:1<br>ሆሴዕ 1:1፤ሚክያስ 1:1 | | 786-746 | 783-743 | 782/81-753 | አሞጽ 1:1፤ 7:9-11 |
| (አካዝ የጋራ አገዛዝ) | ---------- | ---------- | 744/43-732/31 | II ነገ. 15:30-16:20<br>II ዜና. 27:9-28:27 | ዘካርያስ | 746-745 | 743 | 753-752 | II ነገሥ.15:8-12 |
| አካዝ | 735-715 | 736-728 | 732/31-716/15 | ኢሳ. 1:1፤ 7:1፤ 14:28፤ 38:8<br>ሆሴዕ 1:1፤ሚክያስ 1:1 | ሰሎም | 745 | 743 | 752 | II ነገሥ. 15:10፥13-15 |
| (ሕዝቅያስ የጋራ አገዛዝ) | --------- | ---------- | 729-716/15 | II ነገ. 16:20፤ 18:1-20፥21<br>II ዜና. 28:27-32:33<br>ምሳ. 25:1 | ምናሔ | 745-738 | 743-737 | 752-742/41 | II ነገሥ. 15:14፥16-22 |
| ሕዝቅያስ | 715-687 | 727-699 | 716/15-687/86 | ኢሳ. 1:1፤ 36:1-39:8<br>ሆሴዕ 1:1፤ሚክያስ 1:1<br>ማቴ. 1:9-10 | ፋቂስያስ | 738-737 | 737-736 | 742/41-740/39 | II ነገሥ. 15:23-26 |
| (ምናሴ የጋራ አገዛዝ) | --------- | -------- | 696/95-687/86 | II ነገ. 20:21-21:18፤<br>23:12፥26፤ 24:2 | ፋቁሔ | 737-732 | 736-730 | 740/39-732/31 | II ነገሥ. 15:27-31፤ 16:5<br>II ዜና. 28:6፤ኢሳ. 7:1 |
| ምናሴ | 687/86-642 | 698-643 | 687/86-642/41 | II ዜና. 32:33-33:20<br>ኤር. 15:4፤ II ነገ. 21:18-26 | ሆሴዕ | 732-724 | 730-722 | 732/31-723/22 | II ነገሥ. 17:1-18 |
| አሞን | 642-640 | 643-641 | 642/41-640/39 | II ዜና. 33:20-25<br>ኤር. 1:2፤ሶፎ. 1:1<br>I ነገሥ. 13:2-3 | የሰማርያ በአሦር እጅ መውደቅ | 724 ቅ.ል.ክ | 722 ቅ.ል.ክ | 722 ቅ.ል.ክ | |

| የይሁዳ ነገሥታት (የቀጠለ) | | | | | የእስራኤል ነገሥታት (የቀጠለ) | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ስምና ጊዜው | ብራይት | ያንግ | ሃሪሰን | የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎች | ስምና ጊዜው | ብራይት | ያንግ | ሃሪሰን | የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎች |
| ኢዮስያስ | 610-609 | 640-609 | 640/39-609 | II ነገ. 21:24፤ 22:1-23:30<br>II ዜና. 33:25-35:27<br>ኤር. 1:2፤ሶፎ. 1:1<br>ማቴ. 1:10-11 | | | | | |
| ኢዮአክስ | 609<br>(3 ወር) | 609 | 609 | II ነገሥ. 23:30-34<br>II ዜና. 36:1-4 | | | | | |
| ኢዮአቄም | 609-598 | 609-598 | 609-597 | II ነገሥ. 23:34-24:6፥19<br>II ዜና. 36:4-8<br>ኤር. 1:3፤ 22:18-23፤ 25:1፤<br>26:1፤ 27:1፤ 35:1፤<br>36:1<br>ዳን. 1:1-2 | | | | | |
| ዮአኪን | 598/97<br>(3 ወር) | 598 | 597 | II ነገ. 24:6፥8-17፤ 25:27-30<br>II ዜና. 36:8-9<br>ኤር. 52:31፤ሕዝ. 1:2 | | | | | |
| ሴዴቅያስ | 597-586 | 598-587 | 597-587 | II ነገሥ. 24:17-25:7<br>II ዜና. 36:10-11<br>ኤር. 1:3፤ 21:1-7፤ 24:8-10፤ 27:1፤ 32:4-5፤ 34:1-22፤ 37:1-39:7፤ 52:1-11<br><br>ሰቆቃወ ኤርምያስ | | | | | |
| የኢየሩሳሌም በባቢሎን እጅ መውደቅ | 586 ቅ.ል.ክ | 587 ቅ.ል.ክ | 587 ቅ.ል.ክ | | | | | | |

በቀናት አቆጣጠር ባለው ችግር ላይ ለተሻለ ማብራሪያ ኢ.አር. ቴይሊ፣ *የዕብራውያን ነገሥታት ምሥጢራዊ ቁጥሮች* ተመል


ANCIENT
NEAR EAST
N
S
E
W


PALESTINE
0 10 20 30 40
SCALE IN MILES

# I እና II ዜና መዋዕል መግቢያ

I. የመጽሐፉ ስም

ሀ. የመጽሐፉ ስም በዕብራይስጥ "ቃላት /ሁነቶች/ የቀናቱ /ዓመታቱ/" የሚል ነው፡፡ ይህም የዓመታቱ ዜና መዋዕል በሚል መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ ይመስላል፡፡ እነዚሁ ተመሳሳይ ቃላት በአንዳንድ መጻሕፍት ርዕስነት ተከስተዋል፣ በI ነገሥት 14:19፣29፤ 15:7፣23፣31፤ 16:5፣14፣20፣ 27፤ 22:46.ላይ እንደተጠቀሱት የጽሑፍ ምንጮች፡፡ ሐረጉ ራሱ ከሠላሳ ጊዜ በላይ ጥቅም ላይ ውሏል፣ በI እና II ነገሥት፣ እናም ዘወትር "ዜና መዋዕል" በሚል ይተረጎማል፡፡

ለ. LXX እሱን ርዕስ ያደረገው "የተገደፉ/የተተዉ ነገሮች በሚል ነው፣ /የይሁዳ ነገሥታትን በተመለከተ፡፡" ይህም የሚያመለክተው ዜና መዋዕል ለሳሙኤል እና ነገሥት መሆኑን፣ የዮሐንስ ወንጌል ደግሞ ለሲኖፕቲክ/ቀዳሚዎቹ ወንጌላት እንደሆነ፡፡

ሐ. ጀሮም በላቲን ትርጉሙ፣ በቫልጌት ርዕስ የሰጠው "የሙሉው ቅዱስ ታሪክ ዜና መዋዕል" በሚል ነው፣ ምክንያቱም የዘር ሐረጉ ወደ ኋላ ተመልሶ ወደ አዳም በመሄዱ እና ተጓዳኝ መጻሕፍት የሆኑት ዕዝራ/ነህምያ ከድኅረ-ግዞት ጊዜ ጋር ስለሚዛመዱ፡፡

መ. 1 እና 2 ዜና መዋዕል በዕብራይስጥ በመጀመሪያ አንድ መጽሐፍ ነበሩ፣ በLXX ነው የተከፋፈሉት፣ ሳሙኤልና ነገሥት እንደተደረጉት፡፡

II. ቅዱስ ቃላዊነቱ

ሀ. ይህ የመጨረሻው መጽሐፍ ነው፣ የዕብራይስጥ ካኖን "የጽሑፎች" ምድብ፡፡ ይህ ማለት የዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻ መጽሐፍ ነው ማለት ነው፡፡

ለ. የእሱ አቀማመጥ በዕብራይስጥ ካኖን የሚያመለክተው፡
1. ኋለኛ የጽሑፍ ቅንብር መሆኑን፤
2. አጠቃሎሻዊ ባሕርዩን
3. እንደ ዕዝል መታየቱን
4. በቅዱስ ቃልነት ኋላ ላይ ተቀባይነት ማግኘቱን፡፡

ሐ. LXX እሱን የሚያስቀምጠው ከነገሥት ኋላና ከዕዝራ በፊት ነው፡፡ ዕዝራ/ነህምያ ከዜና መዋዕል ቀድመው መቀመጣቸው የሚያስገርም ነው፣ የዚህ ምክንያት ሊሆን የሚችለውም ከዜና መዋዕል የአጠቃሎሽነት ባሕርይ ወይም በአዎንታዊ ማስታወሻ በመጨረሱ ይሆናል፡፡

III. ዘውግ

ሀ. ይህ መጽሐፍ ታሪካዊ ትርክት ነው፣ ነገር ግን ተለይቶ በተመረጠ ሥነ-መለኮታዊ መልኩ፡፡

ለ. እሱም አብዛኛዎቹን የአገዛዞቹን አሉታዊ ገጽታዎች አስወግዷል፡ የ
1. ዳዊት
2. ሰሎሞን
3. "መልካሞቹ" የይሁዳ ነገሥታት፡
   ሀ. አሳ
   ለ. ኢዮሳፍጥ
   ሐ. ኦዝያ
   መ. ሕዝቅያስ
   ሠ. ኢዮስያስ

IV. ደራሲነት

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ደራሲው የሚለው የለም፡፡

ለ. ባባ ባትራ 15ሀ እንደሚለው ዕዝራ የዜና መዋዕልን የትውልድ ዘር ግንድ ለገዛ ራሱ እንደ ጻፈ ነው፡፡ ይህም በሁለት መንገዶች ተተርጉሟል፡
1. ዕዝራ ዜና መዋዕልን ጽፏል
2. ዕዝራ በዜና መዋዕል የተጀመረውን ታሪክ አጠናቋል፣ በገዛ ራሱ ጊዜ

ሐ. ዕዝራ 1፡1-4 እና II ዜና መዋዕል 36:22-23እጅግ ተመሳሳይ ናቸው፣ በዕብራይስጥ፡፡ ሁለቱም ያንግ እና ሀሪሰን የሚሉት ዜና መዋዕል ቀድሞ እንደ ተጻፈ ነው፡፡ ይህም በከፊል ተረጋግጧል፣ በባቢሎናውያን ጸሐፍት የአጻጻፍ ዘዴ፣ ሁለት ሥራዎችን አንድ ላይ በማያያዝ፣ "በማያያዣ-መስመር /ሐረግ" ወይም ተምሳሌት፡፡ ዘዴው በራቢያዊ ጽሑፎች ላይ አይታይም፡፡ ይህም የሚያመለክተው ዕዝራ፣ ዜና መዋዕልን እንደ ታሪካዊ መግቢያ መጠቀሙን ነው፣ ለገዛ ራሱ ሥራ፣ ይኸውም የአይሁድን ሕዝብ ታሪክ መጻፉን ለመቀጠል፡

መ. የዜና መዋዕል ደራሲ /ዎች/ እና ዕዝራ/ነህምያ ተመሳሳይ ሥነ-መለኮታዊ መሻትና አስተሳሰብ አላቸው፡
1. በቤተ-መቅደስና በክህነት ላይ ያተኩራሉ /በተለይም በሌዋውያን ዝርዝር/
2. የስታስቲካዊ መዝገቦችንና የየትውልዶች የዘር ሐረግን በጣም ይጠቀማል
3. ቃላቱና ጽሑፋዊ ስልቶቹ ተመሳሳይ ናቸው
4. መባል የሚቻለው፣ እነርሱ የሚለዩበት፡
   ሀ. ስሞችን በተለየ ፊደል መጻፋቸው
   ለ. ዜና መዋዕል በዳዊት የንግሥና መስመር ላይ ሲያተኩር፣ ዕዝራ/ነህምያ በሙሴ ኪዳን ላይ መሆኑ

ሠ. ዊሊያም ኦልብራይት ደራሲነቱን የሰጠው ለዕዝራ ነው፣ በ428 እና 397 ቅ.ል.ክ መካከል፡፡ የዕዝራ ተሐድሶ በዕዝራ 7-10 ላይ የሚገኘው በ458-457 ቅ.ል.ክ ተከስቷል፣ በአርጤክስስ I በኩል፡፡

ረ. ዜና መዋዕል በርካታ ምንጮችን ይጠቀማል፡
1. ቀደም ብለው የተጻፈውን ቅዱስ ቃል፡
ሀ. ዜና መዋዕል ግማሹን ሳሙኤልንና ነገሥትን ይጠቀማል፣ ቢያንስ ተመሳሳይ ምንጮችን
ለ. I ዜና መዋዕል አንዳንድ የብኪ ጽሑፎችን ለይቶ የሚያውቅ ይመስላል፡
(1) ዘፍ. 35:22 -- 5:1
(2) ዘፍ. 38:7 -- 2:3
(3) ዘፍ. 38:30 -- 2:4፣6
(4) ዘፍ. 46:10 -- 4:24
(5) ዘፍ. 46:11 -- 6:16
(6) ዘፍ. 46:13 -- 7:1
(7) ዘፍ. 46:21 -- 7:6፣12
(8) ዘፍ. 46:24 -- 7:13
(9) ሩት 4:18-21 -- 2:11-13
(10) I ሳሙ. 27:10 -- 2:9፣ 25-26
(11) I ሳሙ. 31:1-6 -- 10:1-12
ሐ. NIVየጥናት መጽሐፍ ቅዱስ የዜና መዋዕል መግቢያ እንደ ምንጭነት የሚያካትታቸው፡
(1) ፔንታቲዩች
(2) መሳፍንት
(3) ሩት
(4) I ሳሙኤል
(5) ነገሥት
(6) መዝሙር
(7) ኢሳይያስ
(8) ኤርምያስ
(9) ሰቆቃው-ኤርምያስ
(10) ዘካርያስ

2. የተጻፉ ታሪካዊ ሰነዶች፣ ከተከፋፈለው መንግሥት፡፡
ሀ. ይፋዊ የቤተ-መንግሥት ሰነድ ሊሆኑ የሚችሉት፡
(1) የንጉሥ ዳዊት ዜና መዋዕል፣ I ዜና. 27:24
(2) የይሁዳ እና የእስራኤል ነገሥታት መጽሐፍ፣ II ዜና. 16:11፤ 25:26፤ 28:26፤ 32:32
(3) የእስራኤል እና የይሁዳ ነገሥታት መጽሐፍ፣ II ዜና. 27:7፤ 35:27፤ 36:8
(4) የእስራኤል ነገሥታት መጽሐፍ፣ Iዜና. 9:1፤ II ዜና. 20:34
(5) የእስራኤል ነገሥታት ቃል፣ II ዜና. 24:27፤ 33:18
ለ. ነቢያት፤
(1) የንጉሥ ዳዊት ሥራ፣ I ዜና. 29:29:
(ሀ) የሳሙኤል፣ ነቢዩ ዜና መዋዕል
(ለ) የነቢዩ ናታን ዜና መዋዕል
(ሐ) የጋድ፣ ነቢዩ ዜና መዋዕል፡፡
(2) የሰሎሞን ሥራ፣ II ዜና. 9:29:
(ሀ) የነቢዩ ናታን ማስታወሻዎ /ጽሑፎች/
(ለ) የሲሎናዊውአሂኛ ትንቢት
(3) የይሮብአም I ሥራ፣ በነቢዩ ኢዶ ራዕይ፣ II ዜና. 9:29
(4) የሮቦአም ሥራ፣ II ዜና. 12:15 ላይ:
(ሀ) የነቢዩ ሼማያህ መዛግብት /ማስታወሻዎች
(ለ) ኢዶ ነቢዩ
(5) የአቢጃ ሥራ II ዜና. 13:22 ላይ በነቢዩ ኢዶ
(6) የኢዩ ሥራ II ዜና. 20: 34 ላይ በሀናኒ ልጅ
(7) የምናሴ ሥራ II ዜና. 33:19 ላይ በሆዛይ (LXX "ነቢዩ")
ሐ. ነገዳዊ የትውልድ መዛግብት:
(1) ስምዖን፣ I ዜና. 4:33
(2) ጋድ፣ I ዜና. 5:17
(3) ቢንያም፣ 7:9
(4) አሴር፣ 7:40
(5) እስራኤል ሁሉ፣ 9:1
(6) ሌዋውያን በረኞች /በር ጠባቂዎች/፣ 9:22 (አንድምታው የሚሆነው እናንዳንዱ የሌዋውያን ምድብ መዛግብት እንደሚኖሩት ነው [1 ዜና. 23:1፤ 28:13፤ II ዜና. 35:4])፡፡
መ. የውጭ ምንጮች:
(1) የሰናክሬ ደብዳቤዎች፣ II ዜና. 32:17-70
(2) የቂሮስ አዋጅ፣ II ዜና. 36:22-23

ሰ. እንደ ዕዝራ-ነህምያ፣ ዜና መዋዕል የበርካታ ሕዝቦችን ትውልድ ዘርዝሯል፡፡ ከእነዚህ አንዳንዶቹ ወደፊተኞቹ፣ ከአራት በኋላ ወደ ስድስት ትውልድ ይራዘማሉ፡፡ ይህን ነገር ለመመልከት ሁለት መንገዶች አሉ፡
1. እነዚህ የአዘጋጆች ተጨማሪዎች ናቸው፤
2. እነዚህ የዘመኑ ቤተሰቦች /ነገዶች/ ናቸው እንጂ ትውልዶች አይደሉም፡፡

V. ጊዜው

ሀ. በዜና መዋዕል ውስጥ ሁለት ጽሑፎች አሉ፣ ጊዜውን የሚጠቁሙ፣ ከግዞት መልስ በኋላ፣ ዜና መዋዕልን ለመጻፍ፡
1. I ዜና መዋዕል 3፡19-21፡፡ ይህ የዘሩባቤል ዘርዮች ዘርዝር ነው፡
ሀ. አንዳንዶች እስከ ስድስተኛ ትውልድ ይላሉ
ለ. ሌሎች ሁለት ትውልድ ብቻ ይላሉ፣ አራት የዳዊት ቤተሰብ ዝርዝርን ተከትሎ፣ እነርሱም የዘሩባቤልን ሁለት ትውልዶች አቻ የሆኑትን - ፔላቲያህ እና ጄሻይያህ /ያንግ እና ሃሪሰን/
ሐ. LXX የዘሩባቤል ዝርዮችን ዝርዝር እስከ አስራ አንደኛ ትውልድ ያራዝመዋል /ይህም የአዘጋጆች ማሻሻያውን ያሳያል/
2. I ዜና መዋዕል 3፡22-24 - ይህ የሴኬንያ ዝርዮች ዝርዝር ነው፣ ቁ. 21 ላይ የተጠቀሰው፡
ሀ. አንዳንዶች የሚሉት ዝርዝሩ ለአራት ትውልዶች ነው /NIV የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ/
ለ. ይህ እውነት ከሆነ፣ እንግዲያውስ የደራሲው /አዘጋጁ/ ጊዜ ከዘሩባቤል የዘር ሐረግ ይረዝማል፣ 3፡19-21 ላይ
3. II ዜና. 36፡22-23፡
ሀ. ይህ ቂሮስ IIንና የእርሱን አዋጅ ይጠቅሳል፣ ይኸውም ድል ተደርገው የነበሩት ሕዝቦች ሁሉ ወደ አገራቸው እንዲመለሱ የሚፈቅደውን፣ አይሁድን ጨምሮ
ለ. ቂሮስ II አዋጁን ያወጣው በ538 ቅ.ል.ክ ነበር፡፡ የመጀመሪያው መመለስ የተደረገው ወዲያውኑ በይሁዳው መስፍን፣ እሱም የተሾመ ገዥ፣ በሺሽባዛር ነበር፡፡ እሱም መቅደሱን ዳግመኛ መገንባት ጀምሮ ነበር፣ ነገር ግን አላጠናቀቀውም፡፡ ኋላ ላይ፣ በፋርሱ ንጉሥ በዳርዮስ I፣ ሌሎች መመለስ ጀመሩ፣ የዳዊት ዘር በሆነው በዘሩባቤል እና በኢያሱ፣ የሊቀ-ካህን ዝርያ በሆነው፡፡ እነርሱም ቤተ-መቅደሱን ገንብተው በ516 ቅ.ል.ክ አጠናቀቁ፣ በሐጌና በዘካርያስ ማበረታታት፡፡

ለ. ከመጽሐፉ የትውልዶች አጠቃቀስ አኳያ፣ የአጠናቃሪው ጊዜ ሊሆን የሚችለው ከ500-423 ቅ.ል.ክ ነው፡፡ ይህ የማጠናቀቂያ ቀን ተጨማሪ ተደርጎለታል፣ ምክንያቱም በብሉይ ኪዳን የቅርቡ ታሪካዊ ጠቃሽ ሊሆን ስለሚችል፡፡ ዳርዮስ II ዘውድ የጫነው በ428 ቅ.ል.ክ አካባቢ ነው፡፡ እሱም ነህምያ 12፡22 ላይ ተጠቅሷል፡፡ ደግሞም፣ ወግ /ልማድ/ የሚለው የብሉይ ኪዳን ካኖን /ቅዱስ ቃል/ የተጠናቀቀው ይሄን ጊዜ አካባቢ ነው፡፡

ሐ. I ዜና መዋዕል ተመሳሳይ ጊዜ ይሸፍናል፣ እንደ I እና II ሳሙኤል፣ ሆኖም፣ የእርሱ የትውልዶች አጠቃቀስ ወደ ኋላ ተመልሶ አዳምጋ ይሄዳል፡፡ II ዜና መዋዕል ተመሳሳይ ጊዜ ይሸፍናል እንደ I እና II ነገሥት፣ ነገር ግን ከእርሱም ያልፋል፣ ከሞላ ጎደል እስከ ቂሮስ II ድረስ፡፡

VI. ታሪካዊ መቼቱን ስለ ማስረገጥ
ሀ. ጥቂት ርግጠኛ የሆኑ ልዩነቶች አሉ፣ በሳሙኤልና በነገሥት እና በዜና መዋዕል የታሪክ አቀራረብ መካከል፡
1. ዜና መዋዕል ላይ ያሉ ቁጥሮች ከፍ ይላሉ (ያንግ፣ገጽ 394-400)
ሀ. ይህ ባጠቃላይ እውነት ነው፣ I ዜና. 21፡5ን ከ II ሳሙ. 24፡9 ጋር አነጻጽር
ለ. ዜና መዋዕል ዘወትር አነስተኛ ቁጥሮ አላቸው፣ I ነገ. 4፡26ን ከII ዜና. 9፡29 ጋር አነጻጽር
ሐ. አብዛኞቹ የቁጥር ችግሮች በLXX ትርጉም ላይ ይገኛሉ፣ ይህ ማለት ቀደም ብለው ቀኑን ያስቀምጣሉ፣ 250 ቅ.ል.ክ
መ. ኢ.አር. ቴሊ፣ አዲስ ሐሳብ ባለው የተለየ መጽሐፉ የዕብራውያን ነገሥታት ምሥጢራዊ ቁጥሮች፣ *The Mysterious Numbers of the Hebrew Kings, 1954, 1965* ልዩነቶቹን አብራርቷል፡
(1) ሁለት ዓይነት ሥርዓቶች፣ ለአገዛዞች:
(ሀ) ተጨማማሪ ዓመት፤
(ለ) ተጨማማሪ የሌለበት ዓመት.
(2) የአብሮነት /የጋራ/ አገዛዝ
2. ዜና መዋዕል አጽንዖት የሚሰጠው ከዳዊት ዘር ለሆኑት የይሁዳ ነገሥታት አዎንታዊ ገጽታ ነው
3. ዜና መዋዕል ስለ ዳዊትና ሰሎሞን የተባሉትን አብዛኞቹን አሉታዊ ነገሮች ገድፈዋቸዋል /ትተዋቸዋል/፡፡ ሆኖም፣ ያንግ እንደሚያመለክተው /ገጽ 395-398/፣ እሱ ደግሞ ከሞላ ጎደል ሁሉንም ነገር ገድፏል፣ ስለ ግል ሕይወታቸው፣ አሉታዊ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ደግሞ አንዳንዱን አዎታዊ ገጽታዎች፡፡
4. ደግሞም ዜና መዋዕል ስለ ሰሜኑ መንግሥት ሁሉንም ማጣቀሻዎች ገድፏል፡፡ ለምክንያቱ ርግጠኝነት የለም፡፡ ብዙዎች የሚገምቱት፣ ሁሉም የሰሜን ነገሥታት በዳን እና ቤቴል በቆሙት የወርቅ ጥጃ ሳቢያ ስለተኮነኑ /ተወገዙ/ ነው፡፡ ደቡቡ የሚወሰደው ብቸኛ እውነተኛ፣ የታመነ ዳዊታዊ /መሲሓዊ/ መስመር/ዘር ተደርጎ ነበር፡፡

ለ. የዜና መዋዕል ታሪክ ተቀባይነት ድጋፍ ያመዝናል፡
1. በትውልዳዊ ቅደም ተከተል ነገሮች፣ እነርሱም በትይዩነት በተቀመጡ፡
ሀ. ሳሙኤል
ለ. የሙት ባሕር ጥቅሎች
ሐ. LXX
2. የዜና መዋዕል ትውልዳዊ ቅደም ተከተል ነገሮች ከዘፍጥረትና ከዘኍልቊ ጋር በማሶረቲክ ጽሑፎች እና በሳምራውያን ፔንታቲሁች በትይዩ በሚቀመጡበት ጊዜ፣ ታሪካዊ ተቀባይነቱ ድጋፍ ያገኛል

VII. ጽሑፋዊ ምድቦች /ዐውደ-ጽሑፍ/

ሀ. አጭር የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር፡
1. የትውልድ ዝርዝር ነገሮች ከአዳም እስከ ሳኦል፣ I ዜና. 1፡1-9፡44
2. የዳዊት አገዛዝ፣ I ዜና. 10፡1-29፡30

3. የሰሎሞን አገዛዝ፣ II ዜና. 1:1-9:31
4. የሌሎቹ የይሁዳ ነገሥታት አገዛዝ፣ በግዞት እና በቂሮስ፣ II ዜና. 10:1-36:23

ለ. ለተብራራ የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር፡

1. E.J. Young, *An Introduction to the Old Testament*, pp. 401-402
2. R.K. Harrison, *Introduction to the Old Testament*, pp. 1152-1153
3. NIV Study Bible, pp. 581-582

VIII. ዋነኛ ሐቆች

ሀ. ይህ የይሁዳ የተመረጠ ሥነ-መለኮታዊ ታሪክ ነው፣ በI እና II ሳሙኤል እና በI እና II ነገሥት ያሉትን ትይዩ ጽሑፎች በመጠቀምና ከዛም በማለፍ፡፡

ለ. ይህ የተጻፈው ለድኅረ-ስደት ማኅበረሰብ ነው፣ እነርሱም የኪዳን አምላክ አሁንም ቢሆን አምላካቸው መሆኑን ለማወቅ እጅግ ከሚፈልጉት፡፡ መቅደሱ /የዛኔ ንጉሥ ባለመኖሩ/ የእግዚአብሔር ኪዳን መታደስ አትኩሮት ነበር፡፡ ኪዳኑ ያኔም ቢሆን ሁኔታዊ ነበር፣ ለእግዚአብሔር ሙሴአዊ ትዕዛዛት /ሐሳብ/ በመታዘዝ፡፡

ሐ. እሱ በቀዳሚነት የሚያተኩረው እግዚአብሔር ለዳዊና ለልጆቹ በገባው ቃል ኪዳን ላይ ነው፣ II ሳሙኤል 7 ላይ የሚገኘው፡

1. ለይቶ የሚናገረውም በዳዊት ልጆች ላይ ሲሆን፣ መዳረሻውም በመሢሑ ንጉሥ ላይ ነው
2. ለዳዊት፣ ለሰሎሞን እና ለይሁዳ "መልካም" ነገሥታት አዎታዊ ጽሑፍን ይዟል
3. ዕብራውያን በቂሮስ II ወደ ኢየሩሳሌም ስለመመለሳቸው መዝግቧል፣ 36:22-23
4. ለወደፊቱ ዳዊታዊ ንጉሥ /መሢሕ/ አጽንዖት ይሰጣል፡፡ ይሄንን መቀዳጀት ከሚቻልባቸው መንገዶች አንዱ "መልካም" አገዛዝ የነበራቸውን ዳዊትን፣ ሰሎሞንን እና የይሁዳን መልካም ነገሥታትን በመመዝገብ ነበር፡፡ ይህ መሢሓዊ ተስፋ ደግሞ ዘካርያስና ሚልክያስ ላይ ተገልጿል፡፡

መ. ደግሞም የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ እንዲተባበር አጽንዖት ይሰጣል፡፡ ይህም የአጠቃሎሽ ቃል በሆነው "እስራኤል ሁሉ" አጠቃቀም ላይ ይታያል (I ዜና. 9:1፤ 11:1-3፣4፤ 12:38፤ 16:3፤ 18:14፤ 21:1-5፤ 28:1-8፤ 29:21፣23፣25፤ II ዜና. 1:2፤ 2:8፤ 9:30፤ 10:1፣16፤ 12:1፤ 18:16፤ 28:23፤ 29:24፤ 30:1፣6፣25-26፤ 34:7፣9፣33)፡፡

ሠ. የትውልድ ዝርዝሮች ጥቅም ላይ የዋሉት፡

1. እንደ ዕዝራ እና ነህምያ በመሳሰሉት ላይ ነው፣ ይኸውም የተመለሰው እስራኤል ሕጋዊነት የጥንቱ እስራኤል መሆኑን ለማመልከት
2. የዕብራውያንን ታሪክ ወደ አዳም መልሶ ለማጠቃለል

* I እና II ዜና መዋዕል በመሠረቱ እንደ I እና II ሳሙኤል እና I እና II ነገሥት ተመሳሳይ ሁነቶች ከመሆናቸው የተነሣ፣ ለእነዚህ ሁለት መጻሕፍት ምንም ዓይነት ቃላት፣ ካርታዎች፣ ወይም ጥያቄዎች አይኖሩም!

# መግቢያ ለዕዝራ

I. የመጽሐፉ ስም

ሀ. ዕዝራ እና ነህምያ በዕብራይስጥ ካኖን /ቅዱስ ቃል/ /ኤምቲ/ አንድ መጽሐፍ ናቸው፡፡ ባባ ባትራ 15ሀ ዕዝራ ብሎ ነው የሚጠራው፡፡

1. ይህ ያልተለመደ ነው፣ ምክንያቱም ሁለቱም በግልጽ አንድ ዓይነት የትውልድ ዝርዝር በመያዛቸው፡ ዕዝራ 2፡1 እና ነህምያ 7፡6-20፡፡
2. በዝርዝሮቹ ምክንያት፣ ምንም እንኳ በመጠኑ ቢለያዩም፣ በመሠረቱ አንድ ዓይነት ናቸው፣ አንድምታውም እነዚህ ከመነሻውም ሁለት መጻሕፍት እንደሆኑ ነው፡፡
3. ይህም "እኔ" በሚለው የአጠቃቀም ክፍሎች በሁለቱም በዕዝራ 7-10 እና ነህምያ ላይ ተረጋግጧል፡፡

ለ. እነርሱ ተደባልቀው ይሆናል፣ የዕዝራ አገልግሎት /ዕዝራ 7-10/ በነህምያ 8-10 በመቀጠሉ ምክንያት፡፡

ሐ. የዕዝራ እና ነህምያ ስሞች /መጠሪያዎች/ በጥንት ትርጉሞች መካከል ይለያያሉ፡

| LXX | ቫልጌት | ዊስሊፊ እና ኮቨርዳሊ እንግሊዝኛ | ዘመናዊ እንግሊዝኛ |
|---|---|---|---|
| ኢስድራ ቢ /ቤታ/ | ኢስድራስ II ዕዝራ | | ዕዝራ |
| ኢስድራ ሲ /ጋማ/ | ኢስድራስ II | II ዕዝራ | ነህምያ |
| ኢስድራ ኤ /አልፋ/ | ኢስድራስ III | ---- | I ኢስድራስ /ካኖናዊ ያልሆነ/ |
| ---- | ኢስድራስ IV | ---- | II ኢስድራስ /ካኖናዊ ያልሆነ/ |

መ. የመጀመሪያው የዕብራይስጥ ጽሑፍ፣ እነዚህን መጻሕፍት ለመክፈል/ለመለየት የ1448 ዓ.ም የኤምቲ ኅትመት /ቅጂ ነው፡፡

II. ቅዱስ ቃልነቱ

ሀ. መጽሐፈ ዕዝራ የዕብራይስጡ ካኖን ሦስተኛ ምድብ፣ እሱም "ጽሑፎች" ተብሎ የሚጠራው ክፋይ ነው፡፡

ለ. እሱም ኤምቲ ላይ ከዜና መዋዕል ቀድሞ ተቀምጧል፡፡ ይህም ያልተለመደ አመዳደብ ነው፤ የጊዜ ቅደም ተከተሉ ዜና መዋዕል፣ ከዚያም ዕዝራ/ነህምያ መሆን አለበት፡፡ በርከት ያሉ ንድፈ-ሐሳቦች አሉ /ነህምያ፣ II. ለ/፡፡

III. ዘውግ

ሀ. ታሪካዊ ትርክት፣ ቀጥተኛ በሆነ ዝርው /ስድ ንባብ/

ለ. እሱም በርካታ ጥቅሶችን ከሌሎች ሰነዶች ላይ አካቷል
1. ፋርሳዊ
2. አይሁድ

IV. ደራሲነት

ሀ. ባባ ባትራ 15ሀ የሚለው ዕዝራ ይሄንን መጽሐፍ ጽፏል፣ ነገር ግን ይህ ማለት ነህምያንም ደግሞ ጽፏል ማለት አይደለም፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ሌሎች የአይሁድ ምንጮች /ጄማራ/ የሚለው ነህምያ እንደጨረሰው ነው /ዕዝራ - ነህምያ/፡፡ የኤምቲ የመጨረሻ ማስታወሻዎች የተገኙት ነህምያ መጨረሻ ላይ ነው፡፡

ለ. ጆሴፈስ በራሱ *Contra Apion* ላይ፣ 1:8፣ እና የሳርዲሱ ሜሊቶ፣ በኢዩሲበስ እንደተጠቀሰው፣ Eusebius', *Ecclesiastical History* IV:26, ላይ፣ ሁለቱም የዕዝራን ደራሲነት አስረግጠዋል፡፡

ሐ. የዕዝራ ክፋይ፣ እሱም በጸሐፊው ዕዝራ ሕይወት ላይ የሚያተኩረው (ምዕራፍ 7-10) የተጻፈው በአንደኛ መደብ ነው 7:27-28፤ 8:1-34፤ 9:1፡፡ ዕዝራ ካህን ነበር፣ ከሳዶቅ ዘር፣ እንዲሁምጸሐፊ ከፋርስ ቤተ-መንግሥት፣ በአርጤክስስ I (465-424 ቅ.ል.ክ)፡፡

መ. በርካታ ተመሳሳይነቶች አሉ በዕዝራ/ነህምያ እና ዜና መዋዕል መካከል፡
1. የII ዜና. 36:22-23 መዝጊያ ከሞላ ጎደል ልክ ተመሳሳይ ነው፣ ከዕዝራ 1:1-4 ጋር፣ በዕብራይስጥ
2. ሁለቱም ተመሳሳይ ሥነ-መለኮታዊ አስተሳሰብ አላቸው፡
   ሀ. የሚያተኩሩት በቤተ-መቅደስ እና በክህነት ላይ ነው /በተለይም በሌዋውያን ዝርዝር/
   ለ. የተጠናከረ ስታስቲካዊ መዝገብ እና የትውልድ ዝርዝር መጠቀማቸው
3. ቃላታቸውና ጽሑፋዊ ስልታቸው ተመሳሳይ ነው
4. ሁለቱም የቅርቡን ዕብራይስጥ መጠቀማቸው
5. ሆኖም፣ መቀመጥ የሚኖርበት ግልጽ የሆኑ ልዩነቶች መኖራቸው ነው፡
   ሀ. የንጉሣውያን ስሞች ፊደላት ላይ

ለ. ዕዝራና ነህምያ ከሙሴ ጋር በተደረገው ኪዳን ላይ ሲያተኩሩ፣ I እና II ዜና. ደግሞ ከዳዊት ጋር በተደረገው ኪዳን ላይ ያተኩራሉ፡፡

ሠ. ኦሪጅን /185-253/፣ የአሌክሳንደርያ ክርስቲያን ሊቅ መጽሐፉን ለሁለት ለመክፈል የመጀመሪያው ነው፣ ዕዝራ እና ነህምያ በሚል፡፡ ጀሮምም ተመሳሳይ አድርጓል በላቲን ቫልጌት፡፡

ረ. የመጀመሪያው የዕብራይስጥ የእጅ ጽሑፍ፣ መጽሐፉን በመከፋፈል የተጻፈው በ1448 ዓ.ም ነበር፡፡ በግልጽ እንደሚታወቀው፣ በዚህ ጊዜ አይሁድ 22 የብኪ መጻሕፍት ብቻ እንዲኖራቸው ይፈልጉ የነበረው፣ ከ22 የዕብራይስጥ ፊደላት ጋር እንዲገጥሙ በሚል፣ ግን አልሿል፡፡

ሰ. ደራሲው/አጠናቃሪው ብዙ ምንጮችን ተጠቅሟል፡
1. የፋርስ ሰነዶች
2. የአይሁድ ጽሑፎች፡
ሀ. የዕቃዎች ዝርዝር፣ ከያህዌ ቤተ-መቅደስ፣ እሱም በባቢሎን የነበረው 1:9-11፤ 7:19-20
ለ. የተመላሽ ስደተኞች ዝርዝር፣ 2:1-70፤ 8:1-20
ሐ. የዕዝራ የትውልዶች ዝርዝር፣ 7:1-5
መ. በድርብ ጋብቻ ውስጥ የገቡት ሰዎች ዝርዝር፣ 10:18-43

V. ጊዜው

ሀ. ዕዝራ ካህን ነበር፣ ከሳዶቅ ዘር (7:2) እንዲሁምጸሐፊ በአርጤክስስ I አገዛዝ (465-424 ቅ.ል.ክ/፡
1. ዕዝራ ወደ ኢየሩሳሌም መጣ፣ በአርጤክስስ I አገዛዝበሰባተኛው ዓመት፣ 458 ቅ.ል.ክ፣ በሦስተኛው የአይሁድ ስደተኛ ተመላሾች ጋር፡፡
2. ነህምያ ወደ ኢየሩሳሌም መጣ፣ በአርጤክስስ I ሃያኛ ዓመት፣ 445 ቅ.ል.ክ፣ እንደ ፋርስ ገዥ፡፡

ለ. የዕዝራ/ነህምያ የትውልድ ዝርዝር ደራሲውን ወይም አጠናቃሪውን በ5ኛ ክፍለ-ዘመን ቅ.ል.ክ መጨረሻ ላይ የሚያስቀምጠው ይመስላል፡
1. ይህም ግምት ውስጥ የሚያስገባው I ዜና. 3:15-24 የሚዘረዝረው አራት ትውልድ ከዘሩባቤል በኋላ መሆኑን፣ ስድስት ሳይሆን፤
2. ይህም የነህ. 12:10-11 ያዱአ፡
ሀ. ጆሴፈስ በታላቁ እስክንድር /አሌክሳንደር/ ጊዜ ያስቀመጠው ያዱአ አለመሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት /336-323 ቅ.ል.ክ/፤
ለ. ወይም ይህ የትውልድ ዝርዝር በአዘጋጅ ገብቶ ሊሆን ይችላል፣ ዋናው ከተጻፈ በኋላ፣ መረጃውን ወቅታዊ ለማድረግ /ለማሻሻል/፤
ሐ. ወይም እሱ በነህምያ ጊዜ በጣም ልጅ ሊሆን ይችላል፣ እናም በእስክንድር ጊዜ እጅግ በሽምግልና ኖሮ ይሆናል፡፡

ሐ. ይህም የእነዚህ ተዛማጅ ታሪኮች ደራሲነትን የሚያስቀምጠው፣ በግምት፡
1. 440 ቅ.ል.ክ ለዕዝራ
2. 430 ቅ.ል.ክ ለነህምያ
3. 400 ቅ.ል.ክ ለዜና መዋዕል

VI. ታሪካዊ መቼቱን የሚያጠናክሩ ምንጮች

ሀ. የዕዝራ ሰነዶች መልክ፣ የፋርስን ዘመን ይፋዊ ሰነዶች ፈርጅና ስልት ይከተላል፡
1. የቂሮስ አዋጅ /የዕብራይስጥ ትርጉም/፣ 1፡2-4፣ /ወደ ኢየሩሳሌምና ወደ መቅደሱ ስለ መመለስ
2. ሬሁም ለአርጤክስስ I የጻፈው የክስ /ሕግ/ ደብዳቤ፣ 4፡7-16፡፡ /ስለ ኢየሩሳሌም ቅጥር/
3. የአርጤክስስ I ምላሽ፣ ምላሽ፣ 4፡17-22
4. የተንትናይ የክስ ጽሑፍ፣ ለዳርዮስ I 5፡6-17
5. የዳርዮስ I ምላሽ /ስለ መቅደሱ/፡
ሀ. የቂሮስ አዋጅ ተጠቅሷል፣ 6፡2-5
ለ. የዳርዮስ ግላዊ ምላሽ፣ ለተንትናይ፣ 6፡6-12፣13
6. የአርጤክስስ I አዋጅ ለዕዝራ፣ 7፡12-26

ለ. ትልቁ ወረቀት /ፓፒረስ/ /408 ቅ.ል.ክ የዕዝራ/ነህምያ ታሪክ የተቀነባበረበት፣ ሰንበላጥን በመጥቀስ /ሲን-ዑባሊት በባቢሎንኛ/፣ ነህ.2:10፣ 19፤ 4:1፡፡ እሱም ደግሞ የአራምኛ /አራሚክ/ ንግሣዊ ስልትን በማስረጃነት ያሳያል፡፡

ሐ. በርከት ያሉ የነሐስ ሳሕኖች በሶኮት ተገኝተዋል፣ "ለጌሼም ልጅ ለቃይኑ፣" የሚል የተጻፈባቸው፣ ይኸውም የጌሼም ዓረብን ታሪካዊነት የሚያሳይ፣ በዕዝራ/ነህምያ፣ እሱም የቄዳርን መንግሥት የገዛ (ነህ. 2:19፤ 6:1፣6)፡፡

VII. ጽሑፋዊ ምድቦች /ዐውደ-ጽሑፍ/

ሀ. ወደ ኢየሩሳሌም ቀደም ብሎ ስለመመለስ፣ 1፡1-2፡70
1. በቂሮስ አገዛዝ /550-530 ቅ.ል.ክ/ ሰሳብሳር የተሾመ ገዥ ነበር፣ 5፡14፡፡ እሱም የይሁዳ መስፍን ነበር፣ 1፡8፣ የኢዮአኪን ልጅሊሆን ይችላል፡፡ እሱም ወደ ኢየሩሳሌም ከቤተ-መቅደሱ መዝገብ /ሀብት/ ጋር ተመለሰ፣ 1፡1-11፡፡ እሱም የመቅደሱን መሠረት አኖረ፣ ነገር ግን ሊጨርሰው አልቻለም፣ 5፡13-17፡፡
2. በቂሮስ እና ዳርዮስ Iአገዛዝ (4:5፣ 522-486 ቅ.ል.ክ) የዳዊት ዘር የሆነው ዘሩባቤል የተሾመ ገዥ ነበር፡፡ እሱም ከኢያሱ /ጄሹአ/ ጋር ተጎዳኝቶ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሷል፣ የመጨረሻው ሊቀ-ካህን ዘር፣ 2፡1-70፡፡

ለ. ሙሴአዊ አምልኮ-እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም፣ በዘሩባቤልና በኢያሱ ዳግም ስለመጀመሩ፣ 3፡1-6፡22
1. የዳስ በዓልና መደበኛ መሥዋዕት ተጀመረ፣ 3፡1-13
2. ዕቅዱን /ፕሮጀክት/ ለመገንባት ያጋጠሙ ፖለቲካዊ ችግሮች፣ 4፡1-24፡
ሀ. መቅደስ፣ 1-5፣ 24

ለ. የኢየሩሳሌም ቅጥሮች /ግንብ/፣ 6-23

3. ነቢያት ዳግም ግንባታውን አበረታተዋል፣ ነገር ግን ይፋዊውን የፋርስ ፍቃድ እስኪያገኝ መጠበቅ ነበረበት፣ 5፡1-17
4. የቂሮስ አዋጅ ተገኘ፣ እናም መቅደሱን ዳግም ለመገንባት ይፋዊ ፍቃድ ተሰጠ፣ 6፡1-22

ሐ. ሦስተኛው ምልሳት፣ በዕዝራ ጸሐፊው በኩል፣ 7፡1-10፡44

1. የዕዝራ የትውልድ ዝርዝር እና ወደ ኢየሩሳሌም መመለስ፣ 7፡1-10
2. የአርጤክስስ I ደብዳቤ ለዕዝራ፣ 7፡11-26፣እና የእርሱ የምስጋና ጸሎት፣ 7:27-28
3. መመለስ፣ 8:1-36
4. የድርብ ጋብቻ ችግር፣ 9:1-10:44

VIII. ዋነኛ ሐቆች

ሀ. ዕዝራ/ነህምያ የድኅረ-ስደት፣ የፋርስ ጊዜ ታሪክን ቀጠለ፣ II ዜና መዋዕል ሲጠናቀቅ

ለ. እሱም ለስደት ተመላሾቹ ዘር ክብደት ይሰጣል፡

1. የተጠናከረ ነገዳዊ የትውልድ ዝርዝር፤
2. የተጠናከረ የሌዋውያን ምድቦች፤
3. የተመላሾች ሃይማኖታዊ አለማካተት/ማግለል፣ ከአካባቢው ሕዝቦች ጋር ባለው ግንኙነት፤

ሐ. እግዚአብሔር ከያዕቆብ ዘሮች ጋር ያለውን ኪዳን ዳግም አደሰ

መ. እሱም የሚያሳየው የአዲሱን የአምልኮ ፈርጅ ዕድገት ነው፣ ይኸውም በአጥቢያ ምኲራብና በጸሐፍት ላይ የሚያተኩር፡፡ ይህ በርግጥ፣ በኢየሩሳሌም ቤተ-መቅደስ አምልኮ የነበረውን አለማካተት አይደለም፡፡

IX. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት እና ሰዎች በአጭሩ የሚገለጹ

ሀ. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት፡

1. “በኤርምያስም አፍ የተናገረው የእግዚአብሔር ቃል ይፈጽም ዘንድ፣” 1፡1 /NIV፣ “የተነገረው…”/
2. “የሰማይ አምላክ፣” 1፡2 (NASB እና NIV)
3. “እግዚአብሔር መንፈሳቸውን ያነሣሣው ሁሉ፣” 1፡5 (NIV፣ “… ልባቸውን እግዚአብሔር ያነሣሣው”)
4. “የእግዚአብሔርን ቤት ዕቃዎች፣” 1፡7 (NIV፣ “…የመቅደሱ የሆኑትን…”)
5. ኡሪም እና ቱሚም፣ 2፡63 (NASB እና NIV)
6. “በወንዝ ማዶ ያለ ሀገር፣” 4፡16 (NIV፣ “በኤፍራጥስ አሻጋሪ”)
7. ኩብ፣ 6፡3 (NIV፣ “ጫማ”)
8. የሙሴ መጽሐፍ፣ 6፡18 (NASB እና NIV)
9. ጸሐፊ፣ 7፡6 (NIV፣ “መምህር”)
10. ናታኒም፣ 7፡24 (NIV፣ “የመቅደስ አገልጋዮች”)

ለ. ሰዎች፣ በአጭሩ የሚገለጹ፡


1. ቂሮስ፣ 1፡1
2. ሚትሪዳጡ፣ 1:8፤ 4:17
3. ሰሳብሳር፣ 1:8፣11፤ 5:14
4. ዘሩባቤል፣ 2:2
5. ኢያሱ፣ 2፡2
6. አሃሹረስ፣ 4፡6 /NIV፣ ዘሬክሰስ
7. አስናፈር፣ 4፡10 /NIV፣ አሸርባኒፓል/


X. የካርታ ስፍራዎች /አመላካቾች/ /በቁጥር/

1. ኤፍራጥስ ወንዝ
2. ኢየሩሳሌም
3. ሰማርያ
4. አሕምታ (ኢክባታና)፣ 6፡2

XI. ተማሪ-ይዘት ጥያቄዎች

1. ሰሳብሳር እና ዘሩባቤል እንዴት ይዛመዳሉ?
2. 3፡6 ከ5፡16 ጋር ይቃረናልን?
3. ዕዝራ 2 ላይ ያለው ዝርዝር ለምን ነህ. 7 ላይ ተደገመ?
4. የአማልክት /መለኮት መጠሪያ የሆነው የተወቀው የፋርስ ስም፣ በድኅረ-ስደት መጻሕፍት ላይ ለምን አዘውትሮ ለያህዌ ጥቅም ላይ ዋለ?
5. ነቢያቱ ሐጌና ዘካርያስ 5፡1 ላይ ሕዝቡን በሥራው ለማበረታታት ምን ተናገሩ?
6. የቂሮስ አዋጅ ለአይሁድ እጅግ ጠቃሚ የሆነው ለምንድነው?
7. “ድርብ ጋብቻ” ምንድነው? እሱስ ለዕዝራና ነህምያ እጅግ ጠቃሚ ነበረው ለምንድነው?


ANCIENT
NEAR EAST
N
S
E
W


PALESTINE
0 10 20 30 40
SCALE IN MILES

# መግቢያ ለነህምያ

I. የመጽሐፉ ስም

ሀ. ዕዝራ - ነህምያ በኤምቲ አንድ መጽሐፍ ናቸው፣ ዕዝራ በሚል ርዕስ፡፡ የኤምቲ የመጨረሻ ማስታወሻዎች ብቻ በነህምያ መጨረሻ ላይ ይታያሉ፡፡

ለ. ይህ መጽሐፍ በLXX እና ቫልጌትስለሚጠራባቸው የተለያዩ ስሞች ለተሟላ ማብራሪያ /መግቢያ ለዕዝራ፣ I፡፡/

ሐ. ነህምያ የሚለው ስም ፍችው "እግዚአብሔር አጽናንቷል/ተመችቷል/" ማለት ነው፡፡

II. ቅዱስ ቃልነቱ /ካኖናዊነት/

ሀ. መጽሐፈ ዕዝራ-ነህምያ የዕብራይስጡ ካኖን ሦስተኛ ምድብ፣ እሱም "ጽሑፎች" ተብሎ የሚጠራው ክፋይ ነው፡፡

ለ. እሱም "ከዜና መዋዕል" ቀድሞ ይመጣል፣ ይህም የሚያስገርም ነው፣ ምክንያቱም ከታሪካዊነት/ ከጊዜ ቅደም ተከተል አኳያ ከዜና መዋዕል ታሪካዊ ጽሑፍ ተከታይ መሆን ነበረበት፡
1. ዜና መዋዕል ከአዳም እስከ ቂሮስ ማጠቃለያ ነው፡፡
2. ዕዝራ-ነህምያ በቅዱስ ቃልነት ቀድሞ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡
3. ዜና መዋዕል በስተመጨረሻ ነው የተቀመጠው፣ ምክንያም አይሁድ ቅዱስ ቃሉ በአዎንታዊ ማስታወሻ እንዲጠናቀቅ ስለፈለጉ /የቂሮስ አዋጅ/፡፡
4. ማንም ቢሆን በርግጠኝነት ሊያውቅ አይችልም፣ የዕብራይስጥ ካኖንን "የጽሑፎች" ምድብ መስፈርት ወይም ምክንያታዊነት፡፡

ሐ. የመጀመሪያው የኤምቲ ዕብራይስጥ ዕትም /ጽሑፍ/ የከፈላቸው በ1448 ዓ.ም ነበር፡፡

መ. ሆኖም፣ ከውስጣዊ ማስረጃ ግልጽ የሆነው፣ እነርሱ በዋነኛነት/ከመነሻው ሁለት መጻሕፍት እንደነበሩ ነው፡
1. የዕዝራ 2 የተስፋፋው የዘር ሐረግ ዝርዝር፣ ነህ. 7፡6-70 ላይ ተደግሟል፡፡ ስሞቹ በመጠኑ የፊደል ለውጥ አላቸው፤
2. የ"እኔ" ምድቦች ዕዝራ 7፡27-28፤ 8፡1-34፤ 9፡1 ይገኛሉ፣ እንዲሁም የ"እኔ" ምድቦች ነህምያ ላይ ይገኛሉ፡፡

ሠ. ለምን ተደባለቁ?
1. አንድ ታሪክ ስለሚያበጁ፡፡
2. ዕዝራ-ነህምያ በዕብራይስጥ ካኖን የተደባለቁበትን ምክንያት የሚያስረግጠው፣ በብኪ መሆን ያለባቸው መጻሕፍት ቁጥር ከዕብራይስጥ ፊደል ተናባቢዎች ቁጥር ጋር እንዲገጥም/እንዲመሳሰል ስለተፈለገ ነው፡፡ ይህም ማለት የሚከተሉት መጻሕፍት ተደባልቀዋል ማለት ነው፡
   ሀ. መሳፍንት እና ሩት
   ለ. ሳሙኤል
   ሐ. ነገሥት
   መ. ዜና መዋዕል
   ሠ. ዕዝራ - ነህምያ
   ረ. ኤርምያስ - ሰቆቃወ ኤርምያስ
   ሰ. አስራ ሁለቱ መለስተኛ ነቢያት
3. የዕዝራ አገልግሎት፣ ይኸውም ዕዝራ 7-8 ላይ የጀመረው፣ ነህ. 8-10 ላይ ቀጥሏል፡፡

ረ. የመጀመሪያው የኤምቲ ዕብራይስጥ ዕትም/ጽሑፍ የከፈላቸው በ1448 ዓ.ም ነበር፡፡

ሰ. አስገራሚ የሚሆነው የጥንቱ/የድሮው የሶርያ ካኖን እና የሞፕሱስቲአው ቲዎዶር /የአንቲሆች የትርጓሜ ትምህርት ቤት መሪ/ ዜና-መዋዕልን፣ ዕዝራን እና ነህምያን ከተመስጦ መጻሕፍት ዝርዝራቸው ውስጥ ገድፈዋቸዋል /አውጥተዋቸዋል/፡፡

III. ዘውግ

ሀ. ዕዝራ IV፣መ/D ተመልከት /በዕዝራ፣ ነህምያ እና ዜና-መዋዕል መካከል ያለ ተመሳስሎ/
ለ. ዕዝራ IV፣ ሰ/G ተመልከት /የሰነዶች አጠቃቀም/

IV. ደራሲነት

ሀ. ባባ ባትራ 15ሀ የሚለው ዕዝራ-ነህምያ አንድ መጽሐፍ ነው፣ በዕዝራ የተጻፈ፡፡
ለ. ጄማራ የሚለው ነህምያ መጽሐፉን ለመጻፍ ረድቷል (ዕዝራ/ነህምያ)፡፡

V. ጊዜው

ሀ. የ19ኛ እና የፊተኛው 20ኛክፍለ-ዘመን ዓ.ም ሊቃውንት የሚያምኑት የዕዝራ-ነህምያ እና ዜና መዋዕል መጻሕፍት የተጻፉት በአራተኛው ክፍለ-ዘመን ነው ቅ.ል.ክ. ጊዜ፣ ምክንያቱም፡
1. የሊቀ ካህኑ ኢያሱ ዝርያ/ተወላጅ፣ እሱም ዘሩባቤልን የተጎዳኘው፣ በሁለተኛው መመለስ ጊዜ /በቂሮስ ሥር/ትዕዛዝ/ ዮአዳን ነበር፤ እሱም ነህምያ 12፡10-11፣ 22 ላይ ዝርዝሩ አለ፡፡

2. እነርሱ የሚያስረግጡት ይህ ዮአዳ በጆሴፈስ መጠቀሱን ነው (*Antiquities*, XI:302-7)) እንደ ሊቀ-ካህን (351-331 ቅ.ል.ክ) ታላቁ እስክንድር ፍልስጥኤምን ሲወር፣ በ333-332ቅ.ል.ክ፤
3. ይህም ስድስት የዘሩባቤል ትውልዶችን ያያይዛል፣ እነርሱም በI ዜና መዋዕል 3፡19-24 የተዘረዘሩት፡
4. አብዛኞቹ እነዚህ ሊቃውንት ደግሞ የሚደግፉት አስተያየት፣ ማለትም፣ ዕዝራ የተመለሰው በአርጤክስስ II (404-358 B.C.) አገዛዝ ሲሆን ነህምያ የተመለሰው በአርጤክስስ I (465-424 ቅ.ል.ክ የግዛት ጊዜ ነው)፤
5. ነህ. 12:26፣ 47 የኋለኛውን አዘጋጅ/አጠናቃሪ ያመላክታል፡፡

ለ. የኋለኛው 20ኛ ክፍለ-ዘመን ወግ-አጥባቂ ሊቃውንት የሚያስረግጡት፣ ለእነዚህ ሦስት መጻሕፍት የሚያስቀምጡት ጊዜ አምስተኛው ክፍለ-ዘመን ቅ.ል.ክ ነው፣ ምክንያቱም፡

1. የነህ. 12:10-11፣22 ዮአዳ ሊሆን የሚችለው፡
   ሀ. ሲጠቀስ በጣም ወጣት ሆኖ፣ እጅግ ረጅም ጊዜ የኖረ፡፡ እሱም ነህምያ ላይ እንደ ሊቀ-ካህን አልተጠቀሰም/ዝርዝር ውስጥ የለም፡
   ለ. ርግጠኛው ዮአዳ አይደለም፣ ነገር ግን የልጅ ልጅ ሆኖ ተመሳሳይ ስም ያለው /*የአብራሪዎች/ተንታኞች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሐተታ*፣ ቅጽ 4 ገጽ 596-586 (*Expositor's Bible Commentary*, vol. 4 p. 596-586)

   ሐ. ጆሴፈስ በስሕተት የፋርስን ዘመን አሳጥሮታል፣ ምክንያቱም የፋርስ ገዥዎች ስሞች በመደገሙ፣ በአምስተኛውና በአራተኛው ክፍለ-ዘመን ቅ.ል.ክ፡
      (1) አርጤክስስ
      (2) ዳርዮስ
2. የዘሩባቤል የዘር-ግንድ በ I ዜና. 3:19-24 የሚሄደው፡
   ሀ. ሁለት ትውልዶች /ያንግ እና ሃሪሰን/
   ለ. አራት ትውልዶች ብቻ ነው
3. ፍልስጥኤም ላይ ተጽዕኖቸውን ላሳረፉ ዋና ሁነቶች ታሪካዊ ጠቃሽ የላቸውም፣ በአራተኛው ክፍለ-ዘመን ቅ.ል.ክ፡
   ሀ. የታላቁ እስክንድር ወረራ (333-332 ቅ.ል.ክ)
   ለ. በአርጤክስስ III የተደመሰሰ ዓመጽ (358-338 B.C.)
4. ዮአዳ ከታላቁ እስክንድር ጋር በአንድ ዘመን የኖረ ነው ቢባል እንኳ፣ ይህ የሌዋውያን ዝርዝር በመጽሐፉ ላይ የታከለው/የተጨመረው በኋለኛ አዘጋጅ ነው፣ እሱን ለማሻሻል ሲባል /ያንግ/፡፡ የአዘጋጅ ማስረጃ ሊኖር ይችላል፣ "በነህምያ ጊዜ፣" በሚለው ሐረግ፣ ነህ. 12፡26፣47፡፡
5. ዕዝራ እና ነህምያ የቀረቡት በኢየሩሳሌም አንድ ላይ እንደሆኑ ሆነው ነው፣ በተለያየ ሥርወ-መንግሥት ሳይለያዩ፡
   ሀ. ሕጉን ማንበብ፣ ነህ. 8፡9፤
   ለ. የኢየሩሳሌም ቅጥር/ግንብ ምርቃት፣ ነህ. 12፡26፣36፡፡

## VI. ታሪካዊ መቼቱን የሚያጠናክሩ ምንጮች

ሀ. ትልልቅ ፓፒረስ/ወረቀት /408 ቅ.ል.ክ./ በዕዝራ/ነህምያ ላይ የተዘረዘሩት ሰዎች የአብዛኞቹ ስሞች ተጠቅሰዋል፡

1. ሰንበላጥ፣ የሰማርያ ገዥ፣ 2:10፣19፤ 4:1፤
2. ዮናታን፣ የሊቀ-ካህኑ የኤልያሴብ የልጅ ልጅ፣ ነህምያ 12:10-11፣ 22፣ 23፤
3. የእነዚህ ሰዎች ተለይተው መጠቀስ ዕዝራና ነህምያ በአርጤክስስ I የአገዛዝ ዘመን ለመኖራቸውና ለመሥራታቸው ማረጋገጫ ነው /464 -424 ቅ.ል.ክ./፡፡

ለ. የሰማርያ ወረቀት የሰማርያን ገዥዎች ዝርዝር ይሰጠናል፣ ከሖሮናዊው ሰንበላጥ እስከ ከተማይቱ በታላቁ እስክንድር መጥፋት 332 ቅ.ል.ክ. ድረስ፡፡ እነርሱም ደግሞ የነህምያ 13፡28ን ሁነቶች ያሳዩናል፣ እንዲሁም ተመሳሳይ የሆኑትን በጆሴፈስ የተመዘገቡትን ሁነቶች፣ በሰንበላጥ III ጊዜ የሆኑት አንድ ዓይነት አይደሉም፡፡

## VII. ጽሑፋዊ ምድቦች /ዐውደ ጽሑፍ/

ሀ. ነህምያ የኢየሩሳሌምን ቅጥር ዳግም ገነባ /ከተማይቱን አነስተኛ አደረጋት/፣ 1፡1-7፡73፡

1. የተዋወቀው በአንደኛ መደብ ነው፣ 1፡1-2፡20፤
2. ቅጥሩ የተገነባው በ52 ቀናት ነው፣ 3፡1-6፡19፤
3. የነህምያ ወንድም፣ ሐናኒ የከተማይቱ ኃላፊነት ተሰጠው፣ 7፡1-73፡፡

ለ. የዕዝራ መንፈሳዊ ተሐድሶ /የዕዝራ 7-10/ መቀጠል፣ 8፡1-10፡39፤

1. ዕዝራ ሕጉን አነበበ፣ ሕዝቡም ምላሽ ሰጠ፣ 8፡1-9፡4፤
2. እግዚአብሔር ለአይሁድ ያደረገው ተቃኘ/ተነገረ፣ 9፡5-31፤
3. ሕዝቡም ራሳቸውን በመሐላ አሰሩ፣ እግዚአብሔርን ለማምለክና ቤተ መቅደሱን ለመደገፍ፣ /የኪዳን መታደስ/ 9፡32-10፡39፡፡

ሐ. የነህምያ አስተዳደራዊ ተሐድሶዎች፣ 11-13፡

1. የነህምያ ወደ ኢየሩሳሌም የመጀመሪያ መመለስ፣ 11-12
   ሀ. የኢየሩሳሌምን ሰዎች ማቋቋም፣ 11፡1-36
   ለ. የካህናትና የሌዋውያን ዝርዝር፣ 12፡1-26፣ 44-47፤
   ሐ. የኢየሩሳሌም ግንቦች ምርቃት፣ 12፡27-43፡፡
2. የነህምያ ወደየሩሳሌም ሁለተኛው መመለስ፣ 13፡1-31
   ሀ. የኪዳን ጥሰቶች፣ 13፡1-5
   ለ. ተሐድሶዎች/ማሻሻያዎች፣ 13፡6-31፡
      (1) ጦብያ ከመቅደሱ ጓዳዎች እንዲወጣ ተደረገ፣ 13:4-5፣ 8-9፤
      (2) የመቅደስ አስራት፣ 13:10-14፤

(3) ድርብ ጋብቻ፣ 13፡1-3፣ 23-29፤
(4) ለመቅደስ የሚሆን የፍጆታ አቅርቦት፣ 13:30-31፡፡

VIII. ዋነኛ ሐቆች

ሀ. ይህ መጽሐፍ በዕዝራ የተጀመረውን ታሪክ የሚቀጥል ነው፡፡ ሁለቱም የኪዳኑ ማኅበረሰብ በተስፋይቱ ምድር ዳግም መቋቋምን ሰንደዋል /በዶሴ ይዘዋል/፡፡

ለ. ዕዝራ የአዲሱ ማኅበረሰብ መንፈሳዊ፣ ኪዳናዊ ሕይወት ላይ እንደሚሠራ/እንደሚገደው ሁሉ፣ ነህምያ ደግሞ የሚሠራው/የሚገደው፡
1. በከተማይቱ ዙሪያ ያለው ጥብቅ ቅጥር፤
2. የከተማይቱ አስተዳደራዊ ገጽታ ነበር፡፡

ሐ. ሁለቱም ዕዝራና ነህምያ የሚገዳቸው የኪዳን /የሙሴ/ ታማኝነት ነበር፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝብ ኃጢአት፣ ከምንዝርና /ጣዖትን ማምለክ/ በቀር በድኅረ-ስደት ማኅበረሰብ ቀጥሎ ነበር፡፡

IX. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት እና ሰዎች በአጭሩ የሚገለጹ

ሀ. ቃላትና ሐረጋት፡
1. ጠጅ አሳላፊ፣ 1፡11 /NASB እና NIV/
2. ኒሳን፣ 2፡1
3. " በድንጋይበሚሠሩትቅጥራቸውላይቀበሮቢመጣበትያፈርሰዋል፣" /NIV፣ "ቀበሮ ቢወጣበት የድንጋይ ቅጥራቸውን ያፈርሰዋል"/
4. "ሴቶች ልጆቻችን ባሪያዎች ይሆኑ ዘንድ ሰጥተናል፣" 5፡5 /NIV፣ "...ባሪያዎች ሆነዋል"/
5. "እኔም ልብሴን አራገፍሁ፣" 5፡13 /NIV፣ "...የልብሴን እጥፋት"/
6. የደመና ዓምድ፣ 9፡12 /NASB እና NIV/
7. ገጸ-ኅብስት፣ 10፡33 /NIV፣ "ጠረጴዛ ላይ የሚደረግ ኅብስት"/
8. ቀጣይነት ያለው...፣ 10፡33 /NIV፣ /NIV፣ "መደበኛ"/
9. በኵራት፣ 10፡35 /NIV፣ "በኵራት"/
10. ከአሥሩክፍልአንዱበቅድስቲቱከተማበኢየሩሳሌም ይቀመጡዘንድዕጣተጣጣሉ፣ 11፡1 /NASB እና NIV/
11. "የሙሴ መጽሐፍ፣" 13፡1 /NASB እና NIV/

ለ. በአጭሩ የሚገለጹ ሰዎች፡
1. ሀናኒ፣ 1፡2
2. አሞናዊው ጦብያ፣ 2፡10፣19
3. ሖሮናዊው ሰንበላጥ፣ 2፡10፣19
4. ዓረባዊው ጌሳም፣ 2፡19
5. አሳፍ፣ 11፡17
6. ኤዶታም፣ 11፡17
7. አርጤክስስ I፣ 13:6

X. የካርታ ስፍራዎች /አመላካቾች/

1. ሱሳ፣ 1፡1
2. አሽዶድ፣ 4፡7
3. "ቼፊሪም፣ በኦኖ ቆላ/ሜዳ፣" 6፡2 /NIV፣ "በኦኖ ቆላ/ሜዳ ባሉ መንደሮች"/

XI. የተማሪ ይዘት ጥያቄዎች

1. ነህምያ ለምን በጣም አዘነ?

2. ኅዘኑን እንዴት ገለጸ?

3. ነህምያ ለምን የፋርስን ወታደሮች ወሰደ /2፡9/ ዕዝራ ግን ሳይወስድ?

4. የነህምያ ቀዳሚ ተግባር ምን ነበር?


5. ድሆቹ አይሁድ በባለጸጎቹ አይሁድ ላይ ለምን አዘኑ /ምዕ. 5/?


6. የምዕራፍ 9ን የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር አስፍር፣ እግዚአብሔር ለአይሁድ ሕዝቦች ያደረገውን፡፡

7. 9፡17 ላይ ያለውን የእግዚአብሔርን ባሕርያት ዘርዝረህ በአጭሩ አብራራቸው፡፡

8. ማንም በኢየሩሳሌም መኖር ያልፈለገው ለምንድነው /ምዕ. 11/?

9. ነህምያ በድርብ ጋብቻ በጣም ቅር የተሰኘው ለምንድነው?


N
W
E
S
ANCIENT
NEAR EAST


PALESTINE
0 10 20 30 40
SCALE IN MILES

# መግቢያ መጽሐፈ አስቴር

I. የመጽሐፉ ስም

ሀ. የተሰየመው በፋርስ ንግሥት ነው፡፡

ለ. ስሟ በዕብራይስጥ ሃደሳ ነበር፣ ፍችውም ለምለም /2፡7/፡፡ ይህ ቃል በአይሁድ ዘንድ የደስታ ተምሳሌት ነው /ዘካ. 1፡8/፡፡

ሐ. ስሟ በፋርስ "ኮከብ" ማለት ነው፡፡

II. ቅዱስ ቃልነቱ /ካኖናይዜሽን/

ሀ. ይህ መጽሐፍ በዕብራይስጦ ካኖን ለመካተት ችግር ነበረው፡
1. ምክንያቱም ባለመጥቀሱ ሊሆን ይችላል፡
ሀ. ምንም ዓይነት የእግዚአብሔርን ስም፤
ለ. መቅደስን፤
ሐ. የሙሴን ሕግ፤
መ. መሥዋዕት፤
ሠ. ኢየሩሳሌም፤
ረ. ጸሎት /ምንም እንኳ በአንድምታ ቢኖርም/፡፡
2. የሙት-ባሕር ጥቅሎች፣ እነርሱም በ1947 የተገኙት የሁሉንም የብኪ መጻሕፍት ቅጂዎች ይዘዋል /በሙሉ ወይም በከፊል/ ከአስቴር በቀር
3. አስቴር፣ እንደ ሩት፣ አኪ /አዲስ ኪዳን/ ላይ አልተጠቀሰም
4. እሱ የተደባለቀ ቅኝት ከአታቾች አግኝቷል/ተደርጎበታል፡
ሀ. የኢየሩሳሌም ታልሙድ /ሜጊላ 7ሀ/ የሚለው የዕብራይስጥ ካኖን የ"ነቢያት" ክፍል፣ እና የ"ጽሑፎች" ምድብ"፣ወደ ፍጻሜ ደርሰዋል፣ ነገር ግን ቶራ እና አስቴር ፍጻሜ አላገኙም፡፡ እነርሱ ፈጽሞ አልጠፉም /ከኢ.ጄ. ያንግ የተወሰደ/፤
ለ. ማይሞኒደስ፣ የአይሁድ ተንታኝ፣ የመካከለኛው ዘመን /1204 ዓ.ም/ የሚለው፣ እሱ በጠቀሜታ ከሙሴ ሕግ የሚቀጥል ነበር፤
ሐ. ማርቲን ሉተር፣ የፕሮቴስታንት ተሐድሶ አራማጅ፣ የሚለው እርሱ ከካኖን መውጣት አለበት፣ ምክንያቱም እጅግ ይሁዲነት ስላለበት /እሱም ደግሞ ብሏል ያዕቆብ እና ራዕይም እንዲሁ/፡፡
5. እሱም ከአወዛቢ መጻሕፍት አንደኛው ነበር በጃምኒአ በፈሪሳውያን ውይይት የተካሄደበት፣ ከ70 ዓ.ም በኋላ፡፡
6. የ"መጽሐፈ መክብብ፣" ደራሲ ደግሞም "የቤን ሲራክ መጽሐፈ-ጥበብ" ተብሎ የሚጠራው፣ ይኸውም በ180 ቅ.ል.ክ. የተጻፈ ስለ አስቴር ፈጽሞ አልተናገረም፡፡
7. በአይሁድ ካኖን የተካተተ ሊሆን የሚችለው ሙሴያዊ ያልሆነውን የፑሪም በዓል መገኛ ለማብራራት ነው /9፡28-31፡፡ በመቃብያን II 15፡36 ፑሪም "የመርዶክዮስ ቀን" ተብሏል፡፡

ለ. መጽሐፈ አስቴር የአምስቱ ጥቅሎች፣ ይኸውም *Megilloth*ተብሎ የሚጠራው ልዩ ዝርዝር ክፋይ ነው፡፡ እነዚህም አምስት አናሳ መጻሕፍት፡ ሩት፣ መክብብ፣ መኃልየ መኃልይ፣ ሰቆቃወ ኤርምያስ እና አስቴር፣ ሲሆኑ እነርሱም የዕብራይስጥ ካኖን "የጽሑፎች" ምድብ ክፋይ ናቸው፡፡ እነርሱ እያንዳንዳቸው ተለይተው በዓመታዊ የበዓል ቀናት ይነበባሉ፡፡ አስቴር ፑሪም ላይ ይነበባል፡፡

ሐ. የአስቴር ጽሑፍ በኤምቲ እና LXX መካከል እጅግ ይለያያል፡፡ LXX በጣም ሲረዝም፣ የመርዶክዮስንና የአስቴርን ጸሎት ይጨምራል፡፡ ይህም የተጨመረው መጽሐፉ በአይሁድ ካኖን ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ ለማገዝ ሊሆን ይችላል፡፡

መ. የሂፖ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ (393 ዓ.ም) እና የካርቴጅ (397 ዓ.ም) የአስቴርን ስፍራ በክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ ላይ አረጋግጠዋል/አጽንተዋል፡፡

III. ዘውግ

ሀ. እሱ ታሪካዊ ትርክት ነው /10፡2 ላይ አንባቢው የመርዶክዮስን ጽሑፍ ለገዛ ራሱ እንዲያነብ ይበረታታል፣ በፋርስ የቤተ መንግሥት ጽሑፍ/መዝገብ፡፡/

ለ. አንዳንዶች ታሪካዊ ፈጠራ /ልቦለድ/ ይሉታል፣ መንፈሳዊ እውነትን ለመግለጥ
1. የውስጠ-ወይራ ዘይቤ አጠቃቀም
2. በጥንቃቄ የተሸረበ ሴራ
3. ዋነኞቹ ገጸ-ባሕርያት በታሪክ የማይታወቁ

IV. ደራሲነት

ሀ. ስለዚህ ስም-የለሽ /ስያሜው ያልታወቀ/ መጽሐፍ ደራሲ ማንነት በርካታ ንድፈ-ሐሳቦች ይገኛሉ፡
1. ራቢ /መምህር/ አዛርያስ የሚለው፣ ጆያክ ኢም በዳርዮስ I አገዛዝ ጊዜ ሊቀ-ካህን የነበረው፣ በኋለኛው ስድስተኛው ክፍለ ዘመን ቅ.ል.ክ. ጽፎታል፤
2. ታልሙድ፣ ባባ ባትራ 15ሀ የሚለው፣ የታላቁ ምኩራብ ሰዎች የአስቴርን ሚና /ሥራ/ ጻፉ፡፡ እነዚህ ባጠቃላይ በኢየሩሳሌም የነበሩ የመሪዎች ቡድን ሲሆኑ በዕዝራ ተጀምሮ ኋላ ላይ የአይሁድ ጉባኤ የሆነ ነው፡፡ "ጽፈዋል" የሚለው ቃል ጥቅም ላይ ቢውልም፣ "አዘጋጅተዋል፣" "አጠናቅረዋል፣" ወይም "አሰባስበዋል" ለማለት ነው፤
3. ኢብን ኢስራ፣ የአሌክሳንደርያ ክሌመንት እና ጆሴፈስ / *Antiquities*፣ 11፡6፡1/ የሚሉት መርዶክዮስ ጽፎታል፣ ነገር ግን አስ. 10፡3 ይሄንን የሚቃረን ይመስላል /በኋለኛ አዘጋጅ እስካልተጨመረ ድረስ/፤

4. ኢሲዶር እና አውግስቲን የሚሉት፣ ዕዝራ ጻፈው ነው፡፡

ለ. ማንም እንደማያውቀው ግልጽ ነው፡፡ ርግጠኛ የሚሆነው፣ በፋርስ በግዞት ያለ አይሁዳዊ፣ እሱም ስለ ፋርስ ቤተ-መንግሥት በደንብ የሚያውቅ መሆኑ ነው፡፡

ሐ. ይህ ያልታወቀ ደራሲ ምንጮችን ይጠቀማል፡
1. የመርዶክዮስ ማስታወሻ፣ 9፡20፤
2. የፋርስ ታሪካዊ ሰነዶች፣ 2:23፤ 3:14፤ 4:8፤ 6:1፤ 8:13፤ 10:2፤
3. ሥነ ቃል ሊሆንም ይችላል፣ በተለይም በየአውራጃዎቹ ምን እንደተደረገ፤
4. «መጽሐፍ» የሚለው 9፡32 የሚጠቅሰው በርግጠኝነት አይታወቅም፡፡

V. ጊዜው

ሀ. ይህ መጽሐፍ የፋርስን ንጉሥ አህሹረስ የሚባለውን ጠቅሷል፣ ይኸውም በፋርስኛ «ብርቱ ሰው» ማለት ነው፡፡ አብዛኞቹ ሊቃውንት የሚስማሙት ይህ ንጉሥ በታሪክ የሚታወቅ፣ በግሪክ ማዕርግ ዘረክሲስ I ነው /486-465 ቅ.ል.ክ/

ለ. LXX እና ጆሴፈስ፣ የሚጠሩት ግን "አርጤክስስ" በሚል ነው፣ ይኸውም የዘረክሲስ ተኪ/ወራሽ አርጤክስስ I /465-424 ቅ.ል.ክ፡፡/

ሐ. አስቴር ምዕራፍ 1፣ የፋርስን የዕቅድ ሁኔታ ያንጸባርቃል፣ ግሪክን ለመውረር፡፡ ከታሪክ ጸሐፊው፣ ከሔሮዱቱስ እንደምንረዳው /2፡8/ ፋርስ ግሪክን ወርራለች፣ እንደገናም በ408 ቅ.ል.ክ. ወደ ኋላ ተመልሳለች/አፈግፍጋለች፡፡ እሱ የሚለው፣ የፋርስ ንጉሥ ወደ አገሩ ተመልሶ ከሚስቶቹና ከቋባቶቹ ጋር በቤተ መንግሥቱ ረዥም ጊዜ አሳልፏል /9፡108/፡፡

መ. እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ዜና መዋዕላዊ ቅደም ተከተል መጽሐፉን የሚያስቀምጠው በዕዝራ ምዕራፍ 6 እና 7 መካከል ነው፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ የ57 ዓመት ልዩነት በዕዝራ ጽሑፍ /ጉዳይ ጋር በተያያዘ/ አለ፡፡ ሰውየው ዕዝራ እስከ ምዕ. 7 ድረስ አይተዋወቅም፡፡

ሠ. አስቴር 10፡1-3 የሚያመለክተው ከዘረክስስ I ሞት በኋላ ያለውን ጊዜ ነው፡፡ እሱም በ465 ቅ.ል.ክ. ተገድሏል፡፡

ረ. ከኋለኛው አምስተኛው ክፍለ ዘመን ቅ.ል.ክ. የሆነ ጊዜ አሳማኝ ይመስላል፣ ምክንያቱም፡
1. አስቴር ላይ ያለው የዕብራይስጥ መልክ፣ ዜና መዋዕል፣ ዕዝራ እና ነህምያ ላይ ያለውን መምሰሉ፤
2. የፋርስ የትውሰት/ውርስ ቃላት መገኘት፤
3. የደራሲው የፋርስን ወግ/ልማድ እና የቤተ-መንግሥቱን ሕይወት ማወቅ፡፡ አንድ ምሳሌ የሚሆነን 1፡6-8፣ 10 ነው፡፡

VI. ታሪካዊ መቼቱን የሚያጠናክሩ ምንጮች

ሀ. የኒፑር ኩኒፎርም ሰሌዳዎች፣ በአርጤክስስ I የአገዛዝ ዘመን የተጻፉት (465-424 ቅ.ል.ክ.) እንደሚያረጋግጡት በርካታ የአይሁድ ሕዝብ በሜሶፖታሚያ ነበሩ፣ ወደ አገር መመለሱ በቂሮስ II ከተፈቀደ በኋላ፣ በ538 ቅ.ል.ክ፡፡

ለ. የሔሮዱቱስ ታሪክ፡

1. የሔሮዱቱስ ታሪክ ስለ ዜረክሰስ 1፣ ከአስቴር የታሪክ መስመር/አካሄድ ጋር የሚገጥም ይመስላል፡
ሀ. ግሪክን ለመውረር ዕቅድ ለማውጣት ጉባኤ ተጠርቷል፤
ለ. ከተሸነፈ በኋላ ብዙውን ጊዜውን በቤተ መንግሥት ከሚስቶቹና ከቀኅባቶቹ ጋር አሳልፏል፤
ሐ. ዜረክሰስን እንደ አቋመ-ቢስ፣ ባለጌ፣ እና ስሜታዊ ሰው አድርጎ ገልጾታል፡፡
2. ይህ፣ በሁለት መንገድ የሚቆርጥ ነው፡፡ ሔሮዱቱስ ደግሞ የዜረክሰስን ሚስት ሰይሟል፣ ገለጻም አድርጓል፡፡ ስሟ አሜስትሪስ ነው፣ እሷም "የሰባቱ ቤተሰብ" ከሚባሉት ነች፡፡ የፋርስ ንጉሥ ሰባት የቅርብ አማካሪዎች አሉት /1፡14/፡፡ ሔሮዱቱስ እንደጠቀሰው አሜስትሪስ ዜረክሰስ I ን ተጎዳኝታዋለች፣ በግሪክ ዘመቻው ወቅት፡፡

ሐ. የፐረስፖሊስ ኢላማይት ሰሌዳዎች /በዳርዮስ Iእና ዘረክሲስ I ያገዛዝ ዘመን/ የመርዶክዮስን ስም በዝርዝሩ ይዘዋል፣ እንደ በረኞች አለቃ፡፡

VII. ጽሑፋዊ ምድቦች /ዐውደ ጽሑፍ

ሀ. NIV የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ የፍሬ ሐሳብ ዝርዝር እጅግ ረጂ ነው፡፡ እሱም የአስቴርን ሦስት ግብዣዎች ይጠቀማል፣ እንደ መዋቅር የታሪኩን ፍሰት ለመከተል፡
1. የንጉሡ ግብዣ፣ 1:1-2:18፤
2. የአስቴር ግብዠ፣ 2:19-7:10፤
3. የፑሪም ግብዣ፣ 8-10፡፡

ለ. ለተብራራ የፍሬ ሐሳብ ዝርዝር፡
1. NIV Study Bible, p. 719
2. *Expositor's Bible Commentary*, vol. 4, p. 796

VIII. ዋነኛ ሐቆች

ሀ. መጽሐፉ ሙሴያዊ ያልሆነ ዓመታዊውን የፑሪም በዓል በግልጽ ያስተዋውቃል /9፡28-32/፡፡ ሌላው ሙሴያዊ ያልሆነ ብቸኛ የአይሁድ ዓመታዊ በዓል ሃኑካህ ነው፡፡ ማለፊያ/መልካም የማሳያ ሰንጠረዥ ገጽ 176፣ NIV የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ ላይ አለ፡፡

ለ. እሱ ለእግዚአብሔር ያለን ታማኝነት የሚያበረታታ ነው፣ በስደት ጊዜ /በተለይም በግዞት በቆዩት ዘንድ/፡፡

ሐ. እሱ የእግዚአብሔርን የምሪት እጅ በታሪክ ያሳያል፣ በእስራኤል ብቻ ሳይሆን በፋርስም፡፡ ምንም ዓይነት የአምላክ ስም አለመኖሩና ከተለመደው የአይሁድ መንፈሳዊ ልምምዶች ምንም ነገር አለመጠቀሱ /ከጾም በቀር/ ጽሑፋዊ ማራኪነቱ ለእግዚአብሔር ምሥጢራዊ ተጽዕኖና ሁሉንም የሰው ልጆችን ታሪክ የሚመራ ለመሆኑ ማሳያ ነው /4፡14/፡፡

መ. አንዳንዶች ይሄንን መጽሐፍ የሚመለከቱት በሰይጣን እንድተደረገ ሌላ ሙከራ ነው፣ የኪዳኑን ማኅበረሰብ ብሎም መሢሑን ለማጥፋት!

1. የአዳም ውድቀት፤
2. የመላእክት ከሰው ጋር መደባለቅ /ዘፍጥረት 6/፤
3. የአብርሃምና ይስሐቅ ሚስቶቻቸውን መስጠት፤
4. የአይሁድ ሕዝብ ጥፋት፣ አስቴር ላይ፡፡

IX. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት እና ሰዎች በአጭሩ የሚገለጹ

ሀ. ቃላትና ሐረጋት፡

1. ”ሰባቱ ጃንደረቦች፣” 1፡10 /NASB እና NIV/
2. ”የፋስና የሜዶን ሰባቱ መሳፍንት፣” 1፡14 /NIV፣ ”ሰባቱ መሳፍንት…”/
3. ”እንዳይፈርስም በፋርስና በሜዶን ሕግ ይውጣ፣” 1፡19 /NASB እና NIV/
4. ቍባቶች፣ 2፡14 (NASB እና NIV)
5. አጋጋዊው፣ 3፡1፣ 10፤ 8:5 (NASB እና NIV)
6. ፉር፣ 3:7፤ 9:24 (NASB እና NIV)
7. የማኅተም ቀለበት፣ 3:10፤ 8:2 (NASB እና NIV)
8. አገረ ገዢ፣ 3:12(NASB እና NIV)
9. “የወርቅ ዘንግ፣” 4:11፤ 5:2 (NASB እና NIV)
10. "ቁመቱ ኀምሳ ክንድ የሆነ ግንድ፣" 5:14፤ 7:9-10 (NIV፣ “ሰባ አምስት ጫማ ከፍታ”)
11. "እነዚህ የፉሪም ቀኖች፣" 9:28-32 (NASB እና NIV)


ለ. በአጭሩ የሚገለጹ ሰዎች፡

1. አሃሹረስ፣ 1፡1 /NIV፣ ”ዘረክሰስ”/
2. አስጢን፣ 1፡9
3. መርዶክዮስ፣ 2፡5
4. አጋጋዊው ሐማ፣ 3፡1


X. የካርታ ስፍራዎች - ካርታ የለውም

XI. የተማሪ ይዘት ጥያቄዎች

1. በአስጢን እምቢ ማለት የንጉሡ አማካሪዎች በጣም ቅር የተሰኙት ለምንድነው?
2. መርዶክዮስ ለሐማ ያልሰገደው ለምንድነው?
3. ሐማ አይሁድን ሁሉ ለማጥፋት የፈለገው ለምንድነው፣ አንድ አይሁድ አልሰግድለት ስላለ?
4. ሐማ አይሁድን ለማጥፋት ምን ምክንያት ለንጉሡ አቀረበ /ምዕ. 3/?
5. የአይሁድ የኀዘን ሥርዓት መልኮችን ዘርዝር፣ 4፡1-3 ላይ የተመዘገቡትን፡፡
6. የጥበቃና ክብካቤ ሥነ-መለኮታዊው ዶክትሪን ከ4፡14 ጋር እንዴት ይዛመዳል?
7. 8፡17 ከመጽሐፉ ዓላማ ጋር እንዴት ይገጥማል/ይሰማማል?


ANCIENT
NEAR EAST
N
S
E
W

# PALESTINE



# መግቢያ ለጥበብ ሥነ-ጽሑፍ

I. ዘውጉ

ሀ. የተለመደው ጽሑፋዊ ዓይነት በጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ

1. ሜሶፖታሚያ (1 ነገ. 4:30፤ኢሳ. 47:10፤ዳን. 2:2)
   ሀ. ሱሜርያ የዳበረ የጥበብ ወግ/ልማድ ነበረው፣ በሁለቱም በምሳሌም ሆነ በሙገሳ ግጥም /ኢፒክ (NIPPUR)፡፡
   ለ. የባቢሎን ምሳሌያዊ ጥበብ ከካህን/አስማተኛ ጋር ይያያዛል፡፡ እሱም ግብረገብ-ተኮር /ሞራል-ተኮር/ አይደለም፡፡ እሱም እንደ እስራኤል የዳበረ ዘውግ አይደለም፡፡
   ሐ. አሦር ደግሞ የጥበብ ወግ/ልማድ አለው፣ የአሂቃር አስተምህሮ፡፡ እሱም የሰናክሬ አማካሪ ነበር (704-681 ቅ.ል.ክ)፡፡
2. ግብፅ /1ነገ. 4፡30/
   ሀ. "የቪዚር /ከፍተኛ ባለ ሥልጣን/ ፐታህ-ሆቴፐ አስተምህሮ" በ2450 ቅ.ል.ክ አካባቢ የተጻፈ፡፡ የእሱ ትምህርት በአንቀጽ ነው፣ በምሳሌያዊ መልክ/ቅርጽ ሳይሆን፡፡ እነርሱም የተዋቀሩት አባት ለልጁ እንደሚናገር ነው፣ እንዲሁ ደግሞ "የንጉሥ ሜሪ-ካ-ሪ፣" በ2200 ቅ.ል.ክ. አካባቢ፡፡
   ለ. የአሜን-ኢም-ኦፔት ጥበብ፣ 1200 ቅ.ል.ክ. አካባቢ የተጻፈ፣ እሱም ከምሳ. 22፡17-24፡22 ጋር እጅግ ተመሳሳይ ነው፡፡
3. ፍንቄ
   ሀ. ከዑጋሪት የተገኘው ማስረጃ እንደሚያሳየው በፍንቄአውያንና በዕብራይስጥ ጥበብ መካከል የቅርብ ግንኙነት አለ፣ በተለይም በልኬት /የግጥም አንጓ/፡፡ አብዛኞቹ ያልተለመዱ ቅርጾች እና ያልተለመዱ ቃላት፣ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ የጥበበ ሥነ-ጽሑፍ ላይ ያሉት አሁን የምናውቃቸው ሆነዋል፣ በራስ ሻምራ /ዑጋሪት/ አርኪዖሎጂያዊ ግኝቶች፡፡
   ለ. መኃልየ መኀልይ ከፍንቄአውያን የሰርግ መዝሙር ጋር እጅግ ተመሳሳይነት አለው፣ *ዋሰፓስ* ተብሎ ከሚጠራው፣ 600 ቅ.ል.ክ. አካባቢ ከተጻፈው፡፡
4. ከነአን /ኤር. 49፡7፤ አብድ. 8/ - ኦልብራይት፣ በዕብራውያን እና በከነአናውያን የጥበብ ሥነ-ጽሑፍ መካከል ያለውን ተመሳሳይነት ገልጧል፣ በተለይም ከራስ ሻምራ ጽሑፎች፣ ከዑጋሪት፣ በ15ኛ ክፍለ ዘመን ቅ.ል.ክ. አካባቢ የተጻፈ፡፡
   ሀ. ዘወትር አንድ ዓይነት ቃላት በጥንድ ይቀርባሉ
   ለ. በተገላቢጦሻዊ ትይዩ ሐረጎች ይቀርባሉ
   ሐ. የአርዕስት ማስታወሻ/መግለጫ አላቸው
   መ. ሙዚቃዊ ቃና /መግለጫ/ አላቸው
5. መጽሐፍ ቅዱሳዊ የጥበበ ሥነ-ጽሑፍ እስራኤላዊ ያልሆኑ በርከት ያሉ ጽሑፎችን ያካትታሉ፡
   ሀ. ኢዮብ ከኤዶም
   ለ. አጉር ከማሳ /የእስራኤላዊ ንጉሣዊ መንግሥት በሳዑዲ ዓረቢያ /ዘፍጥረት 25፡14 እና 1 ዜና መዋዕል 1፡30/
   ሐ. ልሙኤል ከማሳ

ለ. ጽሑፋዊ ባሕርያት

1. በቀዳሚነት ሁለት የተለዩ ዓይነቶች
   ሀ. ምሳሌያዊ /በመነሻነት ሥነ-ቃል/
      (1) አጭር
      (2) በቀላሉ ከባህል አኳያ በቀላሉ መረዳት የሚቻሉ /የተዘወተረ ልምምድ/
      (3) ሐሳብ የሚጭሩ - አሳሪ የእውነት መግለጫዎች
      (4) ዘወትር ተቃርኖን የሚጠቀሙ
      (5) እንዳጠቃላይ እውነት ናቸው፣ ነገር ግን ዘወትር ተለይተው የማይተገበሩ
   ለ. የረዘመ የጎለበተ ልዩ ርዕስ፣ የጽሑፍ ሥራዎች /ዘወትር በጽሑፍ መልክ/ እንደ ኢዮብ፣ መክብብ እና ዮናስ...
      (1) መነባንብ
      (2) ምልልስ
      (3) መጣጥፍ
      (4) እነርሱም የሚያተኩሩት በሕይወት ዋነኛ ጥያቄዎችና ምሥጢሮች ላይ ነው
      (5) ጠቢባኑ ሥነ-መለኮታዊውን አቋም /ሁኔታ/ ለማጠየቅ/ለመፈተን ፍቃደኛ ናቸው!
   ሐ. የጥበብ ሰውኛ መጠሪያ /ዘወትር አንስታይ/ሴቴ/ ነው፡፡ ጥበብ የሚለው ቃል ሴቴ ነው፡፡
      (1) ምሳሌ ላይ ጥበበ ዘወትር የምትገለጸው እንደ ሴት ነው
         (ሀ) በአዎንታ:
            1) 1:20-33
            2) 8:1-36
            3) 9:1-6
         (ለ) በአሉታ:
            1) 7:6-27
            2) 9:13-18
      (2) ምሳሌ 8:22-31 ላይ፣ ጥበበ እንደ ፍጥረታት በኵር ሰውኛ ዘይቤ ተገልጿል፣ እግዚአብሔር ሁሉንም በፈጠረበት /3፡19-20/፡፡ ይህም የዮሐንስ የ«ሎጎስ» አጠቃቀም ዳራ የሆነ ይመስላል፣ ዮሐንስ 1፡1፣ ይኸውም ኢየሱስ መሢሑን ለማመልከት፡፡
      (3) ይህም ደግሞ መክብብ 24 ላይ ሊታይ ይችላል፡፡
2. ይህ ሥነ-ጽሑፍ ከሕግና ከነቢያት የተለየ ነው፣ እሱ የሚመለከተው ግለሰቦችን እንጂ ሕዝቡን ባለመሆኑ፡፡ ምንም ዓይነት ታሪካዊም ሆነ አምልኳዊ ጠቃሽነት የለውም፡፡ እሱም በቀዳሚነት የሚያተኩረው በዕለታዊ፣ ስኬታማ፣ ደስተኛ፣ ግብረ-ገባዊ ሕይወት ላይ ነው፡፡
3. መጽሐፍ ቅዱሳዊ የጥበብ ሥነ-ጽሑፍ በአወቃቀሩ ከአካባቢው ጎረቤቶች ጋር ሲመሳሰል፣ በይዘቱ ግን ይለያል፡፡ አንዱ እውነተኛው አምላክ ሁሉም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥበብ የተመሠረተበት መሠረት ነው (ኢዮብ 12:13፤ 28:28፤ምሳ. 1:7፤ 9:10፤መዝ.111:10)፡፡ /እሱም በባቢሎን አፕሱ፣ ኢአ ወይም ማርዱክ ነው፡፡ በግብፅ ቶት ነው፡፡/

4. የዕብራይስጥ ጥበብ እጅግ ተግባራዊ ነው፡፡ እሱም የተመሠረተው በልምድ ላይ ነው እንጂ በልዩ መገለጥ ላይ አይደለም፡፡ እሱም የሚያተኩረው አንድ ግለሰብ በሕይወት እንዴት ስኬታማ እንደሚሆን ነው /በሕይወት ሁሉ፡ የተቀደሰ እና ሥጋዊ /ሃይማኖታዊ ያልሆነ/፡፡ እሱ መለኮታዊ ነው "ሁነኛ ተግባራዊ ፍርድ፡፡"
5. የጥበብ ሥነ-ጽሑፍ የሰዎችን አስተሳሰብ፣ ልምምድ እና አስተውሎት በመጠቀሙ ምክንያት እሱ ዓለም-አቀፋዊ፣ ባህል ተሻጋሪ ነው፡፡ እሱ ባለ አሀዳዊ አምልኮ፣ ሃይማኖታዊ ርዕዮተ-ዓለም ነው፣ እሱም ዘወትር የማይቀመጥ፣ ያም የእስራኤልን ጥበብ መገለጣዊ ያደረገ፡፡

II. ታሳቢ መገኛዎች/ምንጮች

ሀ. የጥበብ ሥነ-ጽሑፍ በእስራኤል እየጎለበተ የመጣው ለሌሎቹ የመገለጥ ዓይነቶች አማራጭ ወይም አመዛዛኝ ለመሆን ነው፡፡ (ኤር.18፡18፤ ሕዝ. 7፡26)
1. ካህን - ሕግ - መልክ /የተጠቃለለ/
2. ነቢይ - ንግር - ተግባራዊ ሐሳብ /የተጠቃለለ/
3. ጠቢብ - ጥበብ - ተግባራዊ - የተሳካ የየዕለት ሕይወት /ግለሰባዊ/
4. በእስራኤል ሴት ነቢያት እንደነበሩ ሁሉ፣ እንዲሁ ደግሞ ሴት ጠቢባን ነበሩ (II ሳሙ. 14፡1-21፤20፡14-22)፡፡

ለ. ይህ ዓይነቱ ሥነ-ጽሑፍ እየዳበረ የመጣው፡
1. እንደ ቃላዊ ተረቶች በእሳት ዙሪያ
2. እንደ ቤተሰብ ወግ፣ ወደ ወንዶች ልጆች በመተላለፍ
3. በንጉሣዊ ቤተ-መንግሥት በመጻፉና በመደገፉ፡
   ሀ. ዳዊት ከመዝሙር ጋር ይያያዛል
   ለ. ሰሎሞን ከምሳሌ ጋር ይያያዛል (1 ነገ. 4፡29-34፤መዝ. 72 እና 127)
   ሐ. ሕዝቅያስ የጥበብ ሥነ-ጽሑፍን ከማረም ጋር ይያያዛል፡፡

III. ዓላማ

ሀ. እሱ በመሠረቱ በደስታ እና በስኬት ላይ "እንዴት" እንደሚተኮር ነው፡፡ እሱ በቀዳሚነት በትኩረቱ ግለሰባዊ ነው፡፡ እሱም የተመሠረተው፡
1. ባለፉት ትውልዶች ልምምዶች፣
2. በሕይወት ያለ የምክንያትና ውጤት ግንኙነት፡፡

ለ. እሱም የኅብረተሰቡ እውነትን የማስተላፊያ እና የቀጣዩን ትውልድ መሪዎች እና ዜጎች ማሠልጠኛ መንገድ ነው፡፡

ሐ. የብኪ ጥበብ፣ ምንም እንኳ ዘወትር ባይገልጸውም፣ የኪዳኑን አምላክ ከሕይወት ሁሉ ጀርባ ይመለከተዋል፡፡

መ. እሱም ልማዳዊውን ሥነ-መለኮት መፈተሻና ሚዛን ለመጠበቂያ መንገድ ነው፡፡ ጠቢባን ነጻ-አሳቢዎች ናቸው፣ በመጽሐፍ እውነት የማይታሰሩ፡፡ እነርሱ "ለምን፣" "እንዴት፣" "ስለ ምን?" ብለው ለመጠየቅ ይደፍራሉ፡፡

IV. የመተርጎሚያ ቁልፎች

ሀ. አጭር ምሳሌያዊ መግለጫዎች
1. የሕይወትን የተለመዱ ነገሮች ያያሉ፣ እውነትን ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋሉትን፡፡
2. ማዕከላዊውን እውነት በቀላል አብራሪ ዓረፍተ-ነገር ይገልጻሉ፡፡
3. ዐውደ-ጽሑፍ፣ ትይዩ ምንባቦችን በተመሳሳይ ርዕሰ-ጉዳይ ዙሪያ ለማግኘት አይረዱም፡፡

ለ. ረጅም ጽሑፋዊ ሥራዎች/መልኮች
1. የሙሉውን ማዕከላዊ እውነት መግለጽህን ርግጠኛ ሁን፡፡
2. ከዐውደ-ጽሑፉ ላይ ቁጥሮችን/ጽሑፎችን አትውሰድ፡፡
3. የጽሑፉን ታሪካዊ ሁነት ወይም ምክንያት አረጋግጥ፡፡

ሐ. አንዳንድ የተለመዱ የተሳሳተ ትርጓሜዎች /ፊ እና ስቱዋርት፣ *መጽሐፍ ቅዱስን ከነ ሙሉ ጠቀሜታው እንዴት ማንበብ እንደሚቻል*፣ ገጽ 207(Fee & Stuart, *How to Read the Bible for All It Is Worth*, p. 207)
1. ሰዎች ሙሉውን የጥበብ መጽሐፍ አያነቡትም /እንደ ኢዮብ እና መክ./ ብሎም ማዕከላዊ እውነቱን አይፈልጉም፣ ነገር ግን ከዐውደ-ጽሑፉ የመጽሐፉን ከፊል ይመዙና በዘመናዊው ሕይወት ላይ በጥሬው ተግባራዊ ያደርጉታል፡፡
2. ሰዎች የጽሑፋዊ ዘውጉን የተለየ መሆን አይረዱም፡፡ ይህ እጅግ የታመቀ እና ዘይቤአዊ የሆነ የጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ ሥነ-ጽሑፍ ነው፡፡
3. ምሳሌዎች የአጠቃላይ እውነት መግለጫዎች ናቸው፡፡ እነርሱ የእርማት መሣርያዎች ናቸው፣ በተለየ እውነት፣ በእያንዳንዱ ጉዳይ፣ በየጊዜው እንኳ ባይሆን የእውነት መግለጫ ላይ፡፡

V. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎች

ሀ. ብሉይ ኪዳን
1. ኢዮብ
2. መዝሙር 1፣ 19፣ 32፣ 34፣ 37፣ 49፣ 73፣ 104፣ 107፣ 110፣ 112፣ 127-128፣ 133፣ 147፣ 148
3. ምሳሌ

4. መክብብ
5. መኃልየ መኃልይ
6. ሰቆቃወ ኤርምያስ
7. ዮናስ

ለ. ተረፈ/ተጨማሪ ቅዱስ ቃላዊ
1. ጦቢት
2. የቢን ሲራክ ጥበብ /መክብብ/
3. ጥበበ-ሰሎሞን /የጥበብ መጽሐፍ/
4. IV መቃብያስ

ሐ. አዲስ ኪዳን
1. የኢየሱስ ምሳሌዎችና ምስያዎች
2. የያዕቆብ መጽሐፍ

# የዕብራይስጥ ቅኔ

I. መግቢያ

ሀ. ይህ ዓይነቱ ሥነ-ጽሑፍ የብሉይ ኪዳንን 1/3 ይሸፍናል፡፡ እሱም በተለየ መልኩ "ነቢያት" እና "ጽሑፎች" ምድብ ላይ የተለመደ ነው፣ በዕብራይስጥ ካኖን፡፡

ለ. እሱም ከእንግሊዝኛ ቅኔ እጅግ የተለየ ነው፡፡ የእንግሊዝኛ ቅኔ እያደገ የመጣው ከግሪክ እና ከላቲን ቅኔ ነው፡፡ የዕብራይስጥ ቅኔ ከከነአን ቅኔ ብዙ የሚጋራው አለ፡፡ ቅላጼአዊ ስንኞች/መስመሮች፣ ልኬት ወይም ዜማ በቅርብ ምስራቅ ቅኔ አይገኝም፡፡

ሐ. የአርኪዎሎጂ ግኝት፣ ከእስራኤል በስተሰሜን ዑጋሪት /ራስ ሻምራ/ ላይ፣ ሊቃውንትን ረድቷቸዋል፣ የብኪን ቅኔ ለመረዳት፡፡ ይህ ከ15ኛው ክፍለ-ዘመን ቅ.ል.ክ የሆነ ቅኔ ከመጽሐፍ ቅዱስ ቅኔ ጋር ግልጽ የሆነ ግንኙነት አለው፡፡

II. የቅኔ አጠቃላይ ባሕርያት

ሀ. እሱ እጅግ እምቅ ነው፡፡

ለ. እሱ እውነትን፣ ስሜትን ወይም ልምምድን በምናባዊ መልኩ ለመግለጽ ይሞክራል፡፡

ሐ. እሱ በቀዳሚነት የጽሑፍ ነበር፣ የቃል ሳይሆን፡፡ እሱ አወቃቀሩ ጥብቅ ነው፡፡ ይህም አወቃቀር የሚገለጸው፡
1. ተመጣጣኝ ስንኞች/መስመሮች /ትይዩነት/
2. የቃላት ጨዋታ /ማቀያየር/

III. መዋቅር

ሀ. ቢሾፕ ሮበርት ሎውዝ፣ በመጽሐፉ፣ *Lectures on the Sacred Poetry of the Hebrews* (1753) የመጀመሪያው ነው፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅኔን እንደ ሚዛናዊ የአስተሳሰብ ስንኞች ባሕርይ ለማስቀመጥ፡፡ አብዛኞቹ ዘመናዊ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች የቅኔን ስንኞች ለማሳየት ተበጅተዋል/ተስተካክለዋል፡፡
1. ተመሳሳዮች - ስንኞቹ ተመሳሳይ ሐሳቦችን በተለያየ ቃላት ይገልጻሉ፡
   ሀ. መዝሙር 3:1፤ 49:1፤ 83:14፤ 103:3
   ለ. ምሳሌ 20:1
   ሐ. ኢሳይያስ 1:3
   መ. አሞጽ 5:24
2. ተቃራኒ - ስንኞቹ ተቃራኒ ሐሳቦችን ይገልጻሉ፣ በተቃርኗዊ መንገድ ወይም አዎንታዊ እና አሉታዊ በማስቀመጥ፡
   ሀ. መዝሙር 1:6፤ 90:6
   ለ. ምሳሌ 1:6፣29፤ 10:1፣12፤ 15:1፤ 19:4
3. መደባለቅ/ማሻሻል - ቀጣዮቹ ሁለት ወይም ሦስት ስንኞች ሐሳቡን ያዳብሩታል - መዝ. 1:1-2፤ 19:7-9፤ 29:1-2

ለ. Briggs በመጽሐፉ ላይ፣ *General Introduction to the Study of Holy Scripture* (1899) የዕብራይስጥ ቅኔ ትንተናን ቀጣይ ደረጃ አዳብሯል፡
1. ተምሳሌታዊ - አንደኛው ሐረግ ጥሬአዊ እና ሁለተኛው ዘይቤአዊ፣ መዝ. 42:1፤ 103:3፡፡
2. ከላይማታዊ ወይም ደረጃ-መሰል - ሐረጎቹ እውነትን የሚገልጹት ሽቅብ በሚሄድ መልኩ ነው፣ መዝ. 19:7-14፤ 29:1-2፤ 103:20-22፡፡
3. የታጠፈ ወይም የተገላቢጦሽ - ተለጣጣቂነት ያላቸው ሐረጋት፣ ዘወትር ቢያንስ አራቱ በውስጣዊ አወቃቀር ይዛመዳሉ፣ ስንኝ/መስመር 1 ከ4 ጋር እና 2 ከ3 ጋር - መዝ. 30፡8-10ሀ

ሐ. G.B. Gray በመጽሐፉ፣ የዕብራይስጥ ቅኔ መልኮች (*The Forms of Hebrew Poetry* 1915) የሚዛናዊ ሐረጋትን ጽንሰ-ሐሳብ አዳብሯል፣ በተጨማሪ፡
1. ፍጹም የተመዛዘነ - ይኸውም በአንደኛው መስመር የሚገኘው እያንዳንዱ ቃል፣ ከሁለተኛ መስመር በሚገኝ ቃል ተደግሟል፣ ተመዛዝኗል - መዝሙር 83፡14 እና ኢሳይያስ 1፡3
2. ያልተፈጸመ ሚዛን፣ ይኸውም ሐረጋቱ ተመሳሳይ ርዝመት የላቸውም - መዝ. 59:16፤ 75:6

መ. የድምጽ ፈርጅ ዓይነቶች
1. በፊደላት መጫወት/ማቀያየር /መስቀልያ/ /ዕንቆቅልሻዊ/
2. በተናባቢዎች መጫወት/መቀያየር /ተናባቢያዊ/
3. በአናባቢ መጫወት/መቀያየር /አናባቢያዊ/
4. በቃላት ድግግሞሽ መጫወት /የቃላት አስቂኝ አጠቃቀም/
5. ተመሳሳይ ድምጽ ባላቸው ቃላት መጠቀም /ድምጸ-ቀድ/
6. ልዩ አከፋፈትና አዘጋግ /አካታች/

ሠ. በርካታ ዓይነት ቅኔዎች በብሉይ ኪዳን ይገኛሉ፡፡ አንዳንዶቹ ርዕስ-ተኮር ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ ቅርጽ-ተኮር ናቸው፡
1. የመሰጠት መዝሙር - ዘኁ. 21:17-18
2. የሥራ ዘፈኖች - (ተጠቅሰዋል፣ ነገር ግን አልተመዘገቡም፣ መሳ. 9:27) ላይ፤ ኢሳ. 16:10፤ ኤር. 25:30፤ 48:33

3. የሙገሳ ግጥሞች - ዘኊ. 21:27-30፤ ኢሳ. 23:16
4. ማኅሌተ-ገንቦ /የመጠጥ ዘፈን/ - አሉታዊ፣ ኢሳ. 5:11-13፤ አሞጽ 6:4-7 እና አዎታዊ፣ ኢሳ. 22:13
5. የፍቅር ግጥሞች - መኃልየ መኃልይ፣ የሠርግ ዕንቆቅልሽ - መሳ. 14:10-18፣ የሰርግ ዘፈን - መዝ. 45
6. ሰቆቃ/ሙሾ - (ተጠቅሷል ግን አልተመዘገበም፣ II ሳሙ. 1:17 እና II ዜና. 35:25 ላይ) II ሳሙ. 3:33፤ መዝ. 27፣ 28፤ ኤር. 9:17-22፤ ሰቆ.፤ ሕዝ. 19:1-14፤ 26:17-18፤ ናሆ. 3:15-19
7. የጦርነት ዘፈኖች - ዘፍ. 4:23-24፤ ዘጸ. 15:1-18፤ ዘኊ. 16:35-36፤ ኢያ. 10:13፤ መሳ. 5:1-31፤ 11:34፤ I ሳሙ. 18:6፤ II ሳሙ. 1:18፤ ኢሳ. 47:1-15፤ 37:21
8. ልዩ የመሪ ቡራኬ ወይም ምርቃት - ዘፍ. 49፤ ዘኊ. 6:24-26፤ ዘዳ. 32፤ II ሳሙ. 23:1-7
9. አስማታዊ ጽሑፎች - በለዓም፣ ዘኊ. 24:3-9
10. ቅዱስ ግጥሞች - መዝሙር
11. ዕንቆቅልሻዊ መስቀልያ ግጥሞች - መዝ. 9፣34፣37፣119፤ ምሳ. 31:10 እና ሰቆቃወ 1-4
12. ርግማን - ዘኊ. 21:22-30
13. የቀልድ/የትችት ግጥሞች - ኢሳ. 14:1-22፤ 47:1-15፤ ሕዝ. 28:1-23

IV. የዕብራይስጥን ቅኔ ለመተርጎም መመሪያ

ሀ. የአንጓውን ወይም የግጥም ክፍሉን ማዕከላዊ እውነት መፈለግ /ይህ ዓይነት በዝርው /ስድ ንባብ/ እንዳለ አንቀጽ ነው፡፡/ የተመት የመጀመሪያው ዘመናዊ ትርጉም ነው፣ ቅኔን በአንጓዎች የለየ፡፡ ዘመናዊ ትርጉሞችን አወዳድር፣ ለረጂ የይዘት እይታ፡፡

ለ. ዘይቤአዊ አባባሎችን ለይና በዝርው ግለጽ፡፡ ይህ ዓይነቱ ሥነ-ጽሑፍ እጅግ የታመቀ፣ አብዛኛው በአንባቢው ይሞላ ዘንድ የተተወ መሆኑን አስታውስ፡፡

ሐ. ረጅም ጉዳይ - ተኮር ግጥሞችን ከጽሑፋዊ ዐውዳቸው እና ከታሪካዊ መቼታቸው ጋር ማዛመድህን ርግጠኛ ሁን፡፡

መ. መሳፍንት 4 እና 5 እጅግ ረጂ ነው፣ ቅኔ ታሪክን እንዴት እንደሚገልጽ ለማየት፡፡ መሳፍንት 4 ዝርው ሲሆን፣ መሳፍንት 5 ደግሞ ቅኔ ነው፣ የአንድ ዓይነት ሁነት፡፡

ሠ. የተካተቱትን የትይዩ ዓይነቶች ለመለየት ሞክር፣ ተመሳሳይ ቢሆኑ፣ ተቃራኒ፣ ወይም ድብልቅ፡፡ ይህ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

# መግቢያ ኢዮብ

I. የመጽሐፉ ስም

ሀ. መጽሐፉ የተሰየመው በዋናው ገጸ-ባሕርይ ስም ነው፡፡ ኢዮብ እጅግ የተለመደ ስም ነው፡፡ የትርጉሙ ፍችም፡
1. "አባት የት ነው"
2. "ጠላትነት"
3. "የሚጸጸት"

ለ. ይህ ብርቱ፣ ጥበባዊ እና ትርጉም ያለው መጽሐፍ ነው፡
1. ሉተር የሚለው፣ "እሱ አስደናቂ እና እጅግ ከፍ ያለ ነው፣ ከሌላ ከማናቸውም የቅዱስ ቃሉ መጽሐፍ ይልቅ"
2. ቴኒሰን የሚለው፣ "እሱ ታላቅ ቅኔ ነው፣ ለጥንታዊውም ሆነ ለዘመናዊው፡፡"
3. ካርሊሊ የሚለው፣ "በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም ሆነ ከእርሱ ውጭ እኩል የሆነ ደረጃ/ማዕርግ ያለው አልተጻፈም፡፡"

II. ቅዱስ ቃልነቱ /ካኖናይዜሽን/

ሀ. እሱ የዕብራይስጥ ካኖን በጽሑፎች ምድብ ውስጥ ነው፡፡

ለ. እሱ በዕብራይስጥ ኤምኤስኤስ የተቀመጠው ከዘዳግም መጽሐፍ ቀጥሎ ነው፣ ምክንያቱም ሁለቱም ኢዮብ እና አብርሃም ከተመሳሳይ ታሪካዊ ዘመን ጋር ስለሚገጥሙ፡፡

ሐ. የአሁኑ የኢዮብ አቀማመጥ ስፍራ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ የቅኔ መጻሕፍት የተጀመረው በቫልጌት ሲሆን፣ የጸናውም በትሬንት ጉባኤ ነው፡፡

III. ዘውግ

ሀ. ኢዮብ በጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ እጅግ ከሚታወቀው "የጥበብ ሥነ-ጽሑፍ" ከሚባለው ጽሑፋዊ ዘውግ ክፍል ነው፡፡

ለ. መጽሐፉ በቀዳሚነት ዝርው/ስድ ንባብ መግቢያ /1-2/ እና መዝጊያ /42/ ያለው የቅኔ መጽሐፍ ከመሆኑ የተነሣ፣ በሊቃውንት መካከል ስለዚህ ዘውግ ብዙ ውይይት ተካሂዷል፡
1. ታሪካዊ ትርክት
2. ድራማዊ አቀራረብ፣ የፍልስፍናዊ/ሥነ-መለኮታዊ ጭብጥ
3. ምሳሌ

ሐ. ኢዮብ አንዳንድ ጽሑፋዊ ተመሳሳይነት አለው /ነገር ግን ሥነ-መለኮታዊ ጭብጥ ሳይሆን፡
1. የሱሜርያን ጽሑፍ፣ "ሱሜርያን ኢዮብ" የሚባለው ከ2000 ቅ.ል.ክ አካባቢ ጊዜ
   ሀ. አንደኛ መደብ አቤቱታ/ምሬት አሰሚ
   ለ. ስለ የማይገባው ሥቃይ
   ሐ. በመለኮት የተተወ
   መ. በፍርድ ቤት እንዲታይለት የሚጠይቅ
   ሠ. ኃጢአት የተገለጠ
2. የባቢሎን ጽሑፍ፣ "የጥበብን አምላክ አመሰግናለሁ" ተብሎ የሚጠራ፡፡ እሱም አንዳንድ ጊዜ፣ "የባቢሎን ኢዮብ" ተብሎ ይጠራል፣ ከ1300 – 1100 ቅ.ል.ክ አካባቢ ጊዜ፡፡
   ሀ. አንደኛ መደብ መነባንብ
   ለ. በአማልክት ችላ ተባለ እንዲሁም በጓደኞቹ ተተወ
   ሐ. የጤናና ሀብት በመጨረሻ መመለስ
3. የባቢሎን ጽሑፍ፣ "ስለ ሰው መከራ ምልልስ" ተብሎ የሚጠራ፡፡ እሱም አንዳንድ ጊዜ "የባቢሎን ሥነ-መለኮት/ቴዎዲሲ" ተብሎ ይጠራል፣ ከ1000 ቅ.ል.ክ. አካባቢ ጊዜ፡፡
   ሀ. ዕንቆቅልሻዊ ቃል/ትዕዛዝ ስለ መከራ
   ለ. መከራ በሚቀበልና በጓደኛ መካከል
   ሐ. ጓደኛ ልማዳዊውን አመለካከት ይከላከላል፣ መከራ ተቀባዩም ግልጽ የሆኑትን ችግሮች ለቅሞ ያወጣል/ያመለክታል፣ እንደ ኃጢአተኛ መበልጸግ ያሉትን
   መ. ችግሮቹ ሁሉ ከሰው ውድቀት የመጡ ናቸው፣ በተወሰነ ነጥብ
4. የግብጽ ጽሑፍ፣ "የአንደበተ-ርቱዕ ባላገር የተቃውሞ ንግግር" ተብሎ የሚጠራ፡፡
5. የግብጽ ጽሑፍ፣ "አንዱ ከነፍሱ ጋር ያደረገው ጠብ/ውዝግብ፣ ሕይወት ስላታከተው" ተብሎ የሚጠራ፡፡ እሱም ደግሞ "ራስን ከመግደል ጋር ጠብ" በሚል ይጠራል፡፡

መ. መጽሐፉ በርከት ያሉ የዘውግ ዓይነቶችን ይዟል፡፡ እሱም ከማናቸውም ምድብ ጋር አይገጥምም፡፡
1. መነባንብ/ለራስ መናገር
2. ምልልስ
   ሀ. ከጓደኞች
   ለ. ከእግዚአብሔር
3. በዝርው የሚከፍት እና የሚዘጋ

IV. ደራሲነት

ሀ. የማን መጽሐፍነቱ አይታወቅም፡፡

ለ. ባባ ባትራ 14ለ የሚያስረግጠው፣ ሙሴ መጽሐፉን እንደጻፈው ነው፡፡ አንዳንድ የዕብራይስጥ ጽሑፎች እና የሶርያ ትርጉም፣ ፔሺታ ከዘዳግም ቀጥለው ያስቀምጡታል፡፡

ሐ. የአይሁድ ፈላስፋ የኢዮብን ታሪካዊ ሕይወት በመውሰድ ፍልስፍናዊ፣ ሥነ-መለኮታዊ እውነትን ለማስተማር አሻሽሎት ሊሆን ይችላል፡፡

መ. አንዳንድ ሊቃውንት የሚያስረግጡት ግጥሙ፣ ምዕራፍ 3-41፣ የተጻፈው በጥንታዊ ደራሲ ሲሆን፣ የዝርው ቅድመ-ታሪክ /1-2/ እና ድኅረ-ታሪክ /42/ ተጨማሪ የተደረገው በኋለኛ አዘጋጅ ነው፡፡
የሆነ ሆኖ፣ መታወስ የሚያስፈልገው፣ እኛ በዘመናዊ፣ ምዕራባዊ ባህል የጥንታዊውን ቅርብ ምስራቅ የአጻጻፍ ፈርጅ እና ብልሃት ሙሉ ለሙሉ መረዳት አለመቻላችን ነው፡፡ የሐሙራቢ ሕግ የሚከፍተውና የሚዘጋው በቅኔ ሲሆን፣ ዝርው በመካከል አድርጎ ነው፡፡

ሠ. ኢዮብ ሰውየው
1. ኢዮብ የድሮ ታሪካዊ ሰው ነው፣ ምክንያቱም፡
   ሀ. እሱ ሕዝቅኤል 14፡14 ፣ 20 እና ያዕቆብ 5፡1 ላይ በመጠቀሱ
   ለ. ስሙ፣ ምንም እንኳ ተመሳሳይ ሰው ላይሆን ቢችልም፣ በአርማንያ ጽሑፎች፤ በግብፅ የውግዘት ጽሑፎች፤ በማሪ ጽሑፎች፣ እና በዑጋሬታዊ ጽሑፎች ላይ ይገኛል
   ሐ. የገንዘብ መቁጠሪያ 42፡11 ላይ የሚገኘው፣ ኬሲታህ፣ በሌላ ስፍራ ላይ የሚገኘው ዘፍ. 33፡19 እና ኢያ. 24፡32 ላይ ብቻ ነው
2. ኢዮብ በግልጽ አይሁዳዊ አይደለም
   ሀ. የእግዚአብሔር አጠቃላይ ስሞች አጠቃቀም፣ በኢዮብ እና በጓደኞቹ፣ በንግግራቸው
      1. *Elohim* /እግዚአብሔር/ ምዕራፍ 1-2 እና 20፣ 28፣ 32፣ 34፣ 38
      2. *El* /እግዚአብሔር/ ብዙ ጊዜያት
      3. *Shaddai* /ሁሉን ቻይ/ ብዙ ጊዜያት
   ለ. ከኤዶም የሆነ ጠቢብ ሰው ይመስላል
      1. *ዖፅ* (ዘፍ. 36:28፤ ኤር. 25:20፤ ሰቆ. 4:21)
      2. ቴማን (ዘፍ. 36:11)
      3. "የምስራቅ ሰው" ከሚለው ጋር የሚነጻጸር (ኢዮብ 1:3፤ መሳ. 6:3፣33፤ ኢሳ. 11:14፤ ሕዝ. 25:4፣10)

V. ጊዜው

ሀ. የመጽሐፉ ታሪካዊ መቼት ከአባቶች ጊዜ ጋር ይገጥማል፣ ከሁለተኛው ሚሊኒየም ቅ.ል.ክ፡፡ አንዳንድ ምሳሌ የሚሆኑ፡
1. ኢዮብ ለቤተሰቡ እንደ ካህን ያገለግላል /1፡5/
2. የኢዮብ ረጅም ዕድሜ -- 140+ ዓመት /42፡16/
3. ከፊል ዘላናዊ የሕይወት ስልት፣ የቤት እንስሳትን በማርባት፡፡
4. የሳባውያን ወሮበላ ቡድኖችና የከለዳውያን ዘራፊዎች /1፡15፣17/
5. ኢዮብ የዓመቱን ከፊል ከተማ ውስጥ ሲኖር፣ የዓመቱን ከፊል ደግሞ ከከብቶቹ ጋር ይኖራል፡፡

ለ. ዘውጉ የመጽሐፉን ጊዜ ያደረገው የጥበብ ሥነ-ጽሑፍ መውጣት በነበረበት ዘመን ነው፡፡ ይህም ከዳዊት ጊዜ ጀምሮ እስከ ይሁዳ ነገሥታት፣ በተለይም በሕዝቅያስ ጊዜ ነው፡፡

ሐ. አር.ኬ. ሃሪሰን የሚያምነው መጽሐፉ የተጻፈበት ጊዜ፣ ከአምስተኛው ክፍለ-ዘመን ቅ.ል.ክ. መጨረሻ ወዲህ አይሆንም፣ ይህም ከማስረጃው ጋር በተሻለ ይገጥማል፡፡

VI. ታሪካዊ መቼት

ሀ. የዖፅ ርግጠኛ ስፍራ አልለየም፡፡ ሁለት ዋነኛ ንድፈ-ሐሳቦች አሉ፡
1. በኤዶም ምድር
   ሀ. በጠቢባን/ብልህ ሰዎቹ የሚታወቀው፣ ኤር. 49፡7
   ለ. ከሦስቱ አንደኛው ጓደኛው ከቴማን ነው፣ በኤዶም ያለ ከተማ፡፡ እሱም የተሰየመው በዔሳው ዝርያ ነው፣ ዘፍ. 36፡15፡፡
   ሐ. ዖፅ እንደ ሴይር ሆሪው/ሆሪአዊው ዝርያ/ትውልድ ተጠቅሷል፣ ዘፍ. 36፡20-30፡፡ እነዚህ ሕዝቦች ከኤዶም አገር/ስፍራ ጋር ይዛመዳሉ፡፡
   መ. ዖፅ ከኤዶም ጋር ነው የተገለጸው፣ ሰቆ. 4፡21 ላይ፡፡
2. በአራም ምድር
   ሀ. አራማዊ የአጻጻፍ ስልት እና ቃላት በኢዮብ ላይ በተደጋጋሚ ታይተዋል፡፡
   ለ. የከለዳውያን ዘራፊዎች መገኘት 1፡17፡፡
   ሐ. ዘፍ. 10፡23 ዖፅን ከአራም ጋር ያስተሳስራል፣ ዘፍ. 22፡20-22፡፡
3. ዖፅ የሚለው ስም በርከት ያሉ ከፍልስጥኤም በስተምስራቅ ያሉ ነገዶችን ያካትታል፣ በስተሰሜን ከአራም እስከ ኤዶም በስተደቡብ፡፡

VII. ጽሑፋዊ ምድቦች

ሀ. ዝርው ቅድመ-ታሪክ /የሰማያዊ ጉባኤ/፣ 1-2

ለ. የኢዮብ ጓደኞች፣ 3-37
1. የኢዮብ ሰቆቃ፣ 3
2. ሦስት ዙር ምልልስ፣ 4-31

ሀ. የመጀመሪያው ዙር፣ 4-14
   (1) ኤልፋዝ፣ 4-5
   (2) ኢዮብ፣ 6-7
   (3) በልዳዶስ፣ 8
   (4) ኢዮብ፣ 9-10
   (5) ሶፋር፣ 11
   (6) ኢዮብ፣ 12-14
ለ. ሁለተኛው ዙር፣ 15-21
   (1) ኤልፋዝ፣ 15
   (2) ኢዮብ፣ 16-17
   (3) በልዳዶስ፣ 18
   (4) ኢዮብ፣ 19
   (5) ሶፋር፣ 20
   (6) ኢዮብ፣ 21
ሐ. ሦስተኛው ዙር፣ 22-31
   (1) ኤልፋዝ፣ 22
   (2) ኢዮብ፣ 23-24
   (3) በልዳዶስ፣ 25
   (4) ኢዮብ፣ 26
   (5) የኢዮብ ማጠቃለያ፣ 27
   (6) የደራሲው ማስታወሻ /የጥበብ ምስጋና እና ምሥጢር/፣ 28
   (7) የኢዮብ መነባንብ፣ 29-31

3. የኤሊሁ አስተያየት፣ 32-37
   ሀ. ዝርው፣ 32፡1-5
   ለ. ቅኔ፣ 32፡6-37፡24

ሐ. እግዚአብሔር ለኢዮብ ምላሽ ሰጠ፣ 38፡1-42፡6
1. እግዚአብሔር እንደ ፈጣሪ ምላሽ ሰጠ፣ 38-39
2. እግዚአብሔር እንደ ፈራጅ ምላሽ ሰጠ፣ 40፡1-2፣6-41፡34
3. ኢዮብ ተጸጸተ፣ 40፡3-5 እና 42፡1-6

መ. ዝርው ድኅረ-ታሪክ፣ 42፡7-17

VIII. ዋነኛ ሐቆች

ሀ. ይህ መጽሐፍ የተጻፈው ልማዳዊውን የኪዳን ሥነ-መለኮት ለማመዛዘን ነው /ዘዳ. 27-29/ ማለትም ጻድቃን በዚህ ሕይወት እንደሚባረኩ እና ኃጢአተኞች በዚህ ሕይወት እንደሚቀጡ፡፡ ይህ ልማዳዊ የአይሁድ ሥነ-መለኮት የሚተላለፈው /ተግባቦት የሚያገኘው/ በሦስቱ የኢዮብ ጓደኞች ንግግር ነው፡፡ ደግሞም ሲያስተውሉት አስገራሚ የሚሆነው፣ ለልማዳዊው ሁኔታ የተለየ ፈታኝ ሆኖ የቀረበው እንደ ኤሊሁ ያለው ወጣት ነው፣ እሱም በይፋ ሁለቱንም ኢዮብና ሦስቱን በዕድሜ የሚበልጡትን ጓደኞቹን ያረመውና ያስተካከለው፡፡

ለ. ይህ መጽሐፍ፣ እግዚአብሔር ጻድቅ እንደሆነና በመጨረሻም ነገሮችን ትክክል/መልካም እንደሚያደርግ የሚያስረግጥ ነው፣ በዚህ ዓለምም ሆነ፣ /ኢዮብ እንደተመለሰለት፣ 42፡10-17/ ወይም በሚመጣው (14:7-17፤ 19:23-27፡፡)

ሐ. መከራ ሁሉ ከግል ኃጢአት የሚመጣ አይደለም፡፡ ይሄንን ነው ሦስቱ ጓደኞች ያስረገጡት (ዝኪ. 4:7-11፤ 8:3-7፤ 11:13-15፤ 15:12-16፤ 22:21-30)፡፡ ይህ ፍትሐዊ ያልሆነ የወደቀ ዓለም ነው፡፡ አንዳንዴ ኃጢአተኞች ይበለጽጋሉ /መዝ. 73/፡፡ ጻድቅም ዘወትር መከራ ይቀበላል፡፡ ሰይጣን ኢዮብን በጸጋው/በብልጽግና በመታመኑ ከሰሶታል፡፡

መ. ይህ መጽሐፍ ስለ መንፈሳዊው ዓለም ውስጠት/ይዘት ይሰጠናል፡፡ ከሳሽ አለ፣ የታወቀ የሰው ጠላት፡፡ ሰይጣን የእግዚአብሔር አገልጋይ ነው፣ ከሳሽ መልአክ በብኪ (A.B. Davidson, *An Old Testament Theology*, published by T & T Clark pp. 300-306)፡፡ ለመገምገም አስቸጋሪ የሚሆነው፣ ሰይጣን የሚለው ቃል ለምን የተወሰነ አንቀጽ እንዳለው ነው፡፡ እሱ ከስሙ ይልቅ ተግባሩን ስለሚገልጽ/ስለሚያመለክት፡፡ በዛ ያሉ አካላት "ከሳሽ" በሚል ተገልጸዋል፡፡
1. ሰው /አካል/
   ሀ. I ሳሙ. 29:4
   ለ. II ሳሙ. 19:22
   ሐ. I ነገሥ. 5:4
   መ. I ነገሥ. 11:14-22፣ 23-25
   ሠ. መዝ. 71:13
   ረ. መዝ. 109:6፣ 20፣ 29
2. መልአካዊ
   ሀ. የእግዚአብሔር መልአክ - ዘኍ. 22:21
   ለ. ሰይጣን - ኢዮብ 1-2፣ I ዜና. 21:13፤ ዘካ. 3:1-2

ሠ. እግዚአብሔር ለኢዮብ ፈጽሞ አልገለጠለትም፣ ከመከራው በኋላ ያለውን ምክንያት፡፡ ሕይወት ምሥጢራዊ ነው፡፡ በእግዚአብሔር መታመን እጅግ ጠቃሚ ነው፣ ከመረጃ ይልቅ!

IX. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት እና ሰዎች በአጭሩ የሚገለጹ /NASB/


ሀ. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት
1. ፍጹም፣ 1:1፤ 2:3 (NASB እና NIV)
2. የአምላክ ልጆች፣ 1:6፤ 2:1 (NIV፣ "መላእክት")


3. ገል፣ 2:8 (NIV፣ "የሸክላ ስባሪ")
4. ሲኦል፣ 7:9፤ 11:8 (NIV፣ "መቃብር")
5. ደንገል፣ 8:11 (NASB እና NIV)
6. ረዓብ፣ 9:13፤ 26:12-13 (NASB እና NIV)
7. ሲኦል፣ 26:6፤ 28:22፤ 31:12 (NIV፣ "ጥፋት")
8. ቤዛ፣ 33:24፤ 36:18 (NASB እና NIV)
9. ሌዋታን፣ 3:8፤ 41:1 NASB እና NIV)
10. ጉማሬ /ብሔሞት/፣ 40:15 (NASB እና NIV)
11. ቲዎዲሲ/የሥነ-መለኮት ዓይነት

ለ. ሰዎች
1. "የምስራቅ ሰዎች፣" NASB፣ /NIV፣ "የምስራቅ ሰዎች ሁሉ"/ 1፡3
2. ሰይጣን፣ 1፡6
3. ሳባውያን፣ 1፡15
4. ከለዳውያን፣ 1፡17
5. ሁሉን የሚችል ሻዳይ *(Shaddai)*፣ 6:4፣14፤ 13:3፤ 22:3፣26
6. ኤሊሁ፣ 32፡2

X. የካርታ ስፍራዎች /አመላካቾች/
1. *ዖጽ*፣ 1፡1
2. ቴማን፣ 4፡1
3. ኤዶም

XI. የተማሪ የውይይት ጥያቄዎች
1. እግዚአብሔርን መፍራት ምን ማለት ነው? 1:1፣9፤ 28:28
2. ኢዮብ ኃጢአት የሌለበት (ነውር የሌለበት) ነበርን? 1:1፣8፣22
3. "የምስራቅ ሰዎች" እነማን ናቸው?
4. ኢዮብ ለቤተሰቡ እንደ ካህን የሚያገለግልበት እውነታ፣ የመጽሐፉን ዘመን ለማወቅ እንዴት ይረዳል? 1፡5
5. ሰይጣን በሰማይ በእግዚአብሔር ፊት መሆኑ አንድምታው ምንድነው? 1፡6-12
6. ሰይጣን ኢዮብን በእግዚአብሔር ፊት የከሰሰው በምን መልኩ ነው? 1:6-12፤ 2:1-6
7. 14:7-17 እና 19:23-29 *የሥጋ* ትንሣኤን ያስተምራልን፣ ለምን ወይም ለምን አይደለም?
8. እግዚአብሔር የኢዮብን ጥያቄ ፈጽሞ አልመለሰምን?
9. ኢዮብ ኃጢአት መሥራቱን ፈጽሞ አልተቀበለምን? 40:3-5፤ 42:1-6
10. እግዚአብሔር ሦስቱ የኢዮብ ጓደኞች ምን እንዲያደርጉ ነገራቸው? /42/
11. ኢዮብ ራሱን ጻድቅ ማድረግ ማስረገጡ በእግዚአብሔር ባሕርይ ላይ ምን ተጽዕኖ አመጣ? 40፡8


ANCIENT
NEAR EAST
N
S
E
W


PALESTINE
0 10 20 30 40
SCALE IN MILES

# መግቢያ ለመዝሙረ ዳዊት

I. የመጽሐፉ ስም

ሀ. በዕብራይስጥ ርዕሱ "የምስጋና መዝሙር" ወይም "ውዳሴ" (*Tehillim ቴሂሊም*) ነው፡፡ ይህ አስገራሚ ነው ምክንያም አብዛኞቹ መዝሙራት ወዮታ ወይም ምሬት በመሆናቸው፡፡

ለ. በLXX ርዕሱ "(*psalmos ሳልምስ)* ነው፣ ፍችውም "ጅማት መነተት/መልቀቅ" /የክር ሙዚቃ መሣርያ/፡፡ ይህ የግሪክ ቃል ለመዝሙር ጥቅም ላይ ውሏል፣ ሉቃስ 20:42፤ 24:44 እና ሐዋ. 1:20፡፡ መዝሙራት ሁሉ ከሙዚቃ ጋር ታጅበው ይዘመራሉ ማለት አይደለም፣ ነገር ግን ይህ የሙሉው መጽሐፍ ርዕስ እየሆነ በመምጣቱ እንጂ፣ LXX፡፡

II. ቅዱስ ቃልነቱ /ካኖናዊነት/

ሀ. መዝሙር "ጽሑፎች" የሚባለው የዕብራይስጥ ካኖን ሦስተኛ ምድብ ክፋይ ነው፡፡ ይህ የዕብራይስጥ ካኖን ምድብ የተደራጀው፡
1. የጥበብ ሥነ-ጽሑፍ
   ሀ. ኢዮብ
   ለ. መዝሙር
   ሐ. ምሳሌ
2. የበዓላት መጻሕፍት (Megilloth ሜጊሎዝ)
   ሀ. ሩት
   ለ. መክብብ
   ሐ. መኃልየ መኃልይ
   መ. ሰቆቃወ ኤርምያስ
   ሠ. አስቴር
3. ታሪካዊ መጻሕፍት
   ሀ. ዳንኤል
   ለ. ዕዝራ
   ሐ. ነህምያ
   መ. ዜና መዋዕል

ለ. መዝሙር እንደ ስብስብ የተገኙት LXX እና የሙት ባሕር ጥቅሎች ላይ ነው፡፡

ሐ. መዝሙር በአኪ ተዘውትሮ የሚጠቀስ ነው፣ ከሌላው የብኪ መጽሐፍ ይልቅ፡፡

III. ዘውግ

ሀ. ይህ የጽሑፍ ዓይነት በጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ የተለመደ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መዝሙራት የውዳሴ ዓይነቶችን ከባቢሎን፣ ግብፅ እና ከነአን ይካፈላሉ፡፡ ሊቃውንት የቀረበ ግንኙነት በመካከላቸው ተመልክተዋል፡
1. መዝሙር 104፡20-30 እና የግብፃውያን ውዳሴ ለአቶን (14ኛ ክፍለ-ዘመን ቅ.ል.ክ)
2. መዝሙር 29 ከሞላ ጎደል ከዑጋሪታዊ ግጥም ከበአል ጋር መንታ ነው፣ ከመለኮቱ ስም በቀር፡፡

ለ. በአርኪዎሎጂ ፍለጋ ከዑጋሪት ከተማ የተገኘው የራስ ሻምራ ጽሑፍ በከነአን ቅኔ እና በመዝሙር መካከል ያለውን ተመሳሳይነት ያሳያል፡፡

ሐ. ጽሑፋዊ መልኩ ጥንታዊ ዘውግ ነው፣ በእስራኤል ዘንድ፡
1. የሙሴ መዝሙር፣ ዘጸ. 15፡1-17
2. የማርያም መዝሙር፣ ዘጸ. 15፡21
3. የእስራኤል መዝሙር፣ ዘኁ. 21፡17-18
4. የዲቦራ መዝሙር፣ መሳ. 5
5. የሐና መዝሙር፣ 1 ሳሙ. 2፡1-10
6. የቀስት መዝሙር፣ ከያሻር መጽሐፍ፣ II መዝ. 1:17-27

መ. ሦስት መርሐዊ መልኮች፡
1. የምስጋና መዝሙሮች - ባሕርያቸው "እግዚአብሔርን አመስግኑ፣" "ለጌታ ዘምሩ፣" ወዘተ በሚል ተተኳሪ መጀመራቸው ነው
2. የወዮታ መዝሙራት - ባሕርያቸው "ጌታ ሆይ፣" በሚል አመልካቻዊ/አቤቱታ መጀመራቸው ነው፣ አቤቱታን ወይም ርኅራኄ መሻትን በማስከተል
3. የጥበብ መዝሙራት - ከጥበብ ሥነ-ጽሑፍ ጋር ተመሳሳይ ምድብ አላቸው

IV. ደራሲነት

ሀ. የአብዛኛው መዝሙር ልማዳዊው ደራሲ በርዕሱ ወይም በኅዳግ መግለጫው ላይ ተሰጥቷል፡፡ እነዚህን ርዕሶች/መጠሪያዎች ለመመልከት ሁለት መንገዶች አሉ፡
1. እነርሱ የዕብራይስጡ ጽሑፍ ክፋይ ናቸው፣ ስለዚህ፣ ካኖናዊ ናቸው፡፡ ሆኖም፣ ከሙት ባሕር ጥቅሎች የተገኙት መዝሙራት እነዚህ ርዕሶች እና የኅዳግ ማስታወሻዎች የሏቸውም።
2. እነርሱ ዋና አይደሉም፣ ከተመስጧዊው ደራስያን ጋር፣ ስለዚህ መታየት የሚገባቸው እንደ ጥንታዊ ልማዳዊ እንጂ ተመስጧዊ እውነት አይደለም፡፡ ቢያንስ ከእነርሱ ሁለቱ ከሌሎቹ ካኖናዊ ጽሑፎች ጋር የማይጣጣሙ ይመስላል፡

ሀ. የመዝ. 34 ርዕስ/መጠሪያ አልያም I ሳሙ. 21:10
ለ. የመዝ. 56 ርዕስ/መጠሪያ አልያም I ሳሙ. 21:10
3. ሌላው ችግር የዕብራይስጡን መስተጻምር "የ" በበርካታ መንገዶች መረዳት ስላለ ነው፡
ሀ. "የተጻፈው"
ለ. "ለ -- ተጻፈ"
ሐ. "ወደ-- ተጻፈ"
መ. "በዚህ ጊዜ የሆነ"
ሠ. "በዚህ ትዕዛዝ"

ለ. የኤምቲ የደራስያን መጠሪያ ስም፡
1. ዳዊት፣ (I ሳሙኤል 16:16-18)፣ (ኤምቲ) የ73 ደራሲ፤ (LXX) የ84 ደራሲ፤ (ቫልጌት) የ53 ደራሲ
2. ስማቸው የማይታወቅ - 50 መዝሙራት: 1፣ 2፣ 10፣ 33፣ 43፣ 71፣ 91፣ 93-97፣ 104-107፣ 118-119፣ 135፣ 137፣ 146-150
3. አሳፍ፣ የዳዊት የመዘምራን አለቃ (I ዜና. 15:16-17፤ 16:5) 12 መዝሙራት: 50፣ 73-83
4. የቆሬ ልጆች፣ የሌዋውያን ዘማሪዎች ወገን (I ዜና. 9:19፤ 15:17) 11 መዝሙራት: 42-49 ከ43 በቀር፣ 84-88 ከ86 በቀር
5. ኤዶታም፣ የሌዋውያን የመዘምራን አለቃ፣ (I ዜና. 16:41-42፤ 25:1-3፤ II ዜና. 5:12) 3 መዝሙራት: 39፣ 62፣ 77
6. ሰሎሞን፣ 2 መዝሙራት: 72፣ 127. "የተጻፈው፣" "ለ -- ተጻፈ፣" "ወደ-- ተጻፈ፣" "የእከሌ፣" "በዚህ ጊዜ" ወይም "በዚህ ትዕዛዝ፡፡"
7. ሙሴ፣ 1 መዝሙር: 90
8. ኢዝራሂቲ (I ዜና. 6:33፤ 15:17)
ሀ. ኤታን፣ መዝሙር 89 (አንዳንዶች አብርሃም ይላሉ) I ዜና. 15:17፤19
ለ. ኤማን፣ መዝሙር 88 (ደግሞም የቆሬ ልጅ) I ነገ. 4:31፤ I ዜና. 4:31፤ 15:19

ሐ. የደራሲነት ልማድ ከአይሁድ ጽሑፎች
1. ባባ ባትራ 14ለ- "ዳዊት የመዝሙር መጽሐፍን ጻፈ፣ በአስር ሽማግሌዎች ርዳታ፣ በአንደኛው አዳም ርዳታ፣ እና መልከ-ጼዴቅ እና አብርሃም እና ሙሴ እና ሔማን እና ኤዶታም እና አሳፍ እና ሦስቱ የቆሬ ልጆች"
2. ሳንሄድሪን /ጠቅላይ የአይሁድ ጉባኤ/ 38ለ /ታልሙድ/ መዝ. 139ን ለአዳም፣ እና መዝ. 110ን ለመልከ-ጼዴቅ በአስተዋጽዖነት ፈርጀዋል፡፡

መ. LXX መዝሙራትን ለኤርምያስ፣ ሕዝቅኤል፣ ሐጌ እና ዘካርያስ በአስተዋጽዖነት ፈርጇል (112፣ 126፣ 127፣ 137፣ 146-149)

V. ጊዜው

ሀ. የመዝሙርን ጊዜ መወሰን በሁለት ምክንያቶች የተነሣ አስቸጋሪ ነው፡
1. ግለሰባዊ መዝሙራት የተለየ አጋጣሚ/ሁነት፣ እንዲጻፉ ምክንያት የሆናቸው
2. መዝሙራት የተሰበሰቡት በማዘጋጀት ሂደት ነው፣ በአምስት መጻሕፍት

ለ. መዝሙር ግጥሞችን ያካትታል፣ ከእስራኤል ሕይወት ዘመናት ሁሉ፡
1. የአይሁድ ወግ/ልማድ ይላል፡
ሀ. አዳም መዝ. 139ን ጻፈ
ለ. መልከ-ጼዴቅ መዝ. 110ን ጻፈ
ሐ. አብርሃም መዝ. 89ን ጻፈ
መ. ሙሴ መዝ. 90ን ጻፈ
2. ዘመናዊዎቹ ሊቃውንት/አስተምህሮት መዝሙርን በሦስት ዋና ዋና ጊዜያት ይከፋፍለዋል፡
ሀ. ቅድመ-ግዞት (መጻሕፍት፣ I፣ II፣ እና IV)
ለ. ግዞታዊ (መጽሐፍ III)
ሐ. ድኅረ-ግዞት (መጽሐፍ V)

ሐ. ግልጽ የሆነው ነገር አብዛኞቹ መዝሙራት በዳዊት አስተዋጽዖ መወሰዳቸው ነው፡
1. ዳዊት የዜማ አቀናባሪ፣ ተጫዋች እና ዘማሪ ነበር፣ I ሳሙ. 16:16-18
2. እሱ የሌዋውያንን የዝማሬ ቡድን ወይም የመቅደስ ዘማርያንን አነሣስቶ አደራጅቷል፣ I ዜና. 15:1-16:43፣ 25:1-31፤ II ዜና. 29:25-30
3. የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ የመዝሙር መጻሕፍት በእሱ አስተዋጽዖ ነው የተመዘገቡት፣ መዝ. 72፡20
4. መዝሙራት በሁሉም በአምስቱም የዝማሬ መጻሕፍት ላይ ይገኛሉ

VI. የዝማሬ መዋቅር

ሀ. አጠቃላይ ጭብጥ ወይም ፈርጅ የለም፡፡ ያለው፡
1. አጠቃላይ መግቢያ (የጻድቅ ሰው ባሕርያት) - መዝ. 1 እና መዝ. 2
2. እያንዳንዳቸው የመጽሐፉ አምስቱ ምድቦች አምላክን በማመስገን ያበቃሉ፣ 41:13፤ 72:18-19፤ 89:52፤ 106:48
3. አጠቃላይ መዝጊያ (ውዳሴ አምላክ) - መዝሙር 150

ለ. የአምስቱ መጻሕፍት ባሕርያት
1. መጽሐፍ 1 - መዝሙር 1-41
ሀ. ሁሉም ከ4 በቀር፣ የዳዊት አስተዋጽዖ ተደርገው ነው የተወሰዱት (1፣ 2፣ 10፣ 33)
ለ. ያህዌ እንደ እግዚአብሔር መጠሪያ በብዛት ይገኛል፣ ያህዌ 273፣ ኤሎሂም 15
ሐ. ዳዊት ከሳኦል ጋር በተጋጨበት ጊዜያት ይመስላል
2. መጽሐፍ 2 – 42-72 (72:20 አዘጋጁን ያመለክታል)

ሀ. መዝሙር 42-49 የቆሬ ልጆች (ከ43 በቀር)
ለ. ኤሎሂም እንደ እግዚአብሔር መጠሪያ በብዛት ይገኛል፣ ኤሎሂም 164፣ ያህዌ 30
ሐ. የዳዊት የንጉሥነት ቀናት ሊሆን ይችላል

3. መጽሐፍ 3 - መዝሙር 73-89
ሀ. መዝሙር 73-83፣ አሳፍ
ለ. መዝሙር 84-88፣ የቆሬ ልጆች /ከ86 በቀር/
ሐ. 26 መዝሙራት የዳዊት አስተዋጽዖ ተደርገው ተወስደዋል
መ. ያህዌ እንደ እግዚአብሔር መጠሪያ 44 ጊዜያት፤ ኤሎሂም 43 ጊዜያት
ሠ. የአሦር ቀውስ ሊሆን ይችላል

4. መጽሐፍ 4 -መዝሙር 90-106
ሀ. መዝሙር 101፣ 103 ለዳዊት
ለ. መዝሙር 90 ሙሴ
ሐ. ሌሎቹ ሁሉ የታወቀ ስም/ምንጭ የላቸውም
መ. ያህዌ 104 ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል፤ ኤሎሂም 7 ጊዜ
ሠ. የባቢሎን ቀውስ ሊሆን ይችላል

5. መጽሐፍ 5 - መዝሙር 107-150
ሀ. መዝሙር 119 የተስፋፉ የቃላት ዕንቆቅልሽ ነው፣ በእግዚአብሔር ቃል ላይ
ለ. ያህዌ 236 ጊዜ፤ ኤሎሂም 7 ጊዜ
ሐ. መዝሙር 146-150 የምስጋና መዝሙሮች ናቸው፣ ሁሉም "እግዚአብሔርን አመስግኑ" በማለት የሚጀምሩ
መ. በእግዚአብሔር የወደፊት ባርኮት ተስፋ ማድረግ ሊሆን ይችላል

ሐ. የመዝሙር ቆጠራ ልዩነቶች

1. ኤምቲ ኤምኤስኤስ
ሀ. ቤራኮዝ 9ለ -- መዝሙር 1 እና 2 እንደ 1 ተቆጥረዋል
ለ. ሻባዝ 16 - አጠቃላይ የመዝሙራት ቁጥር 147 ነበር፣ ያዕቆብ በሕይወት ከኖረባቸው ዓመታት ጋር ለመግጠም

2. LXX
ሀ. መዝሙር 9 እና 10 አብረው አንድ የቃላት ሰንጠረዥ መዝሙር ያበጃሉ
ለ. መዝሙር 114 እና 115 ሁለቱም አብረው ተደጋጋሚ ምስጋና መዝሙሮች ናቸው
ሐ. መዝሙር 116 እና 147 እያንዳንዳቸው ለ2 ተከፍለዋል

3. የመዝሙራቱ ቁጥር ከጥንታዊው ምኩራብ ዓመታዊ የቅዱስ ቃሉ ንባብ ዑደት ጋር ሊያያዝ ይችላል

መ. መዝሙርን ለመመደብ/ለመቦደን ናሙና/ማሳያ መንገዶች:

1. በጭብጥ ወይም በርዕስ
ሀ. የምስጋና ዝማሬዎች
(1) ለእግዚአብሔር እንደ ፈጣሪ፣ 8፣ 19፣ 104፣ 139፣ 148
(2) ለእግዚአብሔር ባጠቃላይ፣ 33፣ 103፣ 113፣ 117፣ 134-136፣ 145-147
ለ. ምስጋና የማቅረብ ዝማሬዎች፣ 9-10፣ 11፣ 16፣ 30፣ 32፣ 34፣ 92፣ 116፣ 138
ሐ. ወዮታ/ሙሾ/አቤቱታ
(1) የተጠቃለለ፣ 12፣ 14፣ 44፣ 53፣ 58፣ 60፣ 74፣ 49፣ 80፣ 83፣ 85፣ 89፣ 90፣ 94፣ 106፣ 123፣ 126፣ 137
(2) የግለሰብ 3-7፣ 13፣ 17፣ 22፣ 25-28፣ 31፣ 35፣ 38-43፣ 69-71፣ 86፣ 88፣ 102፣ 109፣ 120፣ 130፣ 139-143
መ. የንጉሣዊነት ማዕርግ ዝማሬዎች
(1) እግዚአብሔር እንደ ንጉሥ፣ 47፣ 93፣ 96-99
(2) የእስራኤል ንጉሥ ወይም መሢሕ፣ 2፣ 18፣ 20፣ 21፣ 45፣ 72፣ 89፣ 101፣ 110
ሠ. ዝማሬ ስለ ጽዮን፣ 46፣ 48፣ 76፣ 84፣ 87፣ 122
ረ. የጋራ አምልኮ ዝማሬዎች
(1) የኪዳን መታደስ፣ 50፣ 81
(2) ክህነታዊ ባርኮቶች፣ 134
(3) ስለ መቅደስ፣ 15፣ 24፣ 68
ሰ. ዝማሬ ስለ ጥበብ፣ 36፣ 37፣ 49፣ 73፣ 111፣ 112፣ 127፣ 128፣ 133
ሸ. ዝማሬ በያህዌ ታማኝነት ላይ ስለ መታመን፣ 11፣ 16፣ 23፣ 62፣ 63፣ 91፣ 121፣ 131
ቀ. ሐሰተኛ አማልክትን እና አመንዝራነትን/ጣዖት አምላኪነትን ማውገዝ፣ 82፣ 115

2. በደራሲው ወይም በተናጋሪው
ሀ. የዳዊት ዝማሬዎች ባብዛኛው *ያህዌን* እንደ መለኮት ስም በመጠቀም፣ መዝ. 1-41
ለ. የዳዊት ዝማሬዎች ባብዛኛው *ኤሎሂምን* እንደ መለኮት ስም በመጠቀም፣ መዝ. 51-72
ሐ. ዝማሬ፣ በዳዊት ሌዋውያን የዜማ ሰዎችና መዘምራን
(1) ቆሬ እና ልጆቹ፣ መዝ. 42-49፣ 84-88
(2) አሳፍ እና ልጆቹ፣ መዝ. 73-83
መ. ዝማሬ፣ በአመስጋኞች፣ መዝ. 111-118፣ 140-150
ሠ. ዝማሬ በመናኞች/መንፈሳዊ ተጓዦች/፣ በበዓል ቀን ወደ ኢየሩሳሌም ለአምልኮ የሚመጡ፣ መዝ. 120-134

3. በእስራኤል ታሪክ፣ ታሪካዊ ሁነቶች፣ በኅዳግ ማስታወሻው ወይም በይዘቱ ላይ በመመሥረት፣ መዝ. 14፣ 44፣ 46-48፣ 53፣ 66፣ 68፣ 74፣ 76፣ 79፣ 80፣ 83፣ 85፣ 87፣ 108፣ 122፣ 124-126 እና 129

ሠ. ተጓዳኝ መዝሙራት

1. መዝሙር 14 እና 53 አንድ ዓይነት ናቸው፣ ከእግዚአብሔር ስም በቀር
ሀ. መዝሙር 14 ያህዌ አለው

ለ. መዝሙር 53 ኤሎሂም አለው
2. መዝሙር 103 እና 104 ተያይዘዋል፡
ሀ. አንድ ዓይነት መክፈቻና መዝጊያ
ለ. መዝ. 103 ያህዌ አለው፣ እንደ አዳኝ እና ተቤዢ
ሐ. መዝሙር 104 ኤሎሂም አለው፣ እንደ ፈጣሪና መጋቢ/ደጋፊ
3. መዝሙር 32 እና 51 ሁለቱም ከዳዊት ኃጢአት ጋር የተያያዙ ናቸው፣ ከቤርሳቤህ ጋር ከፈጸመው
4. መዝሙር 57:7-11 እና 60:5-12 በመዝ. 108 ተደባልቀዋል
5. መዝሙር 18፣ II ሳሙ. 21:1-51 ላይ ተደግሟል

ረ. 150 መዝሙራት በ5 መጻሕፍት ለምን ሆኑ
1. 150 መዝሙራት ከ150 የምኩራብ ምድቦች፣ ማለትም በየሰንበቱ ለሕዝብ ንባብ ከሚቀርቡት ጋር በትይዩ ተቀምጠው ይሆናል፡፡
2. አምስት መጻሕፍት ከአምስቱ የሙሴ መጻሕፍት ጋር በትይዩ ተቀምጠው ይሆናል፡፡

## VII. ዜማ-ነክ ቃላት፣ በመዝሙር

ሀ. ዜማ-ነክ ቃላት በኀዳግ ማስታወሻ ላይ የተለያዩ ዓይነት መዝሙራትን ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውለዋል
1. *MIZMOR* ማለት "ጅማት/ክር መሳብና መልቀቅ" ነው፡፡ እነዚህም መዝሙራት በዜማ መሣርያዎች ታጅበው የሚዘመሩ ናቸው ማለት ነው፡፡ የዚህ ዓይነት 57 አሉ፡፡
2. *SHIR*ሁሉንም ዓይነት መዝሙሮች ያመለክታል፡፡ የዚህ ዓይነት 30 አሉ፡፡
3. *MASCHIL*ወይም *MASKIL* የልዩ ክህሎት ወይም የትምህርት መዝሙራትን የሚገልጹ ዝማሬዎች ናቸው፡፡ የዚህ ዓይነት 30 ናቸው፡፡
4. *MITCHTAM* ወይም *MITKHTAM* -የዚህ ቃል ፍቺ ርግጠኝነት የለውም፡፡ ከታሳቢ የዕብራይስጥ ሥር፣ ሊሆን የሚችለው "ወርቃማ" ወይም "የከበረ" ነው፤ ከአካድያን ሥር፣ ሊሆን የሚችለው "የተሸሸገ" ወይም "ያልታተመ" ነው፤ ከዓረብኛ ሥር፣ ሊሆን የሚችለው "ማስተሥረይ" ወይም "ይቅር ማለት" ነው፡፡ የዚህ ዓይነት 6 ናቸው፡፡
5. *PALAL* ማለት ጸሎት ነው፡፡ እሱም የዳዊትን መዝሙር በመጽሐፍ I እና II (መዝሙር 72:20) ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ እሱም ደግሞ መዝ. 17፣ 86፣ 90፣ 102፣ 142 እና እንዲሁም 122 ላይ በኀዳግ ማስታወሻ ላይ ይገኛል፡፡

ለ. ዜማዊ ቃላት፣ መዝሙርን መጫወትን ወይም መዘመርን የሚገልጹ
1. *SELAH*71 ጊዜ በ39 መዝሙሮች እና ዕን. 3፡3፣9፣13 ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ፍችው ርግጠኝነት የለውም፡፡ በርከት ያሉ ንድፈ-ሐሳቦች አሉ፡
ሀ. ከLXX "በመሐል የሚሆን" ለመሐከለኝነት ወይም ድራማዊ ውጤት
ለ. ከዕብራይስጥ ሥር "ከፍ ማድረግ፣" ስለዚህ፣ ማንሻ ወይም የድምጽ ከፍ ማለት
ሐ. ራቢዎች የሚሉት እሱ እንደ ማስረገጫ ነው፣ "አሜን" እንደማለት፣ ፍችውም "ዘላለም፡፡"
2. *SHIGGAION* ወይም *SHIGIONOTH* መዝ. 7 እና ዕን. 3 ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ እሱም ወዮታ ወይም ሙሾ ነው፣ ኀዘንን የሚገልጽ፡፡ እሱም እጅግ ስሜታዊ የቅኔ መልክ አለው፡፡
3. *NEGINOTH* 6 ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል፣ እና ዕን. 3፡19፡፡ ፍችውም "በጅማት/ክር የዜማ መሣርያዎች" ማለት ነው፡፡
4. *SHEMINITH* ሁለት ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ፍችው የሚሆነውም "በባለ ስምንት ቃና" ወይም "በስምንት" ነው፡፡ እሱም *ALAMOTH* ተቃራኒ ነው፣ ስለዚህ፣ ለወንድ ድምጽ ሊሆን ይችላል (I ዜና. 15:21)፡፡
5. *MECHILOTH* 4 ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ እሱም የሚያመለክተው የሴት ከፍተኛ ድምጽን ነው (I ዜና. 15:20)፡፡
6. *GITTITH* አንድ ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ፍችውም "በንፋስ የዜማ መሣርያዎች" ማለት ነው፡፡
7. *ጊቲዝ* 3 ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ፍችውም "በበገና" ማለት ነው፡፡
8. በርከት ያሉ ማጣቀሻዎች አሉ፣ ተለይተው ለተሰየሙ ቃናዎች፣ መዝ. 9፣ 22፣ 45፣ 53፣ 56፣ 57-59፣ 60፣ 62፣ 69፣ 75፣ 77፣ 80 እና 88

## VIII. የመዝሙራት ዓላማ

ሀ. እስራኤል የሚያምነው ሕይወት ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር በኪዳን ተዛምዷል በሚል ነው፡፡ መዝሙራት ከሰው ወደ እግዚአብሔር የተለቀቁ ጥልቅ የሕይወት ስሜቶች ናቸው፡፡

ለ. እስራኤል የሚያምነው በአንድና በአንድ ብቻ ግላዊ፣ ተንከባካቢ አምላክ ነው፡፡ እምነት አካላዊ አምልኮ ወይም የጋራ መርሕ/የእምነት መግለጫ አይደለም፣ ነገር ግን የግልና የየቀኑ እንጂ፡፡ የመዝሙራቱ ቅኔአዊ መልክ፣ ሃይማኖታዊ ማንነታችንን ለእግዚአብሔር ለመግለጽ ይረዳናል፡፡ የብኪ ዋነኛው ገጸ-ባሕርይ እግዚአብሔር ነው!
ሐ. መዝሙራት ሁሉ የጀመሩት በግለሰብ እምነት መግለጫነት ይሆናል፣ ኋላ ላይ ለማኅበረሰቡ እምነት ጥቅም ላይ ቢውሉም (መዝ. 23፤ 139፣ ወዘተ)፡፡

## IX. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት እና ሰዎች በአጭሩ የሚገለጹ

ሀ. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት
1. "መለየት" (*kadosh*)4:3 (NASB እና NIV)
2. "መታመን" (*emeth*) 4:5 (NASB እና NIV)
3. "መንገዴን በፊትህ አቅና" 5፡8 (NASB እና NIV)
4. "ቸርነት" (*hesed*) 6፡4 (NIV፣ "የማይወድቅ ፍቅር")
5. "ንስሐ" 7፡12 (NIV፣ "መመለስ")
6. "የሰው ልጅ፣" 8፡4 (NASB እና NIV)
7. "ማዳን፣" 9፡14 (NASB እና NIV)
8. "ጉድጓድ፣" 9፡15 (NASB እና NIV)

9. "ጽዋ፣" 11፡6፤ 75፡8 (NIV፣ "ዕድል-ፈንታ")
10. "ጽድቅ፣" 15፡2 (NIV፣ "ጻድቅ")
11. "ኪሩብ፣" 18፡10 (NIV፣ "*cherubim*")
12. "እንደ ብሖር እግሮች፣" 18፡33 (NIV፣ "የኢጋዘን እግር")
13. "ረድኤቱ፣" 19፡14 (NASB እና NIV)
14. "ዕጣ፣" 22፡18 (NASB እና NIV)
15. "በሞት ጥላ መካከል፣" 23፡4 (NASB እና NIV)
16. "በክንፎህ ጥላ፣" 57፡1፤ 91፡4 (NASB እና NIV)
17. "ማቅ፣" 69፡11 (NASB እና NIV)
18. "የሕያዋን መጽሐፍ፣" 69፡28፤ 139፡16 (NASB እና NIV)
19. "የድጥ ስፍራ፣" 73፡18 (NIV፣ "የድጥ ቦታ")
20. "የኃጥአን ቀንዶች፣" 75፡10 (NASB እና NIV)
21. "በኮረብታዎች፣" 78፡58 (NASB እና NIV)
22. "ረዓብ፣" 89፡10 (NASB እና NIV)
23. "አሸነፍኋቸው፣" 118፡10፣11፣12 (NASB እና NIV)
24. "የማዕዘን ድንጋይ፣" 118፡22 (NIV፣ "የማዕዘን ራስ ድንጋይ")
25. "የመሠዊያ ቀንዶች፣" 118፡27 (NASB እና NIV)

ለ. ሰዎች


1. የሠራዊት ጌታ (ያህዌ ሳቦዝ) NASB፣ 24፡10 (NIV፣ "ኃያል አምላክ")
2. ኤዶታም፣ 62 መግቢያ (NASB እና NIV)
3. እስማኤላውያን፣ 83፡6 (NASB እና NIV)
4. መልከጼዴቅ፣ 110፡4 (NASB እና NIV)


## X. የካርታ ስፍራዎች

1. ጽዮን፣ መዝ. 2፡6
2. ባሳን፣ 22፡12
3. ቃዴስ-በርኔ፣ 29፡8 /NIV፣ "ቃዴስ"/
4. አርሞንኤም ተራራ፣ 42፡6 (NIV፣ "የአርሞኤም ከፍታ")
5. ሴሎም፣ 78፡60
6. ታቦር ተራራ፣ 89፡12
7. ብዔል-ፌጎር፣ 106፡28 (NIV፣ "የፌጎር ብዔል")

## XI. የተማሪ ይዘት የውይይት ጥያቄዎች

1. መዝ. 2 ለምን እንደ ሁለንተናዊ እና መሢሓዊ መዝሙር ተደርጎ ይቆጠራል?
2. መዝ. 18፡1-2 ላይ የሚገኙትን እግዚአብሔርን ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋሉትን የተለያዩ ዘይቤዎችን ግለጽ፡፡
3. መዝ. 19 ላይ የሚገኙትን ሁለት ዓይነት መገለጦች ዘርዝር፣ አብራራም፡፡
4. መዝ. 22 ከትንቢታዊነት መልኩ የሚገልጸው ምንድነው?
5. የመዝ. 32 እና 51ን ታሪካዊ ዳራ አብራራ፡፡
6. መዝ. 38 ስለ ምንድነው የሚናገረው /በገዛ ራስህ ቃላት፡፡/
7. የመዝ. 42፡1ን ዘይቤ አብራራ፡፡
8. 51፡11-12 ስለ ምን እንደሚናገር ግለጽ፡፡
9. እግዚአብሔርን መፍራት ማለት ምን ማለት ነው? 67፡7
10. መዝ. 73 ከምን ዓይነት የሕይወት ጉዳይ/ሁኔታ ጋር ነው እየታገለ ያለው?
11. ስለ መዝሙር 119 መዋቅር ያልተለመደው ነገር ምንድነው? የእርሱስ አጠቃላይ ርዕሰ-ጉዳይ ምንድነው?
12. መዝ. 139 ስለ ምን ዓይነቱ የሕይወት ጉዳይ ነው እየተናገረ ያለው?


ANCIENT
NEAR EAST
N
S
E
W


PALESTINE
0 10 20 30 40
SCALE IN MILES

# መግቢያ ለመጽሐፈ ምሳሌ

I. የመጽሐፉ ስም

ሀ. በዕብራይስጥ ርዕሱ፣ የመጀመሪያዎቹ ሰባት ቁጥሮች/ስንኞች እና ጭብጡ ነው፣ ቁ. 7፡፡

ለ. በLXX "የሰሎሞን ምሳሌዎች" በመባል ይጠራል፡፡

ሐ. በቫልጌት "የምሳሌዎች መጽሐፍ" በመባል ይጠራል፡፡

መ. የእንግሊዝኛው ርዕስ የመጣው ከዕብራይስጡ ቃል *mashal* ነው፣ "መምሰል"፡፡ ምሳሌዎች አጭር፣ ሐሳብ ቀስቃሽ መግለጫዎች/ዓረፍተ-ነገሮች ናቸው፣ ዘወትርም በሁለት መስመር፡፡

II. ቅዱስ ቃልነቱ /ካኖናዊነት

ሀ. እሱም የዕብራይስጥ ካኖን "ጽሑፎች" በመባል የሚታወቀው ሦስተኛ ምድብ ክፋይ ነው፡፡

ለ. ታልሙድ፣ ባባ ባትራ 14ለ፣ የሚለው የጥበብ መጻሕፍት ቅደም ተከተል መዝሙር፣ ኢዮብ እና ምሳሌ ነው፡፡ እሱም የደራሲነት አስተዋጽዖውን የሚሰጠው፡

1. መጽሐፈ-ኢዮብን ለሙሴ
2. መዝሙርን ለዳዊት
3. ምሳሌን ለሕዝቅያስ

ሐ. ራቢዎች የሚያስረግጡት ሰሎሞን፣ እሱም በጥበቡ ዝነኛ የነበረው፣ ሦስት መጻሕፍትን ጽፏል፡

1. መኃልየ መኃልይን ወጣት በነበረ ጊዜ፣
2. ምሳሌን መካከለኛ ዕድሜ ላይ በነበረበት ጊዜ፣
3. መክብብ ባረጀና በተመረረ ጊዜ፡፡ ይህ ወግ/ልማድ እነዚህን ሦስት መጻሕፍት አንድ ላይ በመመደብ ይገለጻል፣ LXX ላይ፡፡

III. ዘውግ

ሀ. ምሳሌዎች የተለዩ ዓይነት የጥበብ ሥነ-ጽሑፍ ናቸው፡፡

ለ. በርካታ ዓይነት ምሳሌያዊ አባባሎች አሉ (Clyde Francisco, *Introducing the Old Testament,* p. 265)

1. ታሪካዊ ምሳሌዎች - እነዚህ ዝነኛና ታዋቂ ያለፉት አነጋገሮች ናቸው፣ የአሁኑ ዘመን እውነታ የሆኑት፡፡
2. ዘይቤአዊ ምሳሌዎች - እነዚህ ባለ ሁለት መስመር አባባሎች ናቸው፣ ነገሮችን የሚያወዳድሩ፡
   ሀ. አወዳዳሪዎችን በመጠቀም፣ "ይመስላል" ወይም "እንደ" የመሳሰሉትን
   ለ. ተቃርኖን በመጠቀም
3. ዕንቆቅልሻዊ - እነዚህ ዕንቆቅልሾች ወይም አእምሮን የሚያመራምሩ ናቸው፡፡
4. ምስያዊ ምሳሌዎች - እነዚህ ረጅም፣ በደንብ የተደራጁ ንጽጽሮች ወይም ተቃርኖዎች ናቸው፡፡
5. ትዕዛዛዊ ምሳሌዎች - እነዚህ እውነታ ናቸው፣ ወጣት ወንዶችን ለመግራትና ለማሠልጠን፣ ለመንግሥታዊ አገልግሎት ወይም ለአመራርነት፡፡

ሐ. ምሳሌዎች እንደ መዝሙራት ትይዩነትን ይዘዋል፡

1. ተመሳሳይ ትይዩ - ምሳ. 8፡1
2. ተቃራኒ ትይዩ - ምሳ. 28፡1
3. ድብልቅ ትይዩ - ምሳ. 26፡1

IV. ደራሲነት

ሀ. ምሳሌዎች ከወግ/ልማድ አኳያ ከሰሎሞን ጋር ነው የሚያያዙት፣ ከዝሙራት ከዳዊት ጋር እንደሚያያዙት ሁሉ፡፡ ይህም የሆነው ሰሎሞን በጥበቡ ዝነኛ ስለነበረ ነው (1 ነገሥ. 3:12፤ 4:29-34፤ 10:1)፣ እንዲሁም ደግሞ የሰሎሞን ስም በመጠቀሱ ነው፣ ምሳ. 1:1፤ 10:1 እና 25:1 ላይ፡፡

ለ. ምሳሌ የአዘጋጆች ማጠናቀር ውጤት ነው፣ እንደ መዝሙር፡፡ በርከት ያሉ ደራስያን ተጠቅሰዋል፡

1. ሰሎሞን - 1:1፤ 10:1፤ 25:1
2. ጠቢባን ሰዎች (መካሮች) - 22:17፤ 24:23
3. አጉር - 30:1
4. ልሙኤል - 31:1

ሐ. ምሳሌ ላይ የአዘጋጅነት ሂደት 25፡1 ላይ ሊታይ ይችላል፣ እዛም ላይ እንደተቀመጠው የሕዝቅያስ ቤተ-መንግሥት ሰዎች የሰሎሞንን ምሳሌዎች እንዳጠናቀሩ የሚያሳየው፡፡ አብዛኞቹም ከዚህ ጊዜ በፊት ቃላዊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

መ. ምዕራፍ 30-31 በማሳ ሰዎች ነው፡፡ ይህን ቃል በተመለከተ በተርጓሚዎች መካከል አንዳንድ አለመግባባት አለ፡፡ አብዛኞቹ የእንግሊዝኛ ቅጅዎች ይሄንን ቃል የሚተረጉሙት "ንግር" ወይም "ሸክም/ጭብጥ" በሚል ነው፡፡ የአይሁድ የኅትመት ማኅበረሰብ በአሜሪካ፣ እሱን የሚተረጉመው እንደ ቦታ ስም ነው፡፡ ይህ ቃል *MASSA*፣ በሳዑዲ ዓረቢያ ያለ የአንድ እስማኤላዊ መንግሥት ጠቃሽ ነው (ዘፍ. 25:14 እና 1 ዜና. 1:30)፡፡

ሠ. ግልጽ የሆነ ተመሳሳይነት አለ፣ "በጠቢባን ቃል" 22:17-24:22 እና በ "አሜኒሞፔ መመሪያ/ ማስተማሪያ" መካከል፣ ጊዜውም ከግብፅ 1200 ቅ.ል.ክ አካባ የሆነ፡፡ ለተሟላ ማብራሪያ፣ John H. Walton, *Ancient Israelite Literature in Its Cultural Context*, Grand Rapids: Zondervan, 1990. pp. 192-197፡፡

V. ጊዜው

ሀ. የዚህ መጽሐፍ ጊዜ እንደ መዝሙር ተመሳሳይ ችግር አለው፡፡ ሁለት ጊዜያት አሉ፣ ግምት ውስጥ የሚገቡ፡
1. የግለሰብ ምሳሌዎች ጊዜ፣
2. እነርሱም በእኛ ካኖናዊ መጽሐፍ የተሰባሰቡበት ጊዜ፡፡

ለ. አብዛኞቹ ምሳሌዎች ተመልሰው ወደ ሰሎሞን ጊዜ ይሄዳሉ፣ በተለይም 10:1-22:16 እና 25:1-29:27፡፡

ሐ. በርካታ ተመሳሳይነቶች አሉ፣ በአጉር ቃላት፣ ምዕራፍ 30 እና በዑጋሪት የራስ ሻምራ ጽሑፎች መካከል፡፡ እነዚህ ጽሑፎች ከ15ኛ ክፍለ-ዘመን ቅ.ል.ክ ናቸው፡፡

መ. ካኖናዊ የሆነው የምሳሌ መጽሐፍ፣ ምዕራፍ 1-29 በሕዝቅያስ ጊዜ የተጠናቀሩ ናቸው (710-687 ቅ.ል.ክ)፡፡ የመጨረሻዎቹ ሁለቱ ምዕራፎች ኋላ ላይ የተጨመሩ ናቸው፡፡

VI. ታሪካዊ መቼት

VII. ጽሑፋዊ ምድብ

ሀ. የመጽሐፉ ርዕስ፣ 1፡1-6

ለ. የጭብጥ መግለጫ፣ 1፡7

ሐ. የጥበብ ምስጋና /ሰውኛ/፣ 1፡8-9፡18

መ. የሰሎሞን ምሳሌዎች /ተቃራኒ ጥንዶች/፣ 10፡1-22፡16

ሠ. የጠቢባን ቃላት (ከግብፃውያን ጥበብ ጋር ተመሳሳይ)፣ 22:17-24:22

ረ. ተጨማሪ የጠቢባን ቃላት፣ 24:23-34

ሰ. የሰሎሞን ምሳሌዎች (ጭብጣዊ)፣ 25:1-29:27

ሸ. የአጉር ቃላት (ለተጠራጣሪዎች ምላሽ)፣ 30:1-33

ቀ. የልሙኤል ቃላት (ከእናቱ)፣ 31:1-9

በ. የመልካም ሴት ምስጋና (ዕንቆቅልሻዊ/ዘወርዋራ)፣ 31:10-31

VIII. ዋነኛ ሐቆች

ሀ. ምንም እንኳ አዘውትሮ ባይቀመጥም፣ ምሳሌ የተመሠረተው አሀዳዊውን ግላዊ አምላክ ግምት ውስጥ በማስገባት ነው፣ እሱም ሕያው/ንቁ የሆነ በሁለቱም በፍጥረትና በግለሰብ አማኞች ሕይወት ላይ (ዝከ. 1:7፤ 3:5-6፤ 9:10፤ 14:26-27፤ 19:23)፡፡

ለ. የዚህ ዓይነቱ ሥነ-ጽሑፍ አመዛዛኝነቱ ከ (ኤር. 18:18፤ ሕዝ. 7:26):
1. "ሕግ" /ካህናት/
2. "ነቢያት" /ነቢያት/
እሱም ከእስራኤል ታሪክ ወይም የሃይማኖት ሥርዓት አኳያ የተቃኘ አይደለም፣ ነገር ግን ከደስታ፣ ከግብረ-ገብ እና ስኬታማ ሕይወት ጋር እንጂ፣ ከግለሰብ እስራኤላውያን፡፡

ሐ. በዋነኛነት እሱ የተበጀው ባለጠጋ ወጣት ወንዶችን ለማሠልጠን ነው፣ ለመንግሥታዊ አገልግሎት ወይም ለማኅበረሰብ መሪነት /ዝከ. 1፡8-9/፡፡

መ. እሱም ተመስጧዊ ውስጣዊነቱ ለየዕለቱ፣ ተግባራዊ፣ መልካም አኗኗር ነው፡፡ እርሱም ባሕርዩ እንደ "መለኮታዊ ነጂ ስሜት/ግሩም የሆነ ስሜት ነኪ" ነው፡፡

ሠ. መታወስ ያለበት፣ ምሳሌዎች አጠቃላይ የእውነት መግለጫ መሆናቸው ነው፡፡ እነርሱም ዘወትር ችግሮቹን ወይም ግለሰቡ ያለበትን ሁኔታ አያብራሩም ወይም ግምት ውስጥ አያስገቡም፡፡

IX. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት እና ሰዎች በአጭሩ የሚገለጹ፡

ሀ. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት

1. ምሳሌ (*mashal)*፣ 1:1 (*ማሻል*)፣ 1:1 (NASB እና NIV)
2. ጥበብ *(hokmah)*፣ 1:2 (NASB እና NIV)
3. እግዚአብሔርን መፍራት፣ 1፡7 (NASB እና NIV)
4. "ጥበብ በጎዳና ትጮኻለች፣" 1፡20 (NIV፣ "ጥበብ በጎዳና በጩኸት ቃል ትጣራለች")
5. "አላዋቂዎች... ፌዘኞች... ሰነፎች፣" 1፡22 (NIV፣ "ገራገሮች... አላጋጮች... ሞኞች")
6. ልዩ ሴት፣ 2፡16 (NIV፣ "ጋለሞታ")
7. "እሷ የሕይወት ዛፍ ነች፣" 3፡18 (NASB እና NIV)
8. "በእግዚአብሔር ፊት ርኩስ የሆነ፣" 3:32፤ 17:15 (NIV፣ "እግዚአብሔር ይጸየፋል")
9. "ከገዛ ራስህ የውኃ-ዕቃ ጠጣ፣" 5፡15 (NASB እና NIV)
10. "ቃል መግባት፣" 6፡1 (NIV፣ "መዋስ")
11. ምናምንቴ ሰው *(belial)*፣ 6፡12 (NIV፣ "ተንኮለኛ")
12. "እግዚአብሔር የመንገዱ መጀመሪያ አደረገኝ፣" 8፡22 (NIV፣ "እግዚአብሔር እንደ ቀድሞ ሥራው መጀመሪያ አደረገኝ")
13. "ሲኦል እና ገሃነም በእግዚአብሔር ፊት የታወቁ ናቸው፣"15፡11፤ 27፡20 (NIV፣ "ሞትና ጥፋት በእግዚአብሔር ፊት የታወቁ ናቸው")
14. ታዳጊ *(Go'el)*፣ 23፡11 (NIV፣ "መከታ")
15. አራጣ፣ 28፡8 (NIV፣ "የበዛ አራጣ")
16. ንግር /ማሳ/፣ 30፡1፤31፡1 (NASB እና NIV)

ለ. ሰዎች

1. የሕዝቅያስ ሰዎች፣ 25፡1
2. አጉር፣ 30፡1
3. ኢቲኤል፣ ኢቲኤል፣ እና ኡካል፣ 30፡1
4. ልሙኤል፣ 31፡1

X. የካርታ ስፍራዎች/አመላካቾች — የለም

XI. የተማሪ ይዘት የውይይት ጥያቄዎች

1. የዕብራይስጥ ቃላት "ጥበብ" እና "ዕውቀት" በመካከላቸው ያለው ልዩነት ምንድነው?

2. 1፡7 እጅግ ጠቃሚ የሆነው ለምንድነው?


3. ጥበብ ለምን በሴት ሰውኛ ዘይቤ ቀረበ?

4. የጥበብ ድርሻ በፍጥረት ላይ ምንድነው? (ዝከ. 3:19፤ 8:27)


5. "ሁለቱን መንገዶች" አብራራ (4:10-19)፡፡

6. የ30፡7-9ን ጸሎት አብራራ፡፡

7. 31፡10-31 ላይ የመልካም ሴትን አስተዋጽዖ/እሴት ዘርዝር፡፡


ANCIENT
NEAR EAST
N
S
E
W

# PALESTINE



# መግቢያ ለመጽሐፈ መክብብ

I. የመጽሐፉ ስም

ሀ. የዕብራይስጡ ስም" (*Qoheleth)* ቃላት፣ የዳዊት ልጅ፣ የኢየሩሳሌም ንጉሥ" የሚል ሐረግ ነበር፣ ከ1፡1፡፡ የእርሱ አጭር መጠሪያ ቆኸሌዝ ነበር፣ ይኸውም ለሰሎሞን ጥቅም ላይ የዋለ፣ 1 *ነገሥ*. 8፡1 ላይ፡፡ እሱም የሴቴ አንቀጽ ነው፣ ከዕብራይስጡ (*Qahal*)፣ "ማኅበረ-ምዕመናን" ወይም "ጉባኤ፡፡"

ለ. መጽሐፉ "ኢክሌዚያስቴዝ /መክብብ" በመባል ይጠራል፣ ይኸውም ከLXX ላቲናዊ መልክ የሆነ። ይህ የግሪክ ቃል ሲሆን "የሚሰበስብ" ማለት ነው፣ "መጥራት" ከሚለው ሥር፡፡

ሐ. (*Qoheleth* ) የሚለው ቃል ፍችው፡
1. ታዳሚዎችን የሚሰበስብ ሰው ነው፣ ስለዚህ፣ መምህር፣ ሰባኪ፣ ተከራካሪ/ያደባባይ ሰው፣ ወዘተ…
2. ምናልባትም በዘይቤነት፣ እውነትን የሚሰበስብ፣ ፈላስፋ ወይም ጠቢብ ሊሆን ይችላል፡፡

II. ቅዱስ ቃልነቱ/ካኖናዊነት

ሀ. መክብብ የጥበብ ሥነ-ጽሑፍ አንድ ምሳሌ ነው፡፡ እሱም የተራዘመ ማሳያ ነው፣ ለአንድ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ፣ እንደ ኢዮብ፡፡

ለ. እሱም የሦስተኛው ምድብ ክፋይ ነው፣ "ጽሑፎች" ተብሎ የሚጠራው የዕብራይስጥ ካኖን፡፡

ሐ. እሱም ደግሞ የአምስቱ አናሳ መጻሕፍት፣ ሜጊሎዝ ወይም "አምስቱ ጥቅሎች" ተብለው የሚጠሩት ልዩ ምድብ ክፋይ ነው፡፡ እነዚህ እያንዳንዳቸው በዓመታዊ የበዓል ቀናት ይነበባሉ፡፡ መክብብ በዳስ ወይም በድንኳን በዓል ላይ ይነበባል፡፡

መ. ከዚህ መጽሐፍ ጽንፋዊ ባሕርይ የተነሣ፣ እሱ በወግ አጥባቂ ራቢያዊ፣ የሻማይ ትምህርት ቤት ተቀባይነት አላገኘም ነበር፣ ነገር ግን በሊበራል ራቢያዊ የሂላል ትምህርት ቤት ድጋፍ አገኘ፡፡ ይህ ውይይት/ክርክር እስከ ጃሚያ ጊዜ እንኳ ቀጥሎ ነበር፣ ከኢየሩሳሌም ውድቀት በኋላ /70-90 ዓ.ም/፡፡

ሠ. በርከት ያሉት የብኪ ካኖናዊ መጻሕፍት ተቀባይነትን ለማግኘት ችግር ነበረባቸው፡
1. መክብብ - መራራ፣ አሉታዊ፣ ወግ/ልማዳዊ መንፈስ የሌለው
2. መኃልየ መኃልይ - አካላዊ ፍቅርን ስለሚያስረግጥ
3. አስቴር - እግዚአብሔርን ወይም የአይሁድ መቅደስን ወይም ስፍራዎችን ስለማይጠቅስ
4. ሕዝቅኤል - የእሱ መቅደስ ከሙሴ የተለየ ስለሆነ
5. እና በተወሰነ ደረጃ፣ ዳንኤል - የፍጻሜ ጥፋት ትንቢቶች የሆኑት ምዕራፍ 7-12

ረ. መክብብ በመጨረሻ ተቀባይነት ያገኘበት ምክንያት፡
1. ለሰሎሞን አስተዋጽዖ በመስጠቱ፣
2. ወግ/ልማዳዊ ማጠቃለያ ስላለው፣
3. የሰዎች የሕይወት ልምድ እውነታ ጽምጸት ስላለው እና በድኅረ-ግዞት አይሁድ ማኅበረሰብ የነበረውን ውዥንብር/መደነጋገር ስለሚገልጥ፡፡

III. ዘውግ

ሀ. መክብብ እንደ ኢዮብ መተርጎም የሚኖርበት በጥቅል/ሙሉውን ነው፡፡ እሱም እስከ ምዕ. 12 ድረስ በውስጠ-ወይራ/ዘይቤ የተደራጀ ነው፡

ለ. እሱም በአስተውሎትና በአስገራሚነት የኀለበተ ውስጠ-ወይራ የሕይወት አተያይ ነው፣ አምላክን ካላካተተ፡፡ ቁልፉ ሐረግ "ከፀሐይ በታች" ነው፣ 1፡3፣ 9፣ 14፤ 2፡11፣ 17፣ 18፣ 19፣ 20፣ 22፤ 3፡16፤ 4፡1፣ 3፣ 7፣ 15፤ 5፡13፣ 18፤ 6፡1፣ 5፣ 12፤ 7፡11፤ 8፡9፣ 15፣ 17፤ 9፡3፣ 6፣ 9፣ 11፣ 13፤ 10፡5፤ 11፡7፤ 12፡2 (31 ጊዜ)፡፡

IV. ደራሲነት

ሀ. የመጽሐፉ ደራሲ /ምንጭ/ አይታወቅም፡፡

ለ. የአይሁድ ወግ/ልማድ የሚለው፣ እሱ ሰሎሞን ከጻፋቸው ሦስት መጻሕፍት መካከል አንደኛው ነው፡ /ሚድራሽ ሺር ሃሽረም ራባህ 1፣ 1፣ ክፍል 10)
1. መኃልየ መኃልይ፣ ወጣት በነበረ ጊዜ፣
2. ምሳሌ፣ መካከለኛ ዕድሜ ላይ ሳለ፣
3. መክብብ፣ በሸመገለና በተመረረ ጊዜ፡፡

ሐ. ሰሎሞን በርግጥ ተቃርኗዊ የአጻጻፍ ስልት አለው፣ ምዕራፍ 1-2፣ በጥበቡ፣ ሀብቱ እና በሥልጣኑ ምክንያት፡፡ ነገር ግን እሱ እውነተኛው ደራሲ ላለመሆኑ ጠቋሚዎች አሉ፡
1. 1፡12 ላይ፣ "እኔም በእስራኤል ላይ በኢየሩሳሌም ንጉሥ ነበርኩ፡፡" /NIV/ - ሀላፊ ጊዜ
2. 1፡16 ላይ፣ " ከእኔ አስቀድመው በኢየሩሳሌም ላይ ከነበሩት ሁሉ ይልቅ..." /NASB/ - ዳዊት ብቻ ነበር ከሰሎሞን በፊት
3. 4፡1-3፣ 5፡8 እና 8፡9 መንግሥታዊ ግፍ/አግባብ ያልሆነ አያያዝ/ ተብራርቷል፣ ግን እንደ ተስፋ ቢስ፡፡
4. የሰሎሞን ስም በመጽሐፉ ላይ አይከሰትም፡፡

መ. ለሰሎሞን ደራሲነት ምሑራዊ ክርክር (*Introduction to the Old Testament*, by C. F. Keil, vol. 1, pp. 516-529)፡፡

ሠ. ባባ ባትራ 15ሀ የሚለው፣ የሕዝቅያስ ሰዎች ምሳሌን፣ መክብብን እና መኃልየ መኃልይን ጻፉ፣ ነገር ግን ይህ ማለት፣ በግልጽ የጥበብ መጻሕፍትን እነርሱ አዘጋጁት ወይም አጠናቀሩት ማለት ነው፡፡

ረ. (*Qoheleth* ቆኸሌዝ) የሚለው ቃል የተጸውዖ ስም ወይም መጠሪያ/ማዕርግ ሊሆን ይችላል፡፡ እሱም መጠሪያ ይመስላል፣ ምክንያቱም፡
1. እሱ የተወሰነ/በግልጽ የተቀመጠ አንቀጽ አለው፣ 7፡27 እና 12፡8 ላይ፣
2. እሱም አንስታይ/የሴት መልክ ይዟል፣ ሹመቱን የሚያመለክት፣ ነገር ግን ተባዕታይ/የወንድ ግሦችን ይጠቀማል፣
3. እሱም ያልተለመደ ቃል ነው፣ በዚህ መጽሐፍ ላይ ብቻ ሰባት ጊዜ የሚገኝ፡፡

ሰ. ብቸኛው የመጽሐፉ ክፍል፣ እሱም ደራሲውን ወይም ኋለኛውን አዘጋጅ የሚገልጠው 12፡9-14 ነው፡፡ እሱም በርግጥ ጠቢብ፣ የጥበብ መምህር ነው፡፡

ሸ. አጠቃላዮቹ አያዎዎች /ፓራዶክስ/ ወይም ተቃርኖዎች ተብራርተዋል፣ እንደ፡
1. ውስጠ-ወይራ፣ ሕይወት ያለ እግዚአብሔር /"ከፀሐይ በታች"/
2. ወግ/ልማዳዊው የአይሁድ ጥበብ እና ተግዳሮቱ /ለመነቀፍ/ለመጣል ተጠቅሰዋል/
3. የጥበብ መምህር እና የእርሱ ተማሪኪ/ተደሳች ወጣት ተማሪ እና ተራኪ /ምልልስ/
4. በወደቀው ሰው ውስጥ ያለ ግጭት/ተቃርኖ /የሕይወት ጋዜጣ/
5. ኋለኞቹ አዘጋጆች፣ ለምሳሌ፣ 12፡9-12 (*Qoheleth* ) አዎንታዊ የሆኑ/ እና 12፡13-14 / *(Qoheleth* ለቆኸሌዝ) አሉታዊ የሆኑ/፡፡

V. ጊዜው

ሀ. ሁለት ጉዳዮች አሉ፣ የመክብብን ጊዜ በተመለከተ፡
1. መጽሐፉ በተጠናቀረበት ጊዜ፣
2. በመጨረሻው ካኖናዊ መልክ ላይ ሲቀመጥ፡፡

ለ. ታሪካዊ መቼቱ ከሰሎሞን ጊዜ በኋላ መሆን ይኖርበታል፡፡ እሱ እንደ ጽሑፋዊ ተቃርኖ ተገልጿል፣ ምዕራፍ 1-2 ላይ፡፡

ሐ. የመጽሐፉ የመጨረሻ መልክ ወደ ኋለኛ ጊዜ ያመለክታል፡
1. የዕብራይስጡ ስልታዊ/ስታይል መልክ፣ ድኅረ ግዞት ነው፣ ነገር ግን ከ400-300 ቅ.ል.ክ በፊት፡፡
   ሀ. አራማዊ ቃላትና ገለጻዎች
   ለ. የዕብራይስጥ መልክ
2. ጽሑፋዊ ትይዩዎች አሉ፣ በፍንቄአውያን የጥበብ ሥነ-ጽሑፍ፣ 600-400 ቅ.ል.ክ አካባቢ፡፡
3. የመክብብ ጠቃሾች ይገኛሉ፣ በቤን ሲራክ የጥበብ ጽሑፎች ላይ፣ 180 ቅ.ል.ክ አካባቢ የተጻፉት፡፡
4. በርከት ያሉ የመጽሐፈ መክብብ አነስተኛ ክፍሎች ከሙት ባሕር ጥቅሎች ላይ ተገኝተዋል /4ኪው/፡፡ እነዚህም የሚያስቆጥሩት ጊዜ የሁለተኛው ክፍለ ዘመን ቅ.ል.ክ መጨረሻ ላይ ነው፡፡

VI. ጽሑፋዊ ምድብ

ሀ. ይህ መጽሐፍ የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝሩን ለማዘጋጀት አስቸጋሪ ነው፡፡ እሱም የሕይወት ጋዜጣ ነው የሚመስለው፣ ከተዋቀረ ጽሑፋዊ ሥራ ይልቅ፡፡ እሱም ከራቢያዊ ትምህርት ጋር ይመሳሰላል፣ "ዕንቍ በድሪ/በክር" ተብሎ ከሚጠራው፡፡ ሆኖም፣ ኅብራዊ ሐሳቦች ይኖራሉ፣ ካልሆነም ኅብራዊ ጭብጥ፡፡

ለ. የአዘጋጆች ተጨማማሪዎች ተደርገው ሊሆን ይችላል፡
1. መክፈቻ፣ 1፡1
2. አካታች 1፡2 እና 12፡8 አንድምታዎች 1፡1 እና 12፡9-14 ተጨማሪዎች ናቸው
3. ሁለት ተጨማሪ ቅጥያዎች፡
   ሀ. 12፡9-12 /በሦስተኛ መደብ/
   ለ. 12፡13-14 /ወግ/ልማዳዊ ሥነ-መለኮት/

ሐ. ምዕራፍ 1-2 ሰሎሞንን እንደ ጽሑፋዊ ተቃርኖ መጠቀማቸው ግልጽ ነው፡፡

መ. ምዕራፍ 3 አስደናቂ ግጥም ነው፣ የጋራ ስለ ሆነው የሰው ሕይወት ልምድ፡፡

ሠ. ቀሪው በቀላሉ የፍሬ-ሐሳቡ ዝርዝር አይወጣም!

VII. ሥነ-መለኮታዊ ጉዳዮች

ሀ. የዚህ መጽሐፍ በቅዱስ ቃል /ካኖን/ ውስጥ መገኘት ዓይነተኛው ሐቅ የሚመስለው፣ እግዚአብሔር ቅኑን፣ በጥርጣሬ የተሞላውን ፈላጊ እንደማይተወው ለማሳየት ነው፡፡

ለ. የመዳረሻውን ጥያቄ መጠየቅ አይነቀፍም፡፡

ሐ. መክብብ የእግዚአብሔርን ሕልውና ግምት ውስጥ ያስገባል፣ ብሎም የተጻፈው በብኪ እምነት ፍሰት ውስጥ ነው፡፡

መ. ክፉ የሰው ውጤት ነው፣ የእግዚአብሔር ሳይሆን (ዝከ. 7:29፤ 9:3)፡፡

ሠ. የእግዚአብሔር መንገዶች ሊታወቁ አይችሉም፡፡ ሰው የግድ መታገል ይኖርበታል፣ ለሕይወት ፍቺ!

ረ. ከሕይወት ወዲያ ስላለው ቀጥተኛ አተያይ ላይ ያለ ጥርጣሬና፣ እግዚአብሔርን ሙሉ ለሙሉ ለማወቅ በሰው ችሎታ ላይ ያለ ጥርጣሬ፣ ግን አሁንም እግዚአብሔር ቸር ነው፡፡

ሰ. ዓለም፣ ባለበት መልኩ፣ ፍትሐዊ አይደለም፣ ጨካኝ ነው፣ አንድ ተጨማሪ ነገር መኖር አለበት!

ሸ. በሕይወት ውስጥ ተካተት -- እሱ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነውና፡፡ በእርሱ ተደሰት፣ መቼም ሆነ የትም ቢሆን፡፡ /2፡24/

ቀ. ቀለል ያሉ መልሶች፣ ከሕይወት ልምምዶች ጋር የማይገጥሙ ከሆኑ፣ መልሶች "አይደሉም፡፡" የሕይወትን ትርጉም የለሽነት እውነታ የግድ ልንጋፈጥ ይገባል፣ እግዚአብሔር ከሌለበት፡፡

VIII. ዋነኛ ሐቆች

ሀ. የእርሱ ዋነኛ ዓላማ ከእግዚአብሔር ውጭ የሆነ የሰው ሕላዌ ትርጉም-የለሽ /ከንቱ/ መሆኑን ማሳየት ነው፡፡ እሱም፣ በራሴ ብቁ ነኝ የሚሉትን ቁስ-አካላውያን ወይም ምሑራንን ለመለወጥ የቀረበ ጽሑፍ ነው፡፡ ቢ. ኤች. ካሮል የሚለው፣ በእርሱ የክህደት ዘመን፣ መክብብና ኢዮብ በእርሱ ላይ ከተፈጥሮ በላይ በሆነ ኃይል ተጽዕኖ አሳድረዋል፣ የሕይወትን ባዶነት በመግለጽ፣ ብሎም ወደ እግዚአብሔር በማሳየት፡፡

ለ. ደስታ እና ተድላ ይገኛሉ (2:24፤ 3:12-13፣ 22፤ 5:18-20፤ 8:15፤ 9:7-9፤ 12:13-14):
1. በእምነትና ለእግዚአብሔር በመታዘዝ፣
2. በቤትና በቤተሰብ ከሚገኝ ደስታ፣
3. በሥራ፡፡

ሐ. ይህ መጽሐፍ ስለ እግዚአብሔር ሕላዊ የእውቀት ጉድለት/ጥርጣሬ አለው፣ እንዲሁም ስለ ከሕይወት በኋላ፡፡ እሱም የመዳረሻውን እውነታ ጥያቄዎች አይመልስም፣ ነገር ግን ስለ አሁኑ ተጨባጭ እውነታ ጥያቄ ይጠይቃል፡
1. ለአይሁድ፣ ጥልቀት የሌለውን የተጋነነ በልማዳዊ ሥነ-መለኮታውያን የሚደረገውን ስሕተት ያመላክታል /"ሁለቱ መንገዶች"/፡፡
2. ለባዕድ አምልኮተኞች /ጣዖት/፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያልሆነ የምድራዊ ሕይወትን ኪሳራ ያሳያል፡፡
3. ለሕይወት ጥያቄዎች የሚሆኑ ቀላል መልሶች ዘወትር ስሕተት ናቸው፡፡ ምሥጢር ይኖራል፣ ለእምነት እንኳ ቢሆን! ራዕይ ሁሉንም አይገልጥም!

መ. ይህ ደራሲ ተፈጥሯዊ መገለጥን ይጠቀማል፣ የተለየ መገለጥን ሳይሆን፣ ሕይወትን ለመመርመር፡፡ የእግዚአብሔር የኪዳን ስም፣ ያህዌ በመጽሐፉ ላይ አይገኝም፡፡ እንደ ሌሎቹ የጥበብ ሥነ-ጽሑፎች የእግዚአብሔር አጠቃላይ ስም፣ *Elohim* ነው ጥቅም ላይ የዋለው፡፡

ሠ. ይህ መጽሐፍ ጥርት ያሉና ቅቡልነትን ባገኙ ምሳሌዎች ላይ ሚዛኑን ያደርጋል /ያመዛዝናል/፣ ለሕይወት ስኬትን በሚሰጡት፡፡ በሕይወት ላይ፣ በተፈጥሮ ላይ፣ በሰው ላይ፣ በእግዚአብሔር ላይ ምሥጢር አለ፡፡ ቁልፉ የሚገኘው እምነትጋ ነው፣ ዕውቀትጋ ሳይሆን፤ በቤተሰብ ዘንድ፣ በውርስ ላይ ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ዘንድ፣ በሰው ሳይሆን፡፡ የሕይወት ቀለል ያለ ደስታ፡ ቤተሰብ፣ ሥራ፣ ጓደኞች፣ መብል በዚህ ሕይወት ደስታን ይሰጣሉ፡፡ ቀጣዩ ሕይወት የተሸፈነ ነው፣ እግዚአብሔር ግን እዚያ አለ!

IX. ቃላት/ሐረጋት እና ሰዎች በአጭሩ የሚገለጹ


ሀ. ቃላት/ሐረጋት
1. "የከንቱ ከንቱ" 1፡2 (NIV፣ "ትርጉም አልባነት! ትርጉም አልባነት!")
2. "ከፀሐይ በታች" 1፡3 (NASB እና NIV)
3. "በጥበብ መብዛት ትካዜ ይበዛልና" 1፡18 (NIV፣ "በጥበብ መብዛት ኀዘን ይበዛልና")
4. "ለሁለቱም መጨረሻቸው አንድ እንደሆነ አስተዋልሁ" 2፡14 (NASB እና NIV)
5. "እሱም ደግሞ ዘላለማዊነትን በልቡ ሰጠው" 3፡11 (NASB እና NIV)
6. "እግዚአብሔር በርግጥ ይፈትናቸዋል..." 3፡18 (NASB እና NIV)
7. "ከእነዚህ ከሁለቱ ይልቅ ገና ያልተወለደው ይሻላል..." 4፡2-3 (NIV፣ "ከእነዚህ ከሁለቱ ይልቅ ገና ያልተፈጠረው ይሻላል")
8. "እግዚአብሔርን ፍራ" 5፡7 (NIV፣ "በእግዚአብሔር ፍርሃት ቁም")
9. "ብርን የሚወድድ ብርን አይጠግብም" 5፡10 (NASB እና NIV)
10. "እጅግ ጻድቅ አትሁን፥ እጅግ ጠቢብም አትሁን" 7፡16 (NASB እና NIV)
11. "ጉድጓድን የሚምስ ይወድቅበታል" 10፡8 (NASB እና NIV)
12. "እንጀራህን በውኃ ፊት ላይ ጣለው፣ ከብዙ ቀን በኋላ ታገኘዋለህና" 11፡1 (NASB እና NIV)


ለ. ሰዎች
1. *(Qoheleth* ቆኸሌዝ) 1፡1
2. ጠባቂ 12፡3-4 (NIV፣ "የቤት ጠባቂዎች")
3. አንድ እረኛ 12፡11
4. ልጄ 12፡12

X. የካርታ ስፍራዎች - የለም

XI. የተማሪ የውይይት ጥያቄዎች

1. የዚህ መጽሐፍ አጠቃላይ ዓላማ ምንድነው?
2. ሰሎሞን የምዕራፍ 1-2 ጽሑፋዊ ተቃርኖ ለምን ሆነ?
3. ሰው እንዴት ከእንስሳት ጋር እንዴት ይመሳሰላል፣ ይለያያልም? 3፥12-22
4. እግዚአብሔርን ልናውቀው እንችላለን?
5. ደስታ የት ነው የሚገኘው?
6. ይህ መጽሐፍ የተጻፈው ለማነው፣ ለምን?


ANCIENT
NEAR EAST
N
S
E
W


PALESTINE
0 10 20 30 40
SCALE IN MILES

# መግቢያ ለመኃልየ መኃልይ

I. የመጽሐፉ ስም

ሀ. ይህ መጽሐፍ፣ ልክ እንደ ሌሎቹ የብኪ መጻሕፍት ሁሉ፣ በመነሻው/በዋናነት የተሰየመው በመጽሐፉ የመጀመሪያዎቹ ጥቂት ቃላት ነው፡፡ በዕብራይስጥ የመጀመሪያዎቹ ቃላት "መኃልየ መኃልይ ይኸውም የሰሎሞን"፣ የሚል ነው፣ በዕብራይስጥ የላቀ ደረጃ የተቀመጠ፡፡ የሚሰጠው አንድምታም ከንጉሣዊ የፍቅር መዝሙራት እጅግ የተሻለው የሚል ነው፡፡

ለ. መጽሐፉ ደግሞ "ካንቲክለስ" /የፍቅር ግጥሞች ስብስብ/ በመባል ይታወቃል፣ ቫልጌት ላይ፡፡ (*canticum canticorum*)

II. ቅዱስ ቃልነቱ (ካኖናይዜሽን)

ሀ. በዚህ መጽሐፍ ያልተለመደ ይዘት ምክንያት በቅዱስ ቃልነት አቋም /ካኖኒካል/ ተቀባይነት ለማግኘት ችግር ገጥሞታል፡

1. የራቢያዊ ትምህርት ቤት ሻማይ /ወግ አጥባቂ/ መጽሐፉን ተቃውሟል፡፡
2. የራቢያዊ ትምህርት ቤት ሂላል /ለዘብተኛ/ መጽሐፉን አጽንቷል/ተቀብሏል፡፡
3. በራቢያዊ የጃሚያ ጉባኤዎች /90 ዓ.ም/ መጽሐፉ አሁንም ገና እያከራከረና እንደ ካኖናዊ ለመቀበል ጥያቄ እያስነሣ ነው፡፡
4. በራቢ አኪባ /አቂባ/ መሪነት እሱ በመጨረሻ እንደ ካኖናዊ ተቀባይነት አገኘ፡፡ እሱ ስለዚህ መጽሐፍ የሚለው፣ "ዓለም ሁሉ ምንም ረብ/ጠቀሜታ የለውም፣ መኃልየ መኃልይ ለእስራኤል ከተሰጠበት ቀን ይልቅ፣ ሁሉም ጽሑፎች ቅዱስ ናቸው፣ መኃልየ መኃልይ ግን ቅድስተ-ቅዱሳን ነው፡፡"

ለ. እሱም በልዩ ዝርዝር ውስጥ ካሉት መጻሕፍት የመጀመሪያው ነው፣ ከዕብራይስጥ ካኖን የጽሑፍ ምድብ፣ *Megilloth* ሜጊሎዝ /አምስቱ ጥቅሎች/ ተብሎ ከሚጠራው፡፡ እያንዳንዱ በዓመታዊ የበዓል ቀን ይነበባል፡፡ መኃልየ መኃልይ በፋሲካ በዓል ላይ ይነበባል፡

1. መኃልየ መኃልይ - ፋሲካ
2. ሩት - በዓለ ኀምሳ/ጰንጠቆስጤ
3. መክብብ - የዳስ ወይም የድንኳን በዓል
4. አስቴር - ፉሪም
5. ሰቆቃወ ኤርምያስ - የኢየሩሳሌም መውደቅ እና የሰሎሞን ቤተ-መቅደስ መፍረስ

ሐ. የዕብራይስጥ ካኖን የጽሑፍ ምድብ መኃልየ መኃልይን ከመዝሙር፣ ምሳሌ እና ኢዮብ በኋላና ከሩት፣ ሰቆቃ፣ መክብብ እና አስቴር በፊት ያስቀምጠዋል፡፡ የእንግሊዝኛው መጽሐፍ ቅዱስ የLXXን ቅደም ተከተል ይከተላል፡፡

III. ዘውግ

ሀ. ዘውግ ዋና ጉዳይ ነው፣ መጽሐፍን ለመተርጎም፡፡ ዘውግ ወሳኝ ነገር ነው፣ የዋነኛውን ደራሲ ዓላማ ይዘት ለመለየት፡፡ መጽሐፉ ሙሉ በሙሉ የተጻፈው በቅኔ ነው፡፡

ለ. ንድፈ-ሐሳቦቹም፡

1. የአይሁድ ምሳሌ/ምስያ - ሚሽናህ፣ ታልሙድ እና ታርጉምስ፣ ሁሉም የሚያረጋግጡት፣ ይህ መጽሐፍ የሚገልጸው የአይሁድን ታሪክ ነው፣ እግዚአብሔር ለእስራኤል ባለው ፍቅር አኳያ፡፡ እስራኤል የያህዌ ሙሽራ ነች /ዘጸ. 34:15-16፤ ሌዋ. 17:7፤ 20:5-6 እና ዘኁ. 14:33)፡፡
2. የክርስቲያን ምሳሌ/ምስያ - ኦሪጅን፣ ጀሮም፣ አትናስዩስ፣ አውግስቲን፣ ቶማስ አኩናስ እና ሉተር ሁሉም የሚያስረግጡት ይህ መጽሐፍ የሚገልጸው ቤተ-ክርስቲያንን ነው፣ ከክርስቶስ ፍቅር አኳያ፡፡ ዘወትርም ኤፌ. 5፡21-31 እንደ ትይዩ ይሰጣል፡፡
3. ወግ/ልማዳዊ የሰርግ መዝሙሮች - ትርጉም ያለው ተመሳሳይነት አለ፣ በዚህ መጽሐፍ እና በሶርያ የፍቅር ግጥሞች መካከል፣ 600 ቅ.ል.ክ አካባቢ፣ *wasfs* በመባል የሚታወቀው፡፡ ሙሽሪትና ሙሽራው የመልካም ምኞት መግለጫ ይለዋወጣሉ፣ እርስ በርሳቸው "ንጉሥ" እና "ንግሥት" ተብሎ በመጠራራት፡፡ እንዲሁም ደግሞ ከግብፃውያን የፍቅር ግጥሞች ጋር አንዳንድ ትይዩዎች አሉ፣ ፍቅረኛዋ "እኅት" ተብላ የምትጠራበት (4:9-10፣12፤ 5:1-2)፡፡ ይህ ዓይነቱ ሥነ-ጽሑፍ ታማኝን የሚያመሰግን፣ በጊዜው የሆነ የሰው ፍቅር በጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ እጅግ የታወቀ ነበር፡፡
4. ድራማ
   ሀ. መጽሐፉ ድራማ ነው፣ በርከት ባሉ ተዋንያን የሚተወን፡
      (1) ንጉሥ፣
      (2) የሰሜናዊ አገር ልጃገረድ፣
      (3) የሰሜናዊ አገር/አካባቢ ፍቅረኛ፣
      (4) ኅብረ-ዘማርያን ወይም የቆነጃጅት ስብስብ /"የኢየሩሳሌም ሴት ልጆች"/፡፡
   ለ. የዚህ ዓይነቱ መድረክ ከምዕራፍ 1 ሊቀርብ ይችላል፡
      (1) ቁ. 2-4ለ፣ ሙሽሪት
      (2) ቁ. 4ሐ-ሠ፣ ኅብረ ዘማርያን (ዝከ.2:7፤ 3:6-11፤ 5:9፤ 6:1፣13፤ 8:5፣8)
      (3) ቁ. 5-7፣ ሙሽሪት
      (4) ቁ. 8፣ ኅብረ-ዘማርያን
      (5) ቁ. 9-10፣ ሙሽራው
      (6) ቁ. 11፣ ኅብረ-ዘማርያን
      (7) ቁ. 12-14፣ ሙሽሪት
      (8) ቁ. 15፣ ሙሽራው
      (9) ቁ. 16-17፣ ሙሽሪት
   ሐ. የሰሜናዊው ልጅ ጓደኛ ንድፈ-ሐሳብ የተመሠረተው፡

(1) ፍቅረኛው እረኛ ተብሎ ተጠርቷል፣ በጎቹን የሚያሰማራ፡፡
(2) መጽሐፉ በሰሜን ነው የሚያበቃው፣ በኢየሩሳሌም ሳይሆን፡፡
(3) ቆነጃጅቱ ተነቅፈዋል፣ 6፡8-9፡፡

መ. የግሪኩ ጽሑፍ *Sinaiticus* ለእያንዳንዱ ክፍል ርዕስ አለው፣ ከሙሽሪትና ከሙሽራው ጋር የሚያያዝ፡፡

5. ምስያ - ይህ ንድፈ-ሐሳብ ጥሬአዊውንና ተምሳሌታዊውን ለማደባለቅ ይሞክራል፡፡ እሱም የሰው ግብረ-ሥጋ ግንኙነት ያለውን ደስታ በጽኑ ይወስዳል፣ እናም የአንድ ለአንድ ጋብቻን አንድምታ፡፡ ብሎም የአጠቃላዩን ምድብ ዓላማ ይመለከታል፣ ከእስራኤል ጋር በተያያዘ፡፡

6. ጥሬአዊ - ይህ ንድፈ-ሐሳብ የሚያስረግጠው እግዚአብሔር የሰጠውን የሰው ግብረ-ሥጋ ግንኙነት ገጽታ ነው፡፡ እሱም መጽሐፉን ፊት ለፊት ባለው መልኩ ይወስዳል፡፡ ይህ አተያይ በሞሱስቲያው ቲዎዶር፣ ተቀባይነት አግኝቶ ተራምዷል፣ የአንቲሆቻውያን የትርጓሜ ትምህርት ቤት ብሩኅ ብርሃናት ከሆኑት መካከል አንደኛው፡፡

ሐ. ይህ መጽሐፍ ሁነኛ የጥበብ ሥነ-ጽሑፍ አይደለም፣ ሆኖም እሱ በተመሳሳይ መንገድ ይሠራል፣ ወጣት ወንዶችን ለማሠልጠን፡፡ እሱም ከአንድ ለአንድ ጋብቻ ጋር በተያያዘ የሞራል ገጽታ እንዲኖር የሚያደርግ ይመስላል፣ እንዲሁም የሰው የግብረ-ሥጋ ግንኙነት በተገቢው ጊዜና፣ ከተገቢው ሰው ጋር ሲፈጸም የሚኖረውን ንጽሕናና ውበት፡፡

IV. ደራሲነት

ሀ. ባባ ባትራ 15ሀ የሚለው ሕዝቅያስና ሰዎቹ መጽሐፉን ጻፉት ነው፡፡ "ጻፈ" ማለት በግልጽ፡ ሰበሰበ ወይም አዘጋጀ ማለት ነው፣ ደረሰ ሳይሆን /ምሳ. 25፡1/፡፡

ለ. የአይሁድ ወግ/ልማድ ዘወትር የሚያስረግጠው ሰሎሞን ይሄንን መጽሐፍ እንደጻፈ ነው፡

1. የእርሱ ስም 1፡1፣5፤ 3:7፣ 9፣ 11፤ 8:11፣ 12 ላይ ስለሚገኝ፡፡
2. "ንጉሥ" የሚለው ቃል 1:4፣ 12፤ 7:5 ላይ ስለሚገኝ፡፡
3. የግብፅ ፈረሶች ተጠቅሰዋል፣ 1:9 ላይ፣ ይኸውም ከሰሎሞን አገዛዝ ጋር የሚገጥም (1 ነገሥ. 10:28)፡፡
4. ደራሲው መልክዓ-ምድራዊ ስፍራዎችን ጠቅሷል፣ ፍልስጥኤምን አካልሎ፣ ሶርያ እና የዮርዳኖስ ዙሪያ ስፍራዎችን፣ እስከ አራባ ታች ድረስ፡፡ ይኽም የሰሎሞንን ንጉሣዊ ግዛት መልክዓ-ምድራዊ ዳርቻ ያመላክታል፡፡
5. ራቢዎች የሚሉት ሰሎሞን ወጣት በነበረበት ጊዜ የፍቅር መዝሙሮችን ጽፏል /መኃልየ መኃልይ/፣ ጎልማሳ ሲሆን ምሳሌዎችን /ምሳሌ/ ጽፏል እንዲሁም ዕድሜው ሲገፋ የነገሮችን ሁሉ ከንቱነት ጽፏል /መክብብ/፡፡

ሐ. አንዳንድ አሉታዊ ምክንያቶች በሰሎሞን ደራሲነት ላይ፡

1. ርዕሱ በዕብራይስጥ፣ "መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን" ፍችው የሚሆነው፡
   ሀ. በሰሎሞን፣
   ለ. ለሰሎሞን፣
   ሐ. ስለ ሰሎሞን፣
   መ. በሰሎሞን ጊዜ፣
   ሠ. በሰሎሞን አገባብ/መንገድ፡፡
2. ይህ መጽሐፍ የሚፈጸመው በሰሜን እስራኤል ነው /7፡10-13/ እናም በኢየሩሳሌም የሴቶች መኖርያ አይደለም፡፡
3. መጽሐፉ ማስረገጥ የሚሞክረው የአንድ ለአንድ ጋብቻ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት መልካምነትና ጠቀሜታ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከሰሎሞን ሕይወት ጋር የሚገጥም አይደለም፡፡ ሰሎሞን የመኃልየ መኃልይ ጽሑፋዊ አቀንቃኝ/መሣርያ ሊሆን ይችላል፣ የመክብብ እንደሆነ ሁሉ 1-2 (E. J. Young, *An Introduction to the Old Testament*, p. 268)፡፡

V. ጊዜው

ሀ. እንደ አብዛኞቹ የብኪ የጥበብ መጻሕፍት፣ ስለ ጊዜው ሁለት ገጽታዎች አሉ፡

1. ዋነኛው ታሪካዊ መቼት፣
2. የመጽሐፉ ጊዜና መልክ፣ በቅዱስ ቃሉ /ካኖን/ ባለበት ሁኔታ፡፡

ለ. ታሪካዊ መቼት፡

1. የሰሎሞን ጊዜ፡
   ሀ. የንጉሡ ሥልጣን በርካታ ሚስቶችን ለመውሰድ፣
   ለ. የሴቶች መኖርያ መኖሩ፣ እንደ ኅብረ-ዘማርያን፣
   ሐ. ሰፊና የተለያዩ መልክዓ-ምድራዊ ስፍራዎች እውቀት /ብሎም እንስሳትና ዕጽዋት/፡፡
   መ. ኢየሩሳሌም ከቴርሳ ጋር ትይዩ ተደርጋለች፣ እሷም ከሰማርያ በፊት የእስራኤል ዋና ከተማ የነበረች /ኦምሪ/፣ 6፡4፡፡
2. የመጽሐፉ የመጨረሻ መልክ፡
   ሀ. የአንስታይ ጾታው አነጻጸሪ የድርጊት ቃሉ የኋለኛው/የቅርቡ ዕብራይስጥ ነው (ዝከ. 1:12፤ 2:7)
   ለ. የአራማዊና የግሪክ የትውስት ቃላት አጠቃቀም
      (1) ገነት
      (2) ያትክልት ስፍራ
      (3) አልጋ
      (4) ሠረገላ

ሐ. ዘመናዊው አስተምህሮ አይስማማም፡

1. E. J. Young –– የሰሎሞን ጊዜ
2. W. F. Albright–– - አምስተኛ-አራተኛ ክፍለ-ዘመን ቅ.ል.ክ
3. R. K. Harrison- የመጨረሻው ቅርጽ/መልክ ከግዞት በፊት ወዲያውኑ

VI. ጽሑፋዊ ምድቦች

ሀ. መጽሐፉ ላይ በርከት ያሉ አስቸጋሪ ገጽታዎች አሉ፡፡ አንዱ ሊደነቅ ይችላል፣ ኅብራዊ ጭብጥ ወይም ዓላማ ወይም ተለጣጣቂነት ያላቸው ግጥሞች ካሉ፡፡

ለ. የሚከተሉት ቁጥሮች ለመተርጎም አስቸጋሪ ናቸው፣ ከኅብራዊ ጭብጥ አኳያ፡

1. 2:15 3. 8:5ለ-ሠ
2. 5:7 4. 8:8-9

ሐ. መጽሐፉን ከኅብራዊ ጭብጥ አኳያ ለመተርጎም ያለው ብቸኛ መንገድ የሦስቱን ሰዎችና የኅብረ-ዘማርያኑን ድራማዊውን ትዕይንት መውሰድ/ማካተት ነው፡

1. ንጉሡ
2. የሰሜናዊ አገር ልጃገረድ
3. የሰሜናዊ አገር ፍቅረኛ
4. የቆነጃጅት ስብስብ እንደ ኅብረ-ዘማርያን

መ. ይህ መጽሐፍ፣ እንደ አስቴር ማንኛውንም የእግዚአብሔርን ስም አልያዘም /8፡6 የሚተረጎመው "የሚነድ ነበልባል" በሚል ነው፣ በአይሁድ የኅትመት ማኅበር የአሜሪካ ትርጉም ላይ/፡፡

VII. ዋነኛ ሐቆች

ሀ. ይህ በግልጽ የሰውን የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ንጽሕናና ውበት የሚያስረግጥ ነው፣ 8፡6-7፡፡ ይህ ግልጽ የሆነ ማስረገጫ ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን ከሌላው አኳያ ሲታይ ግን፡ (1) የዳዊት የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ኃጢአት እና የእሱ መዘዝ፣ በቤተሰቡ ላይ፣ እና (2) የሰሎሞን አመንዝራነት፣ ዕድሜው ከገፋ በኋላ፣ በባዕድ ሚስቶቹና በሃይማኖታቸው ሳቢያ፣ ይህ አስፈላጊው መግለጫ ነበር፡፡

ከግሪክ ሃይማኖታዊ ድርብነት አኳያ ይህ እውነት ዛሬ በርግጥ ያስፈልጋል፡፡ መንፈሳዊነት ራስን የመካድ /ዓለማዊ ደስታን ፈጽሞ የመተው ሁኔታ አይደለም! ሥጋዊው በራሱ ሁኔታ ክፉ አይደለም፡፡

ለ. ብዙዎች ይሄንን መጽሐፍ የሚመለከቱት ከብኪ ምስያ አኳያ ነው፣ እግዚአብሔር እንደ ባል እና እስራኤል እንደ ሚስት /ማለትም፣ ራቢያዊ ትርጉም፣ የዘጸአት እና የሆሴዕ 1-3/፡፡

ሐ. ሁለቱንም ማለትም ዘውግ እና ማዕከላዊ ዓላማውን የመለየት ችግር፣ አንዱን ከቀኖናዊ ትርጉሞች እንዲጠበቅ ያደርጉታል፡፡

መ. መጽሐፉ ለሃይማኖታዊ ወይም ብሔራዊ ጭብጥ ፍንጭ የለውም፡፡ ይህም ለቅዱስ ቃላዊ መጽሐፍ እጅግ ያልተለመደ ነው፡፡

VIII. ቃላት/ሰዎች በአጭሩ የሚገለጹ

ሀ. ቃላት/ሐረጋት

1. ከርቤ 1:13፤ 3:6፤ 4:6፣14፤ 5:1፣5፣13 (NASB እና NIV)
2. "ጥቃቅን ቀበሮዎች፣" 2:15 (NASB እና NIV)
3. "በሌሊት የሚወድቅ ፍርሃት፣" 3:8 (NASB እና NIV)
4. "ንግሥታት... ቊባቶች፣" 6:8፣9 (NASB እና NIV)
5. ሮማን፣ 7:13 (NASB እና NIV)
6. ማኅተም፣ 8:6 (NASB እና NIV)
7. እርስዋ ግንብ ነች፣ 8:9 (4:12) (NASB እና NIV)

ለ. ሰዎች


1. "ንጉሥ፣" 1፡4ለ፣ 12
2. "እኔ ጥቁር ነኝ፣ ነገር ግን ውብ ነኝ፣" 1፡5 /እኔ ጥቁር ነኝ፣ ግን ውብ ነኝ"/
3. "መንጋህን ወዴት ታሰማራለህ...፣" 1፡7 /NIV፣ "...ማልቀም... /ሣር ማስጋጥ/"/
4. "እኔ የሳሮን ጽጌረዳ፣ የቆላም አበባ ነኝ፣" 2፡1
5. "የኢየሩሳሌም ቆነጃጅት፣" 2፡7
6. ጠባቂ፣ 3፡3፤ 5፡7
7. "አንቺ ሱላማጢስ፣" 6፡13

IX. የካርታ ስፍራዎች


1. ዓይንጋዲ፣ 1፡14
2. ሳሮን፣ 2፡1
3. ሊባኖስ፣ 4፡8
4. አርሞንኤም ተራራ፣ 4፡8
5. ቴርሳ፣ 6፡4
6. ገለዓድ፣ 6፡5 /የገለዓድ ተራራ፣ 4፡1/
7. ደማስቆ፣ 7፡4
8. ቀርሜሎስ ተራራ፣ 7፡5

X. የተማሪ ይዘት ጥያቄዎች

1. መጽሐፉ ለምን በቅዱስ ቃሉ /ካኖን/ ውስጥ ተካተተ?
2. የዚህ መጽሐፍ ገኸ/ዋነኛ/ የሆነ ትርጉም በራሳቸው በአይሁድ ዘንድ ምንድነው? ለምን?
3. ይህ ምን ዓይነት ሥነ-ጽሑፍ ነው? ይህስ ምን ልዩነት ያመጣል?
4. በመጽሐፉ ውስጥ የእግዚአብሔር ስም ወይም የእስራኤል ታሪክ ለምን ፈጽሞ አልተጠቀሰም?
5. መጽሐፉ ኅብር ያለው /ወጥ የሆነ/ ጭብጥ አለውን?
6. "የኢየሩሳሌም ቆነጃጅት" እነማናቸው?
7. ታሪኩ የተካሄደባቸውን የተለያዩ ስፍራዎች ዘርዝር፡፡


N
W
E
S
ANCIENT
NEAR EAST

# PALESTINE



# የብሉይ ኪዳን ትንቢት መግቢያ

I. *መግቢያ*

*ሀ.* *የመክፈቻ መግለጫዎች*:

1. *አማኙ ማኅበረሰብ ትንቢትን እንዴት እንደሚተረጉም ስምምነት ላይ አልደረሰም። ሌሎች እውነቶች በክፍለ-ዘመናት መካከል ቀጥተኛ ወደሆነ አቋም ተደራጅተዋል፣ ይሄኛው ግን አይደለም።*
2. በርከት ያሉ የብኪ ትንቢት ደኅና አድርገው የተገለጹ ደረጃዎች አሉ፡
   *ሀ. ቅድመ-ንጉሣዊ አገዛዝ*፡
   (1) ነቢያት ተብለው የተጠሩ ግለሰቦች
   (ሀ) አብርሃም - ዘፍ. 20:7
   (ለ) ሙሴ - ዘኍ. 12:6-8፤ ዘዳ. 18:15፤ 34:10
   (ሐ) አሮን - ዘጸ. 7:1 (የሙሴ ቃል አቀባይ)
   (መ) ማርያም - ዘጸ. 15:20
   (ሠ) ሞዳድ እና ኤልዳድ - ዘኍ. 11:24-30
   (ረ) ዲቦራ - መሳ. 4:4
   (ሰ) ስሙ ያልተጠቀሰ - መሳ. 6:7-10
   (ሸ) ሳሙኤል - 1 ሳሙ. 3:20
   (2) ነቢያት እንደ ቡድን የተጠቀሱበት - ዘዳ. 13:1-5፤ 18:20-22
   (3) የትንቢት ቡድን ወይም ጉባኤ - 1 ሳሙ. 10:5-13፤ 19:20፤ 1 ነገ. 20:35፣41፤ 22:6፣10-13፤ 11 ነገ. 2:3፣7፤ 4:1፣38፤ 5:22፤ 6:1፣ ወዘተ.
   (4) *መሢሕ ነቢይ ተብሎ ተጠርቷል* - ዘዳ. 18:15-18
   ለ. *ያልተጻፉ ንጉሣዊ አገዛዛውያን (እነርሱ ንጉሥን ያመለክታሉ)*:
   (1) ጋድ - 1 ሳሙ. 22:5፤ 11 ሳሙ. 24:11፤ 1 ዜና. 29:29
   (2) ናታን - 11 ሳሙ. 7:2፤ 12:25፤ 1 ነገ. 1:22
   (3) አኪያ - 1 ነገ. 11:29
   (4) ኢዩ - 1 ነገ. 16:1፣7፣12
   (5) ስሙ ያልተጠቀሰ - 1 ነገ. 18:4፣13፤ 20:13፣22
   (6) ኤልያስ - 1 ነገ. 18-11 ነገ. 2
   (7) ሚክያስ - 1 ነገ. 22
   (8) ኤልሳዕ - 11 ነገ. 2:8፣13
   ሐ. የጥንቶቹ (ክላሲካል) የጽሑፍ ነቢያት (እነርሱ ሕዝቡን ብሎም ንጉሡን ነበር የሚመለከቱት)፡ - ኢሳይያስ-ሚልክያስ (ከዳንኤል በቀር)

*ለ.* *መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት*

1. *(Ro'eh ሮሀ )*= "ነቢይ፣" 1 ሳሙ. 9፡9። *ይህ ማጣቀሻ ራሱ የሚያሳየው Nabi. ናቢ ወደሚለው* ቃል የተደረገውን ሽግግር ነው። *Ro'eh ሮሀ* ከአጠቃላይ ቃል "ማየት" ማለት ነው። ይህ ግለሰብ የእግዚአብሔርን መንገዶችና ዕቅዶች የተረዳ ነው፣ እናም በሆነ ነገር ላይ የእግዚአብሔርን ፍቃድ ለማስረገጥ ምክር ይጠየቃል።
2. *(Hozeh ሆዜሀ)* = "(*Nabi* ነቢይ)፣" 11 ሳሙ. 24:11። እሱ በመሠረቱ *የሮሀ ተመሳሳይ* ነው። እሱ ካልተለመደው ቃል ከ "መመልከት" ነው። ያልተወሰነው አንቀጽ መልኩ አብዛኛውን ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውለው ነቢያትን ለማመልከት ነው።
3. *Nabi' ናቢ* = "ነቢይ" ከአካድያኑ *ግሥ* ከ *Nabu* ናቡ ጋር ተዛማጅ ነው = "መጥራት" እና ዓረብኛ *Naba'a ናባ* = "ማስታወቅ/ማወጅ።" ይህ በብሉይ ኪዳን እጅግ የተለመደ ቃል ነው፣ ነቢይን ለመጥራት። እሱም ከ300 ጊዜ በላይ ጥቅም ላይ ውሏል። ትክክለኛው *ሥርወ-ቃል* በርግጠኝነት ባይታወቅም ነገር ግን *"መጥራት"* በአሁኑ ጊዜ የተሻለ አማራጭ ይመስላል። የተሻለ *መረዳት ሊመጣ የሚችለው ያህዌ፣ ሙሴ ከፈርዖን ጋር ያለው ግንኙነት በአሮን በኩል መሆኑ* የገለጸበት ነው (ዘጸ. 4:10-16፤ 7:1፤ ዘዳ. 5:5። ነቢይ ከእግዚአብሔር ለእሱው ሕዝብ የሚናገር ነው (አሞጽ 3:8፤ ኤር. 1:7፣17፤ ሕዝ. 3:4።)
4. *ሦስቱም ቃላት ለነቢያት አገልግሎት ጥቅም ላይ የሚውሉ ናቸው* 1 ዜና. 29:29፤ ሳሙኤል - *Ro'eh; ሮሀ*፤ ናታን - *Nabi' ናቢ* እና *ጋድ - (Hozeh ሆዜሀ)*።
5. *('ish ha - 'elohim), ኢሽ ሃ - ኤሎሂም*፡ "የእግዚአብሔር ሰው፣" የሚለው ሐረግ ደግሞ ሰፋ ያለ መጠሪያ ነው፣ ስለ እግዚአብሔር ለሚናገር። እሱም 76 ጊዜ ያህል በብኪ ጥቅም ላይ ውሏል፣ "ነቢይ" በሚለው መልኩ።
6. "ነቢይ" የሚለው ቃል በዋነኛነት/በመነሻነት የግሪክ ነው። እሱም የመጣው፡ (1) ቀድሞ (ፕሮ) = "በፊት" ወይም "ለ"፤ (2) /phemi ፊሚ /= "መናገር" ከሚለው ነው።

II. የትንቢት ፍቺ

*ሀ.* "ትንቢት" የሚለው ቃል በዕብራይስጥ ሰፋ ያለ የፍቺ መስክ አለው፣ ከእንግሊዝኛ ይልቅ። የታሪክ መጻሕፍት የሆኑት ከኢያሱ እስከ *ነገሥት* (ከሩት በቀር) *"ቀዳሚዎቹ ነቢያት"* በሚል በአይሁድ *ተፈርጀዋል/ተሰይመዋል*። ሁለቱም አብርሃም (ዘፍ. 20፡7፤ መዝ. 105፡5) እና ሙሴ (ዘዳ. 18፡18) ነቢያት ተብለው ተጠርተዋል (ደግሞም ማርያም፣ ዘጸ. 15፡20)። ስለዚህ ከግምታዊ የእንግሊዝኛ ፍች ተጠንቀቁ!

*ለ.* *"ትንቢታዊነት፣ ተቀባይነት ባለው መልኩ ሊፈታ/ሊባል የሚችለው ታሪክን በመረዳት ነው፣ እሱም ፍችን የሚቀበለው ከመለኮታዊ እይታ፣ ከመለኮታዊ ዓላማ፣ ከመለኮታዊ ተሳትፎ አኳያ ብቻ ነው፣" የተርጓሚዎች የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ-ቃላት*፣ ቅጽ 3 ገጽ 896 (*Interpreter's Dictionary of the Bible*, vol. 3, p. 896)፡፡

ሐ. “ነቢይ፣ ፈላስፋ አልያም ስልታዊ ሥነ-መለኮታዊ አይደለም፣ ነገር ግን የኪዳን መካከለኛ/ማላጅ እንጂ፣ እሱም የእግዚአብሔርን ቃል ወደ ሕዝቡ የሚያደርስ፣ የወደፊታቸውን ለማስተካከል፣ የአሁናቸውን በማደስ፣” “ነቢያትና ትንቢት፣” (*Encyclopedia Judaica* vol. 13 p. 1152)፡፡

III. የትንቢት ዓላማ

ሀ. ትንቢት፣ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚናገርበት መንገድ ነው፣ አሁን ላሉበት መቼት/ሁኔታ ምሪት የሚሰጥበት፣ እና እሱ የሕይወታቸውና የዓለም ሁነቶች ተቆጣጣሪ መሆኑን ተስፋ እንዲያደርጉ። የእነርሱ መልእክት በመሠረቱ አጠቃላይ ነው። ይህም ማለት፣ ለመገሥጽ፣ ለማበረታታት፣ እምነትንና ንስሐን ለማነሣሣት፣ እና ለእግዚአብሔር ሕዝብ ስለ ራሱና ስለ ዕቅዶቹ ለማሳሰብ ነው። እዚህጋ የግድ መታከል የሚኖርበት፣ እሱ ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው የእግዚአብሔርን ቃል አቀባይ ምርጫ በግልጽ ለመግለጥ ነው (ዘዳ. 13:1-3፤ 18:20-22)። ይህ፣ በመዳረሻው ተወስዶ መሢሑን ያመለክታል።

ለ. ዘወትር ነቢዩ የሱን ቀን ታሪካዊ ወይም ሥነ-መለኮታዊ ቀውስ ወስዶ፣ ይሄንን በፍጻሜአዊ መዳረሻ መቼት ይነድፈዋል። ይህ የፍጻሜ ዘመን የታሪክ አተያይ በእስራኤል የተለየ ነው፣ እናም የእርሱ የመለኮት ምርጫና የኪዳን ተስፋዎች መልኮች።

ሐ. የነቢይ አገልግሎት ለማመዛዘን (ኤር. 18፡18) እና የሊቀ ካህኑን አገልግሎት ለመተካት ይመስላል፣ እንደ እግዚአብሔር ፍቃድ ማወቂያ መንገድ። ዑሪምና ቱሚም ከእግዚአብሔር ቃል አቀባይ በሆነ የቃል መልእክት ተሻሽለዋል። የነቢይ አገልግሎት ደግሞ በእስራኤል ያለፈ ይመስላል፣ ከሚልክያስ በኋላ። እሱም እስከ 400 ዓመት ድረስ ዳግም አልተከሰተም፣ በመጥምቁ ዮሐንስ። የአዲስ ኪዳን የ “ትንቢት” ስጦታ ከብሉይ ኪዳን ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ግልጽ አይደለም። የአዲስ ኪዳን ነቢያት (ሐዋ.11:27-28፤ 13:1፤ 14:29፣32፣37፤ 15:32፤ I ቆሮ. 12:10፣28-29፤ ኤፌ. 4:11) በቅዱስ ቃሉ ላይ የአዲስ መገለጥ ገላጮች አይደሉም፣ ነገር ግን መጻዒውን ወይም የወደፊቱን የእግዚአብሔርን ፍቃድ በኪዳን ሁኔታዎች የሚገልጹ ናቸው።

መ. ትንቢት በማያካትት መልኩ ወይም በቀዳሚነት በባሕርዩ ትንበያዊ <u>አይደለም</u>። ትንበያ የእሱን አገልግሎት እና የእሱን መልእክት ማስረገጫ መንገድ ነው፣ ነገር ግን መታወስ የሚኖርበት “ከ2% ያነሰው የብኪ ትንቢት መሢሐዊ መሆኑን ነው። ከ5% ያነሰው በተለይ የአዲስ ኪዳን ዘመንን ይገልጻል። ከ1% ያነሰው ወደፊት ስለሚመጡት ሁነቶች ያተኩራል።” (Fee & Stuart, *How to Read the Bible For All Its Worth*, p. 166)፡፡

ሠ. ነቢያት እግዚአብሔርን ለሕዝቡ ሲወክሉ፣ ካህናት ደግሞ ሕዝቡን ለእግዚአብሔር ይወክላሉ። ይህ አጠቃላይ መግለጫ ነው። የተለዩዎች አሉ፣ ዕንባቆምን የመሰሉ፣ እሱም ለእግዚአብሔር ጥያቄ የሚያቀርብ።

ረ. ነቢያትን ለመረዳት አዳጋች ከሚሆኑት ምክንያቶች አንዱ፣ መጻሕፍታቸው እንዴት እንደተዋቀሩ አለማወቃችን ነው። እነርሱ የታሪክ ቅደም ተከተላዊ አይደሉም። እነርሱ ጭብጣዊ ይመስላሉ፣ ነገር ግን አንዱ በሚጠብቀው መንገድ ዘወትር አይሆኑም። ዘወትርም ግልጽ የሆነ ታሪካዊ መቼት፣ የጊዜ ቅምብብ፣ ወይም በንግሮቹ /ትንቢቶቹ/ መካከል ግልጽ ምድብ  አይኖርም። እነዚህ መጻሕፍት አስቸጋሪነታቸው፡ (1) በአንድ ቁጭታ መነበብ አለመቻላቸው፤ (2) በየርዕሱ የፍሬ ሐሳብ ዝርዝር ማውጣት አለመቻሉ፤ እና (3) በያንዳንዱ ንግር/ትንቢት ማዕከላዊውን እውነት ወይም የደራሲውን ዋነኛ ሐሳብ ማስረገጥ አለመቻል ናቸው።

IV. የትንቢት ባሕርያት/ጠባያት

ሀ. በብሉይ ኪዳን “የነቢይ” እና “ትንቢት” ጽንሰ-ሐሳብ እየዳበረ የመጣ ይመስላል። በድሮው እስራኤል፣ የነቢያት ኅብረት እየዳበረ መጥቷል፣ በጠንካራ ማራኪ መሪ የተመራ፣ እንደ ኤልያስ ወይም ኤልሳዕ ባሉት። “የነቢያት ልጆች” የሚለው ሐረግ አንዳንዴ ቡድኑን ለመጥራት ጥቅም ላይ ውሏል (II ነገ. 2)። ነቢያት በጽኑ ስሜት (መንፈስ) የመወሰድ ባሕርይ አላቸው (I ሳሙ. 10:10-13፤ 19:18-24)።

ለ. ቢሆንም፣ ይህ ዘመን በፍጥነት ወደ ግለሰባዊ ነቢያት ተሸጋገረ። እነዚያ ነቢያት ነበሩ (እውነተኞቹም ሆኑ ሐሰተኞቹ) ከንጉሡ ጋር የሚታወቁ፣ በቤተ መንግሥትም የሚኖሩ (ጋድ፣ ናታን)። ደግሞም፣ ነጻ የሆኑ ነበሩ፣ አንዳንድ ጊዜ ባጠቃላይ ከእስራኤል ኅብረተሰብ አቋም (ሁኔታ) ጋር ያልተያያዙ (አሞጽ)። እነርሱ ወንድም ሴትም ናቸው (II ነገሥ. 22:14።)

ሐ. ነቢይ ዘወትር መጻዒውን የሚገልጽ ነው፣ በሰው አፋጣኝ ምላሽ ላይ የሆነ። የነቢይ ተግባር ዘወትር የነበረው እግዚአብሔር ለፍጥረቱ የነበረው የማይታጠፍ ዕቅድ ነው፣ ይኸውም በሰዎች ምላሽ ተጽዕኖ የማያድርበት። ይህ ሁለንተናዊ የመዳረሻዊ ዕቅድ የተለየ ነበር፣ በጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ ነቢያት መካከል። ትንቢት እና የኪዳን ታማኝነት መንታ ተተኳሪዎች ናቸው፣ የትንቢታዊ መልዕክቶች (ፊ እና ስቱዋርት፣ ገጽ 150)። ይህም የሚያመለክተው ነቢያት በቀዳሚነት ኅብራዊ ትኩረት እንዳላቸው ነው። እነርሱ ዘወትር፣ ነገር ግን የማያካትት ባልሆነ መልኩ፣ ለሕዝቡ ይገልጻሉ።

መ. አብዛኛው ትንቢታዊ ነገር በቃል የሚቀርብ ነበር። ኋላ ላይ ነው በጭብጥ መልኩ፣ በቅደም ተከተል (ታሪክ) ወይም በሌሎች የቅርብ ምስራቅ ሥነ-ጽሑፍ ፈርጆች የተደባለቀው፣ እሱም ለእኛ የማይገኝ። እሱ ቃላዊ ስለነበር እንደ ዝርው ጽሑፍ የተዋቀረ አይደለም። ይህም መጻሕፍቱን ለማንበብ በውል (ቀጥ ብሎ) ለማንበብ አስቸጋሪ አድርጎታል፣ እንዲሁም ለመረዳትም አስቸጋሪ አድርጎታል፣ ያለ ተለየ ታሪካዊ መቼት።

ሠ. ነቢያት በርከት ያሉ ፈርጆችን ይጠቀማሉ፣ መልእክታቸውን ለማስተላለፍ፡

1. የፍርድ ቤት ትዕይንት - እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ ፍርድ ቤት ይወስዳል፣ እሱም ዘወትር የፍቺ ጉዳይ ነው፣ ያህዌ ሚስቱን ይንቃል/ይተዋል (እስራኤል) ታማኝ ስላለመሆኗ (ሆሴዕ 4፤ ሚክያስ 6)።
2. የቀብር ሙሾ - የዚህ ዓይነቱ መልእክት እና የባሕርያቱ ልዩ ዜማ “ወዮ” እሱን ራቅ አድርጎ ያስቀምጠዋል፣ እንደ ልዩ መልክ (ኢሳይያስ 5፤ ዕንባቆም 2)።
3. የኪዳን ባርኮት መግለጫ - የኪዳን ሁኔታዊ ጠባይ አጽንዖት ተሰጥቶታል፣ እንዲሁም የሚያስከትለው ውጤት፣ በሁለቱም በአዎንታዊና በአሉታዊ፣ ለወደፊት ተለይተው ተቀምጠዋል (ዘዳ. 27-28)።

V. መጽሐፍ ቅዱሳዊ መለያዎች ለእውነተኛ ነቢይ ማረጋገጫ

ሀ. ዘዳግም 13፡1-5 (ትንበያዎች/ምልክቶች)

ለ. ዘዳግም 18፡9-22 (ሐሰተኛ ነቢያት/እውነተኛ ነቢያት)

ሐ. ማቴዎስ 7 (የሕይወት ስልት)

መ. 1 ዮሐንስ 4፡1-6 (ዶክትሪናዊ ትኩረት)

ሠ. ወንዶችም ሆነ ሴቶች ለነቢይነት ወይም ለነቢይትነት ይጠራሉ ይመደባሉም
1. ማርያም - ዘጸ. 15
2. ዲቦራ - መሳ. 4፡4-6
3. ሕልዳና - II ነገ. 22:14-20፤ II ዜና. 34:22-28

ረ. በአካባቢው ባህል ነቢያት የሚለዩት በመለኮታዊነት መልኩ ነው። በእስራኤል እሱ የነበረው፡
1. ሥነ-መለኮታዊ ፍተሻ - የያህዌ ስም
2. ታሪካዊ ፍተሻ - ትክክለኛ ትንበያዎች።

VI. ትንቢትን ለመተርጎም የሚያግዝ መመሪያ

ሀ. የዋነኛውን ነቢይ (አዘጋጅ) ሐሳብ ፈልግ፣ የእያንዳንዱን ትንበያ/ንግር ታሪካዊ መቼትና ጽሑፋዊ ዐውደ-ጽሑፍ በመመዝገብ/በመገንዘብ። እሱም ዘወትር የሚያካትተው እስራኤል የሙሴን ኪዳን መስበሩን ነው፣ በሆነ መንገድ።

ለ. ሙሉውን ትንበያ አንብበህ ተርጉም፣ ክፋዩን ብቻ ሳይሆን፤ በይዘት መልክ የፍሬ ሐሳብ ዝርዝሩን አውጣ። እሱም ከአካባቢው ትንበያዎች ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ተመልከት። የሙሉውን መጽሐፍ የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር ለማውጣት ሞክር።

ሐ. የምንባቡን ጥሬአዊ ትርጓሜ አስብ፣ የሆነ ነገር ራሱ በጽሑፉ ላይ ለዘይቤአዊ አጠቃቀም እስካላመለከተህ ድረስ፤ ከዚያም ዘይቤአዊውን ቋንቋ በዝርው አስቀምጠው።

መ. ተምሳሌታዊ ድርጊቶችን ከታሪካዊ መቼትና ትይዩ ምንባቦች አኳያ ተንትን። ለማስታወስ ርግጠኛ ሁን፣ ይህ ጥንታዊ ቅርብ ምስራቃዊ ሥነ-ጽሑፍ፣ ምዕራባዊ ወይም ዘመናዊ ሥነ-ጽሑፍ አለመሆኑን።

ሠ. ትንበያዎችን በጥንቃቄ ተመልከት/ያዝ፡
1. እነርሱ በማያካትት መልኩ ለደራሲው ቀን ናቸውን?
2. እነርሱ በእስራኤል ታሪክ በጊዜው ተፈጽመዋልን?
3. እነርሱ ገና የወደፊት ሁነት ናቸውን?
4. እነርሱ ያለፈው ዘመን ተፈጻሚነትና ገና የወደፊትም ተፈጻሚነት አላቸውን?
5. የመጽሐፍ ቅዱስ ደራስያን ለምላሽህ እንዲረዱህ ፍቀድ፣ ዘመናዊዎቹ ደራስያን ሳይሆኑ።

ረ. ልዩ አትኩሮቶች
1. ትንቢት የሚለየው/የሚታወቀው በሁኔታዊ ምላሽ ነውን?
2. ትንቢቱ የሚመለከተው በርግጠኝነት ይታወቃልን (እናም ለምን)?
3. ለሁለቱም መጽሐፍ ቅዱሳዊ እና/ወይም ታሪካዊ፣ ድርብ አፈጻጸም የመሆን ዕድሎች አሉ ወይ?
4. የአኪ ደራስያን በተመስጦ ሆነው፣ መሢሑን ለመመልከት ችለዋል፣ በብኪ በብዙ ስፍራዎች፣ ያም ለእኛ ግልጽ ያልሆነ። እነርሱ የቃሉን አጠቃላይ ምድብ ወይም የቃላት ጨዋታ (ቅይይር)ተጠቅመው ይመስላል። እኛ ተመስጧዊ እስካልሆንን ድረስ አገባቡን (አያያዙን) ለእነርሱ ልንተውላቸው ይገባል።

VII. አጋዥ መጻሕፍት


ሀ. *A Guide to Biblical Prophecy* by Carl E. Armerding and W. Ward Gasque

ለ. *How to Read the Bible for All It Is Worth* by Gordon Fee and Douglas Stuart

ሐ. *My Servants the Prophets* by Edward J. Young

መ. *The Expositor's Bible Commentary*, vol. 6 "Isaiah - Ezekiel," Zondervan

ሠ. *The Prophecies of Isaiah* by J. A. Alexander, 1976, Zondervan

ረ. *Exposition of Isaiah* by H. C. Leupold, 1971, Baker

ሰ. *A Study Guide Commentary*, "Isaiah" by D. David Garland, 1978, Zondervan

# መግቢያ ለትንቢተ ኢሳይያስ

I. የመግቢያ መግለጫ

ሀ. ኢሳይያስ በተደጋጋሚ ተጠቅሷል፣ ብኪ ላይ፣ ከሌላ ነቢይ ይልቅ (ከ411 ጊዜ በላይ)። የእርሱ መልእክት የነበረው፡
1. አንድ አምላክ
2. አንድ ዓለም
3. አንድ እምነት

ለ. ኢሳይያስ አስደናቂ መሢሐዊ ነው፡
1. ልዩ ልጆች፣ ምዕራፍ 7-14
2. ያገልጋይ መዝሙሮች፣ ምዕራፍ 42:1-9፤ 49:1-7፤ 50:4-11፤ 52:13-53:12፣
3. ቀጣዩ መሢሐዊ መንግሥት (አዲስ ዘመን)፣ ምዕራፍ 56-66

ሐ. E. J. Young, in *An Introduction to the Old Testament)* እንዳለው፡
1. "የኢሳይያስ መጽሐፍ በቀጥታ የሚታየው ከብኪ ትንቢቶች ታላቁ እንደሆነ ነው" ገጽ 168።
2. "ከእስራኤል ነቢያት ሁሉ፣ ኢሳይያስ የእግዚአብሔርን ሐሳብና ለዘመኑ ያለውን ዕቅድ እጅግ በተጠናቀቀ መልኩ ተገንዝቦታል" ገጽ 171
3. "በመንፈሳዊ ውስጠት እሱ ከብኪ ሁሉ ሊሻሻል/ሊበለጥ የማይችል ነው" ገጽ 172

II. የመጽሐፉ ስም

ሀ. መጽሐፉ የተሰየመው የትንቢቱን ቃል አቀባይ ተከትሎ ነው

ለ. የስሙ ፍቺ "የያህዌ ማዳን" ወይም "ያህዌ ያድናል" ማለት ነው። የዕብራይስጥ ስሞች በ "ኢያህ" የሚጨርሱ የያህዌ አጽኅሮተ-ቃል ናቸው፣ ልክ እንደ እንግሊዝኛ ስሞች በ "ጄ" እና በአናባቢ እንደሚጀምሩ፣ ለምሳሌ ጆሽዋ/ኢያሱ እና ጆኤል/ኢዩኤል።

III. ቅዱስ ቃልነቱ (ካኖናይዜሽን)

ሀ. ይህ ከኋለኞቹ ነቢያት አራት ጥቅሎች የመጀመሪያው ነው፡

1. ኢሳይያስ
2. ኤርምያስ
3. ሕዝቅኤል
4. አስራ ሁለቱ (መለስተኛ ነቢያት)

ለ. እሱም ቀደም ብሎ ሙሉ ለሙሉ በእስራኤል ቅዱስ ጽሑፎች ተቀባይነት አግኝቷል።

IV. ዘውግ

ሀ. የኢሳይያስ ጽሑፋዊ ክህሎት ከሁሉም የብኪ ነቢያት ይልቃል። የእሱ የቃላት ጨዋታ እና ቅኔ አስገራሚና ስሜት የሚያጭሩ ናቸው። መጽሐፉ ባብዛኛው ቅኔ ነው።

ለ. ኢሳይያስን በአንድ ጊዜ ቁጭ ብሎ ማንበብ አዳጋች ነው። የመጽሐፉን የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር ለማውጣት አስቸጋሪ ነው። ይህም የሆነው ኢሳይያስ ሰባኪ ስለ ሆነ ነው፣ ደራሲ ወይም አዘጋጅ ሳይሆን። የእሱ መጽሐፍ የእሱን የቃል መልእክቶች መዝግቦታል። እነርሱም አንዳንዴ አንድ ላይ ተያይዘዋል፡
1. በጭብጥ፣
2. በታሪክ/ሁነት ቅደም ተከተል፣
3. በጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ ባህላዊ አገባቦች፣ ይኸውም ከእኛ እጅግ የተለዩ የሆኑ።

V. ደራሲነት

ሀ. የአይሁድ የደራሲነት አተያይ
1. የታልሙዱ ባባ ባትራ 15ሀ የሚለው ሕዝቅያስና የእርሱ ሰዎች ጽፈውታል (ማለትም፣ አዘጋጅተውታል ወይም አጠናቅረውታል) ኢሳይያስን፣ ምሳሌን፣ መክብብን እና መኃልየ መኃልይን። ይህ የሚያመለክተው ሙሉው መጽሐፍ ከነቢዩ መሆኑን ነው።
2. ቤን ሲራክ፣ "መጽሐፈ-ጥበብ 49:17-25፣ 185 ቅ.ል.ክ አካባቢ የተጻፈ፣ የሚለው፣ "የኢሳይያስ ልጅ አሞጽ፣" መጽሐፉን እንደጻፈው ነው (1:1፤ 12:1፤ 13:1)።
3. II ዜና መዋዕል 32:32 የኢሳይያስን ራዕይ ያስረግጣል እንዲሁም ከነገሥታት ጋር ያለውን ትይዩነት (II ነገ. 18:19-20:19።)
   ሀ. በኢየሩሳሌም ካለ ባለጠጋ ምሁር ቤተሰብ፣ ይልቁንም የንጉሥ ዖዝያን የአጎት/አክስት ልጅ።
      (1) አንዳንድ ማስረጃዎች እንደሚያመለክቱት "ኢያህ፣" እሱም የያህዌ ምኅጻረ-ቃል የሆነ፣ ከሞላጎደል በማያካትት መልኩ በይሁዳ ንጉሣዊ አገዛዝ ቤተሰብ ዘንድ የተለመደ መጠሪያ ሆኖ ነበር።
      (2) ኢሳይያስ ከነጉሡ ጋር ያለው ቀረቤታ ደግሞ የእሱን ቤተሰባዊ ግንኙነት መኖር ያጠናክራል።
      (3) ታልሙድ፣ "ሜግ." 10ለ
   ለ. ነቢይቱን አግብቷል (8፡3)
      (1) የመጀመሪያ ልጅ፣ "ሼር-ጃሹብ፣" ፍችውም "ቅሬታው ይመለሳል"
      (2) ሁለተኛ ልጅ፣ "ማኸር-ሻላል-ሃሽ-ባዝ" (8፡3) ፍችውም "ምርኮ ፈጠነ፣ ብዝበዛ ቸኮለ"

ሐ. ኢሳይያስ ረዥም የትንቢት አገልግሎት አለው፣ ከብኪ ነቢያት ይልቅ። እሱ በይሁዳ የእግዚአብሔር ቃል አቀባይ ነበር፣ ከኢዮአታም ጊዜ አንሥቶ (742-735 ቅ.ል.ክ) እስከ ሕዝቅያስ ድረስ (715-687 ቅ.ል.ክ) እንዲሁም በምናሴ አገዛዝም የመኖር ዕድል አለው (687-642 ቅ.ል.ክ)፤ ምናሴ የጋራ ገዥ ሊሆን ይችላል 696 ቅ.ል.ክ

መ. II ዜና. 26:22 ኢሳይያስን የሚያመለክት ከሆነ እንግዲያውስ እሱ የንጉሥ ዜና መዋዕል ይፋዊ ጸሐፊ እና ጠባቂ (መዝገብ ያዥ) ነው ማለት ነው።

ሠ. ወጎች እንደሚሉት እሱ በምናሴ አገዛዝ በመጋዝ ለሁለት ተሰንጥቋል።

4. ሞሰስ ቤን ሳሙኤል ኢብን ጌካቲላ፣ 110 ዓ.ም አካባቢ፣ የሚለው ምዕራፍ 1-39 የኢሳይያስ ነው፣ ነገር ግን ምዕራፍ 40-66 የተጻፈው በሁለተኛው የመቅደስ ዘመን ነው (በፋርስ ዘመን፣ 538-430 ቅ.ል.ክ)
5. ኢብን ዕዝራ (1092-1167) የጌካቲላን ምሪት ተከትሎ ምዕራፍ 40-66 የኢሳይያስ መሆኑን ክዷል (አልተቀበለም)።

ለ. ዘመናዊዎቹ ሊቃውንት ስለ ደራሲው ያላቸው አተያይ

1. የተሻለ ታሪካዊ ጭምቅ-ሐሳብ ይገኛል፣ R. K. Harrison's *Introduction to the Old Testament*, Eerdmans, 196) *የብሉይ ኪዳን መግቢያ ላይ*፣ ኤርድማንስ፣ 1969።
   የተሻለ ማብራሪያ፣ ሁለት ደራስያን ሊኖሩ የሚችሉበት ቴክኒካዊ ምክንያቶች ማስረገጫ (S. R. Drivers' *Introduction to the Literature of the Old Testament*, reprint 1972) ላይ ሊገኝ ይችላል።
2. ምንም ዓይነት የዕብራይስጥ ወይም የግሪክ (LXX) ፈጽሞ አልተገኙም፣ በምዕራፍ 1-39 እና 40-66 መካከል ያለውን ክፍፍል የሚያመለክቱ።
   ሀ. በምዕራፍ 33 መጨረሻ ላይ የሁለት መስመር ክፍተት አለ፣ በሙት ባሕር ጥቅሎች ላይ። ይህ የሚያመለክተው በዚህ ነጥብ ላይ ክፍፍል መኖሩን ነው፣ ምዕራፍ 39 ላይ ሳይሆን።
   ለ. ትይዩ አወቃቀር ያለ ይመስላል በ1-33 እና 34-66 መካከል። ይህ ድርብ አወቃቀር፣ በደራሲው በገዛ ራሱ ቀን ላይ የተመሠረተ እና ከዚያም በወደፊቱ፣ በዕብራይስጥ ነቢያት ዘንድ የተለመደ ነው (ሕዝቅኤል፣ ዳንኤል እና ዘካርያስ)።
3. ዘመናዊው አስተምህሮት ሙሉ ስምምነት ላይ አልደረሰም፣ ምን ያህል ደራስያን እንደሆኑ ወይም የቱጋ መጽሐፉን መከፋፈል እንደሚቻል።

ሐ. አንዳንድ ምክንያቶች ስለ ኢሳይያስ ኅብር/አንድነት

1. ሃያ አምስት ቃላት በሁለቱም በኢሳይያስ ክፍሎች ይገኛሉ፣ እነርሱም በብኪ በየትኛውም ስፍራ የማይገኙ (NIV፣ *መግቢያ* ለኢሳይያስ፣ ገጽ 1014)።
2. "የእስራኤል ቅዱስ" የሚለው መጠሪያ 13 ጊዜ ምዕራፍ 1-39 ላይ እና 14 ጊዜ ምዕራፍ 40-66 ላይ ሲገኝ በቀሪዎቹ የብኪ መጻሕፍት ሁሉ ላይ ስድስት ጊዜ ብቻ ይገኛል።
3. ኢየሱስ፣ ዮሐ. 12፡38፣40 ላይ ከሁለቱም ከኢሳ. 53፡1 እና 6፡10 ላይ ጠቅሶ፣ የሁለቱንም ባለቤትነት ለኢሳይያስ ሰጥቷል።
4. ከኢሳ. 40-66 የተወሰዱ ምንባቦች፣ ባለቤትነቱ ለኢሳይያስ ተሰጥቷል፣ ማቴ.3:3፤ 8:17፤ 12:17፤ ሉቃ. 3:4፤ 4:17፤ ዮሐ. 1:23፤ ሐዋ. 8:28 እና ሮሜ. 10:16-20 ላይ
5. ምንም ዓይነት ጽሑፋዊ ማስረጃ የለም፣ መጽሐፉ ምዕራፍ 39 ላይ ስለመከፈሉ (ኤምቲ ወይም ዲኤስኤስ)።
6. ከታሪክ አኳያ ምንም የተጠቀሰ የለም፣ የታላቁ ነቢይ (ዲድራ-አይዛያ/ኢሳይያስ) በ6ኛ ክፍለ-ዘመን። አር.ኬ. ሃሪሰን፣ *መግቢያ ለብሉይ ኪዳን* ላይ፣(R. K. Harrison, in Introduction to the Old Testament,) ስለዚህ ርዕሰ-ጉዳይ አክሎም፣
   "ጽሑፋዊ ስልቱን በተመለከተ ክርክሮች አጠቃላይ ተቀባይነቱ ላይ እጅግ ተካሂደዋል፣ በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ-ዘመን ማጠናቀቂያ ላይ፣ ነገር ግን በጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ ቋንቋዎች ሰፊ ግንዛቤ አኳያ እነርሱ አሁን እናሳ ጠቀሜታዊ አቋም እንዳላቸው ይታሰባል። የስልታዊ ግንዛቤዎች/አቋሞች እጅግ ሕሊናዊ መሆን፣ ለግራፍ-ዌልሃውሰን ጽሑፋዊ ትንተና ንድፈ-ሐሳብ አራማጆች ጥያቄ ለማቅረብ ረድቷል፣ እሱም የሚለው በተመለከተው ነገር ላይ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ደራሲው በተጻፈ የሚደረግ ጥልቅ ምርመራ፣ በእያንዳንዱ ክፍል እና በአጠቃላይ አካሉ መካካል ያለውን ኅብር በተመለከተ፣ ከዚያም የዚያን ዋነኛ አካል ክፍሎች የእሱ እንዳልሆኑ መካድ አይቻልም፣ በእያንዳንዱ ምዕራፍ ላይ ያሉት ጽሑፋዊ መልኩና ቃላቱ መንታዊ (አንድ ዓይነት) እንዲሆኑ በማሰብ። ባጠቃላይ በቀደምት መርማሪዎች ዘንድ አልተከሰተም፣ ማለትም የአንድን ጥንታዊ ደራሲ ስልት ጽንሰ-ሐሳብ ለማካሄድ፣ በጥንቃቄ እንደተሞላ ምርመራ፣ ስለ እሱ የተጻፉት ነገሮች ላይ ሁሉ፣ በጊዜ ቅደም ተከተል የተቀመጡትን የዋናውን አካል ክፍሎች መካድ የሚቻለውና ተቀባይነት ሊኖረው የሚችለው ግን በአንዳንድ ውጫዊ ቁጥጥር ባለው ጥብቅ ምርምር ብቻ ነው።" ገጽ 776

መ. አንዳንድ ምክንያቶች ለኢሳይያስ ብዝኃ/ድርብ ደራሲነት።

1. ከምዕራፍ 40-66 "ኢሳይያስ" የሚለው ስም አልተጠቀሰም።
2. ምዕራፍ 40-66 ከኢሳይያስ ታሪካዊ መቼት ጋር አይገጥምም።
3. ኢሳይያስ ማጣቀሻዎች ላይ መደባለቅ ያለ ይመስላል፡
   ሀ. የአሦር ወረራ፣ ግዞት እና የእነርሱ ፍርድ
   ለ. የባቢሎን ወረራ፣ ግዞት እና የእነርሱ ፍርድ።
4. ግልጽ የሆኑ አንዳንድ ምክንያቶች አሉ፣ የብዝኃ/ድርብ ደራሲነትን ንድፈ-ሐሳብ ለመንደፍ፡
   ሀ. የታሪካዊ መቼቱ ለውጥ
      (1) ቅድመ-ወረራ ይሁዳ፣ 1-39
      (2) ግዞት፣ 40-55
      (3) ድኅረ-ግዞት ይሁዳ፣ 56-66
      (4) ኢሳይያስ 1-39 ላይ መቅደሱ ፈጽሞ አልፈረሰም፣ 40-66 ላይ ባጠቃላይ ቀደም ብሎ ፈርሷል። ደራሲው ግዞተኛ ይመስላል።
   ለ. ቃላት ተቀይረዋል፣ የእግዚአብሔርን ምርጥ ለማግለጽ፡
      (1) መሢሐዊ ሕፃን
      (2) መከራ የሚቀበል አገልጋይ
      (3) እስራኤል እንደ፡

(ሀ) ሚስት (50፡1)
(ለ) የያህዌ አገልጋዮች (54፡17)

5. ዘመናዊ ወግ-አጥባቂ ሊቃውንት፡
ሀ. E. J. Young's *መግለጫ*፣ ስለ 56-66 የሰጠው ኢጋኸር ነው፣ "ሌላው ይሁንታ የሚሆነው መንፈሳዊ- መር የሆነ፣ አዘጋጅ የሰበሰበው ትንቢት፣ ከተለያዩ ነቢያት፣ ከኢሳይያስ አስተምህሮት፣ በዚህ ምድብ ዙሪያ ያሉ መሠረታዊ ጭብጦች፡፡" ገጽ 188
ለ. G. R. K. Harrison's *መግለጫ*፣ "የአሁኑ ጸሐፊ የያዘው አመለካከት፣ ኢሳይያስ፣ እንደ አብዛኞቹ በተጨባጭ እንዳሉ ትንቢታዊ ጽሑፎች፣ በቃላት እንደሚተላለፉ ስብስቦችን ይወክላሉ፣ በተለያየ ጊዜ የተሰጡ፣ እና ስለዚህ ሥራው የተለያየ አያያዝ ይገጥመዋል፣ አንድ ላይ ያለ ችግር ከሚሄዱት ከዋነኞቹ የብሉይ ኪዳን ትንበያዎች ጋር፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ፣ መገንዘብ ጠቃሚ የሚሆነው በተለያዩ የስልት ወይም ሥነ-ጽሑፋዊ አገላለጾች ላይ መሠረት በማድረግ የሚካሄዱት ክርክሮች በዚህ አግባብ ወዲያውኑ ይበላሻሉ፣ ስብስቡ በተገቢው መልኩ አጠቃላዩን የደራሲውን ስልት እንዲወክል ተወስዶ፣ በእርሱ የፈጠራ ተግባር የተለያየ ጊዜን እየወከለ እያለ እንኳ፡፡ ሥራውን ስብስብ ነው ብሎ ለማረጋገጥ የሚደረገው ገለጻ፣ በእዛ ነገር በተሻለ መልኩ በትንቢቱ መክፈቻ ቁጥር (ቃል) ላይ ጎልቶ ይታያል፣ ይኸውም ለሥራው እንደ ርዕስ የሚቆጠር፣ እንዲሁም ስለ መገለጥ ሥራው ለይቶ የሚናገር፣ ማለትም ኢሳይያስ የአሞጽ ልጅ በራዕይ የተቀበለው፣ ይሁዳ እና ኢየሩሳሌምን በተመለከተ፣ በዖዝያን፣ ኢዮአታም፣ አካዝ፣ እና ሕዝቅያስ ዘመን፡፡ ከሁሉ ስብስቦች ተገቢ በሆነ መልኩ ማስረጃ የሚሆነው መጽሐፉ የያዘው የተመረጠውን የተገኘውን ትንቢታዊ ቃል እና ስብከቶች ብቻ ነው፣ እናም እጅግ ግምታዊ ቢሆን ነው፣ ኢሳይያስ አሁን ከተረፈው (ከተገኘው) የበለጠ ነገር ጽፏል ብሎ ለመቀበል፡፡ የትንቢቱ ጠባይ፣ እንደ ስብስብ ቀጥሎ ተጠቁሟል፣ ኢሳ. 2፡1 እና 13፡1 ላይ የጎዳግ ማስታወሻ፣ ይኸውም ቀደም ብሎ የተሰበሰበ የቃል ትንቢትን የሚወክል ወይም የሚያመለክት፡፡" ገጽ 780

6. የምዕራፍ 40-66 ጽሑፋዊ ስልት ከምዕራፍ 1-39 ይለያል፡፡

ሠ. ስለ ደራሲው የማጠቃለያ አስተያየት
1. መልካሞቹ ሊቃውንት አለመግባባታቸውን ቀጥለዋል፣ የብኪ መጽሐፋችን የሆነው ኢሳይያስ ወደ አሁኑ ቅርጽ (መልክ) እንዴት እንደመጣ (ዲኤስኤስ እና ኤምቲ)፡፡ ዋነኛው አጽንዖት መቀመጥ የሚኖርበት በእርሱ ተመስጧዊነት እና ታማኝነት ላይ ነው፣ የእግዚአብሔርን ባሕርይና ዓላማ በመግለጥ ረገድ፡፡
2. ማንኛውንም ዓይነት ቅድመ-ግምት መቀበል አይኖርብንም፣ እግዚአብሔር በኢሳይያስ በኩል ያደረገውን የታመነ መገለጥ የሚክድ፡፡ ይህም ደግሞ የሚያካትተው የትንቢታዊ ቃልን ቀድሞ አለመቀበልን ጭምር ነው፣ እንዲሁም ብኪን በማያካትት መልኩ ሰዋዊ፣ የዘመኑ፣ ታሪካዊ ጽሑፍ ዝቅ የሚያደርገውን፡፡

## VI. ጊዜው

ሀ. ኢሳይያስ የ8ኛ ክፍለ-ዘመን ነቢያት ክፍል ነው
1. ዮናስ፣ አሞጽ እና ሆሴዕ በሰሜን በኩል፣ በኢዮርብአም II አገዛዝ ዘመን (786-640 ቅ.ል.ክ)
2. ኢሳይያስ እና ሚክያስ በደቡብ

ለ. እሱም የተወለደው በ760ዎቹ ቅ.ል.ክ ሲሆን፣ ለትንቢት አገልግሎት የተጠራው ደግሞ በ742 ቅ.ል.ክ አካባቢ ነው፣ ዖዝያን በሞተበት ዓመት (6፡1)፡፡ ዖዝያን ደግሞ አዛርያ ተብሎ ይጠራል (783-742 ቅ.ል.ክ)፡፡

ሐ. ኢሳይያስ ረጅም አገልግሎት አለው፣ ከዖዝያን የመዝጊያ ዓመታት (783-742 ቅ.ል.ክ) ኢዮአታም (742-735 ቅ.ል.ክ)፣ አካዝ (735-715 ቅ.ል.ክ)፣ ሕዝቅያስንም አካቶ (715-687 ቅ.ል.ክ) ምናሴንም ሊሆን ይችላል (687-642 ቅ.ል.ክ)፡፡

መ. አር. ኬ. ሃሪሰን (R. K Harrison) እንደሚያስቀምጠው መጽሐፉ የነቢይ ጽሑፍና ስብከት ስብስብ ነው፣ የብዙ ዓመታት፣ በርከት ባሉ የይሁዳ ነገሥታት፡፡ እሱም በመጨረሻ የተጠናቀረውና የተዘጋጀው ከነቢዩ ሞት በኋላ ነው፣ በ630 ቅ.ል.ክ አካባቢ፡፡

## VII. ታሪካዊ መቼት

ሀ. የስምንተኛ ክፍለ-ዘመን ነቢያት
1. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነገሮች የሚገኙት፡

| | |
|---|---|
| ሀ. II ነገሥት 14፡3-17፡6 | ሠ. ሆሴዕ |
| ለ. II ዜና መዋዕል 25-28 | ረ. ኢሳይያስ |
| ሐ. አሞጽ | ሰ. ሚክያስ |
| መ. ዮናስ | |

2. ቀላል የሆነው ማጠቃለያ፣ የአመንዝራነት መግለጫ፣ በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል የሆነው ሆሴዕ ላይ ሊታይ ይችላል፡
ሀ. 2፡16፣ "ዳግመኛም በኣሌ ብለሽ አትጠሪኝም"
ለ. 4፡12-13፣ "...ሴቶች ልጆቻቸው ይገለሙታሉ..."
ሐ. 4፡17፣ "ኤፍሬም ከጣዖታት ጋር ተጋጠመ፤ ተወው"
መ. 13፡2 "ወንዶቹ እምቦሳውን ሳሙ!" (አምልኮታዊ መሳለም)
3. ማኅበራዊ መቼት
ሀ. ጊዜው የኢኮኖሚያዊ ብልጽግናና ወታደራዊ መስፋፋት ነበር፣ ለእስራኤልም ሆነ ለይሁዳ፡፡ ሆኖም፣ ይህ ብልጽግና ጠቀሜታው ለሀብታሙ መደብ ብቻ ነበር፡፡ ደሀው ይበዘበዝል ይጨቆናል፡፡ እሱም ከሞላ ጎደል "ብር እና ጠመንጃ" ተጨማሪ ጣዖታት የነበሩበት ጊዜ ይመስላል!

ለ. ማኅበራዊ ዋስትናና ንብረት፣ የእስራኤልም እና የይሁዳ በርከት ካሉ መንሥኤዎች ጋር ይዛመዳል፡
(1) ረጅምና የበለጸገ የኢዮርብአም II አገዛዝ (786-746 ቅ.ል.ክ) በሰሜን እና የዖዝያን (783-742 ቅ.ል.ክ) በደቡብ፡፡
(2) አሦራውያን ሶርያን ድል ማድረጋቸው፣ በአዳድ-ኒራሪ III በ802 ቅ.ል.ክ
(3) በእስራኤልና በይሁዳ መካከል ግጭት አለመኖር፡፡

(4) ከሰሜን ወደ ደቡብ የሚዘልቁት የንግድ መስመሮች ላይ የሚጣለው ግብርና ብዝበዛ (ሀብት ማሰባሰብ)፣ በፍልስጥኤም የመሬት (የብስ) ድልድይ ላይ፣ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ማምጣት ችሏል፣ ሀብታሙ መደብ አባካኝ እንዲሆን አድርጓል።

ሐ. "የሰማርያ መነጠል" ይኸውም በኢዮርብአም II ያገዛዝ ዘመን የሆነ፣ የሰሎሞንን የመሰለ አስተዳደራዊ አደረጃጀት እንዲኖር ያደረገ ይመስላል። ይህም "ባላቸው" እና "በሌላቸው" (ሀብታምና ደሀ) መካከል ያለውን ሰፊ ክፍተት የሚያረጋግጥ ይመስላል።

መ. የባለጠጎች ታማኝ አለመሆን አሞጽ ላይ በግልጽ ተኮንኗል፣ እሱም "የማኅበራዊ ፍትሕ ነቢይ" የሚባለው። የዳኝነት ሥርዓቱ ጉቦኛ መሆን እና የግብይት ሚዛኖች ሀሰተኛ መሆን ሁለት ግልጽ የሆኑ የግፍ ምሳሌዎች ናቸው፣ በሁለቱም በእስራኤልም ሆነ በይሁዳ በአጠቃላይ የተለመዱ።

4. ሃይማኖታዊ መቼት

ሀ. በርካታ ውጫዊ ሃይማኖታዊ ድርጊቶች የሚፈጸሙበት፣ ነገር ግን እጅግ ያነሰ እውነተኛ እምነት የነበረበት ጊዜ ነበር። የከነአን የመራባት የአምልኮ ሥርዓት ከእስራኤል ሃይማኖት ጋር የተደባለቀበት ነበር። ሕዝቡ አመንዝራዎች ነበሩ፣ ነገር ግን ያህዌአዊነት ይሉት ነበር። የእግዚአብሔር ሕዝብ ፖለቲካዊ ጉድኝት ውስጥ መግባቱ፣ ወደ ጣዖት አምልኮና ልምምድ ውስጥ አስገባቸው።

ለ. የእስራኤል አመንዝራነት II ነገ. 17:7-18 ላይ ተመልክቷል።

(1) በቁጥ 8 ላይ የከነዓናዊያንን የአምልኮ ሥርዓት ተከተሉ

(ሀ) የልምላሜ አምላክ (ሌዋዊያን 18፡22-23)

i) ከፍ ባለ ቦታ ላይ ቁ፣9፣10፣11

ii) የተቀደሰ አምድ (ባኣል) ቁ. 10፣ 16

iii) አሼራም፣ ቁ. 16 እንዚህ ከእንጨት የሚሰሩ ሴት ምስሎች ሆነው ከ በዓል ቅርፅ ጋር የሚሄዱ ናቸው፡፡ እነዚህ የተቀረፁ ወይም አፀዶች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

(ለ) ጥንቆላ ፣ ቁ. 17። ይህ ሌዋ. 19-20 እና ዘዳ. 18 ላይ ተኮንኗል/ተወግዟል።

(2) ቁ. 16 ላይ እነርሱ ሁለቱን የወርቅ ጥጃዎች ማምለካቸውን ቀጥለዋል፣ በያህዌ ተምሳሌትነት፣ በዳንና ቤቴል ላይ በኢዮርብአም I የተቀመጡ (I ነገ. 12:28-29)።

(3) ቁ. 16 ላይ የባቢሎንን አማልክት አስታሮትን አምልከዋል፡ ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት እና ኅብረ-ከዋክብት።

(4) ቁ. 18 ላይ የፍንቄውያንን የመራባት የእሳት ጣዖት፣ ሞሎክን አምልከዋል፣ ልጆቻቸውን በመሠዋት (ሌዋ. 18:21፤ 20:2-5)። ልምምዱም "ሞሎክ" ይባላል። እሱም የጣዖት ስም አይደለም።

ሐ. በአላዊነት W.F. Albright's *Archaeology and the Religion of Israel* p. 82ff)

(1) የእኛ የተሻለ ምንጫችን "የዑጋሪት የበአል ኢፒክ" ነው።

(ሀ) እሱም በአልን የሚገልጸው እንደ ወቅታዊ፣ የሚሞት እና የሚነሣ ጣዖት አድርጎ ነው። እሱም በ *ሞት* (የጣዖት ስም) ተሸንፎ ከምድር በታች ታስሯል። በምድር ያለ ሕይወት ሁሉ ፍጻሜውን አግኝቷል። ነገር ግን በሴቷ ጣዖት *(Anat)* በመታገዝ እሱ ተነሥቶ *ሞት*ን አሸንፏል፣ በየጸደዩ። እሱ የመራባት ጣዖት ነበር፣ በማስመሰል አስማት የሚመለክ።

(ለ) እሱም ደግሞ *Hadad* በመባል ይታወቃል።

(2) *ኤል* የከነአናውያን ጣዖታት ሁሉ አለቃ ጣዖት ነው፣ ነገር ግን የበአል ታዋቂነት ስፍራውን አስለቀቀው።

(3) እስራኤል የሲዶናውያን በአላዊነት እጅግ ተጽዕኖ አሳድሮበታል፣ በኤልዛቤል በኩል፣ እሷም የሲዶናውያን ንጉሥ ልጅ የነበረች። እሷም በኦምሪ ለልጁ ተመረጠች፣ ለአክአብ።

(4) በእስራኤል በአል ይመለክ የነበረው በአጥቢያው ከፍተኛ ስፍራዎች ላይ ነበር። እሱም ተምሳሌት የሚሆነው ከፍ የተደረገ ድንጋይ ነበር። የእሱም ጓደኛ (ሚስት) አሼራህ ነች፣ ተምሳሌት የተደረገላትም የተጣመመ ግንድ ነው፣ ተምሳሌትነቱም የሕይወት ዛፍ።

መ. በርከት ያሉ የአመንዝራነት (ጣዖት አምላኪነት) ምንጮችና ዓይነቶች ተጠቅሰዋል።

(1) የወርቅ ጥጃዎች በቤቴልና በዳን፣ በኢዮርብአም I ተቀምጠዋል፣ ያህዌን ለማምለክ።

(2) የሲዶናውያን የመራባት ጣዖት እና የሴት ጣዖት፣ በአጥቢያ ከፍተኛ ቦታዎች።

(3) ተፈላጊው አመንዝራነት፣ በዛ ጊዜ በነበረው ፖለቲካዊ ኅብረት (ቃል-ኪዳን)።

5. የአሦር እና የባቢሎን ወረራ አጭር ማጠቃለያ፣ በስምንተኛው ክፍለ-ዘመን በፍልስጥኤም ላይ ተጽዕኖውን ያሳረፈ፡

ሀ. አራቱ የስምንተኛ ክፍለ-ዘመን ነቢያት በንቃት እየሠሩ ነበር፣ በጤግሮስ-ኤፍራጥስ ኢምፓየር ጊዜ በአሦር። እግዚአብሔር ይሄንን ጨካኝ መንግሥት ተጠቀመ በሕዝቡ ላይ ለመፍረድ፣ በተለይም በእስራኤል።

(1) ተለይቶ የተቀመጠው አጋጣሚ የዮርዳኖስ አካባቢ የፖለቲካ እና ወታደራዊ ኅብረት፣ እሱም "ሲሮ-ኤፍራማቲክ ሊግ/ማኅበር" በመባል የሚታወቀው መቋቋም ነው (735 ቅ.ል.ክ)። ሶርያና እስራኤል ይሁዳን ለማስገደድ ሞክረዋል፣ አሦርን በመቃወም እንዲተባበራቸው። በምትኩ አካዝ ለአሦር ደብዳቤ ላከ፣ እንዲረዳው። የመጀመሪያው ብርቱ፣ ሰፊ-ግዛት-ተኮር የአሦር ንጉሥ ቲግላዝ- ፒሌሰር III (745-727 ቅ.ል.ክ)፣ ለወታደራዊ ግጥሚያ/መቋቋም ምላሽ ሰጥቶ ሶርያን ወረረ።

(2) ኋላ ላይ የአሦር አሻንጉሊት ንጉሥ፣ ሆሺኤ (732-722 ቅ.ል.ክ)፣ በእስራኤል፣ ደግሞ ዓመጸ፣ ለግብፅ ጥያቄ አቅርቦ። ሻልማኔሰር V (727-722 ቅ.ል.ክ) እስራኤልን በድጋሚ ወረረ። እሱም እስራኤል ከመረታቱ በፊት ሞተ፣ ነገር ግን የእሱ ወራሽ ሳርጎን II (722-705 ቅ.ል.ክ)፣ የእስራኤልን ዋና ከተማ ሰማርያን ያዘ፣ በ722 ቅ.ል.ክ። አሦር በዚህ አጋጣሚ ከ27000 በላይ እስራኤላውያንን አጋዘ (አፈናቀለ)፣ ቲግላዝ-ፒሌሰር ቀደም ብሎ በ732 ቅ.ል.ክ በሺህዎች የሚቆጠሩትን እንዳጋዘ።

ለ. ከአካዝ ሞት በኋላ (735-715 ቅ.ል.ክ) ሌላ ወታደራዊ ኅብረት ተመሠረተ፣ በዮርዳኖስ አካባቢ አገሮች እና በግብፅ፣ አሦርን በመቃወም (714-711 ቅ.ል.ክ)። እሱም "የአሽዶድ ዓመጽ" በመባል ይታወቃል። በርካታ የይሁዳ ከተሞች ተደመሰሱ፣ አሦር በድጋሚ በወረረበት ጊዜ። መነሻው ላይ ሕዝቅያስ ይሄንን ኅብረት ደግፎት ነበር፣ ኋላ ላይ ግን ድጋፉን አስወጣ።

ሐ. ሆኖም፣ እንደገና ሌላ ኅብረት በአሦር ብርቱ ንጉሥ በሳርጎን II ሞት የተገኘውን አጋጣሚ ለመጠቀም ሙከራ አደረገ፣ በ705 ቅ.ል.ክ፣ ከሌሎች በርካታ ዓመጻዎች፣ እነርሱም በአሦር ኢምፓየር ውስጥ ከተነሡት ጋር በመሆን።

(1) ሕዝቅያስ በዚህ ዓመጻ ላይ ሙሉ ለሙሉ ተሳትፏል። በዚህ ግጥሚያ ሳቢያ ሰናክሬ (705-681 ቅ.ል.ክ) ፍልስጥኤምን ወረረ (701 ቅ.ል.ክ) በኢየሩሳሌምም ከተማ አጠገብ ሰፈረ (II ነገ. 18-19፤ ኢሳ. 36-39) ነገር ግን ይህ ሠራዊት ተአምራዊ በሆነ መልኩ በእግዚአብሔር ተደመሰሰ።

(2) በሊቃውንት መካከል አንዳንድ ጥያቄዎች አሉ፣ ሰናክሬ ምን ያህል ጊዜ ፍልስጥኤምን እንደወረረ። (ምሳሌ፡ ጆን ብራይት አንድ ወረራ አለው በ701 ቅ.ል.ክ እናም ሌላ ታሳቢ በ688 ቅ.ል.ክ፣ ገጽ 270።)

(3) ሕዝቅያስ በአሦር ቁጥጥር ሥር ከመሆንን ተርፎ ነበር፣ ነገር ግን ከኩራቱ የተነሣ የይሁዳን መዝገብ (ሀብት) ለባቢሎናውያን ልዑካን በማሳየቱ፣ ኢሳይያስ የይሁዳን በባቢሎን እጅ መውደቅ ተነበየ (39፡1-8)። ኢየሩሳሌም በናቡከደነፆር እጅ በ587-586 ቅ.ል.ክ ወደቀች።

መ. ኢሳይያስ ደግሞ የእግዚአብሔርን ሕዝብ መመለስ ተነበየ፣ በቂሮስ II፣ የሜዶን-ፋርስ ገዥ አማካኝነት፣ (41:2-4፤ 44:28፤ 45:1፤ 56:11)። ነነዌ በ612 ቅ.ል.ክ በባቢሎን እጅ ወደቀች፣ ነገር ግን የባቢሎን ከተማ በ539 ቅ.ል.ክ በቂሮስ ሠራዊት እጅ ወደቀች። በ538 ቅ.ል.ክ ቂሮስ አዋጅ አወጣ፣ የተጋዙት ሕዝቦች ሁሉ፣ አይሁድንም ጨምሮ ወደ አገራቸው ሊመለሱ እንደሚችሉ። ይልቁንም እሱ ከራሱ ሀብት ልገሳ አደረገ፣ የየአገሬው መቅደሶች ዳግም ይገነቡ ዘንድ።

ለ. የሜሶፖታሚያ ኃይላት አጭር ታሪካዊ ቅኝት (በቀዳሚነት የጆን ብራይትን የእስራኤል ታሪክ፣ ገጽ 462 ፣(John Bright's *A History of Israel*, p. 462ff) የቀን አቆጣጠር መሠረት በመጠቀም)፡

1. የአሦር ሰፊ ግዛት (ኢምፓየር) (ዘፍ. 10፡11)፡

ሀ. ሃይማኖትና ባህል ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድረዋል፣ በሱሜርያን/ባቢሎናውያን ኢምፓየር።

ለ. የገዥዎች ያልተጠናቀቀ/ጊዜያዊ ዝርዝር እና ግምታዊ ቀናት፡

(1) 1354-1318 አሽር-ዑባሊ I፡

(ሀ) የኬጢያውያንን ከተማ ከርከሚሽን ድል አደረገ።

(ለ) የኬጢያውያንን ተጽዕኖ ማስወገድ ጀመረ፣ አሦርም እንዲለማ ፈቀደ።

(2) 1297-1266 አዳድ ኒራሪ I (ብርቱ ንጉሥ)።

(3) 1265-1235 ሻልማንሰር I (ብርቱ ንጉሥ)።

(4) 1234-1197 ቱኩልቲ-ኒኑርታ I

- የመጀመሪያው የባቢሎን ኢምፓየር ድል፣ ወደ ደቡብ ሲል።

(5) 1118-1078 ቲግላዝ-ፒሌሰር I

- አሦር ዋነኛው የሜሶፖታሚያ ኃይል ሆነ።

(6) 1012- 972 አሽር-ራቢ II

(7) 972- 967 አሽር-ሬሽ-አይሱይ II።

(8) 966- 934 ቲግላዝ-ፒሊሰር II።

(9) 934- 912 አሽር-ዳን II።

(10) 912- 890 አዳድ-ኒራሪ II።

(11) 890- 884 ቱኩልቲ-ኒኑርታ II።

(12) 890- 859 አሽር-ናስር-አፓል II።

(13) 859- 824 ሻልማንሰር III።

የቃርቃር ጦርነት በ853

(14) 824- 811 ሻማሺ-አዳድ V።

(15) 811- 783 አዳድ-ኒራሪ III።

(16) 781- 772 ሻልማንሰር IV።

(17) 772- 754 አሽር-ዳን III።

(18) 754- 745 አሽር-ኒራሪ V።

(19) 745- 727 ቲግላዝ-ፒሊሰር III:

(ሀ) በባቢሎናዊ የዙፋን ስም ፎሐ በሚል ነው የሚጠራው፣ II ነገ. 15:19 ላይ።

(ለ) እጅግ ብርቱ ንጉሥ።

(ሐ) እሱም የተሸነፉ ሕዝቦችን የማጋዝ/የማፈናቀል ፖሊሲ ተከተለ።

(መ) በ735 ቅ.ል.ክ የ“ሲሮ-ኤፍራማቲክ ሊግ/ማኅበር” ምሥረታ ነበር፣ እሱም በዮርዳኖስ አካባቢ ሀገሮች የሚገኘውን ወታደራዊ ኃይል ሁሉ ከኤፍራጥስ የውኃ ራስ አንሥቶ እስከ ግብፅ ድረስ የማስተባበር ሙከራ ነበር፣ እየተነሣ ያለውን የአሦርን ወታደራዊ ኃይል ለማግለል/ለማዳከም። የይሁዳው ንጉሥ አካዝ ለመደባለቅ እምቢ ስላለ በእስራኤልና በሶርያ ተወረረ። እሱም ለቲግላዝ-ፒሌሰር III የዕርዳታ ደብዳቤ ላከ፣ የኢሳይያስን ምክር አልሰማ ብሎ (ኢሳ. 7-12)።

(ሠ) በ732 ቲግላዝ-ፒሊሰር III ሶርያን እና እስራኤልን ወርሮ ድል አደረገ፣ አገልጋይ የሆነ ንጉሥም በእስራኤል ዙፋን ላይ አስቀመጠ፣ ሆሼአ ((732-722 ቅ.ል.ክ)። በሺሆች የሚቆጠሩ አይሁድ ወደ ሜዶን ተጋዙ (II ነገ. 15-16)።

(20) 727- 722 ሻልማንሰር V።

ሆሼአ ወዳጅነት ከግብፅ ጋር አደረገ፣ እናም በአሦር ተወረረ (II ነገ. 17)።

(21) 722-705 ሳርጎን II፡

(ሀ) ከሦስት ዓመት ከበባ በኋላ፣ ይኸውም በሻልማንሰር V የተጀመረ፣ የእሱ የጦር አዛዥ እና ወራሽ ሳርጎን II፣ የእስራኤልን ዋና ከተማ ሰማርያን ድል አደረገ። ከ27000 በላይ ወደ ሜዶን ተጋዙ።

(ለ) የኬጢያውያን ኢምፓየርም ድል ሆነ።

(ሐ) በ714-711 ሌለኛው የዮርዳኖስ-ዙሪያ ሀገሮች እና ግብፅ ኅብረት በአሦር ላይ ዓመጹ። ይህም ኅብረት “የአሽዶድ ዓመጽ” በመባል ይታወቃል። የይሁዳው ሕዝቅያስ እንኳ ከመነሻው ላይ ገብቶበት ነበር። አሦር በርከት ያሉ የፍልስጥኤም ከተሞችን ወርሮ ደምስሷል።

(22) 705-681 ሰናክሬ፡

(ሀ) ሌላ የዮርዳኖስ-ዙሪያ ሀገሮች እና ግብፅ ከአባቱ፣ ሳርጎን II ሞት በኋላ ዓመጹ። ሕዝቅያስ ይሄንን ዓመጻ ሙሉ ለሙሉ ደገፈ። ሰናክሬ በ701 ወረረ። ዓመጻው ተደመሰሰ፣ ነገር ግን ኢየሩሳሌም በእግዚአብሔር ሥራ ተጠበቀ (ኢሳ. 36-39 እና II ነገ. 18-19።)

(ለ) ደግሞም ሰናክሬ በኤላም እና ባቢሎን ያለውን ዓመጻ በቁጥጥር ሥር አደረገ።

(23) 618-699 ኢሳርሃዶን፡

(ሀ) የመጀመሪያው የአሦር ገዥ፣ ግብፅን ለማጥቃትና ድል ለማድረግ።

(ለ) እሱም ለባቢሎን ታላቅ ኀዘኔታ ነበረው፣ እናም ዋና ከተማዋን ዳግም ገነባ።

(24) 669-663 አሸርባኒፓል፡

(ሀ) ደግሞም ኦስናፓር በመባል ይጠራል፣ ዕዝራ 4፡10 ላይ

(ለ) ወንድሙ ሻማሽ-ሹም-አኪን የባቢሎን ንጉሥ ተደረገ። ይህም በአሦርና በባቢሎን መካከል በርከት ላሉ ዓመታት ሰላምን አመጣ፣ ነገር ግን የተዳፈነ የነጻነት ትግል በ652 ፈነዳ፣ በወንድሙ የሚመራ።

(ሐ) የቴብስ ውድቀት፣ 663

(መ) የኤላም መሸነፍ፣ 653፣ 645

(25) 633- 629 አሸር-ኢቲል-ኢላኒ።

(26) 629- 612 ሲን-ሻር-ኢሽኩን።

(27) 612- 609 አሸር-ዑባሊት II:

- ዘውድ የደፋ ንጉሥ፣ በስደት ላይ በካራን፣ ከአሸር ውድቀት በኋላ፣ በ614 እና ነነዌ በ612

2. የአዲሲቷ ባቢሎን ኢምፓየር፡

ሀ. 703-? ሜሮዳክ-ባላዳን፡

በአሦር አገዛዝ ላይ በርከት ያሉ ዓመጻዎችን ጀምሯል።

ለ. 652 ሻማሽ-ሹም-አኪን፡

(1) የኢስራዶን ልጅ እና የአሹርባኒፓል ወንድም።

(2) እሱ በአሦር ላይ ዓመጽ ጀመረ ነገር ግን ተሸነፈ።

ሐ. 626-605 ናቦፖላሳር፡

(1) እሱ የመጀመሪያው ንጉሠ ነገሥት ነው፣ የአዲሲቷ ባቢሎን ኢምፓየር።

(2) እሱ አሦርን በደቡብ በኩል አጠቃ፣ የሜዶኑ ሲያካረስ በስተ ሰሜናዊ ምስራቅ ሲያጠቃ።

(3) የጥንቱ የአሦር ዋና ከተማ አሸር በ614 ወደቀች፣ እናም ብርቱዋ አዲሲቷ ዋና ከተማ ነነዌ በ612 ወደቀች።

(4) ቅሬታው የአሦር ሠራዊት ወደ ካራን አፈገፈገ። ይልቁንም እነሱ ንጉሥ አነገሡ።

(5) በ608 ፈርዖን ኒካው II (II ነገ. 23:29) ወደ ሰሜን ዘመተ፣ ቅሬታውን የአሦርን ሠራዊት ለማገዝ፣ እየተነሣ ያለውን የባቢሎንን ኃይል በመቃወም፣ ነጻ ቀጣና በማቋቋም ዓላማ። ኢዮስያስ፣ መልካሙ የይሁዳ ንጉሥ (II ነገ. 23)፣ የግብፅ ሠራዊት በፍልስጥኤም ውስጥ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ተቃወመ። በሜጊዶ መለስተኛ ውጊያ ነበር። ኢዮስያስ ቆሰለ ሞተም (II ነገ. 23:29-30)። ልጁ ኢዮአካስ ነገሠ። ፈርዖን ኒካው II በጣም ዘግይቶ ደረሰ፣ የአሦር ኃይላት በካራን የሚያደርሱትን ጥፋት ለማስቆም። እሱም ከባቢሎናውያን ኃይላት ጋር ተጋጠመ፣ በመስፍኑ በናቡከደነፆር II ከሚመራው፣ እናም በ605 እጅግ አድርጎ ተሸነፈ፣ ከርከሚሽ ላይ፣ ኤፍራጥስጋ።

ወደ ግብፅ ሲመለስም ኢየሩሳሌምጋ ቆመ፣ ከተማይቱንም ዘረፈ። እሱም ኢዮአክስን በሦስት ወር ብቻ ተክቶ ኢጋዘው። እሱም ሌለኛውን የኢዮስያስን ልጅ ኤልያቂምን በዙፋኑ አስቀመጠ (II ነገ. 23:31-35)።

(6) ናቡከደነፆር II የግብፅን ሠራዊት ወደ ደቡብ ሲል በፍልስጥኤም ውስጥ አሳደደ፣ ነገር ግን የአባቱን ሞት ስለተረዳ ወደ ባቢሎን ተመለሰ።

ኋላ ላይ በዛው ዓመት ወደ ፍልስጥኤም ተመለሰ። እሱም ኤልያቂምን በይሁዳ ዙፋን ላይ አስቀመጠው ፣ ነገር ግን ብዙ ሺህ መሪ ዜጎችንና ብዙ የንጉሣውያን ቤተሰብ አባላትን ኢጋዘ። ዳንኤልና ጓደኞቹ በዚህ ግዞት የተካተቱ ናቸው።

መ. 605-562 ናቡከደነፆር II፡

(1) ከ597-538 ባቢሎን ፍልስጥኤምን ሙሉ ለሙሉ ተቆጣጥሮ ነበር።

(2) በ597 ሌላው ከኢየሩሳሌም ማፈናቀል/ማስወጣት ተከሰተ፣ ኤልያቂም ከግብፅ ጋር ኅብረት በማድረጉ ምክንያት (II ነገ. 24)። እሱም ናቡከደነፆር II ከመድረሱ በፊት ሞተ። ልጁም ኢዮአክስ ንጉሥነቱ ለሦስት ወር ብቻ ነው፣ ወደ ባቢሎን እስከሚጋዝ ድረስ። አስር ሺህ ዜጎች፣ ሕዝቅኤልን ጨምሮ በባቢሎን ከተማ አጠገብ፣ በካናል ካባር ዳግመኛ ሰፈሩ።

(3) በ586፣ ከግብፅ ጋር ከተደረገው መነሣሣት/መቃበጥ በኋላ የኢየሩሳሌም ከተማ ሙሉ ለሙሉ ተደመሰሰች (II ነገ. 25) እናም ሰፊ ማፈናቀል/ማስወጣት ተከሰተ። ሴዴቅያስ፣ እሱም ኤልያቂምን የተካው ተጋዘ፣ ጎዶልያስ በገዥነት ተሾመ።

(4) ጎዶልያስ በአይሁድ ዓመጸኛ ኃይላት ተገደለ። እነዚህ ኃይላት ወደ ግብፅ ኮበለሉ፣ ኤርምያስም አብሯቸው እንዲሄድ አስገደዱት። ናቡከደነፆር ለአራተኛ ጊዜ ወረራ አካሄደ (605፣ 596፣ 586፣ 582) እናም ሊያገኝ የቻላቸውን ቅሬታዎቹን አይሁድ አፈናቀለ/አስወጣ።

ሠ. 562-560 ኢቭል-ሜሮዳክ፣ ደግሞም አሜል-ማርዱክ በመባል የሚታወቀው

- እሱ ኤልያቂምን ከእስር ፈታው፣ ነገር ግን በባቢሎን እንዲቀር ተደረገ (II ነገ. 25:27-30፤ ኤር. 52:31)።

ረ. 560-556 ነሪግሊሳዝ።

- እሱ የናቡከደነፆር የጦር አዛዥ ነበር፣ ኢየሩሳሌምን የደመሰሰ።

ሰ. 556- ላባስኪ-ማርዱክ።

- እሱ የነሪግሊሰር ልጅ ነበር፣ ነገር ግን ከዘጠኝ ወራት ብቻ በኋላ ተገደለ።

ሸ. 556-539 ናቦኒደስ፡

(1) ናቦኒደስ ከንጉሣውያን ቤት ጋር ዝምድና አልነበረውም፣ ስለዚህ የናቡከደነፆር II ልጅን አገባ።

(2) እሱም አብዛኛውን ጊዜውን ያሳለፈው ለጨረቃ አማልክት (ጣዖት) "ሲን" መቅደስ በመገንባት ነበር፣ ቴማ ላይ። እሱም የዚች ጣዖት ሊቀ ካህኒት ልጅ ነበር። ይህም የማድሩክን፣ የባቢሎንን ዋነኛ ጣዖት ካህናት ጠላትነት አፈራለት።

(3) እሱም አብዛኛውን ጊዜውን ዓመጾችን በማዳፈንና መንግሥቱን በማጠናከር ነበር ያሳለፈው።

(4) እሱም ወደ ቴማ ተንቀሳቀሰ፣ የመንግሥትን ጉዳይ ለልጁ ለብልጣሶር ተወ፣ በዋና ከተማው በባቢሎን (ዳን. 5)።

ቀ. ?-539 ብልጣሶር (የጋራ አገዛዝ)

- የባቢሎን ከተማ እጅግ በፍጥነት ወደቀች፣ በፋርስ ሠራዊት፣ በጉቲዩሙ ጎብርያስ እጅ፣ የኤፍራጥስን ውኃ መስመሩን አዙሮ ወደ ከተማዋ እንዲገባ በማድረግ፣ ያለ ምንም ተቃውሞ። ካህናቱና የከተማይቱ ሕዝብ ፋርሳውያንን እንደ ነጻ አውጭና፣ ማርዱክን እንደሚመልሱ አድርጎ ነው የቀጠራቸው። ጎብርያስ የባቢሎን ገዥ እንዲሆን በቂሮስ II ተሾመ። ቂሮስ II ወይም ጎብርያስ "የሜዶኑ ዳርዮስ" ሊሆኑ ይችላሉ፣ የዳን. 5:31 እና 6:1። ዳርዮስ ማለት "የንጉሣዊው" ማለት ነው።

3. የሜዶን -ፋርስ 3. የሜዶ-ፋርስ ኢምፓየር፡ የቂሮስ II አነሣስ ጥናት (ኢሳ. 44:28፤ 45:1-7):

ሀ. 625-585 ሳያክስረስ የሜዶን ንጉሥ ነበር፣ እሱም ባቢሎን አሦርን ድል እንዲያደርግ የረዳ።
ለ. 585-550 አስትያገስ የሜዶን ንጉሥ ነበር። ቂሮስ የልጅ ልጁ ነበር፣ ከማንዳኒ።
ሐ. 550-530 ቂሮስ II የአንሻሙ፣ አገል-ጋይ ንጉሥ ነበር፣ ኋላ ላይ ያመጸው፡
   (1) ናቦኒደስ፣ የባቢሎን ንጉሥ፣ ቂሮስን የሚደግፍ።
   (2) ቂሮስ II አስተያገስን ከዙፋን አወረደ።
   (3) ናቦኒደስ የኃይል ሚዛኑን ለማስመለስ ኅብረት ፈጠረ፡
      (ሀ) ከግብፅ።
      (ለ) ከክሮሰስ፣ ከልዳ ንጉሥ (ታናሹ እስያ)።
መ. 547- ቂሮስ II ሳርዴስ ላይ ዘመተ (የልዳ ዋና ከተማ)።
ሠ. ኅዳር 2፣ 539-፣ የጉቲዩም ኅብርያስ ከቂሮስ ሠራዊት ጋር ባቢሎንን ወሰደ፣ ያለ ምንም መቋቋም/ተቃውሞ። ኅብርያስ የባቢሎን ገዥ ተደረገ።
ረ. 539- በጥቅምት ቂሮስ II "ታላቁ" በግሉ እንደ ነጻ አውጪ ገባ። ለብሔራዊ ቡድኖች ያለው የደግነት አቋም (ፖሊሲ) የመፈናቀል ዓመታትን ቀይሮ/ገልብጦ ብሔራዊ ፖሊሲ ሆነ።
ሰ. 538- አይሁድና ሌሎችም ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ተፈቀደላቸው፣ እንዲሁም የየአገራቸውን መቅደስ ዳግም እንዲገነቡ።
ሸ. 530- የቂሮስ ልጅ ካምቢሰስ II ተካው/ወረሰው።
ቀ. 530-522 የካምቢሰስ II አገዛዝ
   - የግብፅን ኢምፓየር በ525 ቅ.ል.ክ. ከሜዶ-ፋርስ ኢምፓየር ጋር ደመረው።
   - ራሱን አጥፍቶ ሊሆን ይችላል።
በ. 522-486 ዳርዮስ I መግዛት ጀመረ
   (1) እሱ የንጉሣዊ ቤተሰብ አልነበረም፣ ወታደራዊ ጀነራል እንጂ።
   (2) እሱ የፋርስን ኢምፓየር አደራጀ፣ ቂሮስ ለሳትራፕስ ያወጣውን ዕቅድ በመጠቀም (ዕዝራ 1-6፤ ሐጌ፤ ዘካርያስ)።
   (3) እሱም እንደ ልዳ የብረት ሳንቲም አዘጋጀ።
ተ. 486-465 የዘረክሲስ I አገዛዝ፡
   (1) የግብፅን ዓመጽ/አብዮት አከሸፈ
   (2) ግሪክን ለመውረር ፈለገ፣ የፋርስን ሕልም ለማሳካት፣ ነገር ግን በቴርሞፖሊ በ480 እና በሳላሚስ በ479 ውጊያ ድል ሆነ።
   (3) የአስቴር ባል፣ እሱም አሃሹረስ ተብሎ በመጽሐፍ ቅዱስ የሚጠራው፣ በ465 ተገደለ።
ቸ. 465-424 አርጤክስስ I ነገሠ (ዕዝራ 7-10፤ ነህምያ፤ ሚልክያስ)፡
   (1) ግሪኮች ርምጃቸውን ቀጠሉ፣ ከፔሎፓኒሲአን የርስ በርስ ጦርነት ጋር እስከሚገጥሙ ድረስ
   (2) ግሪክ ተከፋፈለች (አቴናውያን - ፔሎፓኒሲያን)
   (3) የግሪክ የርስ በርስ ጦርነት በ20 ዓመት አበቃ
   (4) በእነዚህ ጊዜያት የአይሁድ ማኅበረሰብ ተጠናከረ
ኀ. 423-404 ዳርዮስ II ነገሠ
ነ. 404-358 አርጤክስስ II ነገሠ
ኘ. 358-338 አርጤክስስ III ነገሠ
አ. 338-336 አርሰስ ነገሠ
ከ. 336-331 ዳርዮስ III ነገሠ።

4. የግብፅ ጥናት፡
ሀ. Hyksos (እረኛ ነገሥታት - ሴማዊ ገዥዎች) – 1720/10-1550 ቅ.ል.ክ.
ለ. 18ኛ ሥርወ-መንግሥት (1570-1310)፡
   (1) 1570-1546 አሞሲስ
   (2) 1546-1525 አሜኖፊስ I (አሜንሆቴፕ I)።
   (3) 1525-1494 ቱትሞሲስ I
   (4) ? ቱትሞሲስ II
   (5) ? ሃትሺፕሱት
   (6) 1490-1435 ቱትሞሲስ III
   (7) 1435-1414 አሜኖፊስ II
   (8) 1414-1406 ቱትሞሲስ IV
   (9) 1406-1370 አሜኖፊስ III
   (10) 1370-1353 አሜኖፊስ IV (አክሄናቴን)
   (11) ? ስሜንክሃሪ
   (12) ? ቱታንክሃሙን
   (13) ? አይ
   (14) 1340-1310 ሃሬምሃብ
ሐ. 19ኛ ሥርወ-መንግሥት (1310-1200 ቅ.ል.ክ):
   (1) ? ራምሰስ I
   (2) 1309-1290 ሴቲ I
   (3) 1290-1224 ራምሴስ II (ራምሰስ II)
   (4) 1224-1216 ማርኒፕታህ (ሜሪንፕታህ)
   (5) ? አሜንሜሰስ
   (6) ? ሰቲ II
   (7) ? ሲፕታህ
   (8) ? ቴዎስሬት
መ. 20ኛ ሥርወ-መንግሥት (1180-1065 ቅ.ል.ክ):
   (1) 1175-1144 ራምሴስ III

(2) 1144-1065 ራምሴስ IV - XI

ሠ. 21ኛ ሥርወ-መንግሥት (1065-935 ቅ.ል.ክ):

(1) ? ስሜንደስ

(2) ? ሄሪሆር

ረ. 22ኛ ሥርወ-መንግሥት (935-725 - ልብያዊ):

(1) 935-914 ሺሻክ (ሾሴንክ I ወይም ሺሾንግ I)

(2) 914-874 ኦሶርኮን I

(3) ? ኦሶርኮን II

(4) ? ሾሼኔክ II

ሰ. 23ኛ ሥርወ-መንግሥት (759-715 - ልብያዊ)

ሸ. 24ኛ ሥርወ-ምንግሥት (725-709)

ቀ. 25ኛ ሥርወ-መንግሥት (716/15-663 - ኢትዮጵያዊ/ኑብያዊ ):

(1) 710/09-696/95 ሻባኮ (ሻባኩ)

(2) 696/95-685/84 ሺብቴኮ (ሺቢትኩ)

(3) 690/89፣ 685/84

(4) 664 ቲርሃካን (ታሃርቃ)

(5) ? ታንታሙን

በ. 26ኛ ሥርወ-መንግሥት (663-525 ቅ.ል.ክ- ሳይቲክ):

(1) 663-609 ሳሜቲከስ I (ሳምቲክ)

(2) 609-593 ኒኮ II (ኒኾ)

(3) 593-588 ሳሜቲከስ II (ሳምቲክ)

(4) 588-569 አፕሪስ (ሆፍራ)

(5) 569-525 አማሲስ

(6) ? ሳሜቲከስ III (ሳምቲክ)

ተ. 27ኛ ሥርወ-መንግሥት (525-401 - ፋርሳዊ):

(1) 530-522 ካምቢሰስ II (የቂሮስ II ልጅ)

(2) 522-486 ዳርዮስ I

(3) 486-465 ዘረክሲስ I

(4) 465-424 አርጤክስስ I

(5) 423-404 ዳርዮስ II

* ለተለያዩ የሁነት ቅደም ተከተላዊ ዝርዝሮች *Zondervan's Pictorial Bible Encyclopedia*, vol. 2 p. 231) ቅጽ 2 ገጽ 231 ተመልከት።

5. የግሪክ ጥናት፡

ሀ. 359-336 ፊሊፕ II የመቄዶንያው

(1) ግሪክን ገነባ።

(2) በ336 ተገደለ።

ለ. 336-323 አሌክሳንደር II "ታላቁ" (የፊሊጵስ ልጅ)፡

(1) የፋርስን ንጉሥ ዳርዮስ IIIን አስወጣ፣ በኢሱስ ውጊያ

(2) በ323 ቅ.ል.ክ. በባቢሎን በንዳድ (ትኩሳት) ሞተ፣ በ33/32 ዓመቱ።

(3) የአሌክሳንደር የጦር አዛዦች (ጀነራሎች) ኢምፓየሩን ከፋፈሉ፣ በሞተ ጊዜ፡

(ሀ) ካሴንደር - መቄዶንያ እና ግሪክ

(ለ) ሊሲሚከስ - ትሬሲ

(ሐ) ሴሊዩከስ I - ሶርያ እና ባቢሎን

(መ) ፕቶለሚ - ግብፅ እና ፍልስጥኤም

(ሠ) አንቲጎነስ - ታናሹ እስያ (ብዙም አልቆየ)

ሐ. ሴሊዩሲደስ እና ፕቶለሚስ ፍልስጥኤምን ለመቆጣጠር ተቀናቃኝ ሆኑ፡

(1) ሶርያ (የሴሊዩሲድ ገዥዎች)፡

(ሀ) 312-280 ሴለዩከስ I

(ለ) 280-261 አንቲኦከስ I ሶስተር

(ሐ) 261-246 አንቲኦከስ II ቲዩስ

(መ) 246-226 ሴለዩከስ II ካሊኒከስ

(ሠ) 226-223 ሴለዩከስ III ሲራዩነስ

(ረ) 223-187 አንቲኦከስ III ታላቁ

(ሰ) 187-175 ሴለዩከስ IV ፊሎፓቶር

(ሸ) 175-163 አንቲኦከስ IV ኢፒፋነስ

(ቀ) 163-162 አንቲኦከስ V

(በ) 162-150 ዲሜጥሮስ I

(2) የግብፅ (ፕቶለማይክ) ገዥዎች:

(ሀ) 327-285 ፕቶለሚ I ሶተር

(ለ) 285-246 ፕቶለሚ II ፊላዴልፈስ

(ሐ) 246-221 ፕቶለሚ III ኢቬጌተስ

(መ) 221-203 ፕቶለሚ IV ፊሎፓቶር

(ሠ) 203-181 ፕቶለሚ V ኢፒፋነስ

(ረ) 181-146 ፕቶለሚ VI ፊሎሜቶር

(3) አጭር ቅኝት (ዳሰሳ)፡
(ሀ) 301- ፍልስጥኤም በፐሎቶሚ አገዛዝ ሥር ለዓመታት
(ለ) 175-163 አንቲኦከስ IV ኢፒፋነስ፣ 8ኛው የሴሌዩሲድ ገዥ፣ አይሁድን ካስፈለገ በኃይል ጭምር ሔለናዊ ለማድረግ የፈለገ፡
i. የስፖርት ጨዋታ ስፍራዎችን ገነባ
ii. የአምልኮተ-ባዕድ (ጣዖት) መሠዊያ ለዜውስ ኦሎምፒያስ መቅደስ ገነባ

VIII. ጽሑፋዊ ምድቦች

ሀ. አጭር የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር
1. ምዕራፍ 1-39 - ነቢዩና የእርሱ ቀን
2. ምዕራፍ 40-66 (ወይም 40-55 እና 56-60 ሊሆን ይችላል) - አዲሱ ዘመን

ለ. ምዕራፍ 1-39 ፣ የኢሳይያስ ቀን ታሪካዊ መቼት (ቅድመ-ግዞት)
1. ምዕራፍ 1-6፣ በንጉሥ ዖዝያን እና ኢዮአታም
2. ምዕራፍ 7-14፣ በንጉሥ አካዝ
3. ምዕራፍ 15-39፣ በንጉሥ ሕዝቅያስ (ምዕራፍ 36-39 ከII ነገ. 18፡13-20፡19 ጋር ትይዩ ናቸው

ሐ. ምዕራፍ 40-66፣ ግዞታዊ እና ድኅረ-ግዞታዊ ጊዜያት የቀጣዩ ንጉሣዊ መንግሥት ዓይነቶች ናቸው።
1. ምዕራፍ 1-39 የኢሳይያስን ስብከት እንደሚያንጸባርቁና በግልጽ ቃላዊ አቅርቦቶች እንደሆኑ ሁሉ፣ ምዕራፍ 40-55 አዲስ መቼትን ያንጸባርቃሉ። የእግዚአብሔር ፍርድ መጥቷል፣ አሁን ደግሞ መታደስ/መመለስ ዋነኛው ጭብጥ ነው። ደግሞም ስልታዊ ፍንጭ አለ፣ እነዚህ ምዕራፎች ቃላዊ ላለመሆናቸው፣ እንደ ጽሑፋዊ።
2. ምዕራፍ 1-39 በግልጽ የሚናገረው የአሦርን አያያዝ እና የባቢሎንን አያያዝ ነው፣ በዓይነት፣ በተለይም ምዕራፍ 13-14፣ 21 እና 39። ምዕራፍ 40-55 የሚናገረው የፋርስን ጊዜና የእግዚአብሔር ሕዝብ ወደ ተስፋይቱ ምድር መመለሱን ነው።
3. ኋለኞቹ የኢሳይያስ ምዕራፎች፣ 56-66 የመዳረሻ /የመጨረሻ ዓይነት ናቸው፣ ታሪካዊ ዘይቤዎችን በመጠቀም፣ ከጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ፣ ሁለንተናዊውን አህዳዊ የያህዌ አምልኮ ዓለም እንደሚያደርግ በጥላነት/ንግርነት የቀረበበት።

መ. ኢሳይያስን በፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር የማስቀመጥ ችግር
1. አብዛኞቹ ዘመናዊ ሊቃውንት መጽሐፉን ቢያንስ ወደ ሁለት ምድቦች ይከፍሉታል፡ ምዕራፍ 1-39 እና 40-66። አር.ኬ. ሃሪሰን፡ ምዕ. 1-33 እና 34-66 በዲኤስኤስ/ሙባጥ (ሙት ባሕር ጥቅሎች) ላይ ባለው ክፍተት ምክንያት። ይህ ግልጽ የሆነ ክፍል በዲኤስኤስ ላይ በምዕራፍ 33 እና 34 መካከል ያለው፣ ኢሳይያስ የተገኘው በተከታዮቹ ነው፣ በሁለት ቅጾች የሚል ሐሳብ አስነሥቷል። ደብልዩ.ኤች. ብራውንሊ ሁለቱ ቅጾች ከመዋቅር አኳያ እርስ በርስ ይተያያሉ የሚል ሐሳብ አቅርቧል፡

| ቅጽ 1፡ | | ቅጽ 2 |
|---|---|---|
| ምዕራፍ 1-5 | - ውድመት እና መታደስ | ምዕራፍ 34-35 |
| ምዕራፍ 6-8 | - ግለ-ታሪካዊ ነገሮች | ምዕራፍ 36-40 |
| ምዕራፍ 9-12 | - መለኮታዊ ባርኮትንና ፍርድን የሚያስከትሉ ምክንያቶች | ምዕራፍ 41-45 |
| ምዕራፍ 13-23 | -ትንቢት በውጭ ኃይላት (አሉታዊ) | ምዕራፍ 46-48 |
| ምዕራፍ 24-27 | - ሁሉን አቀፋዊ መቤዠት እና የእስራኤል መዳን | ምዕራፍ 49-35 |
| ምዕራፍ 28-31 | - ሥነ-ምግባራዊ ስብከቶች | ምዕራፍ 56-59 |
| ምዕራፍ 32-33 | - የሕዝቡ/መንግሥቱ/ መመለስ | ምዕራፍ 60-66 |

2. አንዳንድ የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝሮች በታሪካዊ መቼቱ ላይ ሲያተኩሩ፣ ሌሎች ደግሞ በመሢሐዊ ይዘት ላይ ያተኩራሉ

| | NIV | ሊዩፖልድ |
|---|---|---|
| ምዕ. 7-12 | "አራማውያንእና እስራኤላውያን በይሁዳ ላይ አሉታዊ አያያዝ ትንቢታዊ ሁነቶች" | "አማኑኤል መጽሐፍ" |
| ምዕ. 28-33 | "ስድስት ወዮታዎች፡ አምስቱ በእስራኤል ታማኝ አለመሆንና አንድ በአሦር" | "የጽዮን መጽሐፍ" (የማዕዘን ድንጋይ) |

3. አንዳንድ ምሳሌዎች፣ ለጽሑፋዊ ምድቦች ርግጠኛ አለመሆን (ምዕ. 1-12)
ሀ. የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር፣ የምዕራፍ 1-12 በ E. Y. Young ፣ ገጽ 211-214፡
(1) 1፡1-12፡6 ትንቢቶች፣ ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን በተመለከተ
(ሀ)1:1-31 ታላቁ ሕጋዊ ሰነድ (መጥሪያ)
(ለ) 2:1-4:6 የመሢሑ አገዛዝ እና ፍርድ በሕዝቡ ላይ
(ሐ) 3:5-30 የይሁዳ ተደጋጋሚ በደሎች
(መ) 6:1-13 ኢሳይያስ ስለ ጌታ ያየው ራዕይ
(ሠ) 7:1-12:6 በአካዝ ያገዛዝ ዘመን የተነገሩ ትንቢቶች
ለ. የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር፣ የምዕራፍ 1-2 R.K. Harrison ገጽ 764፡
(1) ስለ ይሁዳ መፍረስ እና መታደስ የተባሉ ትንቢቶች፣ ምዕ. 1-5
(2) የኢሳይያስ ጥሪ፤ ግለ-ታሪካዊ ነገሮች፣ ምዕ. 6-8
(3) የወቅቱ የዓለም ኢምፓየሮች እና ሚናቸው፣ ምዕ. 9-12
ሐ. የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር፣ የምዕራፍ 1-12 በNIV የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ፣ ገጽ 1016
(1) ምዕራፍ 1-6
(ሀ) መግቢያ፡ በይሁዳ ላይ የቀረበ ክስ፣ ኪዳኑን ስለጣሰ፣ ምዕ. 1
(ለ) የወደፊቱ የይሁዳና ኢሩሳሌም ቅጣትና ክብር፣ ምዕ. 2-4
i) የኢየሩሳሌም የወደፊቱ በረከት (2:1-5)

ii) የጌታ ቅጣት በይሁዳ ላይ (2:6-4:1)
iii) የጽዮን መታደስ (4:2-6)
(ሐ) የሕዝቡ ፍርድና ግዞት (ምዕ.5)
(መ) የኢሳይያስ የተለየ ተልዕኮ (ምዕ.6)
(2) ምዕራፍ 7-12
(ሀ) አካዝ የአራምያውያንንና የእስራኤላውያንን ኅብረት እንዳይፈራ ማስጠንቀቂያ ተነገረው (ምዕ. 7)
(ለ) የኢሳይያስ ልጅ እና የዳዊት ልጅ (8፡1-9፡7)
(ሐ) ፍርድ በእስራኤል ላይ (9:8-10:4)
(መ) የአሦር ኢምፓየር እና ዳዊታዊ መንግሥት (10:5-12:6)
i) የአሦር ጥፋት (10:5-34)
ii) የዳዊታዊ ንጉሥ እና የእርሱም መንግሥት መመሥረት (ምዕ. 11)
iii) የደስታ መዝሙሮች፣ ስለ መዳን (ምዕ. 12)
መ. የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር፣ የምዕራፍ 1-12 በኤች.ሲ. ሊዩፖልድ፣ ገጽ 38-40:
(1) ትንቢቶች፣ ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን በተመለከተ (ምዕ. 1-12)
(ሀ) መግቢያ፡ የኢሳይያስ ልዩ ዓይነት መልዕክት (ምዕ. 1)
i. ርዕሰ-ጉዳይ፣ ቁ. 1
ii. መለኮታዊ የክስ ጽሑፍ፣ ቁ. 2-4
iii. የጠፋው የሕዝቡ ውጫዊ መንግሥት፣ ቁ. 5-9
iv. የወቅቱ የአምልኮ ዓይነት ለመዋጀት ውጤታማ አለመሆን፣ ቁ. 10-15
v. ጥሪ ለንስሐ፣ ቁ. 16-20
vi. የኢየሩሳሌም ሙስና (መበላሸት) አመላካቾች፣ ቁ. 21-33
vii. እስራኤል በፍርድ ይዋጃል፣ ቁ. 24-31
(ለ) በፍርድ በኩል የእግዚአብሔርን ቸርነታዊ ተስፋ መፈጸም፣ ምዕ. 2-6
i. የጽዮን የከበረ መጻዒ (የወደፊት)፣ በመሢሓዊ ዘመን፣ 2:2-5
ii. የጽዮን አሁን አለመክበር (ውርደት)፣ 2፡6-4፡1
ሀ) በወቅቱ ያለው አሳሳች እሴት መግለጫ፣ ቁ. 6-9
ለ) ሊመጣ ያለው አስፈሪ ፍርድ አመላካቾች፣ ቁ. 10-11
ሐ) የጌታ ቀን በአሳሳች እሴቶች ሁሉ ላይ ምን እንደሚያደርግ፣ ቁ. 12-17
መ) የጣዖታት ዕጣ ፈንታ፣ ቁ. 18-21
ሠ) ጌታ ኃላፊነት በማይሰማቸው መሪዎች ላይ ያቀረበው የክስ ጽሑፍ፣ 2:22-3:15
i) የሥርዓተ-አልበኛ መንግሥት መከተል፣ ጌታ ሁሉንም ድጋፍ ሲወስድ ፣ 3፡1-12
ii) ይሄንን ሁሉ ጥፋት ያመጣው የመሪዎች በደል (ኃጢአት)፣ 3፡13-15
ረ) ጌታ በከንቱዎቹና ቸልተኞቹ የኢየሩሳሌም ሴቶች ላይ ያቀረበው የክስ ጽሑፍ፣ 3:16-4:1
ሰ) ጽዮን ነጻች፣ 4:2-6
ሸ) የእግዚአብሔር ፍርድ፣ በኃጢአተኛ ሕዝቡ ላይ፣ ምዕ. 5
i) የወይኑ ቦታ ምሳሌ፣ ቁ. 1-7
ii) እስራኤል ያፈራው ሆምጣጣ ወይን፣ ቁ. 8-23
iii) በአሦራውያን አማካኝነት ሊመጣ ያለው ፍርድ፣ ቁ. 24-30
ቀ) የእስራኤል ፍርድ፣ በነቢያት ዋነኛ ጥሪ ላይ በተካተተው መሠረት፣ ምዕ. 6
i) የነቢዩ ራዕይ፣ ቁ. 1-3
ii) የነቢዩ ምላሽ ለራዕዩ፣ ቁ. 4-5
iii) የእርሱ ስርየት፣ ቁ. 6-7
iv) የእርሱ ተልዕኮ፣ ቁ. 8-9ሀ
v) የእርሱ መልዕክት፣ ቁ. 9ለ-13
ሐ. የአማኑኤል መጽሐፍ (ምዕራፍ 7-12)
i. የአማኑኤል ምልክት፣ ምዕ. 7
ሀ) የላይኛው የኩሬ መስኖ ገጠመኝ፣ ቁ. 1-9
ለ) የዛ ገጠመኝ ቀጣይ ነገር፣ አማኑኤልን የተመለከተ ቃል፣ ቁ. 10-17
ሐ) ተጨማሪ ቀጣይ ነገር፣ የተተነበየው የምድሪቱ ጥፋት፣ ቁ. 18-25
ii. የነውጥ ጊዜያት (734-732 ቅ.ል.ክ) እና እንዴት መገናኘት እንደሚቻል፣ ምዕ. 8
ሀ) የደማስቆና ሶርያ መዘረፍ፣ ቁ. 1-4
ለ) የአሦር ይሁዳን መውረር፣ ቁ. 5-8
ሐ) አማኑኤል ሊሰጥ የሚችለው ደኅንነት፣ ቁ. 9-10
መ) ማን እና ምን መፈራት እንዳለበት፣ ቁ. 11-15
ሠ) በትዕግሥት የመጠበቅ እምነት፣ ቁ. 16-18
ረ) ትክክለኛው መፈክር ለቀኑ፣ ቁ. 19-22
iii. ባለ አራት ስም ሕፃን፣ 9፡1-7
ሀ) ማጠቃለያ፣ ቁ. 1
ለ) ታላቁ ደስታ፣ ቁ. 2-3
ሐ) ምንድነው የተወሰደው? ቁ. 4-5
መ) የታላቁ ደስታ ደራሲ (አስገኚ)፣ ቁ. 6-7
iv. "እጁም ገና ተዘርግታለች፣" 9፡8-10፡4
ሀ) በረከስ ኩራት ሳቢያ፣ በጠላቶች መሸነፍ ይኖራል፣ ቁ. 8-12
ለ) ቀጣይነት ባለው መልኩ ትዕግሥት በማጣት ሳቢያ ከመሪነት መገልበጥ ይኖራል፣ ቁ. 13-17
ሐ) በተዘወተረ ኃጢአተኝነት ሳቢያ የርስ በርስ ጦርነት ይኖራል ቁ. 18-21

መ) ከማኅበራዊ ፍርድ መጓደል የተነሣ የቁጥጥር ቀን ይኖራል፣ 10፡1-4

v. አሦር ወዮለት፣ 10፡5-34
   ሀ) ጉረኛዋ አሦር ከእግዚአብሔር የተሰጣትን ልዩ ተግባር በስሕተት ተረጎመችው፣ ቁ. 5-11
   ለ) የዘገየ ፍርድ ይሄንን ትዕቢተኛ ባለ-ድል ይመታዋል፣ ቁ. 12-14
   ሐ) ስለ ትዕቢተኝነቷ፣ አሦር በዱር እሳት ትቃጠላለች፣ ቁ. 15-19
   መ) ከእግዚአብሔር ፍርድ ጥፋት በኋላ፣ የእስራኤል ቅሬታ ወደ እርሱ ይመለሳሉ፣ ቁ. 20-23
   ሠ) ጽዮን ትድናለች፣ አሦር ስትወድቅ፣ ቁ. 24-27
   ረ) ስልታዊው የአሦር ወደፊት መገስገስ፣ ይኸውም ከሞላ ጎደል ጽዮንን የወሰዳት፣ ከጦር ግንባር እንደ መጣ ዜና ዓይነት ተገልጿል፣ 28-32
   ሰ) ያህዌ ኩሩውን የአሦርን ጫካ ይቆርጣል፣ ቁ. 33-34
   ሸ) ከዳዊት ዘር የሆነው መሢሕና የእርሱ ታላቅ የማዳን ሥራ፣ ምዕ. 11
      i) የመሢሑ መሣርያ፣ ቁ. 1-3ሀ
      ii) እሱ ሥራውን እንዴት እንደሚሠራ፣ ቁ. 3b-5
      iii) የለውጡ (ትራንስፎርሜሽን) ሁኔታ ከተፈጥሯዊው ዓለም ጋር እንኳ ይሰማማል/ይጣጣማል፣ ቁ. 6-9
      iv) የሥራ መዘርዝሩ፣ ለእስራኤል ሊሠራ ያለው፣ ቁ. 10-16
   ቀ) ስለሚመጣው ታላቅ ቀን ምስጋና፣ ምዕ. 12
      i) በእስራኤል በኩል ያለው መረዳት/ውሳኔ ይሄንን ምስጋና ለማቅረብ፣ ቁ. 1-2
      ii) የማጠቃለያ መግለጫ፣ በዛን ቀን ስላለው በረከት፣ ቁ. 3
      iii) ይህን ምስጋና ለማቅረብ ማነሣሻ፣ ቁ. 4-6

## IX. ዋነኛ ሐቆች

ሀ. ኢሳይያስ ይሁዳን በዳዊት ኪዳን ታማኝነት ላይ በተጠያቂነት ይይዘዋል (II ሳሙ. 7) ግን ደግሞ ወደ ዋናው የአብርሃማዊ ኪዳን ዓላማ ተመልሶ ይሄዳል (ዘፍ. 12፡1-3)፣ ይኸውም እግዚአብሔር ዓለምን ለመምረጥ አብርሃምን የመረጠበት። እንዴት ያለው ልዩነታዊ ንጽጽሮሽ ነው፣ ይህ ሁለንተናዊ የያህዌ አገዛዝ መሆን ያለበት። እግዚአብሔር እስራኤልን ብቻ አይመለስም/አይጎበኝም፣ ነገር ግን የእርሷን ተጽዕኖ በዓለሙ ሁሉ ላይ ያሳድራል!

ለ. ኢሳይያስ በተለይ የዓለምን ሁነቶች እንቅስቃሴ ተንብዮአል፣ በገዛ ራሱ ቀን እና በወደፊቱ፣ በዳዊታዊ መንግሥት መመለስ፣ በእግዚአብሔር መሢሕ በኩል ወደሚያመራ (ሚክያስም እንዲሁ)። ይህ መንግሥት ቅዱስና ሁለንተናዊ ነው (ሚክያስም እንዲሁ)። እነዚህ ሁለቱ የኢሳይያስ አሀዳዊ አምላክ፣ ቅዱስ፣ የሚዋጅ መለኮት ገጽታዎች ናቸው።

ሐ. ኢሳይያስ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ በምድራዊ፣ በወደቀ፣ ሰዋዊ ሀብቶች ከታመነ የማይረባ መሆኑን በግልጽ አሳይቷል። መዳን የሚመጣው ከእግዚአብሔር ብቻ ነው!

መ. ኢሳይያስ ሦስቱን እጅግ ብርቱ የሆኑትን የእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ባሕርያት ገልጿል፡
1. የሚመጣው መሢሕ
2. መሢሑ መከራ እንደሚቀበል አጋልጋይ
3. የመሢሑ ሁለንተናዊ ገዥነት

## X. ቃላት/ሐረጋት እና ሰዎች በአጭሩ የሚገለጹ

ሀ. ቃላትና ሐረጋት
1. "ሰማያት ስሙ፣ ምድርም አድምጪ"፣ 1፡2 (NASB እና NIV)
2. "እንደ ጠባቂ ጎጆ፣ በዱባ አትክልት ውስጥ እንዳለ..."፣ 1፡8 (NIV፣ "በዱባ አትክልት ውስጥ እንዳለ ጎጆ")
3. "የመሥዋዕታችሁ ብዛት ለእኔ ምን ይጠቅመኛል? ..." 1፡10-15 (NIV፣ "የመሥዋዕታችሁ ብዛት")
4. "ኑና እንዋቀስ/እንነጋገር..."፣ 1፡18 (NASB እና NIV)
5. "በዘመኑም ፍጻሜ..."፣ 2፡2 (NASB እና NIV)
6. "አሕዛብ ሁሉ ወደ እርሱ ይሰበሰባሉ..." 2፡2-4 (NASB እና NIV)
7. "የአፍንጫ ቀለበት"፣ 3፡21 (NASB እና NIV)
8. "ደመና"፣ 4፡5 (NASB እና NIV)
9. "ማንስ ይሄድልናል?"፣ 6፡8 (NASB እና NIV)
10. "ድንግል"፣ 7፡14 (NIV፣ "ድንግል")
11. "ክፉን ለመጥላት መልካሙን ለመምረጥ ሲያውቅ"፣ 7፡15፣16 (NASB እና NIV)
12. "ለዕንቅፋት ድንጋይና ለማሰናከያ ዓለት"፣ 8፡14 (28፡16) (NASB እና NIV)
13. "የሚያንሾካሹኩትንና ድምጻቸውን ዝቅ አድርገው የሚናገሩትን"፣ 8፡19 (NASB እና NIV)
14. "ለቁጣዬ በትር ለሆነ ለአሦር"፣ 10፡5 (NASB እና NIV)
15. "ቅሬታው ይመለሳል፣ የእነርሱ..."፣ 10፡22 (NASB እና NIV)
16. "ከእሴይ ግንድ ቁጥቋጥ ይወጣል"፣ 11፡1፣10 (NIV፣ "...ከግንድ")
17. "ፀጉራም ፍየሎች"፣ 13፡21፤ 34፡14 (NIV፣ "የምድረ በዳ አራዊት")
18. "በሰሜን ዳርቻ የመሰብሰቢያ ተራራ"፣ 14፡13 (NIV፣ "በተቀደሰው ተራራ ከፍታ ላይ፣ በመሰብሰቢያ ተራራ")
19. "በግብፅ ምድር መካከል ለእግዚአብሔር መሠዊያ"፣ 19፡19 (NIV፣ "... በግብፅ መካከል")
20. አርኤል፣ 29፡1-2፣7 (NASB እና NIV)
21. "ፈጽሞ አጠፋቸው"፣ 34፡2 (NIV፣ "ሙሉ ለሙሉ አጠፋቸው")
22. "ስናጋዬን ባፍንጫህ"፣ 37፡29 (NASB እና NIV)

23. “ኃጢአቴንም ሁሉ ወደ ኋላህ ጣልህ”፣ 38፡17 (NASB እና NIV)
24. “የአምላካችን ቃል ግን ለዘላለም ጸንታ ትኖራለች”፣ 40፡8 (NASB እና NIV)
25. “እርሱ በምድር ክበብ ላይ ይቀመጣል”፣ 40፡22 (NIV፣ “በዙፋኑ በምድር ክበብ ላይ የሚቀመጥ”)
26. “እኔ፣ እግዚአብሔር ፊተኛው፣ በኋለኞችም ዘንድ የምኖር እኔ ነኝ”፣ 41፡4፤ 44፡6 (NASB እና NIV)
27. “ኃጢአትህንም አላስብም”፣ 43፡25 (NASB እና NIV)
28. “ከእኔ ሌላ አምላክ አለን፣ ወይስ ሌላ ዓለት አለን”፣ 44፡8፤ 45፡5 (NIV፣ “ከእኔ ሌላ አምላክ አለን? ዓምባ የለም ማንንም አላውቅም”)
29. “ብርሃንን ሠራሁ፣ ጨለማውንም ፈጠርሁ፤ ደኅንነትን እሠራለሁ፣ ክፋትንም እፈጥራለሁ”፣ 45፡7 (NIV፣ “እኔ ብርሃንን ሠራሁ፣ ጨለማንም ፈጠርሁ፤ እና ብልጽግናን አመጣለሁ፣ ጥፋትንም እፈጥራለሁ”)
30. “እናንተ የምድር ዳርቻ ሁሉ፣ ወደ እኔ ዘወር በሉ፣ ትድኑማላችሁ…”፣ 45፡22 (NASB እና NIV)
31. “ጉልበት ሁሉ ለእኔ ይንበረከካል፣ ምላስም ሁሉ በእኔ ይምላል”፣ 45፡23 (NASB እና NIV)
32. “ስለ እኔ፣ ስለ ራሴ አደርገዋለሁ…” 48፡11 (NASB እና NIV)
33. “በውኑ ሴት ሕፃንዋን ትረሳ ዘንድ ትችላለችን … እሷ ትረሳ ይሆናል፣ እኔ ግን አልረሳሽም”፣ 49፡15 (NASB እና NIV)
34. “የቍጣውን ጽዋ”፣ 51፡17 (NIV፣ “የንዴቱን ጽዋ”)
35. “በእግዚአብሔር እንደ ተቀሠፈ፣ እንደ ተቸገረም…”፣ 53፡4 (NASB እና NIV)
36. “…እግዚአብሔር በደዌ ያደቅቀው ዘንድ ፈቀደ”፣ 53፡10 (NIV፣ “እሱም የእግዚአብሔር ፍቃድ ነው፣ ያደቅቀው እና መከራ ይቀበል ዘንድ”)
37. “ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር የዘላለም ብርሃንሽ”፣ 60፡19-20 (NASB እና NIV)

ለ. ግለሰቦች

1. “የእስራኤል ቅዱሱ” 1:4፤ 41:8-9፤ 42:1፣19፤ 43:10
2. “የጽዮንም ሴት ልጅ” 1፡8
3. “የሠራዊት ጌታ” 1፡9 (NIV፣ “ሁሉን የሚችል አምላክ”)
4. "የእግዚአብሔር ቍጥቋጥ" 4:2
5. ሱራፌል 6:2 (NIV፣ "ሱራፌል")
6. ሺር-ጃሹብ (ያሱብ) 7:3
7. አማኑኤል 7:14
8. ማሀር-ሻላል-ሃሽ-ባዝ 8:3
9. "ሁሉን የሚችል አምላክ" (El Shaddai) 13:6
10. "አንተ የንጋት ልጅ፣ አጥቢያ ኮከብ ሆይ" 14:12
11. "ከምስራቅ አንዱን" 41:2፣25 (44:28፤ 45:1)
12. "ባሪያዬ" 41:8፣9፤ 42:1፣19፤ 43:10፤ 52:13
13. ቤል…ናባው 46:1
14. ጉበኞች 52:8
15. ጃንደረባ 56:3


## XI. የካርታ ስፍራዎች

1. ተርሴስ 2፡16 (NIV፣ “የንግድ መርከቦች”)
2. የኤፍሬም ነገድ 7፡2
3. የጽዮን ተራራ 8:18
4. የዛብሎን ነገድ 9:1
5. ገሊላ 9:1
6. ከርከሚሽ 10:9
7. ሴላ 16:1፤ 42:11
8. ዞአን/ጣኔዎስ 19:13
9. ሜምፎስ 19:13
10. ኔጌቭ 21:1 (NIV፣ “ኔጌቭ”)
11. ቴማን 21:14
12. ጢሮስ 23:1
13. ሲዶን 23:2
14. አራባ 35:1 (NIV፣ “ምድረ-በዳ”)
15. ቀርሜሎስ ተራራ 35:2
16. ሳሮን 35:2
17. አራራት 37:38
18. ቶቤል 66:19
19. ያዋን 66:19 (NIV፣ ግሪክ)


## XII. የተማሪ ይዘት ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር ለምን ሕዝቡን ወደ ፍርድ ቤት ያመጣል? ምን አደረጉ? (ምዕ. 1)
2. እግዚአብሔር መሥዋዕትን ይቃወማልን? (1፡10-15)
3. 5፡1-7 እጅግ ብርቱና አነሣሽ(ስሜትን የሚቀሰቅስ) ለምን እንደሆነ ግለጽ?

4. የኢሳይያስ መጠራት ለምን እስከ ምዕራፍ 6 ድረስ አልተጠቀሰም?
5. ኢሳይያስ የዕብራይስጡን ቃል "ድንግል" 7፡14 ላይ ለምን አልተጠቀመም?
6. ከምዕራፍ 7-12 ያሉትን ስፍራዎች ዘርዝር፣ ሕፃኑ አዲሱን ዘመን ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋለበት።
7. ለሰሜኖቹ ነገዶች የተሰጡትን ሦስት መጠሪያዎች አብራራ፣ 9፡8-9 ላይ ጥቅም ላይ የዋሉትን።
8. የባቢሎን መውደቅ ምዕራፍ 13 ላይ ለምን ተጠቀሰ፣ ኢሳይያስ ምዕራፍ 10 ላይ ስለ አሦር እያብራራ ሳለ?
9. ኢሳ. 14 እና ሕዝ. 28 ከሰይጣን ጋር እንዴት ይዛመዳሉ?
10. የምዕራፍ 36-39 ታሪካዊ መቼት አብራራ።
11. 40፡1-2 የእግዚአብሔር ሕዝብ በግዞት መሆኑን ያመለክታልን? እንደዚያ ከሆነ፣ ይህ ከደራሲነቱ ጋር እንዴት ይዛመዳል?
12. የ42፡1 ባሪያ ከኢየሱስ ጋር እንዴት ይዛመዳል፣ የቁ. 19 ግን ሳይሆን?
13. 52፡13-53፡12 ከኢየሱስ ጋር እንዴት ይዛመዳል? ከእስራኤልስ?
14. የምዕራፍ 56-66 መልክዓ ምድራዊ መቼት ምንድነው?


ANCIENT
NEAR EAST
N
S
E
W

# PALESTINE



# መግቢያ ለትንቢተ ኤርምያስ

I. የመጽሐፉ ስም

ሀ. የተሰየመው ነቢዩን ተከትሎ ነው።

ለ. የስሙ ፍችም፡
1. "ያህዌ በኃይል ይወረውራል"
2. "ያህዌ ይመሠርታል"

II. ቅዱስ ቃልነቱ (ካኖናዊነት)

ሀ. እሱም የዕብራይስጥ ካኖን "ነቢይ" የሚባለው ምድብ፣ ክፋይ ነው።

ለ. በራቢያዊ ሥነ-ጽሑፍ እሱ ዘወትር የነቢያት ቀዳሚ ተደርጎ ነው የሚወሰደው (ማቴ. 27፡9)።

III. ዘውግ

ሀ. ይህ መጽሐፍ በበርካታ ዘውጎች የተበጀ ነው፡
1. ጥንታዊ (ክላሲካል) የዕብራይስጥ ቅኔ (የኤርምያስ ትንበያዎች)
2. የዕብራይስጥ ዝርው (በባሮክ የተጻፈ፣ በሦስተኛ መደብ)
3. የኤርምያስ ስብከት ማጠቃለያ፣ ዘወትር በዝርው (ደግሞም ከባሮክ)
4. ግለ-ታሪካዊ ይግባኞች፣ ለእግዚአብሔር፣ በቅኔአዊ መልኩ (የኤርምያስ ንስሐ/ኑዛዜ)

ለ. ኤርምያስ በግልጽ ሁለቱንም፣ የቃልና የጽሑፍ ትንቢቶችን ያካትታል። ደግሞም ከምዕራፍ 36 እንደምንረዳው አንዳንዶቹ ድጋሚ ተብለው ተጽፈዋል/ተቀድተዋል።

IV. ደራሲነቱ

ሀ. ኤርምያስ ምዕራፍ 52ን አለመጻፉ ግልጽ ነው፣ በቁ. 31-34 ምክንያት፣ እሱም በባቢሎን የተከሰተው ሁነት የተመዘገበበት። ኤርምያስ በአይሁድ አማጽያን ወታደራዊ ኃይላት ተገድዶ ወደ ግብፅ ተወስዷል፣ ከጎዶልያስ ሞት በኋላ፣ የባቢሎናውያን ገዥ ከነበረው።

ለ. ታሳቢ ደራስያን/አዘጋጆች፡
1. ኤርምያስ
2. ባሮክ - የእርሱ ጸሐፊ
3. ኋለኛ አዘጋጅ (ዕዝራ ወይም የታላቁ ምኩራብ ሰዎች)

ሐ. ስለ ኤርምያስ ብዙ እናውቃለን፣ ከሌሎቹ ነቢያት ይልቅ፡
1. ከካህን ዘር (የተጋዘ) ከአብያታር መሆኑ፣ I ነገ. 2:26-27።
2. ለኢየሩሳሌም ቅርብ በሆነው ዓናቶት ማደጉ።
3. በወጣትነቱ በእግዚአብሔር የተጠራ፣ 1:2፤ 25:3 (627 ቅ.ል.ክ)።
4. የሆሴዕና የዘዳግም ሥራዎች ተጽዕኖ ያለበት።
5. እኩያነቱም ከ፡
   ሀ. ዳንኤል　　　　መ. ሶፎንያስ
   ለ. ሕዝቅኤል　　　ሠ. ናሆም
   ሐ. ዕንባቆም
6. ከተጠራ ከአምስት ዓመት በኋላ "የሕጉ መጽሐፍ" በመቅደስ ተገኘ፣ በኢዮስያስ ተሐድሶ ጊዜ። የሚያስገርመው ነገር፣ ግንኙነታቸው በቅዱስ ቃሉ ፈጽሞ አለመጠቀሱ ነው። የሕጉ መጽሐፍ ሲገኝ ንጉሡ ሕልዳና የተባለችውን ነቢይት አማከረ (II ነገሥ. 22:14-20) ኤርምያስን ሳይሆን።
7. ስሜቱ በግልጽ ይታያል፣ በኑዛዜው ወይም በአቤቱታው፡
   ሀ. 11:18-12:6
   ለ. 15:10-21
   ሐ. 17:14-18
   መ. 18:18-23
   ሠ. 20:7-18
8. እሱም በኃይል ተገድዶ ወደ ግብፅ ተወስዷል፣ በአይሁድ ስደተኞች እንዲገደል፣ 43፡6።

V. ጊዜው

ሀ. ኤርምያስ የተወለደው ዓናቶት ነው፣ በ640 ቅ.ል.ክ አካባቢ።

ለ. የኤርምያስ መጽሐፍ ጊዜው 1:2 ላይ ተመልክቷል፣ የሚሸፍነውም ከኢዮስያስ አስራ ሦስተኛ ዓመት እስከ ጎዶልያስ ጊዜ፣ 627 ቅ.ል.ክ - 582 ቅ.ል.ክ። ኤርምያስ ምን ያህል ጊዜ በግብፅ ከስደተኞቹ ጋር እንደኖረ ርግጠኝነት የለውም።

ሐ. ላችኒሽ የተገኘው ጽሑፍ እንደሚገልጸው ከበባው በ587 ቅ.ል.ክ ነው። የእርሱ የዕብራይስጥ ጽሑፍ ዓይነት ከኤርምያስ ጋር ተነጻጻሪ ነው።

መ. የኤርምያስ መልእክት የሚያተኩረው ከሰማርያ መውደቅ አንሥቶ (722 ቅ.ል.ክ) እስከ ኢየሩሳሌም መውደቅ (586 ቅ.ል.ክ) ባሉት ሁነቶች ላይ ነው።

VI. ታሪካዊ መቼት

ሀ. 686 ቅ.ል.ክ. - ምናሴ (686-641 ቅ.ል.ክ) የይሁዳ ንጉሥ ሆነ። እሱ የይሁዳ እጅግ ኃጢአተኛ ንጉሥ ነበር።
ለ. 664 ቅ.ል.ክ. - የግብጽ ኢምፓየር ጥንካሬ አገኘ፣ በሳሜቲከስ (664-610 ቅ.ል.ክ.)።
ሐ. 648 ቅ.ል.ክ. - የኢዮስያስ ልደት።
መ. 642 ቅ.ል.ክ. - አሞን፣ የይሁዳ ንጉሥ በአገልጋዮቹ ተገደለ (II ነገሥ. 21:19-26)።
ሠ. 640 ቅ.ል.ክ. - የመጨረሻው ስኬታማ/የተከናወነለት የአሦር ገዥ፣ አሹርባኒፓል ሞተ።
ረ. 640 ቅ.ል.ክ. - ኢዮስያስ ንጉሥ ሆነ፣ በ8 ዓመቱ (II ነገሥ. 22:1)።
ሰ. 628 ቅ.ል.ክ. - ኢዮስያስ ተሐድሶን አነሳሣ (II ዜና. 34:3፤ II ነገሥ. 23)።
ሸ. 626 ቅ.ል.ክ. - የኤርምያስ መጠራት (ኤር. 1:2)።
ቀ. 626 ቅ.ል.ክ. - ናቦፖላሳዝ (626-605 ቅ.ል.ክ.) የአዲሱ ባቢሎን ንጉሥ ሆነ።
በ. 621 ቅ.ል.ክ. - የሕጉ መጽሐፍ ተገኘ፣ መቅደሱን ዳግም በሚሠሩት ሠራተኞች (II ዜና. 34:8፤ II ነገሥ. 22)።
ተ. 614 ቅ.ል.ክ. - የአሦር ክልላዊ ዋና ከተማ፣ አሸር፣ በአዲሲቷ ባቢሎን እጅ ወደቀ።
ቸ. 612 ቅ.ል.ክ. - ነነዌ፣ የአሦር ቀዳሚ ከተማ፣ በአዲሱ ባቢሎንና በሜዶን ተደመሰሰ።
ኀ. 609 ቅ.ል.ክ. - ኢዮስያስ በሜጊዶ ተገደለ፣ ፈርዖን ኒካው IIን በመቃወም (610-594 ቅ.ል.ክ.) እሱም የአሦር ቅሬታ ሠራዊት እንዲያመልጥ ለመርዳት በመሞከሩ (II ዜና. 35:20-24፤ II ነገሥ. 23:28-30)።
  - ኢዮአሃዝ II (609 ቅ.ል.ክ.)፣ የኢዮስያስ ልጅ፣ በአባቱ ቦታ ነገሠ፣ ነገር ግን ለሦስት ወራት ብቻ። ፈርዖን ኒካው ወደ ግብፅ አጋዘው።
  - ኢዮአኪም (609-598 ቅ.ል.ክ.) በይሁዳ ዙፋን ላይ ተቀመጠ፣ በፈርዖን ኒካው። እሱም በይሁዳ ዙፋን ላይ ተተወ፣ በናቡከደነፆር II በ 605 ቅ.ል.ክ። ኋላ ላይ ዓመጸ፣ ከግብፅ ጋር ኅብረት በመፍጠር። ልጁ፣ ኢዮአኪም፣ በእርሱ ፋንታ ነገሠ፣ ነገር ለሦስት ወር ብቻ፣ እናም በናቡከደነፆር አማካኝነት በሴዴቅያስ ተተካ፣ በ597 ቅ.ል.ክ።
ነ. 605 ቅ.ል.ክ. - አዲሱ ባቢሎን ግብፃውያንንና የአሦርን ሠራዊት ቅሬታ በከርከሚሽ አሸነፈ።
አ. 605 ቅ.ል.ክ. - ናቡከደነፆር II በፍልስጥኤም ውስጥ ተንቀሳቀሰ፣ ግብርና መዋጮ እየወሰደ (ዳንኤልንና የመጀመሪያውን ግዞተኛ ወሰደ)። አራት ወረራዎች ነበሩ፣ ይሁዳንና ኢየሩሳሌምን የጎዱ፣ 605፣ 597፣ 586 እና 582 ቅ.ል.ክ።
ከ. 601 ቅ.ል.ክ - ናቡከደነፆር II በውጊያ ድል ሆነ፣ ግብፅን ለመቆጣጠር በተደረገው (ወደፊት መግፋት አልቻለም)።

VII. ጽሑፋዊ ምድቦች

ሀ. የመጽሐፉ አወቃቀር ርዕሰ-ጉዳያዊ ወይም ጭብጣዊ እንጂ፣ ቅደም ተከተላዊ አይደለም። እሱ ምናልባት በርከት ያሉ የተለያዩ ጥቅሎች/መልዕክቶች ስብስብ ሊሆን ይችላል፣ በኤርምያስ፣ 1-25፣ 30-33 እና 46-51።

ለ. LXX እና ማጽ/ኤምቲ እጅግ ይለያያሉ። 3000 ቃላት አካባቢ ኤምቲ ላይ ያሉ፣ LXX ላይ አልተገኙም። ደግሞም ምዕራፍ 46-51 ላይ ያለው የመንግሥታት/ሕዝቦች ቅደም ተከተል የተለየ ነው፣ ብሎም የእነርሱ አቀማመጥ፣ በመጽሐፉ ላይ፣ ከምዕራፍ 25 በኋላ። ሁለቱም የኤምኤስኤስ ወጎች በሙት ባሕር ጥቅሎች ላይ ተገኝተዋል።

ሐ. ያልተጠናቀቀ የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር (በመሠረቱ ሃሪሰንንናያንግን የሚከተል)፡
1. ምዕራፍ 1 - የኤርምያስ መጠራትና የተሰጠው ተግባር።
2. ምዕራፍ 2-25 - የይሁዳ ኃጢአት፣ ከኤርምያስ አገልግሎት ቀደምት ዓመታት።
3. ምዕራፍ 26-29፤ 34-35 - የነቢዩ ግላዊ ሕይወት።
   ሀ. የያህዌ መልዕክት ለሴዴቅያስ፣ እና የሐናንያ ምላሽ/ተቃውሞ፣ 26-29።
   ለ. ሬካባውያን፣ 34-35
   ሐ. ታሪካዊ ሁነቶች፣ ከኢዮአኪም -ሴዴቅያስ አገዛዝ፣ እና ጎዶልያስ እና ወደ ግብፅ፣ 36-45
4. ምዕራፍ 30-33 - የእግዚአብሔር ሕዝብ መመለስ ተስፋ፡
   ሀ. አካላዊ
   ለ. መንፈሳዊ
5. ምዕራፍ 46-51 - በአካባቢው አገሮች ላይ ትንቢት (ደግሞም ምዕራፍ 25፡12-38)፡
   ሀ. ግብፅ - 46 (ኢሳ. 19፤ ሕዝ. 29-32)
   ለ. ፍልስጥኤም - 47 (አሞጽ 1:6-8፤ ኢሳ. 14:29-32፤ ሕዝ. 25:15-17)
   ሐ. ሞአብ - 48 (አሞጽ 2:1-3፤ ኢሳ. 15-16፤ ሕዝ. 25:8-11)
   መ. አሞን - 49:1-6 (አሞጽ 1:13-15፤ ሕዝ. 25:1-7)
   ሠ. ኤዶም - 49:7-22 (አሞጽ 1:11-12፤ ኢሳ. 21:11-12፤ ሕዝ. 25:12-14፤ አብድዩ)
   ረ. ሶርያ - 49:23-27 (አሞጽ 1:3-5፤ ኢሳ. 17:1-3)
   ሰ. ዓረብ - 49:28-33
   ሸ. ኤላም - 49:34-38
   ቀ. ባቢሎን - 50-51 (ኢሳ. 13:1-14፤ ዕን. 2:6-17)
6. ምዕራፍ 52 - የኢየሩሳሌም መውደቅ (II ነገሥ. 24:18-25:30)

መ. ሲያስተውሉት የሚያስገርመው፣ ምዕራፍ 1-25 የኤርምያስ መልዕክት የሚተዋወቅበት ሐረግ፣ “የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ መጣ” የሚል ሲሆን ምዕራፍ 26-51 ደግሞ የሚያስተዋውቀው፣ “የእግዚአብሔር ቃል ወደ ኤርምያስ መጣ” የሚል መሆኑ ነው።

ሠ. የኤርምያስ ትንቢቶች ሰንጠረዥ/ዝርዝር በገዥው ንጉሥ፡

| | ኢ.ጄ. ያንግ፡ | አር.ኬ. ሃሪሰን፡ |
|---|---|---|
| 1. በኢዮስያስ (640 ቅ.ል.ክ - ) | 1:1-19፤ 2:1-3:5፤ 3:6-6:30፤ 7:1-10:25፤ 11:1-13:27፤ 14:1-15:21፤ 16:1-17:27፤ 18:1-20:18 | 1:1-19፤ 2:1-3:5፤ 3:6-6:30፤ 7:1-10:25፤ 18:1-20:18 |
| 2. በኢዮአሃዝ (609 ቅ.ል.ክ) | | |
| 3. በኢዮአቄም (609 ቅ.ል.ክ) | 25፤ 26፤ 27፤ 35፤ 36፤ 45 46-49 | 11:1-13:14፤ 14:1-15:21፤ 16:1-17:27፤ 22፤ 23፤ 25፤ 26፤ 35፤ 36፤ 45፤ 46-48 |
| 4. በዮአኪን (598 - 596 ቅ.ል.) | | 31:15-27 |
| 5. በሴዴቅያስ (597 ቅ.ል.ክ) | 21:1-22:30፤ 23፤ 24፤ 27 28፤ 29፤ 30-31፤ 32፤ 34፤ 37፤ 38፤ 39 | 21:1-22:30፤ 24:1-10፤ 27፤ 28፤ 29፤ 30-31፤ 32፤ 33፤ 34፤ 37፤ 38፤ 39፤ 49፤ 50:1-51:64 |
| 6. በጎዶልያስ | 40፤ 41፤ 42፤ 43-44:30፤ 50-52 | 40:1-42:22፤ 43:1-44:30 |
| 7. ታሪካዊ ዕዝል | 52፡1-34 | |

VIII. ዋነኛ ጭብጭ

ሀ. የፍርዱ ሰዓት አሁን የሆነው፣ ይሁዳ ንስሐ ባለመግባቱ ምክንያት ነው! ኤርምያስ ለኃጢአት፣ ለፍርድ ከዚያም ለመመለስ አጽንዖት ይሰጣል፤ 1፡4-10።

ለ. የአምልኮ ሥርዓታዊ ወይም አምልኳዊ ሃይማኖት፣ በእግዚአብሔር ላይ ባለ የእምነት ግላዊ የአኗኗር ስልት ካልሆነ ጥፋት ነው! (ምዕ. 7፤ ኢሳ. 29፡13)።

ሐ. ይሁዳ ተስፋ-ቢስ በሆነ መንገድ መንገዷን በአምልኮ ሥርዓት፣ በአመንዝራነት እና በኃጢአት ምክንያት አጣች! እሷ የእግዚአብሔርን ኪዳን አፈረሰች፣ በጋብቻ ውል/መተሳሰር ተምሳሌት የሆነውን (ዝከ. 2፡1-3፡5)።

መ. ግላዊ ንስሐና እምነት የእግዚአብሔር አዲስ ኪዳን መሠረቶች ናቸው (31፡31-34) የቤተሰብ እምነት ሳይሆን (31፡29፤ ሕዝ. 18)።

ሠ. አዲሱ ኪዳን የጸና ነው (31፡35-37) ምክንያቱም እሱ በሰው ሥራ ላይ የተመሠረተ ስላልሆነ፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋና ኃይል እንጂ (ሕዝ. 36፡26-27)።

IX. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት እና ሰዎች በአጭሩ የሚገለጹ (NASB)

ሀ. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት

1. ነቢይ፣ 1፡5 (NASB እና NIV)
2. የለውዝ ዛፍ/በትር፣ 1፡11(NASB እና NIV)
3. ሰሜን፣ 1፡13 (NASB እና NIV)
4. ወገብህን ታጠቅ፣ 1፡17 (NIV፣ “ራስህን አዘጋጅ!”)
5. የፍች ጽሑፍ ፣ 3፡8 (NIV፣ “የፍች ወረቀት”)
6. “ከድንጋይና ከግንድ ጋር አመነዘረች፣” 3፡9 (NASB እና NIV)
7. “የልባችሁን ሸለፈት፣” 4፡4 (NIV፣ “ልባችሁን ተገረዙ”
8. “የገለዓድ የሚቀባ መድኃኒት፣” 8፡22 (NASB እና NIV)
9. “ፀጕራቸውን በዙሪያ የተላጩትን፣” 9፡26 (NIV፣ “በሩቅ ስፍራዎች”)
10. “ሕያው እግዚአብሔርን፣” 12፡16 (NASB እና NIV)
11. “አጥፊውም በቀትር፣” 15፡8 (NIV፣ “በቀትር ጊዜ አጥፊውን አምጥቻለሁ”)
12. “የሰማይ ሠራዊት ሁሉ፣” 19፡13 (NIV፣ “ሰማያዊ/ኮከባዊ ሠራዊት ሁሉ”)
13. ፈጽሞ ማጥፋት፣ 25፡9 (NIV፣ “ሙሉ ለሙሉ ማጥፋት”)
14. “የእግዚአብሔር ቤት ዕቃዎች፣” 27፡16 (NIV፣ “ቁሳቁስ...”)
15. “የያዕቆብ የመከራ ዘመን፣” 30፡7 (NIV፣ “የያዕቆብ የችግር ጊዜ”)
16. አዲስ ቃል ኪዳን፣ 31፡31 (NASB እና NIV)

17. "እምቦሳውን ቆርጠው በቁራጩ መካከል ባለፉ ጊዜ፣" 34፡18 (NIV፣ እምቦሳውን ለሁለት ቆርጠው፣ ከዚያም በቁራጩ መካከል ሲያልፉ")

ለ. ሰዎች


1. ኢዮስያስ፣ 1:2፣3
2. ኢዮአቄም፣ 1:3
3. በአል፣ 2:8
4. ምናሴ፣ 15:4
5. ናቡከደነፆር፣ 21:2፣7
6. ሐናንያ፣ 28:1
7. ባሮክ፣ 32:12፣13፣16
8. ሞሎክ፣ 32:35
9. ሬካባውያን፣ 35:1 (NIV፣ "የሬካባውያን ወገን")
10. ኤቤሜሌክ፣ 38:7
11. ጎዶልያስ፣ 39:14 እና 40-41
12. ፈርዖን ኒካው፣ 46:2 (NIV፣ "ኒኮ")
13. ካሞሽ፣ 48:7፣13፣46
14. ወልደ አዴር፣ 49:27
15. ቤል፣ 50:2፤ 51:44
16. ሜሮዳክ፣ 50:2

X. የካርታ ስፍራዎች (አመላካቾች)


1. አናቶት፣ 1:1
2. ኬቲም
3. ሜምፊስ
4. ሴሎ፣ 7:12
5. የሄኖም ልጆች ሸለቆ፣ 7:31
6. ሰዶም እና ገሞራ፣ 23:14
7. ጢሮስ፣ 25:22
8. ለኪሶን፣ 34:7
9. ምጽጳ፣ 40:6
10. ገባዖን፣ 41:12
11. ቤተ ልሔም፣ 41:17
12. ከርከሚሽ፣ 46:2
13. ቤቴል፣ 48:13
14. ሐዞር/አሶር፣ 49:28
15. ኤላም፣ 49:34

XI. የተማሪ ይዘት ጥያቄዎች

1. የኤርምያስን የፍሬ ሐሳብ ዝርዝር ለማዘጋጀት እጅግ የሚያስቸግረው ለምንድነው?
2. ኤርምያስ ምን ያህል ጊዜ ሰበከ?
3. የ1፡11-16ን ሁለቱን ራዕዮች አብራራ።
4. ምዕራፍ 2 እንደ ፍርድ ቤት ጉዳይ ለምን ቀረበ? (ዝከ. 4-8፣ 9፣ 29)
5. ምዕራፍ 3 ለምን እንደ ፍቺ ጉዳይ ቀረበ?
6. እግዚአብሔር ንስሐን ለማሳየት የጠየቃቸውን አራት ሁኔታዎች ዘርዝር፣ 4፡1-2 ላይ።
7. ምዕራፍ 7 እና 26 እንዴት ይዛመዳሉ?
8. ኤርምያስ መሥዋዕታዊ ሥርዓቱን ኮንዷልን/አውግዟልን፣ ምዕራፍ 7 ላይ?
9. የኤርምያስ የከተማው ሰዎች ለምን ሊገድሉት ሞከሩ? (ምዕራፍ 11-12)
10. 12፡14-17 እና 16፡19-21 እጅግ ጠቃሚ የሚሆነው ለምንድነው?
11. የማኅበሩ/የአጠቃላዩ እና የግለሰብ ኃጢአት እንዴት እንደሚዛመድ አብራራ፣ 16፡10-13 ላይ
12. 17፡10 ከገላ. 6፡7 ጋር እንዴት ይዛመዳል?
13. ኤርምያስ የሸክላ ሠሪውን ዘይቤ/ምሳሌ የተጠቀመበትን የተለያዩ መንገዶች ግለጽ፣ ምዕራፍ 18 እና 19 ላይ


ANCIENT
NEAR EAST
N
S
E
W

# PALESTINE



# መግቢያ ሰቆቃወ ኤርምያስ

I. የመጽሐፉ ስም

ሀ. በዕብራይስጥ (ኤምቲ) ርዕሱ የመጽሐፉ የመጀመሪያ ቃል ነው፣ እሱም "ኧሽ እንዴት" ['echah ] (ዝኪ. 1:1፣ 2:1፣ 4:1)። ይህም ቀብር ላይ የተለመደ ቃል ነው።

ለ. በሴፕቱዋጂንት (LXX) ርዕሱ "የወዮታ ጩኸት" ነበር፣ ከግሪክ ሥር "አሰምቶ መጮኸ" ከሚለው።

ሐ. ታልሙድ እሱን የሚጠራው "ሰቆቃ" በሚል ነው።

መ. ቫልጌት ርዕስ የሰጠው "እሱ የያዘው የነቢዩ ኤርምያስን ሰቆቃ ነው" የሚል ነው።

II. ቅዱስ ቃልነቱ (ካኖናይዜሽን)

ሀ. እሱም በልዩ ከተመዘገቡ መጻሕፍት ዝርዝር ነው፣ ከጽሑፋዊ ምድብ፣ ከዕብራይስጥ ካኖን Megilloth (አምስቱ ጥቅሎች) ከሚባለው። እያንዳንዳቸው በዓመታዊ የበዓል ቀናት ይነበባሉ፡
1. መኃልየ መኃልይ - ፋሲካ
2. ሩት - በዓለ ኀምሳ (ጰንጠቆስጤ)
3. መክብብ - የዳስ (የድንኳን) በዓል
4. አስቴር - ፉሪም
5. ሰቆቃወ-ኤርምያስ - የኢየሩሳሌም መውደቅ እና የሰሎሞን መቅደስ መፍረስ

ለ. የዕብራይስጥ ካኖን ጽሑፋዊ ምድብ መኃልየ መኃልይን የሚያስቀምጠው ከመዝሙር፣ ከምሳሌ፣ እና ከኢዮብ በኋላ እና ከሩት፣ ከሰቆቃወ ኤርምያስ፣ ከመክብብ እና ከአስቴር በፊት ነው። የእንግሊዝኛው መጽሐፍ ቅዱስ የLXX ቅደም ተከተል ይከተላል።

ሐ. ሰቆቃ የሚነበበው በአብ 9 (በሐምሌ እኩሌታ) ነው፣ የሰሎሞን መቅደስ በናቡከደነፆር II ሠራዊት በ586 ቅ.ል.ክ የፈረሰበትን ለማስታወስ። በኋለኛው ይሁዲነት እሱ ደግሞ የኢየሩሳሌምን በሮሜ ጀነራል፣ በቲቱስ በ70 ዓ.ም መውደቅ ይታሰባል።

III. ዘውግ

ሀ. እያንዳንዳቸው አምስቱ ምዕራፎች፣ የተነጠሉ/ለየብቻ የሆኑ ወዮታ/የቀብር ሙሾ ናቸው። እነዚህን የመሰሉ ግጥሞች በጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ የተለመዱ ናቸው፣ ወደ ሱሜር ተመልሰው የሚሄዱ። ለእስራኤል የሚገልጹት በወቅቱ ሁኔታ ማዘንን ነው፣ ነገር ግን ለመጻዒው ተስፋ ማድረግን።

ለ. የመጀመሪያዎቹ አራት ግጥሞች የቃላት ዕንቆቅልሽ ናቸው። እያንዳንዱ ስንኝ/መስመር የሚጀምረው በዕብራይስጥ የፊደል ገበታ ቀጣይ ፊደል ነው። ይህም በተምሳሌትነት ፍጹም የሆነ ኀዘንን መግለጫ መንገድ ነው።

ሐ. የዕብራይስጥ ቅኔ የተመሠረተው በሐሳብ ትይዩነት ላይ ነው፣ በዜማ ላይ ሳይሆን።
1. ስንኙ/መስመሩ ነው እንጂ ቃላት አይደሉም፣ ጽሑፋዊ ቁልፉ።
2. ትይዩነቱ ዘወትር ሁለት ወይም ሦስት ስንኝ/መስመር ነው።
   ሀ. ተመሳሳይ ትይዩ -- ስንኞቹ አንድ ዓይነት አስተሳሰብን በተለያዩ ቃላት ይገልጻሉ
      (1) መዝ. 3:1፤ 8:40፤ 83:14፤ 103:3
      (2) ምሳ. 20:1
      (3) ሰቆ. 1:2፣ 3
      (4) ኢሳ. 1:3
      (5) አሞጽ 5:24
   ለ. ተቃራኒ ትይዩ -- ስንኞቹ/መስመሮቹ የሚገልጹት ተቃራኒ አስተሳሰቦችን ነው፣ ተቃርኖን በመጠቀም፣ ወይም የአንድን ጉዳይ አዎንታዊ እና አሉታዊ በማስቀመጥ።
      (1) መዝ. 1:6፤ 90:6
      (2) ምሳ. 1:29፤ 10:1፣ 12፤ 15:1፤ 19:4
   ሐ. ድብልቅ ትይዩ -- ስንኞቹ ሐሳቡን ያጎለብታሉ
      (1) መዝ. 1:1-2፤ 19:7-9
      (2) ሰቆ. 1:4

IV. ደራሲነት

ሀ. መጽሐፉ ራሱ ደራሲውን አይገልጽም። እሱ የተጻፈው የኢየሩሳሌም ከበባ እና መውደቅ፣ በ586 ቅ.ል.ክ የዓይን ምስክር በሆነ ሰው መሆኑ ግልጽ ነው።

ለ. ባባ ባትራ 15ሀ እና ታርጉምስ ኤር. 1፡1 ደራሲነቱን ለኤርምያስ አድርጎታል።

ሐ. ሴፕቱዋጂንት ለመጽሐፉ በሰጠው መግቢያ ላይ፣ "ይህ የሆነው እስራኤል ወደ ግዞት ከተወሰደና ኢየሩሳሌም የፍርስራሽ ክምር ከሆነች በኋላ ነው፤ ኤርምያስም ተቀምጦ እያለቀሰ ነው፣ ይሄንን ወዮታ ለኢየሩሳሌም ያዘጋጀው፣ እንዲህ ሲል..." እሱም መጽሐፉን ለኤርምያስ ሰጥቶታል።

መ. ቫልጌት በመጽሐፉ መግቢያ ላይ፣ “እሱም ያቀናበረው የነቢዩን ኤርምያስ ሰቆቃ ነው” የሚል አለው።

ሠ. ፔሺታ (የ5ኛ ክፍለ ዘመን ዓ.ም የሶርያ ትርጉም) ለመጽሐፉ የሰጠው ርዕስ “የነቢዩ ኤርምያስ ሰቆቃ መጽሐፍ” የሚል ነው።

ረ. የደራሲነት ማስረጃዎች፡
1. ለኤርምያስ፡
   ሀ. ኤርምያስ ደራሲው ነው ተብሎ የሚታሰበው በII ዜና. 35:25 ምክንያት ነው። ነገር ግን ይህ የሚያመለክተው ለኢዮስያስ የሆነውን የልቅሶ ግጥም ነው እንጂ፣ ለኢየሩሳሌም አይደለም።
   ለ. ኤርምያስ ላይ በርካታ ምንባቦች የእርሱን ኀዘኔታ ይናገራሉ፣ ስለ እሱ ጊዜ ሁኔታ፣7:29፤8:21፤ 9:1፣10፣20 (ሰቆ. 3:48-51)።
   ሐ. የቃላት ተመሳሳይነት አለ።
   መ. 3፡1 ላይ ያለው “እኔ” ኤርምያስን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።
   ሠ. ደራሲው በግልጽ የኢየሩሳሌምን መውደቅ የታዘበ የዓይን ምስክር መሆኑ ግልጽ ነው።
2. የኤርምያስ መሆኑን በመቃወም፡
   ሀ. ኤርምያስ የሚለው፣ እግዚአብሔር ባቢሎንን የላከው ለፍርድ ነው፣ ነገር ግን 3፡59-66 የተለየ ይመስላል።
   ለ. ኤርምያስ ትንቢታዊ መልዕክት እንደተቋረጠ አላለም፣ 2፡9ሐ።
   ሐ. ኤርምያስ ከግብፅ ስለሚገኘው ዕርዳታ ድጋፍ አላሳየም፣ 4፡17።
   መ. ኤርምያስ በሴዴቅያስ ተስፋ አላደረገም፣ 4፡20።
   ሠ. እነዚህ ውስጠ-ወይራዊ ዘይቤ ግጥሞች በጽኑ የተዋቀሩ ናቸው፣ ይኸውም ከኤርምያስ ግብታዊ ስልት እጅግ የሚለዩ።
   ረ. የእያንዳንዱ የአምስቱ ግጥሞች የአወቃቀር ስልት ደግሞ ይለያል። አንዳንዶቹ ረጅም ስንኝ አላቸው፣ አንዳንዶቹ ደግሞ አጭር። በአንድ ዓይነት ፊደል የሚጀምሩት የስንኞቹ ቁጥር ይለያያል። ዘይቤዎቹም ከግጥም ወደ ግጥም ይለያያሉ። ይሄ ሁሉ ከአንድ ደራሲ በላይ መሆኑን ያመለክታል።

V. ጊዜው

VI. /ታሪካዊ መቼት/

ሀ. ታሪካዊው ሁኔታ የኢየሩሳሌም በባቢሎን ሠራዊት እጅ መውደቅ ነው፣ በ586 ቅ.ል.ክ።

ለ. ለታሪካዊ መቼት II ነገሥት 25:8-12 እና ኤር. 52 ተመልከት።

ሐ. አንዳንዶች ይሄንን መጽሐፍ የሚመለከቱት፣ በይሁዳ ከቀሩት አይሁድ ጋር በተዛመደ ነው፣ እነርሱም በየዓመቱ የኢየሩሳሌምን መውደቅ ከሚያስቡት፣ ኤር. 41፡4-5።

VII. ጽሑፋዊ ምድቦች

ሀ. ኢየሩሳሌም ከሚስት እስከ ባርያ/አገልጋይ ሰውኛ ዘይቤ ተጽፋለች፣ ምዕራፍ 1

ለ. መታደል ኃላፊነትን/ተጠየቂነትን ያመጣል፣ የያህዌ ኪዳን ቁጣ፣ ምዕራፍ 2።

ሐ. ኀዘን ግለሰባዊ ሆነ፣ ምዕራፍ 3።

መ. መታደል ኃላፊነትን/ተጠያቂነትን ያመጣል፣ የኪዳን ሕዝቦች ኃጢአት ሥሩ፣ ምዕራፍ 4

ሠ. በኪዳን አምላክ መታመንና ተስፋ ማድረግ፣ ምዕራፍ 5።

VIII. ዋነኛ ሐቆች

ሀ. እነዚህ ግጥሞች የሚገልጹት ኀዘንንና የጥፋት ስሜትን ነው፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ የተሰማውን፡
1. በኢየሩሳሌም ጥፋት፣
2. በመቅደሱ መደምሰስ፣
3. ያህዌ የሙሴን ኪዳን ዋጋ በማሳጣቱ። እነዚህ ጽኑ ስሜት የሚፈጥሩ ናቸው፣ እግዚአብሔር ከገባው ቃል አኳያ በ፡
   (ሀ) II ሳሙ. 7:10-16
   (ለ) ኢሳ. 37:30-35

ለ. እነዚህ ግጥሞች አጽንዖት የሚሰጡት፡
(1) ለእግዚአብሔር ሉዓላዊነት፣
(2) ለእግዚአብሔር ፍትሐዊነት፣
(3) ለእግዚአብሔር ፈርድ፣
(4) ለእግዚአብሔር የማደስ ተስፋ።

ሐ. ይሁዳ ጠፍታለች፣ የሙሴን ኪዳን በማፍረሷ (ዘዳ. 27-28)።በባቢሎን መሸነፍ የያህዌ ድክመት አይደለም፣ ነገር ግን የሕዝቡ ኃጢአት ነው እንጂ። ያህዌ በኃይሉ ድልን ያመጣል፣ በሚመጣው ጊዜ (3:22-23፣ 25)።

መ. የእግዚአብሔር ተስፋዎች ሁኔታዊና ሁኔታዊ ያልሆኑ ናቸው። የኪዳን ጽንሰ-ሐሳብ ተገቢ ምላሽን ይጠይቃል።

IX. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት እና ሰዎች በአጭሩ የሚገለጹ

ሀ. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት

1. “ውሽሞቿ ሁሉ” 1፡2፣ 19 (NASB እና NIV)
2. “ድንግሊቱ የይሁዳ ልጅ” 1፡15 (NASB እና NIV)
3. “የእግሩ መረገጫ” 2፡1 (NASB እና NIV)
4. “ጌታ ጠላት ሆነ” 2፡5 (NIV፣ “ጌታ እንደ ጠላት ሆነ”)
5. “እጃቸውን ያጨበጭባሉ... ይስማሉ... ራሳቸውን ያነቃንቃሉ” 2፡15 (NIV፣ “ያጨበጭባሉ... ይስቃሉ... ይነቀንቃሉ”)
6. “እጆችሽን ወደ እርሱ አንሺ” 2:19፤ 3:41 (NASB እና NIV)
7. "በውኑ ሴቶች ፍሬአቸውን ሕፃናትን ይበላሉን" 2:20፤ 4:10 (NASB እና NIV)

ለ. ሰዎች


1. “ሰውየው እኔ ነኝ” 3፡1


X. የካርታ ስፍራዎች/አመላካቾች

1. ይሁዳ፣ 1፡3
2. ጽዮን፣ 1፡4
3. ኢየሩሳሌም፣ 1፡7
4. ዖፅ፣ 4፡21

XI. የተማሪ ይዘት ጥያቄዎች

1. የሰቆቃወ ኤርምያስን ጽሑፋዊ መዋቅር አብራራ።
2. ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ መከራና መደነጋገርን/ውዥንብር እንዴት መያዝ እንዳለብን በምን መልኩ ያስረዳናል?
3. መጽሐፉ የግዞትን ጉዳይ በምን መልኩ ያያይዘዋል? (1፡5፣ 18)
4. 2፡17 ከዘዳ. 27-28 ጋር እንዴት ይዛመዳል?
5. 3፡19-38 እጅግ ጠቃሚ የሆነው ለምንድነው?


N
W
E
S
ANCIENT
NEAR EAST


PALESTINE
0 10 20 30 40
SCALE IN MILES

# የትንቢተ ሕዝቅኤል መግቢያ

I. የመጽሐፉ ስም

ሀ. እሱ የተሰየመው በዋናው ቃል አቀባይ ነው፣ ነቢዩ ሕዝቅኤል

ለ. የስሙ ፍች "እግዚአብሔር ያጠነክራል፣" ወይም "እግዚአብሔር ብርቱ ያደርጋል" ነው።

II. ቅዱስ ቃልነቱ (ካኖናዊነት)

ሀ. ይህ መጽሐፍ አንዳንድ ችግሮች ነበሩበት፣ በዕብራይስጥ ካኖን ተቀባይነት ለማግኘት፡
   1. የሕዝቅኤል መቅደስና ደንቡ ከሙሴ ይለያል።
   2. ምስል ከሳች ራዕያዊ ቋንቋ፣ በተለይም ምዕራፍ 1፣ 8 እና 10።

ለ. ራቢ ሐናንያ ቤን ሕዝቅያስ፣ የሻማይ ራቢያዊ ትምህርት ቤት፣ እንዳለው፣ 300 ማሰሮ ዘይት ጥቅም ላይ መዋል ይኖርበታል፣ ሕዝቅኤልን ከሙሴ ጋር ለማስታረቅ (ሻብ. 14ለ፤ ሜናሁዝ 45ሀ፤ ሃጊጋህ 13ሀ)።

ሐ. የአይሁድ ወግ/ልማድ የሚለው፣ ኤልያስ ከመሢሑ ቀድሞ ሲመለስ፣ በሕዝቅኤል እና በሙሴ መካከል ያለውን ችግር ይፈታዋል።

III. ዘውግ

ሀ. ይህ መጽሐፍ ብዙ ዘውጎችን ይዟል፡
   1. ትንቢት (ምዕ. 37)
   2. የፍጻሜው ጥፋት ትንቢት (ምዕ. 1፣ 8-10፣ 38-39፣ 40-48)
   3. ቅኔ
   4. ዝርው (ስድ ንባብ)
   5. ተውኔታዊ ምሳሌዎች (ምዕ. 4-7፣ 12)
   6. አጠቃላይ ምድብ (ምዕ. 16)

ለ. ምዕራፍ 40-48 እንዴት እንደሚተረጎም
   1. የመክፈቻ መግለጫዎች
      ሀ. የምዕራፍ 40-48 ጽሑፋዊ ዐውድ የመታደስ ተስፋ ነው፣ ምዕራፍ 33-39 ላይ እንደ ተመዘገበው።
      ለ. ይህ ክፍል ዘርዝር ያለ ውቅራዊ ፈርጅ ነው፣ የፍጻሜ መዳረሻው መቅደስ፣ ዘጸ. 25-27 ለማደሪያው ድንኳን እንደሆነ።
      ሐ. አጭር የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር፡
         1) ምዕራፍ 40-43 — የመቅደስ መታደስ
         2) ምዕራፍ 44-46 — የአምልኮ ሥርዓቱ መታደስ
         3) ምዕራፍ 47-48 — መሬቱ ዳግመኛ ተከፋፈለ
      መ. ይህ ትንቢት ጥንታዊውን ኪዳን ይጠቀማል፣ በእግዚአብሔር እና በአብርሃምና በዘሩ መካከል የተደረገውን፣ በመጨረሻው ዘመን የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚኖረውን ተሐድሶ/መመለስ ለማሳየት።
      ሠ. ከታሪካዊነት አኳያ እነዚህ ምዕራፎች ከግዞት መመለስ ጋር ነው የሚዛመዱት (43፡2)። ደግሞም፣ እሱ በግልጽ የፍጻሜ መዳረሻ ነው፣ በአንዳንድ መልኩ፣ ምክንያቱም እሱ ከድኅረ-ግዞት ጊዜ ጋር ስለማይገጥም።
   2. አንዳንድ ታሳቢ ትርጓሜዎች፡
      ሀ. እሱ በጥሬው ይፈጸማል ማለት ፈጽሞ አይቻልም፤
      ለ. እሱ ሁኔታዊ ትንቢት ነው፣ ይኸውም አይሁድ በተገቢው ምላሽ ያልሰጡበት፤
      ሐ. እሱም በከፊል ተመልሷል፣ ከግዞት በመመለስ ጊዜ፣ በዘሩባቤልና በኢያሱ በኩል፤
      መ. እሱም በሔሮድስ ቤተ-መቅደስ በከፊል ተመልሷል፤
      ሠ. እሱ ዘወትር ተምሳሌታዊ ነው የሚሆነው *(cf. Prophecy Interpreted by John Milton)*
      ረ. እሱ በፍጻሜ መዳረሻው ቤተ-መቅደስ ይፈጸማል።
   3. ይሄንን ጽሑፍ ለመተርጎም ያሉ ችግሮች፡
      ሀ. ምንም ዓይነት የተለየ ታሪካዊ መቼት የለም፣ ለምዕራፍ 38 እና 39 ወይም 40-48። ምንም ዓይነት ታሪካዊ መቼት ባለመኖሩ ምክንያት፣ በጽሑፉም ሆነ በታሪክ፣ አብዛኞቹ ተርጓሚዎች የፍጻሜ መዳረሻ አድርገውታል።፤
      ለ. አዲስ ኪዳን፡
         (1) የፍጻሜ ዘመንን መሥዋዕታዊ ሥርዓት ያላካተተ ይመስላል፣ ዕብ. 9 እና 10፤
         (2) አሕዛብን ያካተተ ይመስላል፣ ሕዝ. 40-48 ባመዛኙ ብሔራዊ ሆኖ ሳለ።
      ሐ. ኢየሱስ አይሁድን ያልተቀበላቸው ይመስላል፣ እንደ እግዚአብሔር የማዳን/መዋጀት መሣሪያ፣ በክፉዎቹ ገባሮች ምሳሌ (ማቴ. 21፡33-46፤ ማር. 12፡1-12፤ ሉቃ. 20፡9-19፤
      መ. ምንም እንኳ እግዚአብሔር ብሔረ-እስራኤልን በፍጻሜው ዘመን መቼት ይጠቀምበታል ብዬ ባምንም (ሮሜ. 9-11)፣ ቤተ-ክርስቲያን መንፈሳዊ እስራኤል መሆኗንም አምናለሁ (ሮሜ. 2፡28-29፤ገላ. 3፡1፤ 6፡16፤ ኤፌ. 2-3።

ሐ. ሕዝቅኤል አብዛኛውን መልዕክቱን ያዘጋጀው በጽሑፍ መልክ ነው። እነርሱ በቃል (በንግግር) የተሰጡ አልነበሩም፣ እንደ ኢሳይያስና ኤርምያስ። እነርሱ እጅግ መዋቅራዊ ናቸው።

IV. ደራሲነት

ሀ. የመጽሐፉ ደራሲነት ፈጽሞ አጠራጥሮ አያውቅም። ሙሉው መጽሐፍ ከ1፡2-3 በቀር የተጻፈው በአንደኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር ነው (ግለ ታሪካዊ።)

ለ. በአይሁድ ወግ/ልማድ፣ ባባ ባትራ 15ሀ፣ የሚለው “የታላቁ ምኩራብ ሰዎች ሕዝቅኤልን እና አስራ ሁለቱን ጽፈዋል።” “ጻፈ” የሚለውን ቃል እንደተመለከትነው፣ ፍችው አዘጋጀ ወይም አጠናቀረ ማለት ነው።

ሐ. Josephus' *The Antiquities of the Jews,* 10:5:1, እንደሚለው፣ ሕዝቅኤል ሁለት መጻሕፍት ጽፏል። ይህም የሚያመለክተው የአብዛኞቹን የዕብራውያን ነቢያትን የአወቃቀር ባሕርይን ነው፣ ምክንያቱም መጽሐፋቸው በቀላሉ ለሁለት ስለሚከፈል። የመጀመሪያው የታሪካዊ መቼት ክፍል የእርሱ የራሱ ጊዜ ነው። ሁለተኛው የመጽሐፉ ክፍል የወደፊቱን ያስቀምጣል (ኢሳ. 1-39 እና 40-66፤ዳን. 1-6 እና 7-12፤ዘካ. 1-8 እና 9-14 እና ሕዝ.1-32 እና 33-48)። ይህ ሊሆን ይችላል ጀሮም ጥርጣሬውን የገለጸበት ምክንያት፣ በሕዝቅኤል ወጥነት ላይ። ደግሞም ጆሴፈስ፣ እሱ ሁለት መጻሕፍት እንደጻፈ ያሰበበት።

መ. ስለ ነቢዩ ሕዝቅኤል የምናውቀው ሁሉ ከመጽሐፉ ነው። እሱም ሌላ የትም ስፍራ ብኪ ላይ አልተጠቀሰም።
1. እሱ ካህን ነበር፣ ከሳዶቅ ዘር፣ 1:3፣
2. እሱ አግብቷል፣ ልጅ ግን አልነበረውም፣ 24:16-18፣
3. እሱ ተማርኮ ተወስዶ ነበር፣ ሃያ አምስት ዓመት ሲሆነው፣ በ597 ቅ.ል.ክ፣ በናቡከደነፆር II፣ ከንጉሥ ዮአኪን ጋር፣ 1:1፤ 1 ነገሥ. 24:14-16፣
4. እሱም ወደ አይሁድ ሰፈራ ተግዟል፣ ከባቢሎን ብዙም ወደማይርቀው፣ በሰው-ሠራሽ ቦይ በኮቦር በኩል፣ 1:1፣3፣ ቴል-አቢብ ወደሚባለው፣ 3:15፣
5. እሱም ቢያንስ ለሃያ ሁለት ዓመት ያህል ሰብኳል፣ 1:1-2፤ 29:17፣
6. እሱ ብርቱ ግን ርኅሩኅ/አዛኝ ነቢይ ነበር፣ 9:8፤ 11:13።

V. ጊዜው

ሀ. እሱ የተወለደው 623 ቅ.ል.ክ አካባቢ ነው፣ በኢየሩሳሌም።

ለ. ሕዝቅኤል ከሰባተኛው ክፍለ-ዘመን ነቢያት መካከል አንዱ ነው፡ ኤርምያስ፣ ዳንኤል፣ ናሆም፣ ዕንባቆም እና ሶፎንያስ።

ሐ. በኢዲሱ የባቢሎናውያን ኃይል መነሣት ጊዜ፣ በናቦፖላሳር እና በአልጋ ወራሹ ናቡከደነፆር II፣ እግዚአብሔር በእነዚህ ነቢያት በኩል ተናግሯል፣ በተለያዩ ስፍራዎች፡
1. ዳንኤል በናቡከደነፆር ምርኮኛ ተደርጎ ተወስዷል፣ በ605 ቅ.ል.ክ። እሱም ወደ ባቢሎን ቤተ-መንግሥት ተግዟል፣ ዳን. 1:1።
2. ሕዝቅኤል በናቡከደነፆር ምርኮኛ ተደርጎ ተወስዷል፣ በ597 ቅ.ል.ክ፣ ከሌሎች 10000 የዕደ-ጥበብ ሞያተኞችና ከንጉሥ ኢዮአቄም ጋር፣ II ነገሥ. 24:14-16።
3. ኤርምያስ በኢየሩሳሌም ቀረ፣ እስከ ጎዶልያስ ሞት ድረስ።

መ. ሕዝቅኤል ለትንበያዎቹ ቀን ጽፏል። እነዚህ ቀናት፣ መጽሐፉ ዜና መዋዕላዊ ቅደም ተከተላቸውን እንዳልጠበቁ ያመላክታሉ፡

| ዓመት | ቀን | ወር | | የዮአኪን የግዞት | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. ራዕይ፣ 1:1 | 5 | 4 | | 13 | |
| 2. ራዕይ፣ 1:2 | 5 | 4 | | 5 | |
| 3. ራዕይ፣ 8:1 | 5 | 6 | | 6 | |
| 4. የሽማግሌዎች ጥያቄ፣20:1 | 10 | 5 | | 7 | |
| 5. የኢየሩሳሌም ከበባ ተጀመረ፣ 24:1 | 10 | 10 | | 9 | |
| 6. በጢሮስ ላይ የተነገረ ትንቢት፣26:1 | 1 | ? | | 11 | |
| 7. በግብፅ ላይ የተነገረ ትንቢት፣ 29:1 | 12 | 10 | | 10 | |
| 8. በግብፅ ላይ የተነገረ ትንቢት፣ 29:17 | 1 | 1 | | 27 | |
| 9. በግብፅ ላይ የተነገረ ትንቢት፣ 30:20 | 7 | 1 | | 11 | |
| 10. በግብፅ ላይ የተነገረ ትንቢት፣ 31:1 | 1 | 3 | | 11 | |
| 11. በግብፅ ላይ የተነገረ ትንቢት፣ 32:1 | 1 | 12 | | 12 | |
| 12. በግብፅ ላይ የተነገረ ትንቢት፣ 32:17 | 15 | (12) | | 12 | |
| 13. የኢየሩሳሌም መውደቅ፣ 33:21 | | 5 | 10 | | 12 |
| 14. የአዲሲቷ ኢየሩሳሌም ራዕይ፣ 40:1 | 10 | 1 | | 25 | |

ሠ. እንዲህም የሕዝቅኤል አገልግሎት በ592 አካባቢ ተጀምሮ፣ ቢያንስ እስከ 570 ቅ.ል.ክ ድረስ ቀጥሏል፣ ሊረዝምም ይችላል።

VI. ታሪካዊ መቼት

VII. ጽሑፋዊ ምድብ

ሀ. የሕዝቅኤል ትንቢት በሁለት ፈጽሞ የተለያዩ መልዕክቶች ሊከፈል ይችላል፡
1. ከኢየሩሳሌም መውደቅ በፊት በ586 ቅ.ል.ክ፣ ስብከቱ ባሕርዩ ለንስሐ ጥሪ ነበር፣ ስለሚመጣው የእግዚአብሔር ፍርድ። (1-32)
2. ከኢየሩሳሌም መውደቅ በኋላ ስብከቱ ወደ ተስፋ፣ መታደስ፣ ይቅርታ ተቀየረ። (33-48)

ለ. አጭር የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር
1. ለአገልግሎት መጠራቱ፣ 1-3።
2. የኪዳኑ ሕዝብ ኃጢአተኝነት እና የኢየሩሳሌም መውደቅ፣ 4-24።

3. የእግዚአብሔር ፍርድ በአካባቢው ሕዝቦች ላይ፣ 25-32
4. የእግዚአብሔር ተስፋ፣ ስለ ሕዝቡ፣ ከተማው እና መቅደሱ መመለስ፣ 33-37።
5. የጥፋት ትንበያ ከሰሜን በኩል ስለሚሆን ወረራ፣ 38-39።
6. ስለሚመለሰው/እሚታደሰው መቅደስ ራዕይ፣ 40-48።

VIII. ዋነኛ ሐቆች

ሀ. አይሁድ መከራ የተቀበሉት በገዛ ራሳቸው ኃጢአት ነው እንጂ በእግዚአብሔር ድክመት አይደለም።

ለ. የኪዳን እምነት ሁለቱንም የተጠቃለለ/የጋራ እና የግለሰብ ገጽታ አለው። አዲስ ኪዳን ይኸውም ኤር. 31፡31-34 ላይ የተጠቀሰው በመሠረቱ ግለሰባዊ ነው፣ እንደ ምዕራፍ 18 እና 33። እሱም ደግሞ በእግዚአብሔር ሥራ ነው፣ ዋስትና ያገኘው (ዝኪ. ምዕራፍ 36-37)። ይህም አንድ ዓይነት (ተመሳሳይ) ማመዛዘኛ ነው፣ በእግዚአብሔር ሉዓላዊነት እና በሰው ኪዳናዊ ኃላፊነቶች መካከል ያለ፣ በአዲስ ኪዳን የሚገኝ።

ሐ. እግዚአብሔር ታማኝ ነው፣ ለአብርሃምና ለዳዊት ዘር። ኪዳኑ ዳግም ይመሠረታል፣ ምዕራፍ 37፣ 40-48። ግዞት የፍቅር ድርጊት ነው!

መ. የአይሁድ ችግር አላበቃም፣ ምዕራፍ 38-39 (ዳን. 7-12)። ቀጣይነት ያለው ትግል አለ፣ በእግዚአብሔር ሕዝብ እና በወደቀው፣ መንፈሳዊ፣ ተፈታኝ ስብዕና መካከል (መዝ. 2)።

IX. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት እና ሰዎች በአጭሩ የሚገለጹ

ሀ. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት
1. ሰቅል፣ 4፡10
2. ቢረሌ ድንጋይ፣ 10፡9 (NIV፣ "ብርጭቆማ ድንጋይ")
3. "በፊታቸውም ግንቡን ንደል፣ በእርሱም ውጣ፣" 12፡5
4. የአስማት ከታብ፣ 13፡18 (NIV፣ "የአስማት ቀመር")
5. "አዲስ ልብና አዲስ መንፈስም ለእናንተ አድርጉ፣" 18፡31 (NIV፣ "አዲስ ልብና አዲስ መንፈስ ይሁንላችሁ")
6. "በእሳት አሳለፉ፣" 20፡26 እና 31
7. *Bamah*፣ 20፡29
8. "ከበትርም በታች አሳልፋችኋለሁ፣" 20፡37
9. የቤተሰብ ጣዖታት፣ 21፡21 (NIV፣ "ጣዖታት")
10. "አፍንጫሽንና ጆሮሽንም ከአንቺ ይቆርጣሉ፣" 23፡25
11. "በእግዚአብሔር ገነት በዔድን ነበርክ፣" 28፡13
12. የክንድ ልኬት (ርዝመት)
13. ዘወትር፣ 46፡15 (NIV፣ "በየማለዳ ማለዳው መደበኛው የሚቃጠለው ቍርባን")


ለ. ሰዎች
1. "አራቱ እንስሶች፣" 1፡5 (NIV፣ "አራቱ እንስሶች")
2. የሰው ልጅ፣ 2፡1
3. ተሙዝ፣ 8፡14
4. ኪሩቤል፣ 10፡6
5. ዳንኤል፣ 14፡14፣ 20
6. ኦሖላ እና ኦሖሊባ፣ 23፡4
7. የሳዶቅ ልጆች፣ 40፡46


X. የካርታ ስፍራዎች/አመላካቾች

1. ኮቦር ወንዝ፣ 1፡1 (NIV፣ "ኮቦር ወንዝ")
2. የከለዳውያን አገር፣ 1፡3 ("የባቢሎናውያን አገር")
3. ጢሮስ፣ 26፡2
4. ያዋን፣ 27፡13 (NIV፣ "ግሪክ")
5. ቶቤል፣ 27፡13
6. ሞሳሕ፣ 27፡13
7. ኖእ፣ 30፡14

XI. የተማሪ ይዘት ጥያቄዎች

1. ሕዝቅኤል ምዕራፍ 1 ላይ ምን አየ? እሱም በባቢሎን ያልተለመደ የሆነው ለምንድነው?
2. ምዕራፍ 2 ላይ ያለው የመጽሐፍ ጥቅል የሚወክለው ምንድነው?
3. ምዕራፍ 4 እና 5 ላይ ያሉት ተምሳሌታዊ ድርጊቶች የሚወክሉት ምንድነው?
4. ምዕራፍ 8 እጅግ የሚያስደነግጠው ለምንድነው? እሱስ እውነተኛ ነው ወይስ ተምሳሌታዊ?
5. ምዕራፍ 1 እና 11 እንደምን ይዛመዳሉ?
6. ምዕራፍ 18 በብኪ እጅግ ያልተለመደ የሆነው ለምንድነው?
7. ሰይጣን ከጢሮስ ንጉሥ ጋር የተዛመደው እንዴት ነው (28)? ምዕራፍ 28 የሰይጣን መግለጫ የሆነው ለምንድነው?
8. ምዕራፍ 36-39 ከሕዝቅኤል ጊዜ ጋር እንዴት ይዛመዳል?
9. ምዕራፍ 18፡30-32 ከ36፡26-27 ጋር እንዴት ይዛመዳል?
10. የሕዝቅኤል መቅደስ ተምሳሌታዊ ነው ወይስ በጥሬው (እውናዊ)?


ANCIENT
NEAR EAST
N
S
E
W


PALESTINE
0 10 20 30 40
SCALE IN MILES

# መግቢያ ለትንቢተ ዳንኤል

I. የመጽሐፉ ስም

ሀ. እሱ የተሰየመው ዋናውን ቃል-አቀባይና ነቢይ ተከትሎ ነው።

ለ. የስሙ ፍቺ "እግዚአብሔር ፈራጄ ነው" ማለት ነው።

II. ቅዱስ ቃልነቱ (ካኖናይዜሽን)

ሀ. ዳንኤል የዕብራይስጥ ካኖን፣ "ጽሑፎች" ተብሎ የሚጠራው ሦስተኛውና የመጨረሻው ምድብ ክፋይ ነው።

ለ. ይህም የሆነበት ምክንያት፡
1. እሱ በአይሁድ ዘንድ እንደ መንግሥት አመራር ነው የሚታየው፣ እንደ ነቢይ ሳይሆን።
2. እሱም የሚያንጸባርቀው የጽሑፉን (የዝግጅቱን) ኋለኛ ቀን ነው።
3. እሱ አራማዊ ክፍሎች ይዟል (2:4ለ-7:28)፣ እንደ ዕዝራ።

III. ዘውግ

ሀ. እሱ እንደ አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ነቢያት የዘውጎች ድብልቅ ነው፡
1. ምዕራፍ 1-6 ታሪካዊ ትርክት ነው፣ በሦስተኛ መደብ የተጻፈ። እነርሱም የዳንኤልን ሕይወትና ጊዜ ያንጸባርቃሉ።
2. ምዕራፍ 7-12 የወደፊት ሁነቶች ናቸው፣ ዘወትር በመጨረሻው ጥፋት ምናባዊ ትንበያ የሚገለጹ፣ በአንደኛ መደብ (ዝኪ. 7:1፣9፤ 8:1፤ 9:2)።

ለ. ይህ የተለየ ዓይነት ታሪካዊ ፈርጅ፣ ከዚያም የወደፊቱ ደግሞ ይገኝበታል፡
1. ኢሳይያስ፣ 1-39 እና 40-66
2. ሕዝቅኤል፣ 1-32፤ 33-48
3. ዘካርያስ፣ 1-8 እና 9-14።

ሐ. የፍጻሜ ጥፋት ሥነ-ጽሑፍ የተለየ የአይሁድ ዘውግ ነው። እሱም ጥቅም ላይ የሚውለው በታላቅ ጭንቀት ጊዜ ነው፣ የእግዚአብሔርን ታማኝነት ለማረጋገጥ፣ ታሪክን መቆጣጠሩና የወደፊቱን ማዳንና ባርኮት ተስፋዎች ለማሳየት።

መ. እሱም ባሕርይ ያደረገው እጅግ ተምሳሌታዊ ቋንቋ መጠቀምን ነው፡
1. ልዩ ምልክቶች/ምስሎች፣
2. እንስሳት፣
3. ቁጥሮች፣
4. ራዕይ/ሕልም፣
5. የመላእክት ምልጃ፣
6. የምሥጢራዊ ቃላት ቀመሮች፣
7. የሰላ ሁለትዮሽ — በመልካም እና በክፉ መካከል።

IV. ደራሲነት

ሀ. መጽሐፉ ደራሲውን አያስቀምጥም። ምዕራፍ 1-6 የተጻፉት በሦስተኛ መደብ ሲሆን፣ 7-12 ደግሞ በአንደኛ መደብ ነው፣ 7:1፣9፤ 8:1፤ 9:1።

ለ. የአይሁድ ወግ/ልማድ፣ ባባ ባትራ 15ሀ እንደሚለው፣ "የታላቁ ምኩራብ ሰዎች ዳንኤልን ጽፈውታል።" ይህ ማለት እነርሱ አዘጋጅተውታል ወይም ቀድተውታል ማለት ነው። ይህም ምክንያት ሊሆን ይችላል፣ ለኋለኛ የዕብራይስጥ ባሕርያቱ።

ሐ. የሚከተሉት ምክንያቶች ተሰጥተዋል፣ ፊተኛውን ወይም ኋለኛውን ጊዜ ለማጠናከር፡
1. ፊተኛ ጊዜ (7ኛ-6ኛ ክፍለ-ዘመን ቅ.ል.ክ)፡
   ሀ. መጽሐፉ የዳንኤል ራዕይ እንደሆነ ይመሰክራል፣ 7:2፣ 4፣ 6፣ 28፤ 8:1፣ 15፤ 9:1-2፤ 10:2፤ 12:4-8።
   ለ. ኢየሱስ የዳንኤልን ደራሲነት ጠቅሷል፣ ማቴ. 24፡15።
   ሐ. የፋርስና የግሪክ ቃላት መገኘት ኋለኛውን ጊዜ አያመለክቱም፣ ምክንያቱም በእነዚህ አገሮች መካከል የንግድ ውሎች ስለነበሩ፣ በዳንኤል ጊዜ።
   መ. የከሕይወት በኋላ ሥነ-መለኮት ደግሞ ኢዮብ ላይና በአንዳንድ መዝሙሮች ሊታይ ይችላል። የመላእክት የዳበረ ሥነ-መለኮት ዘካርያስ ላይ ሊታይ ይችላል።
   ሠ. ዳንኤል የሚገጥመው የእኛን የአሁኑን አርኪዎሎጃዊ ግንዛቤ/መረዳት ነው፣ ስለ ባቢሎናውያንና ፋርስ ንጉሣዊ ቤተ-መንግሥት።
2. ኋለኛ ጊዜ (2ኛ ክፍለ-ዘመን ቅ.ል.ክ)፡
   ሀ. በዕብራይስጥ ካኖን ያለው ስፍራ/አቀማመጥ።
   ለ. የፋርስና የግሪክ ቃላት መኖራቸው።
   ሐ. የከሕይወት በኋላ እና የመላእክት የዳበረ ሥነ-መለኮት።
   መ. የትንቢቶቹ ተለይቶ መቅረብ፣ በተለይም ምዕራፍ 11፣ ከሴሊዩሲድ እና ፕቶሎሚስ ትግል ጋር በተያያዘ፣ ፍልስጥኤምን ለመያዝ።
   ሠ. በዳንኤልና በሌሎቹ የመቃብያን ጊዜ የፍጻሜ ጥፋት ትንቢቶች መጻሕፍት መካከል ያለው ተመሳስሎ።
   ረ. በርከት ያሉ ታሳቢ "ስሕተቶች" በመጽሐፉ፡
      (1) "ጠቢብ ሰው" የሚለው ቃል አጠቃቀም።

(2) ዳንኤል እንደ ጠቢብ (ጠቢብ ሰው)።
(3) ብልጣሶር "የባቢሎን ንጉሥ" ተብሎ ተጠርቷል።
(4) ናቡከደነፆር የብልጣሶር አባት ተብሎ ተጠርቷል።
(5) የ"ሜዶናዊው ዳርዮስ" መጠቀስ።
(6) የፋርስን የአስተዳደር ቃል መጠቀም፣ *satrap*።

መ. የዳንኤል መጽሐፍ ኅብር ሊታይ ይችላል፡
1. በምዕራፍ 2፣ 7 እና 8 መካከል ባለው ዝምድና።

| ምዕ. 2 | ምዕ. 7 | ምዕ.8 |
|---|---|---|
| ወርቅ (ባቢሎን) | አንበሳ | |
| ብር | ድብ | አውራ በግ (ፋርስ) |
| ነሐስ | ነብር | ፍየል (ግሪክ) |
| ብረት/ሸክላ | አውሬ | |

2. አራማዊው ክፍል ከ2፡4ለ-7፡28 ድረስ ይዘልቃል።

ሠ. መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህን ትልልቅ ግዛቶች (ኢምፓየሮች) ለይቷል፡

1. የምዕራፍ 2 ወርቅ፣ እንደ ባቢሎን፣ 2፡38።
2. የምዕራፍ 8 አውራ በግ፣ እንደ ፋርስ፣ 8፡20።
3. የምዕራፍ 8 ፍየል፣ እንደ ግሪክ፣ 8፡21።
4. ስለዚህ፣ አራተኛው መንግሥት ሮም መሆን አለበት። ይህ መንግሥት ነው መሢሑ የሚመጣበት (2:34-35፣44፤ 8:35።)

ረ. ስለ ሰውየው ዳንኤል ምን እናውቃለን፡
1. ወደ ግዞት በ605 ቅ.ል.ክ መወሰዱን፣ 1፡1።
2. ከዋነኛና ባለጠጋ ቤተሰብ ከኢየሩሳሌም መሆኑን፣ 1፡3።
3. ምሑር (በእውቀት የበሰለ)፣ 1፡4።
4. ሕልምና እውቀትን ለመተርጎም ልዩ ተሰጥዖ የነበረው፣ 5፡12፣ 14።
5. ለሁለቱም የታመነ አገልጋይ፡
   ሀ. ለእግዚአብሔር፣ 6፡5።
   ለ. ለንጉሥ፣ 6፡4።

ሰ. የብኪው መጽሐፍ የትንቢተ ዳንኤል፣ ዳንኤል እና የሕዝ. 14፡14፣ 20 እና 28፡3 ዳንኤል አንድ ዓይነት አይደለም። ስማቸው በዕብራይስጥ ተለይቶ ተጽፏልና።

V. ጊዜው

ሀ. ዳንኤል ወደ ግዞት የተወሰደው በናቡከደነፆር II ነው በ605 ቅ.ል.ክ (ዝከ. 1:1)።

ለ. ዳንኤል ሕልም ተርጓሚና የባቢሎንና የፋርስ ነገሥታት አማካሪ ነበር፣ እስከ ቂሮስ II፣ "ታላቁ" ጊዜ ድረስ (ዝከ. 1:21፤ 6:28፤ 10:1)።

ሐ. አንዳንድ ሊቃውንት የትንቢትን ዋጋ የማይቀበሉ፣ በዳንኤል ምዕራፍ 11 ታሪካዊ ዝርዝር ርግጠኝነት ተቸግረዋል። እነሱ የመጽሐፉን ጊዜ የሚያስቀምጡት፣ ከመጨረሻው የተለየ ትንቢት በኋላ ወዲያውኑ ነው፣ በአንቲኦቾስ IV ኢፒፋነስ (175-164 ቅ.ል.ክ)።

መ. በመጽሐፉ ላይ አንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ተውላጠ ስም ጥቅም ላይ እንደመዋሉ መጠን (ዝከ. 7:1፣9፤ 8:1፤ 9:1)፣ ይህ የሚያመለክተው ዳንኤል የመጽሐፉ ደራሲ መሆኑን ነው፣ የእርሱን ስም የያዘውን፣ እናም የመጽሐፉ ጊዜ ከእርሱ የሕይወት ዘመን ጋር ይያያዛል (ይቆጠራል)።

VI. ጽሑፋዊ ምድቦች

ሀ. አጭር የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር
1. የዳንኤል ሕይወት፣ 1-6።
2. የዳንኤል ራዕዮች፣ 7-12።

ለ. የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር በይዘት
1. ዳንኤል በናቡከደነፆር ቤተ-መንግሥት፣ ምዕራፍ 1።
2. የናቡከደነፆር ሕልም እና ትርጓሜ፣ ምዕራፍ 2።
3. የናቡከደነፆር የወርቅ ምስል እና የዳንኤል ሦስት ጓደኞች፣ ምዕራፍ 3።
4. የናቡከደነፆር ሁለተኛ ሕልምና ትርጉሙ፣ ምዕ. 4።
5. የብልጣሶር ግብዣና የባቢሎን ከተማ ውድቀት፣ ምዕ.5።
6. ሜዶናዊው ዳርዮስ እና ዳንኤል በአንበሶች ጉድጓድ፣ ምዕ.6።
7. የአራቱ እንስሶች ራዕይ፣ ምዕራፍ 7።
8. የምዕ. 7 ራዕይ ተብራርቶና ተስፋፍቶ፣ ምዕ. 8።
9. የዳንኤል ለኢየሩሳሌም መታደስ ያለው መቆርቆር፣ ነገር ግን የአይሁድ የወደፊት ችግሮች መታየታቸው፣ ምዕ. 9።

10. መግቢያ ለምዕራፍ 11-12፣ ምዕራፍ 10።
11. ቀጣዩ ትግል፣ በሴሊዩሲድስ እና ፕቶሎሚስ መካከል፣ በፍልስጥኤም ላይ፣ ምዕራፍ 11-12።

VII. ዋነኛ ሐቆች

ሀ. እግዚአብሔር ታሪክን ተቆጣጥሯል ይቆጣጠራልም፤ በእርሱ ታመን እናም በአስቸጋሪ ጊዜ ታማኝ ሆነህ ኑር።

ለ. የእግዚአብሔር ሕዝብ (አይሁድ) መከራ አላበቃም።

ሐ. እግዚአብሔር ዘላለማዊ መንግሥትን በመሢሑ በኩል ያሰናዳል።

መ. የሁለቱም የጻድቅም ሆነ የኃጢአተኛ ትንሣኤ ይኖራል።

VIII. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት እና ሰዎች በአጭሩ የሚገለጹ

ሀ. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት

1. "የከለዳውያን ቋንቋ" (ኩኔፎርም)፣ 1:4 (NIV፣ "የባቢሎናውያን ቋንቋ እና ሥነ-ጽሑፍ")
2. "አራተኛው የአማልክትን ልጅ ይመስል ነበር፣" 3:25 (NASB እና NIV)
3. *Mene, Mene, Tekel Upharsin, 5:25* (NIV, "*...parsin*")
4. "አራቱ የሰማይ ነፋሳት፣" 7:2 (NASB እና NIV)
5. "አራትም ታላላቅ አራዊት ከባሕር ወጡ፣" 7:3 (NASB እና NIV)
6. "መጻሕፍትም ተገለጡ፣" 7:10 (NASB እና NIV)
7. "እስከ ዘመንና እስከ ዘመናት እስከ እኩሌታ ዘመንም፣" 7:25 (NASB እና NIV)
8. ሰባ ሱባዔ (ሰባ ሳምንታት) 9:24 (NIV፣ "ሰባ ሰባቶች")
9. "የአለቃው ሕዝብ፣" 9:26 (NIV፣ "የገዥው ሕዝብ")
10. "የርኩሰቱ ጫፍ፣" 9:27 (NIV፣ "በመቅደሱ ጫፍ ርኩሰቱን ያኖራል")
11. "የጥፋት ርኩሰት፣" 11:31 (NIV፣ "ጥፋትን የሚያስከትል ርኩሰት")

ለ. ሰዎች


1. ኢዮአቄም፣ 1:1
2. ከለዳውያን፣ 2:2 (NIV፣ "ኮከብ ቆጣሪዎች")
3. ብልጣሶር፣ 2:26
4. ጠባቂ መልአክ፣ 4:13 (NIV፣ "መልእክተኛ")
5. ብልጣሶር፣ 5:1
6. ሜዶናዊው ዳርዮስ፣ 5:31-6:1
7. ትንሽ ቀንድ፣ 7:8
8. በጥንት ዘመናት፣ 7:9
9. የሰው ልጅ፣ 7:13
10. ታናሽ ቀንድ፣ 8:9
11. ገብርኤል፣ 8:16
12. ሚካኤል፣ 10:13
13. "የደቡብ መስፍን፣" 11:5 (NIV፣ "የደቡብ ንጉሥ")
14. "የሰሜን ንጉሥ፣" 11:6 (NIV፣ የሰሜን ንጉሥ)

IX. የካርታ ስፍራዎች

1. ሰናዖር፣ 1:2 (NIV፣ "ባቢሎን")
2. ሜዶን፣ 8:20
3. ሱሳ፣ 8:2
4. ኤላም፣ 8:2
5. ግሪክ፣ 8:21

X. የተማሪ ይዘት ጥያቄዎች

1. በምን ዓይነት ሦስት መንገዶች ነው ከለዳውያን የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው?
2. የምዕራፍ 2፣ 7 እና 8 ራዕዮች እንዴት ይዛመዳሉ?
3. 7:10 እና 12:1 ላይ የተጠቀሱት "መጻሕፍት" ምንድናቸው?
4. 9:24-27ን ለመተርጎም እጅግ የሚከብደው ለምንድነው?
5. ምዕራፍ 11 ላይ ያሉት ሁለቱ መንግሥታት (ሕዝቦች) ምንድናቸው?
6. ዳንኤል ላይ ሁለት ትንንሽ ቀንዶች አሉ (7:8 እና 8:9)፣ ማንን የሚወክሉ ይመስሉሃል?
7. በመጽሐፉ የትኛው ስፍራ ነው፣ አጠቃላይ የሙታን ትንሣኤ ርዕሰ-ጉዳይ የተጠቀሰው?


ANCIENT
NEAR EAST
N
S
E
W

# መግቢያ ለትንቢተ ሆሴዕ

I. የመጽሐፉ ስም

ሀ. የተሰየመው ነቢዩን ተከትሎ ነው።

ለ. የስሙ ፍችም "መዳን" ማለት ነው። እሱም በዋነኛነት/በመነሻው የኢያሱ ስም ነበር፣ ዘኍ. 13፡16። እሱም ከሆሼ ጋር አንድ ዓይነት ስም ነው (II ነገሥ. 17፡1)።

ሐ. ሰውየው፡
1. የብኤሪ ልጅ (1፡1)፣
2. የእስራኤል ዜጋ (7፡5) የትኛው ከተማ እንደሆነ ግን አልታወቀም፣
3. አሞጽ ማኅበራዊ ፍትሕ ስለማስፈለጉ እንደተናገረ ሁሉ፣ ሆሴዕም ስለ ኪዳን ታማኝነት አስፈላጊነት ተናግሯል፣
4. እሱም ይጠራ የነበረው፡
   (ሀ) "የእስራኤል ኤርምያስ"
   (ለ) "የብኪው ዮሐንስ ሐዋርያ"
   (ሐ) "የእስራኤል የመጀመሪያው ወንጌላዊ"

II. ቅዱስ ቃልነቱ (ካኖናዊነት)

ሀ. ይህ መጽሐፍ "የኋለኞቹ ነቢያት" ክፋይ ነው (መጽሐፈ ጥበብ/ሲራክ 49፡10)

ለ. እሱም ከአስራ ሁለቱ፣ መለስተኛ ነቢያት ተብለው ከተመደቡት መካከል የመጀመሪያው ነው (ባባ ባትራ 14ለ)
1. እንደ ኢሳይያስ፣ ኤርምያስ እና ሕዝቅኤል፣ በአንድ ጥቅል ተካተዋል።
2. አስራ ሁለቱን ነገዶች ወይም የድርጅትን ተምሳሌታዊ ቁጥር ይወክላሉ።
3. የመጽሐፍን ታሪካዊ ቅደም ተከተል ልማዳዊ አተያይ ያንጸባርቃሉ።

ሐ. "የአስራ ሁለቱ" መለስተኛ ነቢያት ተራ በብዙ ሊቃውንት ዘንድ ከዜና መዋዕል (ከታሪክ ፍሰት) ቅደም ተከተል ጋር ተያይዟል። ሆኖም፣ በዚህ አተያይ ላይ ችግሮች አሉ፡
1. የመጀመሪያዎቹ ስድስት መጻሕፍት በኤምቲ/MT እና LXX መካከል ልዩነት አላቸው።

| ኤምቲ | LXX |
|---|---|
| ሆሴዕ | ሆሴዕ |
| ኢዩኤል | አሞጽ |
| አሞጽ | ሚክያስ |
| አብድዩ | ኢዩኤል |
| ዮናስ | አብድዩ |
| ሚክያስ | ዮናስ |

2. ውስጣዊ ማስረጃው ከዜና መዋዕል (ከታሪክ ፍሰት) አኳያ አሞጽን ከሆሴዕ በፊት ያስቀምጠዋል።
3. ለኢዩኤል የተሰጠው ቀን እጅግ አከራክሯል። እኔ የእርሱን ዝርዝር ያኖርኩት እንደ ቀደምቶቹ ድኅረ-ግዞት ነቢያት ነው፣ ከአብድዩ ጋር።

መ. የሆሴዕ ጽሑፍ ምናልባት ከማንኛውም የብኪ መጽሐፍ እጅግ አስቸጋሪው ነው።
1. የዚህ አንዱ ክፍል ከመጽሐፉ ስሜታዊ ጠባይ ሊሆን ይችላል።
2. ሌላው ክፍል የጽሑፉ አቀዳድ ነው። ኤምቲ እና LXX ይለያያሉ።
3. ሌላው ክፍል የዕብራይስጥ ንግግር በእስራኤልና በይሁዳ መካከል ያለው ልዩነት ነው።

III. ዘውግ

ሀ. እሱ ታሪካዊ ትርክት ነው፣ የስምንተኛው ክፍለ-ዘመን እስራኤላዊ ነቢይ ሕይወትና ጊዜ (በተለይም ምዕራፍ 1-3)።

ለ. የእሱ ሕይወት ምስያዊ በሆነ መንገድ ተወስዷል የእግዚአብሔርን ፍቅር ለማሳየት፡
1. እግዚአብሔር እንደ ታማኝ አፍቃሪ ወጣት (1-3)
2. እግዚአብሔር እንደ አፍቃሪ ወላጅ (11)
3. እነዚህ ዘይቤዎች የተመሠረቱት በእስራኤል መደነጋገር ላይ ነው፣ በአልን (ጣዖት) እንደ "ባል" እና "ጌታ" የወሰዱበት።

ሐ. የተጻፈው በተዋበ፣ ኃይለኛ እና ስሜታዊ ቅኔ ነው፣ ነገር ግን ባልተያያዙ አሀዶች (ምዕራፍ 4-14)

IV. ደራሲነት

ሀ. የጋራ መግባባቱ ሁልጊዜ ለሆሴዕ ነው፣ ምንም እንኳ ስለ እሱ ጥቂት ብናውቅም።

ለ. ባባ ባትራ 15ሀ የሚለው የታላቁ ምኩራብ ሰዎች "አስራ ሁለቱን" ጽፈዋል ነው። ይህም ግምት ውስጥ የሚያስገባው መጠናቀሩን ወይም መዘጋጀቱን መሆን አለበት።

ሐ. አንዳንዶች ጥያቄ አንሥተዋል፡
1. የይሁዳ መጠቀስ፣1:1፤ 4:15፤ 5:5፣10፣12-14፤ 6:4፣11፤ 8:14፤ 11:12፣
2. የወደፊቱ ብልጽግናና መዳን ምንባቦች፣
3. የሆሴዕ ጋብቻ ምዕራፍ 1-2 ላይ በሦስተኛ መደብ ተገልጿል፣ ነገር ግን ምዕራፍ 3 ላይ በሁለተኛ መደብ ነው።

መ. ለተቃውሞዎች ምላሽ፡
1. ሁሉም ነቢያት በእስራኤልና በይሁዳ መካከል የተደረገውን መገንጠል እንደ ስሕተት ይመለከቱታል። ይሁዳ ዘወትር የሚታየው ለአብርሃምና ለዳዊት የተሰጠው የኪዳን ተስፋ ሕጋዊ ወራሽ ተደርጎ ነው።
2. ነቢዩ ፍርድና የተስፋ ትንቢቶችን ይደባልቃል። እነሱ አብረው ነው የሚሄዱት፣ እንደ አንድ መለኮታዊ መልዕክት።
3. ሆሴዕ ምናልባት የስብከቱ ስብስብ ሊሆን ይችላል።

V. ጊዜው

ሀ. ሆሴዕ የስምንተኛው ክፍለ-ዘመን ቅ.ል.ክ ነቢይ ነው
1. ኢሳይያስና ሚክያስ በይሁዳ
2. ዮናስ፣ አሞጽ እና ሆሴዕ በእስራኤል

ለ. ሆሴዕ የአሞጽን አገልግሎት ተከትሏል፣ ተነባብሯልም/ተደርቧል

ሐ. የስብከቱ ጊዜ ሊሆን የሚችለው በ1፡1 ላይ በተጠቀሱት ነገሥታት ጊዜ ነው፡
1. ዖዝያን (የይሁዳ)
2. ኢዮአታም (የይሁዳ)
3. አካዝ (የይሁዳ)
4. ሕዝቅያስ (የይሁዳ)
5. ኢዮርብአም II (የእስራኤል)

መ. በርከት ያሉ ሊቃዊ/ምሑራዊ ሐሳቦች፡
1. ኬይል፣ 790-725 ቅ.ል.ክ
   ሀ. 1፡4፣ ከኢዩ ሥርወ-መንግሥት በፊት የተጀመረ
   ለ. 10፡14፣ በሻልማንሰር V ወረራ የተነገረ/የቀረበ
2. ፍራንሲስኮ፣ 750-735 ቅ.ል.ክ
   ሀ. ከአሞጽ ጥቂት ቀረብ ብሎ
   ለ. በኢዮሮብአም II የመጨረሻ ጊዜያት
   ሐ. ከ735 ቅ.ል.ክ ቀረብ አይልም፣ ምክንያቱም አሦር የገለዓድን አካባቢ ስለወሰደ
3. ሃሪሰን፣ 722 ቅ.ል.ክ በፊት
   ሀ. በኢዮሮብአም II የሞተው በ753 ቅ.ል.ክ ነው።
   ለ. ሜናሂም ለቲግላዝ-ፒሌሰር III ግብር የከፈለው (8፡9) በ739 ቅ.ል.ክ አካባቢ ነው።
   ሐ. የሲሮ-ኤፍራማቲክ ጦርነት ሁነት በ735-734 ቅ.ል.ክ የሚጠቅሰው 5፡8-6፡6 (ደግሞም ኢሳ. 7-14)።
   መ. የሆሴዕ ጊዜ የግብፅን ማጣቀሻዎች ይገልጻሉ፣ 7:11፤ 9:6 እና 12:2 ላይ።
4. ላ ሶር፣ ሁባርድ እና ቡሽ፣ 753 - እስከ 722 ቅ.ል.ክ ኋላ ድረስ።
   ሀ. የተጀመረው ከኢዮሮብአም IIሞት በፊት ነው፣ 753 ቅ.ል.ክ
   ለ. እስከ ሕዝቅያስ አገዛዝ ድረስ ይዘልቃል
      (1) የጋራ አገዛዝ ከ728 ቅ.ል.ክ
      (2) ንጉሥ ከ715 ቅ.ል.ክ
   ሐ. በቲግላዝ-ፒሌሰር III አገዛዝ ዘመን የተሰበከ፣ 745-727 ቅ.ል.ክ

VI. ታሪካዊ መቼት
ዝከ. "ታሪካዊ ዳራ ለስምንተኛው ክፍለ-ዘመን ነቢያት" በኢሳይያስ መጀመሪያ ላይ

VII. ጽሑፋዊ ምድቦች

ሀ. ( *Introduction to the Old Testament* by Clyde Francisco, pp. 150-163) ላይ የተወሰደ)
1. መግቢያ፣ 1:1
2. የሆሴዕ የውስጥ ቀውስ፣ 1:2-3:5
3. የእግዚአብሔር ተቃርኖ ከእስራኤል ጋር፣ 4:1-10:15
4. አባት እና ተገዳዳሪ/አፈንጋጭ ልጅ፣ 11:1-12
5. በስሙ ላይ ምን አለ (ያዕቆብ ወይም እስራኤል) 12:1-15
6. የሕዝብ ሞት፣ 13:1-16
7. የፍርድ አማራጭ 14:1-9

ለ. (*Introduction to the Old Testament* by E. J. Young, ገጽ252-254 ላይ የተወሰደ)
1. የእግዚአብሔር ግንኙነት ከሕዝቡ ጋር፣ 1:1-3:5
2. የነቢዩ የተለያዩ ገለጻዎች/ስብከቶች፣ 4:1-14:9
   ሀ. የሰሜን ነገዶች ኃጢአት፣ 4-8
   ለ. የሰሜን ነገዶች ቅጣት፣ 9:1-11:11
   ሐ. የወደፊቱ ባርኮት፣ ንስሐ ለሚገቡ ሰዎች፣ 11:12-14:9

VIII. ዋነኛ ሐቆች

ሀ. ያህዌ የግል አምላክ ነው። ኃጢአት፣ አፍቃሪውን እግዚአብሔርን መቃወም ነው፣ የኪዳን ሕግጋትን መጣስ ብቻ ሳይሆን (አሞጽ)

ለ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት እጅግ በተሻለ የተመለከተው በግለሰባዊ ቤተሰብ ዘይቤዎች ነው፡
1. ባል (እግዚአብሔር) - ሚስት (እስራኤል)
2. ወላጅ (እግዚአብሔር) - ልጅ (እስራኤል)

ሐ. ያህዌ ከወደቀው ሰው ጋር መሥራትን መርጧል፣ በተስፋ፣ በመሥዋዕት እና በኪዳን በኩል። እነዚህም የሚያካትቱት የግል መታመንን እና የኪዳናዊ ታዛዥነትን ነው።

መ. ለኪዳን ታዛዥ አለመሆን ፍርድን ያስከትላል። ፍርድ ሁልጊዜ ለመመለስ/ለመታደስ ዓላማ ነው። ቅጣት (ሥርዓት ማስያዝ) የወላጅ ፍቅር ድርጊት ነው (ዕብ. 12፡5)። የእስራኤል የወደፊት ባርኮት በአሁኑ መታዘዟ ላይ ይወሰናል።

IX. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት እና ሰዎች በአጭሩ የሚገለጹ

ሀ. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት
1. ግልሙትና፣ 1፡2 (NIV፣ "ጋለሞታ ሚስት")
2. ክርክር፣ 2፡2 (NIV፣ "መገሠጽ")
3. የዘቢብ ጥፍጥፍ፣ 3፡1 (NIV፣ "የተቀደሰ…")
4. ቆሮስ (መስፈሪያ)፣ 3፡2 (NASB እና NIV)
5. የተቀደሰ ዓምድ፣ 3፡4 (NIV፣ "የተቀደሱ ድንጋዮች")
6. *teraphim* ፣ 3፡4 (NIV፣ "ጣዖት")
7. "እግዚአብሔርን አላወቁም፣" 5፡4፣ (NIV፣ "እግዚአብሔርን አላወቁምና")
8. "ድንበርን የሚነቅሉ፣" 5፡10 (NIV፣ "የድንበር ድንጋዮች")
9. "ኤፍሬም ከአሕዛብ ጋር ተደባለቀ፣" 7፡8 (NASB እና NIV)
10. "ሰማርያ ሆይ፣ እምቦሳህን፣" 8፡5 (NIV፣ "ሰማርያ ሆይ፣ የእምቦሳ ጣዖትህ")
11. "ነፋስን ዘርተዋል፣ ዐውሎ-ነፋስንም ያጭዳሉ፣" 8፡7 (NASB እና NIV)
12. "የኀዘን እንጀራ፣" 9፡4 (NASB እና NIV)
13. "እኔም ኤፍሬምን … በእግሩ እንዲሄድ መራሁት፣" 11፡3 (NASB እና NIV)
14. ምሕረት *[hesed]* 4፡1፤ 6፡6፤ 10፡12፤ 12፡6 (NIV፣ "ያለ ምንም ታማኝነት")

ለ. ሰዎች
1. ዖዝያን፣ 1፡1
2. አካዝ፣ 1፡1
3. ሕዝቅያስ፣ 1፡1
4. ኢዮርብዓም የዮአስ ልጅ (II)፣ 1፡1
5. ጎሜር፣ 1፡3
6. ኢይዝራኤል፣ 1፡4
7. ሎሩሃማ፣ 1፡6
8. ሎዓሚ፣ 1፡9
9. ባሌ፣ (NIV፣ "ባሌ")
10. ንጉሥ ኢያሪም፣ 5፡13፤ 10፡6 (NIV፣ "ታላቁ ንጉሥ")

X. የካርታ ስፍራዎች

1. የአኮር ሸለቆ፣ 2፡15 (ኢያ. 7፡26)
2. ጌልገላ፣ 4፡15
3. ቤትአዊን፣ 4፡15 (ቤቴል)
4. ምጽጳ፣ 5፡1
5. ታቦር ተራራ፣ 5፡1
6. ጊብዓ፣ 5፡8
7. ራማ፣ 5፡8
8. አዳም፣ 6፡7
9. ገለዓድ፣ 6፡8
10. ብዔል-ፌጎር፣ 9፡10
11. ሊባኖስ፣ 14፡6-7

XI. የተማሪ ይዘት ጥያቄዎች

1. ሆሴዕ ጋለሞታይቱን አግብቷልን?

2. እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ያለው ኪዳን ሁኔታዊ ነው ወይስ ሁኔታዊ ያልሆነ?

3. በአል እና ጎሜር ከያህዌ እና ከእስራኤል ጋር የሚዛመዱት እንዴት ነው?


4. 6፡1-3 የማስመሰል ንስሐ ተደርጎ የተወሰደው/የታሰበው ለምንድነው?

5. 7፡4-6 እና 8፡4 ያለው "እነርሱ" የሚለው ተውላጠ ስም ማንን ነው የሚያመለክተው?

6. 8፡13 ከ11፡5 ጋር ይቃረናልን?

7. እስራኤል ወደ ግብፅ ነው ወደ አሦር የሚጋዘው? 11፡5ን ከ7፡10፣ 8፡13 እና 9፡3 ጋር በማነጻጸር አብራራ።

8. ፖለቲካዊ ኅብረት በሁሉም የብኪ ነቢያት የተኮነነው/የተወገዘው ለምንድነው?


PALESTINE
0 10 20 30 40
SCALE IN MILES

# መግቢያ ለትንቢተ ኢዩኤል

I. የመጽሐፉ ስም

ሀ. የተሰየመው ነቢዩን ተከትሎ ነው።

ለ. የእርሱ ስም የሁለት የእግዚአብሔር ስሞች ድብልቅ ነው፡
1. ያህዌ - የእግዚአብሔር የኪዳን ስም።
   ሀ. ማንኛውም የዕብራይስጥ ስም በ "ጄ" እና በአናባቢ የሚጀምር ዘወትር የያህዌ ምሕጻረ-ቃል ነው።
   ለ. ማንኛውም የዕብራይስጥ ስም በ "አይኤኤች፣ኢአ" የሚጀምር ደግሞ የያህዌ ምሕጻረ-ቃል ነው (ኢሳይጃ፣ ኤልያስ)።
2. ኤል - የእግዚአብሔር አጠቃላይ ስም።
3. በእነዚህ ሁለት የዕብራይስጥ ስሞች መካከል፣ ግሡ ያህዌን ማመልከት አለበት (ነው) ኤል።

ሐ. ይህ እጅግ የተለመደ የዕብራይስጥ ስም ነው። ከአስራ ሦስት በላይ በታሪካዊ መጻሕፍት ተጠቅሰዋል።

II. ቅዱስ ቃልነቱ (ካኖናዊነት)

ሀ. ይህ መጽሐፍ "ነቢያት" ተብሎ የሚጠራው የዕብራይስጥ ካኖን ምድብ ክፋይ ነው።
ለ. እሱም "አስራ ሁለቱ" ተብሎ የሚጠራው ጥቅል ክፋይ ነው። እነርሱም መለስተኛ ነቢያት በመባል ይጠራሉ፣ ስለ ጽሑፋቸው መጠን ምክንያት።

III. ዘውግ

ሀ. ይህ ግማሽ ዝርው (ስድ ንባብ)፣ ግማሽ የጥንት ዕብራይስጥ ቅኔ ነው።
ለ. ኢዩኤል ሌሎች በርከት ያሉ ነቢያትን የጠቀሰ ይመስላል፡
1. ኢዩኤል 1፡15ሐ - አሞጽ 4፡9፤ ኢሳ. 13:6 ሚኪያስ 4:3
2. ኢዩኤል 2:3 - ኢሳ. 51:3 ወይምሕዝ. 36:35
3. ኢዩኤል 2:10 - ኢሳ. 13:10
4. ኢዩኤል 3:10 - ኢሳ. 2:4፤
5. ኢዩኤል 3:16 - አሞጽ 1:2
6. ኢዩኤል 3:18 - አሞጽ 9:13

ሐ. የኢዩኤል የመጨረሻው ዘመን ምናባዊ ምስያ በፍጻሜ ጥፋት ቃል ተገልጿል፣ "የጌታ ቀን" በሚል።

መ. የአንበጣውን መቅሠፍት መተርጎሚያ ንድፈ-ሐሳቦች፣1:4፤ 2:25።
1. ተምሳሌታዊ/ምስያዊ

| ሀ. የአይሁድ ታርጉም 2፡25 ላይ | ለ. የጎዳግ ማስታወሻ በ6ኛ ክፍለ-ዘመን ኤምኤስኤስ የLXX | ሐ. ክርስቲያን ተንታኞች (18ኛ ክፍለ-ዘመን) |
|---|---|---|
| 1) ሕዝቦች | 1) ግብፃውያን | 1) አሦራውያን |
| 2) ቋንቋዎች | 2) ባቢሎናውያን | 2) ከለዳውያን |
| 3) ገዥዎች | 3)አሦራውያን | 3) መቄዶንያ |
| 4) መንግሥታት | 4)ግሪክ | 4) ሮም |
| | 5)ሮማውያን | |

2. ያለፈ ታሪካዊ
   ሀ. ነቢዩ የዕብራይስጡን ግሥ ሀላፊ ጊዜ ነው የተጠቀመው
   ለ. ይህም የትንበያ ዘዴ ባሕርይ ነበር፣ ሁነቶቹን በነቢዩ ሕይወት ላይ መውሰድ እና ለወደፊቱ መቼት መቀየሻ/መንደፊያ ማድረግ። የእስራኤል የወደፊት የሚወሰነው በአሁኑ የእምነት ንስሐ ምርጫ ላይ ነው።
3. የወደፊት ታሪካዊ
   ሀ. እየመጣ ያለ በጥሬው የተቀመጠ ወረራ አለ፣ በእስራኤል ኃጢአት ምክንያት
   ለ. አንበጣዎቹ የተመለከቱት እነርሱን ለመግለጽ ጥቅም ላይ በዋሉት ዘይቤዎች ነው፡
      1) ፈረሶችን ይመስላሉ
      2) የሰረገላ ድምጽ አላቸው
      3) በሰልፍ ይራመዳሉ
   ሐ. ኢዩኤል ከራዕይ 9፡3-11 ጋር ሊዛመድ ይችላል
4. የመጨረሻው ጥፋት
   ሀ. "የጌታ ቀን" የሚለው መጠቀሱ፣ ይህን ዓይነቱን ዘውግ ያመላክታል
   ለ. ምስል-ከሳች እና እንስሳትን መጠቀም የዚህ ዘውግ ባሕርይ ነው

IV. ደራሲነት
ሀ. ምንም የሚታወቅ ነገር የለም፣ ከነቢዩ ስምና ከአባቱ በቀር፣ ኢዩኤል የባቱኤል ልጅ፣ 1፡1።

ለ. ስለ ነቢዩ ሁለት ወግ/ልማዶች ነበሩ፡
1. ከሮቤል ነገድ (ሱዶ ኢፒፋነስ)
2. ከይሁዳ፣ ምክንያቱም የመቅደሱን የዕለትተ'ለት ነገሮች በማወቁ

V. ጊዜው

ሀ. የመጽሐፉን ጊዜ በትክክል ለማስቀመጥ ምንም መንገድ የለም (ጂ. ካምፐቤል ሞርጋን የሚለው እሱ እጅግ ከድሮዎቹ አንዱ ወይም እጅግ ከቅርቦቹ ነቢያት አንዱ ነው)፡

1. ከውስጣዊ ማስረጃዎች ሁለት ጊዜያትሐሳብ ቀርቦባቸዋል፡

ሀ. ድኅረ-ግዞት ጊዜ፡

1) እሱ መዛመድ ያለበት የይሁዳ የመወረር አደጋ አዝማሚያ ነው፣ በአንበጣው መቅሠፍት ዘይቤ።
2) 3፡2 የሚያመለክተው እስራኤል ቀደም ብሎ መጋዙን ነው። "እስራኤል" የሚለው ስም አሁን ለይሁዳ ጥቅም ላይ ውሏል፣ 2:27፤ 3:1-2፣16።
3) 3፡6 የሚናገረው ስለ ግሪክ የባርያ ንግድ ነው፣ ይኸውም ድኅረ-ግዞት ጊዜን የሚያመለክት።
4) 3፡1፣17 የሚያመለክተው ይሁዳ ቀደም ብሎ ተግዟል፣ እናም ድጋሚ የመወረር አደጋ ውስጥ ነው፣ በኃጢአት ከቀጠለ።
5) የተጠቀሰ ንጉሥ የለም፣ ከድኅረ-ግዞት መቼት ጋር የሚገጥም። ኢዩኤል መልዕክቱን ያደረሰው ለሽማግሌዎችና ለካህናት ነው።
6) ወራሪዎቹ "ሰሜንኞች" በማለት ይጠራሉ፣ ይኸውም የሜሶፖታሚያ የሚያመለክት (አሦር፣ ባቢሎን፣ ፋርስ) ወረራ፣ 2፡ 20።
7) የድኅረ-ግዞት ጊዜ የበአል አምልኮ ባሕርይ አልተጠቀሰም።

ለ. ቅድመ-ግዞት ጊዜ፡

1) መቅደሱን የሚጠቅስ ይመስላል፣ 1:9፣ 13-14፤ 2:17።
2) ጠላቶች 3፡4፣6፣8ላይ ተጠቅሰዋል (ፍንቄአውያን፣ ፍልስጥኤም፣ ዔዶም፣ ሳባውያን) ቅድመ-ግዞት ናቸው እንጂ የግዞት (ጊዜ) አይደሉም።

2. ከውጫዊ ማስረጃ፡

ሀ. በዕብራይስጥ ካኖን የመጽሐፉ ስፍራ የሚያመለክተው ቅድመ-ግዞት ጊዜ ነው።
ለ. እሱም ከአሞጽ ቀጥሎ ሊቀመጥ ይችላል፣ ምክንያቱም ሁለቱም የሚናገሩት ስለ "ያህዌ ቀን" እና ስለ አንበጣ ወረራ ነው፣ እንደ ፍርድ ተምሳሌት። ደግሞም፣ እሱ አዎንታዊ የበረከት ጉብኝት ነው፣ የፍርድ ሳይሆን። ይህም ከድኅረ-ግዞት መቼት ጋር ይገጥማል።

3. ደራሲው የሚያስበው ቀደም ያለውን ድኅረ-ግዞት ጊዜ ነው፣ ይህም ከማስረጃው ጋር እጅግ በተሻለ የሚገጥም።

ለ. ጊዜውን በተመለከተ የነበሩት ንድፈ-ሐሳቦች፣ የፍልስጥኤምን ወረራ መሠረት በማድረግ፡

1. በኢዮአስ የአገዛዝ ዘመን (837-800 ቅ.ል.ክ)
2. በኦዝያ የአገዛዝ ዘመን (783-742 ቅ.ል.ክ)
3. በሴዴቅያስ ያገዛዝ ዘመን (598-586 ቅ.ል.ክ)
4. በዘሩባቤል ጊዜ (598 ቅ.ል.ክ)
5. በሚልኪያስ ጊዜ (430 ቅ.ል.ክ)
6. ወደፊት የሚሆነው የፍጻሜው መዳረሻ የእግዚአብሔር ሕዝብ ወረራ

ሐ. ጽሑፋዊ ግንኙነት አለ፡

1. በኢዩኤል 2:32 እና በአብድዩ 17 መካከል። እነርሱ ሁለቱም ቀዳሚው ድኅረ-ግዞት ናቸው።
2. በኢዩኤል 3:16 እና በአሞጽ 1:2 መካከል። ኢዩኤል ብዙ ነቢያትን ጠቅሷል፣ ምናልባትም ኢዩኤል አሞጽን ጠቅሶ ሊሆን ይችላል።

መ. ጆን ካልቪን ስለ ኢዩኤል ጊዜ መልካም ነጥብ አስቀምጧል፣ "ምንም ርግጠኝነት ስለሌለ፣ እሱ እንደሚያስበው ጊዜውን ሳይወስኑ መተው የተሻለ ነው፤ እኛም እንደምንመለከተው፣ ይህ እጅግም ጠቀሜታ የለውም። የሆሴዕን ጊዜ አለማወቅ በአንባቢው ዘንድ የሚያሳጣው ትልቅ ነገር ይኖራል፣ ያለ ታሪክ እውቀት ሊብራሩ የማይችሉ ብዙ ክፍሎች ስላሉት፤ ነገር ግን ኢዩኤልጋ ይህ በመጠኑ የሚያስፈልግ ነው፣ የእሱ ዶክትሪን አንድምታ በግልጽ የሚታይ ነው፣ ምንም እንኳ የእሱ ጊዜ ግልጽ ባይሆንና ርግጠኝነት ባይኖረውም።"

VI. ታሪካዊ መቼት — የናሽናል ጆግራፊክ መጽሔት፣ የታኅሳስ 1915 (XXVIII፣ቁ. 6) በፍልስጥኤም የአንበጣ መቅሠፍት መዝግቧል። ይህ ጽሑፍ እጅግ ረጂ ነው፣ የነቢዩን ጠቃሽ ለመረዳት።

VII. ጽሑፋዊ ምድቦች

ሀ. የአጥፊው አንበጣ መቅሠፍት ራዕይ ተምሳሌታዊ ውክልናው ወራሪ ሠራዊት ነው፣ 1:1-2፡27
ለ. የጌታ ቀን የበረከት እንጂ የርግማን ቀን አይሆንም፣ ንስሐ ለሚገባው የእግዚአብሔር ሕዝብ፣ 2፡28-3፡21 (ሶፎንያስ ልክ የዚህ ተቃራኒ ነው።)

VIII. ዋነኛ ሐቆች

ሀ. ነቢዩ የእሱን ቀን ሁነቶች የተመለከተው ወደፊት ለሚመጡት ሁነቶች እንደ ጥላ (ንግር) አድርጎ ነው።

ለ. ኢዩኤል ለብሔራዊ የንስሐ ቀን ጥሪ ያደርጋል፣ 1:13-14፤ 2:12-17።

ሐ. የእግዚአብሔር ሕዝብ ንስሐ ከገባ፣ እግዚአብሔር አዲስ የብልጽግና ቀን ያመጣል፣ በሁለቱም በሥጋዊና በመንፈሳዊ (ዘዳ. 27-28።)

መ. እግዚአብሔር በአካባቢው ሕዝቦች ላይ ይፈርዳል! 3፡1-17

ሠ. ይህም አዲሱ የመንፈሳዊ መታደስ ቀን (ዝከ. 2፡28-29) ተጽዕኖውን የሚያሳድረው፡

1. በወንዶችና በሴቶች፤
2. በሽማግሌና በወጣት፣

3. በባርያና በነጻ ላይ ይሆናል። (የሐዋ. 2፤ ገላ. 3፡28)

ረ. "የእግዚአብሔር ቀን" የአሞጽ፣ ኢዩኤል እና ሶፎንያስ ባሕርያዊ (ተዘውታሪ) ሐረግ ነው። በምን መልኩ ለእግዚአብሔር ምላሽ እንደምንሰጠው ይወስነዋል፣ የበረከት ወይም የፍርድ ቀን ለመሆን።

ሰ. የእግዚአብሔር ባሕርይ 2፡13 ላይ ተገልጿል (ዘጸ. 34:6፤መዝ. 103:8-13 እና ነህ. 9:17)።

ሸ. መንፈሱን ማፍሰሱ፣ 2:28-32 ላይ የሚወክለው የአዲስ ኪዳን ዘመንን ነው (ኤር. 31:31-34 እና ሕዝ. 36:26-27)።

IX. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት እና ሰዎች በአጭሩ የሚገለጹ

ሀ. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት
1. "ቅርንጫፎቹም ነጡ፣" 1፡7 (NASB እና NIV)
2. "የእግዚአብሔር ቀን ቅርብ ነው፣" 1፡15 (NASB እና NIV)
3. "በጽዮን መለከትን ንፉ፣" 2፡1፣ 15 (NASB እና NIV)
4. "ልባችሁን እንጂ ልብሳችሁን አትቅደዱ፣" 2፡13 (NASB እና NIV)
5. ቸርነት (*hesed ሄሰድ*)፣ 2፡13 (NIV፣ "ፍቅሩም የበዛ")
6. "መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ፣" 2፡28 (የሐዋ. 2፡16።) (NIV፣ "...በሰዎች ሁሉ ላይ")
7. "የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል፣" 2፡32 (የሐዋ. 2፡21፤ ሮሜ 10፡13።) (NIV፣ "የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል")
8. "በሕዝቤም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ፣" 3፡3 (NASB እና NIV)
9. "ማረሻችሁን ሰይፍ ለማድረግ ቀጥቅጡ..." 3፡10 (NASB እና NIV)

ለ. ሰዎች
1. ሁሉን የሚችል አምላክ (El Shaddai)፣ 1፡15
2. ሳባውያን፣ 3፡8

X. የካርታ ስፍራዎች

1. ጢሮስ፣ 3:4
2. ሲዶና፣ 3:4
3. ፍልስጥኤም
4. ጃቫን (ግሪክ)
5. ኤዶምያስ፣ 3:19
6. ጽዮን፣ 2:1
7. የሰጢም ሸለቆ፣. 3:18 (NIV፣ "...የግራር")

XI. የተማሪ ይዘት ጥያቄዎች


1. 1፡4 ላይ ያሉት አንበጣዎች የተለዩ ዓይነት አንበጣዎች ናቸውን ወይስ በአንበጣ እድገት-ዑደት የተለየ ደረጃ ላይ ያሉ?


2. ካህናቱ እንዲያዝኑ የተነገራቸው ለምንድነው?

3. 1፡15 ላይ ጥቅም ላይ የዋለውን የእግዚአብሔርን ስም ግለጽ።

4. ከምዕራፍ 2፣ አኪ (አዲስ ኪዳን) ላይ ጥቅም ላይ የዋሉት ሁለት ቁጥሮች ምንድናቸው? በማን?

5. 3፡15 በጥሬው ነው ወይስ በዘይቤ፣ ለምንስ?


ANCIENT
NEAR EAST
N
S
E
W


PALESTINE
0 10 20 30 40
SCALE IN MILES

# መግቢያ ለትንቢተ አሞጽ

I. የመጽሐፉ ስም

ሀ. የተሰየመው ነቢዩን ተከትሎ ነው።

ለ. አሞጽ ማለት፡
1. "ሸክም መሆን።"
2. "ሸክም መሸከም።"
3. "ማጽናት፣"
4. አንደኛው ራቢያዊ ወግ/ልማድ እንደሚያስረግጠው፣ ስያሜው መልዕክቱን በሚቃወሙት የተሰጠ ነው፣ እሱ በግልጽ ወይም በጽናት እንዳልተናገረው አንድምታ ያለው።

ሐ. ይህ ብቸኛው በብሉይ ኪዳን ይህ ስም የሚገኝበት ነው።

II. ቅዱስ ቃልነቱ

ሀ. ይህ መጽሐፍ "የኋለኞቹ ነቢያት" ክፋይ ነው።

ለ. እሱም ከ "አስራ ሁለቱ" አንዱ ነው፣ የመለስተኛ ነቢያት ዝርዝር።

ሐ. እሱም በሦስተኛነት ነው የተቀመጠው፣ በመለስተኛ ነቢያት፣ ኤምቲ ላይ፣ ምንም እንኳ LXX እሱን በሁለተኛነት ዝርዝሩ ላይ ቢያስቀምጠውም።

III. ዘውግ

ሀ. ይህ ከጽሑፍ ነቢያት የመጀመሪያው ነው።

ለ. ይህ የጥንታዊ ዕብራይስጥ ትንቢታዊነት ነው። ይህ ግሩም የሆነ የዕብራይስጥ ቅኔና ምናባዊ ምሳሌ ነው።

IV. ደራሲነት

ሀ. የአይሁድ ወግ/ልማድ ዘወትር የሚያስረግጠው ደራሲው የቴቁሔው አሞጽ መሆኑን ነው።

ለ. ሰውየው፡
1. እሱ የይሁዳ ነው ከቴቁሔ፣ ይኸውም ከቤተ ልሔም በስተ ደቡባዊ ምስራቅ በግምት አምስት ማይል ላይ።
2. እሱም ነቢይ አልነበረም፣ አልያም የነቢይ ወገን ክፍል፣ ወይም ቡድን (ዝከ. 7፡14)። በዋነኛነት ነቢያት በማኅበረሰብ አንድ ላይ ነበር የሚኖሩት። ኋላ ላይ አንዳንዶች በቤተ-መንግሥት መታወቅ ጀመሩ።
3. እሱ በግልጽ የኖረው "በአነስተኛ በጎች" ጠባቂነት ነው (ዝከ. 1፡1)። እሱን ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋለው ቃል ያልተዘወተረ ነው፣ ነገር ግን ጥቅም ላይ የሚውለው ለባለ በጎች ነው (II ነገሥ. 3፡4)።
4. እሱም የነበረው፡ (1) የፍራፍሬ ተክል ባለቤት፤ ወይም (2) "ወርካ ለቃሚ" (ዝከ. 7፡14)። ይህም ዓመታዊውን ወደ ሌላ ስፍራ መዛወርን ያካትታል። እነዚህ ዛፎች "በለስ-የእንጆሪ ዘር" በመባል ይታወቃሉ። ፍሬው ባብዛኛው በለስን ይመስላል። እሱም እያንዳንዱ ይቀደዳል/ይወጋል፣ ባግባቡ እንዲበስል። ይህ እጅግ ጠቃሚ የሆነ ምርት ነው፣ ለቅርብ ምስራቅ ሕዝቦች። ዳዊት እንዲያውም ልዩ ወኪል ሾሞ ነበር (I ዜና. 27፡28)።
5. የአይሁድ ወግ/ልማድ የሚለው እሱ የተዋጣለት የሥራ/ንግድ ሰው ነበር። ይህም እጅግ የተለየ ነው፣ ዛሬ ካለው የተለመደ አተያይ አንጻር፣ እሱ ደሀ የገጠር ገበሬ ለመሆኑ። ከእርሱ የቅኔ ክብደት/ከፍተኛነት እና ሙያዊ ሥነ-ጽሑፍ የተነሣ የአይሁድ ወግ ልክ ነው! ከII ሳሙኤል 14፡2 የምንረዳው ቴቁሔ በግልጽ የሚታወቀው በጠቢባን ዜጎቹ ነው። እሱም የመጀመሪያው የእስራኤል ነቢይ ነው፣ መልዕክቶቹን ለመጻፍ። አንደኛ መደብ ነጠላ ተውላጠ ስሙን ተገንዝብ፣ 5፡1፤ 7፡1-9፤ 8፡1 እና 9፡1 ላይ።
6. እሱም የሰበከው ለሰሜን የእስራኤል መንግሥት ነው። እኛ በርግጠኝነት የምናውቀው ቤቴል የመስበኪያ ስፍራ መሆኑን ነው፣ ነገር ግን ምናልባት በርካታ መልከዓ-ምድራዊ ስፍራዎች በእስራኤል ሊኖሩ ይችላሉ።

ሐ. የደራሲነቱ ችግር፣ ችግር አለበት፣ ምክንያቱም፡
1. መጽሐፉ የሚለው እሱ ደሀ የግብርና ሠራተኛ ነው።
2. ስልቱና ቅኔው እጅግ ግሩም ነው፣ እጅግ የተማረ ሰው አንድምታ ያለው።
3. የእሱ ስብከት በቃል ተነግረው ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን እነርሱ እጅግ መዋቅራዊና የተመዛዘኑ ናቸው፣ ይህም የተጻፈ ሥነ-ጽሑፍ መሆኑን የሚያመለክት።
4. ብዙዎች የሚገምቱት አሞጽ የአዘጋጅ ወይም የጸሐፊ ዕርዳታ ማግኘቱን ነው።

V. ጊዜው

ሀ. በአንጻራዊነት የዚህን ትንቢት ጊዜ ማስቀመጥ ቀላል ነው፣ 750 ቅ.ል.ክ አካባቢ፣ 10 ዓመት በመደመር ወይም በመቀነስ።

ለ. የአሞጽ የመጀመሪያው ቁጥር (መስመር) ረጅምና እጅግ ቁልጭ ያለ ጊዜ ለማመላከት የሞከረ ነው፣ ከማንኛውም የብኪ መጽሐፍ ይልቅ፡
1. ዖዝያን የገዛው በ783-742 ቅ.ል.ክ አካባቢ ነው (ብራይት)

2. ኢዮርብዓም II የገዛው በ786-746 ቅ.ል.ክ አካባቢ ነው (ብራይት)
3. የምድር መናወጡም ደግሞ የመጽሐፉን ጊዜ ለማሳየት የተደረገ ሙከራ ነው (ዝከ. 1:1፤ 8:8፤ 9:1፣5)። ጆሴፈስ እሱን የሚያዛምደው ከII ዜና. 26:16-21 ጋር ነው፣ ዖዝያን መሥዋዕት ባቀረበበት ጊዜ። በሃዞር የተደረጉ አርኪዮሎጂያዊ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በ760 ቅ.ል.ክ አካባቢ ነው (ያዲን፣ 1964)።

ሐ. በ5፡8 እና 8፡9 የፀሐይ ግርዶሽ ተጠቅሷል። ይህም በአሦር ሰነዶች ላይ ከተጠቀሰው ጋር አንድ ዓይነት ሊሆን ይችላል፣ ሰኔ 15፣ 763 ቅ.ል.ክ የተከሰተው፣ የሆነ ሆኖ፣ ሌላ ሙሉ ለሙሉ የፀሐይ ግርዶሽ የካቲት 9፣ 784 ቅ.ል.ክ ተከስቷል።

መ. አሞጽ ከአሜስያስ ጋር ተወዛግቧል/ተጋጭቷል፣ ከቤቴል ዋነኛ ካህን፣ በኢዮርብዓም II ሥልጣን ሥር፣ ደግሞም የዚህን መጽሐፍ ጊዜ አመላክቷል (7፡10-17)።

VI. ታሪካዊ መቼት

ሀ. ትይዩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነገሮች ተገኝተዋል፡
1. II ነገሥት 14:3-17:6
2. II ዜና መዋዕል 25-28
3. ሆሴዕ
4. ኢሳይያስ
5. ሚክያስ

ለ. በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ያለ የአመንዝራነት አቋም ቀለል ያለ ማጠቃለያ ሆሴዕ ላይ ሊታይ ይችላል፡
1. 2፡16፣ "ከዚያም በኋላ በኣሌ ብለሽ አትጠሪኝም"
2. 4፡12-13፣ "…ሴቶች ልጆቻችሁ ይገለሙታሉ…"
3. 4፡17፣ "ኤፍሬም ከጣዖታት ጋር ተጋጠመ፤ ተወው"
4. 13፡2፣ "ሰዎች እምቦሳውን ሳሙ!" (አምልኳዊ)

ሐ. ማኅበራዊ መቼት
1. እሱም የኢኮኖሚያዊ ብልጽግናና የወታደራዊ መስፋፋት ጊዜ ነበር፣ ለሁለቱም ለእስራኤልና ለይሁዳ። ሆኖም፣ ይህ ብልጽግና ጠቀሜታው ለሀብታም መደብ ብቻ ነበር። ደሀው ይበዘበዛል፣ ግፍም ይፈጸምበታል። እሱም ከሞላ ጎደል የሚመስለው "ገንዘብ እና ጠመንጃ" ተጨማሪ ጣዖት የሆነበት ነበር!
2. ማኅበራዊ ጽናቱ (አቋሙ) እና ንብረት አያያዙ፣ የሁለቱም የእስራኤልና የይሁዳ በርከት ካሉ ምክንያቶች ጋር ይያያዛል፡
   ሀ. ብልጽግና ያለውና ረጅሙ የኢዮርብዓም II አገዛዝ (786-746 ቅ.ል.ክ) በሰሜን እና ዖዝያን (783-742 ቅ.ል.ክ) በደቡብ።
   ለ. የግብፅና የሜሶፖታሚያ ጊዜያዊ (የወቅቱ) ውድቀት።
   ሐ. አሦራውያን ሶርያን ማሸነፋቸው፣ በአዳድ-ኒራሪ III በ802 ቅ.ል.ክ።
   መ. በእስራኤልና በይሁዳ መካከል የግጭቱ መርገብ (አለመኖር)።
   ሠ. ከሰሜን ወደ ደቡብ የሚዘልቁት የንግድ መስመሮች ላይ የሚጣለው ግብርና ብዝበዛ (ሀብት ማሰባሰብ)፣ በፍልስጥኤም የመሬት (የብስ) ድልድይ ላይ፣ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ማምጣት ችሏል፣ ሀብታሙ መደብ አባካኝ እንዲሆን አድርጓል።
3. "የሰማርያ መነጠል" ይኸውም በኢዮርብአም II ያገዛዝ ዘመን የሆነ፣ የሰሎሞንን የመሰለ አስተዳደራዊ አደረጃጀት እንዲኖር ያደረገ ይመስላል። ይህም "በአላቸው" እና "በሌላቸው" (ሃብታምና ደሀ) መካከል ያለውን ሰፊ ክፍተት የሚያረጋግጥ ይመስላል።
4. የባለጠጎች ታማኝ አለመሆን አሞጽ ላይ በግልጽ ተኮንኗል፣ እሱም "የማኅበራዊ ፍትሕ ነቢይ" የሚባለው። የዳኝነት ሥርዓቱ ጉቦኛ መሆን እና የግብይት ሚዛኖች ሀሰተኛ መሆን ሁለት ግልጽ የሆኑ የግፍ ምሳሌዎች ናቸው፣ በሁለቱም በእስራኤልም ሆነ በይሁዳ በአጠቃላይ የተለመዱ።

መ. ሃይማኖታዊ መቼት
1. በርካታ ውጫዊ ሃይማኖታዊ ድርጊቶች የሚፈጸሙበት፣ ነገር ግን እጅግ ያነሰ እውነተኛ እምነት የነበረበት ጊዜ ነበር። የከነአን የመራባት የአምልኮ ሥርዓት ከእስራኤል ሃይማኖት ጋር የተደባለቀበት ነበር። ሕዝቡ አመንዝራዎች ነበሩ፣ ነገር ግን ያህዌአዊነት ይሉት ነበር። የእግዚአብሔር ሕዝብ ፖለቲካዊ ጉድኝት ውስጥ መግባቱ፣ ወደ ጣዖት አምልኮና ልምምድ ውስጥ አስገባቸው።
2. የእስራኤል አመንዝራነት II ነገ. 17:7-18 ላይ ተመልክቷል።
   ሀ. ቁ. 8 የከነአናውያንን የአምልኮ ልምምድ ተከተሉ።
      1) የመራባት አምልኮ
         (ሀ) ከፍ ባሉ ስፍራዎች፣ ቁ. 9፣10፣11
         (ለ) የከበሩ ሐውልቶች (በአል)፣ ቁ. 10፣16
         (ሐ) የማምለኪያ አጸዶች፣ ቁ. 16 እነዚህ የእንጨት ቅርጾች የበአል የሴት ጓደኛ ምስል ያለባቸው ነበሩ። እነርሱም አንድም የተቀረጹ ግንዶች ወይም ለምለም ዛፎች ነበሩ።
      2) መናፍስት ጠሪነት፣ ቁ. 17። ይህ ሌዋ. 19-20 እና ዘዳ. 18 ላይ በዝርዝር ተብራርቷል።
   ለ. ቁ. 16 እነርሱ ሁለቱን የወርቅ ጥጃዎች ማምለካቸውን ቀጥለዋል፣ በያህዌ ተምሳሌትነት፣ በዳንና ቤቴል ላይ በኢዮርብአም I የተቀመጡ (I ነገ. 12:28-29)።
   ሐ. ቁ. 16 የባቢሎንን አማልክት አስታሮትን አምልከዋል፡ ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት እና ኅብረ-ከዋክብት።
   መ. ቁ. 18 የፍንቄውያንን የመራባት የእሳት ጣዖት፣ ሞሎክን አምልከዋል (ሌዋ. 18:21፤ 20:2-5)።
3. በአላዊነት (cf. W. F. Albright's *Archaeology and the Religion of Israel, page* 82ff)
   ሀ. የእኛ የተሻለ ምንጫችን "የኡጋሬት የበአል ኢፒክ" ነው።
      1) እሱም በአልን የሚገልጸው እንደ ወቅታዊ፣ የሚሞት እና የሚነሣ ጣዖት አድርጎ ነው። እሱም በ*ሞት* (የጣዖት ስም) ተሸንፎ ከምድር በታች ታስሯል። በምድር ያለ ሕይወት ሁሉ ፍጻሜውን አግኝቷል። ነገር ግን በሴቷ ጣዖት በመታገዝ እሱ ተነሥቶ *ሞትን* አሸንፏል፣ በየጸደዩ። እሱ የመራባት ጣዖት ነበር፣ በማስመሰል አስማት የሚመለክ።
      2) እሱም ደግሞ ሃዳድ በመባል ይታወቃል።
   ለ. ኤል የከነአናውያን ጣዖታት ሁሉ አለቃ ጣዖት ነው፣ ነገር ግን የበአል ታዋቂነት ስፍራውን አስለቀቀው።
   ሐ. እስራኤል የሲዶናውያን በአላዊነት እጅግ ተጽዕኖ አሳድሮበታል፣ በኤልዛቤል በኩል፣ እሷም የሲዶናውያን ንጉሥልጅ የነበረች። እሷም በአምሪ ለልጁ ተመረጠች፣ ለአክአብ።

መ. በእስራኤል በአል ይመለክ የነበረው በአጥቢያው ከፍተኛ ስፍራዎች ላይ ነበር። እሱም ተምሳሌት የሚሆነው ከፍ የተደረገ ድንጋይ ነበር። የእሱም ጓደኛ (ሚስት) አሼራህ ነች፣ ተምሳሌት የተደረገላትም የተጣመመ ግንድ ነው፣ ተምሳሌትነቱም የሕይወት ዛፍ።

4. በርከት ያሉ የአመንዝራነት (ጣዖት አምላኪነት) ምንጮችና ዓይነቶች ተጠቅሰዋል።
   ሀ. የወርቅ ጥጃዎች በቤቴልና በዳን፣ በኢዮርብአም I ተቀምጠዋል፣ ያህዌን ለማምለክ።
   ለ. የሲዶናውያን የመራባት አምላክ እና አምላኪት፣ በአጥቢያ ከፍተኛ ቦታዎች።
   ሐ. ተፈላጊው አመንዝራነት፣ በዛ ጊዜ በነበረው ፖለቲካዊ ኅብረት (ቃል-ኪዳን)።

ሠ. የሰሜን ፖለቲካዊ መቼት

1. ኢዮርብዓም II የእስራኤልየመጨረሻው ጠንካራ ንጉሥ ነበር። እሱም ከኢዩ ዘር አራተኛው እና ለመግዛት ከተተነበየለት የመጨረሻው ነበር (II ነገሥት 10:30)። እሱም ረጅምና ከፖለቲካ አኳያ የተሳካለት አገዛዝ ነበር (786-746 ቅ.ል.ክ)።
2. ከኢዮርብዓም II ሞት በኋላ ስድስት ነገሥታት ነበሩ፣ በሃያ አምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ።
   ሀ) ዘካርያ(II ነገሥት 15:8-12)። እሱም ከስድስት ወራት በኋላ ብቻ ተገደለ።
   ለ) ሰሎም (II ነገሥት 15:13-15)። እሱም ከአንድ ወር በኋላ ብቻ ተገደለ።
   ሐ) ምናሔም (II ነገሥት 15:16-22)።እሱም አስር ዓመት ገዛ፣ ነገር ግን ከባድ ግብር ለቴግላዝ-ፒሌሰር III ይከፍል ነበር።
   መ) ፋቂስያስ (II ነገሥት 15:23-26)።እሱም ሁለት ዓመት ነገሠ፣ ተገደለም።
   ሠ) ፋቁሔ (II ነገሥት 15:27-21)።እሱም አምስት ዓመት ነገሠ፣ ተገደለም። እሱም በርከት ያሉ ከተሞች በአሦር ተወሰዱበት።
   ረ) ሆሴዕ (II ነገሥት 15:30፤ 17:1-6)። እሱም ዘጠኝ ዓመት ገዛና በአሦር ተጋዘ፣ በ722 ሰማርያ ስትወድቅ።

3. የአሦርና የባቢሎን ወረራዎች አጭር ማጠቃለያ፣ በስምንተኛው ክፍለ-ዘመን እሱም ፍልስጥኤም ላይ ተጽዕኖውን ያሳረፈ፡
   ሀ) አራቱ የስምንተኛው ክፍለ-ዘመን ነቢያት በተግባር ላይ ነበሩ (ንቁ ተሳታፊ) የአሦር ጤግሮስ-ኤፍራጥስ ኢምፓየር መነሣት ጊዜ። እግዚአብሔር እነዚህን ጨካኝ ሕዝቦች ተጠቅሟል፣ በሕዝቡ ላይ ለመፍረድ፣ በተለይም እስራኤል። ተለይቶ የተቀመጠው ኢጋጣሚ የዮርዳኖስ አካባቢ የፖለቲካ እና ወታደራዊ ኅብረት፣ እሱም "ሲሮ-ኤፍራማቲክ ሊግ/ማኅበር" በመባል የሚታወቀው መቋቋም ነው (735 ቅ.ል.ክ)። ሶርያና እስራኤል ይሁዳን ለማስገደድ ሞክረዋል፣ አሦርን በመቃወም እንዲተባበራቸው። በምትኩ አካዝ ለአሦር ደብዳቤ ላከ፣ እንዲረዳው። የመጀመሪያው ብርቱ፣ ሰፊ-ግዛት-ተኮር የአሦር ንጉሥ ቲግላዝ- ፒሌሰር III (745-727 ቅ.ል.ክ)፣ ለወታደራዊ ግጥሚያ/መቋቋም ምላሽ ሰጥቶ ሶርያን ወረረ።ኋላ ላይ የአሦር አሻንጉሊት ንጉሥ፣ ሆሴዕ (732-722 ቅ.ል.ክ)፣ በእስራኤል፣ ደግሞ ዓመጸ፣ ለግብፅ ጥያቄ አቅርቦ። ሻልማኔሰር V (727-722 ቅ.ል.ክ) እስራኤልን በድጋሚ ወረረ። እሱም እስራኤል ከመረታቱ በፊት ሞተ፣ ነገር ግን የእሱ ወራሽ ሳርጎን II (722-705 ቅ.ል.ክ)፣ የእስራኤልን ዋና ከተማ ሰማርያን ያዘ፣ በ722 ቅ.ል.ክ። አሦር በዚህ ኢጋጣሚ ከ27000 በላይ እስራኤላውያንን አጋዘ (አፈናቀለ)፣ ቲግላዝ-ፒሌሰር ቀደም ብሎ በ732 ቅ.ል.ክ በሺህዎች የሚቆጠሩትን እንዳጋዘ።
   ለ) ከአካዝ ሞት በኋላ (735-715 ቅ.ል.ክ) ሌላ ወታደራዊ ኅብረት ተመሠረተ፣ በዮርዳኖስ አካባቢ አገሮች እና በግብፅ፣ አሦርን በመቃወም (714-711 ቅ.ል.ክ)። እሱም "የአሽዶድ ዓመጽ" በመባል ይታወቃል። በርካታ የይሁዳ ከተሞች ተደመሰሱ፣ አሦር በድጋሚ በወረረበት ጊዜ። መነሻው ላይ ሕዝቅያስ ይሄንን ኅብረት ደግፎት ነበር፣ ኋላ ላይ ግን ድጋፉን አስወጣ።
   ሐ) ሆኖም፣ እንደገና ሌላ ኅብረት በአሦር ብርቱ ንጉሥ በሳርጎን II ሞት የተገኘውን ኢጋጣሚ ለመጠቀም ሙከራ አደረገ፣ በ705 ቅ.ል.ክ፣ ከሌሎች በርካታ ዓመጸዎች፣ እነርሱም በአሦር ኢምፓየር ውስጥ ከተነሡት ጋር በመሆን።ሕዝቅያስ በዚህ ዓመጸ ላይ ሙሉ ለሙሉ ተሳትፏል። በዚህ ግጥሚያ ሳቢያ ሰናክሬ (705-681 ቅ.ል.ክ) ፍልስጥኤምን ወረረ (701 ቅ.ል.ክ) በኢየሩሳሌምም ከተማ አጠገብ ሰፈረ (II ነገ. 18-19፤ ኢሳ. 36-39) ነገር ግን ይህ ሠራዊት ተአምራዊ በሆነ መልኩ በእግዚአብሔር ተደመሰሰ። በሊቃውንት መካከል አንዳንድ ጥያቄዎች አሉ፣ ሰናክሬ ምን ያህል ጊዜ ፍልስጥኤምን እንደወረረ። (ምሳሌ፡ ጆን ብራይት (John Bright) አንድ ወረራ አለው በ701 ቅ.ል.ክ እናም ሌላ ታሳቢ በ688 ቅ.ል.ክ፣ ገጽ 270።) ሕዝቅያስ በአሦር ቁጥጥር ሥር ከመሆንን ተርፎ ነበር፣ ነገር ግን ከኩራቱ የተነሣ የይሁዳን መዝገብ (ሀብት) ለባቢሎናውያን ልዑካን በማሳየቱ፣ ኢሳይያስ የይሁዳን በባቢሎን እጅ መውደቅ ተነበየ (39:1-8)። ኢየሩሳሌም በናቡከደነፆር እጅ በ587-586 ቅ.ል.ክ ወደቀች።
   መ) ኢሳይያስ ደግሞ የእግዚአብሔርን ሕዝብ መመለስ ተነበየ፣ በቂሮስ II፣ የሜዶን-ፋርስ ገዥ አማካኝነት፣ (41:2-4፤ 44:28፤ 45:1፤ 56:11)። ነነዌ በ612 ቅ.ል.ክ በባቢሎን እጅ ወደቀች፣ ነገር ግን የባቢሎን ከተማ በ539 ቅ.ል.ክ በቂሮስ ሠራዊት እጅ ወደቀች። በ538 ቅ.ል.ክ ቂሮስ አዋጅ አወጣ፣ የተጋዙት ሕዝቦች ሁሉ፣ አይሁድንም ጨምሮ ወደ አገራቸው ሊመለሱ እንደሚችሉ። ይልቁንም እሱ ከራሱ ሀብት ልገሳ አደረገ፣ የየአገሬው መቅደሶች ዳግም ይገነቡ ዘንድ።

## VII. ጽሑፋዊ ምድቦች

ሀ. በአሕዛብ ላይ የቀረበ ክስ 1:1-2:3 (እስከ 2:16 ሊዘልቅ ይችላል)
1. ሶርያ (ደማስቆስ)፣ 1:3-5
2. ፍልስጥኤም (ጋዛ)፣ 1:6-8
3. ፍንቂ (ጢሮስ)፣ 1:9-10
4. ኤዶምያስ፣ 1:11-12
5. አሞን፣ 1:13-15
6. ሞዓብ፣ 2:1-3

ለ. በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ የቀረበ የተለየ ክስ፣ 2:4-6:14
1. ይሁዳ፣ 2:4-5
2. እስራኤል፣ 2:6-6:14 (በእስራኤል ላይ የፍርድ ዐውደ-ጽሑፍ፣ እስከ 6:14 ይዘልቃል)

ሐ. የፍርድ ራዕይ፣ 7:1-9:10
1. አንበጣ፣ 7:1-3
2. እሳት፣ 7:4-6
3. ቱምቢ (የግንብ ልኬት ማሳያ)፣ 7:7-17
4. ቃርሚያ (ግርድ)፣ 8:1-14
5. የመቅደሱ ጥፋት (ውድመት)

መ. መሢሐዊ ተስፋ፣ 9:11-15

VIII. ዋነኛ ሐቆች

ሀ. አሞጽ የእግዚአብሔርን ቁጣ የሚያያይዘው እስራኤል የሙሴአዊውን ኪዳን ከመጣሱ ጋር ነው። እኛ ማገናዘብ ይኖርብናል፣ በብሉይ ኪዳን የአጠቃሎሽ ኃላፊነትና በግለሰባዊ እምነት መካከል ያለውን ግንኙነት። እኛም የኅብረተሰባዊ ኃጢአት ችግር አለብን፣ እስራኤል እንዳደረገው ሁሉ፣ ሆኖም፣ ዘወትር በሐሳባችን ሁለት አቋሞች/መለኪያዎች ይኖራሉ፡

1. ግለሰባዊ የግል ሕይወታችንና እምነት፤
2. የተጠቃለለው ማኅበራዊ፣ ሕዝባዊ ሕይወታችን።

ለ. በምድር ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት መኖሩ፣ የያህዌ የፍርድ አካሄድ ዳራ ነው፣ ከእስራኤል ኪዳን ውጭ ባሉት ሕዝቦች ላይ። ይህም የእስራኤል የአሀዳዊ አምላክ መረዳት መሠረት ነው።

ሐ. ምዕራፍ 2፡9-12፣ እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ መፍረዱ መታየት የሚኖርበት በእርሱ የመልካምነት ድርጊት አኳያ ነው፣ በታሪክ ላይ። እግዚአብሔር እስራኤልን መምረጡና ኪዳን ማድረጉ ለጽኑ ፍርዱ ደረጃ ሆኗል። መታወስ የሚኖርበት "ብዙ ከተሰጠው ብዙ እንደሚጠበቅበት" ነው (ሉቃ. 12፡48)።

መ. ምዕራፍ 5 እምነትና ሕይወትን እንዳይለያዩ አድርጎ አያይዟቸዋል! አሞጽ ባለጸጎች ድሆችን መበዝበዛቸውን አውግዟል።

ሠ. እስራኤል በስሕተት ታምና ነበር፡

1. በሃይማኖቷ (ዝኪ. 4:4-5፤ 5:21-23)።
2. በኢኮኖሚያዊ ብልጽግናዋ (ዝኪ. 6:1)።
3. በወታደራዊ ኃይሏ፣ (ዝኪ. 2:14-16፤ 6:1ለ፣ 13)።

ረ. በእስራኤል እምነት-የለሽነት መካከል እንኳ ቢሆን በእግዚአብሔር ኪዳን ላይ ተስፋ አለ፣ በእግዚአብሔር መሢሕ፣ 9፡8ለ-15።

IX. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት እና ሰዎች በአጭሩ የሚገለጹ

ሀ. ቀላት እና/ወይም/ሐረጋት

1. "የምድር መናወጥ፣" 1፡1 (NASB እና NIV)
2. ምሽጎች፣ 1፡7 (NIV፣ "ምሽግ")
3. በትር (የገዥ)፣ 1፡8(NASB እና NIV)
4. "የኤዶምያስን ነገሥታት አጥንት አቃጥሏልና...፣" 2፡1 (NASB እና NIV)
5. "ችጋረኛውንም ስለ አንድ ጥንድ ጫማ፣" 2፡6፤ 8፡6 (NASB እና NIV)
6. "የመሠዊያው ቀንዶች፣" 3፡14 (NASB እና NIV)
7. "የዝኆን ጥርስ ቤቶች፣" 3፡15 (NIV፣ "በዝኆን ጥርስ የተጌጡ ቤቶች")
8. "ዓመት በዓላችሁን ጠልቼዋለሁ፣ ተጸይፌውማለሁ፣" 5፡21(NASB እና NIV)
9. የሰባ፣ 5፡22 (NIV፣ "የተመረጠ የወዳጅነት መሥዋዕት")
10. ቱምቢ፣ 7፡7 (NASB እና NIV)
11. "የሰማርያ ኃጢአት፣" 8፡14 (NIV፣ "የሰማርያ ሃፍረት")

ለ. ሰዎች


1. ናዝራውያን፣ 2:12
2. የባሳን ላሞች፣ 4:1
3. አልቃሾች፣ 5:16 (NIV፣ "አልቃሾች")
4. *Sikkuth* 5:26 (NIV፣ "የማምለኪያ አጸድ")
5. *Kiyyun* 5:26 (NIV፣ "የድጋፍ ግንብ")
6. አሜስያስ፣ 7:10
7. ኢዮርብዓም II፣ 7:10
8. ባለ-ራዕይ፣ 7:12


X. የካርታ ስፍራዎች

1. ቴቁሔ፣ 1:1
2. ቀረሜሎስ፣ 1:2
3. ገለዓድ፣ 1:3
4. ጋዛ፣ 1:6
5. አዛጦን፣ 1:8
6. አስቀሎና፣ 1:8
7. አቃሮን፣ 1:8
8. ቴማን፣ 1:12
9. ባሶራን፣ 1:12
10. ረባት፣ 1:14
11. ቤቴል፣ 4:4
12. ጌልጌላ፣ 4:4
13. ሰዶም፣ 4:11
14. ቤርሳቤህ፣ 5:5
15. ሐማት፣ 6:14
16. ዳን፣ 8:14

XI. የተማሪ ይዘት ጥያቄዎች

1. አሞጽ ደሀ የገጠር ገበሬ ነበር ወይስ ባለጠጋ ሰው?
2. እኛ ኃላፊነት የምንወስደው ለግለሰብ ኃጢአት ነው ወይስ ለኅብረተሰባችን የተጠቃለለ ኃጢአት?
3. የ3፡2-8 አጽንዖት ምንድነው?
4. ቤቴልና ጌልጌላ ለምን ተወገዙ/ተኮነኑ? የ4፡4-5 ሃይማኖታዊ ተግባር ለምን ተወገዘ?
5. እግዚአብሔር የእስራኤልን መሥዋዕት ለምን ናቀ (ሳይቀበል ቀረ)?
6. 5፡25-26 ለመተርጎም እጅግ የሚያስቸግረው ለምንድነው?
7. አሞጽ መሥዋዕታዊ ሥርዓቱን ኮንኗልን?
8. እግዚአብሔር ሐሳቡን ቀይሯልን?
9. ንስሐ መግባት ከይቅርታ ጋር የሚዛመደው እንዴት ነው? (ምዕራፍ 7)
10. የእግዚአብሔር ፍርድ የፍጻሜ መዳረሻዊ (የመጨረሻ) ነው ወይስ ጊዜያዊ?


ANCIENT
NEAR EAST
N
S
E
W


PALESTINE
0 10 20 30 40
SCALE IN MILES

# መግቢያ ለትንቢተ አብድዩ

I. የመጽሐፉ ስም

ሀ. የተሰየመው የነቢዩን ስም ተከትሎ ነው።

ለ. ስሙ "የያህዌ አገልጋይ" ማለት ነው

ሐ. እሱም የተለመደ የዕብራይስጥ ስም ነው (I ነገሥ. 18:3፤ I ዜና. 3:12፤ 7:3፤ 8:38፤ 9:16፥44፤ 12:9፤ 27:19፤ II ዜና. 17:7፤ 34:12፤ዕዝራ 8:9፤ነህ. 10:5፤ 12:25

II. ቅዱስ ቃልነቱ (ካኖናይዜሽን)

ሀ. ይህ መጽሐፍ "የኋለኞቹ ነቢያት" ክፋይ ነው (መጽሐፈ ጥበብ 49፡10)

ለ. እሱም ከ "አስራ ሁለቱ" ውስጥ ነው፣ የመለስተኛ ነቢያት ስብስብ (ቡድን) (ባባ ባትራ 14ለ)
1. እንደ ኢሳይያስ፣ ኤርምያስ እና ሕዝቅኤል፣ እነርሱ በአንድ ጥቅል ተካተዋል
2. አስራ ሁለቱን ነገዶች ይወክላሉ፣ የድርጅትን ተምሳሌታዊ ቁጥር
3. የመጻሕፍቱን ዜና መዋዕላዊ (ቅደም ተከተል) ወግ/ልማዳዊ አተያይ ያንጸባርቃሉ

ሐ. የ "አስራ ሁለቱ" ወይም መለስተኛ ነቢያት ተራ፣ በብዙ ሊቃውንት የሚያያዘው በዜና መዋዕላዊ ቅደም ተከተል ነው። ሆኖም፣ በዚህ አተያይ ላይ ችግሮች አሉ፡
1. ቀዳሚዎቹ ስድስት መጻሕፍት ልዩነት አላቸው፣ በ ኤምቲ/MT እና ኤልኤክስኤክስ/LXX መካከል።

| ኤምቲ/MT | ኤልኤክስኤክስ/LXX |
|---|---|
| ሆሴዕ | ሆሴዕ |
| ኢዩኤል | አሞጽ |
| አሞጽ | ሚክያስ |
| አብድዩ | ኢዩኤል |
| ዮናስ | አብድዩ |
| ሚክያስ | ዮናስ |

2. ውስጣዊ ማስረጃው አሞጽን የሚያስቀምጠው በታሪክ ቅደም ተከተል መሠረት ከሆሴዕ በፊት ነው።
3. የኢዩኤል ጊዜ እጅግ አከራካሪ ነው። እኔ በዝርዝር ላይ ያስቀመጥኩት እንደ ቀደምት ድኅረ-ግዞት ነቢይ አድርጌ ነው፣ ከአብድዩ ጋር በተጓዳኝ።

III. ዘውግ -- ጥንታዊ የዕብራይስጥ ትንቢታዊ ቅኔ

IV. ደራሲነት

ሀ. ስለ ነቢዩ የሚታወቅ ነገር የለም

ለ. በርከት ያሉ ንድፈ-ሐሳቦች፡
1. የጥንታዊ አይሁድ ጠቅላይ ጉባኤ (ሳንሄድሪን) 39ለ (ታልሙድ) የሚለው፣ እሱ የንጉሥ አክአብ አገልጋይ ነበር፣ 1 ነገሥ. 18:3-16
2. ሱዶ-ኢፒፋነስ (ጥንታዊ ቤተ-ክርስቲያን) "የነቢያት ሕይወት" በሚለው ጽሑፉ እንዳለው፣ እሱ የንጉሥ አካዝያስ ከፍተኛ ወታደራዊ ባለሥልጣን ነበር (842 ቅ.ል.ክ) II ነገሥ. 1:12
3. ጆን ካልቪን የሚለው እሱ የኢየሩሳሌም ጥፋት የዓይን ምስክር ነበር (586 ቅ.ል.ክ በናቡከደነፆር II ወይም ባቢሎን)።

ሐ. ስሙ ርዕስ ሆኗል።

V. ጊዜው

ሀ. ይህ መጽሐፍ ከሥነ-ቋንቋ አኳያ ከኤርምያስ 49:7-12 (አብድ. ቁ. 1-9) እና ኢዩኤል 2:32 (አብድ. ቁ.10 ጋር ይዛመዳል):
1. ኢ.ጄ. ያንግ የሚያስቀምጣቸው በዚህ ቅደም ተከተል ነው፡ አብድዩ፣ ኤርምያስ
2. አር.ኬ ሃሪሰን በዚህ ቅደም ተከተል ነው የሚያስቀምጣቸው፡ ኤርምያስ፣ አብድዩ፣ (450 ቅ.ል.ክ) እና ኢዩኤል (400 ቅ.ል.ክ)። ይህም መጽሐፉን ቀደም ያለ ድኅረ-ግዞት ያደርገዋል።
3. ኬይል በዚህ ቅደም ተከተል ያስቀምጣቸዋል፡ አብድዩ፣ ኢዩኤል፣ ኤርምያስ

ለ. ግልጽ የሆነው ነገር፣ መጽሐፉ የሚዛመደው ከይሁዳ መወረርና ከኢየሩሳሌም በኤዶምያስ መስፈራራት ጋር ነው። አንዳንድ ታሳቢ ጊዜያት፡
1. ኢየሩሳሌም በሺሻክ ተወሰደች፣ የግብፅ ፈርዖን፣ በሮብአም አምስተኛ ዓመት፣ 822-915 ቅ.ል.ክ (I ነገሥ. 14:25-28፤ II ዜና. 12:2-10)።
2. ኢየሩሳሌም በዓረብ ሊግ እና በፍልስጥኤም ተወሰደች፣ በኢዮራም አገዛዝ፣ 849-842 ቅ.ል.ክ (II ነገሥ. 8:20፤ II ዜና. 21:16-17፤ 22:1።
3. ኢየሩሳሌም በሶርያውያን ተወሰደች፣ በኢዮአስ አገዛዝ፣ 837-800 ቅ.ል.ክ (II ዜና. 24:23-24)።
4. ኢየሩሳሌም በእስራኤል ተወሰደች (ዮአስ)፣ ከኤዶም መሸነፍ በኋላ፣ በአሜስያስ አገዛዝ (II ነገሥ. 14:7-14 (842 ቅ.ል.ክ.)

5. ይሁዳ በኤዶማውያን ተጠቃ (II ዜና. 28:17፤ 19:8-9፤ II ነገሥ. 16:1-20)።
6. ኢየሩሳሌም በናቡከደነፆር በርከት ያለ ጊዜ ተወስዳለች፣ 605፣ 597፣ 586፣ 582 ቅ.ል.ክ:
   ሀ. 605 ቅ.ል.ክበኢዮአቄም አገዛዝ (ዳን. 1:1-2)
   ለ. 597 ቅ.ል.ክበኢዮአቄም አገዛዝ (II ነገሥ. 24:8-17፤ II ዜና. 36:9-10፤ሕዝ.
   ሐ. 586 ቅ.ል.ክበሴዴቅያስ አገዛዝ (II ነገሥ. 24:18-25:21፤ II ዜና. 36:11-21፤ ሰቆቃ ወኤርምያስ፤ 137:7
   መ. 582 ቅ.ል.ክጎዶልያስ ባቢሎናዊ ገዥ (II ነገሥ. 25:22-26)

ሐ. ሁለት ጊዜያት አሉ፣ የሊቃውንት ድጋፍ ያገኙ፡
1. የኢዮርአም አገዛዝ ፊተኛ ጊዜያት (849-842 ቅ.ል.ክ) ምክንያቱም፡
   ሀ. የመጽሐፉ ስፍራ በ "አስራ ሁለቱ" ውስጥ
      (1) 8ኛ ክፍለ-ዘመን ምድብ፡ አሞጽ፣ ሆሴዕ፣ ሚክያስ፣ (ኢዩኤል?) እና አብድዩ
      (2) 7ኛ ክፍለ-ዘመን ምድብ፡ ናሆም፣ ዕንባቆም እና ሶፎንያስ
      (3) ድኅረ-ግዞት ምድብ፡ ሐጌ፣ ዘካርያስ እና ሚልክያስ
   ለ. አብድዩ የመቅደሱን መፍረስ አልጠቀሰም
   ሐ. የተጠቀሱት መንግሥታት ቅድመ-ግዞት ናቸው፣ ድኅረ-ግዞት ሳይሆኑ
   መ. ኃጢአቶቹ ተመሳሳይ ናቸው፣ በ8ኛ ክፍለ-ዘመን ነቢያት ከተቆጠሩት/ከተለዩት ጋር
   ሠ. ምንም ዓይነት አራማዊ ቃላት፣ ፈሊጦች ወይም መግለጫዎች የሉትም
2. የኋለኛ ቀን ከናቡከደነፆር II የኢየሩሳሌም ወረራ ጋር የሚዛመድ
   ሀ. ቁ. 11-14 ከኢየሩሳሌም መውደቅ ጋር የሚገጥም ይመስላል፣ በ586 ቅ.ል.ክ
   ለ. ኤዶምያስ በዚህ ወረራ ላይ ተሳትፏል
      (1) በይሁዳ ውድቀት መደሰቱ
         (ሀ) መዝ. 137:7
         (ለ) ሰቆ. 2:15-17፤ 4:21
         (ሐ) ሕዝ. 36:2-6
         (መ) I ኢስድራስ 4:45፣ 50
      (2) ለይሁዳ መውደቅ ረድቷል:
         (ሀ) ሕዝ. 25:12-14
         (ለ) ሕዝ. 35:1-15

VI. ታሪካዊ መቼት

ሀ. ኤዶምያስ፣ የትንቢቱ ርዕሰ-ጉዳይ፣ ቁ. 1-9፣ 18፣ 21
1. ኤዶም ከሙት ባሕር በስተምስራቅ ያለ ሕዝብ ነው፣ ከዔሳው፣ ከያዕቆብ ወንድምዘፍ. 25-29፤ 32-33)። ዔዶም ማለት "ቀይ" ነው፣ ዔሳው "ፀጉራም" ማለት ሲሆን (ዘፍ 25:25፣ 30)።
2. እስራኤል ዔዶምን እንዲያከብር ታዟል (ዘዳ. 23:7)
3. እስራኤልና ዔዶም ቀጣይነት ያለው ችግር አለባቸው:
   ሀ. ዘኁ. 20:14-21
   ለ. መሳ. 11:16-17
   ሐ. I ሳሙ. 14:47-48
   መ. II ሳሙ. 8:14
   ሠ. I ነገሥ. 11:14-25
   ረ. II ነገሥ. 14:22፤ 16:5-6
   ሰ. II ዜና. 20:10-30፤ 21:8
   ሸ. አሞጽ 1:6፣ 9
4. ሌሎች በዔዶም ላይ በአሉታ የተተነበዩ:
   ሀ. እስ. 34:5፤ 63:1
   ለ. ኤር. 49:7-22
   ሐ. ሰቆ. 4:21-22
   መ. ሕዝ. 26:12፤ 35:1፤ 36:2-6
   ሠ. አሞጽ 1:11-12
5. ኤዶምያስ የተኮነነችበት/የተወገዘችበት ምክንያት፡
   ሀ. በኩራቷ፣ ቁ. 3-4
      (1) በመልክዓ-ምድራዊ ደኅንነት
      (2) በፖለቲካዊ ኅብረት እና ወታደራዊ ኃይል
      (3) በንግድ ብልጽግና
      (4) በወግ/ልማዳዊ ጥበብ
   ለ. ይሁዳን በማናወጧ/ላይ በማመጿ፣ በዘመዷ ላይ፣ ቁ. 10-14
      (1) በኢየሩሳሌም ውድቀት መደሰት (ሰቆ. 2:15-17፤ 4:21)
      (2) ለመርዳት እምቢ ማለቷ (ቁ. 15)
      (3) ለጠላት ፈጣን ድጋፍ ማድረጓ (ቁ. 14)
      (4) የይሁዳን ንብረት መውሰዷ (ኤር. 13፡19)
   ሐ. ያህዌን መተዋ እና መናቋ (ቁ. 16)

ለ. ኤዶምያስ በእግዚአብሔርና በእሱ ሕዝብ ላይ ያመጹ አሕዛብ ሁሉ ተምሳሌት ነው፣ ቁ. 15-21 (መዝ.2)።

ሐ. ታሳቢ ታሪካዊ የትንቢቱ ፍጻሜዎች
1. የኤዶምያስ በአዲሲቱ ባቢሎን መደምሰስ፣ ከኢየሩሳሌም መውደቅ 5 ዓመት በኋላ አካባቢ፣ 580 ቅ.ል.ክ።
2. የኤዶምያስ ከፔትራ መፈናቀል፣ በናባቴአን ዓረቦች፣ በ550-449 ቅ.ል.ክ አካባቢ (ሚል. 1:2-5)። ኤዶምያስ በነህምያ ዝርዝር ውስጥ አልተጠቀሰም፣ በአካባቢው ጠላቶች፣ ነገር ግን በዓረብ ነገዶች ተተክቷል። ኤዶምያስ ወደ ኔጌቭ ተዟውሯል።
3. የኤዶምያስ ሽንፈት፣ በአሌክሳንደር ጀነራል፣ አንቲጎነስ በ312 ቅ.ል.ክ (በዲኦዶረስ ሴኩለስ ላይ የተመዘገበ)
4. የኤዶምያስ ኔጌቭ ላይ መሸነፍ፣ በጁዳ ማካቤዩስ፣ በ175 ቅ.ል.ክ አካባቢ (I ማካቢስ 5:3፣15፤ II ማካቢስ 10:15፤ Josephus' *Antiquities of the Jews* 12:8:1 ፤ 13:9:1
5. ኤዶምያስ ይሁዲነትን ለመቀበል ተገደደ፣ በጆን ሀይርካነስ፣ በ125 ቅ.ል.ክ። እነርሱ አሁን ኤዶማውያን በመባል ይጠራሉ።
6. የሮም ጀነራል፣ ቲቶ፣ የኤዶማውያንን ተጽዕኖ ሙሉ ለሙሉ ደመሰሰ፣ በ70 ዓ.ም።

VII. ጽሑፋዊ ምድቦች

አጭር የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር *The New International Commentary series on* 'Joel ላይ የተወሰደ፣ በ "ኢዩኤል፣ አብድዩ፣ ዮናስ፣ እና ሚክያስ" በአለን፣ ገጽ 142

ሀ. የኤዶምያስ ጥፋት (2-9)
1. የኤዶምያስ ውድቀት (2-4)
2. የኤዶምያስ ፈጽሞ (ሙሉ ለሙሉ) መገልበጥ (5፣6)
3. የኤዶምያስ ወዳጆች አታላይነት (ክህደት) (7)
4. የኤዶምያስ ጥበብንና ተዋጊዎችን/ኀያላንን ማጣት (8፣9)

ለ. የኤዶምያስ የበደል ሥራ (10-14፣ 15ለ)
1. የኤዶምያስ ወንድማማችነትን አለማክበር/መጣስ (10፣ 11)
2. የኤዶምያስ አሿፊነት (12)
3. የኤዶምያስ ተላላፊነት (13)
4. የኤዶምያስ መተባበር (ከጠላት ጋር)፣ እና የሚመጣው ብድራት/ቅጣት (14፣ 15ለ)

ሐ. ኤዶምያስ በእግዚአብሔር ቀን (15ሀ፣ 16-21)
1. የእግዚአብሔር ቀን (15ሀ፣ 16)
2. የቅሬታዎቹ ሚና (17፣ 21)
3. የይሁዳ እሳት እና የኤዶምያስ ገለባ (18)
4. ዳግም የተገኘ ምድር (19፣ 20)

VIII. ዋነኛ ሐቆች

ሀ. የእግዚአብሔር ጠላቶችና የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶች ይቀጣሉ። ኤዶምያስ እንደ ዓመጸኛ፣ እንደማያምን ሕዝብ ዓይነት (ዝኪ. ቁ. 15)

ለ. እግዚአብሔር ሕዝቡን ያከብራል፣ እንደ ኪዳን ተስፋው። ቅድስና የእግዚአብሔር ግብ ነው፣ ለሕዝቡ።

ሐ. ታሪካዊ ሁኔታው ይገለበጣል። ኤዶምያስ ይደመሰሳል፤ የእግዚአብሔር ሕዝብ ይባረካል።

IX. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት እና ሰዎች በአጭሩ የሚገለጹ

ሀ. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት
1. "እንደ ንስር ከፍ አድርገህ ብትገነባ" 1:4 (NIV፣ "ጎጆህም በከዋክብት መካከል ቢሆን")
2. "በወንድምህ በያዕቆብ ላይ ስለተደረገ ግፍ…" 1:10 (NASB እና NIV)
3. "በኢየሩሳሌም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ" 1:11 (NASB እና NIV)
4. "የእግዚአብሔር ቀን ቀርቦአልና" 1:15 (NASB እና NIV)

ለ. ሰዎች
1. ዔሳው፣ 1:8

X. የካርታ ስፍራዎች (አመላካቾች)
1. ኤዶምያስ፣ 1:1
2. ቴማን፣ 1:9
3. ጽዮን ተራራ፣ 1:17
4. ኔጌቭ፣ 1:19፣ 20 (ወይም "ኔጌብ")
5. ሽፌላህ (ስፋራይድ)፣ 1:19 (NIV፣ "ኮረብታ")
6. ገለዓድ፣ 1:19


XI. የተማሪ ይዘት ጥያቄዎች

1. የአብድዩ መጽሐፍ ማዕከላዊ ጭብጥ ምንድነው?


2. ኤዶምያስ ለምን በከፋ ሁኔታ ተፈረደበት?

3. ኤዶምያስ ለምን ለአሕዛብ ሁሉ እንደ ተምሳሌት ጥቅም ላይ ዋለ?

4. አብድዩ አኪ ላይ ተጠቅሷልን ወይስ ተጠቁሟልን?


ANCIENT
NEAR EAST
N
S
E
W

# PALESTINE



# መግቢያ ለትንቢተ ዮናስ

I. የመጽሐፉ ስም

ሀ. መጽሐፉ የተሰየመው ነቢዩን ተከትሎ ነው

ለ. የስሙ ፍች "ርግብ" ማለት ነው። ይህም የብሔረ-እስራኤል ተምሳሌት ነበር፡
1. በመዝሙሩረኛው በአዎንታዊ መልኩ ነው ጥቅም ላይ የዋለው፣ መዝ. 68፡13፤ 74፡19፤
2. በሆሴዕ በአሉታዊ ነው ጥቅም ላይ የዋለው፣ 7፡11፤
3. በመኃልየ መኃልይ ጥቅም ላይ የዋለው በአዛኝ ዘይቤ ነው፣ 2፡14፤ 5፡2፤ 6፡9።

II. ቅዱስ ቃልነቱ (ካኖናይዜሽን)

ሀ. ይህ መጽሐፍ "የኋለኞቹ ነቢያት" ክፋይ ነው (መጽሐፈ-ጥበብ 49፡10)

ለ. እሱም ከአስራ ሁለቱ የመጀመሪያው ነው፣ የመለስተኛ ነቢያት ስብስብ (ባባ ባትራ 14ለ)
1. እንደ ኢሳይያስ፣ ኤርምያስ እና ሕዝቅኤል፣ እነርሱ በአንድ ጥቅል ተካትተዋል።
2. እነርሱም አስራ ሁለቱን ነገዶች ይወክላሉ ወይም የድርጅት ቁጥርን ተምሳሌት።
3. የመጽሐፉን የታሪክ ቅደም ተከተል ወግ-ልማዳዊ አተያይ ያንጸባርቃሉ።

ሐ. የ "አስራ ሁለቱ" ወይም መለስተኛ ነቢያት ተራ፣ በብዙ ሊቃውንት የሚያያዘው በዜና መዋዕላዊ ቅደም ተከተል ነው። ሆኖም፣ በዚህ አተያይ ላይ ችግሮች አሉ፡
1. ቀዳሚዎቹ ስድስት መጻሕፍት ልዩነት አላቸው፣ በ ኤምቲ/MT እና ኤልኤክስኤክስ/LXX መካከል።

| ኤምቲ/MT | ኤልኤክስኤክስ/LXX |
|---|---|
| ሆሴዕ | ሆሴዕ |
| ኢዩኤል | አሞጽ |
| አሞጽ | ሚክያስ |
| አብድዩ | ኢዩኤል |
| ዮናስ | አብድዩ |
| ሚክያስ | ዮናስ |

2. ውስጣዊ ማስረጃው አሞጽን የሚያስቀምጠው በታሪክ ቅደም ተከተል መሠረት ከሆሴዕ በፊት ነው።
3. የኢዩኤል ጊዜ እጅግ አከራካሪ ነው። እኔ በዝርዝር ላይ ያስቀመጥኩት እንደ ቀደምት ድኅረ-ግዞት ነቢይ አድርጌ ነው፣ ከአብድዩ ጋር በተጓዳኝ።

III. ዘውግ

ሀ. እሱም ከቀሪዎቹ መለስተኛ ነቢያት ይለያል። እሱም ዝርው (ስድ-ንባብ) ነው፣ ከ2፡2-9 በቀር።

ለ. የዮናስ ዘውግ እጅግ አከራክሯል። በርካታ ሊቃውንት የመጻሕፍቱ ተአምራዊነት፣ ትንቢቱ እና ሥነ-መለኮታዊ ገጽታው አይመቻቸውም። አንዳንዶች እሱን የሚያስቀምጡት እንደ፡
1. አሊጎሪ (ምስያዊ)
2. ምሳሌ (ቀልድን በመጠቀም)
3. አጠቃላይ ምድባዊ

ሐ. የዮናስ ስም በዕብራይስጥ ያልተለመደ ነው፣ እንደ አባቱ ሁሉ። ሰውየውና አባቱ በእነዚህ ስሞች II ነገሥ. 14፡25 ላይ ተጠቅሰዋል። እሱም የኖረው በኢዮርብዓም II የአገዛዝ ዘመን ነው (783-743 ቅ.ል.ክ)። ኢየሱስ ዮናስን እንደ ታሪካዊ ሰው ጠቅሶታል፣ ማቴ. 12፡39-40፤ 16፡4 እና ሉቃ. 11፡29።

መ. ዮናስ እንደ ኢዮብ፣ ተጽፎ ሊሆን ይችላል፣ እና/ወይም በጠቢብ ተስፋፍቶ ሊሆን ይችላል፣ ሥነ-መለኮታዊ እውነትን ለማስተማር። አብዛኞቹ ትንቢታዊ መጻሕፍት የነቢዩን መልዕክቶች ያሰፍራሉ፣ ዮናስ ላይ ግን ብቸኛው ትንቢታዊ መልዕክት አምስት ቃላት ናቸው፣ 3፡4 ላይ።

IV. ደራሲነት

ሀ. ደራሲው ነቢዩ ነው። እሱም 1፡1 ላይ ተዋውቋል፣ እንደ ሌሎቹ መለስተኛ ነቢያት።

ለ. ዮናስና አባቱ፣ አማቴ ያልተለመዱ የዕብራይስጥ ስሞች ናቸው፤ ሁለቱም II ነገሥ. 14፡25 ላይ ይከሰታሉ። እሱም የኢዮርብዓም II ነቢይ ነበር፣ ከጋዝ-ሄፈር ናዝሬት አጠገብ።

ሐ. የዕብራይስጥ ጠቢብ የታሪካዊውን ግለሰብ፣ እንደ ኢዮብ ወስዶ፣ አስፋፍቶትም ሊሆን ይችላል፣ ለአሁኑ ሥነ-መለኮታዊ እውነት። ምናልባትም በእስራኤል ንጉሥ ተጠርቶ ሊሆን ይችላል፣ ለእስራኤል ጠላት በመስበኩ ምላሽ እንዲሰጥ። ዮናስ ንጉሣዊ ሰሜናዊ ጸሐፊ/ነቢይ ነው። ይህም በመጽሐፉ ላይ ለምን ባላንጣ (ተቃዋሚ) እንደሆነ ያስረዳል። ጠቢብ ምናልባት ክርክሩን ሰምቶት ሊሆን ይችላል፣ እናም ሁለንተናዊ አንድምታውን አይቶ የዮናስን ልምምድ መዝግቦት/ጽፎት ይሆናል (ጆን ሃሪስ፣ ኢ.ቲ.ቢ.ዩ፣ 1998)።

V. ጊዜው

ሀ. ደራሲው የ11 ነገሥ. 14:25ቱ ዮናስ ከሆነ፣ እንግዲያውስ ቀኑ ከነነዌ መውደቅ በፊት በ612 ቅ.ል.ክ፣ እና በኢዮርብዓም II ያገዛዝ ዘመን (783-743 ቅ.ል.ክ)፣ ድጋፍ ሊያገኝ ግድ ነው።

ለ. ዮናስ ዘወትር ኋላ ላይ እንደ ተጻፈ ነው የሚባለው፣ ነገር ግን ይህ ዘወትር የተመሠረተው፡
1. ንግራዊውን ትንቢት ባለመቀበል
2. በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙትን ከፍጥረት አቅም በላይ የሆኑትን ነገሮች እንደ ታሪካዊነት ወስዶ ባለመቀበል፣
3. እሱ የሚናገረው ስለ ድኅረ-ግዞት ብሔራዊ ኩራትና ስለ አለመከፋፈል ነው የሚል ግምት በመያዝ።

VI. ታሪካዊ መቼት -- በአሦር ታሪክ ላይ ሁለት ጊዜያት አሉ፣ የነነዌ ንስሐ መግባት ሁነቶች/አጋጣሚዎች ሊሆኑ የሚችሉ።
1. በአንድ አምላክ የማመን አዝማሚያ፣ በአዳድ-ኒራሪ III አገዛዝ ዘመን (810-783 ቅ.ል.ክ)
2. ዋነኛው መቅሠፍት በአሦር ላይ፣ በአሱርዳን III አገዛዝ (771-754 ቅ.ል.ክ)

VII. ጽሑፋዊ ምድቦች

ሀ. የምዕራፍ ምድቦች የሁነቶቹን ሂደት ያሳያሉ

ለ. አጭር የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር
1. ምዕራፍ 1 - የእግዚአብሔር ፍቃድ ተተወ፣ በዮናስም ፍቃድ ተተካ። እግዚአብሔር አሸነፈ!
2. ምዕራፍ 2 - ዮናስ ንስሐ ገባ (በሀላፊ ጊዜ የተጻፈ ግጥም፣ እና በኢየሩሳሌም የመቅደስ አምልኮ ገለጻ)
3. ምዕራፍ 3 - የእግዚአብሔር ፍቃድ ተቀባይነት አገኘ። ነነዌ ንስሐ ገባች
4. ምዕራፍ 4 - የእግዚአብሔር ባሕርይ ተገለጠ፣ ከዮናስ አዝማሚያና ድርጊት በተቃራኒው።

VIII. ዋነኛ ሐቆች

ሀ. በዚህ መጽሐፍ አሕዛብ ሃይማኖታዊ ናቸው፣ ነቢዩ ዓመጸኛ ሲሆን
1. ባሕረኞች/መርከበኞች
2. ነነዌዎች

ለ. እግዚአብሔር ለአሕዛብ ያለው ፍቅር በግልጽ ይታያል፣ 3:10 እና 4:11 ላይ። እግዚአብሔር ሰዎችን ብቻ አይደለም የሚወደው፣ እንስሳትንም ደግሞ እንጂ፣ 4:11

ሐ. የተጠሉት፣ ጨካኝ አሦራውያን በያህዌ ተቀባይነት አገኙ፣ ንስሐ በመግባታቸውና በእሱ ላይ ባላቸው እምነት አማካኝነት፣ 3:5-9። አይሁድ እንዲሆኑ አልተጠየቁም።

መ. ዮናስ፣ እግዚአብሔር ለእስራኤል ላደረገው ጥሪ ተምሳሌት ሆኗል፣ ለዓለም የካህናት መንግሥት እንዲሆኑ (ዘፍ. 12:3፤ዘጸ. 19:4-6። እስራኤል ብሔረተኛ፣ የማያካትት እና ኩሩ ሆኗል፣ ወንጌላዊና ተቤዢ/ተዋጂ ከመሆን ይልቅ።

IX. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት እና ሰዎች በአጭሩ የሚገለጹ

ሀ. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት
1. "እግዚአብሔርም ታላቅ ዓሣ አሰናዳ" 1:17 (NIV፣ "...ታላቅ ዓሣን አዘጋጀ")
2. ሲኦል 2:2 (NIV፣ "መቃብር")
3. ጉድጓድ 2:6 (NASB እና NIV)
4. "እግዚአብሔርም ተጸጸተ/ለዘበ"፣ 3:10 (NIV፣ "እሱም አዘነላቸው")
5. "ቸርነትህ የበዛ (*hesed*)፣ 4:2 (NIV፣ "ፍቅርህ የበዛ")
6. "እግዚአብሔርም ቅል/ተክል አዘጋጀ፣ 4:6 ...ትል፣ 4:7፣ ...ነፋስ፣ 4:8 (NIV፣ "አዘጋጀ")
7. "ቀኛቸውንና ግራቸውን የማይለዩ ሰዎች"፣ 4:11 (NASB እና NIV)
8. "እንዲሁም ብዙ እንስሳት"፣ 4:11 (NIV፣ "እና ደግሞም ብዙ እንስሶች")

ለ. ሰዎች
1. አማቴ 1:1
2. "የሰማይ አምላክ" 1:9

X. የካርታ ስፍራዎች/አመላካቾች

1. ነነዌ፣ 1:2
2. ተርሴስ፣ 1:3
3. ኢዮጴ፣ 1:3

XI. የተማሪ ይዘት ጥያቄዎች

1. ዮናስ ታሪካዊ ሰው ነውን?

2. ዮናስ ወደ ነነዌ ለመሄድ ለምን አልፈለገም?


3. ታላቁ ዓሣ የመጽሐፉ ትርጓሜ ዋነኛ ጉዳይ ነውን? ለምን ወይም ለምን አይደለም?


4. የእግዚአብሔርን ባሕርይ ግለጽ። (1፡9፤ 4፡2)

5. ዋነኛው ገጸ ባሕርይ ዮናስ ነው ወይስ እግዚአብሔር? ለምን?

6. ይህ መጽሐፍ ለእስራኤል ምን መልዕክት አለው? ዮናስ እስራኤልን ይወዳልን?

7. ኢየሱስ ይሄንን መጽሐፍ እንዴት ተጠቀመበት? (ማቴ. 12:38-45)


ANCIENT
NEAR EAST
W
N
S
E


PALESTINE
0 10 20 30 40
SCALE IN MILES

# መግቢያ ለትንቢተ ሚክያስ

I. የመጽሐፉ ስም

ሀ. መጽሐፉ የተሰየመው ነቢዩን ተከትሎ ነው።

ለ. ስሙም አጽህሮት ተደርጎ ነው፣ ከሚክይያህ/ሚካ (መሳ.. 17:1፣4፤ 1 ነገሥ. 22:13) ፍችውም "እንደ እግዚአብሔር ያለ ማነው" ማለት ነው።

II. ቅዱስ ቃልነቱ/ካኖናዊነት

ሀ. ይህ መጽሐፍ "የኋለኞቹ ነቢያት" ክፉይ ነው (መጽሐፈ ጥበብ 49፡10)።

ለ. እሱም "የአስራ ሁለቱ" መለስተኛ ነቢያት ስብስብ (ምድብ) የመጀመሪያው ነው (ባባ ባትራ 14ለ)።
1. እንደ ኢሳይያስ፣ ኤርምያስ እና ሕዝቅኤል በአንድ ጥቅል ተካትተዋል።
2. እነርሱም አስራ ሁለቱን ነገዶች ወይም የድርጅትን ተምሳሌታዊ ቁጥር ይወክላሉ።
3. እነርሱም የመጽሐፉን ዜና መዋዕላዊ/የታሪክ ቅደም ተከተል ወግ/ልማዳዊ እይታ ያንጸባርቃሉ።

ሐ. የ "አስራ ሁለቱ" ወይም መለስተኛ ነቢያት ተራ፣ በብዙ ሊቃውንት በዜና መዋዕላዊ ቅደም ተከተል ተያይዟል። ሆኖም፣ በዚህ አተያይ ላይ ችግሮች አሉ፡
1. ቀዳሚዎቹ ስድስት መጻሕፍት ልዩነት አላቸው፣ በ ኤምቲ/MT እና ኤልኤክስኤክስ/LXX መካከል፡

| <u>ኤምቲ/MTኤልኤክስኤክስ/LXX</u> | |
|---|---|
| ሆሴዕ | ሆሴዕ |
| ኢዩኤል | አሞጽ |
| አሞጽ | ሚክያስ |
| አብድዩ | ኢዩኤል |
| ዮናስ | አብድዩ |
| ሚክያስ | ዮናስ |

2. ውስጣዊ ማስረጃው አሞጽን የሚያስቀምጠው በታሪክ ቅደም ተከተል መሠረት ከሆሴዕ በፊት ነው።
3. የኢዩኤል ጊዜ እጅግ አከራካሪ ነው። እኔ በዝርዝር ላይ ያስቀመጥኩት እንደ ቀደምት ድኅረ-ግዞት ነቢይ አድርጌ ነው፣ ከአብድዩ ጋር በተዳኛኝ።

III. ዘውግ

ሀ. እሱ ከሥነ-መለኮት አኳያ እንደ አሞጽ ቢሆንም፣ በስልት ይለያል። ምንም እንኳ ሚክያስ እንደ አሞጽ በተዋበ ቅኔ ባይዋቀርም፣ እሱ ብርቱ የሆነ የእውነት መግለጫ አለው።

ለ. እሱም ባሕርይ ያደረገው ጎን ለጎን በተቀመጡ የፍርድ እና የመታደስ መልዕክቶች ነው፣ ያለ ምንም ልውውጥ። እውነት በሁለት ቀለማት ተመልክቷል፣ ጥቁር/ነጭ!

ሐ. ነቢዩ እጅግ ብርቱ፣ በስሜት የተሞሉ፣ ውስጠታዊ መልዕክቶችን ከኪዳን አምላክ ይሰጣል!

መ. ሚክያስ መጻዒውን የሚተነብይ ነቢይ ነው፡
1. የሰማርያ በአሦር እጅ መውደቅ፣ 1:5-7፤ 6:9-16
2. የኢየሩሳሌም በባቢሎን እጅ መውደቅ፣ 1:9-16፤ 3:12፤ 4:10-12፤ 6:9-16
3. የተጋዘው የአይሁድ ሕዝብ መመለስ፣ 2:12-13፤ 5:5b-9፤ 7:7-20
4. የመሢሑ የትውልድ ስፍራ፣5:2 እና ሁለንተናዊ መንግሥት፣ 5:4
5. እየመጣ ያለው የአሕዛብ መንግሥታት/ሕዝቦች እምነት፣ 4:1-5

IV. ደራሲነት

ሀ. ከወግ/ልማድ አኳያ ሞሬታዊው (ሞሬስ ሄዝ-ጋዝ) ነቢዩ ሚክያስ የሙሉው ትንቢት ደራሲ እንደሆነ ነው የሚወሰደው።

ለ. ዘመናዊዎቹ ሊቃውንት የሚክያስን መጽሐፍ በርከት ባሉ ደራስያን ለመከፋፈል ሞክረዋል፣ በሙሴ ጽሑፎች እንዳደረጉ ሁሉ። ሆኖም፣ ውስጣዊ ማስረጃዎች አሉ፣ መጽሐፉ ኅብር/ወጥነት እንዳለው የሚያሳዩ፡
1. በርከት ያሉ ምዕራፎች "ስሙ" በሚለው የዕብራይስጥ ቃል መጀመራቸው (*shema* ሼማ፣ ዘዳ. 6:4)፣ 1:2፤ 3:1፤ 6:1።
2. "እረኞች"/"በጎች" የሚሉት ዘይቤዎች እስከ መጨረሻው ጥቅም ላይ መዋላቸው 2:12፣ 3:2-3፤ 4:6፤ 5:1፤ 7:14።
3. በመጽሐፉ ሁሉ የሌሎች የስምንተኛ ክፍለ-ዘመን ነቢያት ቃላት መጠቀሳቸው (ዝከ. 4:1-3ከኢሳ. 1:2-4 ጋር)።

ሐ. ሚክያስ፣ በብዙ መንገዱ፣ በስብዕናም ሆነ በመልዕክት ከአሞጽ ጋር ይመሳሰላል። መኖርያ ከተማቸው የሃያ ማይል ርቀት ብቻ ነው ያለው። እነርሱ ሁለቱም ከገጠር የሆኑ ሰዎች ናቸው፣ እንደ ኢሳይያስ በንጉሣዊ ቤተ-መንግሥት በፖለቲካም ሆነ በሥልጣን ትግል ጉዳይ ውስጥ ሳይገቡ።

V. ጊዜው

ሀ. ምዕራፍ 1 ቁጥር 1 የሚክያስን አገልግሎት ጊዜና ርዝማኔ ያስቀምጣል፡ "በኢዮአታም፣ አካዝ እና ሕዝቅያስ ዘመን።"

ለ. ኤርምያስ 26፥18 የሚያስቀምጠው፣ እሱ የተነበየው በሕዝቅያስ ዘመን ነው።

ሐ. 1፥1 ለሰማርያ የተመለከተ ብሎም ለኢየሩሳሌም ሲሆን፣ እናም 6፥1-16 የቤተ-መንግሥት ትዕይንት ሆኖ የእስራኤልን መውደቅ ይተነብያል፣ እሱ የተነበየው ከሰማርያ መውደቅ በፊት መሆን አለበት፣ በ722 ቅ.ል.ክ።

መ. የእርሱ አገልግሎትም ከሰማርያ መውደቅ በኋላም ያልፋል። መጽሐፉ ከእርሱ አገልግሎት ሁሉ መልዕክቶችን ያሰባሰበ ይመስላል።

## VI. ታሪካዊ መቼት

ሀ. ሚክያስ የ8ኛ ክፍለ-ዘመን ነቢይ ነው፣ በደቡባዊው መንግሥት ያገለገለ፣ እንደ አቻው (የአንድ ዘመን) ኢሳይያስ።

ለ. ጊዜውም የብልጽግናና የወታደራዊ መጎልበት/መስፋፋት ነበር። በርካታ ሃይማኖታዊ ድርጊት ነበር፣ ነገር ግን የከነአን የመራባት አምልኮ የያህዌን ስም ይዞ ነበር።

ሐ. እያደገ የመጣው የሶርያ ኢምፓየር፣ በኃያሉ ቲግላዝ-ፒሊሰር III አመራር፣ ለመምታት አቆብቁቦ/እየተጠባበቀ ነበር።

መ. ለተጠናቀቀ ዝርዝር ታሪካዊ ማጠቃለያ ኢሳይያስ ላይ ያለውን ክፍል ተመልከት።

## VII. ጽሑፋዊ ምድቦች

ሀ. ይህ መጽሐፍ ያልተጠበቁ ለውጦችን ባሕርይ አድርጓል፡ 2:5፤12፤ 3:1፤ 6:6-8፤ 7:14-15። ደራሲው ከፍርድ ወደ ደኅንነት ትንበያዎች ይዘዋወራል፣ 2:10-11ን ከ 2:12-13 ጋር አነጻጽር።

ለ. መሠረታዊ የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር

1. በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ የሚመጣው ፍርድ፣ 1:1-16
   ሀ. የሰሜኑ ግዛት፣ 1:5-7
   ለ. የደቡቡ ግዛት፣ 1:9-16 (3:12)
2. የእግዚአብሔር ሕዝብ ቅጣትና መታደስ፣ 2:1-13
   ሀ. የባለጸጎች ማኅበራዊ ኃጢአት፣ 1-11
   ለ. የወደፊቱ ተስፋ፣ 12-13
3. የእግዚአብሔር ሕዝብ አመራር ተወገዘ/ተነቀፈ፣ 3:1-12
   ሀ. የሲቪል መሪዎች፣ 1-4፣ 9፣ 11
   ለ. ነቢያት፣ 5-7፣ (እውነተኛ ነቢይ፣ ቁ. 8)፣ 11
   ሐ. ካህን፣ 11
   መ. ውጤቱ/መዘዙ፣ (4:10)
4. የእግዚአብሔር ሕዝብ የታደሰው/የተመለሰው የወደፊቱ ክብር፣ 4-5
   ሀ. ሁለንተናዊ ግብዣ/ጥሪ፣ ለአሕዛብ ሁሉ፣ 4:1-5
   ለ. ለአንካሳ፣ ለተጣሉት እና ለደካማ ግብዣ/ጥሪ፣ 4:6-8
   ሐ. አማኙ ማኅበረሰብ ጥቃት ደረሰበት፣ ግን ባለ ድል ሆነ፣ 4:9-13
   መ. የመሢሑ መምጣት፣ 5:1-5ሀ
   ሠ. የወደፊቱ በአሦር ላይ የሚሆን ድል፣ 5:5ለ-9
   ረ. የእግዚአብሔር ሕዝብ የወቅቱ ፍርድ፣ 5:1፣ 10-15
5. እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ ፍርድ-ቤት ያመጣል፣ 6
   ሀ. ነቢዩ ስለ እግዚአብሔር ይናገራል፣ 1-5
   ለ. የእግዚአብሔር ሕዝብ ምላሽ ይሰጣል፣ 6-7
   ሐ. ነቢዩ ስለ እግዚአብሔር ምላሽ ይሰጣል፣ 8
   መ. የእግዚአብሔር ፍርድ በሕዝቡ ከተማ ላይ ይወድቃል፡ በኢየሩሳሌም እና/ወይም በሰማርያ፣ 9-16
6. እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ያደረገው ኩነና/ውግዘት እና የበረከት ተስፋ ቀጥሏል፣ 7
   ሀ. የቀጠለው የእግዚአብሔር ሕዝብ ማኅበራዊ ኃጢአት፣ 1-6
   ለ. የወደፊቱ የእግዚአብሔር ሕዝብ መሪ እንደ እግዚአብሔር ይሆናል፣ 14-20

## VIII. ዋነኛ ሐቆች

ሀ. ሚክያስ፣ እንደ አሞጽ፣ የባለጸጎችንና የኃያላንን ማኅበራዊ ኃጢአት ኮንኗል።

ለ. ሚክያስ፣ እንደ ሆሴዕ፣ የነቢያትንና ካህናትን ሃይማኖታዊ ክህደት ኮንኗል (3፥11)

ሐ. ሚክያስ የሁለቱንም፣ የእስራኤልንና ይሁዳን ውድቀትና ግዞት ተንብዮአል፣ በአመንዝራነታቸውና ለኪዳን ታማኝ ባለመሆናቸው ምክንያት።

መ. እግዚአብሔር ጻድቅ (ትክክል) ነው። ሕዝቡ መቀጣት አለባቸው። እግዚአብሔር ደግሞ ቸርና ታማኝ ነው፣ ለኪዳኑ፣ ሕዝቡ (ቅሬታዎቹ) ይዋጃሉ ይታደሳሉም።

ሠ. እግዚአብሔር፣ ሕዝቡ የእርሱን ባሕርይ እንዲያንጸባርቅ ይፈልጋል፣ 6፡8 እምነት የሌለበት የአምልኮ ሥርዓት ሳይሆን (6፡6-7)።

ረ. እስራኤል፣ ይሁዳ እና አማኝ አሕዛብ በመሢሑ መምጣት ይባረካሉ፣ በቤተ ልሔም በሚወለደው (5፡2)። ይህ አዲስ መሪ እንደ ያህዌ ይሆናል (7፡18-20)።

IX. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት እና ሰዎች በአጭሩ የሚገለጹ

ሀ. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት

1. "ተራሮችም ይቀልጣሉ" 1፡4 (NASB እና NIV)
2. "ቁስሏ የማይፈወስ ነውና" 1፡9 (NASB እና NIV)
3. ማሾፍ 2፡4 (NASB እና NIV)
4. "የሕዝቤን ሥጋ በልታችኋል" 3፡3 (NASB እና NIV)
5. ሟርት/መናፍስት ጠሪነት 3፡6(NASB እና NIV)
6. "ጽዮን እንደ እርሻ ትታረሳለች" 3፡12(NASB እና NIV)
7. "አሕዛብ… ሕዝቦች ይመጣሉ…" 4፡1-2 (NASB እና NIV)
8. "ሰይፋቸውን ማረሻ ለማድረግ ይቀጠቅጣሉ" 4፡3 (NASB እና NIV)
9. "አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ" 5፡2 (NIV፣ "አወጣጡ ከቀድሞ የሆነ፣ ከጥንት ጊዜያት")
10. "…የሆዴን ፍሬ ስለ ነፍሴ ኃጢአት እሰጣለሁን?" 6፡7 (NASB እና NIV)
11. አባይ ሚዛን 6፡11 (NIV፣ "የተንኮል መመዘኛ")
12. "ኃጢአታቸውንም ሁሉ በባሕሩ ጥልቅ ይጥለዋል" 7፡19 (NIV፣ በደላችንን ሁሉ ወደ ባሕሩ ጥልቅ ይጥለዋል")

ለ. ሰዎች


1. ናምሩድ፣ 5፡6
2. ባላቅ፣ 6፡5
3. በለዓም፣ 6፡5
4. ዘንበሪ፣ 6፡16

X. የካርታ ስፍራዎች/አመላካቾች


1. ሰማርያ፣ 1፡5
2. ኢየሩሳሌም፣ 1፡5
3. ለኪሶ፣ 1፡13
4. ሞሬሼት-ጌት፣ 1፡14
5. ጽዮን ተራራ፣ 4፡7
6. ቤተ ልሔም ኤፍራታ፣ 5፡2
7. የናምሩድ አገር፣ 5፡6
8. ሰጢም፣ 6፡5
9. ጌልገላ፣ 6፡5
10. ባሳን
11. ገለዓድ

XI. የተማሪ ይዘት ጥያቄዎች

1. የ1፡8-16 ላይ ያሉትን የኀዘን ሥርዓት ዘርዝር።
2. ሁሉም ሦስቱ ትንቢታዊ መልኮች (የተስፋ ንግር፣ የፍርድ-ቤት ትዕይንት፣ እና ወዮታ/ሙሾ) ሚክያስ ላይ ይገኛሉ። ምሳሌዎች ስጥ።
3. ሚክያስ እንዴት አድርጎ አሞጽን ይመስላል?
4. ሚክያስ፣ ኤርምያስ 26፡18 ላይ ለምን ተጠቀሰ?
5. 5፡10-15 ለማን ነው የተመለከተው?
6. እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚያደርጋቸውን ነገሮች ዘርዝር፣ 7፡18-20 ላይ።


ANCIENT
NEAR EAST
N
S
E
W

# PALESTINE



# መግቢያ ለትንቢተ ናሆም

I. የመጽሐፉ ስም

ሀ. የተሰየመው ነቢዩን ተከትሎ ነው።

ለ. የስሙ ፍች "መጽናናት" ወይም "ኀዘኔታ" ነው (ኢሳ. 57፡18)።

II. ቅዱስ ቃልነቱ/ካኖናይዜሽን

ሀ. ይህ መጽሐፍ የመለስተኛ ነቢያት ክፋይ ነው፣ ከጽሑፋቸው ልኬት የተነሣ።

ለ. እነርሱም "አስራ ሁለቱ" በመባል ይጠራሉ። እነርሱ ምናልባት አንድ ላይ የሆኑት በአንድ ጥቅል መካተት ስለሚችሉ ይሆናል።

ሐ. እነርሱም "ነቢያት" ተብሎ የሚጠራው የዕብራይስጥ ካኖን ሁለተኛ ምድብ ናቸው።

መ. አይሁድ በካኖናቸው ውስጥ የሚገቡትን/የሚካተቱትን መጻሕፍት ቁጥር በፊደል ገበታቸው ካሉት ተናባቢዎች ቁጥር ጋር እንዲገጥሙ ይፈልጉ ነበር፣ ስለዚህ በርከት ያሉ መጻሕፍትን ደባልቀዋል።

III. ዘውግ

ሀ. እሱ ጥንታዊ የዕብራይስጥ ትንቢታዊ (ቅኔ) ነው። እሱ ብኪ ላይ ከሚገኙት እጅግ ብርቱ ከሆኑት ግጥሞች አንደኛው ነው።

ለ. ናሆም የተለየና ጥበባዊ ነው፣ በቃላት ምርጫውና በፈሊጦቹ። እሱና ኢሳይያስ ከነቢያት መካከል እጅግ ታላቅ ገጣሚዎች ተደርገው ተወስደዋል። ጽሑፋዊ ግንኙነት በሁለቱ መካከል አለ።

1. ናሆም 1፡4 እና ኢሳይያስ 33፡19።
2. ናሆም 1፡15 እና ኢሳይያስ 52፡7።

ሐ. ናሆም 1፡2-8 ዕንቆቅልሻዊ መዝሙር ነው። የመክፈቻ መዝሙር በመለስተኛ ነቢያት ዘንድ ያልተለመደ ነው።

IV. ደራሲነት

ሀ. ስለ ነቢዩ የሚታወቀው ጥቂት ነው። ብኪ ላይ ስሙ የሚከሰተው እዚህጋ ብቻ ነው።

ለ. እሱም ኤልቆሻዊው በሚል ተጠርቷል፣ ምናልባትም የቦታ ስም ሊሆን ይችላል። በርከት ያሉ ንድፈ-ሐሳቦች አሉ፡

1. ጀሮም እና ኢዩሲቢስ እሱን የሚያስቀምጡት በገሊላ ነው፣ የኤልኮሽ ከተማ።
2. ሌሎች የሚያስረግጡት ቅፍርናሆም ነው፣ "የናሆም አገር/ከተማ፣" ስፍራው ነው፣ ነገር ግን ደጋፊ ማስረጃ የለውም።
3. ሱዶ-ኢፒፋነስ እሱን የሚያስቀምጠው በደቡብ ይሁዳ ነው፣ *The Lives of the Prophets,* XVII፣ የኤልኮሽ/ኤልቆሽ ከተማ፣ ከሚኪያስ ቤት አጠገብ።
4. የዓረብ ወግ/ልማድ፣ የ16ኛ ክፍለ-ዘመን ዓ.ም፣ እሱን የሚያስቀምጠው ኢራቅ ውስጥ ነው (የተጋዙ ወላጆች ልጅ)። የኤልቆሽ ከተማ 24 ማይል ከነነዌ በስተሰሜን ነው።

V. ጊዜው

ሀ. እሱ የተጻፈው ከነነዌ ውድቀት በፊት መሆን አለበት፣ 612 ቅ.ል.ክ።

ለ. እሱ የተጻፈው ከቴብስ ውድቀት በኋላ ነው (ኖ-አሞን) በአሹርባኒፓል፣ በ663 ቅ.ል.ክ (ዝከ. 3፡8) ምክንያቱም በተጠለፈ ውኃ መከላከያ እንደ ተበጀላት ከተማ ምሳሌ ተደርጋ ስለተወሰደች።

ሐ. እሱ ሊጻፍ የሚችለው ከአሹርባኒፓል ሞት በኋላ ወዲያውኑ ነው፣ በ627 ቅ.ል.ክ። እሱ የመጨረሻው የአሦር ጠንካራ ንጉሥ ነበር፣ እናም በ626 ቅ.ል.ክ፣ አዲሲቷ ባቢሎን ነጻነቷን አገኘች፣ በናቦፖላሳር።

VI. አጭር ማጠቃለያ የአሦር እና የፍልስጥኤም ታሪክ

ሀ. ናሆም የአሦርን ውድቀት አመልክቷል፣ ዋና ከተማው ነነዌ የሆነ። እግዚአብሔር ይሄንን ጨካኝ መንግሥት እንደ መሣርያ ተጠቅሟል፣ በእስራኤል ላይ ለሰጠው ፍርድ (ኢሳ. 10፡5)።

ለ. የመጀመሪያው የመመዝገብ (መጻፍ) አጋጣሚ የተከሰተው በኢዩ አገዛዝ ነው (842-815 ቅ.ል.ክ)። በ841 ቅ.ል.ክ የአሦራውያን ንጉሥ፣ ሻልማንሰር III (858-824 ቅ.ል.ክ)፣ ለግብር ክፍያ አስገደደ።

ሐ. ይህም በአዳድ-ኒራሪ III ቀጠለ (810-782 ቅ.ል.ክ)። ደማስቆ ተማረከች፣ ኢዮአስም ግብር ይከፍል ዘንድ ተገደደ።

መ. የመጀመሪያው ዋነኛ ወረራና ማፈናቀል (ካገር ማስወጣት) የተከሰተው በሜናሂም አገዛዝ ነው (752-732 ቅ.ል.ክ) በቲግላዝ-ፒሌሰር III (745-727 ቅ.ል.ክ) በ732 ቅ.ል.ክ። ባጠቃላይ እሱ ፒካህን ተካ (740-732 ቅ.ል.ክ)፣ ከሆሺአ ጋር (732-722 ቅ.ል.ክ) (II ነገሥ. 15:29)፤ I ዜና. 5:6፤ II ዜና. 30:6፤10፤ኢሳ. 9:1። ይህም የፍልስጥኤም አገዛዝ በይሁዳ ላይ ተጽዕኖውን አሳደረ፣ ምክንያቱም አካዝ (735-715 ቅ.ል.ክ) ደግሞ ግብር በመክፈሉ።

ሠ. ሆሺአ እስራኤልን ከግብፅ ጋር ለማስተባበር ሞክሮ ነበር፣ እናም በሻልማኔሰር V ተወረረ (727-722 ቅ.ል.ክ)። ዋና ከተማዋ ሰማርያ፣ በሳርጎን II እጅ ወደቀች ከ3 ዓመት ከበባ በኋላ (721-705 ቅ.ል.ክ)። እስራኤል ወደ ሜዶን ተጋዘ (II ነገሥ. 17:3-20፤ 18:20-21፤ኢሳ. 7:8፤ 8:4፤ 10:11፤ 36:20፤ሆሴ. 9:3፤ 10:6፤14፤ 11:5)። ሳርጎን II ይሁዳን ወርሮ የግዳጅ ግብር ጣለባቸው፣ በ720 ቅ.ል.ክ እና 712 ቅ.ል.ክ።

ረ. በይሁዳ ሕዝቅያስ (728-687 ቅ.ል.ክ) አካዝን ተካ። እሱም በመነሻው ላይ ለሳርጎን II ግብር ይከፍል ነበር። ኋላ ላይ ለአሦር ግብር መክፈል እምቢ አለ (II ነገሥ. 18)።ይሁዳ በሰናክሬ ተወረረ (704-681 ቅ.ል.ክ) በ701 ቅ.ል.ክ፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር መልአክ በተደረገ መቅሠፍት እንዲወጣ ተገደደ፣ እሱም 185,000 የአሦር ወታደሮችን የገደለ (ኢሳ. 10:16፤ 36:1-37:38፤ II ነገሥ. 18:13-19:37፤II ዜና. 32:1-31)።

ሰ. ኋላ ላይ፣ ምናሴ ለኢሳራዶን ለመገዛት ተገደደ (681-669 ቅ.ል.ክ) (II ዜና. 33:1-11)።

ሸ. የኢሳራዶን ልጅ፣ አሹርባኒፓል (638-633 ቅ.ል.ክ)፣ የመጨረሻው የአሦር ብርቱ ንጉሥ ነበር። ከእሱ ሞት በኋላ፣ በፈጣን ውድቀት ዘመን፡

1. ናቦፖላሳር (625-605 ቅ.ል.ክ) ነጻ የሆነች አዲሲቷን ባቢሎን አዘጋጀ።
2. ሳሜቲሁስ I (664-609 ቅ.ል.ክ) ለግብፅ ነጻነትን አቀዳጀ/መለሰ።
3. ኢዮስያስ (640-609 ቅ.ል.ክ) ለይሁዳ ነጻነትን አቀዳጀ/መለሰ።
4. ሳያክሰስ (625-585 ቅ.ል.ክ) ነጻ የሆነች ሜዶንን አዘጋጀ።

ቀ. ነነዌ፣ የአሦር ዋና ከተማ በ612 ቅ.ል.ክ በናቦፖላሳር እና ሳያክሰስ እጅ ወደቀች። አሸር፣ የድሮ ዋና ከተማ ቀደም ብላ በ614 ቅ.ል.ክ ወድቃለች።

በ. ነነዌ 1,850 ካሬ ሽፍናለች፣ እንዲሁም 8 ማይል የተጠናከረ ቅጥር (ግንብ) አላት።

## VII. ጽሑፋዊ ምድቦች

ሀ. መክፈቻ፣ 1:1

ለ. የያህዌን ተበቃይነት እና ቸርነት የሚያሳይ ግጥም፣ 1:2-8 (ከፊል ዕንቆቅልሻዊ/የቃላት ቅንብር)

ሐ. የእግዚአብሔር ባሕርይ እውንነት፣ ፍርድ በነነዌ ላይ፣ መዳን ለይሁዳ፣ 1:9-2:2።

መ. የታላቋን ከተማ የነነዌን ከበባና ውድቀት የሚያሳይ ምስላዊ የቅኔ ጽሑፍ፣ 2:3-3:19።

## VIII. ዋነኛ ሐቆች

ሀ. የመጽሐፉ ትኩረት የነነዌ ጥፋት ነው፣ የጨካኙ የአሦር ኢምፓየር ዋና ከተማ። እሱም ዋና ከተማ የሆነው በሰናክሬ ነው፣ በ700 ቅ.ል.ክ አካባቢ። እሱም የተመለከተው ከጤግሮስ ወንዝ በስተምስራቅ ዳርቻ ነው፣ እናም ደኅና ተደርጎ ተመሽጓል።

ለ. ከተማው ሙሉ ለሙሉ በባቢሎናውያንና ሜዶናውያን በ612 ቅ.ል.ክ ተደምስሷል፣ አሸር በ614 ቅ.ል.ክ እንዳደረገው። እነርሱም ወንዙን ተጠቅመዋል፣ በግንቡ ዙሪያ የሚፈስሰውን። እነርሱም የወንዙን ውኃ አቅጣጫ ወደ ማከማቻዎች አዞሩትና በአንድ ጊዜ ለቀቁት። የውኃው ኃይል የግንቡን ትልቅ ክፍል አፈረሰው፣ 2:6።

ሐ. እግዚአብሔር ጨካኞቹን አሦራውያንን በሕዝቡ ላይ ለመፍረድ ተጠቀመባቸው (ኢሳ. 10:5) ግን አሁን ደግሞ አሦራውያን ተፈረደባቸው። የዘራነውን እናጭዳለን፣ ገላ. 6:7።

## IX. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት እና ሰዎች በአጭሩ የሚገለጹ

ሀ. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት

1. ንግር፣ 1:1 (NASB እና NIV)
2. ራዕይ፣ 1:1 (NASB እና NIV)
3. "እግዚአብሔር ለቁጣ የዘገየ ነው፣" 1:3 (NASB እና NIV)
4. "መሸሸጊያ፣" 1:7 (NIV፣ "መጠጊያ")
5. መከታ፣ 2:5 (NIV፣ "መከላከያ ጋሻ")
6. "የወንዞቹም መዝጊያዎች ተከፈቱ፣ የንጉሡ ቤትም ቀለጠች፣" 2:6 (NIV፣ "የወንዞቹ መዝጊያዎች ተበርግደው ተከፈቱ፣ ቤተ-መንግሥቱም ወደቀ")
7. "ልብስሽን በፊትሽ እገልጣለሁ፣" 3:5 (NASB እና NIV)
8. "ሕፃናቶችዋ በመንገድ ሁሉ ራስ ላይ ተፈጠፈጡ፣" 3:10 (NASB እና NIV)

ለ. ሰዎች

1. ምናምንቴ፣ 1፡15 (NIV፣ “ኃጢአተኛ”)
2. የሠራዊት ጌታ፣ 2፡13 (NIV፣ “ኃያል አምላክ”)

## X. የካርታ ስፍራዎች/አመላካቾች

1. ባሳን፣ 1፡4
2. ቀርሜሎስ፣ 1፡4
3. ሊባኖስ፣ 1፡4
4. ኖእ-አሞን (ቴብስ)፣ 3፡8
5. ነነዌ፣ 1፡1

## XI. የተማሪ ይዘት ጥያቄዎች

1. የዚህ መጽሐፍ ማዕከላዊ ዓላማ ምንድነው?

2. አንዱ ከ1፡3 እና 7 እንዴት ሊዛመድ ይችላል?


3. አንዱ ዮናስን እና ናሆምን እንዴት ሊያዛምድ ይችላል?


4. ናሆም እንደ ታላቅ ባለ-ቅኔ የተቆጠረው ለምንድነው?

5. 2፡6 ከነነዌ ታሪካዊ አወዳደቅ ጋር የሚዛመደው እንዴት ነው?

6. 3፡8-10 ላይ የግብፅ ከተማ የተጠቀሰችው ለምንድነው?

7. የ3፡14-15ን ስላቃዊ አገላለጽ ዘርዝር።


ANCIENT
NEAR EAST
N
S
E
W


PALESTINE
0 10 20 30 40
SCALE IN MILES

# መግቢያ ለትንቢተ ዕንባቆም

I. የመጽሐፉ ስም

ሀ. የተሰየመው ነቢዩን ተከትሎ ነው።

ለ. ዕንባቆም የሚለው ስም ፍችው "መዳበስ" ወይም "ማቀፍ" ማለት ነው።

ሐ. በሴፕቱዋጂንት እሱ የሚጠራው "ሃምባኮም" በሚል ነው፣ ይኸውም የሶርያ ቃል፣ ፍችው "አትክልት" የሆነ።

II. ቅዱስ ቃልነቱ (ካኖናዊነት)

ሀ. ይህ መጽሐፍ "የኋለኞቹ ነቢያት" ክፋይ ነው (መጽሐፈ ጥበብ 49፡10)።

ለ. እሱም ከ"አስራ ሁለቱ" መለስተኛ ነቢያት ስብስብ (ምድብ) አንዱ ነው (ባባ ባትራ 14ለ)።
1. እንደ ኢሳ.፣ ኤር. እና ሕዝቅኤል በአንድ ጥቅል ተካትተዋል።
2. እነርሱም አስራ ሁለቱን ነገዶች ወይም የድርጅትን ተምሳሌታዊ ቁጥር ይወክላሉ።
3. እነርሱም የመጻሕፍቱን ዜና መዋዕላዊ/የታሪክ ቅደም ተከተል ወግ/ልማዳዊ እይታ ያንጸባርቃሉ።

ሐ. የ "አስራ ሁለቱ" ወይም መለስተኛ ነቢያት ተራ፣ በብዙ ሊቃውንት በዜና መዋዕላዊ ቅደም ተከተል ተያይዟል። ግልጽ የሆነው ነገር ናሆም፣ ዕንባቆም እና ሶፎንያስ አንድ ምድብ መሆናቸው ነው።

III. ዘውግ - ነቢይ ሕዝቡን ወክሎ ለእግዚአብሔር ይናገር ዘንድ እጅግ ያልተለመደ ነው። የመጀመሪያው አንቀጽ ከባድ ቃል (ትችት) ወይም እውነትን በታሳቢ ምልልስ የማስተላለፊያ መንገድ ነው።

IV. ደራሲ

ሀ. ይህ ነቢይ ከያህዌ ጋር ይነጋገራል፣ ይሁዳን በተመለከተ። ሌሎቹ ነቢያት ሁሉ ለሕዝቡ ይናገራሉ፣ ስለ እግዚአብሔር ሆነው።

ለ. ይህ ነቢይ ከተመሳሳይ አጠቃላይ ጊዜ ጋር ይገጥማል፣ እንደ ዳንኤል፣ ኤርምያስ፣ ሕዝቅኤል፣ ናሆም፣ እና ሶፎንያስ። እነዚህን ሰዎች የሰባተኛው ክፍለ-ዘመን ነቢያት ብለን እንጠራቸዋለን።

ሐ. እሱ ባለ ዜማ (ዘማሪ) ሊሆን ይችላል፣ ከቤተ መቅደስ ኅብረ-ዘማርያን ጋር በተያያዘ፣ ምክንያቱም፡
1. 3፡1 ላይ *Shigionoth* የሚል ቃል ስላለ። NASB የግርጌ ማስታወሻ እሱን የሚጠራው "ብርቱ ስሜታዊ የቅኔ ዓይነት" በሚል ነው። ይህ የዜማ ቃል ሲሆን ፍችው አይታወቅም፣ ምናልባትም ዕረፍት (ጥቂት የዜማ ዝምታ) ወይም ቀስ እያለ የሚጨምር የዜማ ድምጽ ሊሆን ይችላል።
2. ሌላው ታሳቢ የዜና ቃል ጥቅም ላይ መዋሉ፣ *Selah* 3፡3፣ 9፣ 13 ላይ።
3. 3፡19 ላይ ያለው ሐረግ አጠቃቀም፣ "ለመዘምራን አለቃ፣ በበገናዎች/በክር መሣርያዎች።"

V. ጊዜው (ሁለት ዋነኛ ንድፈ-ሐሳቦች አሉ)

ሀ. የምናሴ አገዛዝ (687 - 642 ቅ.ል.ክ)። ይህ ዘወትር የሚያያዘው ዕንባቆም በቅዱስ ቃሉ ባለው ስፍራ እና ከከለዳውያን መነሣት፣ አዲሱ ባቢሎን ኢምፓየር ጋር ነው (ዕምባቆም 1፡5)።

ለ. የኢዮአቄም አገዛዝ (609-598 ቅ.ል.ክ)። ይህ እሱን የሚያስቀምጠው በፈርዖን ኒካው II ጊዜ ነው፣ ከተማይቱን እንዳጠፋት፣ እና ኋላ ላይም ናቡከደነፆር አጠቃላይ ስፍራውን ሁሉ መውሰዱን፣ ቀሪዎቹ የአሦር ሠራዊትና ግብፃውያን ከርከሚሽ ላይ ከተሸነፉ በኋላ፣ በ605 ቅ.ል.ክ።

ሐ. ሱዶ-ኢፒፋኒስ፣ *Lives of the Prophets (የነቢያት ሕይወት)* ላይ የሚለው እሱ ከስምዖን ነገድ መሆኑን ነው። እሱም የናቡከደነፆርII ወረራን (ግስጋሴ) ሸሽቷል፣ በ586 ቅ.ል.ክ፣ እናም ከከተማይቱ ውድቀት በኋላ ተመልሷል፣ እንዲሁም ከግዞት መልስ ከሁለት ዓመት በፊት (ቀደም ብሎ) ሞቷል። ሆኖም፣ ይህ ምንጭ የዘገየና ርግጠኛ ያልሆነ ነው።

VI. ታሪካዊ መቼት

VII. ጽሑፋዊ ምድቦች

ሀ. መጽሐፉ በሁለት ዋና ዋና ምድቦች ይከፈላል፡
1. ምዕራፍ 1 እና 2 -በነቢዩ እና በእግዚአብሔር መካከል የተደረገ ምልልስ
2. ምዕራፍ 3 - የምስጋና ግጥም፣ እግዚአብሔር ታሪክን ስለመቆጣጠሩ።

ለ. በእግዚአብሔርና በእሱ ነቢይ መካከል የተደረገ ምልልስ፣ 1፡2-2፡20
1. የዕንባቆም አቤቱታ፣ እግዚአብሔር ለቅጣት በመዘግየቱ፣ 1፡2-4
2. የእግዚአብሔር የመጀመሪያ መልስ፣ 1፡5-11
3. የዕንባቆም የሞራል ችግር፣ በእግዚአብሔር ምላሽ፣ 1፡12-2፡1

4. የእግዚአብሔር ሁለተኛ ምላሽ፣ 2፡2-5
ሀ. የእግዚአብሔር ዕቅድ ርግጠኛ ነው፣ ጻፈው፣ 2፡20
1) በእምነት መባረክ፣ 2፡4፣ 14፣ 20
2) በክፉ ላይ ፍርድ፣ 2፡5፣ 6-20
ለ. የእግዚአብሔር ሕዝብ በኪዳን ታማኝነት ላይ ኃላፊነቱን ይወስዳል፣ 2፡4-5 (3፡16-19)
ሐ. እግዚአብሔር የጣዖት ወረራንና አምላክ የለሽነትን ይቀጣል፣ 2፡6-20 (5 ወዮታ)
1) 2፡6-8፣ነውጣዊ ወረራ
2) 2፡9-11፣ነውጣዊ ወረራ
3) 2፡12-14፣ነውጣዊ ወረራ
4) 2፡15-17፣ነውጣዊ ወረራ
5) 2፡18-20፣ጣዖት አምላኪነት

ሐ. ለእግዚአብሔር ያለፈው ጊዜ የማዳን ድርጊት ታማኝነቱ የቀረበ የባርኮት መዝሙር፣ ለወደፊቱም ማዳኑ ተስፋ በማድረግ፣ 3፡1-19
1. የእግዚአብሔር ያለፈው ጊዜ የማዳን ድርጊት በብርቱ ቅኔ መልክ ተገልጿል፣ ዘይቤአዊ መልክን በመጠቀም (3፡1-15)፡
ሀ. ዘጸአት
ለ. ፍጥረት
ሐ. ድል ማድረግ
2. የነቢዩ እምነትና ትዕግሥት፣ በእግዚአብሔር ማዳን ላይ፣ ምንም እንኳ የሚታይ ምልክት ባይኖርም፣ (2፡4፤ 3፡16-19)

## VIII. ዋነኛ ሐቆች

ሀ. ይህ የሞራል ዓለም (ዩኒቨርስ) ነው። ኃጢአት ይፈረድበታል። የእግዚአብሔር የተመረጡ ሰዎች እንኳ ቢሆኑለድርጊታቸው ኃላፊነቱን ይወስዳሉ (ገላ. 6፡7)።

ለ. በዚህ በወደቀው ዓለም እንኳ ቢሆን እግዚአብሔር አሁንም ሁነቶችን ይቆጣጠራል። እሱ ለዓላማው ክፉውን ይጠቀማል፣ ነገር ግን እሱ ደግሞ ይፈረድበታል!

ሐ. እግዚአብሔርን መጠየቅ ተቀባይነት አለው (ይቻላል)። ሆኖም፣ የእግዚአብሔር መገኘት ነው የሚያረካው፣ ምክንያታዊ ምላሽ ሳይሆን።

መ. ይህ መጽሐፍ የጳውሎስ የታወቀው ሥነ-መለኮታዊ ጭብጥ ምንጭ ነው፣ "ጽድቅ በእምነት" የሚለው፣ (ዝከ. 2፡4)።ክፉው በመጨረሻ ራሱን ያጠፋል። የእግዚአብሔር ሕዝብ እምነትን መለማመድ ይኖርበታል፣ በክፉ ቀናት መካከል! እምነት ከወቅቱ ሁኔታ ጋር መያያዝ አይኖርበትም፣ 3፡17-19።

## IX. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት እና ሰዎች በአጭሩ የሚገለጹ

ሀ. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት
1. "ፍርዳቸውና ክብራቸው ከራሳቸው ይወጣል፣" 1፡7 (ዝከ. 1፡11ሐ) (NIV፣ "እነርሱ ለራሳቸው ሕግ ናቸው፣ የገዛ ራሳቸውንም ክብር ያስታውቃሉ")
2. "አቤቱ፣ የተቀደስህ አምላኬ ሆይ፣" 1፡12 (NASB እና NIV)
3. "ዓለቴ ሆይ፣" 1፡12 (NASB እና NIV)
4. "ለመረባቸው ይሠዋሉ፣" ቁ. 15-17 (NIV፣ "ለመረቡ ይሠዋል")
5. "ጻድቅ ግን በእምነት በሕይወት ይኖራል፣" 2፡4 (NASB እና NIV)
6. ሲኦል፣ 2፡5 (NIV፣ "መቃብር")
7. የፌዝ-ዘፈን፣ 2፡6 (NIV፣ "ፌዝ")
8. "ጽዋው በእግዚአብሔር ቀኝ ነው፣" 2፡16 (NASB እና NIV)
9. የጸሎት መዝሙር፣ 3፡1 (NASB እና NIV)
10. ሴላህ፣ 3፡3፣9፣13 (NASB እና NIV)
11. የቀባኸው፣ 3፡13 (NIV፣ "የቀባኸው")
12. "እግሮቼን እንደ ዋላ እግሮች ያደርጋል፣" 3፡19 (NIV፣ "እግሮቼን እንደ አጋዘን እግሮች ያደርጋል")


ለ. ሰዎች - የሉም

## X. የካርታ ስፍራዎች/አመላካቾች


1. ከለዳውያን፣ 1፡6 (NIV፣ "ባቢሎናውያን")
2. ቴማን፣ 3፡3
3. ፋራን ተራራ፣ 3፡3
4. ምድያም፣ 3፡7

## XI. የተማሪ ይዘት ጥያቄዎች

1. መጽሐፉ ከሌሎች መለስተኛ ነቢያት እጅግ የተለየው እንዴት ነው?
2. ምዕራፍ1-2 ላይ ያለውን በእግዚአብሔርና በነቢዩ መካከል የተካሄደውን ምልልስ የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር አውጣ።
3. ዕንባቆም ባለ ዜማ (ዘማሪ) ነበር የሚለው ሐሳብ ከምን የተነሣ ነው?
4. የ1፡16-17ን ምናባዊ ሁኔታ አብራራ።
5. 2፡4 ከዐውደ-ጽሑፉ አኳያ ምን ማለት ነው? ጳውሎስም ሮሜ 1፡17 እና ገላ. 3፡11 ላይ እንዴት ነው የተጠቀመበት?


ANCIENT
NEAR EAST
N
S
E
W

# PALESTINE



# መግቢያ ለትንቢተ ሶፎንያስ

I. የመጽሐፉ ስም

ሀ. የተሰየመው ነቢዩን ተከትሎ ነው።

ለ. የስሙ ፍችም፡
1. "ያህዌ ተሸሽጓል" ወይም
2. "ያህዌ ይጠብቃል"

II. ቅዱስ ቃልነቱ (ካኖናይዜሽን)
ሀ.ይህ መጽሐፍ "የኋለኞቹ ነቢያት" ክፍል ነው (መጽሐፈ ጥበብ 49፡10)።

ለ. እሱም ከ"አስራ ሁለቱ" መለስተኛ ነቢያት ስብስብ (ምድብ) ክፍል ነው (ባባ ባትራ 14ለ)።
1. እንደ ኢሳ.፣ ኤር. እና ሕዝቅኤል በአንድ ጥቅል ተካትተዋል።
2. እነርሱም አስራ ሁለቱን ነገዶች ወይም የድርጅትን ተምሳሌታዊ ቁጥር ይወክላሉ።
3. እነርሱም የመጻሕፍቱን ዜና መዋዕላዊ/የታሪክ ቅደም ተከተል ወግ/ልማዳዊ እይታ ያንጸባርቃሉ።

ሐ. የ "አስራ ሁለቱ" ወይም መለስተኛ ነቢያት ተራ፣ በብዙ ሊቃውንት በዜና መዋዕላዊ ቅደም ተከተል ተያይዟል። ግልጽ የሆነው ነገር ናሆም፣ ዕንባቆም እና ሶፎንያስ አንድ ምድብ መሆናቸው ነው።

III. ዘውግ

ሀ. ይህ የጥንታዊ ዕብራይስጥ ትንቢት (ቅኔ) ነው፣ በኃጢአት፣ ፍርድ እና መታደስ ጭብጦች ላይ የሚያተኩር።

ለ. 3፡14-20 የጥንት ዝማሬ ሊሆን ይችላል።

IV. ደራሲነት

ሀ. መጽሐፉ ያልተለመደ ረጅም የዘር ሐረግ አለው፡ "…ወደ ኩሲ ልጅ፣ ወደ ጎዶልያስ ልጅ፣ ወደ አማርያ ልጅ፣ ወደ ሕዝቅያስ ልጅ፣" 1፡1።
1. ይህም የሚያመለክተው የይሁዳ ንጉሣዊ ዘር መሆኑን ነው። የተመዘገበው ሕዝቅያስ የይሁዳ ንጉሥ ከሆነ (715-687 ቅ.ል.ክ)፣ እንግዲያውስ የረጅም የዘር ሐረጉ ዓላማ ይሄ ይመስላል።
2. ርዝማኔው አይሁዳዊነቱን ለማረጋገጥ ይመስላል፣ ምክንያቱም የአባቱ ስም ኩሲ (*Cushi* ኢትዮጵያዊ) ስለሆነ።

ለ. ብዙዎች የሚያምኑት እሱ የኢዮስያስ የአክስት/አጎት ልጅ እንደሆነ ነው፣ እናም እንደ መልካሙ ንጉሥ በተመሳሳይ መምህራን ሠልጥኖ ሊሆን ይችላል።

ሐ. ብኪ ላይ ሦስት ሌሎች ተመሳሳይ ስም ያላቸው አሉ፡ I ዜና. 6፡36-38፤ኤር. 21፡1፤ II ነገሥ. 25፡18-21፤ 29፡25፤37፡3፤ 52፡24-27፤ዘካ. 6፡10፤14።

V. ጊዜው

ሀ. ሶፎንያስ የተናገረው በንጉሥ ኢዮስያስ የሕይወት ዘመን ነው (640-609 ቅ.ል.ክ)።

ለ. በይሁዳ ከነበረው ውስጣዊ ውጥረት (ቅራኔ) የተነሣ፣ መጽሐፉ ላይ 1፡4-6፣ 8-9፣ 12፤ 3፡1-3፣ የተጠቀሰው፣ መልእክት ተቀባዮቹ ይሁዳውያን ይመስላሉ፣ የኢዮስያስ ተሐድሶ ከመቋቋሙ (ከመደራጀቱ) በፊት (621 ቅ.ል.ክ)።

VI. ታሪካዊ መቼት

ሀ. አንዳንዶች የእግዚአብሔር የወረራ መሣርያ አድርገው የሲዚያንን ዘላን ማኅበረሰቦችን ይመለከታሉ (NIV፣ ፍራንሲስኮ ዌ 626 ቅ.ል.ክ) እነርሱም ቀደም ሲል አሦርን ያጠቁ። ሔሮዱቱስ (1፡103-106) የሚለው ሲዚያን በፍልስጥኤም በኩል አድርገው እስከ ግብፅ ድረስ ወርረዋል፣ በፈርዖን ሳሜቲከስ I (663-609 ቅ.ል.ክ) ከመመለሳቸው በፊት፣ በብድራቱ።

ለ. ምንም እንኳ የሲዚያን ወረራ ሊሆን የሚችል ቢሆንም፣ ምናልባት ባቢሎናውያን ሊሆኑ ይችላሉ፣ ይሁዳን የወረሩት። አብዛኞቹ ሊቃውንት የሚመለከቱት ሊቃውንቱ ባቢሎናውያን እንደሆኑ ነው።

VII. ጽሑፋዊ ምድቦች *Introduction to the Old Testament* by R.K. Harrison, p. 939-940)

ሀ. የእግዚአብሔር ቀን፣ 1፡1-2፡3
1. በበአል አምላኪዎች ላይ የሚደርስ የጥፋት ርምጃ፣ 1፡2-6።
2. የእግዚአብሔር ቀን አንድምታዎች፣ 1፡7-13።
3. የሚከተለው ፍርድ፣ 1፡14-18
4. ፍርድን የማስወገጃ መንገዶች፣ 2፡1-3።

ለ. በባዕዳን ሕዝቦች ላይ የሚሆን ፍርድ፣ 2፡4-15

1. ፍልስጥኤም፣ 2፡4-7
2. ሞአብ እና አሞን፣ 2፡8-11
3. ግብፅ፣ 2፡12
4. አሦር፣ 2፡13-15

ሐ. ወዮታ እና ባርኮት፣ 3፡1-20
1. በኢየሩሳሌም ላይ የፍርድ ርምጃ፣ 3፡1-7
2. ለቀሪዎቹ ታማኞች የሚሆን የበረከት ዋስትና፣ 3፡8-20

VIII. ዋነኛ ሐቆች

ሀ. ይህ ነቢይ ያስጠነቅቃል፣ እየመጣ ስለላው የይሁዳ መወረር። ለዚህ የፍርድ ድርጊት ምክንያቱ በኢየሩሳሌም የነበረው ዓመጻዊ አመንዝራነት (ጣዖት አምላኪነት) ነው፣ በምናሴ የተጀመረው። ሶፎንያስ “የእግዚአብሔር ቀን” የሚለውን ጽንሰ-ሐሳብ ተጠቅሟል። ነቢያት ዘወትር በእነርሱ ጊዜ የነበረውን ቀውስ፣ መጻዒውን የፍጻሜ ዘመን ሁነቶችን በንግርነት ለማቅረብ ይጠቀማሉ።

ለ. 2፡3 ላይ የንስሐ ጥሪ አለ። የይሁዳ ብቸኛው ተስፋ የመሢሑ ፍቅር (3፡17) እና መገኘቱ ነው (3፡15 እና 17)!

ሐ. እግዚአብሔር እስራኤልን ለመቅጣት አሦርን መጠቀሙ ግልጽ ነው፣ እናም ይህ ማጭዴ ለም መሬት ኢምፓየር አሁን ተፈርዶበታል፣ በይሁዳ ላይ እንደሆነው ሁሉ!

IX. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት እና ሰዎች የሚገለጹ

ሀ. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት
1. “የጣዖታት ካህናት፣” 1፡4 (NASB እና NIV)
2. “የሰማይ ሠራዊት፣” 1፡5 (NIV፣ “ከዋክብታዊ ሠራዊት”)
3. “የእግዚአብሔር ቀን ቅርብ ነው፣” 1፡7 (NASB እና NIV)
4. “በመድረኩ ላይ የሚዘልሉትን ሁሉ፣” 1፡9 (NIV፣ “ወደ መድረኩ ደረጃ መውጣት የሚከለክሉት ሁሉ”)
5. “መክቴሽ፣” 1፡11 (NIV፣ “የገበያ ቀበሌ”)
6. “መንገቻም የምድርም አራዊት ሁሉ በውስጧ ይመሰጋሉ፣” 2፡14 (NASB እና NIV)
7. “በእርስዋ በኩል የሚያልፈው ሁሉ እጁን እያወዛወዘ ያፏጫል፣” 2፡15 (NIV፣ በእርስዋ በኩል የሚያልፉት ሁሉ እያፌዙ እጃቸውን ይወዘውዛሉ”)
8. “በቅዱስ ተራራዬ፣” 3፡11 (NIV፣ “በተቀደሰው ኮረብታዬ”)

ለ. ሰዎች
1. ኩሲ፣ 1፡1
2. ሚልኮም፣ 1፡5 (NIV፣ “ሞሎክ”)
3. ከሊታውያን፣ 2፡5 (NIV፣ “ከሬዛይቴ”)

X. የካርታ ስፍራዎች/አመላካቾች
1. ጋዛ፣ 2፡4
2. አስቀሎና፣ 2፡4
3. አዛጦን፣ 2፡4
4. አቃሮን፣ 2፡4
5. ሰዶም እና ገሞራ፣ 2፡9
6. ኢትዮጵያ፣ 2፡12 (NIV፣ “ኩሻውያን”)

XI. የተማሪ ይዘት ጥያቄዎች

1. ሶፎንያስ ከሌሎቹ የብኪ ነቢያት ይልቅ የረዘመ የዘር ሐረግ የኖረው ለምንድነው?


2. የሶፎንያስ የፍርድ ትንቢት ከኖኅ የጥፋት ውኃ የከፋ የሆነው ለምንድነው?


3. “የእግዚአብሔር ቀን” የሚለውን ጽንሰ-ሐሳብ ግለጽ፣ አብራራም።

4. ይሁዳ ከእስራኤል ይልቅ እጅግ ኃጢአተኛና በደለኛ የሆነው ለምንድነው?

5. 3፡9 ሁለንተናዊ ይዘት አለውን፣ ከአሕዛብ ጋር የሚዛመድ? ለምን?

6. 3፡17 የእግዚአብሔርን ልብ እንዴት ያሳየናል?


ANCIENT
NEAR EAST
N
S
E
W


PALESTINE
0 10 20 30 40
SCALE IN MILES

# መግቢያ ለትንቢተ ሐጌ

I. የመጽሐፉ ስም

ሀ. ስያሜው ሰባኪውን ተከትሎ ነው

ለ. የስሙ ፍችም፣ «ክብረ በዓል» ማለት ነው፡፡ ዮድ ወይም «አይ» በመጨረሻ ላይ ያለው የያህዌ ምሕጻረ-ቃል ሊሆን ይችላል፣ እንደዚያም ከሆነ «የያህዌ ክብረ-በዓል» ማለት ነው (I ዜና. 6:30) ወይም «የኔ» የሚለው ተውላጠ ስም፣ ደግሞ ያህዌን ያመለክታል፡፡

II. ቅዱስ ቃልነቱ /ካኖናይዜሽን/

ሀ. ይህ መጽሐፍ «የኋለኞቹ ነቢያት» ክፋይ ነው /መጽሐፈ-ጥበብ 49፡10/፡፡

ለ. እሱም «የአስራ ሁለቱ» ክፋይ ነው፣ የመለስተኛ ነቢያት ስብስብ /ባባ ባትራ 14ለ/፡፡
1. እንደ ኢሳይያስ፣ ኤርምያስ እና ሕዝቅኤል፣ በአንድ ጥቅል ተካተዋል፡፡
2. አስራ ሁለቱን ነገዶች ወይም የድርጅትን ተምሳሌታዊ ቁጥር ይወክላሉ፡፡
3. የመጻሕፍቱን ዜና መዋዕላዊ /የታሪክ/ ቅደም ተከተል ወግ/ልማዳዊ አተያይ ያንጸባርቃሉ፡፡

ሐ. «የአስራ ሁለቱ» ወይም የመለስተኛ ነቢያት ተራ በብዙ ሊቃውንት በታሪክ ቅደም ተከተል ተያይዘዋል፡፡ ሐጌ እና ዘካርያስ ከታሪክ አኳያ ጥንድ እንደሆኑ ግልጽ ነው፡፡

III. ዘውግ

ሀ. ይህ ተለጣጣቂ የሆኑ አራት ወይም አምስት ስብከቶች ነው /1፡13/፡፡
ለ. እሱም ቅኔአዊ አይደለም፡፡

IV. ደራሲነት

ሀ. ሐጌ፣ ዕዝራ 5፡1፤ 6፡14 ላይ እና ዘካርያስ 8፡9 ላይ ተጠቅሷል፣ ከዘካርያስ ጋር ተያይዞ፡፡ እሱ ምናልባት ከግዞት ተመላሽ ሊሆን ይችላል፡፡

ለ. እሱ ደግሞ I ኢስድራስ 6፡1፤ 7፡3፤ II ኢስድራስ 1፡40 ላይ ተጠቅሷል፣ እንዲሁም መጽሐፈ-ጥበብ 49፡11 ከሐጌ 2፡23 የተጠቀሰ ነው፡፡

ሐ. ጄሮም የሚለው እሱ ካህን ነው፣ ነገር ግን ይህ ከ2፡10-19 የመነጨ የተሳሳተ መረዳት ነው፡

መ. ኢዋልድ እና ፑሲ የሚያቀርቡት ሐሳብ፣ 2፡3 የሚያመለክተው፣ እሱ የሰሎሞንን መቅደስ ማየቱን ነው፣ ይህም የ70 ወይም 80 ዕድሜ ባለጸጋ ያደርገዋል፡፡

ሠ. የአሌክሳንደርያው ሲሪል፣ ስለ እሱ ቀን አጠቃላይ የሆነ አስተያየት ይጠቅሳል፣ እሱ መልአክ እንደሆነ፡፡ ይህም የዕብራይስጡን ቃል «መልእክተኛ» በተሳሳተ ከመረዳት የመነጨ ነው፣ 1፡13 ላይ፡፡

ረ. LXX በርከት ያሉ መዝሙራትን የሐጌና የዘካርያስ አስተዋጽዖ እንደሆኑ ይገልጻል፡ 112፣ 126፣ 127፣ 137፣ 146-149፡፡

ሰ. አራቱም ሁሉ የሐጌ ስብከቶች በሦስተኛ መደብ ነው የተመዘገቡት፣ ይህም የሚያመለክተው፡
1. የተለመደ ጽሑፋዊ ብልሃት፣
2. ጸሐፊ ወይም አዘጋጅ፡፡

V. ጊዜው

ሀ. ሐጌ የድኅረ-ግዞት ነቢይ ነው፣ ከእሱ ዘመን ሰው /አቻው/ ዘካርያስ ጋር፡፡

ለ. የመጽሐፉ ጊዜ የሰፈረው ከስድስተኛው ወር የመጀመሪያው ቀን /1፡1/ እስከ ዘጠነኛው ወር ሃያ አራተኛው ቀን /2፡10፣20 በዳርዮስ I ሃይስታስፐስ ሁለተኛው ዓመት ድረስ ነው 521-486 ቅ.ል.ክ)፡፡ ስለዚህ፣ ጊዜው 520 ቅ.ል.ክ ነው፡፡ ይህም አራተኛ ዓመት ነው፣ ሁለተኛው መቅደስ ከመጠናቀቁ በፊት፣ በ516 ቅ.ል.ክ፣ እናም የኤርምያስን ትንቢት ይፈጽማል፣ የሰባ ዓመቱን ግዞት በተመለከተ፣ እሱም በ586 ቅ.ል.ክ የጀመረውን፡፡

VI. የጊዜው ቅደም ተከተል *The Minor Prophets* by Dr. Theo Laetsch, published by Concordia, p. 385.ላይ የተወሰደ፡፡

| የዳርዮስ የግዛት ዓመት | ዓመት ቅ.ል.ክ | ወር | ቀን | ጽሑፍ | ይዘት |
|---|---|---|---|---|---|
| 2 | 520 | 6 መስ/ጥቅ | 1 | ሐጌ 1፡1-11 | ሐጌ ሕዝቡን ለድርጊት አነቃቃ |
| | | | 24 | ሐጌ 1፡12-15 | ሕዝቡ መገንባት ጀመሩ |
| | | 7 ጥቅ/ህዳ | 1 | ሐጌ 2፡1-9 | የእግዚአብሔር መቅደስ ኋለኛው ክብር |
| | | 8 ህዳ/ታህ | ? | ዘካ. 1፡6 | ዘካርያስ ትንቢት መናገር ጀመረ |
| | | 9 ታህ/ጥር | 24 | ሐጌ 2፡10-19 | እግዚአብሔር መባረክን ይጀምራል |
| | | | | ሐጌ 2፡20-23 | የመሢሑ መንግሥት መቋቋም የዓለም ኃይላት ከወደቁ በኋላ |
| | 519 | 11 የካ/መጋ | 24 | ዘካ. 1፡7- 6፡8 | የዘካርያስ የሌሊት ራዕይ |
| | | | | ዘካ. 6፡9-15 | የኢያሱ አክሊል መድፋት፣ ለመሢሑ የክህነት አገልግሎት ቅድመ-ማሳያ |
| 4 | 518 | 9 ታህ/ጥር | 4 | ዘካ. 7፣ 8 | ንስሐ መግባት ተበረታታ፣ ባርኮት ቃል ተገባ |
| 6 | 516 | 12 መጋ/ሚያ | 3 | ዕዝራ 6፡15 | የመቅደስ ምርቃት |
| | | ? | | ዘካ. 9-14 | ከመቅደስ ምርቃት በኋላ |

VII. ጽሑፋዊ ምድቦች -- የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝሩ የተበጀው በነቢዩ ስብከቶች ነው፡፡

ሀ. የመጀመሪያው ስብከት፣ 1፡1-11፣ መቅደሱን ዳግም መገንባት!

ለ. መሪዎችና ሕዝቡ ምላሽ ሰጡ፣ 1፡12-15

ሐ. ሁለተኛው ስብከት፣ 2፡1-9፣ ጉዳዩ የመቅደሱ መጠን አይደለም!

መ. ሦስተኛ ስብከት፣ 2፡10-19፣ የእግዚአብሔር ባርኮት ይፈስሳል /ይትረፈረፋል/ ሕዝቡ ከታዘዙና ቤተ መቅደሱን ዳግም ከገነቡ

ሠ. አራተኛው ስብከት፣ 2፡20-23፣ የመሢሑ ሁለንተናዊ አገዛዝ በዘሩባቤል ንግር /ጥላ/ መደረጉ፡፡

VIII. ዋነኛ ሐቆች

ሀ. መጽሐፉ የሚያተኩረው በሁለተኛው መቅደስ ዳግም ግንባታ ላይ ነው፣ ቀደም ሲል ለበርካታ ዓመታት ችላ የተባለውን፡
  1. ዕዝራ 5፡16 /1ኛ ዓመት - በሰሳብሳር በኩል/
  2. ዕዝራ 3፡8-13 /2ኛ ዓመት - በዘሩባቤል በኩል/

ለ. የእግዚአብሔር የወዲያውኑ /ፈጣን/ የሥጋዊ ባርኮት ተስፋ እና የወደፊቱ መሢሓዊ ባርኮቶች ከመቅደሱ ዳግም ግንባታ ጋር ይያያዛል /የሙሴአዊ ኪዳን መታደስ/፡፡

ሐ. ጉዳዩ የመቅደሱ መጠንና ግርማ አይደለም፣ ከእርሱ መኖር ይልቅ፡፡ የእግዚአብሔር መገኘት፣ ይኸውም እሱ ተምሳሌት የሚያደርገው ነው፣ እውነተኛው ክብር!

IX. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት እና ሰዎች

ሀ. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት

1. «የተሸለሙ ቤቶች፣» 1፡4 (NASB እና NIV)
2. «ልባችሁን በመንገዳችሁ ላይ አድርጉ፣» 1፡5፣7 (NIV፣ «በጥንቃቄ አስቡ…»)
3. «አሕዛብን ሁሉ አናውጣለሁ፣» 2፡7 (NASB እና NIV)
4. «ከፊተኛውይልቅየዚህየሁለተኛውቤትክብርይበልጣል» (NASB እና NIV)
5. «ዘሩባቤል… እንደ ቀለበት ማተሚያ አደርግሃለሁ፣» 2፡23 (NASB እና NIV)

ለ. ሰዎች

1. ዳርዮስ 1፣ 1፡1
2. ዘሩባቤል፣ 1፡1
3. ኢያሱ፣ 1፡1
4. «የሠራዊት ጌታ፣» 1፡2 (NIV፣ «ኃያል አምላክ»)

X. የካርታ ስፍራዎች/አመላካቾች -- የለም

XI. የተማሪ ይዘት ጥያቄዎች

1. የመጽሐፉ ማዕከላዊ ጉዳይ ምንድነው?


2. ድኅረ-ግዞት ተመላሾቹ አይሁድ ለምን በይሁዳ ይሄን የመሰለ አስቸጋሪ ጊዜ ገጠማቸው?


3. የምዕራፍ 2 የትኞቹ ክፍሎች ናቸው መሢሓዊ? ለምን?

4. 2፡3ን አብራራ፡፡

5. 2፡10-19ን አብራራ፡፡

6. ለዘሩባቤል ይህን ያህል ታላቅ ነገር ለምን ተባለለት፣ ታሪክ ስለ እሱ ስኬቶች/ቅድጅቶች በጣም ትንሽ እያለ? /2፡20-23/


ANCIENT
NEAR EAST
N
S
E
W


PALESTINE
0 10 20 30 40
SCALE IN MILES

# መግቢያ ለትንቢተ ዘካርያስ

I. የመጽሐፉ ስም

ሀ. የተሰየመው ደራሲውን ተከትሎ ነው፡፡

ለ. የስሙ ፍች «ያህዌ ያስባል፣» «በያህዌ የታሰበ፣» ወይም «ያህዌ አስቧል» ማለት ነው፡፡ የእሱ ስም አንድምታው፣ ያህዌ ገና አሁንም ቢሆን ከአይሁድ ጋር ነው፣ ኪዳኑንም ይመልሳል ማለት ነው፡፡

II. ቅዱስ ቃልነቱ

ሀ. ይህ መጽሐፍ «የኋለኞቹ ነቢያት» ክፋይ ነው /መጽሐፈ-ጥበብ 49፡10/፡፡

ለ. እሱም ከ «አስራ ሁለቱ» ክፋይ ነው፣ የመለስተኛ ነቢያት ስብስብ /ባባ ባትራ 14ለ/፡

1. እንደ ኢሳይያስ፣ ኤርምያስና ሕዝቅኤል፣ በአንድ ጥቅል ተካትተዋል፡፡
2. አስራ ሁለቱን ነገዶች ወይም የድርጅትን ተምሳሌታዊ ቁጥር ይወክላሉ፡፡
3. የመጻሕፍቱን የታሪክ ቅደም ተከተል ወግ/ልማዳዊ አተያይ ያንጸባርቃሉ፡፡

ሐ. የ«አስራ ሁለቱ» ወይም የመለስተኛ ነቢያት ተራ፣ የታሪክ ቅደም ተከተል በበርካታ ነቢያት ተያይዟል፡፡ ሐጌና ዘካርያስ ከታሪክ አኳያ ጥንድ መሆናቸው ግልጽ ነው፡፡

III. ዘውግ

ሀ. ይህ መጽሐፍ የፍጻሜው ጥፋት ሥነ-ጽሑፍ አንድ ምሳሌ ነው፡

1. ምዕራፍ 1-8 በመሠረቱ ዝርው /ስድ ንባብ/ ነው፡፡
2. ምዕራፍ 9-14 በመሠረቱ ቅኔ ነው፡፡

ለ. ይህ ዘውግ ለአይሁድ የተለመደ አይደለም፡፡ እሱም ዘወትር ጥቅም ላይ የዋለው ተቃርኖ-ሞል አመዛዛኝ ጊዜያትን ነው፣ የእግዚአብሔርን የማይናወጥ አቋም ለመግለጽ፣ ታሪክን እንደሚቆጣጠር እና ለሕዝቡ መድኃኒን እንደሚያመጣ፡፡

ሐ. እሱም ባሕርይ ያደረገው፡

1. የእግዚአብሔርን ሁለንተናዊ ሉዓላዊነት ብርቱ ስሜት/መልክ፣
2. በመልካምና በክፉ መካከል በዚህ ዘመን /ዓለም/ የሚካሄደውን ትግል፣
3. ምሥጢራዊ ኮድ /ተምሳሌታዊ ጽሑፍ/ ቃላት መጠቀሙ፣
4. ተምሳሌት /ምስል ከሳች/ መጠቀሙ፣
5. ቁጥርን መጠቀሙ፣
6. እንስሳትን መጠቀሙ፣ አንዳንዴ እንስሳትን/ሰዎችን፣
7. እግዚአብሔር ራዕዩን የሚገልጸው በሕልሞች ወይም በራዕይ ነው፣ ዘወትርም በመላእክት መካከለኝነት፡፡
8. በቀዳሚነት የሚያተኩረው በወደፊቱ ላይ ነው፡፡

መ. አንዳንድ ሌሎች ምሳሌዎች፡

1. ብሉይ ኪዳን
   ሀ. ዳንኤል 7-12
   ለ. ሕዝቅኤል 37-48 /?/
2. አዲስ ኪዳን
   ሀ. ማቴዎስ 24፣ ማርቆስ 13፣ ሉቃስ 21፣ II ተሰ. 2
   ለ. ራዕይ
3. ካኖናዊ ያልሆኑ
   ሀ. I ሔኖክ
   ለ. IV ዕዝራ /ኢስድራስ/
   ሐ. II ባሮክ

ሠ. ጀሮም ዘካርያስን የሚለው ከብኪ ውስጥ እጅግ በቀላሉ መረዳት የማይቻል /አስቸጋሪ/ መጽሐፍ ነው፡፡ ያም ሆኖ አኪ ውስጥ እጅግ በተጠናከረ መልኩ የተጠቀሰ፡

1. ምዕራፍ 1-8 በራዕይ መጽሐፍ ላይ፡፡
2. ምዕራፍ 9-14 በወንጌላት ላይ፡፡

ረ. እነዚህ ራዕዮች ለትርጓሜ አስቸጋሪ ናቸው፣ ነገር ግን ታሪካዊ መቼቱን ግምት ውስጥ ካስገባን፣ እነርሱ የሚዛመዱት ከመቅደሱ ዳግም ግንባታ ጋር ነው፣ በድኅረ-ግዞት ኢየሩሳሌም፡፡ እነርሱ የሚያተኩሩት በአዲሱ የይቅርታ ዘመን እና በሚመጣው መሢሕ ላይ ነው፡፡

IV. ደራሲ

ሀ. ዘካርያስ እጅግ የተለመደ የዕብራይስጥ ስም ነው፡፡ እሱም በሁለት መንገዶች ይነበባል፡ ዘካርያስ ወይም ዛካርያስ፡፡ ብኪ ላይ 27 ሰዎች አሉ፣ «ኢ» /«ዘ» በሚል የሚነበቡና 2 ሰዎች «አ» /«ዛ» በሚል የሚነበቡ፡፡

ለ. ምዕራፍ 1፡1 የሚለው ካህን መሆኑን ነው (ዕዝራ 5፡1፤ 6፡14፤ነህ. 12፡4፣16)፡፡ በራክዩ የሚለው፣ እሱም 1፡1 ላይ የተጠቀሰው እና ዕዝራ 5፡1 እና 6፡14 ላይ የተገደፈው ለምን እንደሆነ ርግጠኝነት የለም፡፡ ይህም ዘካርያስን ቀደምት ድኅረ-ግዞት ነቢይ ያደርገዋል፣ እንደ ሐጌ እና ሚልክያስ፣ እንዲሁም እንደ አብድዩ እና ኢዩኤልም ቢሆን፡፡

ሐ. ብዙ ዘመናዊ ሊቃውንት የዘካርያስን ኅብርነት/ወጥነት አይቀበሉም፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት፣ ምዕራፍ 1-8 ከምዕራፍ 9-14 እጅግ ስለሚለይ ነው፡፡ ምዕራፍ 1-8 ላይ ነቢዩ ተሰይሟል፣ እናም ታሪካዊ ቀናቱ ተሰጥተዋል፡፡ መቼቱ በግልጽ ድኅረ-ግዞት ነው፡፡ይህ ክፍል በተጠናከረ መልኩ በዮሐንስ ተጠቅሷል፣ በራዕይ መጽሐፉ ላይ፡፡ ሆኖም፣ ምዕራፍ 9-14 ቀኑ አልተጠቀሰም/አልተሰጠውም፡፡ የተሰየመ ነቢይም የለም፡፡ ታሪካዊ መቼቱ የፍጻሜ መዳረሻ ነው። ይህ ክፍል በወንጌላት እጅግ ተዘውትሮ ተጠቅሷል፡፡

ማቴ. 27፡9 ላይ ኢየሱስ ለኤርምያስ የጥቅሱን አስተዋጽዖ ሰጥቷል፣ እሱም ከዘካርያስ 11፡12-13 የሆነውን፡፡ ይህም ከምዕራፍ 9-14 ያለውን ደራሲነት ለዘካርያስ የአለመስጠት አዝማሚያ ጅማሮ ነው፡፡ ያም ሆነ ይህ፣ የሙት ባሕር ጥቅሎች እንኳ ቢሆኑ ዘካርያስ በኅብርነት/ወጥነት አላቸው፡፡ በርከት ያሉ ውስጣዊ ነገሮች አሉ፣ ኅብሩን/ወጥነቱን የሚያመለክቱ፡

1. የቁጥር «ሁለት» አጠቃቀም - 4፡3፤ 5፡9፤ 6፡1፤ 11፡7፤ 13፡8፣
2. የስም ጠቃሽ አጠቃቀም - 2፡7፣10፤ 3፡2፣8፤ 4፡7፤ 9፡9፣13፤ 11፡1-2፤ 13፡7፣
3. «ከሚያልፈው እና ከሚመለሰው» የሚለው ሐረግ አጠቃቀም፣ እሱም፣ በዘካርያስ ያልተለመደ - 7፡14፤ 9፡8፣
4. "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል" የሚለው ተደጋጋሚ አጠቃቀም - 16 ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡
5. "መኖር" የሚለው *qal* መልክ - 2፡8፤ 7፡7፤ 12፡6፤ 14፡10፡፡

(እነዚህ የተወሰዱት R.K. Harrison's *Introduction to the Old Testament*, p 954 ላይ ነው)፡፡ ለመጽሐፉ ኅብር ወጥነት ተጨማሪ ማብራሪያ (E.J. Young's *Introduction to the Old Testament)* p 280 ይመልቱ፡፡

መ. ዘካርያስ የተዋቀረበት ታሪካዊና የወደፊት ክፍል ሐቅ፣ አስገራሚ መሆን አይኖርበትም፡፡ ይሄንን ፈርጅ ቀደም ብለን ተመልክተነዋልና፡

1. ኢሳይያስ 1-39 እና 40-66
2. ሕዝቅኤል 1-29 እና 30-48
3. ዳንኤል 1-6 እና 7-12

ሠ. አዲሱ የብኪ መግቢያ በአንድሪው ሂል እና ጆን ዋልተን ገጽ 421 ላይ የሁለቱንም ምድቦች የፍሬ ሐሳብ ዝርዝር አስቀምጧል፣ ተለጣጣቂነት ባላቸው፣ ተገላቢጦሻዊ ትይዩ ሐረጎች፡፡ ይህ ቋሚነት ያለው ጽሑፋዊ ብልሃት አንድ ደራሲ ለመሆኑ የወደፊቱን ማስረጃ ይሰጣል፡፡

V. ጊዜው

ሀ. ዘካርያስ 1፡1 የሚያስቀምጠው፣ ነቢዩ አገልግሎቱን የጀመረው በዳርዮስ I አገዛዝ በ2ኛ ዓመት በ8ኛ ወር ነው (522-486 ቅ.ል.ክ)፡፡ አብዛኞቹ ሊቃውንት የሚያስረግጡት፣ ይህ ዳርዮስ I ሃይስትራፐስ ነው፣ እሱም የፋርስን መንግሥት የገለበጠ፣ ከካምቢሰስ II በኋላ (530-522)፣ የቂሮስ II ልጅ፣ በ522 ቅ.ል.ክ የሞተ፡፡ ዳርዮስ የፋርስ ጦር ሠራዊት ጀነራል ነበር፡፡

ለ. ይህም ጊዜውን 519 ወይም 520 ቅ.ል.ክ ያደርገዋል /ከሐጌ ከሁለት ወር በኋላ/፡፡ እሱም ለሁለት ዓመት ያህል ሰብኳል(ዝከ. 1፡1፣7፤ 7፡1)፡፡

VI. ታሪካዊ መቼት

VII. ጽሑፋዊ ምድቦች ከ *Introduction to the Old Testament* by R.K. Harrison p 950 የተወሰደ ፡፡

ሀ. ቀናቸው የተጠቀሰ ትንቢቶች፣ ምዕራፍ 1-8
1. መግቢያና የንስሐ ጥሪ፣ 1፡1-6፡፡
2. ስምንት ትንቢቶች ከኢየሩሳሌም መቅደስ ዳግም ግንባታ ጋር የሚዛመዱ፣ 1፡7-6፡15
   ሀ. አራት ፈረሰኞች፤የመለኮታዊ መታደስ ተስፋ፣ 1፡7-17
   ለ. አራት አጥፊ ቀንዶችና አራት ጠራቢዎች፣ 1፡18-21 (2፡1-4 ሄብ/Heb.)
   ሐ. ሊለካ የማይችለው የኢየሩሳሌም ታላቅነት፣ 2፡1-13 (2፡5-17 ሄብ/Heb.)
   መ. የኢያሱ መንጻት፣ ንግር፤ ለእርሱ፣ 3፡1-10
   ሠ. ባለ ሰባት መብራት መቅረዝ፣ 4፡1-14
   ረ. ትልቅ በራሪ የመጽሐፍ ጥቅል፣ 5፡1-4
   ሰ. በኢፍ መስፈሪያ ላይ ያለችው ሴት ወደ ባቢሎን መወሰድ፣ 5፡5-11
   ሸ. አራት በፈረስ የሚጎተቱ ሰረገሎች በምድር ላይ ሲጓዙ፣ 6፡1-8
3. ታሪካዊ ምድብ: ኢያሱ የመሢሑ ተምሳሌት፣ 6፡9-15፡፡
4. የዘካርያስ ጥያቄ፣ ጾምን በተመለከተ፣ 7፡1-8፡23፡፡

ለ. ቀናቸው ያልተጠቀሰ ትንቢቶች፣ 9-14
1. የብሔራዊ ጠላቶች ፍርድ፤ የሚመጣው የሰላም አለቃ፣ 9፡1-17
2. በተመረጠ መንጋ መሰባሰብ፣ በመለኮታዊ መሪ፣ 10፡1-12
3. መልካም እና ሰነፍ እረኞች፤ የመንጋው መቸገር፣ 11፡1-17
4. የፍጻሜ መዳረሻ ትንቢቶች፣ 12፡1-13፡6
5. የመለኮታዊው መንግሥት የሚያጠራ ፍርድ፣ 13፡7-14፡21

VIII. ዋነኛ ሐቆች

ሀ. የመጽሐፉ ዋነኛ ዓላማ የተመለሱትን አይሁድ ማበረታታት ነው፣ መቅደሱን ዳግም ይገነቡ ዘንድ፡፡ ይህም የተጀመረው በሳብሳር ነው፣ ዕዝራ 1፡8፤ 5፡16፣ ነገር ግን በዘሩባቤል ሊቀጥል አልቻለም፡፡ መቅደሱ በርከት ላሉ ዓመታት ችላ ተባለ፡፡ ሐጌ የሚያስረግጠው፣ ይህ

የሆነበት ምክንያት ከሕዝቡ ችላ ባይነት የተነሣ ሲሆን፣ ዕዝራ የሚያመለክተው ደግሞ በአካባቢው ግዛቶች፣ በተለይም በሰማርያ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ምክንያት ነው፡፡

ለ. ይህ መጽሐፍ እጅግ መሢሓዊ ነው፡፡ ስለ ኢየሱስ ሕይወት አብዛኞቹ ትንቢቶች የተገኙት ከምዕ. 9-14 ነው፡፡
1. ንጉሡ ትሑትና በአህያ ውርንጫ የሚቀመጥ ነው፣ 9፡9፣
2. ለሠላሳ ብር የሚሸጥ፣ የአገልጋይ ዋጋ እና የሸክላ ሠሪውን መሬት ለቀብር ቦታ፣ 11፡13፣
3. ከዳዊት ዘር ለመሆኑ አጽንዖት የሚሰጥ፣ 12፡4-9፣
4. «እነርሱም ወደ ወጉት ይመለከታሉ...» 12፡10

ሐ. የእግዚአብሔር ሁለንተናዊ ፍቅርና አገዛዝ 2:11፤ 8:20-23፤ 14:9፣16 ላይ ይታያል፡፡ ነገር ግን ምዕራፍ 9-14 ላይ የሰዎች ሁሉ ሁለንተናዊ ዓመጸ አጽንዖት ተሰጥቶታል፣ 12:3 እና 14:2 (መዝ. 2)፡፡

IX. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት እና ሰዎች በአጭሩ የሚገለጹ

ሀ. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት
1. ተመለሱ፣ 1፡3 (NASB እና NIV)
2. «እኔበታላቅቅንዓትበኢየሩሳሌምናበጽዮንቀንቻለሁ» 1፡14 (NASB እና NIV)
3. «በኢየሩሳሌም ላይ ገመድ ይዘረጋባታል፣» 1፡16 (NASB እና NIV)
4. አራት ቀንዶች፣ 1፡18-21 (NASB እና NIV)
5. «እኔበዙሪያዋየእሳትቅጥርእሆንላታለሁ፣» 2፡5 /NIV፣ «እኔ ራሴ በዙሪያዋየእሳትቅጥርእሆንላታለሁ»/
6. «የዓይኑን ብሌን፣» 2፡8 (NASB እና NIV)
7. «ኢያሱም እድፋም ልብስ ለብሶ ነበር፣» 3፡3 (NASB እና NIV)
8. በራሪ የመጽሐፍ ጥቅልል፣ 5፡1 (NASB እና NIV)
9. ተራፊም፣ 10፡2 (NIV፣ «ጣዖታት»)
10. ሁለትበትሮች፡ «ሞገስ እና ኅብረት» /«ውበት እና ማሰሪያ»/ 11፡7፣ 14 (NASB እና NIV)
11. «ኢየሩሳሌምን ...ዋንጫ... ከባድድንጋይ አደርጋታለሁ፣» 12፡2-3 (NIV፣ «የማይነቃነቅ ዐለት»)
12. «የሕይወት ውኃ ከኢየሩሳሌም ይወጣል፣» 14፡8 (NASB እና NIV)

ለ. ሰዎች፣ በአጭር የሚገለጹ
1. በራክዩ፣ 1፡1፣7
2. የእግዚአብሔር መልአክ፣ 1፡11፤ 3፡1
3. ሰይጣን፣ 3፡1-2
4. ቍጥቋጥ፣ 3፡8፤ 6፡12
5. «ሁለቱ የተቀቡት፣» 4፡14
6. ሐዳድሪሞን፣ 12፡11 /NIV፣ «ሐዳድ ሪሞን»/

X. የካርታ ስፍራዎች/አመላካቾች

1. ጽዮን፣ 1፡14
2. ሰናዖር፣ 5፡11 /NIV፣ «ባቢሎን»/
3. ቤቴል
4. ሐማት፣ 9፡2
5. በመጊዶን ሜዳ፣ 12፡11
6. ደብረ ዘይት /የዘይት ተራራ/፣ 14፡4

XI. የተማሪ ይዘት ጥያቄዎች

1. ዘካርያስ በምን መልኩ ከሐጌ ጋር ይዛመዳል?


2. የ1:7-6:8 ራዕዮች በምን መልኩ ይዛመዳሉ?


3. በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙትን የመሢሑን መጠሪያዎች/ስሞች ዘርዝር፡፡

4. ምዕራፍ 4 ላይ ያሉት ሁለቱ የወይራ ዛፎች እነማናቸው?

5. ምዕራፍ 7-8 ላይ ምን ያህል የጾም ቀናት ተዘርዝረዋል?

6. ምዕራፍ 9-14 ላይ ያሉትን ከክርስቶስ ሕይወት ጋር የሚዛመዱትን ትንቢቶች ዘርዝር፡፡


ANCIENT
NEAR EAST
N
S
E
W


PALESTINE
0 10 20 30 40
SCALE IN MILES

# መግቢያ ለትንቢተ ሚልክያስ

I. የመጽሐፉ ስም

ሀ. የተሰየመው ነቢዩን ተከትሎ ነው፡፡

ለ. የስሙ ፍች «መልዕክተኛዬ» ማት ነው፡፡
1. እሱም ርዕስ ሊሆን ይችላል፣ «መልእክተኛዬ፣» 3፡1፡፡
2. እሱም፣ «መልአኬ» ማለት ሊሆን ይችላል፡፡
3. እሱም የተጸውዖ ስም ሊሆን ይችላል፡፡

II. ቅዱስ ቃልነቱ /ካኖናይዜሽን/

ሀ. ይህ መጽሐፍ «የኋለኞቹ ነቢያት» ክፋይ ነው /መጽሐፈ ጥበብ 49፡10/፡፡

ለ. እሱም «የአስራ ሁለቱ» ክፋይ ነው፣ የመለስተኛ ነቢያት ስብስብ /ባባ ባትራ 14ለ/፡፡
1. እንደ ኢሳይያስ፣ ኤርምያስ እና ሕዝቅኤል፣ በአንድ ጥቅል ተካተዋል፡፡
2. አስራ ሁለቱን ነገዶች ወይም የድርጅትን ተምሳሌታዊ ቁጥር ይወክላሉ፡፡
3. የመጻሕፍቱን ዜና መዋዕላዊ /የታሪክ/ ቅደም ተከተል ወግ/ልማዳዊ አተያይ ያንጸባርቃሉ፡፡

ሐ. «የአስራ ሁለቱ» ወይም የመለስተኛ ነቢያት ተራ በብዙ ሊቃውንት በታሪክ ቅደም ተከተል ተያይዘዋል፡፡ ሚልክያስ በግልጽ የመጨረሻው መለስተኛ ነቢይ ነው፡፡

III. ዘውግ

ሀ. እሱም ቆጥቋጭ/ኃይለኛ ቃላትን ይጠቀማል፣ እውነትን ለማስተላለፍ፡፡ ይህም የጥያቄና መልስ አቀራረብ ነው፡፡ እውነቱ ይቀርባል፣ እና ከዚያም ታሳቢ ተቃዋሚው/የተለየ ሐሳብ ያለው ጥያቄ ይጠይቃል ወይም አስተያየቱን ይሰጣል፣ ተናጋሪው ለሰጠው ምላሽ፡፡

ለ. ሚልክያስ «ዕብራዊው ሶቅራጥስ» በመባል ይጠራል፡፡

ሐ. ሁለቱም ጳውሎስ እና ያዕቆብ ይሄንን ተመሳሳይ ዘዴ ተጠቅመዋል፣ እውነትን ለማቅረብ፡፡

መ. መዋቅሩ፣ «እናንተ ግን ብላችኋል...» በሚለው ሊታይ ይችላል፣ 1፡2፣ 6፣ 7(ሁለቴ)፣ 12፣ 13፤ 2፡14፣ 17 (ሁለቴ)፤ 3፡7፣ 8፣13፣ 14፡፡

ሠ. እሱም የዕብራይስጥ ቅኔ አይደለም፡፡

IV. ደራሲነት

ሀ. የዕብራይስጡ ቃል "*malachi*" 1፡1 ጥቅም ላይ የዋለው፣ ፍችው «መልአክ» ወይም «መልእክተኛ» ማለት ነው፡፡
1. ባብዛኛው እንደ ተጸውዖ ስም ነው የሚወሰደው፡፡
2. LXX እሱን የሚወስደው እንደ ርዕስ/መጠሪያ ነው (ዝከ. 3፡1)፡፡
3. ኦሪጅን የሚያስበው እሱ መልአክን እንደሚያመለክት ነው፡፡

ለ. ታልሙድ /ሜሲላህ 15ሀ/ የሚለው መርዶክዮስ መጽሐፉን ጻፈው ነው፡፡

ሐ. የጆናታን የአራሚክ ታርጉም የሚለው እሱ የዕዝራ መጠሪያ ነው፡፡ ይህን ትርጉም፡ ጀሮም፣ ራሺ እና ካልቪን ተከትለውታል፡፡

መ. ጆሴፈስ በጥንታዊ *Antiquities of the Jews* የአይሁድ ቅርስ፣ 11፡4-5 ላይ ሁሉንም የድኅረ-ግዞት ሰዎች በስማቸው ዘርዝሯል፣ ከሚልክያስ በቀር፡፡

ሠ. ስሙ ከዚህ መጽሐፍ ላይ በተደረጉ በማናቸውም የአኪ ጥቅሶች ላይ በተጓዳኝ አልተከሰተም፡፡

ረ. II ኢስድራስ የድኅረ-ግዞት ነቢያትን ዘርዝሯል፣ እንደ ሐጌ፣ ዘካርያስ እና ሚልክያስ፡፡

ሰ. ሌላ ማንኛውም የትንቢት መጽሐፍ ስያሜው እስካልታወቀ ድረስ፣ ሚልክያስ የተጸውዖ ስም መሆን ይኖርበታል፡፡ ደራሲነት፣ ተመስጧዊነት ላይ ተጽዕኖ እንደሌለው አስታውሱ፡፡

V. ጊዜው

ሀ. በነህምያ እና በሚልክያስ መካከል ከታሪካዊ ዳራ አኳያ ታላቅ ተመሳሳይነት አለ፡
1. በአስራት ላይ ያለ ተቃርኖ፣ ሚል. 3፡8፤ነህ. 10፡32-39፣
2. ድሆች ተጨቁነው ነበር፣ ሚል. 3፡5፤ነህ. 5፡1-5፣
3. የድብልቅ ሃይማኖት ጋብቻ፣ ሚል. 2፡10፣11፤ነህ. 13፡1-3፣ 23-24 (ዕዝራ 9፡1-2)፡፡

ለ. እጅግ የተሻለው አማራጭ የሚመስለው 450-430 ቅ.ል.ክ ነው፣ ነህምያ ወደ አርጤክስስ I ቤተ-መንግሥት ከተመለሰ በኋላ፣ነህ. 13፡6፡፡

VI. በዕብራውያንና በኤዶም መካከል ታሪካዊ ዝምድና፣ 1፡2-5

ሀ. እንደ ዘመድ እንዲያከብሯቸው ተነግሯቸው ነበር፡
1. ዘኍልቁ 20፡14
2. ዘዳግም 2፡4-6

ለ. ከእነርሱ ጋር ብዙ ግጭቶች ነበራቸው፡
1. ዘኍልቁ 20፡14-21
2. መሳፍንት 11፡16
3. I ሳሙኤል 14:47-48

ሐ. በእነርሱ ላይ በአሉታ የተነገረ ትንቢት፡
1. ዘኍልቁ 24:18
2. ኢሳይያስ 34:5፤ 63:1
3. ኤርምያስ 49:7
4. ሰቆቃወ ኤርምያስ 4:21-22
5. ሕዝቅኤል 26:12፤ 35:13፤ 36:2-6
6. አሞጽ 1:11-12

VII. ጽሑፋዊ ምድቦች

ሀ. የሚልክያስ የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር የእርሱን ስድስት የክርክር ሐሳብ ወይም ጠንካራ ቃላትን ይከተላል፡፡ ሚልክያስ ስለ እግዚአብሔር ይናገራል፣ ሕዝቡም ምላሽ ይሰጣል፣ እናም ሚልክያስ ደግሞ ስለ እግዚአብሔር ይናገራል፡፡

ለ. የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር
1. የእግዚአብሔር ፍቅር፣ ስለሚመለሱ አይሁድ፣ 1፡2-5
2. የእግዚአብሔር ውግዘት በካህናት ላይ፣ 1፡6-2፡9
3. የእግዚአብሔር ውግዘት በፍች እና በድብልቅ ሃይማኖታዊ ጋብቻ ላይ፣ 2፡10-16
4. የእግዚአብሔር ውግዘት በመጥፎ አዝማሚያቸው /የፍትሕ አምላክ ወዴት ነው?)፣ 2:17-3:6
5. የእግዚአብሔር ውግዘት ለመቅደሱ ስለሚያደርጉት ድጋፍ፣ 3፡7-12
6. የእግዚአብሔር ውግዘት በመጥፎ አዝማሚያቸው /እግዚአብሔርን ማገልገል ከንቱ ነው!/ 3፡13-4፡3
7. የመጨረሻ ማስጠንቀቂያና ተስፋ፣ 4፡4-6

VIII. ዋነኛ ሐቆች

ሀ. ሚልክያስ የተመላሾቹን አይሁድ የቸልተኝነትና እምነት ማጣት ኃጢአት ሰንዷል /አስፍሯል/፡፡

ለ. ይህ መጽሐፍ በርከት ያሉ ሁለንተናዊ መግለጫዎች ይዟል፡፡ እግዚአብሔር በእስራኤል ይጠቀማል፣ ወደ ዓለም ለመድረስ፣ 1:5፣ 11፣ 14፤ 3:12፡፡

ሐ. የእግዚአብሔር ሕዝቦች የእርሱን ባሕርይ ተገዳድረዋል፡
1. 2፡17 - እግዚአብሔር ለፍትሕ አይሠራም
2. 3፡6 - እስራኤል እስካሁን መኖሩ ከእግዚአብሔር የማይለወጥ ባሕርይ የተነሣ ብቻ ነው፡፡
3. 3፡14 - እግዚአብሔርን ማገልገል ዋጋ የለውም፡፡

መ. ይህ መጽሐፍ መሢሐዊ ተስፋ አለው፣ 3፡1፤ 4፡5፡፡

IX. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት እና ሰዎች በአጭሩ የሚገለጹ

ሀ. ቃላት እና/ወይም ሐረጋት
1. ንግር፣ 1፡1 (NASB እና NIV)
2. «እናንተ ግን ብላችኋል…» 1፡2 (NIV፣ «እናንተ ግን ጠይቃችኋል…»)
3. «አንካሳውንና የታመመውን አቅርባችኋል፣» 1፡8 (NIV፣ «የሚያነክሰውንና የታመመውን እንስሳ»)
4. «እናንተም በንቀት ጢቅ አላችሁበት፣» 1፡13 (NIV፣ «እናንተም በንቀት ጢቅ አላችሁበት»)
5. «ዘራችሁን እገሥጻለሁ፣» 2፡3(NIV፣ «ዝርያችሁን እገሥጻለሁ»)
6. «የእንግዳውንምአምላክልጅሚስትአድርጎአግብቶአልና፣» 2፡11(NASB እና NIV)
7. «እናንተምየምትፈልጉትጌታበድንገትወደመቅደሱይመጣል፣» 3፡1 (NASB እና NIV)
8. «የመታሰቢያመጽሐፍ፣» 3፡16 (NIV፣ «የመታሰቢያ መጽሐፍ ጥቅል»)
9. «የጽድቅፀሐይትወጣላችኋለች፥ፈውስምበክንፎችዋውስጥይሆናል፣» 4፡2 (NASB እና NIV)

ለ. ሰዎች
1. ዔሳው፣ 1፡2-3
2. ያዕቆብ፣ 1፡2
3. ሌዊ፣ 2፡4
4. መተተኞች፣ 3፡5

5. መጻተኛ፣ 3፡5
6. ነቢዩ ኤልያስ፣ 4፡5

X. የካርታ ስፍራዎች/አመላካቾች

1. ኤዶም፣ 1፡4
2. ይሁዳ፣ 2፡11
3. እስራኤል፣ 2፡11
4. ኮሬብ፣ 4፡4

XI. የተማሪ ይዘት ጥያቄዎች

1. ሚልክያስ የተዋቀረው እንዴት ነው?

2. ዔሳው 1፡2 ላይ ለምን ተጠቀሰ?

3. ካህኑና ሕዝቡ ለያህዌ ያላቸውን ንቀት /አለማክበራቸውን/ ያሳዩት እንዴት ነው?

4. 2፡2፤ 3፡9 ላይ የተጠቀሰው ርግማን ከየትኛው የቅዱስ ቃሉ ክፍል ነው የመጣው? እሱስ ምንን ያካትታል?


5. እግዚአብሔር ለምን መፋታትን እጠላለሁ አለ? 2፡16


6. መሢሑ ወደ መቅደሱ በድንገት የሚመጣው እንዴት ነው?

7. 3፡6 እጅግ ጠቃሚ የሆነው ለምንድነው?

8. እግዚአብሔር ለአስራት ብልጽግናን እንደሚሰጥ ቃል ገብቷልን?

9. ኤልያስ ከኢየሱስ በፊት መጥቷልን?


ANCIENT
NEAR EAST
N
S
E
W


PALESTINE
0 10 20 30 40
SCALE IN MILES